# የቁራኛ ህዝቦች ሆይ ስሙ

15

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና የመጅሊስ ጋብቻ ከአህባሻነትም ወደ ዩኒቲ ጉዞውን ቀጥሏል እንደሚታወቀው አስልምና የሰው ልጅ ምድርን ከረገጠበት ጊዜ አንስቶ ጠላቶች ባይተኙም እንኳን እስከዛሬ ድረስ አለ ወደፊትም ይኖራል ምክንያቱም ጠባቂው አላህ ነውና አለም አስልምናን ለማጥፋት ቢሰበሰብ ሊጠፋ የሚችል እምነት አይደለም ይሄንን አስመልክቶ አላህ በቁራን ውስጥ ሰዎች (የአላህን ዲን ባፋቸው ልክ እንደ ሸማ እና ብለው ሊያጠፉት ይፈልጋሉ አላህ ደግሞ ዲኑን ይሞላዋል) ይሰናል። አስልምና ለማጥፋት ቆርጠው የሚያድሩ ምእራባዊያን በአስልምና ላይ ያሴሩት የረጅም ጊዜ እቅድና ሴራ በአሁኑጩ የፌዴራል ጉዳዮች ሚንስቴር አስፈጻሚ እንዲሆን አድገዋል። ይሄው ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከ48 ሚሊየን በላይ መስሊም ባለበት ሀገር ኢትዮጵያ ሶስት ጥያቄ ተጠይቆ መልስ ሲነፈግ ግርም የሚገርም ታሪካዊ ክስተት ተብሎ የሚታሰፍ ብቻ ሳይሆን በትውልድ ላይ ጥቁር ጥላሸት መቀባትም ጭምር ነው አምላ ገነኑ የደርግ መንግስት የሠጥንን የመስሊሞች ተቋም ወይም (መጅሊስ) ሥላጥንን ተገን ያደረገው የፌዴራል ጉዳዮች ሚንስቴር ከመንጠቅም አልፎ በመስሊሞች ላይ ጣቱን ከቀሰረ ሰነባብቶዋል እሄን ብቻ አይደለም መስሊመን ህበረተሰብ እንደ ቡና ቁርስ በመከፋፈል ፖለቲካዊን ያራምዱልኛል ብሎ ያሰባቸው (አህባሻዝም) በመስሊሞች ተቋም ላይ እንደያራሳይት በመለጠፍ ኢትዮጵያዊያን መስሊሞች ላይ ግልጽ የሆነ ጦርነት አውጇል በተለያየ ቦታና በተለያየ ጊዜ በመንግስት አዳራሾችም ጭምር ለአስልምና እንሰራለን በሚል ስም በመስሊመ ላይ ደም አስለቃሽ የሆነ ቁማር ይጫወታሉ (አሳዛኝ መሳይ ቅቡ አንባቸ) እንደሚሉት ነው ነገሩ ምንም ይሁን ምን የትም አብኩተው ጠፍየፈውና ጋግረው ያመጡት እምነት ለኛ ለመስሊሞች እምነት ሊሆን በፍፁም አይችልም። እስከዛሬ ድረስ በመስሊሙ ሥም ሊቸበችቡ የቆዩት ሆድ አምላኪዎች ምርጫ በለው መስሊመን ባሳሳተፉና ዝግ በሆኑ መድረኮች ጋብቻቸውን ለማደስ ሽርጉድ ላይ ናቸው። ሰዎች ለባጢል ሸር ጉድ ሲሉ እኛም ደግሞ ተኝተን አናድርም እንቅልፍም አይዘንም በሀቅ ላይ ወደፊት እንጂ አንድ እርምጃ ወደ ኋላ አንልም ። አላህ ከአውነተኞች ጋር ነውና እናም የአሚኦት አገዛዝና የበታችነት ይዘውን ህገመንግስቱን አክብሮ አላህን መገዛት የበታችነት አይደለም በተጨማሪም የአህባሽና የመጅሊስ ዋናው መሪያቸው ሸፈራው ወይም የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የምርጫውን አቅጣጫ ለማስቀየር ከፍተኛ በጀት መድቦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ስለዚህ ማነው መራጩ ማን ነው ተመራጩ የሚለው እግራችን ወደፊት እየተራመደ እጃችንን ሳንሰበስበው አይናችን ሳንጨፍነው ጠንቀቅ ብለን ልንከታተለው ይገባል። ምክንያቱም የህይወት ጉዳይ ነውና ዲን ከሌለ ሕይወት የለምና ::

በመጨረሻም ተወልደን ባደግንበት ሀገር ኢትዮጵያ በማንም ላይ ወሰን ሳናልፍ በማንም ላይ ድንበር ሳንጥስ በሰላማዊ መንገድ ድምፃችን ይሰማ ::

25

# አላሁአክበር

ኮፒ በማድረግ የቻሉትን ያስተላልፉ!!!

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
531
http://ethcriminalawnetwork.com/

ይህን ጉዳይ በባለቤትነት ሊመራ የሚገባዉ ህዝበ ሙስሊሙ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በሀጉ የተሰጠው መብት ነው። በመሆኑም ምርጫዉ ነፃ እና ፍትሀዊ እንዲሆኑ በሚያስችሉ ኑዋቦች ላይ ህዝበ ሙስሊሙ በራሱ በየአካባቢዉ እየተወያየ ሰንዝቷል። አስካሁን ሙስሊሙ ማህበረሰብ በምርጫዉ ዙሪያ በየአካባቢዉ ባካሄደዉ ዉይይት የምርጫዉን ፍትሀዊነት በሚያረጋግጡ ኑዋቦች ላይ ጠቃሚ፣ አስደሳች እና የሙስሊም ጠላቶችን ሴራ ሊያከሽፍ የሚችል ተመሳሳይ የዉሳኔ አቅም የያዙ መሆናቸው ታውቋል።

መንግስት በየቀበሌዉ እና በየወረዳዉ ሙስሊሙን ማህበረሰብ በመሰብሰብ ሰለ መጅሊስ አመራሮች ምርጫ እያካሄደዉ በሚገኘዉ ስብሰባ ላይ ከሙስሊሙ ከፍተኛ ተቃዉሞ እየገጠመዉ መሆኑና ስብሰባዎቹም ያለምንም ዉጤት ቦተቃዉሞ እየተጠናቀቁ መሆናቸዉ የሚታወስ ነዉ። እንደዚህ ላይነት ስብሰባዎችን ማካሄድ የሚገባዉ ህዝበ ሙስሊሙ እርስ በርሱ ብቻ መሆኑ እየታወቀ ህዝቡ እርስ በእርስ ተወያይቶ ይበጀኛል የሚለዉን አካሄድ እንዲያስቀምጥ መድረኮች ባይመቻቹለትም ሁሉም ይህንን ሴራ ስላወቀ በየአካባቢዉ በመሰባሰብ በምርጫዉ ዙሪያ ተወያይቶ ምርጫው በራሱ ነፃ ተሳትፎ እንዲከናወን ለማድረግ ገለልተኛ አስመራጭ ኮሚቴዎችን ለመምረጥ እንቅስቃሴዎችን ጀምሯል።

በመሆኑም ሁላችንም በየአካባቢያችን እና በየመስጂዶቻችን ተመሳሳይ ዉይይቶችን በማካሄድ ምርጫዉ ነፃ እና ፍትሀዊ እንዲሆን የሚያስችሉ ገለልተኛ አስመራጭ ኮሚቴዎችን ለመምረጥ የሚያግዙ ሂደቶች ላይ ፊርማችንን በማኖርና መሰል በሆነ ተግባሮች ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋፅኦ ልናደርግ ይገባል። በዚህ መልኩ ሰበቡን ካሟላን ጌታ አላህ ይህ ሁሉ ጥረታችንን ያያልና በእዝነቱ መጪረሻዉን ያሳምርልናል ኢንሻአላህ!!

## ዜና

. በኦሮሚያ ክልል የብሔራዊ ደህንነት አባል የሆነው ግለሰብ በአዳማ በተዘጋጀ የአህባሽ የስልጠና መድረክ ላይ በመገኘት ብዙዎችን ያሰቆጣና ህገ መንግስቱን የሚፃረር ንግግር አደረገ። ይኸው ግለሰብ በአወሊያ እየተካሄደ ያለውን የሙስሊሞች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ክፉኛ ያብጠለጠለ ሲሆን ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ጠባብነት እና ፀረ ሕገ መንግስት ይዘት ያለውን ንግግር አሰምቷል። አወሊያ በመሰብሰብ የሚጮኹት ሰዎች ስልጤዎችና ጉራጌዎች አንጂ አሮሞዎች አይደሉም። ስለዚህ እኛ ምን ባይሃን አርፈን የማንቀመጠውን እነሱ ጥቅማቸው ስለተነካባቸው ነው የሚጮኹት እኛ ግን በማለት ንግግሩን ሲቀጥል ከመድረክ ተቃውሞ በርትቶበት ለማቋርጥ ተገዷል። በዚሁ ጊዜ ከመድረክ ጠንካራ ጥያቄዎች ተቀይሰሰት ሲሆን ግለሰቡ መድረክ ላይ ውጥቶ ይህን እየተናገረ ያለው ሙስሊሙን በመወከል ወይስ መንግስትን በመወከል የሚለው ግልፅ አይደለም። ግለሰቡም በሙስሊም ስብሰባ ላይ በመድረኩ ላይ የተገኘሁት ሙስሊም በመሆኔ ነው በማለት ቢመልስ መስሌ ሙስሊክ ይህ አነጋገርህ ፊቃም ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም በኩብዩ ዘመን ህበሻዊው ቢላል ጥቁር ሆኖ ፍጭም ሰብዓዊነቱ በታያበት መልኩ አስተማሪ የሆነ ነገር ስላስተላለፈልን በዘር እና በብሔር በመከፋፈል ግጭት ለማንሳት የምታደርገው ሙከራ ተቀባይነት የለውም በማለት ጩኸቱ በመበርከቱ የተነሳ ሰውዬውን ለማስወጣት ተሞክሯል።

. በናርዌይ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ታሳቅ ህዝባዊ የተቃውሞና የድጋፍ ሠልፍ አካሂደዋል። ሠልፈኞቹ በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላይ እየደረሰ ያለው የጎይማኖት መብት ጥሰት ተቃውመዋል። በአገር ዉስጥ አተካሄደ የሚገኘው ሠላማዊና ሕገመንግስታዊ የመብት ማስከበር እንቅስቃሴም ያላቸውን ድጋፍ ገልጸዋል። ሠልፈኞቹ ከኖርዌይ ፓርላማ ፊት ለፊት በመሰብሰብ በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እየቀረቡ ያሉ ጥያቄዎችን የያዘ ደብዳቤ ለፓርላማው አስንብተዋል። በተጨማሪም ለኖርዌይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሕንኑ ደብዳቤ ማስገባታቸውን ለማወቅ ተችሏል። የሰብአዊ መብት ይከበር፤ የሙስሊሙ ጥያቄ ይመለስ፤ ለፍትህና ሰላም መቆም አሸባሪነት አይደለም፤ የሚሉ መፈክሮችንም አሰምተዋል።

. በሌላ ዜና አቶ አሕመዲን አብዱላዚዝ በድጋሚ ለመመረጥ የሞት ሽረት ትግል እያደረገ መሆኑ የተሠማ ሲሆን በሀረሚያ እና አካባቢው ሰዎች እንዲደግፉት በገንዘብ ይደል ሚና ለመፍጠር እየሞከረ ይገኛል። ይህም በቅስቀሳ ሂደት ፈተና የሆኑበትን አካላት በስማቸው ቼክ እየተፃፈ ለማደለል ሙከራ እስከማድረግ እንደዘለቀ ተጨባጭ መረጃዎች ያሳያሉ። በተያያዘ ዜና ሦስት የመጅሊስ አመራር አካላት ወደ ሳውዲ ዓረቢያ መጓዛቸው ተሰማ። የመጅሊሱ ዋና ፀሀፊ ጀማል መሃመድ ሳፊሆ (ንብረ) እና አቶ ናሲር ያሉበት ይኸው ጉዞ በሦናኑ ሁለት ጀንዳዎች እንዳሉት ታውቋል። በኢጃቸው ያልገባ የህዝቡ መጅሊሙ የሆነውን ባለፈው ዓመት የተቀመጠ 8 ሚሊዮን ብር ወደ ሃገር በመላክ ስልጣን ከመልቀቃቸው በፊት በምርጫ ሽፍን ለሀገሠዋ ሰራቸውን ለማዋል በማሰብ ጉዳን ለማስጨረስና የመጪውን የሐጅ ስርዓት በማስመልከት ሕንፃ ለመከራየት በሚል ነው። 8 ሚሊዮን ብሩን ሃዋላ ለማስላክ 300,000 ሺህ ብር ሊጠየቁ መላኩን ለገዢው ትተው የነመሰከውን ለጠቅ ሀገሠ [illegible] ተመልሰዋል።

. የፌደራል ጉዳዩ ዶ/ር ሽፈራው [illegible] ከህዝቡን አበል ተከፍሎ አሁን ግዜው ሶስ በሶስ ብር ሽፈራው ቢር ሃምሳውን በሚፈልጉት መልኩ እንዴት እንደሚያጠናቅቁ ውይይት አደረጉ። የሚያስፈልገውን በሚሊዮን የሚቆጠር ፈንድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመጅሊስ የተለቀቀለት ሲሆን ትላንት ሃሙስ መጅሊስ ብሩን ተቀብሏል። የፌደራል ጉዳዩ ዶ/ር ሽፈራው ያዉጣው የፃሮጫ ማካሄጃ መመሪያ ለየክልሉ መጅሊስ መስጠቱና መጅሊሶቹም ላዩ ላይ ማህተም እንዳደረጉበት ይታወቃል። በዚህ መመሪያ ላይ በምርጫው መመረጥ የሚችለው ለህገ ወጡ የነ አብዱላሂ መጅሊስና ለሚሰሯቸው ስራዎች በነ አመለካከት ያለውና የአህባሽን ስልጠና የወ[illegible]ዩ ነው ይላል። መንግስት ጣልቃ አልገባውም አያለ ነው እንግዲህ ይህ ሁሉ ግፍ በህዝበ ሙስሊሙ ላይ ፌደራል ጉዳዩ ሚኒስቴር መ/ቤት እየተሰራ የሚገኘው።



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምፃችን ይሰማ!!

ቁ.13

01-10-04 E.C

## 22ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ ፱

### ነፃ የምንለውና ያልመረጥነው ምርጫ ምን ምን መስፈርቶችን ሊያሟላ ይገባዋል?

. በህዝብ የሚመረጥ ነፃና ገለልተኛ አካል:- ነፃና ገለልተኛ አካል የሚቋቋመው በህዝበ ሙስሊሙ ተቃትፎ እንጂ በመጅሊስ መራጭነት ወይም የመጅሊስ አካል በሆነው የኡለማ ም/ቤት አይደለም:: ምክኒያቱም ህጉ ስለሚ ነውና ይውረድ የተባለ አካል ምርጫውን አስፈፅሞ መሰሉን ከመተካት ውጪ ምንም ዓይነት ለውጥ ሊመጣ ስለማይችልና ሂደ ስለማይፈቅድ:: ካ1992ቱ የተጭበረበረ የመጅሊስ ምርጫ , እንኳ ከምርጫው በፊት ቀደም ብሎ ቢሮዎቹ ታሽገው ሂደ ምርጫው የተዘናጋነው:: መጅሊስ ቢሮው ታሽጎ ምርጫውን ካጭበረበረ ከዛ በባስ መልኩ ቢሮው ከፍት ሆኖለትና ለዜቲኖ የማጭበርበሩ ሰራ እያዋለው ምን ዓይነት ምርጫ ሊከናወን ይችላል:: የመንግስት አካልም ህዝበ ሙስሊሙ የእምነት ተቋሜን መሪዎች በፍትህና በነፃነት እንድመርጥ ያስችሉኛል ብሎ የሚያምንባቸውን ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ አካሎች እንዲሰይም ፡ኦኒታዎችን ከማመቻቸት ውጪ በራሱ ይህን ገለልተኛ አካል ሊመርጥም ሆነ ሊያስመርጥ አይችልም:: ይህ የህዝበ ሙስሊሙ መብት ነውና::

. ለእምነት መሪ ምርጫ እመቺ የምርጫ ጣቢያ:- ምርጫ በቀበሌ/በወረዳ ይካሄዳል ይባላል:: ይሁንና ይህ አካሄድ ዘርፈ በዙ ችግሮችን እንደሚፈጥር ይታወቃል:: ቦዮንኛነት አንድ የእምነት መሪ ቡትክክል የሚታወቀውና የሚመረጠው ምእመናኖች ኩሚገኙበት የእምነት ቦታ መስጂድ እንጂ የፖሊቲካና የአስተዳደር ቦታ ከሆነው ቀበሌ አይደለም:: አንድ የእምነት መሪ ከእምነት ተቋሙ ነው መመርጥ የሚገባው:: ቡተዉማሪም ምእመናኑ በመስጂዱ ውስጥ እንጂ በወረዳው ውስጥ ያለውን ሰው አበጥሮ አያውቅም እንኳን ስለ ስብእናው ለማወቅ ቀርቶ ከየት እንደመጣ እንኳ ለማወቅ ቡጣም አዳጋች ነው፤ ለህገ ውጥ መጠጽቀምና መመራረጥ እንዲሁም ምርጫዉን ለማጭበርበርም ከፍተት ይፈጥራል:: በመሆኑም ምርጫችን በመስጂዳችን ሊሆን ይገባል:: በሃገራችን ከቀበሌዎች በቁጥር እምብዛም ያልተናነሱ መስጂዶች ይኛሉ:: መስጂድ ላይኖራቸው የሚችሉ አንዳንድ ቀበሌዎች በአቅራቢያቸው ባለ መስጂድ መመረጥ ይኖርባቸዋል:: ከአንድ በላይ መስጂድ ያላቸው ቀበሌዎች ደግሞ እያንዳንዳቸው በመስጂዶቻቸው ሊመርጡ ይገባል:: ምክኒያቱም በዋኝነት መስጂድ በዙሪያው የሚገኙትን ምእመናኖች ሰብስቦ የያዘ ማን ምን እንደሆነ ተለይቶ የሚታወቅበት ብቸኛ የእምነት ተቋማችን በመሆኑ የእምነት ተቋም መሪ ምርጫችን በመስጂዳችን መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል::

. የምርጫ ቀን:- ከ1992ቱ የተጭበረበረው የመጅሊስ ምርጫ እንኳ የምርጫ ቀኑ ቀደም ብሎ በይፋ መታወጁ ይታወሳል:: የአሁኑ የምርጫ ቀን በይፋ የሁለት ወር እንኳ ጊዜ ባልተሰጠበትና ቀኑ በሚሸጢር ታይዞ ድምጽ ድምጽ ሰው ለማዘጋጀት ሩጫ እየተደረገ ምርጫው እንዴት ተጭማኒነት ይኖረዋል? የምርጫው ቀን ሊደርስ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት ምርጫዉን ይፋ በማድረግ የምርጫ ቅስቀሳ እንዳይኖርና ህዝቡ ማንን መምረጥ እንዳለበት እንዳይወያይ ፋታ በመንሱት በአቅጭ ህዝ ውስጥ እንደገቡ በሆነ የጥድፊያ ምርጫ የፈለጉትን ሰው ለማስመረጥ ማመቻቸት ህገ ወጥና አስነዋሪ ድርጊት ነውና በአፋጣን ሊስተካከል ይገባዋል:: ከወዲሁ ለቅስቀሳ የሚሆን ሰፊና በቂ ግዜ ተሰጥቶ በይፋ በማናናኛ ብዙሃን በሙሉ ሃገሪቱ ውጥኑ ያለው የምርጫ ቀን ይፋ ሊደረግ ይገባል::

ኢስላማዊና ዲሞክራሲያዊ::

. ሁሉን አቀፍና አሳታፊ::

ህገወጡ መጅሊስ ሳይሆን ሰፊው ህዝበ ሙስሊም የመነቡት የምርጫ መመሪያ:- የመራጭና የእጩ መስፈርት፣ የእጩ አቀራረብ፣ አዘገጋብ፣ ድምፅ አሰጣጥና የመጨረሻ አውጪዎች የያዘ::

አንደኛው ሰሞን አካል መሆኑን ና የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ ያካተተ ሰነድ ነው::

እነኚህ ሁሉ የምርጫ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ የሚደረግ ማንኛዉም ምርጫ ተቀባይነት የሌለው ህገወጥ ምርጫ ነው:: ወንጀልም ጭምር ነው:: ህዝብን መናቅና ድምፁን ማጭበርበር ነው:: ምርጫ ሳይሆን መሸለሙን ለመበጣጠት የሚደረግ ቅርጫ ነው::

በመሆኑም ከዚህ በላይ የሰፈሩትን አንኳር ነጥቦች ልብ በማለት ህዝበ መስሊሙ እርስ በርስ ተነጋግሮ ሲያቢታ ያገኘውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም እነኚህን መረጃዎች ላልሰማውና በከተማም ይሁን በገጠር ለሚኖ ወዳጅ ዘመዳችን በአካልም ይሁን በስልክ ለማድረስ ጁማዓ አወሊያ የጣባነውን ቃል ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል::

### የህዝበ ሙስሊሙ አቋም

በቅርቡ ከላይ የተዘረዘሩትን የምርጫ መስፈርቶች በማያሟላና ሁኑ በማይፈቅደው አግባብ የመጅሊስን ሽሩን በመጠቀም የሚፈልጋቸውን ሰዎች ወደ ስልጣን ለማምጣት የፈደራል ጉዳዮች በባለቤትነት እና የበላይ ጠባቂነት የመጅሊስ አመራሮች ምርጫን ለማከናወን እየተንደረደረ ይገኛል:: ይሁንና እንኳንስ በህዝብ ያልተመረጠው መጅሊስ ይቅርና ህጋዊ መጅሊስ ቢሆን እንኳ በምርጫው ውስጥ በምንም መልኩ እጁን ማስገባት አይችልም ይህ ህገ-ውጥ ተግባር ነው:: መንግስትም ምርጫው በሰላማዊ መንገድ እንዲከናወን ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ውጪ በእምነት ተቋም ምርጫ ጉዳይ ውስጥ እጁን

ፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

http://ethcriminalawnetwork.com/

በወረባቦ አካባቢ የተካሄደውን የሰደቃና የአንድነት ፕሮግራም ተካፍለው ወደ ሐይቅ በመመለስ ላይ እያሉ መንገድ ላይ የፌደራል ፖሊሶች ህዝብ የተሳፈረበትን መኪና በማስቆምና ፍተሻ በማካሄድ ተሳፋሪው መህከል የነበሩትን ዳዒ ሙሐመድ ፈረጅንና የደጋኑን ሻኽ- ሸኽ ኢድሪስን ለይተው በማስወረድ ለማሰር ሙከራ ሲያደርጉ የተመለከተው ህዝብ ተቃውሞውን ከሰራችሁ እነሱን ብቻ ለይታችሁ ሳይሆን ሁላችንም በአንድ ላይ ወደ ፖሊስ ጣቢያው እንሄዳለን እነሱን በፍፁም ከኛ ነጥላችሁ ልትወስዷቸው አንፈቅድላችሁም በማለት ሰፊ ተቃውሞ ቢሆን ጉዳዩ ከሰመ ፕሮግራሙን የተካፈሉ የወረባቡ አካባቢ ምእመናን ወዲያውኑ ወደ ሃይቅ የመጡ ሲሆን አጠቃላይ ቁጥሩ ከሁለት ሺህ የሚልቅ ምእመናን በቦታው ላይ እስከ ምሽቱ 3:00 ድረስ ፖሊስ ተከቦ ይቶ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ሳቢያ ዳዒዎቹና ሼኹ ተለቀው በጀመሩው እጀባ ደሴ ድረስ ተሸኝተዋል። ይሁንና መሃመድ ፈረጅን ጨምሮ ከአዲስ አበባ የነጻ ብዙ ዳዒዎችን ለመያዝ ደሴ እስከ አዲስ አበባ ድረስ በመኪና እያሳደዱና በየከተማው ኬላ ላይ እያሰሱ ከፍተኛ ከትትል ቢያደርጉም በአላህ ፈቃድ እነርሱን ሳያገኟቸው በሰላም አዲስ አበባ ገብተዋል።

በሀላባ ቁሊቶ ለሶስት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም እንደሚዘጋጅ ተገለጸ። ዛሬ ጁምዓ የሚጀመረው የሀላባ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም ከመጀመሪያውም ሰላማዊ እንደሆነ ምልክቶች እንደሆነ ምንጮቻችን ጠቁመዋል። በዝግጅቱም ላይ ታዋቂ ዳዒዎችና ከ10ሺ በላይ የሚሆነ ህዝብ ይሳተፋል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑን አብሮ ገልጸዋል።

በአንድነትና በሰደቃ ፕሮግራሙ ላይ ከሙስሊሙ ህብረተሰብ ባሻገር የሌሎች እምነት ተከታዮች እንደተጋበዙ ጠቁመዋል።

የደህንነት አካላት ሳይሆኑ እንዳልቀረ የተገመቱ ሰዎች የአወልያን የጥበቃ ሰራተኞችን በመሰብሰብ ሐምሌ 8 (ሰምንት) የመስጂዱን ቦ[illegible] እንዳያስገቡ ቀጭን ትዕዛዝ አስተላልፈዉ መሄዳቸዉ ተሰማ። ይህ ትዕዛዝ ፕሮግራሙን ለማደናቀፍ መንግስት እያሴረዉ ከሚገኘዉ ሴራ አንደኛዉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

ከተያያዘ ዜና ረቡእ እለት ከአስር ሰላት ቡኋላ የኮልፌ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ሀላፊ ኮማንደር ልኡል፣ የኮልፌ ክ/ከተማ የፍትህና ፀጥታ ጉዳዮች ሀላፊና የኮልፌ ክ/ከተማ አስተዳደር ከአወልያ መስጂድ ኮሚቴና ከአወልያ አስተዳደር ጋር ስብሰባ ማካሄዳቸዉ ተሰማ። በስብሰባዉም የአወልያ የመስጂድ ኮሚቴ የፊታችን እሁድ ሐምሌ 8 ሊያካሂደዉን ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራሙን እንዲያስቆሙ በመንግስት በኩል መጠየቃቸዉ ነዉ የተገለፀዉ። የመስጂዱ ኮሚቴም እኛ ይህንን ማስቆም አንችልም። ይህ ፕሮግራም የግለሰቦች ሳይሆን የህዝቡ ነዉ። ፕሮግራሙ ፍፁም ሰላማዊ ነዉ። ከሌሎች መስጂዶች የተለየ ነገር አይደረግም። ከሌላዉ የሚለየዉ በሁሉም መስጂዶች ይካሄድ የነበረዉ በአንድነት አንድ ቦታ መካሄዱ ብቻ ነዉ በማለት ፕሮግራሙን ማስቆም እንደማይችሉ ገልፀዋል። የመንግስት አካላትም ፊታቸዉን ወደ አወልያ አስተዳደር በማዞር ለአወልያ መስጂድ ኮሚቴ ፕሮግራሙን እንዲያግድ ደብዳቤ ፃፍ። ለኛም ደብዳቤ ፖፍልን። ለመረጃነት ይጠቅመናል በማለት ትዛዛቸዉ ሲያቀርቡ የአወልያ አስተዳደርም እኛ ደብዳቤ ብንፅፍ የሚሰማን [illegible] እኛ በመጅሊስ ስር የተቸገምን ስለሆነ እኛ የምንፅፈዉን ደብዳቤ የሚቀበለን የለም። ደብዳቤ በመፃፍ ጊዜያችንን ከማቃጠል ዉጪ ሌላ ምንም እናተርፍም በማለት አስተዳደሩም [illegible] ፅ የሚካሄደዉን ሀገር አቀፉ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራሙን መሰቆም እንየማይችል ገልፀዋል። ስብሰባዉ አስክ ምሰቱ 2ሰአት የቆየ ሲሆ [illegible] መጠናቀቁን ምንጮቻችን ገልፀዋል።

## የማስመሰያዎች ማጋለጫ

ውድ ሙስሊሞች የአላህ ሰላም በናንተ ላይ ይሁን:: ባሳለፍነው ሳምንት ብዙ የተደበቁ ጉዶችን አየን!! ሰማን!! ሃሰትን ለማንገስ የሚደገው ሩጫ በማን አለብኝ ስሜት በገሃድ ታየ:: እኛም መንግስት በጓዳው ውስጥ ተደብቆ ሲፈፅማቸው የነበሩ የሃሰት ፕሮፓጋንዳዎች እና የመብት ጥሰቶችን በግልፅ ለሚመለከተው ሁሉ ባለፉት ቀናት ሰላሳየልን እናመሰግነዋለን:: ከእንግዲህ ህፃኑም ይሁን አዛውንቱ ሙስሊሙም ሆነ ሙስሊም ያልሆነው እየተፈፀመብን ሰላለው ግፍ ከበቂ በላይ በሆነ ደረጃ እውነታዉን አራሳቸው አሳይተውልናልና::

በገፅ አንድና ከላይ የሰፈሩ ጫናና ትንኮሳዎችን ለተመለከተ ሁሉ የሚከተለውን ለማረጋገጥ ይገደዳል:: ህግን ልናስከብር ነው የቆምነው ባሉበት እንደበታቸው ህግን ተላልፈዋል! መብትን ጥሰዋል! የእመነትና ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ነፍገዋል! ጨርቃችንን ጥለን ቆመን ያጨበጨብንለትን ህገ መንግስት እናስከብራለን እያሉ ህገ መንግስትን ሽርፈዋል! በተጨባጭ የሌለ ስእል በመሳል ህብረተሰቡ ላይ ሽብር ነዝተዋል! የሚፈልጉትን ወንጀል ለመስራት ቀድመው ያንኑ ወንጀል ሰርተዋል በማለት የንፁሃንን መልካም ስም አጥፍተዋል! አውን ይህ ሁሉ በደልና ግፍ ከመንግስታችን የምንጠብቅው ነበርን? እስከዛሬ ድምፃችንን እየሰጠን የመረጥነው የህልውናችን መሰረት የሆነው እምነታችን ላይ ይህን መሰል ግፍ እንዲፈፀምብን ነውን? ይህ ነው ምላሹ?

ቀድሞ የነበሩ አፄዎች አንድ ላይ ቢጋራ ይኖር የነበረውን ማህበረሰብ አኗኗር ባለመቀበል በሙስሊሙ ላይ አጎጣጥረውና ጠራቸውን ሰብቀው የቻሉትን ሁሉ ግፍ በአባቶቻችን ላይ ፈፀሙ:: ለኢስላምና ሙስሊሞች ያላቸውን ጥላቻና ጠላትነታቸውን በግልፅ አወጁ:: ሙስሊሞችን ለማጥቃት የሚያመዛዝኑት ሙናፊቆች ከጎናቸው አሰለፉ:: ዛሬም ይኸው ሁኔታ መልኩንና ገፅታውን ቀይሮ በዲሞክራሲ ስም ከፊት ለፊታችን እየተጋረጠ መሆኑን እንድናስተውል አጅርጎናል:: በቀደሟት ሙስሊም አባቶቻችን ስም መጡ አስተሳሰብ፣ በግድ በዲናችን ላይ ለመጫን፤ መስጂዶቻችንና መድረሳዎቻችን ከዚህ መጤው የአህባሽ አስተሳሰብ ውጪ አስከዛሬ የቆየንበትን ትክክለኛው የዲናችን አስተምህሮ እንዳይኖር በማድረግ ትውልድን ለማኮላሸት የሚደረጉ መፍጨርጨሮችን ተመልከተናል::

ይህ ሁሉ ግን በዲሞክራሲ ሰም ነው የሚደረገው:: ለሙስሊሙ ዘብ የቆሙ በማስመሰል:: ሙስሊምን ከአሸባሪ ቡድኖች ለበጠበቅ ነው በማለት:: በአጠቃላይ እራሳቸውን ለኛ ሙስሊሞች ጥብቅና የቆሙ በማስመሰል በስውር የሚፈልጉትን ድብቅ አጀንዳ ለማስፈፀም ሲረዋጡ መመልከት ምንኛ ያሳዝናል!! ድብቅ አጀንዳቸውን ለማስፈፀምና ይህን ግፍ አልቀበልም ያለን ሁላ ለመድፈቅ እንዲረዳቸው ድብቅ አጀንዳ ያላቸው ቡድኖች ናቸው በማለት የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ጠምዝዘው በንፁሀኑ መብት ጠያቂ ላይ ያላከካሉ:: ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል!! ይኸው ነው እንግዲህ እየሆነ ያለው::

በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ አህባሽን ለማንገስና አህባሽ መራሽ መጅሊስ ለማቋቋም የሚውተረተሩት ይህን ድብቅ ሙስሊሙን በዲሞክራሲ ስም ከፋፍሎ የመምታት አጀንዳ ለማስፈፀም ካልሆነ በቀር ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ ለምን አስፈለገ:: ሀሳባቸው ይህን መሰረት ከላደረጉ ዲሞክራሲን አናሰፍናለን እያሉ «በጻሮ በር የገቡ የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉንም እና ወርደው በምትካቸው በፍትሃዊ ምርጫ የእምነት መሪዎቻችንን እንምረጥ» በማለታችን ይህ ሁሉ ቂያማ ለምን ይወርድብናል?

መብታችን ተገፎ ተሰባስባችሁ ሰደቃ አታድርጉ የምንባልበት፣ ተወካዮቻችን በየቦታው እየተያዙ ዛቻና ማስፈራሪያ የሚለቀቅባቸው ዘመን መጣ? እዚህም እዚያም ትንኮሳዎች ጉድ እኮ ነው!! ይህ ህገ-ወጥ ተግባር ነው!! ህገ መንግስቱን የሚሸራርፍ የመብት ጥሰት ነው!! መብታችንን ለማስከበር ደግሞ እስከመጨረሻው እንታገላለን!! ይህ ደግሞ የማይሻርና የማይሸረሸር አቋማችን ነው!!

እኛ ሙስሊሞች ነን:: ሀገርና ሰላም ወዳድ ዜጎች:: ለሃገራችን ሰላም፣ ልማት፣ እድገትና ብልፅግና ዘብ የምንቆምና ጠንክረን የምንሰራ ሰላማዊ ዜጎች:: የዘመናት መገለሎችን የሻረው ህገ መንግስቱ እንዲከበር ከማንም በላይ በፅኑ የምንፈልግ ህግ አክባሪ ዜጎች:: የሌላውን መብት አክብረን ከሌላ እምነት ተከታይ ወንድሞቻችን ጋር በመቻቻል ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የህብረተሰባዊ ግንኙነት እንዲጎለብት ተግተን የምንቆም ዜጎች:: በአንጻሩ በዲናችን ህልውና ላይ ለሚመጣብን ዲናችንን ለመጠበቅ ሰንል ያለንን ነገር ሁሉ መስአትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆንን ዜጎች ነን::

በመሆኑም መንግስት እየተደረጉበን ያሉ የመብት ጥሰቶች ቆመውና የተፈጠሩ ችግሮች ታርመው በሰላማዊ መንገድ እልባት እንዲያገኙ አሁንም እንጠይቃለን? ትንኮሳዎች ሁሉ ይቁሙ? በየወረዳዉና በየአካባቢው የሚደረጉ ስብሰባዎች ዓላማቸው የህዝብ የሆነውን የምርጫችን በመስጂዳችን ጥያቄና አስመራጩ የመጅሊሱ ኡለማ ም/ቤት ሳይሆን እኛ አምነን በየአካባቢያችን የምንሰይማቸው አካሎች ይሁኑ የሚለውን ጥያቄ ለመቀልበስ መሆኑ ቀርቶ ጥያቄዎቹን ተቀብሎ ለመደገፍ የሚደረጉ እንዲሆኑ እንጠይቃለን?

## ታላቅ ሀገር አቀፍ የሰደቃ የአንድነት የዱዓና የዳዕዋ ጥሪ!!

በአወልያ የፊታችን እሁድ ሀምሌ 8 የሚካሄደዉን ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራሙን ለማከሸፍ ከፍተኛ ጥረቶች እየተነረጉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል:: በዚህም ሙስሊሙን በየአካባቢው በመሰብሰብ አወሊያ አትሂዱ ብሎ ባዶ ሽብር ከመንዛት ጀምሮ እስከ እናቶችንና ትልልቅ ሰዎችን በየሰፈሩ በካድሬዎች አማካይነት ማባበልና ማስፈራራት እየተደረገ ይገኛል::

ባለፈው ሳምንት የተደረጉ የሰደቃ ፕሮግራሞችን ለማኮላሸት ጥረት ሲያደርጉ የከረሙትና ኮሚቴዎቻችንንም ላይ የፎከሩት የአወሊያውን ታላቁ ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራምን ለማስተጓጎል አስበው እንደሆነ ግልፅ ነው:: በመሆኑም በአምባሳደሮችና በሌሎችም አካባቢዎች የታየዉን ከፍተኛ የዲን ፅናት በበለጠ መልኩ በማንገብ ሁሉም የአዲስ አበባ ነዋሪ እንዲመጣ ታላቅ ጥሪ ተላልፏል:: ከሌሎችም ከተሞችና አካባቢዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ እንግዶች ፕሮግራሙን ለመካፈል አዚህ አዲስ አበባ ከዛሬ ጀምሮ አንደሚገቡ ታውቋል:: ይህ ታላቅ ህገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም እስመልከቶ ሁሉም ሙስሊም የአቅሙን አስተዋፅእ በማበርከት በአጭር ሰዓት ውስጥ የተገኘው ምላሽ አስደናቂ ነበር:: ይህም የመዲናችን ሙስሊም ባለው አቅም ሁሉ የሚያደርገዉ ርብርብ ከፕሮግራሙ ስፋት አንፃር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባው ጥሪ ተላልፏል:: ይህን ለማደናቀፍ የሚያደረጉት ሙከራ ሊኖር ቢችል እንኳ የያዝነው ሃላፊነት ሠላማዊና ህገ-መንግስቱን ያከበረ እስከሆነ ድረስ ምን ጊዜም ቢሆን ወደ ፊት እና ወደ ፊት ብቻ በመጓዝ የቤት ስራዎቻችን ለአፍታም ቢሆን ሊደናቀፉ አይገባም:: በመሆኑም የአወሊያ ሐምሌ ስምንት ፕሮግራም ዝግጅት ተጧጡፎ መቀጠሉን እያበሰርናችሁ ሁሉም ሙስሊም ከዛሬ ጀምሮ በቦታው በመገኘት የበኩሉን ዐብነትናዊ ትብብር እንዲያደርግ በድጋሚ ጥሪውን በአላህ ስም ተላልፏል:: አላህ ኸይር ይወፍቀን::



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

# ዲምፃችን ይሰማ!!

ቁ.18

06-11-2004 E.C

27ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ !!


## በኮሚቴዎቻችን ላይ የተፈፀመው ትንኮሳና የህዝበ ሙስሊሙ ቁጣ

ዓለማዊ አለም የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጲያዉያን ሙስሊሞች በፌርማቸዉ አረጋግጠዉ የወከሉት የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኡስታዝ አቡበከር አህመድና ኡስታዝ አህመዲን ጀበል ረቡዕ ቀን ኢስታዝ ካሚል ሸምሱ ደግሞ ሃሙስ ቀን በደህንነቶች ተወሰደው ከንቱ ዛቻና ማስፈራሪያ ተነግሯቸዋል።

ዚህ ዛቻና ማስፈራሪያተብዬዎች መካከል ኡስታዝ አቡበከር አህመድን ከዚህ ቡሀላ በኢትዮጲያ ዉስጥ ለሚፈጠረዉ ችግርና የፈታችን ሐምሌ 8 በአወልያ ይካሄዳል ተባለዉ ፕሮግራም ላይ ለሚፈጠረዉ ችግር ሀላፊነቱን የምትወስደዉ አንተነህ ሲሉ። በእጠቃላይ ለ3ቱም ደግሞ እናንተ ሀገሪቱን ለማተራመስ እየተንቀሳቀሳቹ ትገኛላቹ። ሀገ ጥ ናችሁ። በሰደቃ ስም ሀገሪቱን እያመሳችሁት ትገኛላችሁ። ከዚህ ቡሀላ ማንኛዉም ኢይነት ሰደቃ የሚባል ፕሮግራም አንዳንስማ። ከዚህ ቡሀላ ኮሚቴ ነን የምትሉትን አማርኛ ቋሙ። እናንተ ሀገ ወጦች ናችሁ በማለት ማስፈራሪያቸዉን ለመቀጠል ሲሞክሩ ጀግኖቹ የኢስላም ልጆች እኛ ህገወጥ አይደለንምነ ህገ ወጥ እናንተ ናችሁ በማለት መልሰዋል። ነጎዳቹም እኛ እኩ እ ነ የመጣናች ለሰብሰባ አይደለም። እናንተን አንድም ሙስሊም እልመረጣችሁም። ህዝብ በድምፁ የመረጠዉ ኢህአዴግን ብቻ ነዉ። ከዚህ ቡሀላ መሬ የማበል ነገር መንግስት አየቀባለሁም። መንግስት በ ነ ነ ነ

ድምፃችን ይሰማ!! ቁ.15

# 24ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ !!

15-10-04 E.C

## ህዝበ ሙስሊሙ ዲኑ እንዲነካበት አይፈቅድም!!

አለላሙ አለይኩም:: አሁድ አለት በ አአ ደረጃ በሁሉም ወረዳዎች ላይ ያቀዱትን የምርጫ ህጉን የማያመሟላ የመጅሊስ ምርጫ እንዲተገበር ሙስሊሙን ለማወያየት የተጠራው ስብሰባ ሙሉ በሙሉ በህዝበ ሙስሊሙ ተቃውሞ ተደመደመ:: አላሁ አክበር!! አላሁ አክበር!!

ህዝበ ሙሲሊሙ በሁሉም ወረዳ ማለት ይቻላል «የምመርጠው የእምነት መሪዬን እንጂ የፖለቲካ ተወዳዳሪ አይደለም፣ ምርጫችን በመስጂዳችን ብቻና ብቻ ነው፣ መንግስት በሃይማኖታችን ላይ ጣልቃ መግባት አይችልምና እጁን ከዲናችን ላይ ያንሳልን፣ እናንተ ምን ቤት ሆናችሁ ነው እንዴትና ማንን መምረጥ እንዳለብን ልትነግሩን መድረክ ላይ የወጣችሁት» የሚሉ አስተያየቶች ለመድረክ መሪዎቹ በማያሻማ ቋንቋ ተነግሯቸዋል በተለይ ከአባቶችና ከሽማግሌዎች የተሰነዘሩት አስተያየቶች አስደማሚ ነበሩ « በአድሜያችን ውስጥ እንዲህ ዓይነት ነገር (የአህባሽን አስተሳሰብ) ዓይተን አናውቅም ከአባቶቻችንም አልሰማንም ዲናችን በመጤ አስተሳሰብ ሲጠፋ ደግሞ በጭራሽ ቆመን አናይም ሁሉም ነገራችንን መሰዓትነት ከፍለን እስከመጨረሻው እንታገላለን» ብለዋል ህዝቡም በተ ኛ ተከቢራ በማጀብ አጋርነቱን ገልፆዋል:: በዚህ መልኩ ብዙ የሰብሰባ አዳራሾች በተከቢራ ደምቀው ቁጥር 2 አሠሊያ ሆነው ዉለዋል:: መድረኩ በሽማግሌዎች ዱዓ የተጠናቀቀባቸውም ወረዳዎች አሉ::

ይህ ቢገባቸው ህዘበ ሙስሊሙ ዲኑ እንዲነካበት እንደማይፈቅድ ትልቅ ትምህርት ነበር:: ነገር ግን አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንዲሉ ይህ አልሳካ ቢላቸው ሌላ ሙከራ ለማድረግ ሲፍጨረጨሩ ይታያሉ:: ይኸውም በአንዳንድ አካባቢ የሌላ እምነት ተከታይ ወንድሞቻችንን አከራሪዎች የአስልምና መንግስት ለመመስረት ተነስተዋል በጋራ ሆነን ልናስቆማቸው ይገባልና ምን ትጠብቃላችሁ ከንናችን ሁኑ ዓይነት እንድምታ ያለው መልእክቶችን ለማስተላለፍ ሞክረዋል:: ይሁንና የሌላ እምነት ተከታይ ወገኖቻችን የእምነቱ አባቶች ሳይቀሩ ጥያቄያችንን ጠንቅቀው የሚያውቁ በመጅሊስ ሽፋን የተጫኑብንን ግፍ የተረዱና በየአጋጣሚው በፀሎት ከናንተው ጋር ነን ፈጣሪ መልካም መሪ ይተካላችሁ ሲሉ ነበርና የከረሙት ከመድረክ የተነበበውን ተረት ተረትና መሰረተ ቢስ ውንጀላ ጆሮ አልሰጡትም:: ይሁንና በመድረክ መሪዎቹ ውስጥ ለውስጥ ተዘጋጅተው ስርገው የገቡ አንዳንድ ግለሰቦች ከመድረክ የሚነገረውን በማሚሚት እንድምታውን ለመቀየርና የታዳሚውን ልቦና ለመስረቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል::

በተመሳሳይ በአንዳንድ ወረዳዎች ላይ በድብቅ የሚፈልጉትን ሙስሊሞች ብቻ ጠርተው ቀድመው ካዘጋጇቸው ግለሰቦች (የሌላ እምነት ተከታይም ይገኙበታል) ጋር ደምረው ስብሰባ በማካሄድ አሁድ ቀን በህዝበ ሙስሊሙ የመከነውን ስብሰባቸውን ለማደስ ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል:: በዚህ ስብሰባ ሆን ብለው ጥቂቶች ብቻ ምርጫችን በመስጂዳችን አበዛኛው ምርጫው በውጪዳ ይሁን እንዲሉ አድርገው ይኸው የአብዛኛው ሙስሊም ፍላጎት እኛ እንዳልነው ነው ለማለት ሞክረዋል:: አሁንም ደግመን እንላለን እንዲህ አዓነቱ ቀልድና ንቀት በአፋጣኝ ይቁም እንላለን::

ሌላው ማከሰኞ ቀን መጅሊስ የተለያዩ መስጂዶች ውስጥ የምፈልገውን አሊማ ሊያስፈፅሙሊኝ ይችላሉ በሚል የተወሰኑ ሰዎችን ጠርቶ ስብሰባ አድርጓል:: ከስብሰባው ቡኋላም ምርጫችን በመስጂድ ይሁን የሚሉት እነሱ ናቸው እትስሚችው የሚልና መሰል ፍሬ ቢስ ተረት ተረት የያዘ ፔቲሽንና የአህባሽ መፅሃፍ ለተሰብሳቢዎቹ በመስጠት በየአካባቢው ሂደው ፔቲሽኑን እንዲያስፈርሙ መፅሃፉን እንዲቡትኑ ልከዋቸዋል:: ግን ከሙስሊሙ

ደበቅ እንድም ነገር የለምና በተለያዩ አካባቢዎች እየተጋለጡ ይገኛሉ :: እኛም በየአካባቢያችን ካጋጠሙን ስራቸው የህ- ..ሙ መጅሊስና የአህባሽ መሆኑን በግልፅ በማወጅ በህዝቡ ፊት እናጋልጣቸው::

ከላይ የተጠቀሱትን እየተሰሩ ያሉ ድራማዎች ዲሞክራሲ በሰፈነባት ሃገራችን በሙስሊሙ ላይ ሊፈፀሙ ማየት ልብ ይሰብራል! ይህ ህዝብን የሚያስኮርፍ መልካም አስተታደርን የሚያደፈርስና ለሃገርም ለህዝብም የማይጠቅም ነውር ነውና በአፋጣኝ ይቁም እንላለን:: እኛ ሙስሊሞች በምንም አይነት ስያሜና በመጅሊስ ተራ የማወናበድ ተግባር አንድነታችን ቅንጣት ያህል የማይሸረፍ መሆኑን በተግባር አላይተናል:: ማንም አካል በኛ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ገብቶ ምንም ሊለን አይችልም!! የምንፈልገው ዓይነት ነፃ ምርጫ ይደረግልን ብለናል ይደረግልን!! የምን ማጭበርበር ነው? በመሆኑም ምርጫውን ለማጭበርበር በሚደረጉ ማንኛቸዉም ዓይነት የመጅሊስም ይሁን የመንግስት ማደናገሪያዎች የማንታለልና ጆሮ የማንሰጥ መሆናችንን በድጋሚ በተግባር ማሳየትና ምርጫዉን ነፃና ፍትሃዊ ለማድረግ ያለንን ቁርጠኝነት የበለጠ ልናሳድግ ይገባል::

አላህ ያግዘን ከሁሉ በላይ ሃያልና ቸር ነውና!! አላህ ታላቅ ነው!!

1

ፌርማ ... ር ተመሳክሯል

http://ethcriminalawnetwork.com/

## ድምፃችን ይሰማ

01-10 32

ኢስላም ህይወቴ ነው
ኢስላም ነው እምነቴ
ይከበር ይከበር ይከበር እምነቴ
ይወገድ ፍርሃቴ ይምጣ ነፃነቴ

ሀገ መንግስታዊ የመብት ጥያቄኣችን በአግባቡ አልተመለሰም። ስለዚህ . . . ሰላማዊ እና ታሪካዊ ትግላችን ይቀጥላል።

መሪዎቻችንን ማንም ሊመርጥልን አይገባም!!

እናንተ የእስላም ልጆች ሆይ፡-

ፍትሃዊ ምርጫ ለማካሄድ የተሰራጨውን የፊርማ ማሰባሰቢያ ቅፅ ከየመስጂድው ውስጥ በመፈረም እስላማዊ ሀላፍትናዎን ይወጡ። አደራ . . . አደራ . . . አደራ . . .

በክፍለ ሀገር ወገኖቻችን ላይ የሚደርሰው ህገ-ወጥ ዛቻ እና ማስፈራራት እንዲሁም በህገ - መንግስት ሽፋን ዜጎችን እየተሰጠ ያለው የአህባሽ ስልጠናም ሆነ ፍትሃዊ ያልሆነ ምርጫ ይቁም!!

ይህ ሰላማዊ ድምፃችን ሊሰማ ይገባል !!

ህዝቡ ይከበር !!

አላሁ አክበር አላሁ አክበር አላሁ አክበር

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

537

LCHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

ዜና፡- . የህገ ወጡ መጅሊስ የውለማ መ/ቤት ከትላንት በስቲያ ረቡዕ 20/10/04 የአጠቃላይ ህዝበ ሙስሊሙን ጥያቄ የሚቃረን መግለጫ አወጣ። በመግለጫው ምርጫው የሚከናወነው በቀበሌ መሆኑንና ነሐሴ21 የቀበሌ፣ ነሐሴ28 የወረዳ፣ ጳጉሜ1 የክልልና መስከረም5 የፌደራል ምርጫ እንደሚከናወን ገልፆዋል። ይሁንና ህዝበ ሙስሊሙ ምርጫው እንዳይጭበረበር በመስጂድ መሆን አለበት፤ የህያግኖት መሪዬን የምመርጠው ከሃይማኖት ተቋሜ ከመስጂድ እንጂ ከቀበሌ አይደለምን፤ ከቀበሌ የፖለቲካ እንጂ የህይማኖት መሪ አይመረጥም፤ ሌሎች እምነቶች መሪያቸውን በራሳቸውና በተቋማቸው እንደሚመርጡ ሁሉ እኔም መሪዬን በተቋሜ በመስጂዴ እራሴው ልምረጥ ብሎ ሲያሰማው የነበረውን ጥያቄ የሚቃረን ስለሆነ ህዝበ ሙስሊሙ መግለጫዉን የማይቀበለውና የሚያወግዘው መሆኑን እየገለፀ ይገኛል።

በመግለጫው መስጂድ ሃይድ ላይ ላሉ ሴቶች ስለማይመች ነው ብሎ ያነሳው ምክኒያት ሃይማኖቱን ካለማወቅ የመነጨ ተልካሻና እዚህ ግባ የማይባል ምክኒያት ነው፤ ምክኒያቱም መስጂዱ ውስጥ ገብታ መስገድ እንጂ እግቢው ጉበታ በሚዘጋጀው ድንኳን ውስጥ እንዳተመርጥ የሚያግድ አንድም ነገር በዲናችን የለም ተብሏል። ዛሬ በአወሊያና በሌሎችም ቦታዎች የተሰያየ ከፍለሃገሮችን ጨምሮ ሙስሊሙ ይህን መግለጫ እንደማይቀበለውና በከፍተኛ ሁኔታ በፅኑ እንደሚያወግዘው ይጠበቃል።

. አሕባሽን ለማጠናከር የሱፍያ ማህበር እና አህለሱና በማለት ያቋቋሙትን ሰብሰብ ሰኞ ሰኔ 18-2004 ማዘጋጃ ቤት ሰብስበዋቸዋል። የአህባሽ አቀንቃኝ ናቸው ተብለው የሚታሰቡት ወደ 250 ሰዎች ለስብሰባው የተጠሩ ሲሆን 150 የሚሆኑት ተገኝተዋል። የፌደራል መጅሊስ የውለማ ምክር ቤት ሰብሳቢ እንዲሁም የሥራ አስፈጻሚ እና አባላት የላኮመን ጠርሙን በመሆን ሰዎ ዝርዝር ያቀረበ ሲሆን

ከአስመራጮች፡- 1. አቶ ታደለ ደሳለኝ። 2. ሸህ መዚድ። 3. ሸህ ዓብዳል መሊክ ቀርበዋል።

ከሥራ አስፈጻሚ ውስጥ፡- 1. የነታው ሸኽ ልጅ የሆኑት ሸኽ ያቴ መሀዲን ሊቀመንበር ( እሳቸውን ሊቀመንበር ያደረጉበት ምክንያት እሳቸውን ከፊት በማስቀመጥ ሌሎች ሱፊዮችን እናስገባለን በሚል መሆኑ ታውቋል) 2. ሼህ መሃመድ ኑር ምክትል ሊቀመንበር የተደረጉ ሲሆን 3. የትግራይ ተወላጁና ከዚህ ቀደም በሲኩሪቲ ስራ ላይ ቱስግር የነበረው መ/ር መሃመድ የሱፍ ዓለሙ ፀሃፊ ሆኖ ተሰይሟል።

ከአባል ደግሞ፡- 4. አህመድ ኢብራሂም ከኢቃቂ ክ/ከተማ 5. አወል ላልመዳ ከኢቃቂ ክ/ከተማ 6. መሃመድ አሚን ከጉፋስ ስልክ ሳፍቶ ክ/ከተማ 7. አብዱራህማን አልፈቂህ 8. መሃመድ ኑሪ አልፈቂህ 9. ኡስማን ረዲ

ከአስራ አንዱ የስራ አስፈጻሚና አባላት መካከል ዘጠኙ ከላይ የተጠቀሱት ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሁለቱ ደግሞ እንደኛው አባል የበኒ መስጂድ ምክትል ሊግም ሌላኛው ደግሞ ኳስ ሜዳ ያለው ሐጂ ዩሱፍ መስጂድ ጀምዓ የሚያስገዱት ግለሰብ መሆናቸው ታውቋል። ከአስራ አንዱ አባላት መካከል በመድረክ ላይ ስማቸው የተጠራው (የተነበበው) የዘጠኙ ብቻ የነበረ ሲሆን ይህም የተደረገበት ምክንያት ቀሪዎቹን መጨረሻ ላይ የተጠቱት ሁለቱን ግለሰቦች በማህበረሰቡ ዘንድ "ላለማስጠቆር" እንደሆነ ታውቋል። በዚሁ ስብሰባ ላይ ፀሃፊው አቶ አዘዲን ምርጫው አነሱ በማረጋገጥ መልኩ እንደሚከናወን ገልፀዋል።

. ለ15ኛ ጊዜ በ4 የተለያዩ መድረኮች የተካሄደው የአለም አቀፍ ድምፃችን ይሰማ መድረክ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴውን እንቅስቃሴ በፅኑ እንደሚደግፍ ገልፆዋል። በሚኒሶታ የተካሄደው ኮሚኒቲ፤ የኢቅራዕ ኮሚኒቲ፤ የተውፊቅ እንዲሁም በስውዲን፤ ለኢትዮጲያ ሙስሊሞች ለሚያደርጉት ሰላማዊ ሰልፍ ህ/ሰቡ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ አድርጓል። በቅርቡ ከተቋቋመው ዓለም አቀፍ የኢትዮ ሙስሊሞች ጀስቲስ ካውንስል ጋር በመተባበር ለመፍትሄው አፈላላጊ ኮሚቴው ሙስሊሙ ድጋፍ እንደሚሰጥም ተገልፆዋል።

የፕሮግራሙ አስተባባሪ መሃመድ ሃሰን በዓለም አቀፍ የድምፃችን ይሰማ መድረክ በአስባዓዊ መብት መከበር ላይ ይሰራልም ብለዋል።

ከዝግጅቱ መካከል እንጋፋው ጋዜጠኛ ሁሴን በዳሶ በእንግድነት እንደተጋበዘ ታውቋል። በመጨረሻም በአሜሪካና በአውሮፓ በመጪው አርብ የሰላማዊ ሰልፍ ይካሄዳል ሲሉም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

. ባለፈው ሰምንት በሰለፈ ሷሊሂን፣ በሾንኬ ፈረንሳይ መስጂድና በሃምፃ ካራቆሬ መስጂድ በአይነቱ ልዩ የሆነ የእንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም ተካሄደ። በዚህ ፕሮግራም ላይ ታላላቅ አሊሞች፣ ታዎቂ ዳኢዎች፣ የመስጂድ ኢማሞች እና ሙአዚኖች፣ ታላላቅ የሀገር ሽማግሌዎችና ሙስሊም ባለሀብቶች ተገኝተዋል። በሰለፈ ሷሊሂን የተካሄው ፕሮግራም አንድ ትልቅ ድንኳን ሙሉ የሚሆኑ የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ተካፋይ በመሆን አጋርነታቸውን አሳይተዋል።

ከፍለሃገር የባቲና አካባቢዋ ሙስሊም ኅብረተሰብ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም ከ40,000 በላይ የሆነ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ምዕመናን ታድሞበት በደማቅ ሁኔታ ተካሂዷል። ፕሮግራሙ እንዳይካሄድ እና ይህንም በዝግጅቱ ላይ እንዳይሳተፍ ለመንግስት ሰራተኞች ሳይቀር ከአካባቢው አስተዳደር ትእዛዝ ቢተላለፍም ሁሉንም ይህንን ችላ በማለት ወደ ዝግጅቱ መትመም የጀመረው ገና ቡኋቱ ነበር። ህዝቡን ወደ ዝግጅቱ በማምጣት የተሳካዋ ባጀጆችና ሚኒባሶች ለእንድነት ፕሮግራሙ ነፃ አገልግሎት እንሰጣለን ብለው ለጥፈው በነፃ ህዝቡን ወደ ፕሮግራሙ ቦታ አመላለሰዋል። በቀጣይ አማራ ክልል ከደሴ ከተማ 20 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘዉ ቁሉቢ ወረዳ የፌታችን ቅዳሜ ታላላ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም ለማዘጋጀት የወረዳዉ ሙስሊሞች እየተዘጋጁ መሆናቸዉ ተገልፀዋል።

. ጁምዓ በጅማ ከተማ አምስት መስጂዶች ላይ የተቃውሞ ተክቢራ ነበር። በድሬደዋ ከ3 ሺህ 500 በላይ ምዕመናን ከጁምዐ ሰላት በኋላ በከተማዋ አደባባዮች ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የመጅሊስ ምርጫ ግልጽና ፍትሃዊ እንዲሆን፤ በዚህ ጥያቄ የታሰሩ ሙስሊሞች እንዲፈቱላቸው ጠይቀዋል። ሰላማዊ ሰልፈኞቹ የቢላል መስጂድን መነሻ በማድረግ በከተማዋ ዋና አስፋልት መንገድ በሚገኙ አደባባዮች ከ ከ[illegible] ሜትር በላይ በመጓዝ ተክቢራና መፈክር ሲያሰሙ እንደነበር ተገልፆዋል። አላሁ አክበር!!



http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምፃችን ይሰማ!! 36 ቁ.16

## 25ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ !! 22-10-04 E.C


### «እኔ ነኝ የምወስንልህ» ማለት ፀረ ዲሞክራሲ አካሄድ ነው !!

መጅሊስ ላለፉት ዓመታት ሳንመርጠው በግድ ተጭኖብን የፈፀመብን ግፍ ሳያንስው ከቅርብ ግዜ ወዲህ ሽፋን ሆኖ በሃይማኖታችን ላይ የሙበት ጥሰት በመፈፀም በዲናችን ላይ መጣብን፤ አዲስ መጤ የሆነውን አህባሽ በግድ ተቀበሉ አለን፡፡ ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች በዲናችን ላይ በሚመጣብን ነገር በፍፁም የማንደራደር በመሆኑ፤ ለስድስት ወራት ጠንካራ አንድነታችንን በማሳየት መብታችን እንዲከበር ታግለናል፡፡ አነድነታችን ከሙቼውም ግዜ በላቀ መልኩ ጠንክሮ እኛን ለመከፋፈል የሚደረገውን ጥረት በማምከን ምርጫችን በመስጂዳችን በማለት ምርጫውን ለማጭበርበር የሚደረጉ ጥረቶችን ሁሉ መልሰናል፡፡ ይህ ትግል እስካሁን ብዙ ፍሬዎችን ያስገኘ ሲሆን ከነዚህ ፍሬዎች ውስጥም ሙስሊሙ መሪዎቹን በራሱ መምረጥ ህገ-መንግስታዊ መብቱ መሆኑን አውቆ ራሱን ለምርጫ ማዘጋጀቱ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ በመጅሊስ ጉዳይ ላይ ከማንም በላይ መብትና ግዴታውን በሚገባ አውቋል፡፡ ነጋሪ አያሻውም፡፡

ይህ እየታወቀ ታዲያ ህዝብን መናቅ ለምን ተፈለገ? ስብሰባ ብለው ጠርተውን በሁሉም ወረዳ ጣልቃ አትግቡብኝ፤ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ለማድረግ ምርጫው በመስጂዳችን ሊደረግ ይገባል፤ ይህ ደግሞ የማንደራደርበት መብታችን ነው! ብለን አስረግጠን አቋማችንን ገልፀናል፡፡ ምን እንደምንፈልግ ታይቶ በማይታወቅ ፅናት ለስድስት ተከታታይ ወራት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ጠይቀናል፡፡ እንደ ሙዥገር በመጅሊስ ወንበር ላይ ተጣብቀው ህዝበ ሙስሊሙን ያተራመሱ፣ የመዘበሩ፣ የእምነት ነፃነቱን በመግፈፍ በግድ አህባሽ ካልሆንክ ያሉ ህገ ወጥና ጋጠ ወጥ ግለሰቦች ይውረዱ ብለናል፡፡ አሁን ያሉት የጠገቡት ወርደው ሌላ የተራበ በጓሮ ሌላ እንዳይገባ አስገንዝበናል፡፡ ህገ-ወጥ የመጅሊስ አመራሮችን ስናስወግድ ሌላ ህገ-ወጥ እንዳይተካብን በአፅንኦት ጠይቀናል፡፡ በምትኩ ነፃና ዲሞክራሲያዊ፣ ሁሉ አቀፍና አላታፊ፣ ህጋዊ መሰረት ያለው፣ የህዝብ ይሁንታን ያገኘ፣ ግልጽ፣ ከማንኛውም ሳይነት ማጭበርበር የጠራ ምርጫ ተካሂዶ መሪዎቻችንን እንምረጥ ብለናል፡፡ አለቀ፡፡ ይህ አጭርና ግልፅ ጥያቄ ነው፡፡

ነገር ግን ይህን ሁሉ የመሰለውን የሙበት ጥያቄ ወደ ጎን ብሎ ሎሌና የመጅሊስ አፈቀላጤ የሆኑትን ኢላማ ምክር ቤትን በቴሌቪዥን መስኮት አቅርቦ፤ አንተ የምትጠይቀውን ሳይሆን እኔ የምወስንልህን ተቀበል፡፡ ደጋግመህ እደጠየቅከው ምርጫው በመስጂድ ሳይሆን እኔ እንደምፈልገው በቀበሌ ነው የምታደርገው፤ አስመራጮችን አንተ በምትፈልገው መንገድ ሳይሆን እኔ በምፈልገውና የፈለግኩትን ለመሰየም በሚያመቸኝ መልኩ እሁንም በቀበሌ ነው የምታደርገው፤ በዚህ መልኩ እኔ ባለሥልጣኑን ሲሉተም ውስጥ ስትሄድልኝ የምሰራጫ ሰርቼ አሁን ያሉ መጅሊሶችን እይነት አህባሽ መራሽ መጅሊስ እሾማለሁ፡፡ ለራስህ አንተ ሳትሆን እኔ ነኝ የምወስንልህ፡፡ አንተ የምትለውን አልሰማህም እኔ የምወስንልህን ብቻ ተቀበል፡፡ ተብለናል፡፡

ህዘበ ሙስሊሙ «እንግዲያዉስ እኛም እናንተ የምትሉትን እንሰማችሁም፡፡ የሚሊየኖች የሆነውን የህዝበ ሙስሊሙን ውሳኔ የመሻር መብት ማን ሰጣቸው? ጥያቄዎቻችንን አልቀበልም ብለው ሲያበቁ በቴሌቪዥ መስኮት የፈለጉትን ሰላወሩ ማን እንዲሰማቸው ነው የሚፈልጉት? ማንም? ይህ በምንም መልኩ የማንቀበለውና በፅኑ የምናወግዘው መግለጫ ነው፤ ህዝበ ሙስሊሙን ከምንም ባለመቁጠር ምን የመጣል የፈለግነውን ብናደርግ በሚል ህዝበን ከመናቅ የመነጨ አልባሌ ድርጊት ነው፡፡ ውሸትን በቲቪ ሰለተናገሩት እውነት አይሆንም!! የህዝበን ፍላጎትና ድምፅ የሚሸር ተግባር በቲቪ ሰላስተላለፉ ተቀባይነት አያገኝም፡፡ ሚድያ የሃሰት ወሬን እውነት ማድረጊያ መድረክ አይደለም፡፡» ብሏል፡፡ ስለዚህ የተነገሩት የአካሄድ ስህተቶች ሙሉ በሙሉ ታርመው የምርጫ ስርዓቱ ሊጀመር ይገባል!!!



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፌርማ

539


http://ethcriminalawnetwork.com/

2ኛ የኛን ጥያቄ በተመለከተ ብቸኛ ተወካያችን በፌርማችን የወከልናቸው ኮሚቴዎቻችን ስለሆኑ ለሰጠነው ዝርዝር ሂደት ከኮሚቴዎቻችን ጋር ውይይት ተደርጎ ለምርመራ ላይ ይደረስ። እንደዚሁም ከኮሚቴዎቻችን ስምምነት ውጪ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት የምርመራ ሂደቶች የማንቀበለው መሆኑን አስረግጠን አቋማችንን መግለፅ ይኖርብናል።

ቢሆኑም ሃይማኖታዊ መሪያችንን የምንመርጠው በሃይማኖት ተቀማችን በህገ-ው በመለጂዳችን ነኖው አራሳችን በመሆኑ ዲሞክራሲ ባለበት ሃገር ይህ ሁሉ ኢ-ህገ መንግስታዊና ህገ-ወጥ የሆኑ ተግባሮች በዲናችን ላይ ሲፈፀምብን ዝም ብለን አንደማናይና በፅኑ እንደምንቃወም፤ ስለሆነም ህገ-መንግስቱ በሰ ን የእምነት መሪያችንን በራሳችን የማስመረጥ መብት በሰላማዊ መንገድ በመ ጃዶቻችን ላይ ተግባራዊ እንደምናደርግ ልናረጋግጥ ይገባል።

በመሆኑም ያሰቡትንና እየተገበሩ ያሉትን ህገ-ወጥና የተጭበረበረ ምርጫ የማስፈፀም አንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ሊማከን እና ለ22 ሳምንት የፍ ህንስትን ዲናችንን ማሰቡበት ሰላማዊና ህገመንግስታዊ የመብት ትግል ለማ ጠበቅ፤ ሰርጎቡ ካድሬዎችን መንጥሮ በማውጣት የእምነት መሪዎቻችንን በት ክከል ለይቶ ለማውቅ በሚያስችለን በመስጅዶቻችን ላይ የእምነት መ ችንን በሰላማዊ መንገድ በራሳችን የማስመረጥ መብት ተግባራዊ የ ረግ አንቅስቃሴ መጀመር ተገቢም አስፈላጊም ነውና ልንተገበረው ይገባል ።

## ጀ ማዕን በአወሊያ

[illegible]

ዱ ዓን ሁላችንም ከ ለበታችን ጋር አወሊያ እንገናኝ። በዚህ ታሪካዊ ቀ ለዚህ ጉ ት ዶ ንን ክፍ ለማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ተ ንን አሳራችንን እ ር።

አከበር!!! ጉሪዑ አከበር!!! አላሁ አከበር!!!

2

ፊርማ


540

http://ethcriminalawnetwork.com/

13

ቀጠሮ
30-09-2024 ዓ/ም
ለጠዋት ጠ-ጉለሌ
ወንጀል ችሎት
ከጠዋቱ 3:30 ሠዓት
ለፍትህ ክፍል

12



ምርጫችን በመሰጀዲት !!!

እነሆ ዲናችን ለመጠበቅ የምናደርገው የመቡት ትግላችን ወሳኝ ነጥብ ላይ ይገኛል። ባለፉት ሰዓት በምንሰጣቸው መሀከል፣ ወከባ ብሎታታ መደናገር መምታታትና ትርምስ የመፍጠርና በዚህ መሃል ሊገኝ የሚፈልጋቸውን ሰርጎ ገቦች ካድሬዎች ተቀይሶ ከፍተኛ አንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ፀሃይ ለጥ ሊድርጎ የመማዘት እስተራቴጂ ይገኛል።

ለመፍጠር በማሰብ ከንቱ ምኞት አንዳንድ ወገኖቻችን በዚሁ ህግ-ወጥ የቅድመ ምርጫ ሂደት ውስጥ ስንባት ቡኋላም በማጣራት ስም እነሱን አንቅር በመትፋት የሚፈልገውንና ቀድሞ ያዘጋጁት ካድሬዎች ብቻ ለመውሰድ አንቅስቃሴም እያደረገ ነው።

ም ይሁን ምን ሂደቱ ህገ-ወጥ ነውና አንገበርለትም። መድረሰም ሆነ መንግስት ነኝም ሆነ ሌላመርጠናልን አይችሉም። መብቱ የላቸውም። ይህ ሂደት ህገ-መንግስቱ ው ህገ-ወጥና በህዝብ ላይ የሚፈፀም ወንጀል ነው። ለዚህ ይረዳናል በማለ ጉዳቶች የተዘጋጀውና ወደየ ክልሉ ተበትነ የገባነውን በምርጫው የሚመረጡት በጻር ሉ መሰረ ነጥቦችን የያዘ የምርጫ ማስ ጋር አመቺ መመሪያ አውጥተል። ሉ ለመጅሲስ ወይም ለሚሰራው ለራ ጋር ያመረጥነው መድረክስ ይመራዩኒየማንጅ የአህሰሸ አንን ለ ታውም ያስገጣን ይኸው ያመረጥነው መድረክስም በጋራ እንጂ በተግባር አለችም ብሎ የተከሠውን ድጋፍ እየደለምን መድረክስም በጋራ እንጂ በተግባር አለችም ብሎ የተከሠውን ም ተጠናክሮና በረጅራል ጉዳዮች ተሰሰክ እያሰራ መሆኑ ነው። የአህሰሸ ስልጠናም ሰራ ስለምንቃወመው በአስቸኳይ አንዲቆም ጠይቀናል። በተደጋጋሚ ጊዜ ተጠይቆ ሳለምንቃወመው በአስቸኳይ አንዲቆም ጠይቀናል። በተደጋጋሚ ጊዜ ተጠይቆ ምላሽ አላተሰጠም። ምላሽ የመስጠት ፍላጎትም የለም።

ይህም ህገ-ወጥ ጉዳና ሪገጠ ህገ-ወጥ ተግባርን መፈፀሙን ቀጥሏል። ምርጫውን ለመምበርበር አመቺ ነው ባሉት መንገድ የምርጫ ቀን ለዝግጅት እንዳደጻ አንድ ወርና ከዚያ በላይ እስቀደም ሳይሰናበትና መጅሲስ ሳይታወጅ በህዝብ የሚመረጥ ገቢአተኛ ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚሽኖች ሳይኖሩ፣ ተመራጭ አጨዎች ተለይተው ሳይታወቁ፣ በቂ የምርጫ ትስትላ ሳይደረግ፣ ሪቴ ሳይዋቀር፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሳይዋቀር መሰል መሰረታዊ የምርጫ መሰረቶች ተጥሰው ሲካሄድ ለማድረግ ወስነዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከዛሬ ጀምሮ በየቀበሌው ሰለ ምርጫው ግንዛቤ መፍጠር በማሰብ ሽፋን በሰበሰባቸውን በመድረግና ለህዝብ እሳቢ መሰሉ በመቅረብ ለሚዲያ ሽፋን ለመጠተም ጀምሯል። ስለሆነ ይህ ዓይነቱን በእምነታችን ላይ የተቃጣብ ግፍና ሴራ ደብተውና አስማምረው በየቀበሌው መድረክ ላይ ቢያቀርቡልን ምላሻችን

ከዛው ደብተው ያመጡትን ሴራ ፕሮግራም ማጋለጥ።

1

ከሳሽ ፖሊስ ጣቢያ ተመዝግቧል
ፊርማ

541

http://ethcriminalawnetwork.com/

ረኪቲ 24/03/04



መጅሊስን የተቃወመው ጥቂት የህብረተሰብ ክፍል ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ መስሊሞች ፣ኡለማዎች ፣ዳዒዎች፣ ሙስሊም ምሁራኖችና ተማሪዎች ፣ የዕድሜ ባለፀጋዎች፣ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መሆናቸውን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይወቅልን እያልን ድምፃችንን እናሰማለን።

## መጅሊሰን ስንቃወም

እኛ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች መጅሊስን ስንቃወም ስሜታችንን ተከትለን ስውር የፖለቲካ አጀንዳ አንግበን የስልጣን ጥማት ኖሮብን ወይም ዓለማዊ ጥቅም አጣጉቶን ሳይሆን የእስልምና ኃይማኖታችን ሲሸራረፍ ወሰኑ ሲጣስ ደግ ሲሸረብበት በዓይናችን በማየታችንና በጆሮአችን በመስማታችን ምክንያት መሆኑን አጠንረን ለማስገንዘብ እንወዳለን።

አህባሽን የምንቃወመው ከእስልምና ኃይማኖት ያፈነገጠ በፈተናው ሼህ /በአብዱላህ አል ሃረሪ/ የተፈለሰፈና በአይሁዶች የተቀነባበረ ድጋፍ የሚረዳ እስልምናና ሙስሊሞችን ለማዳከም በመንግስት አንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሙሉ ድጋፍ ሰጪነት ህገ መንግስታዊ መብታችንን በኃይል በመደፍጠጥ ብሎም የህገ መንግስት አንቀፆችን በመጣረር በግድ የአህባሽን ፍልስፍና ተቀበሉ በመባላችን ነው።

## አህባሽ/የፈተናው ሼህ/ ለሚያራምዳቸው ፍልሰፍናዎች በጥቂቱ

1ኛ. ቁርዓን የአላህ ቃል አይደለም ማለቱ።
2ኛ. ሳሃቦችን/የነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዓ.ወ./ ባልደረቦችን በተናጠል ትችት /ወቀሳ/ ቢሰነዘርባቸው ችግር የለውም ማለቱ።
3ኛ. ሙስና/ጉቦ/መቀበልም ሆነ መስጠት መፍቀዱ
4ኛ. ታላላቅ የኢስላም ሊቃውንቶችን በከሃዲነት መፈረጁ እና ወዘተ ...

ለመሆኑ አንዳንድ ባለስልጣናት የህዝብ ሚዲያዎችን በመጠቀም በመላው አገራቱ ያሉ ሙስሊሞች እየጠየቁ ያሉትን ጥያቄ ወደ ፖለቲካ አጀንዳ በመጠምዘዝ ህዝቡ ያልጠየቀውንና የመጠየቅ ዓላማው ያልሆነውን በሸሪዓ ህግ አንተዳደር አስላማዊ መንግስት እንመስርት የሚሉትን የኃይማኖት ግጭት በመፍጠር ሀገሪቱ ወደ ከፋ ብጥብጥ ሊከቷት ነው እያሉ የሚያስተላልፉት መልዕክት ከአንድ ህዝብን ከሚመራ አካል የማይጠበቅና የበሬ ወለድ ተረት ተረት መሆኑን መላው የአገሪቱ ማህበረሰብ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ አለማወቃቸው በጣም ያስገርማል።

## ምርጫ

(11)

የመጅሊስ አመራሮች ምርጫ በጊዜ ገደብም ሆነ በድንገት ይደረግ ሊባል ይችላል። ስለሆነም በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ ሙስሊሞች ብንቃወም በመከታተል ምርጫው እንዳይጭበረበር የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብናል ለዚህም ሊመሩን የሚችሉ ወኪሎቻችንን ከወዲሁ በየአካባቢያችን በጥንቃቄ በመመልመል ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

በመሆኑም የረጋ ውሳኔ ቅቤ ይወጣዋልና በየመስጂዳችን በተከበረና ያልመረጥናቸው የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉንም፣ የአህባሽ አስተምሮን አንተበልም የሚሉ መፈክሮችን በማሰማት ሰላማዊ ትግላች፣

## ሰላማዊ መሆናቸው ይቀጥላል።።

ኢንሻአላህ
አላሁ አክበር!

ካፒ አደርገው ያለተካልሃ

ከሳሽ ምስክሮ
ፌርማ

542

http://ethcriminalawnetwork.com/

በኋላ ከየሁዳዎች ጋር በሚስጢር ይገናኝ ጀመር። ክፍተኛ ገንዘብ ተመድቦለት እ.ኤ.አ በ1982 የሊባኖስ የርስ በርሱ ጦርነት ጊዜ ድምፁን አጥፍቶ ሀይሉን አጠናክሮ፡ ከዚያ በ1980ዎች አስራኤል ሊባኖስን ስትወርና ስታጠቃ የሙስሊሞች ጀመዓ ስትወጋ አህባሾችን ግን ተወቻቸው። ምክንያቱም የርሷ ወዳጅ ናቸውና ነው። በ1990 አህባሾች በአስራኤል ተረድተው ወደ ፖለቲካ ገቡ። በ1992 የሊባኖስ ምርጫ ጥቂት ወንበር አሸንፈው ፓርላማ ገቡ። ቀስ በቀስ የራሳቸውን ሚሊሻ ጦር መለመሱ። ሙስሊሙን ማበጣበጡን ገፍተው ቀጠሉ። ክነርሱ ውጭ ያለውን ሁሉ ‹‹ካፊር›› እያሉ መፈረጁ ተያያዙት። ልመንግስትና ለእስራኤል መረጃ እየሰጡ ሙስሊሙን ማስመታት ጀመሩ። ራሳቸውን በውሸት ‹‹የሻፊዒ መዝሀብ እንከተላለን›› እያሉ ያስወራሉ። አህለል ሱንና ነው። አሻዓሪና ማቶሪዲ ነን ይላሉ። ሱፊያም ነን ይላሉ። ሆኖም የሰፊያ ዓሊሞች በሊባኖስ በሌሉች ሀገራትም መጀመሪያ እውነት ሱፊያ ናቸው ብለው ተሸደውደው ነበር። ሆኖም በሒላ በገርዝር ሲያውቋቸው አጋልጠው ምላሽ ጻፉባቸው። ለወም እንዲያውቃቸውን እና እናዳይከተሏቸው አስጠነቀቁ።እውነታው ግን አነርሱ የአስራኤል ቀኝ እጅ ናቸው። ቀስ በቀስ አል-ሀበሽ የሱንና መንገድ እየበከለ ሺዓ፣ ሪፉኢ፣ መቭጂአ፣ተክፊር፣ሱፊ፣አል-ጀበሪ፣ ቃዲሪያና ጃህሚያ ወዘተ መንገዶችን ቀይጦ(ስፕሪስሪስ) አድርጎ የራሱን አዲስ መንገድ ፈጠረ። የዓለም ሙስሊሞችን ማከፋር ያዘ። ኧብደላ አል-ሐረሪ ‹‹ላውዲ እንዴት ሸፈረች?›› ብሎ ሁሉ መጽሀፍ ጽፏል። የነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) አገር መካና መዲና የካፊር አገር ብሎ ጽፏል። ይህ ብቻ የየሁዳ መሰሪያ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ሰመሆኑ አቋማቸው ምንድነው? ቀጥሎ ጥቂቶችን ብቻ እናያለን፦

1. ክካፊር ጋር ቁማር መጫወት፣ የካፊርን (ክርስቲያን) ጎረቤት መስረቅና ማጭበርበር ይቻላል ብሎ ያስተምራል።ዋናው እንዳይነቃ በድብቅ ማድረግና ዋናው መጠንቀቅ ነው ብሎ ያስታምራል። (መጽሐፉ ሰሪህ አል-በያን፣ገጽ 133)
2. ሰሀቦችን ይሳደባል። አንዳንዶቹን ለሀቦች ካፊር ናቸው ይጀሀነም ናቸው ብሎ ጽፏል። ለምሳሌ ታላቁን የነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ሶሳባ ሙአዊያ ኢብኑ አቢሱፍያን ካፊር የጀሀነም ሲል ገልጿል። የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) ባለቤት አዒሻን ተሳድቧል።
3. በጎጃሳ መስገድ ይፈቀዳል ይላል።(መጽሐፉ ቡግዮቱ ሚሊቦ፣ገጽ 99-100)
4. ዚክር የለም ይላል። ዚክ አእስልምና ማዕዘናት አንዱ ነው። አህባሾች ግን ለው ዚክ እንዳያወጣ ከወረቀቱ ብር(ኖት) ላይ ዚክ የለበትም ይላሉ። ይህ ማለት በባንክም ይሁን በቤትም ቢሊዮን ብር አንኳ ካለው ዚክ አይስጡ ብሎ ይቀሰቅሳሉ።
5. ዕቁ (ወለድ) መውሰድን ያበረታታሉ። ባንክ ገንዘብ አስቀምጠው ባንኩ የካፊሮች(ወይም ስራ አስኪያጁ ካፊር(ክርስቲያን) ስሆነ ጠላታችን ስለሆኑ ወለዱን መውሰድ ይቻላል ብለው ያስተምራሉ።



6. ሴቶቻቸው ሻሽ ብቻ ሰድርገው ሱራ ማድረግ ይችላሉ ያሉ። ጂንስና ቲሸንጋም ያበረታታሉ።
7. በለባኖስ ስር የመሪቃ ባንድ አላቸው ይህ ባንዳቸው ‹‹James last›› ይባላል። ዓመታዊ የሙዚቃ ድግስ ያደርጋሉ። በዛ ላይ ሴቶችና ወንዶች በጋራ ይጨፍራሉ።
8. የአሮንቢ ሴትን ፎቶ፣ ቪዲዮ አልያም በመስታወት ውስጥ ራቁታን አንኳ ብትሆን በስሜትም ቢሆን ማየት ይቻላል። ከቁርአንና ሱና ተቃራኒ ሆነው የተከለከለው በዓይን በቀጥታ ማየት ብቻ ነው ብለው ያስተምራሉ።
9. ‹‹ሪፋዒ›› የተሰኘ ጦሪቃን ያስፋፋሉ። በኢትዮጵያ ጀምረዋል ይህ ጦሪቃ ከሺዓ ጋር የሚያመሳስለው ብዙ እምነት አለው። የኢትዮጵያ ሙስሊም ግን ሰኒ ነው።
10. እምነት በልብ ነው ባይሰገዱም ኢባዳ ባይሰሩም አንዴ አመንኩ ማለት በቂ ነው ብለው ያስተምራሉ። (መጽሀፍ አ-ደሊል አልቀዊም፣ ገጽ 7)
11. ብዙ ታዮቻቸው በአሜሪካና ካናዳ የቂብላ አቅጣጫ ካልተቀየረ ብለው ረብሻ ፈጥረዋል። በመጨረሻም ከመስጊዱ ሲባረሩ የራሳቸው መስጊድ በተለየ ቂብላ ላይ ሰሩ። አሁን ከሙስሊሙ በተለየ ቂብላ ነው መስገዳቸው።
12. ይሚያሳዝነው አይቃወሙትም።ራሳቸውም ይፈፅማሉ። ለሊሀር የማጠቃመቢያ ‹‹ሀዲሠል ኢል-አሀብ›› ብለው የሚጠሩት ነገር አላቸው።
13. ቁርኣን የሚበረል ይሆን እንጂ የአላህ ቃል አይደለም ብለዋል። የአላህ ቃል አየባነም ይላሉ።
14. የሚገርመው ይህ ሁሉ የጥመት መንገድ እየተከተሉ ሱፊያ ነን፣ ሻፊዒ መዝሀብ ተከታይ ነን ይላሉ።
15. ክነርሱ አምነት ወጥ ያሉ ዓሊሞችን እንዳያነብያሩ ሆን ብለው ያስጠነቅላሉ። ይደኔይባሉ፣ ያሳስራሉ፣ ያውሳሉ። በአንድ ወቅት በሊባኖስ ይህ ጉባዐ በስሩት ፈጥረው ‹‹ሸሪዓ መጽሔት›› በቁጥር 574 አተሙ ‹‹ሊባኖስ ጦርነት በመስጂዱ ውስጥ›› በሚል ርዕስ ጽሑፍ አስገበሱ ነበር።
16. ዓመታዊ የሴቶቻቸው የሂጃብ ፋሺን ሾው አላቸው። በዚያ ላይ ሂጃብ ክሚለብሱ ሴቶች ጋር በጋራ ይጨፍራሉ። ይህ እንዳይህ በጣም በጥቂት አቋማቸው ነው። ብዙ አቋማቸውን ወዲያውኑ ግልጽ አያደርጉም። መጀመሪያ ብያካማ ነን ይገባሉ። ቁጥኝን ተከታይ ካደረጉ በኋላ ቀስ በቀስ ያፈነገጠውን ጎዳናቸውን ማስተማር ይጀምራሉ። ከመጀመሪያ ሆን ብለው ኸሳፍ ያለበትን ኑጥብ ብቻ እያነሱ ተከታይ ለመፍጠር ይጥራሉ። በዚያውም መሰለመን ማወክ ይፅምራሉ። በአጠቃላይ ዘዴያቸው አደገኛ ነው። በዓለም ላይ ያሉ ሁለሞች በርካታ ፈተዋ ሰጥተውባቸዋል። አል-አዝሀር ዩኒቨርሲቲ፣ መዲና ዩኒቨርሲቲ እና የዓለም የሁለማ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ዩሱፍ አል-ቀርዷዊና ሌሉች በርካታ ዓሊሞች አህባሽ የጥመት መንገድ ላይ እንዳሉ ፈተዋ ሰጥተዋል። በመጽሐፍም ጽፈዋል። እንጂህን ነው እንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፋፋት የሁዶች እየሰሩ ያሉት።



መጅሊስና መንግስትም ሙስሊሙን ወደዚህ መንገድ ለማስገባት ቆርጠው ዩተነሱት። ታዲያ መፍትሄው ምን ይሆን? አህባሾችን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ጥረቱ ከተጀመረ ጥቂት የቆየ ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይታወቅ ስር እየሰደዱ ነው። ለምሳሌ በጎንደር፣ትግራይ፣ ነቀምት፣ አዲስ አበባ 3 ቁጥር ማዘሪያ ቶታል፣ መከሊ እና ሳፍቶ ለፊር፣ አሮሚያ ውስጥ መሠረት ለመጣል እየታገሉ ነው። በነዚህ አካባቢዎች ሙስሊሙን አከራሪ፣አሸባሪ፣ ወሀቢያ፣ ጃንፊኛ ወዘተ በማለት ማጥላላት ጀምረዋል። እውቁ ዳዒ ዶክተር ዛኪር ናይክንም ካፊር ብለው ፈርጀዋል። የዳዕዋ ሰዎችንም(ተብሊግ) ዳዕዋ ሰዎች ጋርም በዓለም ላይ ከረር ባለ ግጭት ዉስጥ በቅርቡ ገብተዋል። መጅሊስ የሙስሊሙ ተቋም ቢሆንም አመራሩ በፀረ-ኢስላሚ ሥራ ላይ ተሰማርቷል። በሌላ አነል የማመራ የጠላት መሳሪያ ሆኗል። ምርጫ ተደርጎ ትክክለኛ የሙስሊሙ ወክል ሰመረ አልቻለም። በሙስናና በፀረ- ኢስላም ተግባር የተሰማራ ሆኗል። መንግስትም የሙስሊሙን ፈጽሞ መስማት አልፈለገም። ምን ያመጣሉ? በሚል ንቀት ታውሯል። ታዲያ በየሁዳና ነሲራ ሴራ ዲናችንን ሲበረበር እጃችን አጣጥፈን መቀመልከት አለብን? በየአከባቢያችን መሸራ አድርገን ለመከላከል እንነሳ! ለስፋፋሉን ለተነሱት ሴረኞች ፈጽሞ አጅ አንስጥ! ይህ ሁሉ ድፍረት የተሰማቸው በዲናችን የሚፈጸመውን ሴራ ስለማንከታተል ነው። ተነሱ መጅሊስ ሙስሊሙን እንዳይወክል እንግለፅ! ላልሰማው እናሰማ! ህዝባችንን እናንቃ! ሴራቸው መች ይህ ብቻ ይሆንና? ኢስላማዊ ድርጅቶችን ለማዘጋት ቆርጠው ተነስተዋል። ተማሪዎችን ለመማፋትና ለሳትና ጂልባብ እንዳይለብሱ ለማድረግ ተነስተዋል። ዲናችንን ለመከላከል ይሀን ወረቀት ያባዙና በስተመም ሆነ ገጠር ላለው ሙስሊም ያሰራጩ። ዲንዎን ከጥፋትና ከጥቃት ያድኑ! የነብያችንን (ሶ.ዐ.ወ) ሱንና ትክክለኛውን የቁርአን መንገድ ትተን የየሁዳ መሰሪያ እንድንሆን ታቀደ! እንዴት ቢንቋን ነው ጃል?! መተኛት አይበቃንምን ያ መስለመ! (ገርገርር መረጃ ከፈለጉ በኢንተርኔት (www.antihabashis.com) ወይንም በሶማል ላይ ለያያም በአገሀር የኒቨርሲቲ ዑለሞች ፈትዋ ላይ ጽሏል።) ይህ ወረቀት አባዝቶን በረመዷን ከፍተኛ አጅር እንግኝ! ለአላህ ዳዕቁመ! ዳዕዋ እስኪቆም፣ መስጊዶቻችን እስኪጠቁ፣ ዲናች እስኪ ቦረቦር ዝም ማለት አለብን በአንድነት ሆስተን የየሁዳን ሴራ እናክሽፉ! ኢስላምን የሁዳና ተባባሪዎች ሲበረቡ ምን አድርገክ ብሎ አላህ ነገ በቂያማ ቢጠይቀን ምን ይሆን መልሳችን? ወሰላሙ ዓላይኩም!

*ቢያንስ ይህን ወረቀት በማባዛትና በማሰራጨት አጅር ያግኙ! ሐላፊነቶንም ይወጡ!!*



http://ethcriminalawnetwork.com/

# በዲናችን እንፅና!!

አል-ሐምዱሊላሂ ረቢል ዓለሚን ሙስሊም ላደረገን ጌታችን ምስጋና ይድረሰው! ሰላምና እዝነቱ በአሸረፈልኽቆቅ መሐመድ(ሲ.ኢ.ወ) ላይ ይሁን። እናንተዬ ረመዷን ከመግባቱ አሯሯጡን አያችሁ? ስንቶቻችን በረመዷን ተጠቅመን ይሆን? ስንቶታችን ቁርአንስ ቀርቷን አኽተምን? ተራዊህስ ሰገድን? ረመዷን ተጠቀምንበት? የጊዜው አሯሯጥ እንደ ጀት ነው! ክዚያም ባለ እክ! ወደ ዋናው ጉዳያችን እንግባ። ስንቶቻችን በዲናችን ላይ ስለመጽናት ክራሳችን ጋር መሹራ አድርገን እናውቃለን? አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይላል፡ ‹‹ጌታህን ሞት እስኪመጣ ድረስ አምልከው›› (አል-ሒጅር 15:99)። እንዲሁም ‹‹አላህ አማኞችን በዚህችም በመጪውም ዓለም በፅኑ ቃል ያፀናቸዋል።››(ኢብራሒም 14:27) ሲል ይናገራል። ያረቢ ከምታፀናቸው አማኞች አድርገን! እንደ ሙስሊምነታችን በዲናችን ቁርአንና ሱንናን አጥብቀን ይዘን ቀጥ የምንል አድርገን! የማንም አስተላለብና ሴራ ከዲናችን ሊያወጣን አይገባም። እንደታዘዝነውም በኢስላም ቀጥ ማለት መቻል አለብን! በቁርኣን ላይ አላህ(ጀለጀላሉሁ) እንዲህ ይመክረናል፦ ‹‹እንደ ታዘዝሽው ቀጥ በል›(ሁድ 11:112)። ሙስሊም የማንንም መንገድ ሳይሆን የስይዳችንን ሱንና አጥብቆ ይይዛል። ወደዚያ ጥሪ ያደርጋል። ያስተምራል። የየሁዳንና ነላራን ፍላጎት መቼም አይከተልም! አላህ በቁርኣኑ እንዲህ ይመክራል፦ ‹‹በመሆኑም (የሰውን ልጅ ወደ እውነት) ጥራ። እንደታዘዝክውም በቅን ፍኖት ላይ ዕና። የነርሱን ስሜትና ፍላጎት አትከተል።›› (ቁርኣን 42:15) የኢስላም ጠላቶች ሁሌም በሙስሊሙ ላይ ይዶልታሉ። ያፈራሉ! ስለሆነም ንቃት ያስፈልገናል። ያሳወቁ አሰቱ እንደሚባለው ሴራቸውን ባለማወቃችን ስንቶቻችን አለቅን?! በጥሞና ይከተሉ። የኛ የሙስሊሞች ነገር አባት አለባ ሆኗል! ስለዚህ ተነስና ሰዲናችሁ ቁሙ። አስቲ ስንቶቻችን የሰሞኑን በእስራኤል የተሳከልንን የአሀባሽ አደጋ ሰምተናል? መጅሊስ ከየሁዳ ጋር ሆኖ ሙስሊሙን ሊበክል ቆርጦ መነሳቱን ሰምተናል? በሐረር ከተማ የተካሄደውን ግብኤስ ሰምተናል? ነገሩ እንዲህ ነው። የሙስሊሙን አንድነትና ህልውና አደጋ ላይ መጣል የዘውትር ህልማቸው የሆነው የሁዶች ለሙስሊሙ ብዙ መሰናክሎችን አዘጋጅ። አንዱ በኛ አገር እንዲሰፋፋ ዘመቻ የተጀመረው ‹‹አሕባሽ›› ነው። ሙስሊሙን እርስ በርስ በማባላት እነርሱ በሰላም ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ፈለጉ። በኢትዮጵያ እንዴት “አህባሽን” ማስፋፋት አለብን ብለው ከቱሳቪቭ ዩኒቨርሲቲ ሀጋይ ኤርሊች የተባለ ሰላይ ወደ ኢትዮጵያ ላኩ። ሰውየው የእስራኤል ሰላይና የጦር ሠራዊት አባል ሲሆን በ1967 የ6ቱ ቀን ጦርነት ተጠባባቂ ወታደር ሆኖ ተሳትፎም ነበር። ጥናት አደረገና ሙስሊሙን ለመከፋፈል በአብደላ አል-ሐረሪ የተመራውን የአህባሽ ቡድን ለማስፋፋት ቆርጦ ተነሳ። አቅዱን የዛሬ ሦስት ዓመት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አቀረበ። በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን



(1ዐ)

በእንግሊዘኛ ፕሮግራም (ማታ ኢቲቪ) ላይም አቀረበ። መጽሐፍም ጽፎ አሰራጨ። ሰማንያዎች ባለስልጣናት ጭምር አዳረሰ። በግል ጉብኝታቸው። ሥራውን ተቀብለውም ደገፉት። ከዚያም ዓለማውን ከዳር ለማድረስ ማገዝ ጀመሩ። በቶታል(ሦስት ቱቦር ማዞሪያ አዲስ አበባ) የተከፈተላቸውን ትምህርት ቤታቸውን መደገፍ ጀመሩ። በዲን ተመሳስለው እያስተማሩ ዓላማቸውን ዳብቀር ጀመሩ። ሰው ሲያውቅ እነርሱ ጋር የሚሻርም ነገር። በየጊዜው እያስተማሩ በሺዎች አስበው። ሙስሊሙን ለማናቆር ሲሰሩ ነበር። በቅርቡ ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት ሙስሊም ጋንዲ የጀመረላቸው ሲሆን መንግስትም መጅሊስ ይህን የየሁዳ አገዛ ያልተለየውን የአህባሽን መንገድ ተከትሎ ህዝቡ በዚህ መንገድ እንዲጠመቅ ሥራ ጀመረ። ቁጥራቸው 1300 ያህል የመጅሊስ አባላትና ደጋፊዎቻቸው ከመላው ኢትዮጵያ ወደ ሐረር ተጠሩ። የኢፌዲሪ የፌዴራል ጉዳዮች ነበር መድረኩን ያቀናበረው። ሚኒስትሩም ዶ/ር ሽፈራው ተክለማሪያምም ዋና አቀናባሪ ሆነው ሙስሊሙም ጭምር ከሚከፍለው ግብር ላይ ስድስት ሚሊዮን ብር ለአኩይ አላማቸው መደቡ። ዶ/ሩ ጴንጤ ሲሆኑ በደቡብ በተለይም በሆሳዕና ባለውና ሙስሊሙን ለማክፈር በሚሰራው የጲንጤ ‹‹ሲኖዶስ›› የቦርድ አባል ናቸው። እኒህ ሰው ናቸው እንግዲህ በሐረሩ ስብሰባ ከአሕባሽ መንገድ ሌላ አትከተሉ። መጅሊስን የማይታዘዝ ፀረ-ልማት፣ ፀረ-ህገ መንግስት ብለው ሲደሰኩሩ የተሰሙት። ይባስ ብለው የሱንና ተከታዮችን አክራሪ ብለው ፈረጁ። በየትኛቱ ኢስላማዊ ህግጋትን የሚጋፋ መመሪያ ከመስከረም 2004 ጀምሮ እንደሚተገበርም መግለጻቸውን ከሚዲያዎች አነበብን። ሙስሊም ተማሪዎችም አክራሪ ሆነዋል አሉ። በዚህ መድረክ የኢትዮጵያ መንግስት ሕገ መንግስቱን ጥሶ በሃይማኖታችን (በዲናችን) ጣልቃ ገብቶ ሊያፋጀን 15 የአህባሽ ተከታዮችን ባሉበትና አስመጣ፣ ፓርትራም ካምጋኒ ባለቤትነም አቶ አብዲልከሪም በድሪም ከመንግስት ጋር ሆኖ እንቅስቃሴው ይገፋ። በየወሩ አንድ ሚሊዮን ብር እያወጣለት ነው። መንግስት ሙስሊሙን ለማክበርና ለማጋጨት ምን ያህል እንደቆረጠና ከየሁዳ ጋር አብሮ ተባበረ የሚያስየው መንግስት ከሊዝ ነፃ 100 ሺህ ካሬ ሜትር መሬት በየሁዳ ለሚታገዘው አህባሽ ኮሌጅ መከፈቻ ብሎ ሁሉንም ወራት በፊት በነፃ ሰጣቸው። መስገጃ ለመስራት በስንት ግድያ የሚወሰደውን መሬት ለመስጠት ፈቃደኛ የልሆኑት ለሙስሊሞች አስበው ሳይሆን ሊያፋጁን አስተሳሰቡን ማስፋፊያ ኮሌጅ ሊከፍቱለት ሰጧት። ወይስ አይ ፍስጋ? በሐረሩ የማጥመቂያ ፕሮግራም በጋላ በጎሮን ሆቴል ጋዜጣዊ መግለጫ በፊደራል ጉዳዮች ተሰጠ። እነርሱ ያመጡት ዶ/ር ሰግር ቃዲ አብራኡ ሱንውን ሙስሊም በአክራሪነት ፈርደው። እነርሱ አሸባሪ ካልሆኑ ማነው አሸባሪ ? አሉ። በኢትዮጵያ አህባሽን ለማሸፋፋት አብደላ አል-ሀረሪ በ2008 መንግስት ሊያስመጣ ዝግጅቱን ጨርሶ ነበር። ሆኖም በረመዳን አሸረር አዋከር ሊመጣ ከማቲ ተዋቅሮ በለይ



ጀት ሊያመጡት እያሰቡ አላህ ቀደማቸው። በረመዳን ሁለት ግታ አላህ አብደላህ አል-ሐረሪን በቃህ ብሎት ወደ አኪራ ወሰደው። ሞተ። አትዳቸውም ከሸፈ። አሪን ደግሞ ዳግም ተጠናክረው መጡ። ከሀረሩ በኋላ ለሁለተኛ ዙር ከረመዳን በኋላ በሸዋል ወር ደግሞ በዚህ በአዲሱ የአህባሽ መንገድ ስድስት ሺህ ሙስሊሞችን ለማስገባት መጅሊስና መንግስት በጋራ እየተሯሯጡ ነው። ሁለተኛውን ዙር አወሊያ ውስጥ እና በክፍለ አገር ለማካሄድ ፈልገዋል። እስከ ዛሬ በምርጫ ስንመርጠው የከረምነው መንግስት መጀመሪያውኑ እንዲመቸው ብሎ የራሱን ካድሬዎች እየመለመለ የሙስሊሙ መሪ ናቸው እያለ ወደመጅሊስ አስገባቸው። ህዝቡ ሳይመርጣቸው ነበር መንግስት በጓሮ በር የሚልካቸው። ህዝበ ሙስሊሙ ችል(ዝም) ስለማል ያሻቸውን ሲሰሩ ነበር። ይኸውም አሁንም እንደ ክዚህ ቀደሙ ዓላማውን ለማሳካት መሳሪያ አድርጓቸው አብዛኞቹ ሃይማኖትን ሽፋን አድርገው ወደ መጅሊስ የመጡ የፖለቲካ ካድሬዎች ናቸው። ሀጂና ሼህ ተብለው ሰልጠነው መጡ። አቤት ማስመሰል ሲችሉበት! አሁን ለሚያያቸው ሼኽ አይመስሉም? የቅርብ ጊዜ እቅዳቸውን በሐረር በአቋም መግለጫ አውጥተዋል። በጋዜጣ (ሰለፊያ) አላነበቡምን? ግልፅ ዳዕዋ ማስቆም! አህባሽ ማስፋፋት? መስጊድና መድረሳ አንዳያሰራ ነው ዓላማቸው። ለያሁዳ ሴራ መንገድ መጥረግ ነው ተልኮአቸው!! ሰው እንዴት ሙስሊም ነኝ እያለ ከየሁዳ ጋር ተጣብሮ በአላህ ዲን ጎደ ያሴራል? ኢናሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂዑን! የመጅሊስ ሰዎች በዲኑ ላይ እያሴሩ ነው። አንድም የሰሩት ከይር ሥራ አለመኖሩ! ሰዉ አማራጭ ሲያጣ አንዲት የት-ብብር ደብዳቤ ሽፋኑ ዝግጅቱ “ከመጅሊስ ጋር በመተባበር” እየተባለ ይነገራል(ሰምሳሊ ኤግዚብሽኑና የሚሊኒየሙ የቁርአን ውድድሩ)።ይህ ከመጀረፃ ጀርባ ለሚሰሩት የጥፋት ስራ ሽፋንና ከለላ ሆኖላቸው። ለመሆኑ የሁዳዎች በሀበሻ ሙስሊሞች ውስጥ ሊያስፋፋልን የሚፈልጉት የአህባሽ መንገድ ምንድነው? ቀጥለን የምንመለከተው ይሆም በጥቂቱም ቢሆን የአደጋጋቸውን ክፋት ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ይህን የሀበሺ (አህባሽ) መንገድ የጀመረው አብደላ አል-ሐረሪ የተባለ ግለሰብ ነበር። ግለሰቡ ሐረር የተወለደ ሲሆን የሀይለ ስላሴ መንግስት ቀኝ እጅ ነበር። ከሃይለስላሴ አማካኝ አንደርጌ ጋር ሆኖ ዓለሞችን ሲያለሰቅ፣ መብትና እኩልነት የሚሉትን ሙስሊሞችን ሲያጠቃ እና ሲሰልል ቆየ። አ.ኤ.ፖ በ1940 (1367 ሂጅራ) ላይ በሐረር የቁርአን ሂፍዝ ማዕከል መምህራንን አሳስሮ መርከዙን አስዘጋ። የመርከዙን ዳይሬክተር ሼህ ኢብራሂም ሀሰንን አሳስሮ 23 ዓመታት አስረፈደባቸው። አብደላ አል-ሐረሪ የፈጠረው ፊትና ፈትነተልኩቡ ያብስ ይታወቃል። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ገመምጣት በሀይሌ ሰፊር ሙስሊሙን ሲያጋጭ ቆይቶ በ1948 ወደ እስራኤል ተንዘ። ለሚመት በዚያ ቆይቶ በ1949 ወደ ሶሪያ ገባ። ከዚያም በ1950 ወደ ሳዑዲ ተገዘ። በሳዑዲ ቁርአን በማቅራት ህዋፍን ማሳደን ቀጠሮ ቀሰ አያለ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች አፈራ። ከአገሪ ከውጭ



http://ethcriminalawnetwork.com/

ስኬታማነት የራሱን አስተዋጽ የሚያደርግ ነው። በአምነት ጉዳዮችም ቢሆን ልዩነት በአገራችን ብቻ ሳይሆን በዮትኛውም ሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ ከሰተት ነው። ከበፊት ጀምሮ የነበረና አብሮን የዘለቀም ነው። ነገር ግን ይህ ልዩነት ሙስሊሞችን እርስ በርሳቸው ካፊር የሚያስብላቸው አይደለም። እንዳዉም እንደ አኸለል ሱና ወል ጀሚዓ አስተምህሮት እንድን ሰው የኩፍር ደረጃ የሚሰጠው አጅግ በጣም ጥብቅና በጣም ውስን በሆነ ሁኔታ ነው። ለዲን አሳቢ ለአገርና ለወገን ተቆርቋሪ የሆኑት የአገራችን እንጋፋ ሙስሊም ምሁራንም በአምነት ጉዳይ ላይ የተለያዩ አስተሳሰቦቻውን በምን መልኩ እንደሚፈቱ በተግባር አሳይተውናል። የአዲስ አበባ ዒሊሞች እንድነት መድረክ መንግስት ለ17 አመት ያከል ይሰራበት የነበረውን ሙስሊሙን የመከፋፈልና እርስ በርሱ የማዋጋት ሴራ ያመከነ አርምጃ ነበር። በዚህም መንግስት እከርካሪውን ነበር የተመታው። መድረኩ ከመንግስት ከፍተኛ ቢሮ በመጣ ትዛዝ እንዲፈርስ ቢደረግም ልዩነትን በውይይትና በመከባበር የመፍታትና በተለይም የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን እንድነት ከመጠበቅ አንጻር ያስተላለፈው አስተምህሮት ይህ ነው ተብሎ በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም። መንግስትም በዚያ በኩል ያደረገው ጥረቱ ሙሞከሩን የተረዳበት አጋጣሚ ነበር። አላማውን ለማሳካት ቆርጦ የተነሳው የኢትዮጵያ መንግስት ግን በአለም ላይ በመሰሪነታቸውና በአረመኔነታቸው ወደር የማይገኝላቸውን አህባሾችን ከቡር አንግዳ እና የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች አጥማቂ አድርጎ አመጣልን። እነርሱም እግራቸው የአገራችንን ምድር ከመርገጡ ሙስሊሞችን ሁሉ አከፈሩ። መላሪያዉን ዘረገፉት። ይህን በአካል በመገኘት ምስክር የሆኑት የፈደራል ጉዳዮች ሚኒስትሩ ዶ/ር ሽፈራው ተጉባኤው ላይ የተገኙትን ታዳሚዎች መላሪያውን ለንዲታጠቁ አዘዙም ሰልመው ለንዲፅሑ አዘዙ።

ውድ ኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሆይ! አባቶቻችንና አያቶቻችን በርካታ የፈተና የመከራ ጊዜያትን አሳልፈው አስልምናን ለእኛ አድርሰውልናል። በአርግጥ ተራው ኢትዮጵያዊ ህይማኖት ሳያግደው ተቻችሎና ተከባብሮ ኖሯልን አየኖረ ነው፣ ወደፊትም ይኖራል። በአምነቱ ላይ የመጣበትን ፈተና ግን ሙስሊሙ አሚን ብሎ የተቀበለበት ጊዜና ቦታ የለም። እቅሙ ሰፈቀደለት መልኩ አምነቱን ለመጠበቅ በስዋዕትነት ከፍሏል - ነፍሱ ሳይቀር። የሙስሊሙ ጠላቶች ግን ተቻችሎ የኖረ አያቱ በቁስላችን ላይ ዛሬ እንጨት ይሰዱቡታል። ታሪክ ራሱን ይደግማል ይባላል። የቡሩ ሚዳ ድንጋጌን ተከትሎ በአጼ ዮሀንስ አራተኛ የተወሰደው አይነት (መልኩ በተወሰነ ደረጃ ለየት ያለ ቢሆንም አላማው ማለትም የማናምንበትን እንቀበል ዘንድ በማስገደዱ ሂደት ግን ተመሳሳይ የሆነ) አርምጃ በእኛ ዘመንም ገቢራዊ ሲሆን አያየነ ነው። ዝም ብለን ልናየው አይገባም። ሂደቶችን በጥንቃቄ ልንከታተላቸው፣ ልንገመግማቸውና በአንድነት አርምጃ ልንወስድባቸው ይገባል።

መንግስት ያስቀመጠልን ሸምቆቆ ያሉ ልዩነቶችን በማሳየት እኛ እርስ በርሳችን ስንናላ እርሱ ደግሞ ሁላችንንም አንድ ላይ ለመዋጥ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት አሁን በኛ ላይ እየተገበረ ያለው በአለም አቀፍ ደረጃ እስልምናን እና ሙስሊሞችን ለማጥፋት በተነሱ አክራሪ አይሁዶችና ክርስትያናት የተሸረበ እና እየተሰራበት ያለ ሴራ አካል መሆኑንም እንዘንጋ። ለህዝብ እና ለአገር ሉአላዊነት ደንታ የሌላቸው የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በአኛ ደም ወሰን የሌለው ዶላር ሊያፍሰብት ነው። በአገራችን ላይ የፈደራል ጉዳይ ሚኒስቴሩ በደቡብ ኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ሲቻላቸው በአርዳታ እያታላለሉ በሌላ ጊዜ በሃይል ከሚያፈናቅሏቸው አክራሪ ክርስትያኖች ይርጋ

የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት

ዳዩ አስተዳደሩን አለ ለኔ ጊባለው ከሙስሊሞች ፊት ለሙስሊሞች መልካም ትምህ ኸና ቆረጠ ሙስሊሞች ምን እና እንዴት ማመን እንደለባቸው ይሰኮረ።

ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሆይ! መንግስት የያዘው አቋም እምረሱታለሁ፣ አጠብሞለሁ የሚለውን ህገመንግስት ዋጋ ቢስ በማድረግ በርካታ አለም አቀፍ ውስጥንና ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው። ምንም አይነት ህጋዊ መሰረት የሌለውም ነው። በአርግጥም ያስብቡትን ከግብ ማድረስ አንጂ ለህገመንግስቱ ደንታ አንደሌላቸው የስርዓቱ ባለስልጣናት ሲገልጹ ተሰምተዋል። ይም ቢሆን ግን ይህን ሂደት መቃዎምና መንግስት ህገመንግስቱን አንዲያከብር መጠየቅ ህገ መንግስታዊ መብት ብቻ ሳይሆን ዜጋዊ ግደታም ነው።

ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሆይ! የሚመጣው ጊዜ ለአገራችንና ለህዝቦቿ ወሳኝ ወቅት ነው። ይህ ታሪክ ያመጣልን እድል፣ ሃላፊነትም ነው። በደሰታ አላቀረሰው። ነገር ግን ድናችንን በትክክል አውቀን፣ በአርሰም ቆጥ ብለን አንጽና። አምነታችንን ለመጠበቅ አንነሳ። ሊከፋፍሉን ለተነሱ ሴረኞች በናዱም አድል አንሰጣ።

ይህን ፓምፍሌት በማሰራጨት የራስዎን ሀላፊነት ይወጡ። ሁላትንም ባለብን ሀላፊነት ተጠያቂዎች ነን።

ነብያችን (ፀወ) «ሁላችሁም ሀላፊዎች ናችሁ። ለሀላፊነታችሁም ተጠየቁበታላችሁ ..... ሁላችሁም ሀላፊነት አለባችሁ ስለ ሥራታችሁም ትጠየቁበታላችሁ» (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

ሙስሊሙን ታበረተሰባችንን አገራችን እና ህዝቦቿን ከሲረኞች ሴራ አላህ (ሱወ) ይጠብቅልን። አሚን።

## ዒድ ሙባረክ

**ኩሉ አሙን ወዓንቱም ቢኸይር**

---

አስተያየትዎን ለethiomuslims.justicefreedom@gmail.com ይላኩልን።

በፍጥነት እያደገ ያለውን ህብረተሰባችንን ፌስቡክ ላይ ይቀላቀሉ፦
http://www.facebook.com/groups/EthioMuslims.justicefreedom/

የፊስቡክ ገፃችንንም ይጎብኙ፦
http://www.facebook.com/pages/Ethiopian-Muslims-for-Justice-and-Freedom/216209875079095

# በዒንዎ ላይ ስለተሸረበው ሴራ ምን ያክል መረጃ ይደርሰዎታል

?

## ሴራውን ለማምከን ምን ያክል ዝግጅት አድርገዋል?

http://ethcriminalawnetwork.com/

# በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ መንግስት የሸረበውን ሴራ ያውቃሉ?

*****

የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ እየደረሰ ያለው በደል ቢተጠናከረ ሁኔታ ቀጥሎ ነው ያለው። የሙስሊሞችን እንድነት በማፈራረስ እምቱን እና አማኞችን ለማዳከም ከዚያም ከአገሪቱ ለማጥፋት መንግስት የረጅም ጊዜ እቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በአገራችንና በታሪካችን ልዩ በሆነ ጥናትና ቅኝበር ጸር ሙስሊም የሆኑ የውጭ የእይሁድና አከራሪ ክርስትያን ሀይላትን ከጎኑ እድርጓል። ለዚህ በከፍተኛ ደረጃ ለተቀነባበረ ሴራ እንደፈለገ ሰብስቦ ያስቀመጣቸውን እና በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ እውቅናም ይሁም ተወካይነት የሌለውን፤ ለሙስሊሙ ጥቅምም እንድትንም አፍታ ቆሞ ያልታየውን መጅሊስን እየተጠቀመ ይገኛል። ይህ እካል መንግስት ካዝናው ዉስጥ አጭቆ የያዘውን ሴራ በተፈለገው ሁኔታና ፍጥነት ማሰኬድ ግን አልቻለም። በዚህ ተሰፋ የቆረጠው መንግስት ከዐረ-ኢስላም ዐረ-ሙስሊም ሽረካዎቹ ጋር በመተባበር ከባዕድ አገር በአለም ሙስሊሞች ዘንድ በከፉፋይነቱ እና ከእስልምና አስተምህርት በብዙ መልኩ ከታከከለናው ትምህርት በመራቁ በታሳላት የእስልምና ምሁራን ፈትዋ የተሰጠበትን የአህባሽ ትምህርት በሙስሊሙ ላይ ለመጫን እቅድ አውጥቶ ተግባር ላይ እያዋለ ይገኛል። የዚህ ሂደት የመጀመሪያ ባይሆንም ከሰሞኑ ግን ይፋ በሆነ መልኩ በህረር ከተማ የመጀመሪያ ጉባኤ ላይ ከሊባናስ 15 የአህባሽ ባለስልጣን በማሟጣት ሙስሊሞችን በአህባሽ አሰቲምህርት የማጥመቅ ሂደት ከህምሌ 6-19, 2003 ላይ ተካሂዷል። በዚህ ጉባኤ ላይ ከአነርሱ አስተምህርት ውጭ ያለን ሁሉ ከሀዲ (ካፊር) በማለት ፊርጀውታል። ይህንን ሂደት ደግሞ የፊደራል ጉዳዮች ሚኒስተር ዶ/ር ሽፈራው ተክለማሪያም "መሳሪያ ነው አየታጠቅን ያለነው። ከዚህ በኋላ ሙተኮስ ብቻ ነው የሚጠበቅብን" በማለት ገልጸውታል። ከዚያም በጊዮን ሆቴል ሌላ ጉባኤ በማካሄድ ይህንኑ የሚያጠናክር መግለጫ ተሰጥቷል። ይህ በሚኒስተሩ የተገለጸው "ሙተኮሱ" ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ወደፊትም በርካታ "መተኮስ" ስራዎች ታቅደዋል።

ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሆይ! አገራቀ፡ እየተደረጉብን ያለውን ወንጀል፣ እየተፈጸሙብን ያለውን ሴራ ተረዱ አንወቅ። ከዚህ ቀጥሎ በሚመጡ ቅዳሜ፣ ሳምንታትና ወራት ውስጥ ቆመ ተብለው ከተያዙ ሴራዎች መካከል እጅግ ጥቂቱን ቁጥሮችን እናቀርባለን።

ሙስሊም ተማሪዎች በአምነታቸውና በትምህርታቸው ላይ እጅ መርሰ የሚደረገውን (ደንብ ለጀደብ ብሰ፣ ለሳት ሰንደይሰማ ለመከልከል) ደንብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዘመን ተማሪዎች ይፀናል (ከመስከረም 2003 ጀምሮ)። ይህ ደንብ ቀደም ብሎ ሊተገበር በቀረበበት ጊዜ ጠንካራ ተቃዉሞ የቀረበበት መሆኑን እናስታውሳለን። በተጨማሪ በአዲስ አበባ መጅሊስ ፅ/ቤት ሥር የህረርና የሶማሌ መጅሊሶች የወሰዱት አቋም ደንቡን መተግበር ማለት ሙስሊሙን ተማሪ መሰረታዊ የሆነውን የዜጎች መብት (የመማር መብት) የሚከድ እንደሆነ ግልጽ ያደረገ ነበር። ይሽው ከሁለት አመት በኋላ ምንም አይነት ማሻሻያ ሳያደረግበት ተግባር ላይ ለማዋል መሞከሩው እንዳለቀ እየተነገረን ነው። ለዚህ ደግሞ የአህባሽን የተጣመመ አስተምህርት እንደ መሳሪያና መረጃ ጥቅም ላይ ይዉላል።

*ረመዳን እንደወጣ (መስከረም 2004) ከ6000 – 10000 የሚጆሙ ሙስሊሞች በህረር ሀምሌ ላይ እንደተደረገው ሁሉ በአህባሽ የአምነት አስተምህርት ያማከመቂያ ጉባኤ ታዘጋጅሏል።* ለዚህም በመላ አገሪቱ ከየተኒሉ 15 ሰዎች (5 ሰው ከመጅሊስ አመራር፣ 5 ሰው ከሀይማኖት ምሁራን፣ 5 ሰው ደግሞ ከወጣቶች የተውጣጣ) እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ እየተመለመሉ ነው። ጉባኤው በአወልያ ማእከልና በከፍለ ሀገራትም እንደሚካሄድ ይጠበቃል። አጥማቂ ቡድን ከሊባናስ ይመጣሉ።

*መሰረዳችን፣ መድረሳዎችንና ሌሎች ለእስላም የሚሰሩ የትምህርት ማዕከላትን የአህባሽን አስተምህርት ለይከተሉም ከተባሉ ግለሰቦች የማጽዳት ዘመቻ ይካሄዳል።* ለምሳሌ በአዲስ አበባ ይህን እቅድ ለማሳካት የመጅሊስ ባለስልጣናት፣ የፓሊስና የደህንነት አካላት በቅርቡ ሚስጥራዊ ስብሰባ አካሂደው እርምጃ የሚወሰድባቸውን መስጅዶች፣ ኢማሞች፣ ኡስታዞች፣ በዚህ ሂደት ውስጥ እነዚህ አካላት ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና ለይተውና እቅድ አውጥተው አስቀምጠዋል። እርምጃው እንደሚወሰድባቸው በቀዳሚነት ከተነሱት መካከል የዳዒሻ መስጂድ፣ የፊትህና የሸኽ ሙሀመድ መስጂዶች ይገኙበታል።

*የአህባሽን አስተምህርት የማያስተምሩ የመሰለም ጀሊ ጀርመሽንና የመናናኛ አውታሮች ላይ ሰርምጃ ይወሰዳል።* በዚህ በኩል ትኩረት የተሰጠባቸው የሙስሊሞች ጉዳይ መፅጀት፣ ቲቪ አፍሪካ፣ ሙስለም ያዚኩንና የህትመትና ማከፋፈያ ድርጅቶች ይገኙበታል። የመሰለያሽ ጉዳይ ሁለተኛ እጭት የመጀመሪያ እትም ለምሳሌ እንደወጣ እጭት ተደርጎበታል፤ ዋና አዘጋጁ በደህንነት አካላት ስራውን እንዲያቆም ካለበለዚያ ለሚወሰድበት እርምጃ እንዲዘጋጅ ተነግሮታል። ቲቪ አፍሪካን በተመለከተ ቅዳሜ አገሰት 28፣ 2003 አህባሾች በአንዋር መስጂድ ባደረጉት ስብሰባ ላይ ቲቪው እንድዘጋ መንግስት የሱዳንን መንግስት ያናግር ዘንድ የሚጠይቅ ቡድን መድበዋል። በዚሁ ወቅት መንግስት ከጎናቸን ሰለሆነ ምንም ፍራቻ ሳይገባቸው አገራቱን "ወህብያ" ካሏቸው ለማጽዳት እንዲሰሩ በስብሰባው ላይ ለተገኙ ጥሪ ቀርቧል። በአብሰባው ላይ ከየመስጂዱ የአህባሽን አመለካከት ይደግፋሉ የተባሉ አራት አራት ሰዎች እንዲገኙ ተደርጎ ነበር። (ቲቪ አፍሪካን በተመለከተ መንግስትም ለጋድ እርምጃ ቀደም ብሎ በመሄድ የቴሊቪን ፕሮግራሙ ለሚተላለፍበት «ለረብ ሳት» ቴሌቪዥኑ "የአገሪቱን አብር መኖር አየረበሸ" በመሆኑ እንዳያስተናግዱ የሚጠይቅ ደብዳቤ አስገብቷል።)

- አዲስ ወደ ዩኒቨርሰቲ የሚገቡ ተማሪዎች፣ የመጂሊስ አመራር አባላት፣ ኢማሞችና የመድረሳ አስተማሪዎች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ይሽው የማጥመቅ ስራ መስከረም ዉስጥ ይከናወናል። ይህ ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ የፊደራል ጉዳዮች ለሁሉም ከልሎች የተዕዝዝ ደብዳቤ የላከ ሲሆን ስራው በክልል መጅሊሶችና በትምህርት ቢሮዎች ሀላፊነት የሚከናዎን ይሆናል።

- አስራ አረት የሚሆኑ አስላማዊ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ እና በመቶ የሚቆጠሩ ኢማሞች፣ ኡስታዞች፣ ዳዒዮች፣ ነጋዴዎችና ምሁራን እንደዚሁም በተለያየ ሀላፊነት ላይ ስርዓቱን አያገለገሉ ያሱ ሳቀሩ ላይ እርምጃ ሊወሰድባቸው ስም ዝርዝራቸው በደህንነት ተይዞ ይገኛል። እዚህ ላይ መጥቀስ የምንሻው ለበርከታ የቲሞች ሚስኪኖች፣ አዛውንትና እቅመ ደካሞች አለኝታ ሆኖ ሲሰራ የነበርው አስላማዊ የበጉ አድራጎት ድርጅት (ኢስላሚክ ሪሊፍ ኦርጋናይዜሽን) እውቅና ተነፍጎት በኢትዮጵያ እንዲቀሳቀስ መደረጉ እና በስሩ ያስተዳድራቸው የነበሩ ተቋማት አወልያ ኩሌጅን ጨምሮ ለመጅሊስ መሰጠቱ የዚሁ ሴራ አ፫ል መሆኑን ነው። የመጅሊሱ ፕሬዝዳንትም ይህን ስኬት "የአከራሪዎች መፈልፈያ የነበረውን ተቋም አፈራርሰናል" በማለት ደስታቸውን በአደባባይ ገልጸዋል።

ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሆይ! እነዚህ አንግድህ በሰፈው ከተጠነሰሰልን ሴራ ተንጨብ ተደርጎ የቀረቡ ናቸው። ከነዚህ የነሱ እርምጃዎች ተከስተው ልናይ አንችላለን። በኋላ ግራ እንዳይጋባን ወይንም ቢታሪክ ተወቃሽ እንሳንሆን በሙስሊሙ ላይ እየተደረገ ያለውን ደባ በቅርበት አንከታተል፣ የሚጠበቅብንን አስተዋጽ ለማበርከት ዝግጁ እንሁን።

ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሆይ! በአምነታችንና በማንነታችን ላይ የተሸረበውን ሴራ ከማዎቅ ጋር አብሮ ልንገንዝበው የሚገባው እነዚህ የሙስሊሙ ጠላቶች ይህንን እኩይ አላማቸውን ለማስፈፀም የሚጠቀሙበት ዘዴንም ነው። ለአቅዳ ለማሰፈጸሚያ ይሆናሉ ተብለው እየተሰራባቸ ካሉ ስትራቴጂዎች መካከል ሰራየ ብሎ ረብሻ ማስነሳትና በዚያ ሰበብ መስሊሞችን በጅምላ ሰር ቤት ማስገባት፣ በግደልና ቁም ስቅል ማሳጣት ይጠቀሳል ነው። ይህ እንግድህ ህጋዊ ሽፋን ለመስጠት ነው። የህይማኖት አከራሪነት ለመዋጋት በማለት መንግስት ባወጣው አገራዊ አቅድ ውስጥም ይህ ብትከክል ተቀምጦ እናገኘዋለን።

በሙስሊሞች መካከል የአስተያየት ልዩነት ከበፊት ጀምሮ የነበረና ወደፊትም የሚኖር ነው። በትክክለኛው የአለማም አስተምህርት ይህ አይነት ልዩነት በመጥፎ የሚታይ ሳይሆን እንዳውም የሚፈለግና ለሙስሊሞች አድጉና

http://ethcriminalawnetwork.com/

## ዜና

- በአዲስ አበባ ቦጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የሚኖሩ ሙስሊሞች የመጅሊስ አመራር ምርጫን ለማካሄድ ለወረዳቸዉ የምርጫ አስፈፃሚዎችን መምረጣቸዉን አስታወቁ:: የወረዳዉ ሙስሊሞች ባሳለፍነዉ እሁድ በሼህ ሆጀሌ መስጂድ ባካሄዱት ስብሰባ ላይ ነዉ ዘጠኝ አባላት ያሉት የምርጫ አስፈፃሚዎችን የመረጡት:: ምርጫዉ ሁሉንም ማህበረሰብ ሴቱንም ወንዱንም ያሳተፈ ሲሆን ፍፁም ዲሞክራሲያዊ እንደነበር ነዉ የተገለፀዉ:: የምርጫዉም ዉጤት ተመራጮቹ ባገኙት ድምፅ መሠረት ከአንድ እስከ ዘጠኝ የተዘረዘሩ ሲሆን በመስጂዱ መግቢያ በር ላይ ለሙስሊሙ በይፉ እንደተሰጠ ነዉ የተገለፀዉ:: እነዚህ አራት ቋሚና አምስት ተጠባባቂ የምርጫ አስፈፃሚዎች በቅርቡ ለሚካሄደዉ የመጅሊስ ምርጫ ለማስተባበር ነዉ በህዝቡ የተመረጡት:: ሁላችንም በያለንበት ቦታና ወረዳ የምርጫ አስፈፃሚዎችን በመምረጥ ምርጫዉን ፍትሀዊ ለማድረግ በሚደረገዉ ጥረት ላይ የበኩላችንን አስተዋፅኦ እናበርክት!!!

- መንግስት በሙስሊሞች የእምነት ጉዳይ ላይ በግልፅ ጣልቃ መግባቱን በሚያረጋግጥ መልኩ የአህባሽን አስተምህሮ በግድ በህዝበ ሙስሊሙ ላይ ለመጫን የሚደርገዉ እንቅስቃሴ እንደቀጠለ መሆኑ ተሰማ:: በትላናንትናዉ እለት በአዳማ ከተማ በተጠናቀቀዉ ስብሰባ ላይ መንግስት የኢትዮጲያ አህለል ሱና ወልጀምአ (ሱኑ ሱፊ) ማህበር መመስረቱ ተገልፆል:: በዚህ ማህበር ምስረታ ላይ የመንግስት ታላላቅ ባለስልጣናት የተገኙ ሲሆን ከነዚህም መካከል አቶ ጁነዲን ሳዶ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ም/ፕሬዝዳንት ተጠቃሽ ሲሆኑ የህገ ወጡ መጅሊስ ፕሬዝዳንትም አቶ አህመዲን ተገኝተዋል::

ይህ ማህበር ዶና አላማዉ የአህባሽን አስተምህሮ በኢትዮጲያ ዉስጥ በከፍተኛ ደረጃ ለማስፋፋት መሆኑ ታዉቋል:: ይህ ማህበር በጅማዉ ሼህ ከድርን በመሳሰሉ ሰዎች የሚመራ ሲሆን ከመጅሊስ በማይተናነስ መልኩ የአህባሽን አስተምህሮ በሙስሊሙ ላይ በግዳጅ ለመጫን የሚደረገዉን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ለመንግስት አገዛ እንደሚያደርግ ነዉ የተገለፀዉ::

የዚህ ማህበር ምስረታ በኢቲቪ የዜና ሽፋን ተሰጥቶት መቅረቡና ስብሰባዉ የተካሄደበት የኦሮሚያ ዉስጥ አዳራሽ መሆኑ ማህበሩ መንግስት እንደመሰረተዉና የሙስሊሞችን ህገ መንግስታዊ መብታቸዉን እየገፈፈ መሆኑን አይተኛ ምሳሌ መሆኑ ተገልፆዋል:: ይህ ማህበር ለኢትዮጲያ ሙስሊሞች ከፍተኛ አደጋ ሊሆን እንደሚችል እየተነገረ ነዉ:: በተመሳሳይም በሚያሳዝን ሁኔታ ለረጅም አመት ሙስሊሞችን ሲያገለግሉ የነበሩ ኢስላማዊ ድርጅቶችን ማን መንግስት እየዘጋ መሆኑ የሚታወስ ነዉ:: ህዝበ ሙስሊሙ አንድነቱን ከመቼዉም በላይ በማጠናከር የቀጠረጡብንን ሴራዎች ለማክሸፍ ቆርጠን መነሳት ይኖርብናል!!!

- የህዝቡ ዉክልና የሌለዉ የኢትዮጲያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ምኪር ቤት ወይም መጅሊስ መተዳደሪያ ደንባቸዉን በድብቅ ማስተካከላቸዉ ተሰማ። ይሀንን ማሻሻያ ያደረጉት ከህዝቡ መሰለሙ ሀገ ዉጥ ናችሁ የህዝብ ዉክልና የላችሁም ስለዚህ ዉረዱ የሚል ተቃዉሞ በቅርቡ ከተነሳባቸዉ በሁላ መሆኑ ተገልፆዋል።
ይህ በድብቅ የተሻሻለዉን መተዳደሪያ ደንብ ያፀደቁትና የፊረሙበት ከሰራ አስፈፃሚዎች መካከል ሰባቱ(7) ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት ስራ አስፈፃሚዎች ግን ስለመሻሻሉ የሚያዉቁት ጉዳይ አለመኖሩ ነዉ የተገለፀዉ። በድብቅ በተሻሻለዉ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 40 ዉስጥ በተጠቀሰዉ መሰረት በሁሉም መቀቅር ዉስጥ የሚገኙ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ የሚደረገው በየ 10 ዓመት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱም ሊዘገይ ይችላል ይላል:: በሙስሊሙ ላይ በመቀለድ መጅሊሰን መኖሪያ ቤታቸው አድርገውታል ::

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፌርማ

547

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምፃችን ይሰማ!!

ቁ.14

08-10-04 E.C

## 23ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ !!

### መልዕክታችን ይድረሳችሁ!!

እስከዛሬ ድረስ በተደረገው የ23 ሳምንታት ሙከትን የማስከበር ሰላማዊ የትግል ጉዞ የህዝብ ድምፅ እንዲሰማ ያልተባለና ያልተነገረ ቁም ነገር የለም። ነገር ግን እነዚህን ቁም ነገሮች ጨብጦ ለሃገር ልማት፣ ለሃገር እድገት፣ ለህዝብ ሙተማመንና የዳበረ የእርስ በርስ ግንኙነት በማሰብ በህዝበ ሙስሊሙ የተነሱትን ለመመለስ ቀላል የሆኑ ጥያቄዎችን በአግባቡ ከማስተናገድ ይልቅ የተለያየ ሽፋን በመስጠት ወደ ጎን መባሉን አስተውለናል።

ይህ ምንም ማብራሪያ የማያስፈልገው እንደ ፀሃይ ብርሃን ፍንትው ብሎ የሚታይ ፍፁም የሙብት ጥያቄ የሙብት ትግል ነው። ይህን ትግል ያዩ የሰሙ ሁሉ እስኪገረሙ ድረስ መስከረውለታል። ለነገሩ እራሳቸውም ብትሆኑ በተለያየ መድረክ አዎን ሰላማዊ ጥያቄ ነው ሊመለስ ስለሚገባው ደግሞ የሚያረካ መልስ እንሰጣለን ስትሉ ተደምጣችኋል።

ጥያቄው የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ጥያቄ መሆኑ ይታወቃል። እውነታው እየታወቀ ለምን ጥያቄዎቹን በተለያየ መንገድ ቅርፃቸውን ለመቀያየር ሙከራ ይደረጋል? የህዝቡ መሰረታዊ ፍላጎት እየታወቀ ለምን ይህን የህዝብ ፍላጎት የሚሸርና የሌሎችን ፍላጎት የሚያነግስ ሂደት ተመረጠ? ጥያቄው የመሰረተ ሃሳብ ጥያቄ ነው። የተያዘውን አቅጣጫ ህዝበ ሙስሊሙ በምንም መልኩ የማይቀበለው መሆኑ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ለተከታታይ 6 ወራት በተገበረው የፀና ውጥና አንድ የሆነ ሰላማዊ የተቃውሞ ሂደት አሳይቷል።

ሙስሊሙ የሚፈልገው የመጅሊስ መሪ ዓይነቱ እየታወቀ የማይፈልገው እና የመይቀበለዉን በአህባሽ የተጠመቀ የመጅሊስ መሪ ለማስመረጥ ለምን ሽርጉዱ በዛ? መጅሊስ ከአህባሽ ጋር ያደረገዉን ጋብቻ በይፋ ሰምተናል። ሊመሆኑ መንግስትስ ከአህባሽ ጋር ጠንከር ያለ ዝምድና በውስጥ ለውስጥ መስርቷል እስከንል ድረስ ለምን ለአህባሾችና ለአስተምህሮዋቸው ጥብቅና ተቆመላቸው?

አሁን አዲስ አበባን ጨምሮ በየከፍለሃገረሩ እየተሰራ ባለው መልኩ ምርጫዉን አጣድፎና በዚ በዛ ብሎ የሚፈልጓቸውን አካሎች የመጅሊስ መሪ አድርጎ መሰየም ለማንም የማይበጅ ሀገርንም በእጅጉ የሚጎዳ ተግባር ነውና ልትገሽ ጥቅም ተብሎ ለብዙ ጊዜ የተገነባዉን መልካም ስም ማጥፋትና በህዝብና በሃገር ላይ ችግር መጎተት ይቅር እንላለን።

ህዝበ የመረጣቸውን ተወካዮቻችንን ማወያየት አለመፈለግና ብሎም የማጥላላት አዝማሚያ ተመልክተናል። በእንባሩ ግን ህዝቡ አይወክሉኝም ህገወጦች ስለሆኑ ይውረዱልኝ ብሎ አንቅሮ የተፋቸውን የመጅሊስ አመራሮች አቅፎና ከጉያ ሰር ሸጉጦ ቀን ከለሊት እያማከሩና ትእዛዝ እየሰጡ የመንግስት ባለስልጣን እስኪመሰሉ ድረስ አርቦሽና የሰራ ባልደረባ ማድረግ በህዝበ ሙስሊሙ ሙቼም ይቅር የማያስብል ቁስል እያስቀመጥን መሆኑ ደለሚቢት እንላለን።

ህዝበ ሙስሊሙ ለ6 ወር ያህል የተለያዩ ማስፈራሪያዎች፣ የማምታታ መግለጫዎች፣ የመከፋፈልና የማተራመስ ብሎም የማሸማቀቅ ድርጊቶችን ሁላ በሚገርም ተአማስትና ፍፁም ሰላማዊ በሆነ የተቃውሞ ሂደት ውስጥ አልፎ ዛሬ ላይ ደርሷል። ይህ በመንግስት ዘንድ እጅግ ሊያስመሰግነውና ለዚህ ተግባሩ ምላሽ የፊለገዉን እንዲመርጥ ሁኔታዎች በበቂ ደረጃ ሊመቻቹለት ሲገባ በተቃራኒው ጆሮ ዳባ ልበስ የሚያስመስል ሁኔታዎችን በተጨባጭ እያስተዋልን ነው። ይህ አሳፋሪም እስኮዖሪም ድርጊት ነውና በቶሎ ሊታረም ይገባዋል እንላለን።

በመሬት ላይ የሌለ አጉል ስእል በመሳል በጣም ግልፅና ግልፅ የሆኑ ጥያቄዎችን በፅንፈኝነትና በአክራሪነት ጥላሸት እየቀቡ ለመሄድ የሚደረገው ጥረት እራሱ ፅንፈኝነትና አክራሪነት ስለሆነ ሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን የሌላ እምነት ተከታዮችና መሪዎቻቸውም ጭምር የተቃወሙበት ተጨባጭ ነው ያለው።

በመሆኑም ሰነተዋወቅ አንሸዋወድ። በየቦታው እየተደረገ ያለው የምርጫ ድራማ ቆሞ ህዝቡ እየጠየቀ እንዳለው ምርጫው ፍትሃዊና ነፃ ይሁን። ፍትሃዊነት የጎደለዉን ምርጫ አከናውኜ ሰቢቃ ያልተቀበለኝን በአንድ ላይ ፈርጀ እንዲህ እለዋለው ማለት አሁንም ከናንተ የምንጠብቀው ተግባር አይደምና ለ6 ወር የጮህንለትን የፍትህ ያለህ? ድምፃችንን ስሙልን። ድምፃችን ይሰማ !! ድምፃችን ይሰማ !!



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

## የኢትዮጵያ ሙስሊም አቀበቶች

ሚገለጫዎቹ ይለዩ ይሆናል እንጂ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በቡጥጫ እየመጣቸው ያሉት አቀበቶች በሌሎች አገራት ያሉ ሙስሊሞች እየወጧቸው ካሉት አቀበቶች በመሠረቱ ይብሳሉ። በየትኛውም የዓለም ክፍል ብትሄዱ ሙስሊሞች የሚታዩት በጥርጣሬ ነው። በየቦታው ‹‹እንቅፋቶች ናቸው›› ተብለው ሰጋራ ታያላችሁ። የዚህ ወቅት ፈሊጥ ደግሞ ለደህንነት አስጊ እንደሆኑ ተቆጥረዋል። ሰሞኑን ከወደ አሜሪካ አገር ኒዮርክ ክፍለ አገር ‹‹የተሰማ ያለው ነገር ይህንን የሚመስክርልን ነው። ሙስሊሞች በሙስሊምነታቸው ብቻ በድብቅና በግልጽ እየተከሰሱ ይገኛሉ። ‹‹ሙስሊምነታችሁ እስካልተረጋገጠ ንፁህ ናችሁ›› የሚል አዲስ ዕግ የተደረገ ይመስላል።

በታሪክ እንዳነበብነው አፄዎቹ ‹‹ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ›› ሕልም ነበራቸው። በመሠረቱ ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ ከጠላቶቿ በስውር ማንም የሚደግፈው የተቀደሰ ሃሳብ ነው። ነገር ግን ይህን የታቀደሰ ሃሳብ ወደ መሬት ሲያወርዱት በመርገምት ለወሱት። በስመ ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ ሙስሊሙን አሳደዱት፤ ገደሉት፤ አረዱት፤ ሰብዓዊ ክብሩን ገፈፉት። ሙስሊሙን በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ የተደነቀረ ደንቃራ አድርገው ሳሉት።

‹‹ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት›› በሚል ወልጋዳ አስተሳሰብ ሙስሊሙ ዘወትር በጥርጣሬ መታየት እንዳለበት በማድረግ የሚታመን ሕዝብ አደረጉት። በነገራችን ላይ ከላይ እንደጠቀስኩት ሙስሊሙ ላይ በጠላቶች የተሸረበው ሴራ (ልታዊና ድርጅታዊ) ‹‹ሲስተማቲክና ኢንስቲቱሽናላይዝድ›› በመሆኑ ይኸው አሪዎች ካለፉ 80 አመታት ቢያልፉትም እስካሁንም ድረስ ሕያው ሆኖ አለ።

በ2002 የምርጫ ፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር ወቅት አቶ ሬድዋን ሁሴን ‹‹ተቃዋሚዎችን ‹የ‹ሲጅ ማንታሊቲ› ተጠቂ ናችሁ›› ብለዋቸው ነበር። ‹‹የኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት››ን ስነ ልቦናዊ አንድምታ መጠቆማቸው ነው። ነገር ግን ሙስሊሙ አሁንም ፓርቲያቸው በሚመራው መንግስት ውስጥም ለቁጥጥር በማያመች መልኩ በNGO (መያድ) (ግብረ ሰናይ ድርጅት) እየተዳደረ አንዳለ ዘንግተውት ይሆን?

ይኸው አሁን ደግሞ ‹‹ለጸጥታና ደህንነት አጠራጣሪ ናችሁ›› ተብሰን አህባሽን በግድ ሊግቱን የመጅሊስ አመራር ካድሬዎችና አንዳንድ የመንግስት



ባለስልጣናት ትንኮሳ ውስጥ ገብተዋል። እንደ አባቶቻቸው አፄዎች እነዚህ ባለስልጣናትና ካድሬዎች እየተጠቀሙ ያሉት በተቀደሰ ዓላማ ከፈን ውስጥ ተሸፍነው ነው። ‹‹ለልማትና ዲሞክራሲ ደንቃራ ናችሁ›› የሚል ነው የዘመኑ ጭንቋ። ‹‹ልማትና ዲሞክራሲ›› የተቀደሱ ነገሮች ናቸው። የኢትዮጵያ ጠላት ባልሆነ በስተቀር ማንም ልማትና ዲሞክራሲን የሚቃወመው የለም። ነገር ግን ጫፉ ላይ ሲወርድ እንደ አፄዎቹ ሁሉ ሙስሊሙን በጅምላ ለመምታት ዳር ዳር እተባለ ነው። ዳር ዳርም መባል አይደለም፤ ተጀምሯል። ሙስሊሙ ያነሳው ጥያቄ ስለመጅሊሱ መጠናከር፤ መሪዎቹን ስለመምረጥና ተቋሙን ከ NGO (መያድነት) ስለማስለቀቅ መሆኑ ቀርቶ ጥረቱን ለማስቀየስና የአህባሽ ጉዳይ ለማድረግ እየታገሉ ይገኛሉ። አህባሽ በኢትዮጵያ የመንቀሳቀስ መብቱ በህገ መንግሥቱ የተጠበቀ ስለሆነ ሕገ መንግሥቱና ሕግ በሚፈቅደው አቅጣጫ መንቀሳቀስ፤ እምነቱን ማስፋፋት ይችላል። ፖሊስና ደህንነት ቆሞ ሙስሊሙን ከአህባሽ ለማጥመቅ በልማትና ዲሞክራሲ አሳቦ መቅረብ ግን አደጋ ነው።

የአቀበቶቻችን ምሰሶ ይኸው ነው። ከጥንት ከጠዋቱ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በዘለቀ በ‹‹ሲስተማቲክና ኢንስቲቱሽናላይዝድ›› በሆነ መንገድ ሙስሊሙን ቀጣጫ (ሰናይ) ነገሮች ሁሉ እንቅፋት አድርጎ ማቅረብ ሴራና ስልት ነው። ሪጅሊሳችን እስካሁን NGO (መያድ) የሆነው፤ አባሎቻችንንም መምረጥ እንዳንችል የተደረግነው ሰንኮፉ ጠልቆ በተቀበረ መርዛማ አስተሳሰብ ነው።

እናም ብዙ ጊዜ እነዚህ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ከውጪም ጭምር የሚረዱ በመሆናቸው ጉልበቱም ሃብቱም አላቸው። የተማሩም ጭምር ስለሆኑ ሰራቸውን አዘምነዋል። በተቃራኒው እኛ የነሱን ያህል ሃብት የለንም። ሃብቱም እንዳይኖረን አንድ ከወለድ ነፃ የሆነ (ኢስላማዊ) ባንክ እንኳ እንዳናቋቁም ጠንቅቀው እየሰሩ ነው። እንዳንማር በሶላትና በሂጃብ እያዋከቡን ነው። ከንግዱም ዓለም ተሳትፏችንን ቀስ በቀስ እያሳሱት ይገኛሉ። አሁን ደግሞ ጥራሽነ በሃይማኖታችን መጥተዋል። አያችሁ ምን ያህል የተቀናበረ ሴራ እንደሆነ?

### ሰላማዊው ትግል

ቀስ በቀስ ብዙ እናያለን። የችግሩ ጥልቀት ምን ድረስ እንደሆነም እንረዳለን። ከዚህ አስቀያሚ፤ ስስታምና የኢፍትሃዊነት አድሎዋዊ አቀበት በድል ልንወጣ የምንችለው በሰላማዊ ሁኔታ ነባራዊ ሁኔታዎችን ስናጤን ነው። አብስለሂያማ ‹‹ይኸውላችሁ ብለናችሁ ነበር!›› ማለታቸው አይቀርም።



http://ethcriminalawnetwork.com/

እጅግ አስመስጋኝ ተግባር ነው:: በተመሳሳይ ስህተት ውስጥ ያሉ ሌሎች ዓለሞችም ከእሳቸው ትምህርት ወስደው ለስልጣንና ገንዘብ ሳይሆን ለሐቅ ተገዢ መሆን እንዳለባቸው እንጠቁማለን:: የሸኹ መስጂድ ላይ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ ለመድሊስ እጅግ ቅስም ሰባሪ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል:: አላሁ አክበር!

## መጅሊስ ጥፋቱን ቀጥሏል

ባለፈው እትማችን መጅሊስ በፌደራል ጉዳይ ሚኒስቴር ወሃቢያ አክራሪና አሸባሪ ቡድን ስለመሆኑ የሚያሳይ ጥናት በጽሁፍ እንዲያቀረብ ታዞ እንደነበርና ሰራ አስፈጻሚውን ለብስበ ይህን ስራ እንዲሰሩ ቢጠይቅም ዑለማ ምክር ቤት ነው ይህን መስራት ያለበት በሚል ፍቃደኛ አለመሆናቸውንና በተመሳሳይም የዑለማእ ምክር ቤትም እኛን አይመለከትም ማለቱን አስነብበናል:: መጅሊሱና አንዳንድ የመንግስት አካላት ይህንኑ እኩይ ዐላማ ለማሳካት በያገነው ሳምንት ከየክልሉ ሶስት ሶስት ይህን ዐላማ ሊያሳኩ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ "ዑለማዎች" አዲስ አበባ በአስቸኳይ እንዲመጡ መደገሩን ለማወቅ ተችሏል::

እነዚሁ "ዑለማዎች" በተለይ የመንግስት ሚዲያዎች በመቅረብ ስለ ወሃቢያ አደገኛነት እንዲያስተምሩ ሊደረግ ይችላል የሚል ግምት ያለ ሲሆን ህዝበ ሙስሊሙ ይህን ሴራ ከወዲሁ በመረዳት የሚዲያ ሰለባ እንዳይሆን ከወዲሁ እንጠቁማለን:: በመሰረቱ የሙስሊሙ ሰላማዊ የመብት ጥያቄዎች ወሃቢያ ከሚባል ነገር ጋር ምንም አይነት ትስስር የሌላቸውና ጥያቄውም የሁሉም ሙስሊም ህብረተሰብ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው:: ነገር ግን አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣኖችና ሚዲያዎች ወሃቢይ የሆነው አልቃኢዳ ኢትዮጵያ ውስጥ ህዋስ መስርቷል የሚል ዜና በሰፊው በማሰራጨት ሙስሊሙ ሰላማዊ ጥያቄዎቹን ባለማገባቡ እንዳያቀርብ የማሸማቀቅ ስራ እየሰሩ መሆኑ ይታወቃል::

**መጅሊስ ሳይወ ድ አህባሽ ሳይወገድ ሰላማዊ ትግላችን አይቆምም!**






# ድምፃችን ይሰማ! 4

የተቃውሞ ድምፅ

የካቲት 30/2004 - 9ኛውየተቃውሞ ረኑ


# ዜና

## እውነት መጣ ፣ሐሰት ወደቀ

ባለፈው ጁሙዓ በአወሊያ መስጂድ ከበርካታ የአገሪቱ ክልሎችና ከተሞች አወሊያ የተነሳው ጥያቄ የኛም ጥያቄ በማለት ከየአካባቢያቸው ፊርማዎች አሰባስበው የመጡ ተወካዮች ንግግር አድርገዋል:: በተለይም የመጅሊሱ "ፕሬዝደንት" አቶ አህመዲን ከተማ ከሆነችው የሀረሪ ክምቦልቻን ወክለው የመጡት ሸኽ ተውፊቅ አብዱ ያደረጉት ንግግር እጅግ አስደማሚና አቶ አህመዲን በሬዲዮ ፋና ቀርበው ከክልል ጀምሮ በተዋረድ እስከ ቀበሌ ድረስ በህገብ ተመርጬ ነው የመጣሁት ብለው የተናገሩትን ቅጥፈት ከመሰረቱ የናደ ነበር:: ሸኹ አቶ አህመዲንን ህብረተሰቡ በጭራሽ ያልመረጣቸው መሆኑን ገልጸው አሁን በተደረገው የተቃውሞ ፊርማ ማሰባሰብ ሂደት ከሚህችው ከተማ ብቻ እስካሁን ከ 32000 ሰው በላይ ፊርማ የፈረመ መሆኑንና ከፌራንጎቹ መህከል የ"ፕሬዝደንቱ" ወንድምና አጎትም እንደሚገኙበት አብራርተዋል:: ሸኹ ከምስራቅ ሐረርጌ ዞን ብቻ የተሰበሰቡ ከ 114000 በላይ ፊርማዎች ይዘው የመጡ ሲሆን የምዕራብ ሀረርጌው ተወካይ በበኩላቸው ከ 140000 በላይ ፊርማ ይዘው እንደመጡ አስታውቀዋል:: በአገር አቀፍ ደረጃ እስካሁን ከአንድ ሚሊየን በላይ ሰዎች ፊርመዋል ተብሎ ይገመታል::

በሌላ በኩል ከኦሮሚያ አካባቢ የመጡት ተወካዮች ጥያቄያቸውን ለኦሮሚያ ጽ/ቤት አቅርበው ጽ/ቤቱ ጉዳዩ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴርን እንደሚመለከት ገልጸላቸው ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማቅናበት ሂደት ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል::

## ምክትል ኢማሙ በይፉ ይቅርታ ጠየቁ

በአዲስ አበባ የሚገኘዉ የታላቁ የኑር መስጂድ ምክትል ኢማም ባለፈው ጁሙዓ ለህዝበ ሙስሊሙ በይፉ ይቅርታ ጠየቁ:: ምክትል ኢማሙ ይቅርታ የጠየቁበት ምክንያት ከአስራ አምስት ቀን በፊት ለጁምአ ሰላት በኑር መስጂድ ለተሰበሰበዉ ሙስሊም ህብረተሰብ ወቅታዊውን የሙስሊም እንቅስቃሴ በማውገዝ ሲደረጉት ንግግርና በወቅቱም ከአፋቸው ለወጡ አንዳንድ አያዎ ቃላቶች ነው::: "ባለፈዉ ለተናገርኩት ንግግር ሁላችሁም አፍ (ይቅርታ) አድርጉልኝ" በማለት አጠር ያለ ይቅርታ አቅርገዋል:: የሰው ልጅ አላህ ሲፈጥረው ፍጹም ያልሆነና ስህተትም መስራትም መሰረታዊ ባህሪው ሲሆን ለተሰራ ጥፋት በዚህ መልኩ ይቅርታ መጠየቅ

ወደ ገጽ ሣ ዞሯል



http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌደ[illegible] ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የበጎ አድራጎት [illegible]ሶችና ማህበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Charities and societies Agency

ቁ[illegible] Ref. No. 21/ChsA-13,863
ቀን Date 23 ኅዳር 2004

በኢት/ፌደ/ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ
የታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ለተጠየቅነው ጥያቄ መልስ ስለመስጠት፡፡

ዝርዝራቸው የተገለፀው በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት በኤጀንሲው ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆን አለመሆኑ እንዲረጋገጥ፣ በኤጀንሲው ተመዝግቦ ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ ከእነ መተዳደሪያ ደንቡ እንዲሁም የየድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ እና የቦርድ አባላት እነማን እንደሆኑ ጭምር አጣርተን በፅሁፍ ምላሽ እንድንሰጣችሁ በቁጥር 10343/04 በቀን 15/12/2004 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቃችሁናል፡፡

ስለሆነም ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የተገለፁት 4/አራት/ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በኤጀንሲው ያልተመዘገቡና ሠርተፊኬት የሌላቸው ሲሆኑ የተቀሩት 2/ሁለት/ በኤጀንሲው የተመዘገቡና ሠርተፊኬት ያላቸው መሆኑን እየገለፅን ስም ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ሁለት ገፅ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን በተጨማሪም በኤጀንሲው የተመዘገቡት የሁለቱ ድርጅቶች የሥራ አስኪያጅ ስም፣ የቦርድ አባላት ስም፣ መተዳደሪያ ደንባቸውን እና የመመስረቻ ሠነዳቸው የያዘ ዝርዝር መረጃ በዚህ ሸኝ ደብዳቤ አያይዘን የላክን መሆኑን እናሣስባለን፡፡

በተጨማሪም በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ፈቃድ ሲያወጡ የሚኖራቸው የሥራ ክፍፍል እና ማሟላት የሚገባቸው በአዋጅ የተገለፀ ስለሆነ አዋጅ ቁጥር 621/2001 እና ደንብ ቁጥር 168/2001 እንዲሁም 8/ስምንት/ መመርያዎች በቀን 14/12/2004 እና በቁጥር 21/ChsA-13,422 በደብዳቤ አያይዘን በCD የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኃይለሥላሴ ገብረሚካኤል በርሄ
Hailleselassie Gebremichael Berhie
የምዝገባ ፣ ክትትልና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት
Registration, Monitoring and Support Core Process Owner

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ

551

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፍርድ ቤቱ በጽሁፍ መጠየቅ ፡፡ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
መልስ ከደረሰው ሁለት ቀን ፡፡
ይህ ውሳኔ ለተከሳሽ መድረሱን ከገለጸ ሰባት ቀን
ሞልቶታል ፡፡

ፈ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ፡፡

ፍርድ ቤቱ

ታህሳስ 26/8/2004 ዓ.ም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

بسم الله الرحمن الرحيم

# የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት

THE ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL
Addis Ababa - Ethiopia

المجلس الأعلى للشئون الإسلامية في إثيوبيا
إثيوبيا ـ أديس أبابا

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

ቁጥር Ref. No. ጠ/ም/0079/03/32/04
ቀን Date 17/11/04

በኢ/ፌ/ፖ/ሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ
ለታክቲክ ምርመራ ዳይሬክትሬት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- **በቁጥር ጠ/ም/0061/03/32/04 በቀን 14/11/04 ለተፃፈው ደብዳቤ ተጨማሪ ማብራሪያ ስለመስጠትን ይመለከታል፤**

በኢ/ፌ/ፖ/ሊስ /ወንጀል ምርመራ ዘርፍ የታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 9319/04 በቀን 12/11/2004 የወ/ሮ ሀቢባ መሀመድ ሙሀመድ የተባሉትን ግለሰብ አስመልክቶ ከሳውዲዐረቢያ ኤምባሲ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ስም ገንዘብና የቅዱስ ቁርዐን መፅሐፍ አውጥተው እንዲያከፋፍሉ ከጠ/ም/ቤቱ ፅውቅና የተሰጣቸው ስለመሆኑና ጉዳዩን ም/ቤታችን ያላወቁት ጉዳይ ስለመኖሩ እንዲገለፅላቸ በጠየቃችሁት መሠረት ከፍ ብሎ ቁጥርና ቀኑ በተጠቀሰው ደብዳቤ መልስ የሰጠንበት ቢሆንም ጉዳዩን ይበልጥ ለማጣራት ይረዳችሁ ዘንድ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በስልክ በተጠየቅነው መሠረት ከም/ቤታችን አሠራር አንፃር ማንኛውም ሰው ለመስጊድና ለግል ዕርዳታ ጥያቄ ሳያቀርብ በመጀመሪያ ከም/ቤቱ የታችኛው መዋቅር መስጊድ ጀምሮ በየደረጃው ጉዳዩን አጣርቶ ወደ ጠ/ም/ቤቱ ሲያቀርቡ የመስጊድ ጉዳይ ከሆነ ለጠ/ም/ቤቱ መስጅድና አውቃፍ ዘርፍ ሕጋዊ ደረሰኝና ማህተም ያላቸው መሆኑን ሲረጋገጥ የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከተው ሁሉ በሀገር ውስጥ እርዳታ ማሰባሰብ እንዲችሉ ለ3 ወራት የድጋፍ ደብዳቤ የሚሰጥ ሲሆን በክልሎች ላይ በሚገኙ መስጊዶች ላይ ዕርዳታ ማሰባሰብ እንዲችሉ ከላይ በተጠቀሰው አሠራር መሠረት ለክልሎች የድጋፍ ደብዳቤ በመፃፍና ከዚህም በተጨማሪ ውጪ ሀገር ዕርዳታ እንዲያሰባስቡላቸው የክልሉ እ/ጉ/ከ/ም/ቤትና የመስጊዱ ኮሚቴ በጋራ ባዋቀሩት ኮሚቴ መሠረት ለ3 ወራት የድጋፍ ደብዳቤ የሚፃፍ ሲሆን ም/ቤታችንም ለግለሰብዋ ያፃፈላት የድጋፍ ደብዳቤ አለመኖሩን እናሳውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

Sheikh Ahmedin Sh. Abdullahi Cherif
شيخ احمد الدين شيخ عبد الله
ፕሬዚዳንት
President


251 -11 - 3725965 /3728129/ 3726306/3726307
28441
Fax= 251 -11- 372 59 66
E-mail=eiasc@ethionet.et

٢٥١-١١-٣٧٢٥٩٦٥/٣٧٢٨١٢٩
٢٥١-١١-٣٧٢٢٦٣٠٦/٣٧٢٦٣٠٧
٢٨٤٤١
فاكس =٢٥١-١١-٣٧٢٥٩٦٦
إميل =eiasc@ethionet.et



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ



http://ethcriminalawnetwork.com/

ቁ ቀ ቁ ፲

بسم الله الرحمن الرحيم

# የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት


THE ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL
Addis Ababa - Ethiopia

المجلس الأعلى للشئون الإسلامية في اثيوبيا
إثيوبيا - أديس أبابا

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ


ቁጥር ማ/ም/0061/03132/04
Ref. No.
ቀን 14/11/2004
Date

በኢት/ፌደ/ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ
ለታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ተገቢውን መልስ መስጠት ይመለከታል፤

በኢት/ፌደ/ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ የታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 9319/04 በቀን 12/11/04 በተፃፈ ደብዳቤ ወ/ሮ ሀቢባ ሙሃመድ የተባሉት ግለሰብ ከሳውዲዓረቢያ ኤምባሲ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ስም ገንዘብ እንዲሁም ሃይማኖታዊ የቁርዓን መፅሐፍ አውጥተው እንዲያከፋፍሉ ፅውቅና የተሰጣቸው ወይም ለም/ቤቱ ያሳወቁት ጉዳይ ካለ በተቻለ ፍጥነት ተገልፆ እንዲላክልን ብሎ መጠየቁ ይታወቃል።

በመሆኑም ከላይ በስም ተጠቃሽ ጠ/ም/ቤቱ ምንም ዓይነት እውቅና ያልሰጠ እና ለም/ቤቱም ያሳወቁት ጉዳይ የሌለ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ሐጅ አዛም ዩሱፍ መሐመድ
Haji Azam yusuf Mahammad
الحاج عزام يوسف محمد
ምክትል ፕሬዝዳንት
Vice President
نائب الرئيس

ግልባጭ፤ ▪ ለጠ/ም/ቤቱ ፕሬዚደንት

▪ ለጠ/ም/ቤቱ ዋና ፀሐፊ

ኢ/ኢ/ጉ/ጠ/ም/ቤት

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ


251 -11 - 3725965 /3728129/ 3726306/3726307
28441
Fax= 251 -11- 372 59 66
E-mail=eiasc@ethionet.et

☎ ٢٥١-١١-٣٧٢٨١٢٩/٣٧٢٥٩٦٥
٢٥١-١١-٣٧٢٦٣٠٧/٣٧٢٢٦٣٠٦
٢٨٤٤١
فاكس =٢٥١-١١-٣٧٢٥٩٦٦
إميل =eiasc@ethionet.et



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

12-11-2004
12-11-2004

# የሃሰት ፕሮፖጋንዳ መደጋገም የእምነት መብት ጥያቄን ህገወጥ አያደርገውም!

ህዝበ ሙስሊሙ ያነሳቸውን የመብት ጥያቄዎችን ተንተርሶ በአንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት እየታየ ያለውን ህዝብን የማሸማቀቅና የማዋከብ አመለካከትና ተግባርን ለመቃወም የተዘጋጀ የአቋም ማሳወቂያ ዕሁድ



ሚያዚያ 2004

አዲስ አበባ



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሳይቀር ተቀብለው ባናገሯት ወቅት ተስተዉሏል፡፡ባለፈው በሚሊኒየም በተከበረበትም ወቅትም ይሁን ከዚያ በኃላ ኢትዮጵያን ለሚነቡኙ ቱሪስቶች ‹ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት› ናት የሚለውን ተረት እውነት ለማስመሰልና በየሄዱበት እንዲያስተጋቡ ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ አንስቶ በከተማው አውራ ስፍዎች ላይ ክርስቲያናዊ ገጽታ ያላቸውን ቢልቦርድ በመለጠፍ፤ የታክሲ ሾፌሮችንና ወያሎችን በየአብያተክርስቲኑ በመጋበዝ ለነርሱ ልዩ ቅስቀሳ በማድረግ በየተክሲ ዉስጥ መዝሙር እንዲከፍቱ በማድረግ ለተመልካች ‹ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት› የሚል መልዕክት እያስተላለፉ ይገኛሉ፡፡

የአሁኑ ቆጠራም እንደከዚህ በፊቱ ሙስሊሙን ሆን ተብሎ የማሳነስ ሴራ ከተስተዋለበት የሙስሊሙ መሪ ድርጅት ነው የሚባለው መጅሊስ አንደ ከዚህ ቀደሙ መጅሊስ ፈጽሞ መቀበል የለበትም፡፡ አለመቀበሉንም በይፋ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ለአብነት ያህል የቀድሞው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት መሪ የነበሩት ሼህ አብዱራህማን ሁሴን መንግስት በ1987 ያወጣዉን ‹የህዝብ ቆጠራ ዉጤት› ፈጽሞ አልተቀበሉም ነበር፡፡ ሙስሊሙ ከሀምሳ በመቶ በላይ መሆኑን ያምኑ ነበር፡፡ የሙስሊሙ ቁጥር ነው ተብሎ የሚነገረው ሆን ተብሎ የተሴረ እንጂ ትክክል እንዳልሆነ ያምኑ ነበር፡፡ በፌብረዋሪ 3/2002 በ‹ኢስላሚክ ፖፑሌሽን ዶት ኮም› ድህረ ገጽ ላይ እንደተገለጸው ‹‹ከኢትዮጵያ ህዝብ ዉስጥ ሙስሊሙ 52 በመቶ ነው›› ሲሉ ገልጸው ነበር፡ (http://www.islamicpopulation.com/)
ከኡሁኑ መጅሊስም የሚጠበቅ አለመቀበል፡፡ሙሁራኖቻችንም ሊያስቡበት ይገባል፡፡ ግፍን በዝምታ መመልከት አይገባም፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብም ትክክለኛ ቁጥሩ እስኪገለጽ ድረስ ፈጽሞ መቀበል የለበትም፡፡ ለዚህም ድፍረቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ማሳሰቢያ፡- ይህንን ጽሑፍ ለሚያውቁት ሁሉ ያድርሱ! ኮፒ አድርገው ያባዙ! ስጦታ ይስጡ! በኢሜል ያሰራጩ! ላልሰሙት ያሰሙት! ያድርሱ! አደራ!!

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ታዛቢዎች
1 ሀመዱ ኤል ሀሩን
ስ.ኢሜይል.ኢወጣ.አቶ ቻላቸው
AMI 25/12/05

2) ሚካኤል መኮንን
ከአዲሳ አለማ አነጋገርኩ
25/12/04

15

25/12/04

5

http://ethcriminalawnetwork.com/

በዓለም ላይ እንደታየ[illegible]ሙስሊሙ ቁጥር በ25 ዓመቱ እጥፍ ሲሆን የሌሎች ህዝቦች ቁጥር እጥፍ የሚሆነው በየ56 ዓመቱ ነው፡፡ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችም ቁጥር አጅግ በዝቶ ክርስቲያኖች ሳያስደነግጣቸው አልቀረም፡፡ ለዚህ ሊሆን ይችላል ሰሞኑን ‹‹ሙስሊሞች ብዙ ያገባሉ፤ ብዙ ይወልዳሉ፤እኛ ቶሎ አናገባም፤ብናገባም አብዛኛው ትዳር ይፈርሳል የነርሱ ግን...›› ወዘተ አይነት ቅስቀሳዎች በአዲስ አበባ አብያተክርስቲናት እየተደረጉ መሆኑን መስማታችን ምን ሴራ ይኖር ይሆን? ብለን እንድንጠይቅ ግድ ይሉናል፡፡ ጥርጣሬያችንን ይበልጥ የሚያጠናክረው ደግሞ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ም/ሊቀመንበር ‹ሼህ› ኤሊያስ ሬድማን ከ9 ባልደረቦቻቸው ጋር ወደ ኢንዶኖዥያ ለአስር ቀናት መጓዛቸውን በኢትዮጵያ ራዲዮ መስማታችን ነው፡፡ በጥቅምት 2001 አጋማሽ ወደ ኢንዶኖዥያ የተጓዙት ሀገሪቱ የህዝብ ቁጥርን በስነ ተዋህዶ ዘዴ በመቀነስ ልምድ ስላላት ነው ተብሏል፡፡ ሼህ ኤልያስን እንደቤተክርስቲያን ሁሉ የሙስሊሙ ቁጥር መብዛት ለምን አሳሰባቸው? ማንስ ላካቸው? ኢናሊላሂ ወኢና ኢለይሂራጂዑን!! አምና አል-ቁድስ ጋዜጣ ‹‹ኢትዮጵያ ያላደገችበት ዋነው ምክንያት ገዥዎቿ የሙስሊሙን እንቅስቃሴ ከመከታተልና ለመቆጣጠር በቀር ስለ ልማት የሚያስቡበት በቂ ጊዜ ስለሌላቸው ነው፡፡›› ስትል ጽፋ ነበር፡፡ ሙስሊሙን ለመጫን መሞከር ለምን? ቁጥሩን ለመቆጣጠር መጣጣር ለምን?

አንዳንድ የዋህ ሙስሊሞች የቁጥራችን መብዛት ወይ ማነስ ምንም ፋይዳ የለውም ብለው ማሰባቸው ስህተት የሚሆነውም የዚህን ዘመቻ ስውር ዓላማ ስንረዳ ነው፡፡ ‹‹ቁጥራችን ቢበዛ ባይበዛ ምን ዋጋ አለው? ዋናው ጥራት ነው፡፡››ይላሉ፡፡ በእርግጥ ጥራት ወሳኝ ነው፡፡ ሆኖም ብዛታችን ለምን ይቀነሳል? ስለ ብዛት ስናወራ ስለ ጥራት ለምን ጣልቃ እናስገባለን? በብዛታችን ልክ መብታችንን ሳይሸራረፍ ስናስከብር ነው ጥራትን ማስገኘት የምንችለው፡፡ ስለ ብዛት ስናወራ እባካችሁ ስለጥራት በማውራት ባታዘናጉን ? ‹‹ቁጥራችሁ ትንሽ ነው፡፡ አናሳ ናችሁ፡፡›› ሲሉን ‹‹ከዚህ በላይ መስጂድም ሆነ መድረሳ አያስፈልጋችሁም፡፡ እንዲያውም የስከዛሬው ከቁጥራችሁ በላይ ነው፤ የተወሰነውን መልሱ፡፡ ከእንግዲህ ምንም መብት አትጠይቁ፡፡›› እያሉን መሆኑን እነዴት ይዘነጋናል?

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የሕዝብ ቆጠራ አለመካሄዱን ጠቅሰናል፡፡ የአፄውን ዘመነ መንግስት የተመለከተ የታሪክ መጽሐፍ ያዘጋጁት አንድ ምሁር በአፄው ዘመን የሕዝብ ቆጠራ ያልተካሄደበት አንዱ ምክንያት የክርስትያን ደሴት በምትባል አገር ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሙስሊሞች እንደሚኖሩ ይፋ እንዳይወጣ ከመሻት የመነጨ እንደሆነ ጽፏል፡፡
‹‹ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት›› የሚለውን ቅዠት ለማስጠበቅ ቤተክርስቲያን የማትፈነቅለው ድንጋይ የለም፡፡የዚህ ዉጤቱም ‹‹የዚህች አገር ተወላዮች እኛ ነን፤ሙስሊሙ አርፎ ይቀመጥ አናሳ ነውና!›› የሚለውን እሳቤ ለመፍጠር ነው፡፡ የዉጭ ጸረ-ኢስላምና ሙስሊም ሃይላትም እርሷን ከመተባበር አይቦዝኑም፡፡ አንዳንዴ ‹‹በዙ ለምን ዝምብላችሁ ታያላችሁ?›› ይላሉ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ‹‹ትንሽ ናቸው አይዟችሁ!›› ይሏቸዋል፡፡ የመንግስት ባለስልጣናትም ከዉጭ እንግዳ ሲቀበሉ ስለ ሙስሊሙ ቁጥር የሚናገሩት እንደ እንግዳው አይነት ይለያያል፡፡ለሙስሊም ሀገር እንግዳ ከሆነ ቁጥሩ ከፍ ያለው ነው፡፡ በተቃራኒው ከክርስቲያን ሀገርና ከሌላ ሲሆን ደግሞ ሙስሊሙን ቁጥር ከፍ አድርገው ይናገራሉ፡፡ልብ ብላችሁ ከታዘባችሁ መንግስቲ የሙስሊሙ ድጋፍ በሚሸበትና ችግር ባለበት ወቅት ሚዲያው ስለሙስሊሞች ጥሩ ጥሩንና የሙስሊሙን ቁጥር ግማሽ የሀገሪቱ ህዝብ እንደሆነ ይናገራል፡፡

አንዳንዶች ‹‹የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ድርጅት መሪዋ ሙስሊም አይደሉምን? እንዴት የሙስሊሙ ቁጥር ሲቀነስ ዝም ይላሉ?››ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ በእርግጥ ግለሰብዋ ሙስሊም ናቸው፡፡ ነገር ግን ‹የኅበና ፖሊሲ› ቢሆንስ? ‹የኅበና ፖሊሲ› ያልነው የአጼ ምኒሊክ የጦር መሪ የነበረው ኅበና ይባላል፡፡ ኦሮሞ ነው፡፡ ኦሮሞ መሆኑ ግን በሚኒልክ ተልኮ የአርሲ ኦሮሞዎችን ከመጨፍጨፍ አላገደዉም፡፡ ‹መሪው ኦሮሞ አይደለምን?› መባሉ ተጨባጩን አይለዉጥም፡፡ ለዚህም ነው የእስታስቲኩም ዉጤት የኅበና ፖሊሲ ከመሆን የማይዘለው፡፡
ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያ ‹ክርስቲያን ደሴት ናት› የሚለውን ቅዠት ለዉጭው ህብረተሰብ ለማሳየት በየሚዲያውና በየመድረኩ ቀሳዉስቱን በማሳታፍ መታየትን ሲፈ[illegible]ለው ጉዳይ ይዘዋል፡፡ይህ እርቃናዊነቷን ታዋቂ ዘፋኝ ቢዮንሴን ለመቀበል በሄደችበት ሸርጉዴና አንዲሁም ጳጳስ ሁኗ

ከዋናው ጋር ተመሳክሮ ትክክለኛ ቅጂ መሆኑ ተረጋገጠ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

፡ የፕሮፓጋንዳው ከወ መጣጣፍ ዓይነተኛ ዓላማም ይፋ ሊደረ ለመውን የተዛባ ቁጥር ከወዲሁ ጆሯችን እንዲለምደው ለማድረግ ከመሆን አይዘልም፡፡

ቤተክህነት አምና በተደረገው ህዝብና ቤት ቆጠራ ላይ ተጽኖ ለማሳደር መንቀሳቀሷ ይታወቃል፡፡ የማኅበረ ቅዱሳን ልሳን የሆነው ‹ስምዐ ጽድቅ› ጋዜጣ ክርስቲያኑ ሁሉ በቆጠራው ላይ ይረባረቡ ዘንድ ቀስቀሶ ነበር፡፡ይህ ብቻም ሳይሆን የሙስሊሙን ቁጥር በመቆጣጠር እንቅስቃሴ ላይ የረጅም ጊዜ ልምድ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ በሰኔ 18/2007 ላይ ‹www.Ethiopianmuslims.net› የተሰኘው ድህረ ገጽ እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር፡- ‹‹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አቡን በሚደረገው ቆጠራ ቀድመው መንግስት የሙስሊሙን ቁጥር በጥንቃቄ እንዲከታተል አስጠንቅቀው ነበር፡፡›› (Fact or Fiction book? Monday, 18, June 2007)

የቁጥር ሽሚያ(የህዝብ ብዛት አኃዝ በመቶኛ) ለፖለቲካ መሳሪነት እየዋለ ይገኛል፡፡ ሙስሊሙን በተጨባጭ ከመግፋት፥ መብቱን ከማስጣስ፡ እኩልነቱን በገሃድ ከማስተባበል በመቶኛ አኃዝ ላይ ተጽኖ በማሳደር መብቱን ሊሸራርፉ ይተጋሉ-የቤተክህነት ሰዎች፡፡ የሙስሊሙ አኃዝ አነሰ ማለት በተጨባጭ የሙስሊሙን ቁጥር ባያሳንሰውም በርካታ መብቶቹን ግን እንዳያገኝ ያደርጉታል፡፡ ይህ ማለት የመብት ጉዳይ ላይ መጠየቅ የሚችለው ሙስሊሙ ተቀምሮ በተለገሰው አኃዝ ልክ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ‹አናሳ ነችሁ አርፋችሁ ተቀመጡ፡፡ቁጥራችሁ አነሳ ሆኖ ለምን ይህ ሁሉ መስጂድ? ለምን ይህን ያህል... ወዘተ› ይባላል፡፡‹ይብቃቸው፡፡ይቀነስ› ወዘተ ሲባል ይዘለቃል ማለት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሙስሊሙን በጉልበቷ ሥር ለማንበርከክ በፖለቲካውና ሴራዎችን ከማቀናበር ሌላ በዋንኛነት የተያየዘችው ሙስሊሙን ክፉኛ ሊጎዳው የሚችለውን የህዝብና ቤት ቆጠራ ዉጤት ላይ ተጽኖ ማሳደርና ዉጤቱን ማዛባትን ነው፡፡ በመስክ ቆጠራ ላይ የተሰማሩት የማህበረ ቅዱሳን አባላት መምህራን ምን እንደ ሰሩ ምን ይታወቃል? የመስክ ቆጠራ ከተዛባ እንዴት ትክክለኛ የሙስሊሙ አኃዝ ይነገራል ተብሎ ይጠበቃል? የሚገርመው በቆጠራው ወቅት የክርስቲያን ድርጅች ከላይ እስከ ታች ሲረባረቡ ከሙስሊሙ ወገን ሙስሊሙ እንዲቆጠር እንኳ የሙስሊሙ ‹መሪ ድርጅት› መጅሊስ አንዳች አለመባሉ አሳዘኝ ነገር ነው፡፡

አሁን የኢትዮጵያ ህዝብ 80ሚሊዮን እንደ ደረሰ ይገመታል፡፡ ቆጠራው ሳያልቅ ‹‹አፈሪካን ፕሬስ›› የተሰኘው የዜና አገልግሎት በማርች 21/2008 በሞሊድ ዜና ላይ ‹‹ኢትዮጵያውን ሙስሊሞች ከተገመተው 80 ሚሊዮን ህዝብ ዉስጥ 40% ናቸው›› ሲል ገልጸ ነበር፡፡( www.africanpress.worldpress.com) እንዚህ ሁሉ በእርግጠኝነት የሚነግሩን በሙስሊሙ ቁጥር ጉዳይ ላይ የተሸረበ ሴራ እንዳለ ነው፡፡

የህዝብና ቤቶች ቆጠራ በትክክ ቢካሄዱና ዉጤቱም ሳይዛባ መገለጹ ለአንድ ሀገር ያለው ጠቀሜታ ቀላል አይደለም፡፡ በፖለቲካ ብልጣ ብልጥነት ዉጤቱን በማዛባት ሳይበልጡ መብለጥ የሀገር እድገት ቁልቁል ይነዳዋል፡፡ ዉጤቱ ሳይገለጽ እስከ አሁን መቆየቱ በራሱ አጠያያቂ ነገር ነው፡፡ በድሮች እንዲህ ብለው ነበር አሉ፡-‹‹አንዲት ሀገር በተለያዩ የኑሮ ዘርፎች እድገትንና መሻሻልን ታመጣ ዘንድ በመንግስትና በዜጎች መካከል መተማመን መኖር ወሳኝ ነው፡፡ የህዝቦችን ቁጥር በተመለከተ ህዝቦች በመንግስት ላይ ያላቸው አለመተማመን እንዲቀጥል መደረግ የለበትም፡፡ ››(የበድር ዓለም አቀፍ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረቡት ጥያቄዎች፤ ገጽ 14፤ www.ethiopianmuslims.net በተሰኘው ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል፡፡)

ዋነኛው የዚህ ሴራ ዓላማ ግን ከዚህም ያለፈና አደገኛ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላይ በማነጣጠር ተጸእኖ ከበቁት መጻሕፍት ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት መቻቻል አለ?›› በሚል ርዕስ የተጻፈው የሸህ ሳሙኤል መፅሐፍ የአዲስ አበባን ሕዝበ-ሙስሊም ቁጥር ከመስጂዶች ብዛት አንጻር ያሰላና በከተማይቱ የሚኖረው ሕዝበ-ሙስሊም ሊኖረው ከሚገባው የላቀ ወይም የበዛ መስጂድ እንዳለው ሊጠቁመን ሞክሯል፡፡ የዚህ ሁሉ ‹ሐተታ ዘጉልቆ› ማሠሪያውም ይህ ነው፡፡ ቁጥራችን ላይ ማለም፤ ከዚያም መብታችን ላይ መተኮስ!! እንግዲህ የዘንጋ ሰንጋው ርዕስ ልብ በሉ - ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት መቻቻል አለ?›› ሲል ይጠይቃል እንጂ እንዲህ እያለመ፣ እንዲህ እየተከሰ፣ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ለሚጠይቅ ምን ተብሎ ይመለሳል?

ETHCRIMINALAWNETWORK

http://ethcriminalawnetwork.com/

ብሶት ሊቀይረው አልቻለም፡፡ በተቃራኒው በመጨረሻው የህዝብና ቤቶች ቆጠራም መሰረት የሙስሊሙ ቁጥር ከጠቅላላው የሀገሪቱ ህዝብ ብዛት አንድ ሦስተኛ እንኳን እንዳልሆነ እንገነዘባለን፡፡ ይህ አሃዝ ከዚህ በፊት እውቅና ከነበረውና የሙስሊሙ ቁጥር ወደ 45% ከሚገመተው አሀዝ በእጅጉ አንሶ እናገኘዋለን፡፡ የዚህን ክስተት ትንታኔ ጉዳይ ለባለሞያዎች ተወት አድርገን ቁጥሩ እንዲያንስ ተደርጓል፡፡ በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያውያን ልጆች አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍሰው እዉን ባደረጉት የዲሞክራሲ ስርዓት ዉስጥ አግባብ ያለው ዉክልና እንዳይኖረኝ፤ በሀገሬ ጉዳይም ላይ ተገቢዉን ቦታ እንዳልይዝ ተደርጌያለሁ የሚለው የሙስሊሙ የብሶት ጥያቄ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ስር እየሰደደ ይገኛል፡፡ በመንግስት እዉቅና ያለው የሙስሊሞች አሃዝ በአለም አቀፍ ደረጃ ዉድቅ ተደርጓል፡፡መንግስታዊ ያልሆኑ አለም አቀፍ ድርጅቶች የሰበሰቡትን መረጃ ድጋፍ በማድረግ ባሰሉት ስሌት መሰረት ሙስሊሙ ከ45-50% እንደሚሆን በመገመት በሀገሪቱ ዉስጥ የበላጭነቱን ደረጃ ይሰጡታል፡፡ ይህም ሁኔታ መንግስት ይፋ ባደረገው አሃዝ ላይ ሙስሊሙ ያለዉን ጥርጣሬ አጠናክሯል፡፡››(የበድር ዓለም አቀፍ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረቡት ጥያቄዎች፤ ገጽ 13-14፤ www.ethiopianmuslims.net በተሰኘው ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል፡፡)

የዚህ ቀደሙ ቆጠራ ብዙ ተብሎለታል፡፡የሙስሊሞችና በኦሮሞዎች ተቀባይነት አልነበረውም፡፡ ምክንያቱም ትክክለኛ ዉጤትን ስለማያሳይ!

ይህ በእንዲህ እያለ ነው እንግዲህ በአገሪቱ ታሪክ ለሦስተኛ ጊዜ የተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት በመንግስት ይፋ ከመደረጉ በፊት በሙስሊሙ ቁጥር ዙርያ ቤተ-ክህነት ተከታታይና የተቀናጀ የማሳነስ ዘመቻ የከፈተችው፡፡ ቤተ ክህነት በዚህ ወቅት ትኩረቷን በሕዝብ ቁጥር፣ በተለይም በሙስሊሙ ሕዝብ ቁጥር ላይ ማድረጓ ለምን ይሆን? አገር አቀፍ የቤቶችና የሕዝብ ቆጠራ ተካሂዶ ውጤቱ ይፋ ከመደረጉ አስቀድሞ የሙስሊሙን ሕዝብ ቁጥር አስልታ ለሕዝብ ለመንገርስ ምን አነሳሳት? እውን በጋዜጠኛ ወይም በምዕመናን ተወካይ አልያም በአንድ ተራ ግለሰብ በግምት የተነገሩ አኃዞች የተሳሳቱ በመሆናቸው ይህንን የማረም አገራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት በመሻት ነውን?

ቤተ ክህነትን ያህል ትልቅ ተቋም የሕዝበ ሙስሊሙን ቁጥር በተመለከተ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መጠነ ሰፊ ዘመቻ የከፈተችው ጥቂት ግለሰቦች በተለያዩ አጋጣሚዎች የተናገሯቸውን የአኃዝ ስህተቶች ለማረም በመሻት ነው ብሎ ለማሰብ እጅግ የዋህ አልያም ጅል መሆን ያስፈልጋል፡፡ በጉዳዩ ዙርያ የተፃፉትን መጻሕፍት ይዘት በጥሞና ያነበበና ዘመቻው የተከፈተበትን ወቅት በውል ያስተዋለ ከዚህ ዘመቻ ጀርባ ምን እንዳለ ለመገመት አያዳግተውም፡፡

አገር አቀፍ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ተካሂዶ የውጤቱ በይፋ መገለፅ እየተጠበቀ ባለበት ወቅት ይህ ዘመቻ በተቀናጀ መልኩ በሰፊው መፋፋሙ፣ ቤተ ክህነት ይፋ በሚደረገው የቆጠራው ውጤት ላይ በሆነ መልኩ ተጽዕኖ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰች እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ይህ ደግሞ ከዚህ ቀደም ተካሂደው ለአገር ውስጥ ፍጆታ ይፋ በተደረጉት አኃዞችና ዓለም አቀፍ የመረጃ ምንጮች በሚያወጧቸው አኃዞች መካከል ሰፊ ልዩነት ከኖረው መጣረስ ጀርባ ቤተ-ክህነት ሚና ነበራት ማለት ነውን? ለሚል ጥርጣሬም ይዳርጋል፡፡

ለምሳሌ የሲ.አይ.ኤ. ዓመታዊ መረጃዎች እስከ ሰኔ 13/2007 ድረስ የሙስሊሞችን ብዛት ከ45-50% ሲል ይገልጽ ነበር፡፡ ነገር ግን በሰኔ 14/2007 የሙስሊሞችን ቁጥር ከመቶ 32% አድርጎ ቁጭ አለ፡፡ ቆጠራ ተደርጎ ሳያልቅ የሙስሊሙን ቁጥር ከ45-50% ወደ 32% ማውረዱ ለምን? የሙስሊሞች ቁጥር ይህ እንዲሆን ተሲሮ ይሆን ? ወይንስ ለቤተ ክህነት ጫና ተንበርክኮው? ወይንስ በዚሁ ቀናት ውስጥ ከ13-18 % የሚሆኑት ሙስሊሞች በአንድ ቀን በወረርሽኝ አልያም በጅምላ ጨራሽ መሳሪያ አልቀው ይሆን ?

በሌላም መልኩ አገር አቀፍ ቆጠራ ተካሂዶ የውጤቱ በይፋ መገለፅ እየተጠበቀ ባለበት ወቅት በቤተ ክህነት አካባቢ ያሉ አካላት የጉዳዩ ባለቤት ክህነው መንግሥታዊ አካል ቀድመው የሕዝበ ሙስሊሙን ቁጥር በማሳነስ ይፋ ለማድረግ ሙከራቸው በራሱ ይፋ ስለሚደረገው (እንደተለመደው የተዛባ) የቆጠራ ውጤት የሚያውቁትና የተሳተፉበትም ነገር እንዳለ ያመላክታል፡

ያዘጋጁት ታዛቢዎች ፡ ሀጋሙኤል፡ አሸናፊ
አክሊሉ ፡ ኢሜል ፡ ሲወጣ ፡ እዩቻለሁ
ፊርማ 25/12/04
አክሊሉ ሲወጣ እያጣራሁ
ፊርማ 25/12/04
በዐዲስ አበባ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ሃጎሚል ታደሰ
25/12/04

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

Attachment 1 Monday NOV 24. 2008 4:33 AM

# ሴራ በሙስሊሙ ቁጥር ላይ

በኢትዮጵያ ታሪክ የሕዝብ ቆጠራ ለመጀመርያ ጊዜ የተካሄደው በዘመነ ደርግ ነው፡፡ በረኻው የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ዘውዳዊ ሥርዓት አንድም ጊዜ ሀገር አቀፍ የሕዝብ ቆጠራ ተካሂዶ አያውቅም፡፡ በዘመነ ደርግ ለመጀመርያ ጊዜ የተካሄደው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራም ቢሆን በምልዐት አልተከናወነም፡፡ በጊዜው የጦርነት ቀጣና በነበሩት የኤርትራና የትግራይ ገጠራማ አካባቢዎች፣ እንዲሁም በቀድሞው ባሌ ክ/ሀገር ደቡባዊ ክፍል እና በሐረርጌ ቆላማ አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ በአኗኗሩ አርብቶአደር በመሆኑ ምክንያት በቆጠራው ውስጥ ሳይካተት ቁጥሩ በግምት እንደተወሰደ የጽሑፍ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ፕሮፌሰር አልቤርቶ ስባኪ ‹ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ፋሽሽት የወረራ ዓመታት› በሚለው መጽሐፋቸው በገጽ 180 ላይ በጣልያን ወረራ ወቅት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከሀገሪቱ ህዝቦች ዉስጥ ግማሽ እንደነበሩ ጽፈዋል፡፡የደርጉ የመጀመሪያ ሊቀመንበር ሚካኤል አማን አንዶም ለዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ከሀገሪቱ ህዝብ ዉስጥ 55 በመቶ መሆናቸውን ገልጸ ነበር፡፡(አዲስ ዘመን ጋዜጣ መስከረም 6/1967)

በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን (CSA) መሥሪያ ቤት በወቅቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ የተደረገው የአገሪቱ ሕዝብ ቁጥር 42 ሚሊዮን ነበር፡፡ የውጭ መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጥር ጠቅመለከተም ሆነ ተያያዥ ለሆኑ የዴሞግራፊ መረጃዎች በዋነኛ ምንጭነት የሚጠቅሱት ይህንኑ መስሪያ ቤት ነበር፡፡ ይኸው ባለስልጣን መሥሪያ ቤት በዋቢነት በሚጠቀስባቸው የውጭ አገር ሰነዶች ላይ የ1987 የቤቶችና የሕዝብ ቆጠራ ውጤትን መነሻ ባደረገ የሕዝብ ቁጥር እድገት ግምት (Projection) መሠረት ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1999 የአገሪቱ ሕዝብ ቁጥር 59.7 ሚሊዮን ገደማ እንደነበር በወቅቱ የታተሙ ስመ ጥር ዓለም አቀፍ ዓመታዊ መፅሔቶች ይነግሩናል፡፡ እነዚሁ ዓመታዊ መፅሔቶች ታዲያ ሌላም የሚነግሩን አኃዛዊ መረጃ አለ - በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች ቁጥር፡፡

በዚህ ረገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ ተቀባይነት ባላቸው ዓመታዊ መፅሔቶች ላይ ስናይ የኖርነው በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች ቁጥር ከቶውንም ለአገር ውስጥ ፍጆታ በመንግስት ይፋ ከሚደረገው የማይባጥም ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ እ.ኤ.አ. በ1999 መባቢያ ላይ የታተመው የኒው ዮርክ ታይምስ አልማናክ (The New York Times Almanac — Millennium Edition) እ.ኤ.አ. በ1999 የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 59,680,383 እንደሆነ ይገልፃል፡፡ የሃይማኖት ስብጥርና የተከታዮችን ብዛት በተመለከተ ከ45-50% ሙስሊም፣ ከ35-40% የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፣ የሌሎች ሃይማኖቶችና የባህላዊ እምነት ተከታዮች ደግሞ 12% መሆናቸውን አስፍሯል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2001 ታትሞ የወጣው The World Almanac እና የዚያው ዓመት የCIA Fact Book ከዚህም ትንሽ ከፍ ያለ አኃዝ ያስነብቡናል፡፡ በዚያን ጊዜው የሕዝብ ቁጥር ላይ ተመሥርተን እንኳ ብናሰላ የሙስሊሙ ሕዝብ ቁጥር ከ26.8 ሚሊዮን እስከ 29.8 ሚሊዮን የሚደርስ እንደነበር እንረዳለን፡፡ ይህ አኃዝ የዛሬ አሥር ዓመት ገደማ የነበረውን የአገሪቱ የሕዝብ ቁጥር መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ዛሬ ከአሥር ዓመት በኋላ አጠቃላይ የአገሪቱ ሕዝብ ቁጥር ወደ 80 ሚሊዮን አካባቢ እንደተጠጋ እየተነገረ ነው፡፡ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ የአገሪቱ ሕዝብ ቁጥር በ20 ሚሊዮን ገደማ ጨምሯል፡፡ በዚህ መሠረት የሙስሊሙ ሕዝብ ቁጥር ከ36 ሚሊዮን እስከ አርባ ሚሊዮን እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ ዋሽንግተን ፖስት እንዲህ ይላል፡- ‹‹አርቶዶክስ ክርስትና ከብሔራዊ መገለጫ ጋር በሚያያዝበት ኢትዮጵያ፣ የሰፋ ህዝብ ጥናት ባለሞያዎች ኢትዮጵያውያንና የአሜሪካ ባለስልጣናት እንደሚሉት የሙስሊሙ ቁጥር ወደ ግማሽ የቀረበ ነው፡፡ ››( Washington Post,Sunday, May 13, 2007)

በድር ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ድርጅት ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አንዲህ ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡-

‹‹ግዥዎች ኢትዮጵያ ‹የኢትዮጵያውያን ደሴት› ገጽታን እንዳትላበስ ለማድረግ ከወሰዱት በተለይም የሙስሊሙን ህልውና ለመካድ ከተጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ ቁጥራቸውን አሳንሶ ማቅረብ የሚለው አንዱ ነበር፡፡ አሁን ባለው መንግስት እውቅና ያለው የሙስሊሙ ቁጥርም ይህን

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

# በሥራ ላይ እያሉ ጉዳት የደረሰባቸው አውቶቡሶች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | የሾፌር ስም | ጉዳት የደረሰበት አውቶቡስ የሌዳ ቁጥር | ጉዳት የደረሰበት አውቶቡስ የጦን ቁጥር | የጉዳቱ ዓይነት | አደጋው የደረሰበት ቦታ | የጉዳቱ ግምት /በብር/ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ደረጀ ጉልማ | 3.75189 | 7184 | የፊት መስታወት መሰንጠቅ | መርካቶ ቀጠና | 21,640.00 |
| 2 | ካሣ ደግፌ | 3.73962 | 7216 | 1 አነስተኛ የጦን መስታወት መሰበር | መርካቶ ቀጠና | 1,755.00 |
| 3 | ያዕቆብ መሐመድ | 3.00534 | 6293 | የኋላ መስታወትና 1 የጦን ተንሸራታች መስታወት መሰበር | አውቶቡስ ተራ | 3,021.02 |
| 4 | ሚፍታ አብደላ | 3.76592 | 7238 | የግንባር መስታወት መሰበር | መርካቶ ቀጠና | 24,120.00 |
| 5 | አደም ተሰፋዬ | 3.19067 | 6419 | 2 የፊት መስታወት መሰበር፣ የፊት ኮርነር መስታወት መሰበር፣ 3የቀኝ ተንሸራታች መስታወት መሰበር፣ የፊት የግራ ፍሬቻ መሰበር | መርካቶ ቀጠና | 11408.01 |
| | | | | ጠቅላላ ድምር | | 61,944.03 |

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

561

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አንበሳ የከተማ አውቶቡስ
አገልግሎት ድርጅት

Anbessa City Bus
Service Enterprise

ቁጥር No. አስአአድ/ምዋሥ/105/04

ቀን Date 20 ሐምሌ 2004

**በፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ**
**ለታክቲክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክትሬት**
**አዲስ አበባ**

ጉዳዩ፡- ማረጋገጫ ስለማቅረብ፡

ሐምሌ 14 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 9:00 ሰዓት ሲሆን አገልግሎት በመስጠት ላይ ከነበሩት የአንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት አውቶቡሶች መካከል በመርካቶ አካባቢ በተፈጠረው ሁከትና ብጥብጥ የደረሰውን የጉዳት መጠን እንድንገልፅ በቁጥር 9516/04 ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ መጠየቃችን ይታወሳል፡፡

ስለሆነም በመርካቶ አካባቢና በአውቶቡስ ተራ በሥራ ላይ የነበሩ አውቶቡሶች ላይ ድንጋይ በመወርወር 4 አውቶቡሶች መስታወታቸው የተሰበረ ስለሆነ የግምት መጠኑ ብር 61,944.03 /ስድሳ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ አርባ አራት ብር ከዜሮ ሶስት ሣንቲም/ በመሆኑ በድርጅታችን ላይ የደረሰውን የንብረት ኪሳራ ከግምት ውስጥ በማስገባት አጠፊዎቹ ለሕግ እንዲቀርቡና እንዲጠየቁ ተደርጐ የደረሰብን የንብረት ኪሣራ እንዲተካ እንዲደረግልን እየጠየቀን የደረሰውን ጉዳት መጠን 1 ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አብርሃም ፋንታው
ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ

ግልባጭ
• ለዋና ሥራ አስኪያጅ
አስአአድ

☎ 29 33 79 ስልክ 29 33 96
✉ 472 Fax
ቴሌክስ
Telex Cable ACBSE
21689
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa; ETHIOPIA

862

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድር ህንፃ ነጋዴዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
# DIR BULIDING MERCHANTS PRIVATE LTD. COM

ቁጥር ድሕ/አክ47ፖ/00364/04
Re .No _____
ቀን 17/11/2004
Date _____

ክቡር አቶ ከፍኪ አብጋ
ለ4ኛ ፖሊስ ጣቢያ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በሕንፃ ላይ ስለደረሰ የንብረት ጉዳት፣

ሐምሌ 14 ቀን 2004ዓ/ም በመርካቶ አካባቢ በተፈፀመው ሕገወጥ ተግባር ሳቢያ በመንግስትና በግል ድርጅቶች ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱ ይታወቃል።

ስለዚህ የንብረት ጉዳት ከደረሰባቸው አንዱ የአክሲዮን ማህበራችን ሕንፃ ስለሆነ ግምቱ ብር 27,347.90 /ሃያ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ አርባ ሰባት ብር ከዘጠና ሳንቲም/ የንብረት ጉዳት የደረሰ መሆኑን እንገልፃለን።

ድር ሕንፃ ነጋዴዎች ኃ.የተ.የግ.ማ. ☎76 36 34 Der Building Merchants

ሰላምታ ጋር

አበበ ከበርኩ
ሥራ አስኪያጅ

ዙህ ሠሪዱ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

☎0112/76 63/22

8555

563

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አዲስ አበባ _____ ቀን _____

ፕሮቶኮል ቁጥር 03-5753

የፖሊስ ሠራዊት ሆስፒታል

Police force Hospital

Addis Ababa

# የምስክር ወረቀት

CERTIFCATE

ስም ከነአባት ኮን/ል አንበሴ ሞርካ

Name and father's Name _____

የበሽታው ዓይነት ወይም የደረሰበት ተደበደብኩን በለው መጥተው በቀን 07/11/04 ዓ/ም በድንገተኛ ክፍል የታከሙ ሲሆን በምርመራ ላይ በጎለኛው የጭንቅላት ቆዳቸው ላይ 0.3 ሳ/ሜ የሚሆን ቁስል ፣ አብጠት እና መካከለኛ የደም መፍሰስ የነበራቸው ሲሆን አስፈላጊውን ህክምና አግኝተው በአሁኑ ሰዓት በደህና ሁኔታ ላይ መሆናቸውን በዚህ የህክምና ማስረጃ እናረጋግጣለን::

በመኝታ የታከሙበት ከ _____ እስከ _____

Admited as In-patient Frome _____ Till _____

በተመላላሽ የታከሙበት ከ 07/11/04 እስከ 07/11/04

Treated as out-patient from' _____ Till _____

የተሰጠዉ ዕረፍት ከ _____

Rest Required _____

Healing time _____

ተርጓሚ አረፍት

Translator

የሆስፒታሉ ዲሬክተር

Hospital Director

ሐኪሙ

The Doctor

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

Dr. YILMA BOGALE
INTERNIST

564

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌዴራል ፖሊስ ፌዴራል ሆስፒታል
Federal Police Referral Hospital

ቁጥር 282/ጠ50/59
ቀን 12/11/04

በአዲስ አተማ ክ/ከ/ፖሊስ መምሪያ
ለመርካቶ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ
አዲስ አበባ፤

ስለ ኮን/ል አንበሴ ሞርካ የህክምና ማስረጃ ሠርተፊኬት እንዲላክላችሁ በቁጥር 04/234/04 10/11/2004 ዓ/ም የፃፋችሁልንን ደብዳቤ ይመለከታል።

በመሆኑም በስም የተጠቀሰ·ትን አባል ጉዳት የሚገልፅ 1 ገጽ የሃኪም ማስረጃ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

/ ከሀሰላምታ ጋር /

ዶ/ር ይልማ ቦጋለ
የውስጥ ደዌ በሽታዎች
Dr. YILMA BOGALE
INTERNIST

ግልባጭ
❖ ለፌዴ/ፖ/ሪፈ/ሆ/ል ሚ/ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ፖሊስ/ል

Tel 0115-518470
ፖ/ኦ/ር ሳጥ ቁ
Fax 157954
P.O. Box 21652

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አዲስ አበባ _____ ቀን _____

ፕሮቶኮል ቁጥር 206882

የፖሊስ ሠራዊት ሆስፒታል

Police force Hospital

Addis Ababa

የምስክር ወረቀት

CERTIFCATE

ስም ከነአባት ኮን/ል በየነ ሀይሉ

Name and father's Name _____

የበሽታው ዓይነት ወይም የደረሰበት ተደበደብኩኝ ብለው መጥተው በቀን 09/11/04 ዓ/ም በድንገተኛ ክፍል የታከሙ ሲሆን በምርመራ ላይ 0.1 ሳ/ሜ የሚሆን ቁስል በቀኝ የጐን የአይን ሽፋን ላይ ቁስል /ጭረት /የነበራቸው ሲሆን የደም መፍሰስ በወቅቱ አልነበረውም በአይን ሀኪም ታይተው አስፈላጊውን ህክምና አግኝተው በአይናቸው ላይ ችግር እንደሌላቸው የታወቀ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በደህና ሁኔታ ላይ መሆናቸውን በዚህ የህክምና ማስረጀ እናረጋግጣለን::

በመኝታ የታከሙበት ከ _____ እስከ _____

Admited as In-patient Frome _____ Till _____

በተመላላሽ የታከሙበት ከ 09/11/04 እስከ 09/11/04

Treated as out-patient from _____ Till _____

የተሰጠዉ ዕረፍት ከ የአስር ቀን የህክምና እረፍት::

Rest Required _____

Healing time _____

ተርጓሚ አረፍት

Translator

የሆስፒታሉ ዲሬክተር

Hospital Director

ሐኪም

Dr.YILMA BOGALE

INTERNIST

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ _____

566

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል

# Federal Police Referral Hospital

ቁጥር 281/ጠ50/ፀ9

ቀን 12/11/04

በአዲስ አተማ ክ/ከ/ፖሊስ መምሪያ
ለመርካቶ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ
አዲስ አበባ፤

ስለ ኮን/ል በየነ ሐይሉ የህክምና ማስረጃ ሠርተፊኬት እንዲላክላችሁ በቁጥር 04/261/04 11/11/2004 ዓ/ም የፃፋችሁልንን ደብዳቤ ይመለከታል።

በመሆኑም በሽም የተጠቀሱትን አባል ጉዳት የሚገልፅ 1 ገጽ የሃኪም ማስረጃ ከዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

/ ከሠላምታ ጋር /

ዶ/ር ይልማ ቦጋለ
የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት
Dr. YILMA BOGALE
INTERNIST

ግልባጭ
- ለፌዴ/ፖ/ሪፈ/ሆ/ል ሚ/ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ፖ/ሆ/ል

Tel 0115-518470 Fax 157954 P.O. Box 21652

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

567

ECHN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አዲስ አበባ _____ ቀን _____

ፕሮቶኮል ቁጥር 206253

የፖሊስ ሠራዊት ሆስፒታ

Police force Hospital

Addis Ababa

# የምስክር ወረቀት

# CERTIFCATE

ስም ከነአባት ኮን/ል ቡሽራ ሄርጳሳ

Name and father's Name _____

የበሽታው ዓይነት ወይም የደረሰበት በቀን 06/11/04 ዓ/ም በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት የሽንት ፊኛቸው አካባቢ ሀይለኛ ህመም ያጋጠማቸው ሲሆን ለህክምና በመጡበት በ07/11/04 ዓ/ም በተደረገላቸው የሽንት ምርመራ የሽንት ፊኛ ቁስለት ስለገጠማቸው ህክምናና የሶስት ቀን እረፍት ተሰጥቶአቸዋል::

በመኝታ የታከሙበት ከ _____ እስከ _____

Admited as In-patient Frome _____ Till _____

በተመላላሽ የታከሙበት ከ 07/11/04 እስከ -

Treated as out-patient from _____ Till _____

የተሰጠዉ ዕረፍት ከ 03/ ሶት ቀን/::

Rest Required _____

Healing time _____

ተርጓሚ አረፍት

Translator

H/O.Mesfin Begale

የሆስፒታሉ ዲሬክተር

Hospital Director

ሐኪሙ

The Doctor

H/O.Mesfin Begale

ዶ/ር ይልማ ቦጋሌ
የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት
Dr.YILMA BOGALE
INTERNIST
የኢትዮጵያ ጤና አገ/ዲሬክተር/
ፌዴራል ሚ/ዲሬክተር

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ _____

568

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል
# Federal Police Referral Hospital

ቁጥር 253/ሠ6ዐ/59

ቀን 12/11/04

በአዲስ አተማ ክ/ከ/ፖሊስ መምሪያ

ለመርካቶ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ

አዲስ አበባ፤

ስለ ኮን/ል ቡሸራ ሄርጳላ የህክምና ማስረጃ ሠርተፊኬት እንዲላክላችሁ በቁጥር 04/236/04 10/11/2004 ዓ/ም የፃፋችሁልንን ደብዳቤ ይመለከታል::

በመሆኑም በስም የተጠቀሱትን አብል ጉዳት የሚገልፅ 1 ገጽ የሃኪም ማስረጃ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን::

/ ከሠላምታ ጋር /

ዶ/ር ይልማ ቦጋለ
የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት
Dr. YILMA BOGALE
INTERNIST

ግልባጭ

- ለፌዴ/ፖ/ሪፈ/ሆ/ል ሚ/ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ፖ/ሆ/ል

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ

Tel 01154 36470
Fax 157954
P.O. Box 21652

569

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

አዲስ አበባ _____ ቀን _____

ፕሮቶኮል ቁጥር 148868

የፖሊስ ሠራዊት ሆስፒታል

Police force Hospital

Addis Ababa

የምስክር ወረቀት

CERTIFCATE

ስም ከነአባት ኮ/ር ግርማዬ ገ/ሚካኤል

Name and father's Name _____

የበሽታው ዓይነት ወይም የደረሰበት በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት በቀን 06/11/04 ዓ/ም በቀኝ እግራቸው በታችኛው አጥንት ላይ 3 C.M X 0 .5 C.M የሚሆን ጉዳት ደም እየፈሰሳቸው መጥተው የተጐዳው የአካል ክፍልም አስፈላጊውን ህክምና የተደረገላቸው ሲሆን ደም የሚፈሰው ቦታ ተሰፍቷል። በተጨማሪም በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያ በቀን 07/11/04 ዓ/ም 1ኛ/ የቀኝ አይናቸው ነጩ ክፍል ላይ 2 M.M የሚሆን የመቀደድ ጉዳት 2ኛ/ በዚሁ አይናቸው የመስታወት ክፍል ላይ የመፋቅ ጉዳት፣

3ኛ/ የቀኝ ጉንጭ የላይኛው ክፍል 1 C.M የመቀደድ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

በመኝታ የታከሙበት ከ _____ እስከ _____

Admited as In-patient Frome _____ Till _____

በተመላላሽ የታከሙበት ከ 08/11/04 እስከ 09/11/04

Treated as out-patient from _____ Till _____

የተሰጠዉ ዕረፍት ከ አንድ ሳምንት የእረፍት ጊዜ ተሰጥቶአቸዋል።

Rest Required _____

Healing time አሁን በክትትል ላይ በተሻለ ለሙጥ ላይ ይገኛሉ።

ተርጓሚ አረፍት

Translator

የሆስፒታሉ ዲሬክተር

Hospital Director

ሐኪሙ

The Doctor

Dr. YILMA BOGALE

INTERNIST

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል
# Federal Police Referral Hospital

ቁጥር 327/ms0/59

ቀን 12 11 04

በአዲስ አተማ ክ/ከ/ፖሊስ መምሪያ
ለመርካቶ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ
አዲስ አበባ፤

ስለ ኮማንደር ግርማይ ገ/ሚካኤል የህክምና ማስረጃ ሠርተፊኬት እንዲላክላችሁ በቁጥር 04/235/04 ፤10/11/2004 ዓ/ም የፃፋችሁልንን ደብዳቤ ይመለከታል።

በመሆኑም በስም የተጠቀሱትን አባል ጉዳት የሚገልፅ 1 ገጽ የሃኪም ማስረጃ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

/ ኃይላማሪያም ጋር /

ዶ/ር ይልማ ቦጋለ
የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት
Dr. YILMA BOGALE
INTERNIST

ግልባጭ
- ለፌዴ/ፖ/ሪፈ/ሆ/ል ሚ/ዳይሬክተር ጽ/ቤት
ፖሊስ

ከሳሳው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

Tel 01 65 43470
P.O. Box 21652
Fax 157954

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

አዲስ አበባ ——— ቀን ———

ፕሮቶኮል ቁጥር 03-5753

የፖሊስ ሠራዊት ሆስፒታል
Police force Hospital
Addis Ababa

የምስክር ወረቀት
CERTIFCATE

ስም ከነአባት ኮን/ል አንበሴ ሞርካ

Name and father's Name

¾uiታው ዓይነት፡- ተደበደብኩኝ ብለው መጥተው በቀን 07/11/04 ዓ/ም በድንገተኛ ክፍል የታከሙ ሲሆን በምርመራ ላይ በኃለኛው የጭንቅላት ቆዳቸው ላይ 0፡3 ሴ/ሜ የሚሆን ቁስል እብጠት እና መካከለኛ የደም መፍሰስ የነበራቸው ሲሆን በወቅቱ አስፈላጊውን ህክምና አግኝተው የነበረ ሲሆን የነበራቸው የጭንቅላት ጉዳት መጠነኛ የነበር እና በወቅቱ በደህና ሆኔታ ላይ መሆናቸው በዚህ የህክምና ማስረጃ እናረጋግጣለን።

በመኝታ የታከሙበት ከ ——— እስከ ———

Admited as In-patient Frome ——— Till ———

በተመላላሽ የታከሙበት ከ 07/11/04 እስከ 07/11/04

Treated as out-patient from ——— Till ———

የተሰጠዉ ዕረፍት ከ ———

Rest Required ———

Healing time ———

ተርጓሚ አረፋት
Translator

የሆስፒታሉ ዲሬክተር
Hospital Director

ዶ/ር ይልማ ቦጋለ
የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት
Dr.YILMA BOGALE
INTERNIST
የኢትዮጵያ ፓሊስ ጤና አገልግሎት ሬፈሬራል ሚ/ዳይሬክተር

ሐኪሙ
The Doctor

572

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌዴራል ፖሊስ ሪፈራል ሆስፒታል

# Federal Police Referral Hospital

ቁጥር 17576 /ከመደ/ሆ

ቀን 05/02/05

በኢትዮ/ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ

ለታክትክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክት

አዲስ አበባ፡-

ስለ ኮን/ል አንበሴ ሞርካ የህክምና ማስረጃ ሠርተፍኬት እንዲላክላችሁ በቁጥር ለት/ፖ/ፖ/ጠ/ፀ41/ዐ2005 በ02/06/ዐ5 ዓ.ም የጻፋችሁልንን ደብዳቤ ይመለከታል።

በመሆኑም በስም የተጠቀሱትን አባል ጉዳት የሚገልጽ ገጽ የሃኪም ማስረጃ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን።

ለሰላምታ ይቸገ

ዶ/ር ይልማ ቦጋለ
የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት
Dr.YILMA BOGALE
INTERNIST
የኢትዮጵያን ፖሊስ ሠራዊት አገ/ጸ/ሬት/ ሪፈሆስፒ ሜዲካል ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ለሬፓ/ሪፈ/ሆ/ል/ሜ/ዳይሬክተር ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ከቀናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ


Tel 0115-518470
ምስር ቁጥ ፬
Fax 157954
P.O. Box 21652


http://ethcriminalawnetwork.com/

## የምርመራው ዓላማ

ከላይ በ"ሀ" ፊደል ከተ/ቁ1-8 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በ"ለ" ፊደል ከተ/ቁ1-8 ከተጠቀሱት ማመሳከሪያ የእጅ ፅሁፎች ጋር ተመሳክረው ተመሳሳይ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ ነው።

## የምርመራው ሂደትና የተገኘው ውጤት

ከላይ በ"ሀ" ፊደል ከተ/ቁ1-8 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በ"ለ" ፊደል በተ/ቁ1-8 ከተጠቀሱት ማመሳከሪያ የእጅ ፅሁፎች ጋር አንድ በአንድ እየተነፃፀሩ በልዩ ልዩ አጉልተው በሚያሳዩ የሰነድ መመርመሪያ መሳሪያዎች ረዳትነት ተመርምረዋል።

በተደረገውም ምርመራ ከላይ በ"ሀ" ፊደል ከተ/ቁ1-8 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በሆሄያት አመሰራረት፣ በአጣጣል ባህሪይ፣ እንዲሁም በልዩ ልማዳዊ ምልክቶች በ"ለ" ፊደል በተ/ቁ1-8 ከተጠቀሱት መማመሳከሪያ የእጅ ፅሁፎች ጋር ግንኙነት/ተመሳሳይነት/ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

ስለዚህ በምርመራው ውጤት መሰረት፦

1.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ1 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በሸህ መክተ ሙሐ የተፃፉ ናቸው።

2.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ2 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በሙኒር ሁሴን የተፃፉ ናቸው።

3.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ3 እና ተ/ቁ3.1 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በየሱፍ ጌታቸው የተፃፉ ናቸው።

4.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ4 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በአህመዲን ጀበል የተፃፉ ናቸው።

5.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ5 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በአህመድ ሙስጠፋ የተፃፉ ናቸው።

6.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ6 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በመሀመድ አባተ የተፃፉ ናቸው።

7.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ7 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በአቡበክር አለሙ የተፃፉ ናቸው።

8.ከላይ በ"ሀ"ፊደል በተ/ቁ8 የተጠቀሱት ተመርማሪ የእጅ ፅሁፎች በበድሩ ሁሴን የተፃፉ ናቸው።

ምርመራው በፌደራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በሚገኘው የሰነድ ምርመራ ላቦራቶር በ29/12/2004 ዓ/ም በኢ/ር አርአያ ታደሰ እና በ/ረኢ/ር ግርማይ ምሩፅ ተከናወነ።

## የመርማሪዎች ፊርማ

1.....
አርአያ ታደሰ
(ኢ/ር)

2.....
ግርማይ ምሩፅ
(ረ/ኢ/ር)

ከዋናው ፊርማ ጋር ተመሳክሯል

574

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌ.ፎ/1.2/99/493/2005

## የሰነድ ምርመራ ውጤት መግለጫ

የኢት/ፌደ/ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ ታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 10632/04 በ25/12/04 በተጻፋው ደብዳቤ ቀጥሎ ያለውን ምርመራ እንድናደርግ ጠየቁ።

### ተመርማሪና ማመሳከሪያ

ሀ/1.የመጀመሪያው ገፅ ላይ በቀይ ማርከር መከተ መ.ሔ ተብሎ የተፃፈበት ቡናማ ቀለም ባለው አጀንዳ ውስጥ የተፃፉ የእጅ ፅሁፎች፣

2.አልሀምዱሊላህ እኛ ሙስሊሞች ሰላማዊ ህዝቦች... ብሎ በሚጀምር ሰነድ ላይ በሁለቱም ገፅ በኩል ያለው የእጅ ፅሁፍ፣

3. ለሱመያ መሸጊድ ኮሚቴ.... ብለው በሚጀምሩ 02 ገፅ ሰነዶች ላይ ያለው የእጅ ፅሁፍ፣

3.1"COMMERTIAL BANK OF ETHIOPIA" በሚል አጀንዳ ላይ ያለው የእጅ ፅሁፍ፣

4.የመጀመሪያው ገፅ ላይ በቀይ ማርከር A.02 እና በቀይ እስክሪፕቶ አህመዲን ጀበል ተብሎ የተፃፈበት አጀንዳ ላይ ያለው የእጅ ፅሁፍ፣

5.በ22-06-2010 በተዘጋጀና meeting 2 ብሎ በሚጀምሩና በላቦራቶሪ ክፍላችን በቀይ እስክሪፕቶ "ተመ" የተለባቸው 04 ገፅ ሰነዶች፣

6."Tayba Tv channel" በሚል አጀንዳ ውስጥ እና ከላይ ከሸፋኑ ኢትዮጵያ በሚለው ደብተር ውስጥ በላቦራቶር ክፍላችን በቀይ ቀለም ተመ2 የተባለባቸው የእጅ ጽሁፎች፣

7.ከማስታወሻ ደብተር ተነቅለው የወጡ 11 ገፅ ሰነዶች በላቦራቶሪ ክፍላችን በቀይ እስክሪፕቶ "ተመ" የተባለባቸው፣ በጥቁር ማርከር 003C፣ 002B፣ 001A የተባለባቸው፣"Global memo book" በሚሉ 03 የማስታወሻ ደብተሮች፣ "Sinarline" ማስታወሻ ደብተር በውስጥ በኩል ከቨሩ ላይ በጥቁር ማርከር "C" የተባለበት፣አረንጓዴ ከቨር ያለው፣ጥቁር ከቨር ያለውና የፊት ለፊት ከቨር የሌላቸው ሁለት ማስታወሻ ደብተሮች፣

8.Name ከሚለው ፊት ለፊት መሀመድ አባተ በሚል ደብተር ውስጥ ያለው እና በላቦራቶሪ ክፍላችን በቀይ እስክሪፕቶ "ተመ1" የተባለበት የእጅ ፅሁፍ ተመርማሪ፣

ለ/1.ሼህ መከተ መ.ሔ ቀደም ሲል ፎርም 3 አዲስ መታወቂያ በሚል 03 ገፅ፣ በ13/10/99 ዓ/ም፣ በ11/10/99 ዓ/ም፣ በ16/07/2000ዓ/ም ለተለያዩ ጉዳዮች እና ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርበው የፃፏቸው ናቸው ተብለው የተላኩልን፣

2.ሙኒር ሁሴን ቀደም ሲል በ15/3/97ዓ/ም ለተለየ ጉዳይ እና ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርበው የፃፏቸው ናቸው ተብለው የተላኩልን፣

3.የሱፍ ጌታቸው ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርበው የፃፏቸው ናቸው ተብለው የተላኩልን፣

4.አህመዲን ጀበል በ18/12/04 ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርቦ የፃፈው ነው ተብሎ የተላከልን፣

5.አህመድ ሙስጠፋ ቀደም ሲል በ26/01/03ዓ/ም፣ በ26/07/03ዓ/ም፣ 18/02/97ዓ/ም 02 ገፅ በ26/01/2003ዓ/ም እና ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርበው የፃፏቸው ናቸው ተብለው የተላኩልን፣

6.መሀመድ አባተ ቀደም ሲል በ17/02/93ዓ/ም፣ በ4/9/95ዓ/ም እና ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርበው የፃፏቸው ናቸው ተብለው የተላኩልን፣

7.አቡበከር አለሙ ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርበው የፃፏቸው ናቸው ተብለው የተላኩልን፣

8.በድሩ ሁሴን በ18/12/2004 ምርመራውን በጠየቀው ክፍል ቀርበው የፃፏቸው ናቸው ተብለው የተላኩልን የእጅ ፅሁፍ ማመሳከሪያ፣

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

ETCLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

# በፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ የፎርንሲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት

## FEDERAL POLICE CRIME INVESTIGATION SECTOR FORENSIC INVESTIGATION DIRECTORATE

ቁጥር ፌፎ1.2/99/493/05
ቀን 29/12/2004

ለፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ የታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት

**አዲስ አበባ**

ስለ እነአቡበከር አህመድ የሰነድ ምርመራ ጉዳይ በቁጥር 10632/04 በ25/12/04 የተፃፈልንን ደብዳቤ ይመለከታል።

ስለዚህ በጥያቄው መሰረት ምርመራውን አጠናቀን፡-

1.ሁለት (02) ገፅ የምርመራ ውጤት መግለጫ፣

2.ሰላሳ አንድ (31) ገፅ ተመርማሪ ሰነድ፣

3.ሃያ አንድ (21) ገፅ ማመሳከሪ ሰነድ፣

4.በድምሩ ሀምሳ አራት (54) ገፅ ሰነዶችን በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት የላክን መሆኑን እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ደረጀ ደለለኝ
ምክትል ኢንስፔክተ
Dereje Delelegn
(Deputy Inspector)

የፌደራል ፖሊስ ማጅስ ት ሂመራ ዳይሬክቶሬት
ደብዳቤው ገቢ ቁ 30/12/04
የመዝገብ ቁጥር 10632/04
ዶሴ ቁጥር

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

576

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

ECHN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ይድረሰ ለኢትዮጵያን በሙሉ::

መጅሊሰን የተቃወመው ጥቂት የህብረተሰብ ክፍል ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ መስሊሞች ፣ኡለማዎች ፣ዳዒዎች፣ ሙስሊም ምሁራኖችና ተማሪዎች ፣ የዕድሜ ባለፀጋዎች፣ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መሆናቸውን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይወቅልን እያልን ድምፃችንን እናሰማለን::

## መጅሊሰን ሰንቃወም

እኛ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች መጅሊስን ስንቃወም፣ስሜታችንን ተከትለን ስውር የፖለቲካ አጀንዳ አንግበን የስልጣን ጥማት ኖሮብን ወይም ዓለማዊ ጥቅም አንጉቶን ሳይሆን የእስልምና ኃይማኖታችን ሲሸራረፍ ወሰኑ ሲጣስ ደባ ሲሸረብበት በዓይናችን በማየታችንና በጆሮአችን በመስማታችን ምክንያት መሆኑን አበክረን ስማስገንዝብ እንወዳለን::

አህባሽን የምንቃወመው ከእስልምና ኃይማኖት ያፈነገጠ በፊተናው ሺህ /በአብዱላህ አል ሃረሪ/ የተፈለሰፈና በአይሁዶች የተቀነባበረ ድጋፍ የሚረዳ እስልምናና ሙስሊሞችን ለማዳከም በመንግስት አንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሙሉ ድጋፍ ሰጪነት ህገ መንግስታዊ መብታችንን በኃይል በመደፍጠጥ ብሎም የህገ መንግስት አንቀፆችን በመፃረር በግድ የአህባሽን ፍልስፍና ተቀበሉ በመባላችን ነው::

## አህባሽ/የፈተናው ሺህ/ ስሚያራምዳቸው ፍልስፍናዎች በጥቂቱ

1ኛ. ቁርዓን የአላህ ቃል አይደለም ማለቱ::
2ኛ. ሲሃቦችን/የነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዓ.ወ./ ባልደረቦችን በተናጠል ትችት /ወቀሳ/ ቢሰነዘርባቸው ችግር የለውም ማለቱ::
3ኛ. ሙስና/ጉቦ/መቀበልም ሆነ መስጠት ፀፍቀዱ
4ኛ. ታሳላቅ የኢስላም ሊቃውንቶችን በከሃዲነት መፈረጁ እና ወዘተ ...

ለመሆኑ አንዳንድ ባለስልጣናት የህዝቡ ሚዲያዎችን በመጠቀም በመላው አገሪቱ ያሉ ሙስሊሞች እየጠየቁ ያሉትን ጥያቄ ወደ ፖለቲካ አጀንዳ በመጠምዘዝ ህዝቡያልጠየቀውንና የመጠየቅ ዓላማው ያልሆነውን በሸሪዓ ህግ አንተዳደር አስላማዊ መንግስት እንመስርት የሚሉትን የኃይማኖት ግጭት በመፍጠር ሀገሪቱ ወደ ከፋ ብጥብጥ ሊከቷት ነው እያሉ የሚያስተላልፉት መልዕክት ከአንድ ህዝብን ከሚመራ አካል የማይጠበቅና የበሬ ወለድ ተረት ተረት መሆኑን መላው የአገሪቱ ማህበረሰብ ጠንቅቆ አንደሚያውቅ አለማወቃቸው በጣም ያስገርማል::

## ምርጫ

የመጅሊስ አመራሮች ምርጫ በጊዜ ገደብም ሆነ በድንገት ይደረግ ሊባል ይችላል:: ስለሆነም በመላው ሀገሪቷ የሚገኙ ሙስሊሞች በንቃት በመከታተል ምርጫው እንዳይጭበረበር የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብናል::ለዚህም ሊመሩን የሚችሉ ወኪሎቻችንን ከወዲሁ በየአካባቢያችን በጥንቃቄ በመመልመል ማዘጋጀት ይገባናል::

በመሆኑም የረጋ ውሳኔ ቅቤ ይወጣዋልና በየመስጂዳችን በተክቢራ ያልመረጥናቸው የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉንም፣ የአህባሽ አሰተምህርትንም አንቀበልም የሚሉ መፈክሮችን በማሰማት ሰላማዊ ትግላችን

ሰላማዊ መብታችን ይከበርልን

ኢንሻአላህ

አጭር አደርገው ያለተካልሽ

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

አንድነታችንን ጠብቀን ከተጓዝን ህገወጡን መጅሊስና አህባሽን ገርስሰን እንጥላለን:: አንድነታችንን ከጠበቅን ሌሎች የሃይማኖት ተቋማት ተከታዮቻቸውን በመንፈሳዊ፣ በኢኮኖሚና በልማት ዘርፎች እያንቀሳቀሱት መጅሊሶች ግን ሙስሊሙን በነዚህ ዘርፎች ከማገዝ ይልቅ ሆዳቸውን ብቻ ሲሞሉ ሲያንገበግበው የነበረው ሙስሊም ትክክለኛ መሪዎቹን ይመርጣል:: ኢንሻአላህ!!

**አንድነታችን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች**

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ከምንጊዜውም በላይ አንድ መሆንና የመጣባቸውን አይሁዳዊ መርህ-ግብር መመከት ዲናዊ ኃላፊነታቸው ነው:: ሁሉም ሙስሊም በነፍስ-ወከፍ ከአላህ (ሱ.ወ) ፊት በዚህ ታሪካዊ ክስተት ስለፈፀመው መልካም ወይም አፍራሽ ተግባር ይጠየቃል:: የኢትዮጵያ ሙስሊም እጅግ ወሳኝ ወቅት ላይ የመሆኑ ነገር ተጠያቂነቱን የበለጠ ከፍ ያደርገዋል:: በዚህ ሂደት ሁለት ዓይነት ስህተቶችን እጅግ ነቅተን መጠበቅ ይኖርብናል::

1ኛ. በሱፊያ (አሽዓሪያ) የአስተሣሠብ መስመር ስም አህባሽን ለማስረፅ የሚደረገውን እንቅስቃሴ

2ኛ. አህባሽን በመቃወም ስም የተቃውሞው አንድ አካል የሆኑትን የአሽዓሪያ (ሱፊያ) አስተሳሰብ መስመር ላይ ያሉ ሙስሊሞችን የሚነካ ድርጊት::

እነዚህ ስህተቶች እጅግ ወሳኝ ከመሆናቸው አኳያ መብራራት ይፈልጋሉ

1ኛ በሱፊያ (አሽዓሪያ) የአስተሣሠብ መስመር ስም አህባሽን ለማስረፅ የሚደረገው እንቅስቃሴ

አህባሽ ሙስሊሞችን የመከፋፈል አጀንዳ ያለው፣ እጅግ እንግዳ የሆኑ አስተሣሠቦችን የሚሠብክና ዓለማቀፍ የኢስላም ሊቃውንት በአንድ ድምፅ ያወገዙት አስተሣሠብ ነው:: አህባሽ የኢስላም ጠላቶች /አይሁዶች/ ሙስሊሙን ለማኮላሸት ድምፅ የለሽ መሣሪያ እንደሆነ ተገንዝበው ያደራጁት አንጃ ነው:: ወደ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ራሱን ያሰርፅ ዘንድም ብዙሃኑ ሙስሊም ሊቀበለው ይችላል ብለው ያሰቡትን መልክ ቀብተውታል:: "በዓቂዳ የአሽዓሪያ ተከታይ ነኝ፣ በፊቅህ መዝሀብ ደግሞ የሻፊዒያ መስመር ላይ ነኝ" የሚል ማወናበጃ ተላበሰ:: በርግጥም ከአሽዓሪያ የአስተሣሠብ መስመር ጋር የጋራ የሚያደርጉት ነጥቦችን እምኑ ውስጥ ማካተቱ አልቀረም:: በዚሁ ማወናበጃ ባይሳካለትም ብዥታ ለመፍጠር ሞክሯል:: መጅሊስም ይህንኑ ማሳሳቻ ያዘሉ መግለጫዎቹን ለሕዝብ ሲነዛ መቆየቱ የዚሁ አኩይ ተልዕኮ አካል ነው::

መሪያቸው "ዓብደላህ አል-ሀረሪ" እኩይ አስተሣሠቡን የተቃወሙትን አሊያም ያወገዙትን የአሽዓሪያ/ሱፊያ ዑለማዎች በገሀድ ማክፈሩን ለሚያውቁ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ይህን መሰል መግለጫ በመንግስት ሚዲያ መሰጠቱ ያሳዝናል:: ምን እየታሰበልን ነው ጃል! ያሰኛል? የሱፊያና የአሃባሽ አካሄድ በጭራሽ ግኑኝነት የሌላቸው አካሄዶች መሆናቸው ግልጽ ጉዳይ ነው:: ሱፊያዎች ጭንቀታቸው ሙስሊሙ እንዴት አንድ ሆኖ ንጹህ ቀልብ ይዞ አላህ ፊት ይቀርባል ሲሆን የአህባሾች ዐላማ ግን ሙስሊሙ እርስበርሱ እየተናቆረ ለጠላት እጅ የሚሰጥበትን መንገድ ማመቻቸት ነው::

ስለሆነም በሱፊያ/አሽዓሪያ ስም ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ ሊጫን የታሰበውን



አስተሣሠብ እንቃወማለን:: ያልመረጥናቸው የመጅሊስ አመራሮች እምነት ሊመርጡልን ቀርቶ በስማችን ሊናገሩ አይቻላቸውም:: ከኢስላም ሌላስ ምን ዓይነት እምነት ሊመረጥልን??!

2ኛ. አህባሽን በመቃወም ስም የተቃውሞው አንድ አካል የሆኑትን የአሽዓሪያ (ሱፊያ) አስተሳሰብ መስመር ላይ ያሉ ሙስሊሞችን የሚነካ ይሮጊት::

በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላይ ያንዣበበውን ሃይማኖታዊ ፈተና ለመመከት በቁርጠኝነት የእምነቱ ከፍሎች ያሉ የአስተሣሰብ ልዩነቶችን ወደጎን ብሎ አንድነትን ማጠናከር የግድ ነው:: በመሆኑም እየተካሄደ ያለው የመብት እንቅስቃሴ ሁሉንም ወገኖች ያቀፈ ሆኖ ይታያል:: አላሁ አክበር!! የኢስላም መሠረቶችና የእምነታችን ማዕዘኖች አስተሣሠረውን በእምነታችን ላይ የመጡብንን ፈታኝ ሙከራዎች እየሠባበርናቸው እንገኛለን:: ኧልሃምዱሊላህ!!

ስለ አንድነታችን ስናወራ አንድ ነጥብ ለሁላችንም ግልጽ መሆን አለበት:: የኢትዮጲያ ሙስሊም አንድ ሆኗል ስንል የተለያዩ የደዕዋ አካሄድ መስመሮች የሉም ማለታችን አይደለም:: ተብሊግ፣ ስለፊያ፣ ሱፊያ(አሽዓሪያ)...ከዚህ ቀደምም የነበሩና አሁንም ያሉ፣ ምን ላይ ትኩረት ሰጥተን ነው ዳዕዋ ማድረግ ያለብን የሚለው ነጥብ የተለያየ አስተያየት የሰጡ የደዕዋ መስመሮች ናቸው:: ሁሉም ግን ኢስላምን ለማገልገል ነው ደፋቀና የሚሉት:: በ1999 የሙስሊሙን አንድነት ለማጠንከር ሲንቀሳቀስ የነበረውና ከሱፊያው በኩል በሙፍቲ ሐጂ ዑመር መሪነትና ከሰለፊያው በኩል በዶር. ጀይላን መሪነት ተቋቁሞ የነበረው የዑለማኦች ኮሚቴ እነዚህ አስተሣሠቦች መሠረታዊ የኢስላም አስተምህሮቶች ላይ ልዩነት የሌላቸው አመለካከቶች መሆናቸውን በግልጽ አስቀምጧል:: እነዚህ ታላላቅ ዐሊሞቻችን ሰለፊያም ይሁን ሱፊያ(አሽዓሪያ) የአህለሱና ወልጀመዓህ የአስተሣሠብ መስመር ውስጥ የታቀፉ መሆናቸውን በማያዳግም ሆኔታ አረጋግጠዋል:: (ይህ ኮሚቴ ጠላቶቻችን የሙስሊሙን አንድነት የማፈልጉ በመሆናቸው በመጅሊስ መፍረሱ ይታወሳል::)

አህባሽ አገራችን ሲገባ በቀላሉ ተቀባይነት ለማግኘት ሱፊያን ነኝ ብሎ ለማወናበድ መሞከሩንና በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከሱፊያ ጋር ተመሳሳይ አቋም ይዞ መቅረቡ ግልጽ ነው:: በመሆኑም አሁን ያለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሱፊያውም ሰለፊያውም በጋራ እየካሄደው ካለ ከመሆኑ አንጻር አህባሽን በምናወግዝበት ጊዜ አህባሽን ነጥሎ መምታት ሲቻል አህባሽና ሱፊያ/ አሽዓሪያ/ የሚጋሩባቸውን ነጥቦች ማንሳት እጅግ ከባድ ስህተት ነው:: አህባሽን የምንቃወምባቸው ምክኒያቶች ለሁላችንም ግልጽ ሊሆኑ ይገባቸዋል:: ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. ከአይሁድ ጋር ባላቸው ትስስር (RAND 2003 ሪፖርትን ይመልከቱ)::
2. ሙስሊሙን የመከፋፈልና የማዳከም አጀንዳ ስላላቸው::
3. ለዘመናት ሙስሊሙን ሲያወዛግቡ የነበሩና አሻሚ አስተሳሰቦችን በማግዘፍ ሙስሊሞች እንዲነታረኩና እንዲለያዩ በማድረግ ከዋናው የዲናቸው ኃላፊነት እንዲርቁ ማድረግ::
4. በተለያየ መዝሀብ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ዑለማኦች በተለያየ አጋጣሚ የሰጧቸውን ወጣ ያሉ ፈትዋዎች በመለቃቀምና አንድ ላይ በመሰብሰብ ባዕድ መዝሀብና አመላካከት የገነባ በመሆኑ::
5. ታላላቅ የሙስሊሙን ዓለም ዑለማኦች (የሱፊያን ጨምሮ) ያከፈሩ መሆናቸው::



http://ethcriminalawnetwork.com/

6.የሙስሊሙ ኡማ ወሳኝና የጋራ አጀንዳዎች ላይ ግድየለሽና አቋም የለሽ መሆናቸው:: ለዚህም ማሳያው ሌሎች ወገኖች በሃይማኖታዊ ጉዳዮቻችን ላይ ጣልቃ እንዲገቡ ማድረጋቸውና ሙስሊሞችን በዓለም አቀፍ ደረጃም ሊያስጠይቁ የሚችሉ ከባድ ስያሜዎችን (አሸባሪ፣ አክራሪ፣ ፅንፈኛ...) በመስጠት ለኢስላም ጠላቶች አሳልፈው በመስጠት ተባብረው መስራታቸው ይጠቀሳል::

በሱፊያ ስም አህባሽን ለማስረፅ የሚደረገውን ማወናበጃ እንደምንጠነቀቅ ሁሉ የአህባሽን አስተሣሠብ በሚጋለጥ ስም በሱፊያ/አሸዓሪያ የአስተሣሠብ መስመር ላይ ውግዘት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል:: የዚህ መሰሉ ድርጊት ተፈጽሞ ቢገኝ እንኳን የምንቃወመው መሆኑንና የተቃውሞ እንቅስቃሴውን የማይወክል መሆኑ ግልጽ መሆን ይኖርበታል:: ተቃውሞው የአንድ ቡድን ሳይሆን የተብሊጉም የሰለፊያውም የሱፊያውም ነው:: አላሁ አክበር!!

አህባሽና አንዳንድ የመንግስት አካላት የሚሹት እኛን በመውሊድና በአላህ መልካም ሥሞችና ባህሪያት ዙሪያ በሚነሱ ልዩነቶች እርስ በርሳችን በጭቅጭቆች ላይ እንድንጠመድና መሰረታዊ ጥያቄዎቻችንን እንዳናነሳ ነው:: የእርስ በርስ ጭቅጭቅ ውስጥ የተጠመደ ማህበረሰብ ደግሞ እንኳን መብቱን ሊጠይቅና ህልውናውም ያሰጋዋል:: ሙስሊሙ ህልውናውን የሚፈታተኑ በርካታ ጉዳዮች እያሳሰቡት ባለበት ወቅት መቋጫ በሌላቸውና ለብዙ መዶ አመታት ውለማኦች መካከል በነበሩ ቅርንጫፋዊ ጉዳዮች መጠመድ በታሪክ የሚያስወቅስ ስህተት ነው:: በአላህ ፈቃድ ልዩነቶቻችንን አቻችለን አህባሽና የመጅሊስ አመራሮች እስኪወገዱ በጽናት እንታገላለን::

ጥያቄያችን የመብት ጥያቄ እንጂ አንዱን የአስተሣሠብ መስመር ለማንሰ አለመሆኑን ቢግልፅ እናውጃለን! ሁሉንም ወገኖች ያካተተ ሕዝብ የመረጠው መጅሊስ እንዲኖረን እንሻለን:: አህባሽ ከሁሉም የኢስላም አስተሣሠብ መስመሮች ያፈነገጠ በመሆኑ በጋራ እንቃወመዋለን:: በእምነት ተቋሞቻችን ላይ መሰበክ እንደሌለበት፣ ኢማሞቻችን መገደድ እንደሌለባቸውና የእምነት ነፃነታችን ህገ መንግስታዊ መብታችን ነውና ያለምንም መሸራረፍ መከበር እንዳለበት በጋራ ድምፃችንን እናሰማለን:: አላሁ አክበር!!

መጅሊሶችና አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት የአህባሽ ስልጠና በሰፊው እንደሚቀጥል በአደባባይ እየለፈፉ ይገኛሉ:: በቅርቡም በአገር አቀፍ ደረጃ ለ16 ሺህ ሰዎች ስልጠና ለመስጠት መጅሊስ በዝግጅት ላይ መሆኑ ታውቋል:: አንዳንድ ባለስልጣናት በአዲስ አበባና በክልሎች የኢህአዴግ አባላትንና ህብረተሰቡን በመሰብሰብ አወሊያ ላይ የሚደረገው እንቅስቃሴ ለአገር ስጋት መሆኑንና ኢሰላማዊ መንግስት ለመመስረት የሚደረግ እንቅስቃሴ ጥንሰስ መሆኑን ሲሞግቱ ተስተውለዋል:: እነዚህና መሰል እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩን ነገር ቢኖር ትግላችን ገና የመጨረሻ ውጤቱ ላይ እንዳልደረሰና ወደፊትም ከባድ ስራ እንደሚጠብቀው ነው:: ይህ ትልቅ ትግል ደግሞ ከምንም ነገር በላይ አንድነታችንን የሚጠይቅ በመሆኑ በጋራ ለመታገል እንዘጋጅ:: አወሊያ ለሶስት ሳምንት መሰብሰባችን ይቆማል ማለት ትግላችን ይቆማል ማለት አይደለምና ሁላችንም በየመስጊዳችን ሰላማዊ ጥያቄያችንን እናሰማ! ለክርስቲያን ወገኖቻችንም ስጋት እንዳይሰማን እና መብታችንን የምንጠይቅ ሰላማዊ ሰዎች መሆናችንን እናውጅ! አላሁ አክበር!




# ድምጻችን ይሰማ

7

የተቃውሞ ድምጽ | ጁሙዓ መጋቢት 21፣ 2004– 12ኛ የተቃውሞ ሳምንት


## ትግሉም ድሉም የሁሉም ነው!

ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የዲናችን ንቃት አመራርና ሀገራዊ አጠቃላይ ችግሮቻችንን የገዙ የመጅሊሱ ሕገ-ወጥ አመራሮችን ከትከሻችን ላይ አውርደን ድምፃችንን ማሰማት ከጀመርን ሰነባበትን:: ሁሉንም ዓይነት የበደል እንቅስቃሴዎች ያከሸፈው የሕዝበ ሙስሊሙ የመብት ጥያቄ መልካም ጎዳና ላይ እንዳለ ብዙዎቹ ይመሰክራሉ:: እስካሁን ባደረገውም እንቅስቃሴም የዋናው ድል ዋዜማ የሆኑ በርካታ ድሎች መጎናፀፍ ችሏል:: ከነዚህም መካከል:

1ኛ. ለዘመናት በሚደረግ ዳዕዋ እንኳን ሊገኝ የማይችል ታሪኩ የማይታወቅ አንድነት መፈጠሩ ትልቅ ድል ነው:: ለብዙዎች ይህ ታሪካዊ አንድነት ከአላህ (ሱ.ወ) ለኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የተሰጠ ልዩ ስጦታ እንደሆነ ይመሰክራሉ:: አህባሽ በመሰረቱ ሙስሊሙን በመከፋፈል እርሱ በርሱ ሲባላ እንዲኖር ለማድረግ ታስቦ ከውጭ የመጣ አንጃ ሆኖ ሳለ በተቃራኒው ይህ አንድነት መፈጠሩ በትክክልም የአላህ ስጦታ መሆኑን ያረጋግጣል::

2ኛ. የሙስሊሙን ሕብረተሰብ ሰላማዊነት በገሀድ ያሳየ መሆኑ ሌላኛው ውጤት እንደሆነ ይጠቀሳል:: በመቶ ሺዎች የሚቆጠርና እጅግ አስከፊ በደል በአምነቱ ላይ እየተፈፀመበት ያለ ሕዝበ ሙስሊም አንድ ቦታ ላይ ተሰባስቦ አንዲት ጠጠር ሳይወረውር እጅግ ሊስላማዊና ሠላማዊ በሆነ መንገድ መብቱን የመጠየቅ ባህሉ ብዙዎችን አስደምሟል:: "ሰላምን የማያናጉ፣ ሰላምን ማናጋት ለሚፈልጉትም ክፍተት የማይሰጡ!" ሲሉም አንድ የመንግስት ባለስልጣን የተቃውሞ እንቅስቃሴውን ገልፀውታል::

3ኛ. ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በዓለም አቀፍ ደረጃ ማንነቱ የተዋለጠውን የአህባሽ አስተሣሠብ በመቃወም ዲናቸውን ለመጠበቅ ያላቸውን ቁርጠኝነትና ንቃት ማረጋገጣቸው::

4ኛ. ሕዝባዊ የመብት ትግሉ ያስቡትን ሁለገብ ጫናዎች ሁሉ ተቋቁሞ የሀገሪቱን ሁሉንም ክፍሎች እያዳረሰ መገኘቱ ሌላኛው ድል እንደሆነ ይጠቀሳል::

ከላይ የጠቀስናቸው ድሎች ሁሉ መሳካት የቻሉት አንድነታችንን ጠብቀን በመንቀሳቀሳችን ነው:: ሙስሊሙ ህብረተሰብ ከዚህ ቀደም በጥቃቅን ልዩነቶች እርስ በርሱ ሲሻኮት የመጅሊሱ ባለስልጣናት ይህን ክፍተት በመጠቀም ሲመራረጡ፣ ያሻቸውን ሲሰሩና ሙስሊሙን ሲመዘብሩ ቆይተዋል:: በዚህ ስራቸው የመረረ ተቃውሞ ሰላላጋጠማቸው ይህ አልበቃ ብሏቸው ከአይሁድ ጋር በማበር አህባሽን እምጥተው ሙስሊሙን የበለጠ ሊሰነጣጥቁትና ሽባ ሊያደርጉት አሴሩ:: አላህ ግን ዲኑን የሚጠብቀው አላህ ነውና ባልተጠበቀ ሁኔታ አላህ ሙስሊሙን አንድ አደረገውና ሴራቸውን የአይሁድ ሴራ እንዲጋፈጥ አነሳሳው:: አላሁ አክበር!! አሁንም ይህን



ሃሪ አድርገው ይኸ ተሳልፋ!

http://ethcriminalawnetwork.com/

## ሐምሌ 6/2004 ከሌሊቱ 5:40 — 6:00 ሕገ-ወጥ አዛን የተደረገባቸው መስጅዶች

| ተ.ቁ. | የመስጅዱ ስም | የሚገኝበት ቦታ | ክፍለ ከተማ |
|---|---|---|---|
| 1 | መርከዘል አንሷር | አየር ጤና | ኮ/ቀራኒዮ |
| 2 | መዓዝ ኢብኑጀበል | ካራ ቆሬ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 3 | ሰለፊያ | ስልጤ ሰፈር | ኮ/ቀራኒዮ |
| 4 | መስዓብ | ዓለም ባንክ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 5 | ሱና | ካራ ቆሬ ስልጤ ሰፈር | ኮ/ቀራኒዮ |
| 6 | ፋርቃን | ካራ ቆሬ ስልጤ ሰፈር | ኮ/ቀራኒዮ |
| 7 | ኻሊድ ኢብኑ ወሊድ | ካራ ቆሬ ስልጤ ሰፈር | ኮ/ቀራኒዮ |
| 8 | ጠለሃ | ዓለም ባንክ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 9 | ፈትህ | ጨው በረንዳ | አዲስ ከተማ |
| 10 | ባዩሽ | አደሬ ሰፈር | አዲስ ከተማ |
| 11 | ሸህ ሆጀሌ | ሩፋዔል | ጉለሌ |
| 12 | ሰላም | ቄራ | ቂርቆስ |
| 13 | ሰላም | ጃክሮስ | ቦሌ |
| 14 | ሰለፊ ሷሊሂን | ጉለሌ | ጉለሌ |
| 15 | ወሌ መስጅድ | አቧሬ | የካ |
| 16 | ተባረክ | ም/ባቡር | ኮ/ቀራኒዮ |
| 17 | ሽይር | አየር ጤና | ኮ/ቀራኒዮ |
| 18 | ዋህዳ | ካራቆሬ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 19 | አልይ | ካራቆሬ/ስሌጤ ሰፈር | ኮ/ቀራኒዮ |
| 20 | አወሊያ | አወሊያ ት/ቤት | ጉለሌ |
| 21 | ኑር | ፒያሣ | አራዳ |
| 22 | ቢላል | መሳለሚያ | አዲስ ከተማ |
| 23 | ቁባ | ኰልፌ አጠና ተራ | አዲስ ከተማ |
| 24 | መአዝ ኢብኑጀበል | ቀራኒዮ ድልድይ አጠገብ ወረዳ 10 | ኮ/ቀራኒዮ |
| 25 | ነዚራ | የሸ ደበሌ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 26 | ዑበይ | ኰልፌ ጠሮ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 27 | ጃፈር | ሎሚ ሜዳ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 28 | ዓሊ | ሎሚ ሜዳ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 29 | ዑስማን | ሎሚ ሜዳ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 30 | ሶራምባ | ሎሚ ሜዳ | ኮ/ቀራኒዮ |
| 31 | ጅማ አባጅፋር | ጅማ ሠፈር | ልደታ |
| 32 | አንሷር መስጂድ | አየር ጤና | ኮ/ቀራኒዮ |

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፌርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

2ኛ. ሐምሌ 14/2004 በአንዋር መስጂድ የተፈጠረውን ረብሻ አስመልክቶ በደብዳቤ ቁጥር አ/ም/2/1/12/2004 ቀን 1/12/2004 በተፃፈ የሕዝበ ሙስሊሙ ችግር አፈላላጊ ነኝ በማለት ራሱን የሰየመው ቡድን ባደራጃቸው ህገ-ወጦች

- ሐምሌ 14/2004 ከጧቱ 12:00 ጀምሮ መስጊዱን በመቆጣጠር አላህ ወክበር በማለት በርካታ ወጣቶችን በማሰባሰብ መስጊዱን ሲረብሹ ውለዋል።
- በተፈጠረው ረብሻ በዕለቱ ዋና ኢማም እና ም/ኢማሙ የዕለቱን ሶላቶች ሳያስግዱ ቀርተዋል።
- የመስጊዱ ሙዓዚኖች ለተለመደው ሶላት አዛን ማድረግ አልቻሉም ሕገ-ወጦቹ በራሳቸው ሙዓዚን እና ኢማም እንዲሰግዱ አድርገዋል።
- ቀኑን ሙሉ ሕገ-ወጥ ወጣቶችን በማደራጀት በ3ቱም በሮች ላይ ሕገ-ወጥ ፍተሻ አድርገዋል።
- የመስጊዱ ጥበቃዎች እና ሐዲሞች ሥራቸውን እንዳያከናውኑ አድርገዋል።
- በዚህም መሠረት በዕለቱ የነበሩት፡-

| ጥበቃዎች | ሐዲሞች |
|---|---|
| 1. ዓሊ ሠይድ | 7. ናስር ሸህ አናመድ |
| 2. አህመድ እንድሪስ | 8. ሻፊ አህመድ |
| 3. ጎዲሙ መሀመድ | 9. ከድር አህመድ |
| 4. ዑስማን ኢብራሂም | 10. አብደላ ቡሴር |
| 5. ሰዒድ መሀመድ | 11. ከድር ጣሂር |
| 6. ናስር ቡሴር | 12. ሙስጠፋ መሀመድ ናቸው |

- በመስጊዱ ንብረት ላይ የደረሠው ጉዳት፡-

ሀ. የአምፕሊፋየር ማስቀመጫ ሳጥን ሰብረው ለድምፅ ማጉያነት ተጠቅመዋል።

ለ. የጀኔሬተር ቁልፍ ሰብረው በጄኔሬተሩ ከተጠቀሙ በኋላ በሌላ ቁልፍ ቆልፍው የቀየሩት ቁልፍ ለጥበቃ ሠራተኛ ኃላፊ ለነበረው ጠርተው ለአቶ ናስር ሰጥተዋል። በማለት አሳውቀውናል። በመሆኑም የተፈፀሙት ህገወጥ ድርጊቶች ተገቢውን በማስረጃ እንዲጣራ እንዲደረግልን በትህትና እንጠይቃለን።

ከሠላምታ ጋር

ሐጂ አዛም ዩሱፍ መሐመድ
Haji Azam yusuf Mahammad
الحاج عزام يوسف محمد
ም/ፕሬዝዳንት
Vice President

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

582

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

بسم الله الرحمن الرحيم

# የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት

THE ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL
Addis Ababa - Ethiopia

المجلس الأعلى للشئون الإسلامية في إثيوبيا
إثيوبيا - أديس أبابا

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

ቁጥር Ref. No. ጠ/ም/0174/03/23/04
ቀን Date 02/12/2004

በኢ/ፌደ/ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ
የታክቲክ ምርመራ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- **በህገ-ወጡ 17ቱ ኮሚቴ አባላት ወይም ቡድን አማካይነት በአወሊያ እና በአንዋር የተፈፀሙትን ሕገ-ወጥ ተግባራቱ መግለፅ ይመለከታል፤**

1ኛ. የአወሊያ ዋና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ቁጥር አ/ዋ/ማ/ጽ/ቤት 03/00272/04 ቀን 21/11/2004 በዓራልን ደብዳቤ መሠረት:-

- በግቢው ባለፉት ስምንት ወራት በየሣምንቱ ጁመዓ በሚል ምክንያት የህገ-ወጥ ሙስሊሙ መፍትሔ አፈላላጊ ነን ብለው ለማፅዳት ምንም ዓይነት ፈቃድ ሳይጠይቁ ሕገ-ወጥ ስብሰባዎችን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ።
- በተጨማሪም ሐምሌ 8/2004 ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ህገ-ወጥ ሙስሊም ከአዲስ አበባ እና ከክልሎች በመጥራት ህገ-ወጥ ስብሰባ ለማድረግ በማቀዳቸው ከሐምሌ 6/2004 ከቀኑ 9:00 ሰዓት ጀምሮ በግቢያችን በሠደቃ ስም በሬዎችን በማረድ፣ ድንኳን በማዘጋጀት እና አዳራችውን በግቢው ለማድረግ መሰባሰብ መጀመራቸውና ህገ-ወጥ ድርጊቱም ለሚመለከታቸው የፀጥታ ኃይሎች በማሳወቃችን ከምሽቱ 3:30 ሰዓት ጀምሮ በቁጥጥር ሥር ሊውሉ ችለዋል።

በዚህም የደረሱት ጉዳቶች:-

- የመስጂዱ አጠቃላይ መስኮትና በር መስታወቶች አውድመዋል።
- የአዳራሹ የበር መስታወት እና በር ተሰብሯል።
- የካሌጁ የንብረት ክፍል በር ተሰብሯል።
- በወቅቱ ግምቱ በር 55,000.00 ብር በላይ የሚያወጣ ንብረት ወድመዋል በማለት አሳውቀውናል።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ


☎ 251 -11 - 3725965 /3728129/ 3726306/3726307
✉ 28441
Fax= 251 -11- 372 59 66
E-mail=eiasc@ethionet.et

☎ ٢٥١-١١-٣٧٢٥٩٦٥/٣٧٢٨١٢٩
٢٥١-١١-٣٧٢٦٣٠٧/٣٧٢٢٦٣٠٦
✉ ٢٨٤٤١
فاكس =٢٥١-١١-٣٧٢٥٩٦٦
إميل =@ethionet.et


583

http://ethcriminalawnetwork.com/

በአደባባይ ከሚደረግ ሰደቃ በድብቅ ሰው ሳያይህ ለድህ የምትሰጠው ሰደቃ (ምፅዋት አላህ ዘንድ የተወደደ በመሆኑና ከይስሙልኝ፣ ከጉራ ነፃ ስለሆነ ነው። እነዚያ ሰው እንዲሰማላቸውና ለጉራ ሰደቃ የሚያደርጉ ከአላህ (ሱ.ወ) ዘንድ ከፍተኛ ዛቻና ማስጠንቀቂያ የመጣባቸው ናቸው።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል።

እናንተ ያመናችሁ ሆይ እንደዚያ ገንዘቡን ለሰዎች ለማሳየት ሲል እንደሚሰጠውና በአላህና በመጨረሻውም ቀን እንደማያምነው ሰው ምፅዋቶቻችሁን በመመፃደቅና በማስከፋት አታበላሹ። (ምዕራፍ አልበቀራ አንቀጽ 264)

እንግዲህ ከአደባባይና በግልፅ የሚደረግ ሰደቃ (ምፅዋት) ከላይ ከተጠቀሰው ችግር ነፃ ካልሆነ ከንቱ ስራ፣ ውጤት አልባ መሆኑ በዚህ አያት (አንቀጽ) በግልፅ ተቀምጧል። ሰሞኑን በአዲስ አበባ እና በተለያዩ ክልሎች የአንድነት ሰደቃ በመባል ተሰብስቦ የግለሰቦችን ስም እያነሱ ማጣጣል እንደዚሁም መንግስትን ለመርገም ሲደረግ የነበረው ለአድማ እና ለሁከት የተዘጋጀ ድግስ እንጂ ሰደቃ አይባልም።

በመሆኑም ማብራሪያውን ፅፈን የላክን መሆኑን እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ሸኽ ዓ/ዲን ዓ/ዓዚዝ

የአገር አቀፍ ዑለማዎች ም ቤት

ዋና ፀሐፊ

الشيخ عز الدين عبد العزيز

الأمين العام في مجلس العلماء في اثيوبيا

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፈርማ

584

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ኢስላማዊ የፈትዋ ም/ቤት
مجلس العلماء للأفتاء والبحوث العلمية ف اثيوبيا

ቁጥር ኢ/ፈ/ም/ቤ/ 129/04
ቀን ሰኔ 25/2004

ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ም/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- <u>የሰደቃ ትርጉም እና ማብራሪያ ሁኔታ መግለፅ ይመለከታል</u>፤

ሰደቃ (ምፅዋት) ማለት በተለያዩ በጐ ሥራና መልካም ተግባር ላይ የአላህን ውዴታና ምንዳ ብቻ በመፈለግ የሚደረግ ሰደቃ (ምፅዋት) ተብሎ ይጠራል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል (ከገንዘብም የምትለግሱት (ምንዳው) ለነፍሶቻቹህ ነው የአላህንም (ውዴታውን) ለመፈለግ እንጂ፤ አትሹም፤ ከገንዘብም የምትለግሱት ሁሉ (ምንዳው) ወደ እናንተ ይሞላል። እናንተም አትበደሉም ምዕራፍ አልበቀራ አንቀፅ 272 በሌላ አያት (አንቀፅ) እነዚያን ሰደቃ የሚያበሉ ሰዎች ምልክታቸውን አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ በማለት ይገልፃል።

(ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ለምርኮኛም፣ ለእስረኛም ያበላሉ የምናበላቹህ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው ከናንተ ዋጋንም ምስጋናንም አንፈልግም። (የዘመናት ምዕራፍ ከአንቀጽ 8 — 9)

ከዚህ አንቀፅ የምንረዳው አንድ ሰው ሰደቃ (ምፅዕዋት) በሚያደርግበት ጊዜ ለድብቅ ተልዕኮ አስቦ ወይም ከሚሰጠው ሰው ክብርና ሞገስ ፈልጎ ወይም በዚህ ምፅዋት በእሱ ዓላማ እንዲሰለፍ አስቦ ካደረገ ትርፉ ድካም እንጂ ከአላህ (ሱ.ወ) የሚያገኘው ምንዳ የለውም። የሰደቃ (ምፅዋት) ዓላማ ስለሳተ።

ሰደቃ (ምፅዋት) አላህ ዘንድ የተወደደውና የበለጠ የሚሆነው በድብቅ የሚደረግ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል። (ምፅዋቶችን ብትለግሱም እርሷ መልካም ናት ብትደብቋትና ለድሆች ብትሰጧትም እርሷ ለናንተ በላጭ ናት። ከሐጢያቶቻችሁም ክናንተ ይብሳል አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

525

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

مجلس العلماء للافتاء والدعوة
والبحوث العلمية فى إثيوبيا

بسم الله الرحمن الرحيم

انما يخشى الله من عباده العلماء

የኢትዮጵያ ዑለማዎች
የፈትዋና ደዕዋ ም/ቤት

ቀን ሐምሌ 2ዐ/2ዐዐ4
ቁጥር ኢዐዘፈ/ዐ126/ዐ4

تاريخ ----------
رقم ----------

ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ም/ቤት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- ስለ አዛን ማብራሪያ እንድንሰጥ የተጠየቅነው መልስ መስጠትን ይመለከታል፣

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ም/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ጠ/ም/01ዐ2/03/22/04 ቀን 20/11/2004 ዒሔ፞ሜሌ 6/2004 ከሌሊቱ 5:40 እስከ 6:ዐዐ ድረስ በአዲስ አበባ በሚገኙ አንዳንድ መስጂዶች የተደረገውን አዛን ማብራሪያ እንድንሰጥ እና እንድንልክ የተጠየቅነው

አዛን ማለት በዓረብኛ ቋንቋ መሠረታዊ ትርጉሙ (ሊውሥ )ማሳወቅ ሲሆን ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ ) በሐዲሳቸው እንደገለፁት ደግሞ አዛን ማለት የሰላት ወቅት መግባቱን የሚያመለክት ሲሆን በዚሁም መሠረት ዙሁር ከቀኑ 6:30 -7:ዐዐ ሰዐት ይጀምራል ዙሁር ግን 2 አዛን ሲኖረው የ3ዐ ደቂቃ ልዩነት፣ አሱር ከቀኑ 9:30 -9:45 መግሪብ ከምሽቱ 12: 45 እና ዒሻ ከምሽቱ 2:ዐዐ ሰዓት እና ፈጅር አዛን በላት ናቸው ::

ለ. የሰላት ወቅት መደረሱን የሚያሰውቅ ሲሆን ከተጠቀሰው ለአታት ውጭ በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ መስጂዶች ሐምሌ 6/2004 ከሌሊቱ 5:40 እሰከ 6:ዐዐ የተደረገው የአዛን ጥሪ ጊዜ መሆኑን እንመለከታለን ::

ሸኽ ዒዘዲን ዓ/ዓዚዝ
የአገር አቀፍ ዑለማዎች ም ቤት
ዋና ዐሐፊ

الشيخ عز الدين عبد العزيز
الأمين العام فى مجلس العلماء

☎ 0113 72 81 32/ 0113 72 59 65
✉ 659 የፖስታ ኮድ 1110
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ

هاتف :- ٠١١٢٧٦١٠٢٦
الرمز البريدى ص ب ٦٥٩
اديس ابابا – اثيوبيا

E-mail=eiasc@ethionet.et

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ህዝቡ ለወከላቸው አካላት ተገቢ ካልሆኑ ሰዎች መቆጠብና ኮሚቴውን ህገወጥ ማለት ከኮሚቴው ጋር የሚወያየውን መንግስትንም መስደብ ነው የሚል ቁርጠኛ አቋም መያዙ::
- የመብት ጥያቄ ሂደቶቹ ሰላማዊ መሆናቸውን መመስከር ከብዙዎቹ ጥቂቶች ናቸው::

ይሁንና የሂደቶች ማማር የውጤት ማማርን ያመጣል ተብሎ ቢታመንም በእኛ ተጨባጭ ግን ምላሽ የሚጠበቅበት የየካቲት 26/2004 ቀጠሮ ብቸኛ የተሞላባቸው ንግግሮች፤ ከጥያቄዎቹ ግልፅነት በተፃራሪ በአሻሚና አተገባበራቸው ከህዝቡ ፍላጎት ተፃራሪ በሆኑ ውሳኔዎች የተሞላ ሆኖ ተገኝቷል:: ይህንንም አስመልክቶ የቅሬታ አቤቱታ ለሚመለከተው አካል የገባ ሲሆን ጥያቄዎቹ ተጨባጭ ምላሽ ይፈልጋሉና ለቀጣይ የስልጣን እርከኖች ቀረቡ::

VII. ለፌ/ጉ/ሚ/ር ሲቀርብ ህጋዊ የተባለ ህዝብ ለጠ/ሚ/ር ሲቀርብ ህገወጥ ሊሆን አይችልም!

ህዝበ ሙስሊሙ ላለፉት ሃያ አመታት ምንም አይነት ብአምነቱ ላይ የደረሰበት በደል የለም ለማለት አይቻልም:: ሆኖም ግን በጉዳዮቹ ላይ የመንግስት ቅርብ ድጋፍና ክትትል አልተለየውምና ገኖ የወጣበት አጋጣሚ እምብዛም አልታየም:: አንድ ህዝብ ምደራዊ ድሎቱን የሚቀንሱ፤ ማለሰባዊ ፍላጎቱን የሚቀናቀኑ የመብት ጥሰቶችን እስከመጨረሻው ሊችላቸው አልያም እስኪስተካከሉ ሊታገሳቸው ይችል ይሆናል:: ነገር ግን አማኝ በመሆንና ባለመሆን መካከል የሚገኙ ትላልቅ ገመዶች ሲበጠሱበት ግን ከነርሱ ቀድሞ የእርሱ እስትንፋስ መቆምን ይሻል::

ጥያቄዎቹን፤ አቅራቢዎቹንም ሆነ አቀራረባቸውን አለመልክቶ ለመንግስት አካላት ከቀረቡበት ግዜ አንስቶ እስከ የካቲት 26 ባሉት ግዜያት የተሰነዘሩ ክሶች፤ የተለጠፉ አፍራሽ ስያሜዎች በተለይ ከመንግስት አካል በይፋ አልተሰማም:: የጥያቄዎቹን አለመመለስ ግልፅ በሆነ አቤቱታ አቅርቦ በጥያቄዎቹም፤ በጠያቂዎቹና በአቀራረቡ ምንም አይነት የይዘት ለውጥ ሳይኖር ከ የካቲት 26 በኋላ ግን ከተለያዩ መስመሮች ፍፁም የማይጠበቅ እና ህዝብ በመንግስት ላይ ያለውን አመኔታ የሚንድ አፍራሽ ፕሮፖጋንዳዎች ተደመጡ:: ለነዚህ ፕሮፖጋንዳዎች ደግሞ የፌት አውራሪነቱን ሚና በመጫወት ላይ የሚገኘው የፌ/ጉ/ሚ/ር የተለያዩ የስራ ሃላፊዎች በመገናኛ ብዙሃን የሰጧቸው መግለጫዎችና ቃለመጠይቆች ናቸው:: ለአብነት ያህልም የመጋቢት 9



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

## VI. መንግስት የዜጎችን ጥያቄ የማድመጥ ግዴታ አለበት

በአንድ በኩል የመጅሊስ ውንጀላዎች መበርከት በሌላ በኩል የተለያዩ አካላት ፍርደ ገምድል ብይኖች ካነሳቸው ጥያቄዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው የሚተማመነው መብት ጠያቂው ህዝበ ሙስሊም ለጥያቄዎቹ መልስ ያፈላልጉለት ዘንድ በወከላቸው ኮሚቴዎች አማካኝነት የተለያዩ የመንግስት መስሪያቤቶችን በር አንኳኩቷል። በነዚህ ሂደቶች ውስጥ ሳይጠቀሱ የማይታለፉ ነጥቦች አሉ፡-

- ህዝበ ሙስሊሙ የመብት ጥሰቶቹ መንስኤ ሙሉ በሙሉ የመጅሊስ አመራሮች እንደሆኑ ያምን ነበር።
- መልስ ለማግኘት የሚቻለው በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ብቻ ነው ብሎ አምኖ ተንቀሳቅሷል።
- ከጥያቄዎቹ ፍትሃዊነት፤ ግልፅነትና መልስ ሊሰጠት ካላቸው ቀላል ይዘት አንፃር ፈጣን ምላሽ ማግኘት ቢቻልም የተሰጡትም ረዥም ቀጠሮዎች በትእግስት በመጠባበቅ ለሀገ ያለውን ተገዥነት በተግባር አሳይቷል።
- መልስ ይነገርበታል ተብሎ በሚገመተው የመሰብሰቢያ ስፍራ በቋሚነት በመገኘት ለጥያቄዎቹ መመለስ ያለውን ፅኑ አቋም አሳይቷል።

ከላይ ካነሳናቸው ነጥቦች ተቀራራቢ በሆነ መልኩ ከመጅሊስ የተለመዱ ውንጀላዎች በስተቀር ቀድሞ የነበሩት የአንዳንድ ባለስልጣናት የተሳሳተ ውንጀላ እና የተዛቡ ሚዲያ ዘገባዎች ጥያቄዎቹ ቀርበው የምላሽ ቀጠሮ እስከተሰጠበት ድረስ ባሉት ግዜያት ቢያንስ ጋብ ያሉበት ወቅትም ነበር።

በሂደቱ በመንግስት በኩል ከተንፀባረቁት አቋሞች ውስጥ

- ጥያቄዎቹን ለማድመጥ ያሳየው ቁርጠኝነት።
- የጥያቄዎቹን አግባብነትና እንደ መንግስት መልስ የሚሹ መሆናቸውን እምነት ማሳደሩ።
- ጉዳዩን በጥልቀት ለማየትና ሰፊ ግዜ በመውሰድ ምላሽ ለመስጠት ቻል መግባቱ።



ECLN
588
http://ethcriminalawnetwork.com/

በይፋ ወደ ተቃውሞ ገብተናል፡፡ ባለስልጣናቱ እንደተናገሩት ‹‹ስልጠናውን መስጠት ያስፈለገው እምነታቸውን አጥብቀው የያዙ መስሏቸው ሳያውቁት በአክራሪነትና ፅንፈኝነት መረብ ውስጥ እየተገፉ የገቡ በመኖራቸው እነሱን ‹‹ወደ ቀጥተኛው እስልምና›› ለመመለስ እንጂ ‹‹እንደ ወሃብያ ያለ ወሮበላን አስር ቤት ለማኘር›› ስልጠና አስፈላጊ አለመሆኑን፤ በዚህም ስልጠና ምዕመኑን ወደ ቀጥተኛው እስልምና ሊመሩት እንደሆነ ከፖለቲካ መዛህፍት የተቀመመ ሃይማኖታዊ ትንታኔ በመስጠት የስልጠናውን አላማ ጥርት ባለ ቋንቋ አስረድተውናል፡፡ በባለስልጣናቱ ‹‹ ጠርዘኛ፤ አክራሪ፤ ወሃብያ›› ተብሎ የተፈጠረው ማደናገሪያ ስያሜ ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ይሏታል ጅግራ እንደሚሉት ብሂል በመጅሊስና አጋሮቹ የጥፋት ወጥመድ አልያዝ ያለውን ህዝበ ሙስሊም መጠሪያ ተደርጎ በመወሰድ ላይ ይገኛል፡፡

አመት ሊሞላው ጥቂት ወራት የቀሩት የመብት ጥሰት ከተጀመረ አንስቶ መጅሊስ በደለኝ፤ በመጅሊስ የተሳሳተ መረጃ አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት ጣልቃ ገብነት ታይቶባቸዋል ሲል ለነበረው ህዝበ ሙስሊም ከባድ መርዶ ነገሩት፡፡ በአንድ በኩል የበርካታ ባለስልጣናት በስልጠናዎቹ ወቅት ህገመንግስትን ከማስተማር እና ፀጥታ ከማስጠበቅ የዘለለ ሚና አልነበረንም መባሉን የሻረ ግልፅ አንድን አስተምህሮ የማስፋፋት ሃላፊነት መ/ቤቱ ሲወስድ ተበዳዩን ህዝበ ሙስሊም ክስህን በመጅሊስ ላይ ሳይሆን በፌ/ጉ/ሚ/ር ላይ አነጣጥር የሚል ከባድ መልእክት አስተላልፏል፡፡ ዛሬ ላይ ቆም ብለን ስናስበው ፌ/ጉ/ሚ/ር ለህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ሊኖረው እንደማይችልም መረዳት ከነበረብን ግዜ በጣም መዘግየታችን አውቀናል፡፡ የረፈደ ቢመስልም ዛሬ ግን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ዳግም ላንማፀን ለጥያቄአችን ትክክለኛ መልስ ከምንጠብቅበት የመንግስት የስልጣን እርከን ተሸጋግረናል፡፡

ይህን ምክንያቱ ያልታወቀ የአስተምህሮት መረጣ ውስጥ ገብተናል ካሉት ጀምሰምን ተከትሎ ህዝበ ሙስሊሙ ላይ ሁለት አይነት አስተሳሰብ መስረፅ ጀመረ፡፡ በአንድ በኩል ጉዳዩን ተጋፍተን የማንዘልቀው የማይከሰሰውና የማይገሰሰው መንግስት ጋር መላተም ነው ሲሉ በሌላ መልኩ እና አብዛሃኛው ህዝበ ሙስሊም አቋም ግን ህግ ባለበት ሃገር ማንም ህገወጥ እንዲሆን አይፈቀድለትምና አማኞች ተስፋ አይቆርጡም ብለን በጥያቄአችን እንገፋለን የሚል ነው፡፡

## VIII. መንግስት በጉዳዩ ላይ ያለውን ግልፅ አቋም ያሳውቀን

ከላይ እጅግ በጥቂቱ ለማየት እንደሞከርነው ኢህአዴግን ወክለው በየመድረኩ የተገኙት ባለስልጣናት ያሳዩት የተደበላለቀ አንዳንዴም ጥላቻና ንቀት የተሞላበት ጣልቃ ገብነት ዛሬም



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሪፖርተር ጋዜጣ ከሚ/ሩ ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም ጋር ያደረገው ቃለምልልስ ያስነበባቸው አቋሞች ግርምትንና ትዝብትን የፈጠሩ ክስተቶች ናቸው፡፡

የስራ ሃላፊዎቹ በተለይም የፌ/ጉ/ሚ/ር ሚኒስትሩ የነዚህን ግልፅ የመብት ጥሰት ጥያቄዎች ከዚህ ቀደም በይፋ አግባብነት ያላቸው ሲሉ እንዳልተደመጡ እና ጠያቂውንም ህዝበ ሙስሊም ሰላማዊነቱን መመስከራቸውን የዘነጉት በሚያስመስል መልኩ ‹‹አሁን ለመጨረሻ ግዜ ምሽጋችን ተመታ ማለት ነው፡፡ ይኼ ተመታ ማለት የአይዲዮሎጂው መፍለቂያና ማስተማሪያ ማዕከልና የእኛ ህልውና አበቃ ማለት ነው በሚል ነው የመጨረሻ የሞት ሽረት አድርጎ የመንቀሳቀስ ስራ ውስጥ እየተገባ ነው ያለው›› ሲሉ አዲስ አበባ በአንድ ቦታ ብቻ የሚሰበሰቡ መቶ ሺዎችን ማብጠልጠል ቢዳፍሩም በመላ ሃገሪቱ መሰል ተቃውሞ ይዘው ቢሯቸውን ላንኳኩ የክልል አቤቱታ አቅራቢዎች ግን ያሉት ነገር አልነበረም፡፡ ከየካቲት 26 በፊት ሰላማዊ የነበረው ህዝበ ሙስሊም በሳምንታት እድሜ እንዴት ወደ ‹ምሽጉ የፈረሰበት ፅንፈኛ› ሊቀየር እንደቻለ ለሰሚው ግራ ነው፡ ፡ እንደፀሃይ ብርሃን ፍንትው ያሉት እጅግ ግልፅ ጥያቄዎችስ በምን አይነት አተረጓጎም የእስላማዊ መንግስት ማቋቋ ተብለው ሊወሰዱ እንደሚችሉ ማንም ሊረዳው አይችልም፡፡

በሃላፊዎቹ የተነገሩት እጅግ አደገኛ ነጥቦች በሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን በሌሎች እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ልብ ውስጥ ሊፈጥር የሚችለው ውዥንብር እና እሱን ተከትሎ ሊመጣ የሚችለው ህዝባዊ ቀውስ ሃያል በሆነ ነበር፡፡ የጥያቄዎቹን ግልፅነትና ይዘት አቅራቢው ህዝበ ሙስሊም በተረዳበት መጠን የሌሎች እምነት ወገኖች መረዳታቸው በአቅራቢዎቹና በጥያቄዎቹ ላይ የታየውን ቅፅበታዊ የአተረጓጎም አደገኛ ለውጥ መሰረተ ቢስነት ሊያጋልጥ ሊረጋገጥ ችሏል፡፡ አመራሩ የህዝብ የሰላ ጫፍ ሆኖ አርቆ ማስተዋል ሲጠበቅበት የተቃውሞ ሰልፎች በታየባቸው የመንግስት ተወካዮች ብናፍርም ህዝብ የዲፕሎማቲክነቱን ሚና ሲወጣ ማየቱ ግን በዜግነት የሚያኮራ ታላቅ ብስራት ነው፡፡

መረሳት የሌለበት ሌላውና ትልቁ ነጥብ ደግሞ ሚ/ር መ/ቤቱ በሃገሪቱ ከሚገኙ የስልጣን እርከኖች አንዱ እንጂ ብቸኛና የበላይ አይደለም፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ የእምነቴ ህልውና ነው ብሎ በሚያምንበት ነጥብ ላይ በተካሄደው የመብት ጥሰት እንዲቆም ጥያቄዎቹን ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት አቅርቦ መልሱን እንደከዚህ ቀደሙ በትእግስት በመጠባበቅ ላይ ሳለ በምን እይታ ህገወጥ ሊባል ይችላል፡፡በእርግጥ የስልጠናው መባቻ አካባቢ የተለያዩ ባለስልጣናት በይፋ የተናገሩትን አስተምህሮቱን መቃወም በህግ ተጠያቂ የሚያደርግ ህገ ወጥ ተግባር መሆኑን የሚያስይዙ ንግግሮች በርካታ ቢሆኑም የባለስልጣን ስህተት በእምነታችን ላይ እንድንፈርድ ስለማያደርገን



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

2. በመጅሊስ ፊታውራሪነትና ባንዳንድ የመንግስት አካላት ድጋፍ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ በግዴታ እየተጫነ ያለውን የአህባሽ አስተምህሮና አስተሳሰብ ሙሉ ለሙሉ እንዲቆም። አህባሽ እንደማንኛውም የእምነት ተቋም ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ እንደሚችል በህገ መንግስቱ በግልፅ የተቀመጠ እንደመሆኑ በሙስሊሙ ተቋማት ላይ ግን ሙሉ ለሙሉ እጁን እንዲያነሳ እንጠይቃለን።

3. አወሊያ ብቸኛ የሙስሊሙ ሚሲዮን ት/ቤት ሲሆን ይህ ተቋም በውስጡ ብዙ ማዕከላት በመያዝ ለሙስሊሙ ህ/ሰብ ዘርፈ ብዙ ግልጋሎቶችን ሲሰጥ ቆይቷል። ይህ ተቋም የህዝበ ሙስሊሙ ብቸኛ አንጡራ ሀብት ነውና በህዝበ ሙስሊሙ ሊተዳደር ይገባዋል። በመሆኑም ይህን ተቋምበአደባባይ የወረሰው መጅሊስ ተቋሙን ለህዝበ-ሙስሊሙ በመመለስ እጁን ከአወሊያ እዲያነሳልን እንጠይቃለን።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

591

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ጥያቄዎቹ እና ጠያቂዎቹ ላይ የተፈጠረው የማዋከብና የማሸማቀቅ ተግባር ጠያቄዎቹን በስልትም ሆነ በሃይል ማስቆም ቢሳካለት እንኳን እነዚህ ነባና ፍትሃዊ ጥያቄዎች ግን በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ዘመን ሰሚ ያጡ የህዝበ ሙስሊሙ ፍትሃዊ ድምፆች ተብለው በታሪክ መዘገባቸው አይቀርም፡፡

## XI. ዛሬም ለጥያቄዎቻችን በቂና ግልፅ ምላሽ ይሰጠን ስንል እንጠይቃለን

ባሳለፍናቸው የመብት ጥያቄ ሂደቶች የጥያቄዎቻችንን ይዘትና ፍትሃዊነት ለማስረዳት ያልፈነቀልነው ድንጋይ አልነበረም፡፡ ለመንግስት አካላት እና ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ጥያቄዎቻችን ምን እንደሆኑ፤ ምላሽ አገኙ የሚባሉትስ መቼ ነው የሚለውን በማያሻማ አገላለፅ በማስረዳታችን ሁሉም ማለት በምንችልበት ደረጃ የየትኛውም እምነት ተከታይ ወገኖቻችንን ‹ጥያቄዎቻችሁ የመብት ጥያቄዎች ናቸው የመንግስትን ምላሽ ይሻሉ› የሚል አኩሪ የህዝብ ለህዝብ አጋርነት አፀፋ ለማግኘት ችለናል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ሁሉም ማለት ባንችልም በሂደቱ ውስጥ እጃቸው ያለበት አብዛኞቹ ባለስልጣናት ለህዝብ ከህዝብ ይልቅ የሚያውቁለት እነርሱ እንደሆኑ የሚያስመስል፤ ሚሊዮኖች የሆኑ የመብት ጠያቂዎችን የጥቂት ፅንፈኞች ጀሌዎች አስመስሎ በማወጅ ብዙሃንን ያላዋቂ አድርጎ የመሳል ችግር፤ የመብት ጠያቂውን ህዝበ ሙስሊም እምታቸውን የታደጉ መስሏቸው የተታለሉ ናቸው የሚል ሙስሊሙን ያላምነቱ ባዳ አድርጎ የማቅረብ አጓጉል አካሄድ ተስተውለዋል፡፡

አልፎ አልፎም የጥያቄዎቹን ይዘትና የአቀራረብ ሰልታቸውን በማድ በመጠምዘዝ አቅጣጫ ለማሳት ሲሞከርም አስተውለናል፡፡ እነዚህ ሁላ ነገሮች ግን የተነሳበትን ለሚያውቀው ህዝበ ሙስሊም መድረሻውን አያስጠፉትምና መቼም አይሳካም፡፡ ጥያቄዎቻችን ለማንም የማይከብዱ እጅግ በጣም ቀላልና ግልፅ ቢሆኑም ዛሬም ደግመን እንደሚከተለው አስቀምጠናቸዋል፡፡

1. በህዝበ ሙስሊሙ ይሁንታ ባላገኙና ባልተመረጡ በጓሮ በር ገብተው የሙስሊሙን ሁለንተናዊ ሰብዕና በመግፈፍና የመጅሊስን ተቋም በብልሹ አሰራር እየመዘበሩ ያሉትን የመጅሊስ አመራሮች ሙሉ በሙሉ ተወግደው ሙስሊሙ ማህበረሰብ ለሀይማኖቱም ለሃገሬም ይጠቅመኛል የሚለውን መሪ በየመስጂዱ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፤ ህዝብ በተሰማማበት የምርጫ ስረዓት፤ አስመራጭ፤ ታዛቢ፤ አስፈጻሚ ነጻ፤ ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ እንዲካሔድ ይፈልጋል፡፡



ECN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለግዜውም ቢሆን በቂ ምላሽ አለማግኘቱ በጥያቄዎቻችን ላይሆን ምላሽ መስጠት በሚገባቸው አካላት ላይ ነው እንድናፍር የሚያደርገን፡፡ ለዚህም ትልቅ ማስረጃ መሆን የሚችለው የቅርብ ግዜ ትዝታችን የሆነውና የ1966ቱ መላው የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መሰረታዊ የመብት ይከበርልኝ ጥያቄ ነው፡፡ ምንም እንኳን ወቅቱ የመብት ጥያቄን ሊያውም ሙስሊሙ ህብረተሰብ ለማንሳት ይደፍራል ተብሎ በማይታሰብበት፤ የስልጣን ዙፋኑ ሰማያዊ በሆነ ሹመት የተደላደለ ተደርጎ የሚቆጠር አምባገነን የአፄ ስርዓት በነበረበት ወቅት ለኛ ለሙስሊሞች የጨለማውን ዘመን የማስቆምና ያለማስቆም የህልውና ጥያቄዎችን ያነገበ ታሪካዊ ክስተት ተመዝግቧል፡፡

በዚያን ወቅት የተነሱት ጥያቄዎች ካላቸው እጅግ ወሳኝ ይዘትና ስርዓቱ ከነበረበት እጅግ የገዘፈ ፀረ ኢስላም አስተሳሰብ አንፃር ሲቃኝ የማይጠበቅ ግን ደግሞ የእኛ የሙስሊሞችን ታሪክ የቀየረ፤ ‹በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሙስሊሞች› ከመባል ‹ሙስሊም ኢትዮጵያውያን› ያስባለን፤ በወሳኝ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይም ቀጥተኛ ተሳታፊና ተጠቃሚ የመሆን መብትን ያጎናፀፈ ነበረ፡፡ የደርግ ስርዓትም እንደ አቋም ፀረ ሁሉም ሃይማኖት ቢሆንም ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ግን ለዘመናት የተነፈጉትን ከሌሎች አቻ ሃይማኖቶች እኩል መቆጠራቸውን የሚያረጋግጡ አያሌ ለውጦችን ያገኙበት ሁኔታ ነበረ፡፡ ዛሬ ዛሬ የእምነት ነፃነት ዳግም ጥያቄ ለመሆን በማይችልበት መልኩ መልስ አግኝቷል ተብሎ በሰፊው በሚቀነቀንበት የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. መንግስት ዘመን እጅግ ቀላል ግን ደግሞ ወቅታዊ የሆኑ የመብት ጥያቄዎቻችንን የሚያደምጥና በቀናነት አጢኖ አጥጋቢ ምላሽ የሚሰጥ አካል አልተገኘም፡፡ ሃገራችን በብዙ መልኩ ወደፊት ስትራመድ የሙስሊሞችን የመብት ጥሰት ለማስቆም ወሳኝ አመራር መታጣቱ ግን ግዜውን ከ 38 አመታት በፊት በያዝነው ሳምንት ላይ ሙስሊሞች ላነሳነው የመብት ጥያቄ የወቅቱ አምባገነን መሪዎች የሰጡንን ጆሮ ያህል እንኳን ማጣታችን ፍትህ በስርዓቱ አተረጓጎም ለሙስሊሞች ሲሆን ይለይ ይሆን ብለን እንድንጠራጠር አስገድዶናል፡፡

ጉዳዩን በቀና አእምሮ ስናስበው ደግሞ ‹አስቀድሞ የበሰለ ፍሬ አለቅድሞ ይቆረጣል› የሚለው ብሂል እውነት ነውና ይህን መሰሉ ሙስሊሙን የማሸማቀቅና የማቅለብ ሴራ ላይደገም ይቀበር ዘንድ ዋስትና የሚያስፈልገው መልስ ስለሚፈለግ ለዚህ የሚሆን ትዕግስትና ፅናት ህዝበ ሙስሊሙ የተማረበትም ታሪካዊ ሃገራዊ አጋጣሚ ነው፡፡ በትጥቅ ትግል ወቅት ያገኘውን የአላማ ፅናት ይለውን ፋይዳ የሚያስረዳ ትምህርት ያስተማረን ኢህአዴግ በሰላማዊ የመብት ጥሰት ይቁም ጥያቄያችን ላይ ይህ መሰሉን አይሰራም ብሎ እንደማይሞግተን እናምናለን፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎቻችን ሁሉ ምላሽ አግኝተው ደማቅ ታሪክ እንዲሆን ስንመኝ ይህ ላይሆን ቀርቶ የመብት



593

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሸኸየውን አስተምህሮ እውነተኝነቱን የመሰከሩት ባለስልጣናትን ጨምሮ ሌላ ማንም አካል ፈለጉን የመከተል መብቱ የተጠበቀ መሆኑን የሃገራችን ህገመንግስት ይደነግጋል፡፡ እኛም እናከብረዋለን፡፡ ሆኖም ግን በመንግስት የ‹ጥናት ሰነዶች› የ‹አክራሪ እስልምና› መገለጫዎች ተብለው ፍርደ ገምድል የተበየነባቸው በርካታ እስላማዊ ክንዋኔዎችና ማህበራዊ ትስስሮች ሙስሊሙን ለማሸማቀቅ ማንም እንዳሻው እየተጠቀመበት በመሆኑ ‹የጥናቱን› ባዶ ይዘት እንደምንኮንነው ሁሉ በሸኸየው የተፈበረከውን ‹አዲስ የተጠና ሃይማኖትም› መቃወማችን ህገ መንግስታዊ መብታችን ነው፡፡ ይህንንም ህገመንግስታዊ መብት መጠቀምና በወገኖቻችን መስዋዕትነት የተቋቋሙ የሃይማኖት ተቋሞቻችን ከምንጩ የተቀዳው ነባሩ እስልምና ሳይሆን የዚህ ‹አዲስ የተጠና ሃይማኖት› መሰበኪያ መሆናቸውን መቃወም ‹‹ወሃብያዎች፤ አክራሪዎች፤ ፅንፈኞች፤ ፀረ ሰላሞች›› እና ሌላ ብዙ ብዙ እየተባልን አንዳንዴም ይህን ተከትሎ በታችኛው የአስተዳድር መዋቅር አካባቢ የሚወሰዱ ሚናቸውን ያልለዩ አስተዳደራዊ በደሎች እየተበራከቱ ነውና እነዚህ የማሸማቀቅና የማዋከብ አስተሳሰቦችና ተግባራት መቆም በማስቆም የዜጎቹን መብትና ደህንነት ሊያስጠብቅ ይገባዋል እንላለን፡፡

በሌላ በኩል የአስተሳሰቡ ፈላስፋም ሆኑ እስከ አሁን ያሉዋየትኛውም ሃገር ዜጋ የሆኑ ተከታዮቻቸው የሃይማኖት መስመራቸውን ‹‹አህባሽ›› የሚለው መጠሪያቸው የሚታወቅና የሌላው አለም ተከታዮቻቸው ሳይቀሩ በዚህ ስያሜ እንደሚኮሩበትም በይፋ መግለፃቸው በተጨባጭ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ሌላ ድብቅ አላማ ያለ በሚያስመስል ሁኔታ የአስተምህሮቱን አምላኪዎች ‹‹ሱፊ-ሱኒ›› ተቃዋሚዎቹን ደግሞ ‹‹ወሃብያ፤ አክራሪ....›› እያሉ መከፋፈልና ማዋከብ ለሃገርም ለህዝብም አይበጅምና ይቁም እንላለን፡፡ በተግባር እንደምናየውም የባለስልጣናቱን አይዞህ ባይነት ተንተርሰው በየትኛውም የኢትዮጵያ ታሪክ ያላየነውን የትኛውም ግፈኛ ባለስልጣን በህዝባችን ላይ ያልፈፀመውን ሙስሊሙን የመሰነጣጠቅ እስትራቴጂ ‹‹ሱፊ›› አልያም ‹‹ወሃብያ›› ብለህ ሚናህን ለይተህ ተመዝገብ እየተባሉ ፎርም ማስሞላት መጀመሩ ከዚህም አልፎ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ሙስሊም አባላትን ‹‹ወይ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ን አልያም ወሃብያን ምረጥ›› እያሉ ማሸማቀቅ ተለምዷልና ይህ ሙስሊሙን የማዋከብና የማሸማቀቅ ጥቁር ታሪክ በእንጭጩ መቀጨት ለጋራ ኢትዮጵያችን ይበጃልና ግዜ አይሰጠው እንላለን፡፡

## X. ሁሉም ዘመናት ያልተሰሙ የንፁሃን ዜጎች ድምፆች አሏቸው

ታሪክ እንደሚያስተምረን አድማጭ ያገኙ ጩኸቶች ሁሉ ትክክለኛ፤ መፍትሄ ያጡ ብሶቶች ሁሉ ደግሞ መሰረተ ቢስ እንዳይደሉ ነው፡፡ የህዝበ ሙስሊሙ የእምነት ነፃነት ጥሰት ይቁም አቤቱታ



ECHR
594
http://ethcriminalawnetwork.com/

አለቀ እንዴ› የሚያስብሉ ‹ጥናት› ተብለው በቀረቡ የአናቅፅ ሰነዶች ፣የአክራሪ እስልምና› መገለጫዎች ተብለው የተነገሩን በዛሬው የመረጃ ትስስር አለምን ጉድ ባደረገበት ዘመን ቀርቶ በድንጋይ ዳቦ ዘመንም አድማጭ ያገኛሉ ብሎ መገመት ያዳግታል፡፡ አንዳንድ ባለስልጣናት የህገመንግስት፤ የፖሊሲና እስትራቴጂ አተገባበር የሚያግዙ መፃህፍትና ጥናቶችን ሳይሆን በአረበኛ የተዘጋጁ የእስላማዊ መፃህፍትን ከጫፍ እስከጫፍ አጥላብጠናል በሚያስብል ድፍረት በቀጥታ እንደነገሩን የአብደላህ አልሃረሪ ፈለግ የሚሰብከው ‹የአክራሪነት አስተሳሰብን በቅዱስ ቁርዓንና ሃዲስ አስተሳሰብ ቀይረው ማስተማር ነው› ብለውናል፡፡ ግና የእምነቱ ባለቤቶችና በውስጥ ያሉ የእውቀት ባልተቤቶች ብቃቱ ስላላቸው ብቻ ሳይሆን ክብራቸውም ስለሚፈቅድላቸው በአብደላህ አልሀረሪ አቋም ላይ ፈትዋ ሰጥተዋል፡፡ የሸኸየውን አስተምህሮ ዘመን ተሸጋሪውን እስልምና ለፁለቱም አለማት ፈጣሪ ሳይሆን ምድራዊ ስልጣንን ለተቆናጠጡ እንደ መጅሊስ አመራር ላሉ የስልጣንና የነዋይ አፍቃሪዎች እንዲሆን በርዘውና ከልሰው አዘጋጅተውታል፡፡ ይህም አስተሳሰብ የአቋማቸው ተቀናቃኝ ለሆነው ህዝበ ሙስሊም መድፈቂያ የተዘጋጀ ‹የተጠና ሌላ አዲስ ሃይማኖት› እንደሆነ በማይናወጥ መረጃ አስረግጠዋል፡፡

የፅንፈኝነት አስተሳሰቦችና ድርጊቶች እንዳይባባሱ መንግስት ህግ በማስከበሩ ረገድ ካለው ሚና ባልተናነሰ ሁኔታ የሃይማኖት ተቋማትም ወሳኝ ሚና መጫወት ይገባቸዋል ብለን እናምናለን፡፡ የሃይማኖት ተቋማቱ አክራሪነትን በብቃት ለመከላከል የሚችላቸው ግን በቅድሚያ በህዝቡ ቅቡልነትን አግኝተው ሁሉም እንደ አባትና መመለሻ አድርጎ ሊቀርባቸው የሚያስችል ተቀባይነትና ጥንካሬ ሲኖራቸው ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ህዝብን ለማስተማር ከእምነቱ ሰፈነገጠ አስተሳሰብ በማጥመቅ ሳይሆን ከእምነቱ ምንጭ በተቀዱ ድንጋጌዎችና መመሪያ በዘመቻ መልክ ሳይሆን በተጠናና ሁሉን ባማከለ አተገባበር፤ መንግስት ሃይማኖትን ሸፋን አድርጎ በአንዱ እምነት ላይ ብቻ በሚያደርገው ጣልቃ ገብነት ሳይሆን ሁሉም የሃይማኖት ተቋማትና ምዕመኑ በየእምነቶቻቸው ውስጥ ስልት ቀይሰው ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ ያጠፋውንም ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲያገኝ የሚያስችል መንገድ ሲኖራቸው ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በየትኛውም ቦታና ግዜ በማንኛውም አካል የሚፈፀምን ‹የጥፋት፤ የሽብር እና የእልቂት› ተግባራት እንደምናወግዘው ሁሉ ‹የአክራሪነት አስተሳሰብን ለመቀልበስ› በሚል ሰበብ ዜጎችን የእምነት ነፃነት በመንፈግ የመንግስት ባለስልጣናት የሚያሳዩዋቸውን ያልተገሩ የንግግርና የተግባር ጣልቃ ገብነትንም እናወግዛለን፡፡



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

ላይ የመንግስት ትክክለኛ አቅጣጫ ነው ብለን ከመውሰዳችን በፊት በይፋ ለመስማት የምንጠብቀው ሌላ የስልጣን እርከን እንዳለ ይሰማናል፡፡ እነኚሁ ባለስልጣናት በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የፓርቲያቸውን ትክክለኝነት ከሚያስረዱበት እጅግ በተሻለ ፅናት የአብደላህ አልሃረሪን አስተምህሮ ትክክለኝነትና የነባሩ የኢትዮጵያ እስልምና ገፅታ አድርገው ለመጋት መሞከራቸው በእምነታችን ላይ መሳለቅ ብቻ ሳይሆን በታሪካችን ላይም ማፌዝ ነውና ዳግም ላይነሳ ይብታ እንላለን፡፡

ጉዳዩ የእምነት ህልውናን ያዘለ ቀይ መስመር ነውና የሃሰት ፕሮፖጋንዳ በየትኛውም ምድራዊ በሆነ ከፍተኛ በሚባል የስልጣን እርከን ላይ ባለ አካል ቢደጋገም ነገሩን እውነት ሊያስብለው የሚችልበት በር ላይከፈት ከተዘጋ የኒያ ታላቅ ነቢይ የነብዩ መሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና የባልደረቦቻቸው እንዲሁም ከእርሳቸው በኋላ ቅኑን መንገድ የተከተሉት ትውልዶች የህይወት ታሪክ አስተምሮን አልፏል፡፡ በነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ‹‹የእስልምናን መንገድ እንድተው ፀሃይን በቀኝ እጄ ጨረቃን ደግሞ በግራ እጄ ላስቀምጥልህ ቢሉኝ እንኳ አላህ እውነትን እስኪያሰፍን አሊያም እስክ ሞቴ ፍንክች አልልም›› የተባለለት የእውነት ጎዳና እስልምና ዛሬ በመጅሊስ አመራሮች በሽራፊ ሳንቲም ገበያ ላይ ወጥቷል፡፡ ድንበር ባለፉ ባለስልጣናትም ከአንድሺህ አራት መቶ አመት በፊት ሰዎች ህይወታቸውን የሰዉለት ቀያቸውን ጥለው የተሰደዱለት እስልምና የሸኽ አብደላህ አልሃረሪ ፊለግ ነው መባል የእስልምናን እውነተኝነት እንደ መንግስት ያፀደቀች የመጀመሪያዋ ሃገር ኢትዮጵያ ዛሬ ደግሞ አስተምህሮቱን በማጥላላት የመጀመሪያዋ ልትሆን ይሆን ያስብላል፡፡ ይህን ለማለት ግን አሁንም የቀረን የስልጣን እርከን አለና መንግስት ሊከተለው በሚችለው በማንኛውም የውስጥ አሰራር ድንበር ያለፉትን ባለስልጣናትን በማረም ፍትህን በሰላምና በትዕግስት እየጠበቀ ላለው ህዝበ ሙስሊም አቋሙን ግልፅ ያድርግልን እንላለን፡፡ የህዝብን ቅሬታ መስማት ውለታ ሳይሆን የመንግስት ትልቅ ስራ ነውና መንግስት ግዴታውን ይወጣ፡፡

## IX. ሙስሊሙን ያለአግባብ በስጋት መፈረጅ፣ ማዋከብና ማሸማቀቅ በአፋጣኝ ይቁምልን

ከላይ ባነሳናቸው እጅግ በጣም ጥቂት ነጥቦች መንግስት ‹‹የጥናት ሰነድ›› እያለ በየመድረኩ የሚያቀርባቸው ፅሁፎች በአጠናን ስልትም ሆነ በመረጃ ተዓማኒነታቸው ጉድለት ‹ጥናት› የሚባለውን ደረጃ ፈፅሞ ሊያገኙ የማይገባቸው እንደሆኑ መረዳት አያዳግትም፡፡ እነዚህ በሳይንሳዊ ዘዴ ያልተተነተኑ፣ መረጃቸው ተበጥሮና ተነፍቶ እውነታው ከእንክርዳዱ ያልተለዩ ‹ምነው ምሁርሽ



http://ethcriminalawnetwork.com/

የመብት ጠያቂዎች ስብስብን አስመልክቶ በተለይም የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት አካባቢ በመጅሊስ አመራሮች እና አንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን የተሰጡት ስያሜዎች ከተሰብሳቢዎቹ ማንነትም ሆነ ከተጠየቁት ጥያቄዎች ጋር ምንም የማይዛመድ ነበር፡፡ ‹‹የግል ጥቅም ፈላጊዎች፤ ድብቅ አጀንዳ ያላቸው፤ የተማሪዎችን ጥያቄ አንተርሰው የተሰባሰቡ ፅንፈኞች›› እና የመሳሰሉት የህዝቡን ቁስል ከማዳን ይልቅ እያመረቀዙት የስቃይ ጩኸቱ ይበልጥ እንዲበረታ አደረጉት፡፡ ከዚህ በተቃራኒ መንግስት በጉዳዩ ላይ ህዝቡን ለማወያየት ባደረጋቸው ሙከራዎች የብዙሃኑን ስሜት በትክክል ያደመጠ ቢመስልም ‹‹መጅሊስ ተሳስቷል›› ከማለት ይልቅ ‹‹ሙስሊሙ አማኝ ተሸውዷል›› የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን የሚያሳዩ አመላካች ነገሮች ነበሩ፡፡

በዚህም የህገመንግስት ሉአላዊነት የሚረጋገጠው በህዝብ ሉአላዊነት እንደሆነ የሚያምነው ኢህአዴግ፤ የሚወስናቸው ሁሉም ውሳኔዎች ከህዝብ ጥቅም አንፃር እንደሚቃኛቸው ያስረዳን መንግስት፤ ከራስ በላይ የህዝብ ጥቅምን ማስቀደም ለዚህም ሲባልም ብዙ መስዋዕትነትን መክፈል እንደሚገባ አምናለሁ ያለን ኢህአዴግ በሙስሊሙ አጀንዳ ሲሆን ከህዝብ በላይ ለህዝብ የማውቀው እኔ ነኝ በሚሉ ባለስልጣናት በየመድረኩና በየሚዲያው ተወክሎ ስናገኘው በመንግስታችን መዋቅር ውስጥ በወሳኝ ሃገራዊ አጀንዳዎች ላይ እንደሀ ማማከር ልመራሮች መኖራቸው ልባችንን ነክቶታል፡፡

የነዚህን ሚዛን የሳቱ አመራሮችን አቋም በመንተራስ ‹‹የመብት ጥያቄዎቹ ፅንፈኞች ናቸው፤ መንግስትም ከጎናችን ነው›› የሚሉ ማስፈራሪያዎች የመጅሊሱ የዘወትር መፈክሮች ሲሆኑ ‹‹ጥያቄዎቻችን ህጋዊ ናቸው፤ ፈጣሪም ከጎናችን ነው›› የሚሉ ድምፆች ደግሞ በህዝቡ ወገን በረቱ ፡፡ አግባብ ያልሆነ ስልጣንን ከሚሸሸው ኢስላማዊ ስብዕና በተፃራሪ የስልጣን እድሚአቸውን ለማራዘም፤ የውስጥ ችግራቸውን ለመሸፈን የሚራወጡት በህዝብ የተተፉ የመጅሊስ አመራሮች በአንዳንድ ባለስልጣናት አይዞህ ባይነት የልብልብ በማግኘት የብዙሃኑን የመብት ጥያቄ ፀረ ሰላም ሃይሎች የሚነዙት አሉባልታ ነው ለማለት ያዘጋጇቸው የፕሮፖጋንዳ ፕሮግራሞች ሙሉ በሙሉ በሚያስብል ሁኔታ በህዝቡ ተቀባይነትን ማግኘት አልቻሉም፡፡ አሁንም ህዝቡ ተታሎ ይሆን? ከዚህ በተቃራኒ ጥያቄአችሁ የኛም ጥያቄ ነው በማለት ዝርዝር አካባቢያዊ የመጅሊስ በደሎችን የሚያትቱ አቤቱታዎችና የተቃውሞ ፊርማዎች ከመላ ሃገሪቱ ይጎርፍ ጀመር፡፡ አንዳንድ አካላት ግን ዛሬም ህዝብ ተታሎ ነው ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ የሁሉ ነገር መሰረት የሆነው ህዝብ ስንቴ ይታለል ስንቴስ ይሳሳት ይሆን?



ፊርማ ጋር ተመሳክሯል
597
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለጥቂቶች የመንግስት ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ተደርጎ ቢታይም ለብዙሃኑ ሙስሊም ግን በመጅሊስ የተሳሳተ መረጃ የተመሩ ‹አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት› ግዜአዊ ስህተት ተደርጎ ነበር የተወሰደው፡፡ በወቅቱ የሚያመዝነው እውነታም ይኸው ነበር፡፡ በመጅሊስ እየተፈፀመ ያለው በየትኛውም መመዘኛ ለድርድር በማይቀርበው የእምነት ነፃነት ጥሰት እና በውይይት መድረኮች የተንፀባረቁ እሳቤዎች የማይገናኙ በመሆናቸው ህዝበ ሙስሊሙ የመርህ ይከበር ይፋዊ ተማፅኖውን በመላ ሃገሪቱ ማሰማቱን ቀጠለ፡፡ [illegible] በመደረግ ላይ ካሉ የተማፅኖ ጥሪዎች አንዱ በአዲስ አበባ በተለይም በአወሊያ ግቢ መካሄድ ላይ ያለው የ‹መብት ጥሰት ይቁም› ይገኝበታል፡፡

ህዝበ ሙስሊሙ ያነሳውን የመብት ጥያቄን ተከትሎ በመንግስት ይፋ አስተባባሪነት በርካታ የውይይት መድረኮች፤ የተለያዩ መግለጫዎች ተሰጥተዋል፡፡ በነዚህ ወቅቶች ግን ከተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናትና መገነኛ ብዙሃን የተደመጡ ነገሮች መንግስት በጉዳዩ ላይ ያለውን ግልፅ አቋም ከማንፀባረቅ ይልቅ በመጅሊስ የተፈጠረውን ውዥንብር ይበልጥ በማስፋት ህዝብን ግራ የሚያጋቡ ሆነው ነው የተገኙት፡፡ ከፊሎቹ ዘገባዎች እና የውይይት መድረኮች ‹ በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ትርጉም ያለው የአክራሪነት ፍላጎት አለ ብሎ መደምደም አይቻልም› ሲሉ ከፊሎቹ ደግሞ ‹ወታደራዊ ክንፍ ያለው የእስልምና አክራሪ አደረጃጀት በሃገራችን በተጨባጭ ይገኛል› ሲሉ በመላው አለም የሚገኙ የፀረ ሽብር ታጋዮች ከየትኛውም ሃገር ይልቅ ወደ ኢትዮጵያ ቀድመው ሊዘምቱ ይገባ ነበር የሚያስብል የተጋነነ ድምዳሜ ነበራቸው፡፡ በዚህም ህዝበ ሙስሊሙን ለእምነቱ ባዳ ለሃገሩም እንግዳ የሆነ እስኪመስለው ድረስ ፍፁም የሚጣረሱ ጉዳዮች ተናፈሱ፡፡ ጨቋኙ የደርግ ስርዓት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ይታገል የነበረውን የኢህአዴግ ሰራዊት በህዝቡ ውስጥ ጭራቅ አስመስሎ በመሳል በተለያዩ ሰያሜዎች ህዝብን ያደናግር እንደነበር ማንም ኢትዮጵያዊ አይዘነጋውም፡፡ በዛሬ በሙስሊሞች ጉዳይ ተጨባጭ ሁኔታ የአህባሽን አስተምህሮት የሚቃወሙና መብታችን ይከበር በማለት አቤት የሚሉትን ሁሉ ‹ወሃብያ› በማለት ቀንድ እና ጥርስ ያለው ህዝብ ጨራሽ ጭራቅ አድርጎ ለህዝብ ማቅረብ ያረጀና ያፈጀ ስልት ነው፡፡ ከዚህም በላይ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር፤ ዜጎች ጥቅማቸውንና መብታቸውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማራመድ፤ ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል መፍጠር የሚያስችል ስርዓት ተገንብቷል ተብሎ በታመነበት በዚህ በአዲሷ ኢትዮጵያ ዘመን የመብት ጥያቄን ‹አክራሪነት› እና ‹ፀረ-ህገመንግስት›› የሚያሰኝ ምንም በር የለም፡፡



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚያስመስሉ አንዳንድ ባለስልጣናትም ጭምር የስልጣንና የነዋይ ፍቅር እምነታቸውን እንዲሸጡ ያደረጋቸው የመጅሊስ አመራሮች በቀደዱለት የጥፋት ቦይ ለመፍሰስ ያልፈቀደውን ህዝበ ሙስሊም ሁሉ በጅምላ የሚጠሩበት ስልታዊ የማግለያና የማሸማቀቂያ ስያሜ ሆኗል። በነዚህ ሁላ ሂደቶች ውስጥ ግን ህዝቡ መጅሊስንና አስተምህሮቱን በስውር እና በተበጣጠሰ መልኩ ከማውገዝ አልፎ ወደ መንግስት የተሰነዘረ የጣልቃ ገብነት ወቀሳ እምብዛም አልነበረም።

## V. የመርህ ይከበር ሃገራዊ ህዝባዊ ተማፅኖ

መጅሊስ መራሹ የአህባሽ አስተምህሮ በየደረጃው ላሉ የመጅሊስ አመራሮች ብቻ በመሰጠት ይቆማል ተብሎ ሲጠበቅ ህብረተሰቡን እስከ ታች ድረስ በመውረድ ለማሰልጠን የተያዘውን ዕቅድና ዝግጅት በመገናኛ ብዙሃንና በሚድ አደባባይ ሳይቀር ይታወጅ ጀመር። በአተገባበር ሂደትም በየመድረኩ የታዩ እንግዳ አስተምህሮዎች የእምነቱን ክብር ያጎደፉና የአማኙን መብት የተጋፉ ግልፅ ህገወጥ ተግባራት በተጨባጭ ታይተዋል። የመጅሊስ አመራሮችና አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት የሸኽ አብደላህ አልሃረሪን በነባሩ የኢትዮጲያ እስልምና ፊለግ የጠለቀ እውቀት ያላቸው መሆናቸውን ሽንጣቸውን ገትረው መከራከራቸው ለምን ብለን እንድንጠይቅ አስገድዶናል። ቀድሞውኑ ያለህዝብ ይሁንታ በህዝበ ሙስሊሙ ላይ በግድ ተጭነው ያሉት የመጅሊስ አመራሮች አይደለም የሃይማኖቱ ሊቃውንትን የእውቀት ጥልቀትና እውነተኝነት ለማረጋገጥ፤ እጅግ መሰራተዊ የሚባሉ የሃይማኖቱ ድንጋጌዎችን በወጉ ማወቃቸውን የሚጠራጠሩት ብዙዎች ናቸው። በየመድረኩ የሸኽየውን የእውቀት ምጥቀትና በመላው አለም የሚሰበከው እርሳቸው ያስተማሩት ፊለግ እንደሆነ፤ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ሲያስተምር የነበረው ሙስሊሙ በነባሩ እስልምና ላይ ያለውን እውቀት ከፍ ለማድረግ ነው ሲሉ በአስተምህሮቱ እና በአተገባበሩ ላይ ያሉትን ፍፁም ከኢስላም ያፈነገጡ አስተሳሰቦች የቀድሞው ሙስሊም እምነት በማለት ሊያሳምኑን የሚሞክቱት የመንግስት ሹመኞች ግን ምንጫቸው ከወዴት ግባቸውስ ወዴት እንደሆነ መለየት ተስኖናል። እምነታችንን ለመበረዝ የተከፈተብንን ጥቁር ዘመቻ ስንቃወምም ለአክራሪነት አስተሳሰባቸው ቦታ እንዳያጡ ብዙሃኑን [illegible] መብት የሚያግዱ ተባልን።

የመጅሊስ አመራሮች እንደገለፁት ከመንግስት አካላት በተለይም ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ባደረግናላቸው ግብዣ መሰረት የተለያዩ የስራ ኃላፊዎች በስልጠናው ላይ [illegible] ህገ መንግስት አስተምረዋል ሲሉ ተደመጡ። በስልጠናዎቹ መድረኮች መንግስትን ለመወከል ከተገኙ አካላት የተደመጡ ንግግሮች ህገ መንግስት የማስተማርን ድንበር ዘልሎ መገኘታቸው



ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
599
http://ethcriminalawnetwork.com/

## IV. ከተሳሳቱ ደምዳሜዎች የመነጩ የተሳሳቱ መፍትሄዎች

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) የተቋቋመው ምንም እንኳ በጨቋኙ የደርግ ስርዓት ቢሆንም አላማዎቹና ጅምር ተግባሮቹ ግን ለታሪክ የሚዘከር ቁም ነገር አላቸው፡፡ በሁሉም ዘንድ ይከበሩ የነበሩት የተቋሙ ጠንሳሽና አመራሮቹ በአርቆ አስተዋይነታቸውና በእውነተኛ አባትነታቸው ሁሌም ይወሳሉ፡፡ እስልምናና ሙስሊሞች የአለም አቀፉ ፖለቲካ አጀንዳ ከመሆናቸው በላይ ከላይ እንደማሳያ ያነሳናቸው ሃገራዊ የተዛቡ ምልከታዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ተቋሙ ከምን ግዜውም በተሻለ በተደራጀና በህዝብ ተቀባይነት አግኝተው አባታዊ ሃላፊነትን በሚወጡ አመራሮች መወከል ይጠበቅበት ነበር፡፡ ግና ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነ፡

የኢስላም አስተምህሮ አክራሪነትንና ፅንፈኝነትን ለመዋጋት በራሱ ከበቂ በላይ ሲሆን ጠርዘኛ አስተሳሰቦችንና ጥራዝ ነጠቅ ግለሰቦችን በማረቅ ላይ የሃይማኖት መሪዎች ሚና እጅጉን የነላ ነው፡፡ የተቋማችን መሪዎች ግን እንደ ሃይማኖት መሪነት ጉዳዩን ከእምነት አንፃር በመተንተንና ነባራዊውን ሁኔታ በጥልቀት በመፈተሽ ሁሉን ያማከለ የውይይት እና የመፍትሄ ማፈላለግ ስራን በመስራት ነገሮችን ፈር ማስያዝ ሲቻል፤ ከህዝበ ሙስሊሙ ተጨባጭ ሁኔታ ይልቅ የመንደር ‹እስላማዊ አክራሪነት› መፈክርን በማንገብ ሙስሊሙን አክራሪና ፅንፈኛ ከማለት አልፈው አሸባሪ ብለው ለመፈረጅም ይዳዳቸዋል፡፡ በዚህ ብተሳሳቱ ድምዳሜ ተነስተውም የተሳሳተ የመፍትሄ ሃሳብ ወለዱ፡፡ ሰዎች የራሳቸውን የእምነት የአስተሳሰብ መስመር እንዳይከተሉ በማስገደድ የራስን የአስተሳሰብ መስመር በሌሎች ላይ ለመጫን መንቀሳቀስ አክራሪነት እንደሆነ እየተወሳ ለእምነቱም ሆነ ለአማኙ ባእድ አስተምህሮን በህዝበ ሙስሊሙ ላይ በመጫን አክራሪነት የመጅሊሱ መገለጫ ባህሪ ሆነ፡፡ የመጅሊስ አመራሮች እንደግለሰብ የፈለጉትን የአስተሳሰብ መስመር የመከተል መብት ቢኖራቸውም በበርካታ አለም አቀፍ ምሁራን ከእስልምና ማፈንገጡ የተነገረለትን የአብደላህ አልሃረሪን የአስተሳሰብ መስመር የሚከተለውን ስርዓተ ሃይማኖት ከማስተማር ባለፈ ከዚህ ውጪ ያሉ **ሌሎች የአስተሳሰብ** መስመሮች የተሳሳቱ ናቸው በማለት ምዕምኑን ‹‹ወሃብያ፤ ጠርዘኛ፤ አክራሪ›› **ብሎ በመፈረጅ** ለኢማምነት አይበቁም፤ ለመድረሳ አስተማሪነት አይመጥኑም፤ በማለት **ህዝብን መደግስቶጣት** ድርጊት ፈጽሟል፡፡ ከዚህ ቀደም የመጅሊስ አመራሮች ‹‹ወሃብያ›› በሚባል **ምናባዊ አካል** የሰየሙት አዚህ ግባ የማይባሉ ቅቅን እምነት ነክ ልዩነቶች የሚያሳዩ ግፋ ሲልም ህገወጥ ስልጣናቸውን የሚቃወሙትን ሚዛናዊ ይሆናቸው ዘንድ ነበረ፡፡ ዛሬ ላይ ግን የስልጣን ሹመታቸው ከመጅሊስ ባጅ/ቤት የሆነ

ECHN
ፌርማ ጋር ተመሳክሯል
600
http://ethcriminalawnetwork.com/

ማስተጋባት፤ ቁርዓን ተቀደደብን እያሉ ማራገብ፤ ሙሃደራ በሚባል የመንደር አደረጃጀት መሰባሰብ፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ቅበላና መሸኛ ፕሮግራም ማዘጋጀት ብሎም በትምህርት የደከሙትን በማገዝና በማስጠናት የመረዳደት ስልት እንዲሁም በምርጫ፤ በስብሰባዎችና በልማት ስራዎች የመንግስት ዋነኛ ደጋፊ መስሎ መቅረብ›› የመሳሰሉና ሌሎች እጅግ አሳዛኝ ነጥቦች ‹‹የእስላማዊ አክራሪነት›› መገለጫዎች ናቸው ተብለው በመንግስት በይፋ ታወጁ፡፡ አብዛሃኛው ህዝበ ሙስሊምም ባሉት የመረጃ መረቦች ባነበባቸው እነዚህ ‹የመንግስት የጥናት ሰነዶች› የመንግስት አቋም የሚወለደው ከመንደር አሉባልተኞች ነው እንዴ ሲል አመክኖአዊ የሆነ ታሪካዊ ጥያቄ አንስቷል፡፡

እነዚህ በየትኛውም አለማዊም ሆነ ሃይማኖታዊ መመዘኛዎች የአክራሪነት መገለጫ መሆን የማይችሉ ኢትዮጵያዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን የመንግስት አካላት በህዝቡ ውስጥ ለማስረፅና ለመከላከል ብለው ወዳመኑት እርምጃ ሲገቡ ጉዳዩ ላም ባልዋለበት ነውና ለብዙሃኑ ህዝበ ሙስሊም ‹ዘመኑ የወለዳቸው ሙስሊሙን ማሸማቀቂያ አጀንዳዎች› ተደርገው መወሰዳቸው አልቀረም፡፡ ለዚህም በቂ አመክኖአዊ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡ የቀድሞዎቹን የግፍ አገዛዝ እንተወውና የአፄዎቹ ስርዓት መቋጫ ላይ ሙስሊሙ ካገኛቸው ጠባቦ መብቶች አንዱ በደረሰበት የስግደት ስርዓቱን መፈፀም ነው፡፡ ይህን መብቱን ለመተግበር ይሁ የሚጓዛቸው ሽርጥና የውሃ መያዣ ጡሌ በየሄደበት ‹ሽርጣምና ጡሌአም› ተብሎ በህብረተሰቡ እንዲሸማቀቅ ይደረግባቸው የነበሩ ነጥቦች ናቸው፡፡ ዛሬ ላይ የተገኘው አንፃራዊ ነፃነት የወለዳቸው የእምነት ነፃነት መገለጫዎች የሆኑ ዳዕዋ(ሙሃደራ)፤ ማህበራዊ ትስስር እና የመብት ጥሰት አቤቱታ የፅንፈኝነት መገለጫዎች ሲባሉ ለብዙሃኑ ሙስሊም ‹የዘመናችን ሙስሊሙን የማሸማቀቂያ አጀንዳዎች› እንጂ ሌላ ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም፡፡ ለምን ቢባል መንግስት ያመጣውን ልማትና ዴሞክራሲ ከቀደምት መንግስታት አንፃር አወዳድሮ ማሳየት የሚወደስ ተግባር ሆኖ ሲወሰድ ሙስሊም ዜጎች ከቀደምት ስርዓቶች አንፃር ያገኙትን ነፃነት በማጉላት መናገርና የቀድሞዎቹን መኮነን የአክራሪነት መገለጫ ሊባል አይገባምና፡፡ ከዚህም አልፎ ‹የተበደለናል አቤቱታ› የአክራሪነት መገለጫነቱን ማንግስት ማፅደቁ የበደሉን ህጋዊነት ማመንም ተደርጎ የሚወሰድበት አረዳድም ይኖራል፡፡



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፎርማ

601

http://ethcriminalawnetwork.com/

ዴሞክራሲያዊ መብቶች በህገመንግስታችን ሙሉ ጥበቃ እንደተደረገላቸው በትነገረን ማግስት ፍፁም ነፃ የሆኑ ሃይማኖታዊ ክንዋኔዎች ‹‹አክራሪነት›› ፈፃሚዎቹ ደግሞ ‹‹አክራሪዎች› ተብለው ሲብጠለጠሉ እኔን አይመለከተኝም በሚል ዳር ቆሞ ማየት ብዝሃነትን የሚቀበልና በእኩልነት የሚያስተናግድ ህገ-መንግስት በሙስሊሙ ላይ ሲሆን የተለየ ትርጉም ይሰጠዋል በሚል ስጋት ውስጥ የወደቅን በርካቶች ነን፡፡

ከሙስሊሙም ሆነ ከክርስቲያኑ ወገን ፅንፈኝነት የተጠናወታቸው አልያም ግላዊ እና ቡድናዊ በሆኑ ስህተቶች የሚፈፀሙ ማንም ጤናማ አእምሮ ያለው አካል ሊያወግዛቸው የሚገቡ ጥፋቶች እንዳሉ እናምናለን፡፡ ተግባሩንም በጽኑ እናወግዛለን፡፡ ነገር ግን ሚዛኑን በሙስሊሙ በኩል ባጋደለ መልኩ በማጉላት ‹‹ እስላማዊ አክራሪነት›› የለት ከለት የመንግስት አካላት አጀንዳ ተደረገ፡፡ የጅማውን የአብያተ ክርስቲያናት ቃጠሎ ሙስሊሙ ህብረተሰብ በአንድ ድምፅ እንዳወገዘው ሁሉ የጉራጌ ዞን ስምንት መስጂዶች ቃጠሎንም ህዝበ ክርስቲያኑ በአንድ ድምፅ አውግዞታል፡፡ በእርግጥም ሊወገዙ የሚገባቸው ህገ ወጥ ተግባራት ናቸውና፡፡ መንግስት በህገወጦች ላይ የተለየ እርምጃ መውሰድ ሲጠበቅበትና በሁለቱም ወገን የደረሱ ጥፋቶችን ማስተማሪያ ሊሆን በሚችል መልኩ ለህዝብ ማቅረብ ሲጠበቅበት በክርስቲያን ወገኖቻችን ላይ የደረሰውን የህግ ጥሰት በማጉላት ሌላኛውን በማደብዘዝ የሚና መደበላለቅ ታየ፡፡

ከዚህም አልፎ በመንግስት የተዘጋጁ ‹የጥናት ሰነዶች› ለመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ ተማሪዎችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያየ ሽፋን ተሳቢሶ ዕውቀትን መቅሰሚያነት መቅረብ የተለመደ ስራ ሆነ፡፡ መንግስት በጥናት የተደገፈ የግሉ ሚዛናዊ መጽሔቶችን ለአንባቢ ማቅረቡም ሆነ ለህብረተሰቡ ማቅረቡ አበጀህ የሚያስብልና የመንግስትና የህዝቡን አብሮነት የሚያጎለብት ሁነኛ መፍትሄ ነው፡፡ ነገር ግን በነዚህ የመንግስት ‹የጥናት ሰነዶች› የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን አስመልክቶ የተካተቱ በርካታ ነጥቦች አንድም እስልምናን ተንተርሶ በአለም አቀፍ ደረጃ በተነሳው የፖለቲካ ውጣ ውረድ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ያላቸውን አቋም በውል ያላጤነ በሌላ መልኩ ደግሞ ቀድሞ የጥቂት የጥፋት ሃይሎች የመንደር አሉባልታ የነበሩ ‹‹የእስላማዊ አክራሪነት›› መገለጫዎችን ከነእንክርዳዳቸው በመውሰድ ይፋ የአክራሪነት መገለጫ አድርጎ መፈረጁ ለኛ ለሙስሊሞች አስደንጋጭም አሳዛኝም ነበር፡፡ በዚህም አካሄድ ጉዳዩ ጥልቀት ባለው መልኩ አለመመርመሩን ከማሳየት ባለፈ በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላይ ሌላ የታሪክ ምዕራፍ የተከፈተ የሚያስመስልባቸው ሁኔታዎችም ተስተውለዋል፡፡ ለዚህም እንደማሳያ የሚሆነን ቀድሞ በአሉባልታ ደረጃ ከጥቂቶች ስንሰማ የኖርናቸውን ‹‹በቀድሞ ነገስታት ተጨቁነናል በማለት



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያገኘውን ነፃነት ባለመቀበል እና ሙስሊሙን ስጋት አድርጎ በመሳል ሙስሊሙን ወደ ቀድሞ ይዞታው መመለስ ነው፡፡ በዚህም ኢትዮጵያን ወደ ቀድሞው ጥቁር ታሪኳ የመቀልበስ የረዥም ግዜ ግባቸውን እውን ለማድረግ ይታትራሉ፡፡

በነዚህ ጥቂት የመንደር አሉባልታዎች፤ በራሪ ወረቀቶች፤ መፅሄቶች እና አልፎ አልፎ መልክ እና አቅጣጫ ጠቋሚ ሆነው በተዘጋጁ መፅሄፎች ‹‹አክራሪ እስልምና›› የለት ከለት አጀንዳ ተደረገ፡፡ ለባዶ ተረታቸውም ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቧቸው ነጥቦች እንደወቅቱና እንደፀሃፊው ቢለያይም የነገሩን አሳሳቢነትና ኢትዮጵያን ከአክራሪነት ሳይሆን ከእስልምና መከላከል የሚመስሉበትን ሁኔታ ለማስረዳት ጥቂቶቹን ብንጠቅሳ ‹‹ ቁርአናችን ተቀደደ፤ እስልምና ተናቀ፤ ተገፋን የሚሉ ፕሮፖጋንዳዎችን የሚነዙ፤ የመስጂድ ቦታ ካልተሰጠን የሚሉ፤ የቀደምት ነገስታት እስልምናን ጨቁነዋል የሚል አሉባልታ ደጋግመው የሚያስተጋቡ፤ ንጉስ አስሃማ (ነጃሺ) ሰልሚል የሚሉ፤ ሱሪ ከፍ የሚያደርጉ፤ ፂም የሚያሳድጉ፤ አክሱም መስጂድ ይሰራ በማለት የሚሞግቱ፤ ኢማም አህመድን በጀግንነት የሚያደንቁ፤ የሙስሊሙ ቁጥር አንሶ ነው የተገመተው ብለው የሚከራከሩ እና ሌሎች ለቁጥር የሚታክቱ የኢትዮጵያ ሙስሊም ወደ አክራሪነት እየተቀየረ መሆኑን ማሳያ ተደርገው የተሳሉ ነጥቦች ናቸው፡፡ ከነዚህ በፅሁፍ መልክ ይዘው ከሰፈሩ አሉባልታዎች በተጨማሪ በመኖሪያ መንደሮቻችን፤ በትምህርት ተቋሞቻችን፤ እና በሌሎች የአገልግሎት መስጫ ስፍራዎች በጥቂት የጥፋት ሃይሎች የሚነዙት የአክራሪነት ወሬዎች ለቁጥር ይታክታሉ፡፡ ‹‹ ጥቁር ተከናንበው የሚሄዱ፤ ዳዕዋ እያሉ ወሳዊሰላፊያ የሚያስተ በትምህርት ተቋማት ውስጥ ካልሰገድን የሚሉ፤ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የታሰበና የመሸኛ ፕሮግራሞች የሚያዘጋጁ.....ወዘተ የሚሉ ይገኙባቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ የብሂረሰቦች የታፈኑ መብቶች፤ የተገደቡ ነፃነቶች ሲፋ ወጥተው ሲታዩ የዴሞክራሲ ፍሬነታቸው ታምኖበት በአዎንታዊነት ይወሰዱ፡፡ የመሰማቱ እና የተገደበው የሃይማኖት ነፃነት መገርሰሱ ማሳያ ለሆኑ የአምልኮ ተግባራት ግን በተቃራኒው የአክራረነት መገለጫ ተደርገው ይገለጻሉ፡፡ እነዚህ የመንደር አሉባልታዎችንም ከነእንክርዳዳቸው የመቀበል አዝማሚያ በአንዳንድ ባለስልጣናትና መገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ይስተዋላል፡፡ መንግስት አባታዊ ሃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ዜጎች ከሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ የዴሞክራሲ ፍሬ፤ የነፃነት መገለጫ፤ መብት የመጠየቅና የሙተግበር ባህል መዳበር፤ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ አዲሱ ገፅታ የሆኑትን መለየትና የህብረተሰቡን የተዛባ አመለካከት በህገ መንግስታዊ ማስረጃዎች ማሳመን ይገባው ነበር፡፡ የግለሰቦችም ሆነ የቡድን ሰብአዊና



ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለማየት መላው ህዝባችን በነበረው ምኞት ሁሉም ህዝባችን ታግሏል፤ ብዙዎቹም ለዚህ ዓላማ መስዋዕት ሆነዋል፡፡ የዚህ ታላቅ መሰዋዕትነት ፍሬዎች አንዱ የሃይማኖት ነፃነት እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ሙስሊምም እምነቱን ያለመሸማቀቅ እና ያለመሸራረፍ ሙሉ በሙሉ እንዲተገብር የሚያስችል እድል አግኝቷል፡፡

ነባሩ የኢትዮጵያ እስልምና የሚለው ሃረግ በተለይ ከመሪዎቻችን ደጋግሞ ጆሯችን ላይ ሲያቃጭል፤ አንዳንድ ባለስልጣናት በመስጂድ ውስጥ ያደጉ ይመስል እስልምና ወደሃገራችን ከገባበት ግዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ሙስሊም ይከተለው የነበረው እንዲህ ያለውን ነው፤ ይሄኛው የእስልምና አስተምህሮ መገለጫ አይደለም በማለት ሃይማኖታዊ ፈትዋ (ብይን) ሲሰጡ መደመጣቸው የተዛባ ግለሰባዊ አስተያየታቸውን ብቻ ሳይሆን የወከሉት ስርዓት ጓዳ ላይም ትዝብትን የሚያሳድር ነው፡፡ ይህንን ‹ነባሩ› እየተባለ የሚተረክልንን ግን ደግሞ በተጨባጭ በመንግስት እየተያዙ ያሉ አቋሞችና እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ወደ ነባሩ የተሸማቀቀ ማንነታችሁ፤ ወደ ጥንቱ ውስን የእምነት ነፃነታችሁ፤ ወደ ቀድሞው የድብቅ አምልኮአችሁ... ተመለሱ እየተባልን እንደሆነ ተሰምቶን ስጋት ካደረብን ውሎ አድሯል፡፡ ህገ መንግስቱ በፀደቀ ማግስት የመንግስት ልዕልና መሰረቱ የህዝቦች ልዕልና እንደሆነ በመተማመን የተገኘውን ነፃነት በማወቅ እና በመተግበር ላይ ያለውን ሙስሊም ያለበትን ተጨባጭ ወደኋላ በመተው የግል ድብቅ አጀንዳ ያለ በሚያስመስል መልኩ ‹መቻቻል› የሚለውን ቃል የዜጎች መከባበርና መፈቃቀር መሆኑ ቀርቶ አሃዳዊ እምነት መከተል በሚያስመስል መልኩ መግለጫዎቹ የመስቀል ዳመራ ማብራትና የጥምቀት ታቦት መሸኘት ተደርጎ መሳሉ ይህንኑ የላቀደችሁት ደግሞ ነባሩን የመቻቻል ባህላችንን ያፈረሱ ሲባል ለህገ መንግስቱ የእንጀራ ልጅነህ እየሠራ እንደሆነ የሚቆጥረው ሙስሊም ቁጥሩ እያሻቀበ ነው፡፡

## III. የመንግስት አቋምን የወለዱ የጥፋት ሃይሎች ተረቶች

እስከ ቅርብ ግዜያት ድረስ ከመንግስት ባለስልጣናትም ሆነ መገናኛ ብዙሃን ከሙስሊሙ የህብረተሰብ ክፍል ለኢትዮጵያ ስጋት ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ አመለካከትም ሆነ ተግባር ሲወራ አልሰማንም፡፡ ልንሰማም አይጠበቅም፡፡ ሆኖም ግን የቀድሞዎቹን ስርዓት ከሚናፍቁ፤ የሙስሊሙ ነፃነት ማግኘት ካልተዋጠላቸው፤ አንዳንዴም ጓዳዩን በቅንነት ለመረዳት ፍላጎት ከማጣት የመነጩ በየመንደሩና በየመጣጥፎች ላይ የሚነዙ አጓጉል አስተሳሰቦች ጥቂት ቢሆኑም ሲደመጡ ግን ቆይተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ አስተሳሰቦች መነሻቸው የተዛባ በመሆኑ ደግሞ ድምዳሜአቸውም ሚዛኑን የሳተ ነው፡፡ ዋና አላማቸውም በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሙስሊሙ



ከዋናው ፈርማ ተመሳክሯል

604

http://ethcriminalawnetwork.com/

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

## I. መግቢያ

ከቅርብ አመታት ወዲህ የሃገሪቱን አንጋፋ ሃይማኖቶች አስመልክቶ በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ከሚቀርቡ አሉታዊ ይዘት ካላቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ ‹‹ መቻቻልን የሚያደፈርሱ›› የሚለው ቃል በጋራ ‹‹ነባሩን እስልምና የሚንዱ›› የሚለው ደግሞ ለሙስሊሞች በተናጠል ጥቅም ላይ መዋላቸው የተለመደ ነው፡፡ በተለይ ለኛ ለሙስሊሞች የቀደምት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ይከተሉት የነበረውን ከምንጩ የተቀዳውን እስልምና ችላ የተባለ በማስመሰል ከኛ በላይ ለኛ የሚያስቡልን መስለው በቀረቡ አካላቶች እየተነገረን ይገኛል፡፡ ነባሩ የኢትዮጵያ እስልምና የሚለው ሃረግ ያለቦታው እና ያለአግባብ እየተተረጎመ እና እየተሰላ ህዝብን ለማደናገር እንዳስፈላጊነቱ የሚስልና የሚዶመዱም ተደርጎ ‹መሰንጠቂያ ማሽን› ይሆን ዘንድ ሆን ተብሎ የተነሳነ የጥፋት ሃረግ መሆኑ ግን ለብዙዎቻችን ግልፅ ነው፡፡ ምክንያቱም ቢሳሳም እስልምና ነባሩና አዲሱ፤ አፍሪካዊ እና አረባዊ፤ የነጭና የጥቁር የሚል ስያሜ ሊሰጣቸው የማይገባ እምነት ነውና፡፡

## II. ነባሩ የኢትዮጵያ እስልምና የሚለው ሃረግ እንዴት ተመዘዘ?

የኢትዮጵያን ታሪክ ያነበበ ቀርቶ ያለፉትን ሁለት መንግስታት የማየት እድል ያጣ ኢትዮጵያዊ የኛ የሙስሊሞችን ነባራዊ ገፅታ በውል ይረዳል የሚል እምነት አለን፡፡ የእስልምና ሃይማኖት መሰበክ ከጀመረበት ግዜ አንስቶ የአለም ፍፃሜ ድረስ የይዘት ለውጥ እንደማያመጣ እርግጥ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በነበሩባቸው የታሪክ ውጣውረዶች የሚያሳዩዋቸው የአመልከ አተገባበር፤ ማህበራዊ መስተጋብር፤ ሁለንተናዊ ሃገራዊ ተሳትፎ ግን በሁሉም ዘመናት አንድ አይነት ነበሩ ለማለት አይቻልም፡፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ መ[illegible]ሊሞች ስንባል መኖራችንን የተረዳ ማንም አካል እነዚህ አስተሳሰባዊ ሳይሆኑ ተግባራዊ ልዩነቶች ለምን ተፈጠሩ ብሎም ይጠይቃል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በቀደምት ስርዓቶች ሙስሊሙ ሙሉ የሃይማኖት አስተምህሮቱን መተግበር የሚያስችል ነፃነት ነበረው ብሎ መናገር እንደማይቻል ሁሉ ዛሬ ላይ በሙስሊሙ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ የታዩ ለውጦች መብትን ከመተግበር ያለፉ አመለካከት ነክ ይሉ[illegible] ለውጥ ናቸው ብሎ መሞገትም ከንቱ ነው፡፡ እነዚህ ለውጦች ፊዕሞ መሠረት የላቸውም ብሎ መሞገት ‹‹አዲሲቷ ኢትዮጵያ›› የሚባል ታሪክ የለም ብሎ እንደመሞገትም ይቆጠራልና፡፡ ምክንያቱም የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፣ መልካም አስተዳደር የሰፈነባት



ቀናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በሸሞሌ አካባቢ ሕዝቡን ሊያነሳሳ የሚችል 5 ሺህ የሚበተን ወረቀት መዘጋጀቱንና ይህንኑ ወረቀት የሚበትኑ 10 ሴቶችን እንዳዘጋጀ በ16/6/2004 አሊ ለተባለ ሰው መግለፁ፡፡

ህብረተሰቡን ለመቀስቀስ የሚያስችሉ በርካታ የተዘጋጁ ሲዲዎችን እንደሚሰጠው በ24/4/2004 መሐመድ ለተባለ ሰው ያሰሰበው መሆኑ፡፡

በመውሊድ ቀን በየክፍለከተማው የአህባሽ አስተምሮት ለመስጠት ስለታሰበ ህብረተሰቡ አስቀድሞ በመረዳት በየመስጊዱ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ማሰማት እንዳለበትና የጁመአ ቀንም በአወሊያ በመገናኘት ተቃውሞአቸውን መቀጠል እንደሚገባቸው በ7/5/2004 ለአንድ ሰው መግለፁ፡፡

ህብረተሰቡን ሊያነሳሱ የሚችሉና በየአካባቢው የሚበተኑ ወረቀቶችን አዘጋጅተው መጨረሻውንና በየመስጊዱ ለማዳረስ ማቀዳቸውን በ8/6/2004 ለአንድ ሰው መግለፁ፡፡

በመቀሌ ዩኒቨርስቲ 6 ተማሪዎች በግቢ ውስጥ አትስገዱ



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4. | ካሊድ ኢብራሂም | | 911694683 | 9221511554 | ያለው መንግስት እንደሆነ እየተደረገ ያለው ነገር ሕዝቡን ከተቃውሞ ሂደት የማያወጣ እንደሆነ ነገር ግን የምርጫው ሂደት በግልፅነት ከተቀመጠ ተቃውመው ሊቋጭ እንደሚችል በ23/9/2004 ለሚሮን (የሰብ ሰሀራን ጋዜጠኛ) መግለፁ፡፡<br><br>በጅማ ከተማ ለመካሄድ በታሰበው የሰደቃና የአንድነት ፕሮግራም ላይ መገኘት እንደሚፈልግና ሌሎች አካባቢዎችም የጅማውን ፕሮግራም እንደ ምሳሌ አድርገው እንደሚንቀሳቀሱና በተለያዩ ቦታዎችም መድረክ ለማዘጋጀት እየታሰበ እንደሚገኝ በ1/11/2004 ለአንድ ሰው መግለፁ፡፡<br><br>ለመንግስት ያቀረቡትን ጥያቄ መተው አለባችሁ ወይም አቁሙ ብሎ የሚመጣ አካል ካለ በሕዝብ ጥያቄ ላይ ድርድር እንደማይገቡና መፍትሔው መልስ ለማግኘት መንቀሳቀስ እንደሆነ፣ በመንግስት አካላት በተለያዩ ሚዲያዎች ላይ በኮሚቴው ላይ የሚደረገው ውንጀላዎችንና አሉባልታና የስም ማጥፋት ድርጊት የማያሳይ ሲዲ እና መፅሐፍ በኮሚቴው ተዘጋጅቶ ለሕዝቡ በ1/10/2004 እንደሚሰራጭ በ25/9/2004 ለቢላል ሬዲዮ መግለፁ፡፡<br><br>ድምፃችንን እናሰማ በሚል በየአካባቢው ሕዝቡን ለተቃውሞ የሚያነሳሳ ወረቀት ለመበተን በዝግጅት ላይ መገኘታቸውን በ8/6/2004 ለሰዒድ መግለፁ፡፡ |



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አሰላ ላይ የተከሰተው ክስተት ከሂደቱ ጋር ይገናኛል ተብሎ በሚዲያ የሚወራው ነገር እና ህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ነገር እንደሚለያይ፣ እንዲሁም አህባሽን ካልተቀበላችሁ በሚል የታሰሩ ሰዎች አንዳሉ፣ ድርጅት እስከመዝጋት መድረሱንና መነሳሳት ብሄይሚጥ ጣልቃ ገብቷል በሚል አህመዲን ጀበል በ24/8/2004 የደቡቪሊ ሬዲዮ ጋዜጠኛ ለሆነችው ለሂሩት መግለፁን፡፡

የመጅሊሱን ምርጫ የኡለማ ምክር ቤት ማካሄድ እንደሌለበትና ነፃና ገለልተኛ አስመራጭ አካል መቋቋም እንዳለበት፣ በአሰላ ለተገደሉት ሰዎች የኦሮሚያ ክልል መነግስት ማዘኑንና በቀብር ሰን ስርዓቱ ላይ የተገኙ ባለስልጣናት ገንዘብ እንደሰጡ የአይን እማኞች ነግረውናል፡፡ ለማንኛውም ነገሩ በገለልተኛ ወገን ቢጣራ ጥሩ ነው ሲል በ9/9/2004 ለቪ.ኦ.ኤ ጋዜጠኛ ለትዝታ በላቸው መግለፁን፡፡

የመጅሊሱን ምርጫ ለማካሄድ ገለልተኛ አስመራጭ ኮሚቴ ተቋቁሞ ምርጫው በየመስጂዱ መካሄድ እንዳለበትና ምክንያቱም ሙስሊሙ ህብረተሰብ የጠየቀው ምርጫ በመስጂድ እንዲካሄድ እንደሆነ፣ የምርጫውን ሂደት ሙሉ በሙሉ ይዞ እያስኬደው



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 924807178 | 911174112 | እንቅስቃሴ እንደሆነ፣ ከወሀቢያ ወደ ሰለፊያ የስም ለውጥ የተደረገው ወሃቢያ ነኝ የሚል ሰው ስለሌለ እንደሆነና ሰለፊያ የተባለበት ምክንያት ጉዳዮን ከሌሎች አገሮች ጋር ለማስተሳሰር እንደሆነ፣ አህመዲን ጀበል በ11/8/2004 አሜሪካ ለሚኖር አንድ ግለሰብ ስለመግለፁ፡፡<br><br>መንግስት የሰጠው መግለጫ ማስፈራራሪያ እንደሆነና በአዲስ አበባ ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ ይወጣሉ ተብሎ ስለተፈራ በመስጊድ አካባቢ ባሉት ሕንፃዎች ላይ የፀጥታ ሰዎች እንደተቀመጡና አንደርግራውንድ ውስጥም ፖሊስ፣ መከላከያና የፌዴራል ፖሊሶች መመሸጋቸውን አህመዲን ጀበል በ26/8/2004 ለአንድ ሰው መግለፁን፡፡<br><br>የፕሮፖጋንዳ ሥራ ከመስራቱ አንፃር ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ባቀረቧቸው ጥያቄዎች ላይ የተሰጡት መልሶት እንዳሉ ነገር ግን መልሶቹ መሬት ላይ የሚወርዱ መልሶች እንዳልሆኑና ጥያቄአቸውን ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርና ወደ ሌሎች አካላት አሰገብተው የእነሱን ምላሽ እየጠበቁ እንደሆነ፣ |

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ሰው መግለፁን ህዝቡ ተክቢራ እያሰማ ወደ አንዋር መስጂድ ይሂድ እናንተም ቀደም ብላችሁ በአንዋር ተገኝታችሁ ለሕዝቡ አቅጣጫ ስጡ ሲል በ7/11/2004 ለሀሰን አቢ ትዕዛዝ ማስተላለፉን፡፡ |
| 2 | አህመድ ሙስጠፉ | 0911244792 | 091124479 2 | 0911426042 | ከበድር ድርጅት ከውጭ ሃገር ተወክለው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለማነጋገር በሚመጡ አባላት ዙሪያ በመምጣታቸው ተቃውሞ እንደሌላቸውና ነገር ግን ግለሰቦቹ ሎቢ ማድረግ የሚችሉና የማይቀለበሱ መሆን እንዳለባቸው በ13/6/2004 ፊሊ ለተባሉ አሜሪካን ሃገር ለሚገኝ ግለሰብ መግለፁ፡፡ |
| 3. | አህመዲን ጀብል | 0911174712 | 924146084 | 0911174112 | በኑር መስጅ ድ የሚደ ረገው የሰደ ቃ ፕሮግራም ቀ ረ ማለት ለመጅሊስና ለመንግስት ትልቅ ድል እንደሚሆንና ለኮሚቴው ደግሞ ትልቅ ውድቀት እንደሚያስከትልና ይህንን ተከትሎም በሌሎች መስጊዶችም ሊከለክሉን እንደሚችሉ በ29/10/2004 አረዳን ለተባለ ግለሰብ መግለፁን፡፡ |
| | | | 091124479 2 | 0911457799 | ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፓርላማ ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ እንዳልሰጡና ሙስሊም ያልሆኑትን ማስፈራራትና ሙስሊሙን ለመከፋፈል ያደረጉት |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አመቻችቶ ሁሉም ወንድሞች እንዲገኙ ማድረግ እንዳለበት፣ አቡበከር ለሀሰን አቢ ቀጠሮ ስለማስያዙ፡፡

የመጅሊሱ ምርጫ በቀበሌ መካሄድ አለበት ብሎ የኡለማ ምክር ቤት ያወጣውን መግለጫ እንደማይቀበሉ፣ የኡለማ ምክር ቤት እራሱም ሕገ ወጥ የሆነና ተጠሪነቱም ለመጅሊሱ ነው፣ ስለዚህ ያለው ብቸኛ አማራጭ ሙስሊሙ የጀመረውን አቅጣጫ ከግብ ለማድረስ መንቀሳቀስ እንዳለበት፡፡

በ21/10/2004 ለቢላል ሬዲዮ ጋዜጠኛው ለአድር መግለፁን በተመለከተ በኢቲቪ የቀረበውን ዶክመንተሪ ፊልም አስመልክቶ የእኛ ሰዎች በፊልሙ ላይ አይሳተፉ የምንለው ፊልሙን ቆራርጠው እኛን መጠቀሚያ ስለሚያደርጉን ነው ሲል በ25/10/2004 ለኡመር መግለፁን፡፡

ወቅታዊ የሙስሊሙን ጥያቄ በተመለከተ ማንኛውም አደጋ ለመቀበል ዝግጁ እንደሆኑ፣ በ26/10/2004 ለሳልህ መግለፁን በተመለከተ፡፡

በምታደርጉት ስብሰባዎች ላይ የሕዝብ ሙስሊሙን ሃሣብ ማንፀባረቅ አለባችሁ ሲል በ21/10/2004 ለአንድ



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| ተ/ቁ | የታርጌቱ ሙሉ ስም | ስልክ ቁጥር | በድምፅ ያስተላለፈው ቁጥር | በድምፅ የተቀበለው ቁጥር | ይዘቱ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቡበክር አህመድ | 0911246555 | 928796565 | 0911246555 | በ10/7/2004 የተጀመረውን ትግል ለያግዝ የሚችል ሌላ አጋዥ ኮሚቴ እንዲቋቋም እየታሰበበት እንደሆነ አሜሪካ ለሚገኝ ወዘር ለተባለ ግለሰብ መግለፁን፡፡<br><br>በ10/8/2004 በፓርላማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረበው ጥያቄ ትክክል ያልሆነ መሆኑንና የተሰጡትም መልሶች ትክክለኛ እንዳልሆኑ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄውን ከእኛ አንደበት ሰምተው መልስ እንዲሰጡበት ቀጣይ እሳቸውን ለማግኘት ጥረት እንደሚያደርጉ፣<br><br>መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ መግባቱን የሚያሳዩ በተለያዩ መድረኮች ላይ የመንግስት ባለስልጣናት የተናገሩት የተቀዳ ንግግር ሙስሊሙን ህብረተሰብ ለማሸማቀቅ እንደሆነ ሀሰን ለተባለ የሬዲዮ ቢላል ጋዜጠኛ መግለፁን፡፡<br><br>ለሁሉም ወንድሞች በ1/9/2004 በሀሰን አቢ መኖሪያ ቤት በወቅታዊ የሙስሊሞች ጉዳይ ለመሰብሰብ ከሰዓት በኋላ 11:00 ሰዓት ላይ ቀጠሮ እንዲይዝለት ሁኔታውን |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ዝም በማለት ሰላማዊ ትግል እናድርግ መልስ የምንጠብቀው በኮሚቴዎቻችን በኩል ብቻ ይሆናል ሲል ለ11 ሰዎች SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | | 0911698067 | በ09/09/2004 አወሊያ በሚቀጥለው ሣምንት ትግላችን ጁምዓ በአንዋር በምልክት ተቃውሞ ይቀጥላል ሁላችንም አፋችንን በመለጠፍ እጅ ለእጅ በመያያዝ ለመቃወም እንምጣ ሲል ለ16 ሰዎች SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፣ |
| | 0911661584 | 0911234466 | በ21/9/2004 በሙስሊሙ ላይ የታቀደውን ሸር ለመመከት እና በኢቲቪ የተላለፈውን የምርጫ መግለጫ አስመልክቶ ኮሚቴዎቻችን አቋማቸውን ስለሚያሳውቁን አወሊያ እንገናኝ ሲል ለ3 ሰዎች SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፣ |
| | 0911661584 | 0910120685 | በ20/10/2004 እኛ የመቱ ከተማ ሙስሊሞች በሀገራችን ካሉት ከተሞች ሁሉ በተሻለ ሰማችን በደህና ይጠራ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በአሁኑ ሰዓት ግን ከሁሉም የሀገራችን ክፍሎች እስልምናችን እየተጠረገ እና እየተነካ ይገኛል፡፡ የመቱ ሙስሊሞች ለመሆኑ እኛ በሕይወት እያለን ዲናችን (ሃይማኖታችን) የማንም አይሁድ እና የማንም ለሆዳቸው ያደሩ መናፍቅ ካድሬዎች መጫወቻ እንዴት ይሆናል? ነገ አላህ ዘንድ ምን መልስ ይኖረናል? ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፣ |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ታውቋል፡፡ |
| 8 | አሊ መኪ | 928796666 | 912730079 | 928796666 | የኮሚቴው ሰብሳቢ አቡበከርና አህመዲን ጀበል ዘነበወርቅ አካባቢ ተይዘው ተወስደዋል የተጀመረውን የማሰር ዘመቻ በሰላማዊ መንገድ ለመቃወም እንዘጋጅ ሲል በ4/11/2004 ተከታዮቻቸውን ለአመፅ ሊያነሳሳ የSMS መልዕክት ማስተላለፉ ታውቋል፡ እንደዚሁም የሚወክለን መጅሊስ እንፈልጋለን፡፡ ሕዝብን ያላሳተፈ ምርጫ አንቀበልም መልስ በኮሚቴ በኩል ይሰጠን፣ መንግስት ይቲባበረን እንጂ ይምረጥልን አላልንም፡፡<br><br>ጁመአ በአንዋርና በአወሊያ እንገናኝ ይህን መልዕክት ለሌሎች አሰትላልፉ ሲል በ23/9/2004 አመፅ ቀስቃሽ SMS መልዕክት ለተለያዩ ሰዎች ማስተላለፉ፡፡<br><br>በኮሚቴው አባል ካሚል ሸምሱ ላይ የተፈፀመውን እስራት ለመቃወም ዝሁር ሰላት በአንዋር በመገኘት ተቃውሚችንን እናሰማ መልዕክቱንም ለሎሎች አስተላልፍ በማለት በ5/11/2004 አመፅ ቀስቃሽ የ SMS መልዕክት ለተለያዩ ሰዎች ማስተላለፉ፡፡<br>በ10/12/2004 ኮማንደር ጣሃ በአሁኑ ጀመአ ብቻውን ይሰገድ የሙስሊሙን አንድነት በድጋሚ እናሳያቸው አንሻአላህ ለ10 ኣው አስተላልፉ፡፡ |
| 9 | ሀሰን አቢ | 0911661584 | 0911661584 | 0932393670 | በ02/09/2004 ስለወደፊቱ በማሰብ ፀረ ሰላሞችን ለማሳፈር ጁምአን ሁላችንም በየመስጅዶቻችን ከወትሮ በተለየ ሁኔታ |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 0928740990 | 0928740990 | 0912895444 | አያደርገንም ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | 0928740990 | 0928740990 | 0920717448 | በ23/08/2004 ነገ መጅሊስ በማዘጋጃ ቤት ስብሰባ ስለጠራ ሁላችንም ተገናኝተን ተቃውሞአችን ዘመቻ ለመቃወም የግል ጉዳያችንን በመተው ጁምዓ አወሊያ እንገናኝ ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | 0928740990 | 0928740990 | 0910524281 | በ01/08/2004 ብልጠች አይደለንም ብልጣብልጦች ግን አያታልሉንም ጥያቄያችን የግለሰቦች መቀያየር ሳይሆን በመረጥናቸው መመራት ነው ይህ እስከሚረጋገጥ በየጁምዓው አንዋር መስጂድ ተክቢራው ይቀጥላል እንዘጋጅ ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | 0928740990 | 0928740990 | 0911236732 | በ13/07/2004 እስላማዊ ግዴታ ይወጡ!! በሕዝበ ሙስሊሙ ሕጋዊ የመብት ጥያቄ ላይ የተለያዩ የመንግስት ባለስልጣናት በሚዲያዎች እየነዙ ያሉትን ማደናበር ለመቃወም ሁላችንም ቤተሰቦቻችን ጭምር በመያዝ የጁምዓ ሰላትን ለመስገድ እንዲሁም ኮሚቴዎቻችን የደረሱበትን ለመስማት አወሊያ እንገናኝ ሲል SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡<br><br>እስላማዊ ግዴታችንን ለመወጣትና የመንግስት ባለስልጣናትን እንቅስቃሴ ለመቃወም ቤተሰቦቻችንን ጭምር በመያዝ ጁመአን በአወሊያ በመገኘት ተቃውሞአችንን እናሰማ የሚል ቀስቃስ SMS መልዕክት በ13/7/2004 ለፋይዝ ማስተላለፉ |



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 0928740990 | 0928740990 | 0928179814 | ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡<br><br>በ23/08/2004 የመጅሊስ ምርጫ በምስጢር እየተካሄደ ነው ትግላችን ባዶ በማድረግ ድምፃችንን ሊቀማ ነው እና ሁላችንም ነገ በአወሊያና በአንዋር ተቃውሞአችን እናሰማ ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | | 0928740990 | 0928740990 | 0912496429 | በ16/08/2004 የሙስሊሙ ጉዳይ 11ኛው ሰዓት ላይ ደርሷል ፡፡ ሁላችንም የእስላም ወላፈኞች ልንሆንና እናሰማ ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | | 0928740990 | 0928740990 | 0911675875 | በ20/07/2004 የሙስሊም አባቶቻችን እና ወንድሞቻችን ደም በከንቱ አይቀርም!! በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም ያለው መንግስት ሐሙስ በETV በፎከረው መሠረት ጅምላ ቀን አርሲ ውስጥ 7 አህባሺዮ አንቀበልም ያሉ ሼሆችንና ወንድሞቻችንን ገድለው በርካቶችን አቁስለው ከመቶ በላይ አስረዋል፣ ይህንን በመቃወም የፊታችን ጁምዓ በመላው ኢትዮጵያ ሰልፍ ይደረጋል ሲል SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | | 0928740990 | 0928740990 | 0920643774 | በ25/08/2004 ነገ ጁምዓ ሰላማዊ ነገር ግን ጠንካራ የተቃውሞ ድምፃችንን በአንዋር እና በኑር/በኒን/ መስጪድ በመገናኘት እናሰማ በግፍ የተገደሉ ወንድሞቻችን ሸሂዴ (ሰማዕት) እንጂ ሽብርተኞች አይደሉም መንግስት ከሃይማኖታችን እጁን ያንሳ !! ሞት ሸሂዴ (ሰማእት) ያደርጋል እንጂ ከአላማችን ወደኋላ |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 0928740990 | 0928740990 | 0911146335 | በመስጂዳችን ብለን የታገልንለትን ገደል የሚከት መግለጫ መጅሊስ አውጥቷል፡፡ ቀጣይ ሂደታችንን ለማስቀመጥ ነገ አወሊያ እንገናኝ፡፡ አይኖርም ተብሎ የነበረው አወሊያ ነገ በደማቅ ሁኔታ ይካሄዳል ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | 0928740990 | 0928740990 | 0910097901 | በ21/10/2004 በሙስሊሙ ላይ የታቀደውን ሸር ለመመከትና በETV የተላለፈውን የምርጫ መግለጫ አስመልክቶ ኮሚቴዎቻችን አቋማቸውን ስለሚያሳውቁን አወሊያ እንገናኝ ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | 0928740990 | 0928740990 | 0913188063 | በ20/09/2004 ጁምዓ አወሊያ አይኖርም ሁላችንም ከጁምዓ ጀምሮ በየመስጂዳችን አስመራጮችን መርጠን በሚቀጥለው ሣምንት አወሊያ እንገናኛለን በETV ሬዲዮ እና በስብሰባዎች ላይ የሚነዙትን አሉባልታዎች እናወግዛለን ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | 0928740990 | 0928740990 | 0913983640 | በ08/09/2004 የለፋንለት ምርጫ ከንቱ እንዳይቀር ምርጫችን በመስጅዳችን በሚል አቋም ሁላችንም እሁድ በወረዳ 6 የስብሰባ አዳራሽ እንዳንቀር ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | | | | በ7/09/2004 የለፋንለት ምርጫ ፍትሃዊ ለማድረግ እና ድምፃችንን ነጥቀው አህባሾችን ለመሾም የሚደረገውን ጥረት ለማምከን ሁላችንም ድምፅ አወሊያ እንገናኝ ሲል SMS |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 0911217101 | 0911217101 | 0911564509 | አጋጣሚ በመጠቀም ረብሻ ለማስነሳት ይመቻል አስፈላጊ ጥንቃቄ ማድረግ አንርሳ ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፣<br><br>በ10/11/2004 አወሊያ የጦር መሣሪያ ኮሚቴው አስገብቶ ለሕዝቡ ሊያስታጥቁ ሲል ደርሰንበታል ብለው ፖሊስ በሚዲያ ሊያቀርብ ነው፡፡ በዚህም የህሰትና ተራ ድራማ ኮሚቴዎቻችን ሊያስር ነው ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፣ |
| ፯ | መሐመድ አባተ | 0928740990 | 0928740990 | 0911138252 | በ30/10/2004 ሕዝብ ያልመረጣቸው አመፀኞቹ መጅሊሶች የመንግስትን ሃይል ተገን በማድረግ ላፍቶ በሚገኘው አዲሱ መስጂድ ለመቆጣጠር ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ የአካባቢውን ሙስሊም እያዋከቡና እያሰሩ ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሙስሊም ህብረተሰብ ዝሁር ሶላት እዚሁ ላፍቶ እንዲሰግድ እና መስጂዱን እንዲታደገው በአላህ ስም እንጠይቃለን ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| | | 0928740990 | 0928740990 | 0911352926 | በ28/10/2004 ነገረ ጁምዓ አወሊያ አይኖርም በምትኩ አንዋር ድምፃችንን እናሰማለን ከጁምዓ ጀምሮ በየመሲጅዳችን አስመራጮችን መርጠን በሚቀጥለው ሣምንት አወሊያ እንገናኝ ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተ ላለፉን በተመለከተ፡፡<br><br>በ21/09/2004 ድምፃችን እንዳይጭበረበር ምርጫችን |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ምንዳዎን ከአላህ ይጠብቁ፡፡<br><br>የመጅሊሱ ውድቀት ተቃርቧል ሙስሊሙ ትግሉን እስከ ጫፍ ቀጥሏል በርቱ የሚል ቀስቃሽ የSMS መልዕክት በ1/6/2004 መለኮት ለተባለና በዚሁ ዙሪያ በመንቀሳቀስ ላይ ለሚገኝ ማስተላለፉ፡፡ |
| 5. | ካሚል ሸምሱ | 0911373436 | 0911373436 | 0911231140 | በ02/09/2004 ስለ ወደፊቱ በማሰብ ፀረ ሰላሞችን ለማሳፈር ጁምዓ ሁላችንም በየመስጂዳችን በመስገድ በዝምታ ሰላማዊ ትግል እናድርግ፡፡ መልስ በኮሚቴው በኩል ብቻ ይሰጠን ሲል ለ2 ሰዎች SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| 6. | ሰዒድ አሊ ጁሃር | 0911217101 | 0911217101 | 0913188612 | በ02/09/2004 ስለ ወደፊቱ በማሰብ ፀረ ሰላሞችን ለማሳፈር ጁምዓ ሁላችንም በመስጂዳችን በመስገድ በዝምታ ሰላማዊ ትግል እናድርግ፡፡ መልስ በኮሚቴው በኩል ብቻ ይሰጠን ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፣ |
| | | 0911217101 | 0911217101 | 09132114155 | በ16/09/2004 መጅሊሶች ዓመታዊ የቀጥባሬ፣ የአብሬትና የመውሊድ ፕሮግራም ማራመጃ ሊያደርጉ ስለተዘጋጁ ተካፋዮች በተቃውሞ ማስቆም አለብን ሲል ለአንድ ሰው SMS ማስተላለፉን በተመለከተ፣ |
| | | | 0911217101 | 0931393671 | በ06/11/2004 በአሁኑ ሰዓት አወሊያ ግቢ የፌዴራል ፖሊስ ገብተው ረብሻ ለመፍጠር እየሞከረ ነው፡፡ ሕዝቡንም ለማስወጣት ለሰደቃ የተዘጋጀውን በሬ ለመውሰድ ይህን |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | መጅሊስ አይወክለንም የጁመአ ትግል ይቀጥላል። ከአሁን በኋላ አይከፋፍሉንም ነጂስ መጅሊስና አህባሽ የአይሁድ ስራ ወያላ ስለሆነ እናወግዛለን አስተላልፉ። |
| | | | | 922151154 | |
| | | | 913383716 | | በ24/05/2004 ነግ ጠዋት 2:00 ሁሉም ሙስሊም በአወሊያ ተክቢራ እናደርጋለን እንፋዳትዘገዩ አደራ ቢያንስ ለ10 ሰው አስተላልፉ። |
| | | | | 922151154 | |
| | | | 912980664 | | በ14/06/2004 አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላዊ ወበራከቱ መጅሊስ ምርጫ በመላው ሀገሪቱ ግንቦት 5/2004 ይካሄዳል አለ አላሁ አክበር። |
| | | | | 922151154 | |
| | | | 913656900 | | በ14/06/2004 ሙስሊሞች ንቁ መጅሊስና መንግስት ከተለያዩ ሚዲያዎች እያደረጉ ያለውን እንቅስቃሴ እኛ ሙስሊሞች አንቀበልም ምርጫ ለመላው ሙስሊም ሊተው ይገባል የተጣሱው ሕገ መንግስታችን ይከበር አላሁ አክበር አላህን ፈርተው ለ10 ሰው ያስተላልፉ። |
| | | | | 922151154 | |
| | | | 914709484 | | በ24/05/2004 የጁመአ አወሊያ ቀጠሮ እንደተጠበቀ ነው ከሙሰኛ መጅሊስ ተብዬ ጋር ፊፅሞ አንደራደርም ከወንበራቸው እስካልወረዱ ሰላማዊ ትግላችን ይቀጥላል ጁመአ በአወሊያ። |
| | | | | 922151154 | |
| | | | 911694683 | | በ15/06/2004 ጅመአ በአወሊያ ከአሜሪካ የመጡ የበድር አባላት እንዲሁም የአፋር ተወካዮች ስለሚመጡ ሁላችሁም እንዳትቀሩ አላሁ አክበር ቢያንስ ለ20 ሰው ያስተላልፉ |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 928740645 | | 08/06/2004 ወሳኝ ጁመአ ኮሚቴዎቻችን መንግስትን አነጋግረዋል፡፡ አወልያ ይነገራል የተናቀው ሕዝብ ታሪክ ይሰራል ሰላማዊ ትግላችን ይቀጥላል ለ10 ሰው ያስተላልፉ፡፡ |
| | | | 922151154 | |
| | | 926867101 | | በ15/06/2004 ጁመአ አወሊያ እንስገድ አላህን የማይፈራው የመጅሊስ ሰው በFM ለመዋሸት ሞክሯል ማንን ይሸውዳል? ሃይማኖታችንን ጠብቀን ሰላማዊ ትግላችንን እንቀጥልበታለን ለ5 ሰው ይላኩ፡፡ |
| | | | 922151154 | |
| | | 913760305 | | በ08/06/2004 የአወሊያ ሙስሊም ተማሪዎች በሰላማዊ ሰልፍ ላይ ናቸው፡፡ ሌሊቱን በሙሉ ግቢ ውስጥ ነው ያሳለፉት ይህንን ለመቀላቀል ዝግጁ ነህ? |
| | | | 922151154 | |
| | | 912802763 | | በ06/06/2004 አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ መበረካቱ ሰኞ መፍትሔ ስለሚሰጥ ተማሪዎቹን አስገቡና ትምህርት ይጀምሩ በማለት እንዲገቡ ተደርጓል ሰኞ መፍትሔ የማይሰጥ ከሆነ ግን ትግሉን ኡማው ይቀጥላል ጥያቄው የተማሪው ሳይሆን የእያንዳንዳችን ነው መጅሊስን እንደጠላን በጋራ ያሳየነው የመብት አቋም ይቀጥላል ድል ከሀቅ ጋር ነው ተዘጋጁ፡፡ |
| | | | 922151154 | |
| | | 912802763 | | በ06/06/2004 የአወልያ ተማሪዎች ከመንግስት የተገባላቸው ቃል አምነው ገብተዋል ቃሉን ቢያጥፍ ግን ለሙስሊሙ ጩኸት ደንታ እንደሌለው ያሳያልና እራሳችንን እናዘጋጅ |
| | | | 922151154 | |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ነገ (8.11.2004) 3 ሚሊዮን ሕዝብ ወደ ታላቁ አንዋር መስጂድ ይመጣል ሁላችንም ነገ ጠዋት 2፡30 በአንዋር እንገናኝ ሲል ለአመፅ የቅስቀሳ ጥሪ በ7/8/2004 63 ሰዎች የ SMS መልዕክት ማስተላለፉን በተመለከተ፡፡ |
| 4. | ካሊድ ኢብራሂም | 922151154 | 922151154 | 912802763 | በ17/05/2004 አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበራከቱ<br>1. ሁላችንም ጁመአ አወሊያ እንስገድ፣<br>2. በየመስጂዱ ከሰላት በኋላ መጅሊስን በመቃወም አላሁ አክበር እናስተጋባ፣<br>3. የየመስጂዱ ኢማሞች ዱአ አድርጉ አስተላልፉ |
| | | | 922151154 | 911755245 | በ23/05/2004 በፊርማችን ከመረጥናቸው ሰዎች ለሌላ ወኪል እውቅና አንሰጥም ከእነሱ ሌላ በድብቅ ከማንኛውም አካላት ጋር የተደረገው ውይይት የመከፋፈል ዘዴ ስለሆነ ፈፅሞ አንቀበልም እውቅናም አንሰጥም ሙስሊሞች ንቁ፣ ጥያቄያችንን ለመቀልበስ ሙከራ እየተደረገ ስለሆነ ከተንኮሉ እንጠንቀቅ ሰላማዊ ትግላችን ይቀጥላል መጅሊስ የለም አህባሽ የለም አወሊያ የህዝብ ነው አስተላልፉ አላሁ አክበር!!! |
| | | | 922151154 | 911662242 | በ02/06/2004 የመጅሊስ መውደቂያው ቀርቧል፡፡ ሙስሊሞች በሰላም ትግላቸውን ከጫፍ እስከ ጫፍ ቀጥለዋል፡፡ አላህ ሁል ጊዜም ከሀቀኞች ነው መጅሊስ እንደሚለው እኛ አክራሪዎች ተስፈኞች አይደለንም እኛ ሕዝቦች ነን በሕዝብ አክራሪ ተስፈኛ ማለት ንቀት ነው መጅሊስ ሰፊውን ሕዝብ ንቆታል ቢንቀንም በሰላማዊ ትግላችን መጅሊስን እናወርዳለን ኢንሻ ኣለህ አላሁ አክበር ለ10 ሰው ያስተላልፉ፡፡ |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | እናስተጋባ፡፡ አላሁ አክበር ኩቡራ!!! እባክዎን ይህን መልዕክት ያስተላልፉ፡፡ |
| 3. | አህመዲን ጀበል | 0911174712 | 924146084 | 0911174112 | በ02/05/2004 ከመላው ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በሙሉ አርብ 03/5/04 የጁመአን ሶላት በአወሊያ አንድ ላይ ሰግደን አዲሱን የአህባሻን ርዕዮተ አለም የሚከተለውን መጅሊስን በመቃወም ከአወሊያ መስጂድ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገን ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ እናመራለን፡፡ |
| | | | 924807178 | 911174112 | በ02/06/2004 አሰላም አለይኩም ወራህመቱላህ ወበራኩቱ አልጀዚራ ሚዲያን በኢንተርኔት ለማግኘት ሞክሩ ድምፃችን ለአለም ይድረስ፡፡ |
| 4. | ያሚን ኑሩ | 0911012252 | 928796577 | 09110112252 | በ14/06/2004 ሙስሊሞች ንቁ መጅሊስና መንግስት በተለያዩ ሚዲያዎች እያደረጉ ያለውን እንቅስቃሴ እኛ ሙስሊሞች አንቀበልም ምርጫው ለመላው ሙስሊም ሊተው ይገባል፡፡ |
| | | | 912342458 | 0911012252 | በ21/06/2004 መጪው ጅመአ መንገዶች ሁሉ ወደ አወልያ ያመራሉ ቀኑ በአል በመሆኑ 350,000 ሰው ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል ኢንሻ አላህ በድል በአል መታሰቢያ ቀን ሙስሊሙ ሕዝብ ድል ያደርጋል አደራ አደራ ለ10 ሰዎች ያሰሙ፡፡ |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

# በሃይማኖት ሽፋን የተለያዩ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴዎች ለማነሳሳት በስልክ SMS እና በድምፅ ያደረጉዋቸው የመልዕክት ልውውጦች የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ/ቁ | የታርጌቱ ሙሉ ስም | ስልክ ቁጥር | SMS ያስተላለፈው ቁጥር | SMS የተቀበለው ቁጥር | ይዘቱ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቡበክር አህመድ | 0911246555 | 928796565 | 0911246555 | በ27/6/2004 ታሪክ የማይረሳው ንቀት መላው የኢትዮጵያ ሙስሊም ጥያቄ መልስ ሳይሰጠው ለ3ቱም መሰረታዊ ጥያቄዎችን በሃይማኖታዊ ግልቃ አልገባም ያለው መንግስት ሁሉም ባለበት እንዲቀቅል በFM 98.1 ቁጣ በተሞላበት ስሜት ትዕዛዝ ሰጠ:: ይህ ሆን የኢትዮጵያ ሙስሊም ውለታ ለሁሉም ቀን አለው ኢንሻአላህ አላህ የኢትዮጵያን ሙስሊም ከመንግስት ተንኮል ይጠብቀው ለ20 ሰው አስተላልፍ:: |
| 2. | አህመድ ሙስጠፋ | 0911244792 | 0911244792 | 0911426042 | በ23/4/2004 በፌርማችን ከመረጥናቸው ሰዎች ለሌላ ወኪል እውቅና አንሰጥም ከእነሱ ሌላ በድብቅ ከመንግስት ጋር የሚደረገው ውይይት የመከፋፈል ዘዴ ስለሆነ ፈፅሞ አንቀበልም ሰዎችንም አናውቃቸውም ሙስሊሞች ንቁ ጥያቄያችንን ለመቀልበስ ሙከራ እየተደረገ ስለሆነ ከተንኮሉ እንጠንቀቅ ሰላማዊ ትግላችን ይቀጥላል መጅሊስ የለም አህባሽ የለም አወሊያ የሕዝብ ነው አስተላልፉ አላሁ አክበር፣ |
| | | | 0911244792 | 0911457799 | በ1-1/6/2004 አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላህ ነባ የካቲት 11 ቀን ከጧቱ 3:00 አዲስ አበባ የቲያትርና የባህል አዳራሽ (ማዘጋጃ ቤት) በመገኘት ተቃውሚችንን በመጅሊስ ላይ |



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
National Intelligence & Security Service

ቁጥር Ref.No. ጋወ47/ዝ/05
ቀን Date 08 ጥቅምት 2005

ስልክ Tel. 011-551 2766
ፖ.ሣ.ቁ P.O.B. 5721 / 5718

ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- መረጃን ስለመላክ

በሽብርተኝነት የወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው ክስ የተመሰረተባቸው የእነ አቡበከር መሐመድ/13 ሰዎች/ በፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ አንቀፅ 14/1 መሰረት በቴክኒካዊ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ያሰባሰብናቸው የSMS የ9 ሰዎች ያሉበት 12 ገፅ እና የድምፅ የ12 ሰዎች ያለበት 17 ገፅ የሆነ በፅሁፍ የሰፈረ መረጃ መላካችንን እንገልፃለን ::

ከሠላምታ ጋር

ዳንኤል አሊጋዝ

የህግ አገልግሎት ሃላፊ

ከዋናው ጋር ቃመሳከሯል
ፊርማ

625

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ነገ ሁላችንም እንዘጋጅ የአምባገነኑ የኢሃዲግ የጦር ግንባር ጋር እና
የፈራረሰውን የኢህዲግ መንግስት ለመቃወም እንዘጋጅ!!!!!!!!!!!

ታዘቤዎችን ፣ ሳሙኤል ፣ ካሳሁን ፣
አነቆሲን ፣ ተናቆኝ ፣ ያተገኝ
SAMI 25/12/04

አባቴን ለጎዳች አገሬ አልመለስም አርፋለሁ ፣
መቅደስ መኮንን 25/12/04

ገመዚል ፣ አልማሪ -
ሀገ ፣ ቀሽጣ ፣ ለኔ ቃኝ
የተባኝ
25/12/04

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ _____



http://ethcriminalawnetwork.com/

# ወንድሞቻችን በአወሊያ ሸሂድ እየሆኑ ነው እባካችሁ ይህ በዳይ መንግስት በዛሬው ለይላችን እንጣለው ሁላችንም ለነፃነት እንታገል

06/11/04 እ....እ.....እ....እያልኩ ወደ አላህ እያለቀስኩ ነው ሰው ግን እንዴት ዛሬ ይተኛል ፍትህ ናፍቆናል ወንዱ፤ሴቱ፤ሽማግሌው፤ወጣቱ ፤ህጻናት...አህ..... ሁሉም ወደ አወሊያ ይጎርፋል ከሌሊቱ 4፡00 ገደማ መሆኑ ነው የፊታችን እሁድ 8/11/04 ታላቅ ሀገር አቀፍ የሰደቃ እና የአንድነት ፕሮግራም ይካሄዳል መባሉን የሰሙት የመንግስት ካድሬዎች ፕሮግራሙን ለማደናቀፍ ሳምንቱን ሙሉ ሲሞክሩ ዛሬ ጁምአ ላይ የገቡትን ንብረቶች ለመቀማት ሲሞክሩ ውለው ነበር ነገር ግን በአላህ ሀይል ምንም ሳያደርጉ መበተን ተጀምሮ ነበር ነገር ግነ ወደ ማታ አንዳንድ መጥፎ ነገር ሊያደርጉ የሚሞክሩ መሰል። አገር አቀፍ አከባበር፡እንደመሆኑ ከተለያዩ ክ/ሀገራት የሚመጡ እንግዶች መስጅዱ ላይ እያረፉ ነበር በድንገት አንድ ነገር ተሰማ ያም ምን ነበር ፌደራሎች የአወሊያን መስጂድ የውጪ በር በጉልበት በመክፈት ይህን ለሃይማኖቱ የቆመ ህዝብ ሰቅጣጭ በሆነ ሁኔታ ደበደቧቸው የሞቱ ውድሞችን ነገ በአላህ ፊት ከነጥሩ ስራቸው እንገናኛቸዋለን።

6፡00-7፡30 ገደማ አብዛኛው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመስጂዳቸው ተሰባስበው አዛን አሰሙ ከየአካባቢው የተሰበሰበው ምዕመናን ወደ አወሊያ ጉዞ ጀምሮ ነበር ነገር ግን የአስለቃሽ ጭስ በመልቀቃቸው ምክኒያት ህብረተሰቡ መሄድ ሳይችል ቀርቶ ወደየመስጂዱ ሄደዋል በዋናነት በቤተል፡በመርካቶ በብዙ መስጊዶች ሌሊቱን እዛው ለማሳለፍ እየተሞከረ ነው። በጠሮመንገድ ላይ በፊናነስ አስፓልት ላይ በአስለቃሽ ጭስ ሰውን እየቡቱ ነው ሰው እያፈሱ ነው ስዉም በዱአ እና በስቲግፋር ሌሊቱን እያሳለፉ ይገኛል።

አለሁመ ኢሽሀድ..... አለሁመ ኢሽሀድ .....
አለሁመ ኢሽሀድ!!!!!!!!!!!!!

ታዛቢዎች ፣ ሚሊሻ ፣ ፖሊስ ፣ ደህንነት ፣ አነዳሪ ፣ ተክለ ፣ ሰንሰለት
አንክሱ: ሽጉጥ: ሌሎች: ሌ.ወጣ: እዩታለሁ
AMI 25/12/05

ደግ ነገር ተናግሮ አመሰግኑ እናገኛለሁ
በሚንስትሩ መሳሪያ የተገደለ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[Darul hijjra yeda'awa kibeb] በአንዋር የምትገኙ ሙስሊሞች ቪዲዮ** Saturday, July 21, 2012 1:27 PM

**From:** "Seada Hussen" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>

**To:** "Darul hijjra yeda'awa kibeb" <245808822185464@groups.facebook.com>

Seada Hussen posted in Darul hijjra yeda'awa kibeb



**Seada Hussen** 6:26am Jul 21

በአንዋር የምትገኙ ሙስሊሞች ቪዲዮ
መቀረፅ
እዳትረሱ ድል የሙስሊም ነዉ
አላህአክበር !!!!
ከአንዋር ውጪ ያለንም ሁኔታውን በካሜራ
ወይም በሞባይል እንቅረፅ ሙስሊም ሁሉቴ
አይሸወድም

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

LCLN

29/12/2004

29/12/2004

29/12/2004

ከዋና ፈርማ



627

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[United Voice of Ethiopian Muslims Against Ahbash] ድምፃችን ይሰማ** Wednesday, July 18, 2012 12:22 PM

**From:** "Seada Hussen" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>

**To:** "United Voice of Ethiopian Muslims Against Ahbash" <333050436773268@groups.facebook.com>

Seada Hussen posted in United Voice of Ethiopian Muslims Against Ahbash



**Seada Hussen** 5:22am Jul 18

ድምፃችን ይሰማ
የፌታችን ጁምአ በመላዉ ሀገራቱ የታላቁን
የረመዳንን ወር ድባብ በጠበቀ መልኩ
ተቃዉሟችንን በአስደንጋጭ ዝምታ መግለፅ
እንዳለብን ጥሪ ተላልፎል:: በመሆኑም
የፌታችን ጁምአ በሁሉም መስጂዶች በተለይም
በታላቁ አንዎር መስጂድና ኑር መስጂድ
የተለያዩ መፈክሮችን በመያዝ አፋችንን
በፕላስተር ወይም በጨርቅ በመሸፈን
አስደናቂ የሆነዉን ተቃዉሟችንን መግለፅ
ይኖርብናል:: በዚህ ጁምአ ላይ ተቃዉሟችንን
በተከቢራ ሳይሆን የምንገልዉ በአስደንጋጭ
ዝምታ ነዉ:: ከጁምአ ሰላት በሁላ ሁሉም አፍን
በመሸፈን ዝም ጭጭ በማለት ተቃዉሞዉን
መግለፅ ይኖርበታል:: ይህንን የዝምታ
ተቃዉሞ ለሁሉም እናስተላልፍ::

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

LCHR

ስም፡ አያሌው ፈንታ
29/12/2004

ስም፡ ሸሪፍ ሙሐመድ ሁሴን 29/12/2004

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ



http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[YeMuslimoch Dimts የሙስሊሞች ድምጽ] አስደናቂ ንቃተ-ህሊና !!!!! !"** Friday, July 20, 2012 1:11 PM

**From:** "Ebadurehman Mohammed" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>

**To:** "YeMuslimoch Dimts የሙስሊሞች ድምጽ" <458458377517344@groups.facebook.com>

Ebadurehman Mohammed posted in YeMuslimoch Dimts የሙስሊሞች ድምጽ

**Ebadurehman Mohammed** 6:11am Jul 20

አስደናቂ ንቃተ-ህሊና !!!!! !"

ምንም አንኳን ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን እየጠየቅን ያለውን ህጋዊ ጥያቄ ለማደባበስ፣ የአሸባሪን ታፔላ ለመስጠትና የጭፍጨፋ ደባቸው ለመፈጸም እየቆፈሩት ያለውን ጉድጓድ ጀግናው፣አስተዋይና፣ለመሪዎቹ(አሚሮቹ) ታዛዥ ሙስሊም ህብረተሰብ ጉድጓዱን እየዘለለ ማለፉን ቀጥሏል፡፡ አላሁ አክበር ! አለሁ አክበር !



View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

LCLN

ክፍ፡ ፈሀይ፡ ፃንና፡ ጋሪ

አሚሩ ጎሌ 29/12/2004

ታዛቢ

፡ አህመድ አንዱላ ግብረ 29/12/2004

ታዛቢ ሀንዳቆ ገንዘቦ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ



http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[We ARE muslims] ለኢስላም መታሰር አይደለም ለመሞትም ዝግጁ ነን** Friday, July 20, 2012 8:10 AM

**From:** "Ebadurehman Mohammed" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>

**To:** "We ARE muslims" <weare.muslms@groups.facebook.com>

Ebadurehman Mohammed posted in We ARE muslims

**Ebadurehman Mohammed** 1:09am Jul 20

ለኢስላም መታሰር አይደለም ለመሞትም ዝግጁ ነን

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

29/12/2004

29/12/2004

29/12/2004

9/4/2012 9:45 AM

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

## [FEZEKIR CENTER] ምንን ፈርተን ሞት ምንን ፈርተን እስር ሰው ዋሽቶ ይታሰራል ሰው ሰርቆ...

Tuesday, July 31, 2012 8:51 PM

**From:** "Ebadurehman Mohammed" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>
**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Ebadurehman Mohammed posted in FEZEKIR CENTER

**Ebadurehman Mohammed** 5:50pm Jul 31

ምንን ፈርተን ሞት ምንን ፈርተን እስር ሰው ዋሽቶ ይታሰራል ሰው ሰርቆ ይታሰራል ለእስልምና መታሰር እድሉ አይገኝም እንጂ ከተገኘ ሸረፍ ነው ወንድሞች ሞትንም ካገኘ ኢዝ ነው ክብር ነው ያን የሚታደሉት የተመረጡት ብቻ ናቸው አላህ የመረጣቸው ለዚህ ሀላፊነት ያጫቸው ትልቅ ባሮች ብቻ ናቸው አላህ ከወሰነው ውጪ የሚሆን ነገር የለም (ኡስታዝ አቡበከር አህመድ)



View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

LOLIN

ክፍሉ ጸሐፊ 29/12/2004

ታዛቢ ፈንታሁን ተስፋ 29/12/2004

ኢ/ር ማሞ ጥላሁን 29/12/2004

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ



http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[We ARE muslims] አስቸኳይ ስለሆን ለ 5 ሰው ሜሴጅ ይላኩ!** Saturday, July 21, 2012 8:43 AM


**From:** "Ebadurehman Mohammed" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>

**To:** "We ARE muslims" <weare.muslims@groups.facebook.com>

Ebadurehman Mohammed posted in We ARE muslims

**Ebadurehman Mohammed** 1:43am Jul 21

አስቸኳይ ስለሆን ለ 5 ሰው ሜሴጅ ይላኩ!
ወገን ንቃ! ዛሬ አንዋር መስጅድ ተቃውሞ አለ!
ኮሚቴዎቻችንን በህሰት በሽብርተኝነት
አስረው ሊጨርሷቸው ነው! —



View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

LCHR

ከፌ. ፖሊስ የተገኘ ነው
አሳሪ ዓ/ል
29/12/2004

ታዘቡ;
1 ዓለሽ አሻግሬ ገዛው; ፊርማ 29/12/2004
ታዘቡ ረዳኤ ጌታሁን 29/12/2004

ፊርማ ተመሳከሯል

9/4/2012 9:46 AM



6223

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[FEZEKIR CENTER] መንግስት ሚዲያውን ወታደሩንና ደህንነቱን ተጠቅሞ እኛን ደካሞች ቢበድለን...**

Saturday, July 21, 2012 2:09 PM

**From:** "Ebadurehman Mohammed" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>
**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Ebadurehman Mohammed posted in FEZEKIR CENTER

**Ebadurehman Mohammed** 7:09am Jul 21

መንግስት ሚዲያውን ወታደሩንና ደህንነቱን ተጠቅሞ እኛን ደካሞች ቢበድለን ቢያስረንና ቢገድለንም አብሽሩ ያጀመአ ለኛም የሁሉ ነገር ባለቤት የሆነው አላህ አለልን አብሽሩ አብሽሩ አብሽሩ

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

9/4/2012 9:47 AM

f 1

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[FEZEKIR CENTER] በአሁኑ ሰዓት ምን ማድረግ አለብን ?** Friday, July 13, 2012 9:36 PM

**From:** "Nesru Khedir" <notification+zj4os4=_s4yc@facebookmail.com>
**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Nesru Khedir posted in FEZEKIR CENTER



**Nesru Khedir** 2:36pm Jul 13

በአሁኑ ሰዓት ምን ማድረግ አለብን ?
1_ወደ አላህ ማልቀስ ዱዓ ማድረግ
2_በተቻለን አቅም የተጣሩ ኢንፎርሜሽኖችን ቶሎ ቶሎ በትኩሱ ማድረስ
3_በተለይ በ አለም ዓቀፍ ቋንቋዎች (ዓረብኛ እንግሊዝኛ ፈረንሳይኛ >>>) ዜናውን ማሰራጨት
4_ሁላችንም በየቦታው ያለን በቡድን በቡድን በመሆን እንሰባሰብ (ዛሬ ሙስሊሙ እቤት ማደር የለበትም) የቻለ ወደ አዎልያ አልያም በየ አቅራቢያው ያሉ መሳጂዶች ላይ ማደር
5_ለማንኛዉም የጸጥታ አካላት በመተናኮል ጉልበት እንዳይጠቀሙ እድል አለመስጠት

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

LCLN

ክፍ: ፖሊስ: ፕሮግ: ፲፰፻፸፭

ስም: ጌታ

29/12/2004

ታሳሪ

፩ ሳጅን: ገብሬ 29/12/2004

፪ ዳኛሽ ጥሩነህ ግዛው፣ 29/12/2004

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ _____

20

635



http://ethcriminalawnetwork.com/

ጉባ የእንዛዝ መሠይቶች መጠቃ ገቢ፡፡
ስለው ተሰጥኖ መጠኑም ቴክኒኮች የሚሠሩንን ሥራዎች
ገበሬው ሳንዲሰን ተሳትፎውና ተሞክሯቸው (demonstration)
መሆኑን የሚያሳይ ልማ ሥራ ግለሰቡ መመስረት
አንዱ ሥራ ሌላ ጉዳዩን ላስተ መተማመል የሚሠሩ
መሆኑን ገለጹ፡፡

ማክሰኞ 9 Tuesday

- የታሰሩት መጠየቅ ጉዳዩ ለእነሱ ቀን የሚሰጡ
ከተገላገሉ በኋላ ሃኪሞች ቦሌሰዎች የሚሠሩ
ገለጻ ጉዳዩ ከሚሠሩ ጉዳዩ ከሚሠሩ የሚሠሩ
ተቸገሩ የእንዛዝ የሚሰጡ ጉዳዩ ከሚያሳዩ
ለሰዎች ሁሉ ተሰጥኖ ሳሠራ ሳይሰጡ ከሚያሰሙ
ሰዎች ከአስተሳሰብ ተሰጥኖ ሳሠራ ተሰጥኖ የተለያዩ ችሎታዎች
ሰዎች የሩሲ ከአስተሳሰብ ችሎታ (የአእምሮአዊ) ያለመገለጽ
ሰዎች ሁሉ ሰዎች ሰዎች ሰዎች ሰዎች ጉዳዩ ገለጻ

ረቡዕ 10 Wednesday

ECHR
The Office of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Ombudsman
Human Rights Investigation
http://etheriminalawnetwork.com/

ከመሆን ይድናል፡፡ ለዚህም በመጅሊስ ምርጫዎች መስለመ ህብረተሰብ ንቁ ተሳታፊ መሆን ይኖርበታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ምንጭ ዊኪሊክስ ነው፡፡ የዊኪሊክስ መረጃዎች ምንም እንኳ የአሜሪካ ባለስልጣናት እውነትነታቸውን ባይክዱም በሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ ለሚተዳደረው አህመድ መኑር ግን የሚዋጡ አይደሉም፡፡ ለዚህ የሚጠቅሰውም በዊኪሊክስ መረጃዎች ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ለአሜሪካኖች ተናግረውታል ተብሎ የተጠቀሰውን ሀሳብ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስልምና፣ እስላማዊነትና ሽብርተኝነትን ለያይቶ የማየት ችግር አለባቸው፡፡ ምንም እንኳ ይህን አስተሳሰባቸውን በይፋ ለህዝብ ባይናገሩትም ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ሁኔታ "AT THE EPICENTER" OF TERRORISM SINCE THE SEVENTH CENTURY በማለት ገልጸውታል:: ‹‹ይህን ካሉ እኮ እስልምና ለኢትዮጵያ አደጋ እንደሆነ ያስባሉ ማለት ነው፡፡ የእኛ ጠቅላይ ሚኒስትር ደግሞ እንዲህ ይላሉ ማለት ይከብደኛል፡፡ እውነት ብለው ይሆን እንዴ›› ይላል አህመድ፡፡

LCLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ናቸው ብሎ የሚያስባቸው ሰዎች መካተታቸውን በመገንዘብ የኢትዮጵያ መንግስት ከመጋረጃ ጀርባ የራሱን ሰዎች ለማስገባት ተጽእኖ ማድረጉን ዊኪሊክስ ያወጣቸው መረጃዎች እንደሚጠቁሙ ዑስማን ያስረዳል፡፡ እንደ ሰነዶቹ የኢትዮጵያ መንግስት መቼም ቢሆን የመጅሊስ ምርጫ በግልጽና በፍትሀዊነት ተካሂዶ ስልጣኑን የሚይዘው አካል የአስተሳሰብ መርህ ያሳስበዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ‹‹ሰለፊ›› ናቸው ብሎ የሚያስባቸው ሰዎች የመጅሊሱን ደጅ እንዲረግጡ አይፈልግም፡፡ ስለዚህም ምርጫ ሲካሄድ የራሱን አጀንዳ ሊያስፈጽሙለት የሚችሉ ሰዎች ጎልተው እንዲወጡ አስፈላጊውን ነገር ከመጠቀም አይቦዝንም፡፡ ይህ ደግሞ ኢህአዴግ ራሱ የህገ-መንግስቱ መርህ ነው ብሎ የሚያምንበትን መርህ መጣስ ነው፡፡

እንደ ዑስማን ገለጻ ይህ አይነቱ አሰራር ያልተለመደ አይደለም፡፡ የህገራችን መሪዎች ‹‹ቆመንለታል›› የሚሉትን መርህ እንኳ ሳይመቻቸው ሲቀር ከመጣስ ወደኋላ ያሉበት ጊዜ የለም፡፡ አሁን ያለው የህገ-መንግስት ጥሰትም የዚሁ አካል ነው፡፡

ከዑስማን በተቃራኒ ያሉ አንዳንድ ወገኖች ግን መንግስት በሀይማኖት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ሊገባ የሚችልባቸው የህግ አግባቦች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ የህዝብን ሰላም ሊያደፈርስ የሚችል ግልጽና ተጨባጭ አደጋ ሲኖር እንዲሁም የዜጎች መብት ሲጣስ መንግስት ጣልቃ የመግባት መብት አለው ይላሉ፡፡ መንግስት በሙስሊሙ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ሊገባ የቻለውም ከፍተኛ ስጋት ስላለው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

መንግስት ስጋት ቢኖረው እንኳ ስጋቱ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን በአግባቡ ካለማወቅ የመነጨ እንደሆነ የሚያምኑ በርካቶች ናቸው፡፡ መንግስት በሙስሊሞች ዙሪያ የተሳሳተ አመለካከት እንዲይዝ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ የመጅሊስ ሀላፊዎች የሚሰጡት የተዛባ መረጃ ዋነኛው ነው፡፡

ከአመታት በፊት አራት ኪሎ አካባቢ በፈረሰው መስጅድ የተነሳ በተፈጠረው ተቃውሞ አንዳንድ ሙስሊሞች ድንበር በማለፍ ተቃውሞውን ለፖለቲካ አጀንዳነት ሊጠቀሙበት እንደሞከሩ በወቅቱ የመጅሊሱ ምክትል ፕሬዝዳንት የነበሩት አቶ ኤሊያስ ፊድማን ሲገልጹ ነበር፡፡

አቶ ኤሊያስ ለአሜሪካ ኤምባሲ ሰዎች እንደገለጹት ተቃውሞው ከመብረዱ በፊት እንዳንዳንድ ሙስሊሞች ጠቅላይ ሚኒስቴሩ መለስ እንዲወርዱና ሸሪዓዊ መንግስት እንዲመሰረት ሲቀሰቅሱ ነበር፡፡

አቶ ኤሊያስ ይህን መሰል የተዛባ መረጃ ከየት እንዳመጡ ባይታወቅም ይመለከታቸዋል ብለው ለሚያስቧቸው አካላት ግን ማስጠንቀቂያ ቢጤ ሰጥተው ነበር፡፡ የዊኪሊክስ ሰነዶች እንደሚገልጹት አቶ ኤሊያስ ለውጥረቱ ሙስሊሞችን ተጠያቂ አድርገዋል፡፡ ‹‹በህገ-ወጥ መንገድ ገንዘብ ከሳዑዲ በማስመጣት ህገ-ወጥ መስጅድ ሊገነቡ ነበር›› በማለትም ሙስሊሞችን በመኮነን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በወቅቱም ከአዲስ አበባ ከንቲባ ብርሀኑ ደሬሳ ጋር ተገናኝተው መነጋገራቸውን ጠቅሰዋል፡፡

የመጅሊሱ መሪ ከዚህም የባሰ ‹‹መረጃ›› የኢትዮጵያን መንግስት በመወከል ‹‹ምክር›› ግልጸዋል፡፡ እንደ እርሳቸው አባባል በምዕራብ አሮሚያ ነፍጥ ያነገቡ ሙስሊም አክራሪዎች መስጅዶችንና ኢማሞችን አጥቅተዋል፡፡ እነዚህ ታጣቂ ቡድኖች መኖራቸውንና ጥቃት እያደረሱ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግስት ቢያውቅም ‹‹የህገራቱን ገጽታ ከመጠበቅ አንጻር›› ጉዳዩ እንዲሸፋፈን አድርጓል፡፡

ይህ እንግዲህ የሙስሊሞች ብቸኛ መሪ ድርጅት እንደሆነ ከሚነገርለት መጅሊስ ከፍተኛ ባለስልጣን የተገኘ መረጃ ነው፡፡ ‹‹የኢትዮጵያ መንግስት ይህን መሰል መረጃ ከጉዳዩ የቅርብ ባለቤት (From the horse's mouth) ሲደርሰው ለሙስሊሙ ያለውን አሉታሳብ የማይለውጥበት ምክንያት ይኖራል ወይ›› ሲል የህግ አማካሪው መሰውድ ሸረፉ ይጠይቃል፡፡ ይህ መጅሊሱ በታሪኩ ከሰራቸው አሰቃቂ ግድፈቶች አንዱ ነው ሊልም ያክላል፡፡ የህግ አማካሪው እንደሚያስረዳው መንግስት የመጅሊስ አመራሮች ወርሃ በአግባቡ እንዲደረግና ለፖለቲካ ስርአቱ ሳይሆን ለእውነት መቆም የሚችሉ ሙስሊሞች ቢመረጡ እንዲህ አይነት የተዛባ መረጃ ይዞ ከሙስሊሙ ህብረተሰብ ጋ ሆድና ጀርባ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ሕዝብን የማታለል ጥበብ ወይስ...?

ኢትዮጵያዊያን በሩቁ ከሚያዩዋቸውና ሊጠጓቸው ከማይፈልጓቸው ነገሮች አንዱ ፖለቲካ ነው፡፡ ፖለቲካ በቀን ከቀን ውሏችን ከሚያጋጥሙን ክስተቶች ጋር የተቆራኘ እንደመሆኑ መጠን ፖለቲካን ለመጠጋት አለመፈለግ ምክንያት የለሽ ፍርሀት ነው፡፡ አሪስቶትልን የመሳሰሉ ፈላስፎች ‹‹የሰው ልጅ ከማህበረሰቡ ጋር ራሱን አስማምቶ መኖር መቻሉ በራሱ ፖለቲከኛነቱን ያሳያል›› ይላሉ፡፡ በአሪስቶትል እምነት ሰዎች ሁሉ በተፈጥሯቸው ፖለቲከኞች ናቸው፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን መምህሩና የፖለቲካ ሳይንስ አዋቂው አቶ አርካ አቦታ ‹‹ፖለቲካ ማን ምን መቼና እንዴት ማግኘት አለበት የሚለውን በጥበብ መመለስ ነው›› ይላሉ፡፡ የአሪስቶትል መምህር የነበረው ፕሌቶ ፖለቲካን The Supreme and most important art ሲል ከፍተኛ ቦታ ያለውና እጅግ አስፈላጊው ጥበብ በማለት ይክበዋል፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ፖለቲካን The art of deceiving people (ሕዝብን የማታለል ጥበብ) በማለት ከፕሌቶ በተቃራኒ ያስቀምጡታል፡፡ ሁሉም ግን በአንድ ነገር ይስማማሉ፡፡ ፖለቲካ ጥበብ ነው፡፡ ፖለቲከኞች ደግሞ ጥበበኞች፡፡

የአንዲት ሀገር አጠቃላይ ዕድገትም ሆነ ውድቀት በአብዛኛው በፖለቲከኞቿ እጅ ነው፡፡ የፖለቲከኞቿ አስተሳሰብ ሀገሪቱ በምትከተለው ፖሊሲ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፡፡ የሀገርን የፖለቲካ አቅጣጫ መሰረት ሊጠቁሙ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ደግሞ የፖለቲከኞቹ ኢዲዮሲንክራሲ ነው፡፡ ኢዲዮሲንክራሲ የአንድ ሰው አጠቃላይ ዳራ፣ አስተሳሰቡና ተጽዕኖ ያደረጉበትን ነገሮች አጠቃሎ የያዘ ቃል ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የ2ኛ ደረጃ ተማሪ እያለ ሙስሊሞች በጀመዓ ሲሰግዱ ሲያይ የጥላቻ ስሜት የሚያድርበት ወይም የተለያዩ እንቅፋቶችን ለመፍጠር የሚጥር አንድ ሰው በኋለኛው ዘመኑ ከፍተኛ የሚባል የፖለቲካ ስልጣን ቢይዝ ለሙስሊሞች የሚኖረው አመለካከት ጤናማ አይሆንም፡፡ ይህ እንግዲህ የሰውዬው ኢዲዮሲንክራሲ አካል ነው፡፡ የሐገራችን ፖለቲከኞች የኋላ ታሪካቸው ምን ያህል ግልጽ እንደሆነ ባይታወቅም የዛሬው ማንነታቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርግባቸው ግን ግልጽ ነው፡፡ ይህ በእያንዳንዱ ፖለቲከኛ ህይወት ላይ የሚንጸባረቅ እውነታ ነው፡፡ ፕሌቶ ፖለቲካን ‹‹ከሁሉም በላይ አስፈላጊው ጥበብ›› ሲለው ለመልካም ነገር ከሚል የህዝቦችን አኗኗር ለማሻሻል ያለውን ከፍተኛ ሚና በማሰብ ነው፡፡

ከግንቦት 1997 በኋላ በሀገራችን በነበረው አለመረጋጋት ላይ ጥናት ያደረገ አንድ በድን ኢትዮጵያዊያን ፖለቲካን እንደ አደገኛና ክፉ መቅሰፍት እንደሚያወርድ አካል እንጂ ሰዎች አኗኗራቸውን ለማሻሻል እንደፈጠሩት የጥበብ ዘርፍ እንደሚይመለከቱት ያትታል፡፡ ይህ አስተሳሰብ ሊመጣ የቻለውም ባለስልጣኖቻችን ህብረተሰቡ የፖለቲካ ንቃቱ እንዳያድግና መብቱን በአግባቡ እንዳይጠይቅ በሳሉበት የክፉ መቅሰፍት ምስል እንደሆነ የፖለቲካ ሳይንስ ተማሪው ናትናኤል አረጋ ይገልጻል፡፡ እንደ ናትናኤል ገለጻ ፖለቲካ ውስጥ የገቡ ሰዎች በጤናቸው ሲመለሱ አይታዩም፡፡ አንድም የለየላቸው ቀጣፊ ይሆናሉ፡፡ ወይም ደግሞ በቀድሞ ዘመን ጸረ-አብዮት፣ አሁን ደግሞ ሙሰኛ፣ ኪራይ ሰብሳቢ ወዘተ የሚል መለያ እየተለጠፈባቸው የተለያዩ እርምጃዎች ይወሰዱባቸዋል፡፡

ኢትዮጵያዊያን ፖለቲካን ከሚጠሉባቸው ምክንያቶች ሌላኛው የፖለቲከኞቻቸው ‹‹የእኔ አውቅልሀለሁ ስሜትና ቅጥያጣ ነጭ ውሸት›› እንደሆነ ናትናኤል ይናገራል፡፡ ‹‹ፖለቲከኞቻችን ለህዝብ የሚያቀርቡት ዲስኩርና ድርጊቶቻቸው ለየቅል ናቸው›› ሲልም ያክላል፡፡

በናትናኤል ሀሳብ የሚስማማው የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህሩ ዑስማን አደምም (ስመ. ተቀይሯል) ‹‹ፖለቲከኞቻችን ራሳቸው ያረቀቋቸውና የህገ-መንግስቱ መሰረቶች ናቸው የሚባሉ መርሆችን ጭምር ጥሰዋል›› ሲል ይከሳል፡፡ እንደ ምሳሌም ከህገ-መንግስቱ መሰረታዊ መርሆች ውስጥ አንዱ የሆነውና የሙንግስት በህይማኖት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትን የሚከለክለውን ድንጋጌ ጥሰት ይጠቅሳል፡፡ መንግስት በሙስሊሙ ህብረተሰብ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ መግባት የጀመረው የአህባሽ ጉዳይ ከመምጣቱ ከጅማታት በፊት እንደሆነ ዑስማን ይገልጻል፡፡ ካለመታት በፊት በመጅሊስ ያጋጥሩ የነበረው ምርጫ ‹‹ሰለፊይ›

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ
26-12-04
http://ethcriminalawnetwork.com/

ወዳጇ እንደሚለው ‹‹አሁን በአገር የእለት ጉርስን ማሸነፍ የማይችሉ ምንዱባኖች በርክተዋል፡፡ ህሊያዊ ነፃነትን የተነፈጉ መከረኞች ቁጥራቸው ሸ ሆኗል፡፡

አስተዳደራዊ ፍትህን ያጡ ዜጎች የነፃነቱ ትንፋሽ የእባብ መርዝ ሆኖ ነድፏቸዋል፡፡ ከሀገር ተሰዷል፡፡ ዘብጥያ ወርደዋል፡፡ ጥቂት የማይባሉ በችሎት ደጃፍ ለመኮልኮል የቤተ-አምልኮ ደጃፉን የሙጥኝ ለማለት የስላሳው ወጥመድ ስጋት ሆኖባቸዋል፡፡ለፈጣሪያቸው ያደሩ በእለት ሰላታቸው፤‹‹ልቦቻችንን ለፈጣሪያችን ስንል ለሀሴም ፍጥረታት የእዝነት ምንጭ አድርግልን፡፡ስህተቶቻችንን ኃጢያቶቻችንን በምንዳ እና በበጎ ነገር ቀይርልን፡፡››ሲል በሰንበት ወልዖታቸው ‹‹አቤቱ ለበዳዮች ልቦና ስጣቸው ወደ ህሊናቸው መልሳቸው፡፡ እብሪትን አርቅላቸው›› ይላሉ፡፡ እዚህም እዚያ ያሉ መከረኞች የዙፋኑ ጭቆና በቤተ አምልኮአቸው ዙሪያ ያለው ምዝበራ፣በመከራ ቤዛቸው፣ በሽሂድነት ፍትህ ለትውልዱ ነፃነትን ይመኛሉ፡፡

‹‹ሠላም በስምሽ ግፍ መሰራትም ይቁምልሽ!›› ይላሉ፡፡ሰላም ይብዛ፡፡ የፍቅር እና የደህንነት የልማት ብርሃን እንዲሆን

ታዛቢ

መሐመድ ሓሰተ

26-12-04

ታዛቢ

ለኔታ ሀሩን ወራዳ

26-12-04

LCLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሸብረቱኞች›› ነን አምባገነኖችን ማሸነፍ የሚችል ሜንቃ የሌለን የሚል የጋራ ድምፅን ህገ-መንግስትን እና ህግን መሰረት ያደረገ የመፍትሄ መልስ ከመንግስት ይጠ...ያል፡፡ የሃይማኖት መሰረት ያለው የአገሬው ሕዝብ ‹‹ሰለ ሃኖታቹህ እኛ እናውቅላችኋለን ሲሉት ያመዋል፡፡ይከፋዋል፡፡››ይህ የመገፋት የመብት ጥያቄን ከፖለቲካ ጥያቄ ጋር ለውሶ የህገ መንግስቱን የእምነት ነፃነት መገደብ ያሳስባል፡፡ ‹‹የሃይማኖት እኩልነት የማይቀበል፣ የመንግስት የሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ያለመኖሩን የማያመን ፀረ ሰላም፣ ፀረ ዲሞክራሲ፣ ፀረ ልማት›› የሚሉ አማላይ ታላቶች በመደርደር ሽቅብ ያሉት ቁልቁል እያዩን በማሸማቀቅ መከራችንን ሲያበዙት መከረኞችን እንድንፈልግ ማድረጋቸው ማንን ይጠቅማል?

ሙስሊሞች በሃይማኖት ውስጥ ለሚፈጠረው ኺላፍ አማኞች ወደ ቁርአን እና ሐዲስ ተመልሰው በሸራ ሊፈቱት የሚችሉበት ሃይማኖታዊ መርህ ውስጥ ይስተናገዳሉ፡፡ ይህንን ጥረት እነ አቶ ኤልያስ ፊድማን በረጃጅም እጆች ተጠምዝዘው የእነሙፍቲህ ሸህ ዑመር ኢድሪስ በጋራ ችግሮችን የመፍታት ጥረታቸው እንዲመክን የተደረገበት ታሪክ ብዙዎቹ ያስታውሱታል፡፡ የተከበሩ ዑለማዎች በተ...ንኑባቸው መሪዎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ መደረጉ ዛሬ እንቆቅልሽ የሆነባቸው ጥቂቶች እንደሆኑ ግምቱ የሰፋ ነው፡፡ ያ የሙስሊሞች አንድነት እንዲበጣጠሱ ሕብረታቸውን እንዲበትኑ የተፈጠረው የትናንት ጫና ዛሬም ጥላው እንደገዘፈ ነው፡፡

የዲሞክራሲ ጭንብል ተላብሶ አንድነትን የማላም በሃይማኖት ተቋሞች ውስጥ የተሰባሰቡ ኪራይ ሰብሳቢዎች በህጋዊነት ሽፋን ዘመቻቸውን እየቀያየሩ የመሆኑ ግምት የሰፋ ነው፡፡ ‹‹ሙስሊሞች መንግሥት የአሕባሽን ሥልጠና በሊባኖስ ደረሳዎች እንዲሰጥ ማመቻቸቱ አንዱን ነው ለይቶ ሊላውን ለማዳከም መስራቱ በሃይማኖታችን በመግባትም የህገ-መንግስት መርህን ይጥላል፣ ››ይላሉ ሲል ሪፖርተር ጋዜጣ ሚኒስቴሩን የተከበሩ ሽፈራው (ዶ/ር) ተክለማርያምን ጠይቋል፡፡ የሚኒስቴሩ መልስም፡ ‹‹ይህ የወሐብያዎች እና የወሐብያ ድምጽ የሚያስተጋቡት ድምጽ ነው፡፡›› ሲሉ መልሰዋል፡፡ የህዝበ ሙስሊሙን ቅሬታ ሸሽ አብደላህ አልሐረሪ የሚሰጡት ትምህርት ‹‹ነባር›› የእስልምና ትምህርት የሚከተሏቸውን አስተምህሮቶች ነው ‹‹በአህባሽ ዙሪያ የሚነዙት መደናገሮች የወሐብያው ቡድን ነው›› ሲሉ አጣፍተውታል ሚኒስቴሩ፡፡ አቶ ሽፈራው በኢስላም ‹‹ነባር›› ‹‹አዲስ›› የሚል መርህ ያለመኖሩን አማካሪዎ ሊነግሮት ይገባል፡፡ይህ የሰማያዊ እምነቶች ባሕሪ ነው፡፡ ሙስሊሞች ሁሉ የእምነት መርሃቸው የቁርአን እና የሐዲስ ትምህርት ብቻ ነው፡፡ እንደ ዘመን እና እንደ ጊዜ ሊኖሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን መፍትሄ የሚያፈላልግ መርህ አላቸው፡፡ ኢጅማዕ ..... ቂያስ የመሳሰሉ፡፡ለሳለ ሥልጣናቱ አሕባሽን መቃወም ወሐብይነት ነው ብሎ ለመፈረጅ የሚያስደፍር መርህ አለመኖሩን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ፍረጃ በቱሉይ የህዝብ ስልጣን ባለቤት የሆነ የፖለቲካ ሰው በሃይማኖት መርሆች ላይ የሚሰጠው አስተያየት ከፖለቲካ መርህ አኳያ እንጂ ከሃይማኖታዊ ጽንሰ ሃሳብ ሲነሳ ጣልቃ ገብነቱ ይጉላል፡፡ እንደ አዲስ አበባ የፍትህ ቢሮ ሃላፊ አቶ ጸጋዬ ጎይለማርያም ተውልደ እየተቀጣበለ የሚስቅበት አሳፋሪ ስህተት ውስጥ ይጥላል፡፡ ‹‹ቅንጅት እና ኢህአዴግ እንደ እንደማይሆኑ ሁሉ ወሐብይ እና ሰኔይ አንድ ሊሆኑ ለይቻለው›› ማለት ትዝብት ላይ የሚጥል ይሆናል፡፡

ሙስሊሞች የአኼራ ወንድምና እህቶች ናቸው፡፡ ኺላፍ የዲናቸው ሐሩ መሆኑን አይስቱትም፡፡ይህ በእውቀት እንደሚስተናገድም የመቼታል፡፡ አሸን በፖለቲካ መርህ መተሮ መሰነጣጠሩ የዓጋጃ ፖለቲካዊ ፍጅታ እንጂ የአኼራ ጥቅም የለውም፡፡አማን ሙስሊሞች ሲሰባሰቡ የበላይ ፌርዋ የርዘራሄ ብርሃን፣ ከሌሎች ጋር አብሮ [illegible] ሊሻን የተጣበሰ መሆኑን ያምናሉ... ይህን ቁርአን እና የነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጎዳና ይነግረናል፡፡በተግባርም ኖረናል፡፡ የመቻቻል ባለስልጣን እና የመጅሊስ ሹመኞች በሚያገኙት የሚዲያ ሚዲያ የህዝበ ሙስሊሙን ‹‹የመብት ጥያቄ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ››በቅንነት ከማየት ለተግባራዊ ምላሽ የህዝብን ብሶት ከመስማት ከላይ ሆነው የወንጀል ድርጊቶች ከሃማኖት ጋር ማቆራኘታቸው ዛሬ ለምን ያስከፍላል፡፡ መንግስት ዛሬ በሃይማኖት ዙሪያ ያለውን መነቃቃት ‹‹ሸብርተኛ፣ ወሐብይ፣ አክራሪ፣ የፖለቲካ ጥቅም ፈላጊ፣ መንግስትን ለመገልበጥ ያሴሩ›› እያለ በተለያዩ አገላለጽ ተመሳሳይ ሃሳብ ማናንፀባረቁ የዜጎችን ልብ ያሻክራል፡፡ በርካታ ሙስሊሞች ከታች ሆነው የመከራ መከረኞችን ቋንቋ እየተናገሩ ስሙን ሲሉ በጥያቄያቸው ቀጥተኝነት ላይ ባላድርሻ አካላት የተለያዩ ውንጀላን ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡የተፈጠሩ ወንጀሎች ድራማዊ አካሄድ ከሊላቸው የህገራቱ ‹‹የመንጀለኛ መቅጫ ህግ›› ‹‹የሽብርተኞች ህግ እና የፍትህ-ብሔር ህግ›› ምን እየሰሩ ነበር?›› ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡በጅምላ ሃይማኖታችንን ከወንጀል ጋር አጣምሮ ማብጠልጠል የመንግስትን አቋም ከሚደግፈው ባለስልጣናት አይጠበቅም የሚለው ሙግት እንደጋለ ነው፡፡ በተገኘው መድረክ ሁሉ ሚንስቴሩ ዶ/ር ሽፈራው፣የመንግስታት ግንኙነት ተቋማዊ አደረጃጀት ዳይሬክተሬት ጀኔራል አቶ በእውነቱ፣ በፌደራል ጉዳዮች የሃይማኖት ድርጅት እና የማኅበራት ምዝገባ ዳይሬክተር ወይዘሮ ፋንታዬ፣ የሃማኖቶች ጉዳይ ዳይሬክተሬት ጀኔራል አቶ መርሳ ረዲ ፣የኢሕ ፍትህና ፀጥታ ቢሮ ሃላፊ አቶ ወጋዩ የሙስሊሞች አጀንዳ በተነሳበት መድረክ ሁሉ በምክር ቤት ባይወሰንም ወሐብያ የሚባል ‹‹አክራሪ›› ‹‹ሸብርኛ›› ‹‹ጭራቅ›› መሆኑን በልሳናቸህ የመንግስት አቋም መሆኑን ተናግራችኋል፡፡ ወንጀሉንም ዘክዝካችሁል፡፡ወንጀል የሰላም ፀር መሆኑ አሚጋች አይደለም፡፡ የተፈፀመው ወንጀል ‹‹ወሐብይነት››በሚባል አካል ተፈፀሞ ከሆነ ጉዳዩን በሕግ አግባብ ማየት ተገቢ ነው፡፡እኛ ‹‹የኢስላም›› ተከታይ ‹‹ሙስሊሞችን›› የሚሰሙ ጽህዝበ ሙስሊሙ፡ አቋም ከግምት ሳይገባ በሃይፎማኖታዊ ውግዝ የሆኑ ወንጀሎችን ሁሉ ስም አየተሰጠ የመፈረጁ ተልዕኮ ‹‹የማን አጀንዳ ነው?››የሚል መጠይቅ ሆኗል፡፡ ይህ የጅምላ ውንጀላው ‹‹ድራማ›› ማንን ለማስረግ? እነማንን ‹‹ለማሸማቀቅ እንደታሰበ የቆቅ ያህል ነቅተናል በማለት ድርጊቱን በጥርጣሬ የሚጠብቁ ቁጥራቸው ሽቅብ ነው፡፡‹‹ከመጉጋቢ የወጣች በግ በቡቄላ እንዳትበላ››ብለን አደነታችንን አጠንክረናል የሚሉ ያነግበኔ ፅሁ ከፍል ጥምረቶች አዘዚያ አፍ ለአፍ ገጥመው በመከረ-አሸራቸው ሲጫየዩ ቆይተዋል ፡፡

http://ethcriminalawnetwork.com/

መሰንታቸውን ለመንግስት በንዳና ግልውን ሲናገሩ ብዙዎች መንግስት ከቅሬታችን ጎን ይሆናል ባለበት ሽኔታ «የአሕባብ ልዑ
አብደላ አልሐረሪን ስማቸውን ( ጠፉት የወሐቢያው ኔት ወርክ ነው›› ሲሉ የህዝብ ሙስሊሙ ተቃውሞ ድምፅ ደፍጥጠዋል...››
በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የፌዴራሊዝም ስርዐት እና የመንግስት ግንኙነት ተቋማዊ አደረጃጀት ማጠናከር ዳይሮክቶሬት ጀኔራል
አቶ በእውነቱ ብላታ ደበላ፡፡ ይህን ያሉት ደግሞ በቢሾፍቱ ከተማ ለመገናኛ ብዙሃን በተሰጠው ሥልጠና ላይ ነው፡፡ አቶ በእውነቱ
ይህንንም ጠይቀዋል ‹‹ፂሙን በደንብ ትልቅ አሳደጎ ከፖኪስታን የመጣውን ሸኽ መቼ ተቃወማችሁ?›› በማለት፡፡ይህ የግለሰብ እና
የቡድን መብትን ከግምት ያላማስገባት የነፃነት ጫና ከመሆን ባሻገር ‹‹የምንደግፈው እና የምንቃወመውን›› ‹‹ሸኽ›› እስከ መምረጥ
ሲያደርሳቸው ታይቷል፡፡ ዳይሮክቶሬት ጀኔራል አቶ በእውነቱ ብላታ ፡፡ እሳቸው ስለ ሸኽ ፊትናው ሲናገሩ አይተናል ፡፡ይህ የጣልቃ
ገብነታቸውን እንዲህ ሲሉም ተከላክለዋል፡ ‹‹እኝህ ሰው (አብደላ አልሐረሪ)ማለታቸው ነው፡፡ ‹‹ሃይማኖት ለማስተማር ባለመቻላቸው
ነው የተሰደዱት፡፡ ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ ምን ችግር አለው?›› ሲሉም ያማባባሉ፡፡ የፌዴራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሚንስቴር ክቡር
አቶ ሽፍራው (ዶ/ር) ‹‹ወሐቢያ ምንም ማቆሚያ ሳይኖረው ከሳውዲ ዓረቢያ እና ከፖኪስታን ሰዎች እየመጡ ሕዝበ ሙስሊሙን
በማደናገር ሲያስተምሩ ቆይቷል፡፡ በሕዝቦች ዙሪያ የሚነዙት መደናገሮች የወሐቢያው ቡድን ናቸው›› ብለዋል፡፡መቼም ከፖኪስታን
የሚመጡ የዳዕዋ ሰዎች የጀመአቱል ተብሊግ የመርከዝ ሰዎች በዳዕዋቸው ተደናግረናል ከሚለው ስሞታ ይልቅ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን
መርከዛቸው መቀዛቀዝን፡ በዳዕዋ ስም ከፖኪስታን የሚመጡም ሆነ እነሱም ወደ ፖኪስታን የሚያደርጉት ‹‹ቪሩጅ ፊሰቢሊላህ ››
መውጣት ላይ እቀባው ስለተደረገባቸው ቅሬታ እንደገባቸው ለማንም ምስጢር አይደለም፡፡

‹‹የሕዝብ ሥልጣን ባለቤቶች ይህ የሃይማኖት መንደር በውጭ ጣልቃገብነት፡ አውቅልሃለው አካሄድ በመንፈሳዊው መንደር
መርመስመሰቸው ተገቢ አይደለም፤ እጃችሁን አውጡ!›› የሚል ግልጽ ተቃውሞ፤ የህገ-መንግስት ደንብ ይከበር ጥያቄ፡ ሰላማዊ የሆነው
የህገ መንግስታዊ መሰረት ያለው የመብት ጥያቄ ጨቋኝ ከመንግስት መገልበጥ ጋር ማያያዝ ‹‹ሰላም ሲበዛ እራስ ያማል እንዴ?››
ያስብላል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡ ‹‹ቢሾፍቱ የፌዴራል ጉዳይ ሚንስቴር ከኢትዮጵያ ብሮድ ካስት ባለስልጣን ጋር በተብብር ባዘጋጀው
የመገናኛ ብዙሃን ሥልጠና የሃይማኖት ተቋማችን የመጅሊስ አመራሮችን መምረጥ የእኛ የአማኞች ድርሻ ነው፡፡ ሙስሊሙ አሁን
በመጅሊስ የተሰገሰጉ የማይወክሉት መሪዎች ይውረዱ የሚል የተቃውሞ ድምፁን በሰላማዊ መንገድ እየጠየቀ ነው ተብሏል፡፡ ሕዝበ
ሙስሊሙ መንግስትን ፡፡ ይህ ሀሳብ ቡተነሳበት አግባብ በፌዴራል ጉዳይ ሚንስቴር ዳይሬክትሬት ጀኔራል አቶ በእውነቱ
ብላታ‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምቤቱ (መጅሊስን) ህጋዊነት አንቀበልም ማለት የኢትዮጵያን መንግስት አንቃበልም ማለት ነው፡፡
የምን ጠጋ ጠጋ ዋናው ትኩረት መጅሊስ አይደለም፡፡ ይህን መንግስት አንቀበልም ነው፡፡ በደንብ ግልፅ አደርጎ ይውጣልን እና
ይለይልን፡፡ ዞር ብሎ ወደ ጫካ ›› ብለ መጅሊሱን መቃወም መንግስትን መቃወም ነው፡፡የሚል እንደምታ ያለው በሳብ ሰንዝረዋል፡፡
የሕዝበ ሙስሊሙን ጥያቄ ከመንግስት መገልበጥ ጋር ማቆራኘታቸው እና መውንጀላቸው በሕግ አግባብ ላለመጠየቃቸው አምክኖአዊ
ነገር አይኖርም የሚሉትን ሀሳብ እጋራለሁ፡፡እሳቸው የህዝብን ድምጽ ደፍጥጠዋል፡፡ አንፈራም አንጃ ‹‹አስፈራሪቱ ኮሚኒስ፡፡ሃፊ የመሸ
ቢመስልም ነገ መንጋቱ ተፈጥሯዊ ህግ ነው የሚለውን የአዛውንቶች ቢሂል ዕናት እና ሶብርን እንድንሳበስ አድርጓል፡፡አቶ በእውነቱ
በህግ ቁንጽ አግኝጋር ከተባለ ለኒ ‹‹ሙስሊሙ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በትግላቸው የሃይማኖታቸው ተቋም አደርጅተው ቢቋቁሙም
በአዋጅ ያለተቋቋመ በማዘዙት ፍጆደ አታደለ እንደነበር መረጃው አለኝ፡፡እርሶ ግን እንዴት የመብት ጥያቄ የመሰለ በትግል ችግል
የሚያደርጉ ሁሉ እንቅስቀሴያቸው መንግስትን ከመገልበጥ ጋር ያቆራኛሉ?የመንግስት ሥልጣን በሕዝብ ድምፅ የመጣ አይደለም እንዴ?
መንግስታችን እንዲህ ነው እንዴ የሚያስበው ? ‹‹ዞር ብሎ ወደ ጫካ መሞከር ነው፡፡ ትጥቅ ገዝታችሁ ዕድሉን መሞከር ነው፡ትልቁ
ግባቸው ‹‹ኢስላማዊ መንግስት መመስረት ነው›› ››መባሉ የሚያውቁትን ሕዝብ ፍረጃ ግር ብሎኝ ‹ሰላም ሲበዛ እራስ ያማል እንዴ?
›ብዬ ብጠይቅ ወዳጄ የሆነው የልማታዊ ጋዜጠኛ ‹‹ሥልጣን ላይ መቆየት የሚፈጥረው አንባገነንነት ነው፡፡ ፍሬ ይተጥናሀል እዚያ ቤት
ያለው ቁስል በእኛ ቤት የእግር እሳት ነው፡፡›› ነበር ያለኝ፡፡

‹‹መክሬ መክረኞችን አንድ ይደር ጋል››

ወዳጄ እንዲህ ይላል ‹‹አዴስ ዘመን›› ሚዘጠልጠል ሲያምርህ ለሁለት የፌዴራ ሞገድ አደንዳ ሰተህን ለ ‹‹ሐጉህ›› ያከለዎግ በጣ
ግብዓት ስትከጋጅ ጠርዋር፡፡ በማሻከም እረስህን ታሊት ብታገኝ ግር አይበልህ፡፡ ‹‹ያንተ ነፃነት እጅህን በትዘረጋ ሊሎችን አስክልካህ
ድረስ ነው›› የሚለው የየዋነት ፖለቲካ ነው፡፡ በአገርህ ያለው ነፃነት ማንዴላ የተናገዐት የተግል ፍሬ እንዳይመስልህ፡፡ ሙስሊሞች ስለ
ሃይማኖታቸው የተቋም ነፃነት በሰላማዊ መንገድ መታገል የጀመሩት ትናንት እና ጠዋት መስሎህ ከሆነ ስህተት ላይ *ወደቀህልህ፡፡››
ታሪክን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ዲን ልፋት ያስፈልገዋል፡፡ ትግል ነው፡፡ ለዚህ እማኝነት ‹‹የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሞኞቆናና
የትግል ታሪክ›› የሚለውን የአሕመዲን ጀበል የታሪክ መጽሐፍ ማንበብ የትናንት ጠባሳ ለዛሬ ሰላማዊ ቆንፍ ብርሃን ይሆናል፡፡ የታሪኩ
ምእራፍ አውድ ዘመን የራቀ ከሆነ ያ196ቱን ዘፋን የነቀነቀውን በንዳና ወጥቶ ‹‹የሃይማኖት መብት ጀንቱ 13 ጥያቄዎች›› ደርድሮ
የለመጥ ብርሃን ችቦ የፊንጢጣውን የሙስሊሙን ትውልድ የሰላማዊ ትግል ታሪኩን መፈተሽ ግድ ይሰፈ፡፡ ይፍሮችም ልብ እንድንል
የታሪክ ወራሽነታችንን የስታውሳል፡፡ ሙስሊሞች ብለገሩ ሰፊ ቁጥር አላቸው፡፡መንግስትን ማቆም ማመንግሥትን ሙሽር የሚያስችል
የሰላማዊ ትግል አቅምን ህገ-መንግስቱን እና ህግን መሰረት ያደረጉ ፍትህ ይስፈን የሚል የወገኖች ቁም ፈቅድ ታሪክ ንባባቸው የደበዘዘ
አይደለም፡፡ ቅዱስ ቁርአን ‹‹ጭካኔየችው ዕድልን እንዳያድርግህ...›› በማለት ይመክራል፡፡ ፍትህ ሲዛባ ህገ መንግስት
ሲጣስ... ጣልቃ ገብነት ሲበዛ... መብት እና ነፃነትን መጠየቅ የሕገርካ ሂሊም ዘመቀባት ‹‹ሽብርተኛ›› የሚል ፍረጃ ከተሰጠ ‹‹አዎ››

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ሰላም ሲበዛ እራስ ያማል እንዴ?

የሱፍ ጌታቸው

በዓለም ላይ ከሚገኙ መርሆች እና ሕዝብን በአንድ ጥላ ማሰባሰብ የሚችል ትልቁ ፅንሰ ሀሳብ ሃይማኖት ነው፡፡ በዚህ መርህ የሚገኘው ሰላም የፍፁማዊነት ኒሻን አለው፡፡ የመንፈሳዊ ሕይወት ደህንነት ነው፡፡ የእምነት ነፃነት ነው፡፡ ዛሬ ዛሬ ይህ የሰላም ማረፊያ ፊተና ውስጥ ወድቋል፡፡ ታሞ ስውነቱ የከዳው ገመምተኛ መስሏል ፡ግን ለምን? የሃይማኖት ተቋማችን የነፃነት ሽማው ጨቀየ ?

## ‹‹ዞርብሎ ወደ ጫካ..››

የሰሚኑ ወንድሞቼ ‹‹ሰላም ተበዘኽ ርዕሰኽ ይህመካ›› እንዲሉ ሰላም ሲበዛ እራስ ያማል (አስር ጊዜ ሰላም የሚል ሰላም ይነሳል) እንዲሉ፡፡

አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሕውሓት ፓርቲ በብረት ፍልሚያ ድል ቀንቶት (ደርግን ደምስሶ ልትሉት ትችላላቹህ) ሬሳ ተራምዶ ወደ ቤተ-መንግስት በገባ ማግስት ‹‹የአብዮት ጥበቃን›› ‹‹ሰላም እና መረጋጋት›› ጥበቃ ተክቶ እንደነበር የሕውሓት መርነት ድርሳን ይነግረናል፡፡

ሰላም የሃይማኖት መሰረት እና ሃይማኖት የሰላም ነፀብራቅ መሆኑ ይነገራል፡፡ ዛሬ በሰላም እና መረጋጋት ስም ግፍና የደም በለአ የለም ለማለት የሚያስደፍር ኹኔታ ፈለም፡፡ ብዙዎች ባለመረጋጋት እና በሥጋት ማዕበል ወጀቡ ይናጣሉ፡፡ ባለመተማመን እና በፍርሃት ተንበርክከው መግኘታቸው ያሳስባቸዋል፡፡ በየዘመኑ የሚፈራረቁ ‹‹ነፃነት›› የሌላቸው ‹‹ነፃ›› አወጪዎች የመንፈሳዊ ተቋማትን በሸ.ሙተ ጠቅልለው መያዛቸው ይነገራል፤ወይም በእጅ አዙር የሃይማኖት ተቋም መሪነታቸውን (ኢ.ማምነታቸውን) ያንጸባርቃሉ፡፡ ሁሌም እነሱ በሰላማዊ ሃያማኖት ተልዕኮ ውስጥ በሕብራዊነት ውህደት በብዙሃነት ጥምረት ሰላም እንደሚያናጥባቸው ይነገራል፡፡የብዙዎች ፍትህ ይስፈን መርህ የሽብር ቀለም ይቀባል፡፡ የሁሉም የእምነት ተልእኮ በሆነው ‹‹ከክፋት የመከልከል በበጎ የማዘዝ ቤተ አምልኮ ደጃፎች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ካልተሰበከበት፣ ካድሬ ካልተሾመበት ሰላም የለም የሚል ወከባዎች በዝተው ይታያሉ፡፡ ጨቋኞችን የማረቅ ትዕዛቶችን የማላቅ የሰላማዊ ተልዕኮ መሰነቂያ የሆነው የመንፈሳዊ ሕይወት መንደር ‹‹ህሊናዊ ነፃነቱ ተሚል፣ በጣሊቃኒስት ታምሷል›› ብለው የሚወቅሱ በርካታ ናቸው፡፡ የሃይማኖት አማኝም ሆነ ኢ-አማኝ ፓርቲው የእንጀራ ገመድ በሆነላቸው ጠርናፊዎች ካልተጠረነፉ ‹‹ሰላም ተበዛኽ ርዕሰኽ ይህመካ ››በማለት እንድን ተርት ያደርጉናል፡፡

በሃይማኖት ተቋማት ዙሪያ የፖለቲካ ትኩሻቸውን ለማፈርጠም «የሕዝብ ውክልና» ዙፈኖቸውን ከፈጣሪ የተቸረ ግርማ ለማጎናጸፍ ‹‹ትናንሽ አማልክት›› ሆኖ ለመገኘት ‹‹የምናምነውን ከመምረጥ አልፈው ‹‹የሚናምነውን›› መርጦ ድጋፍ እስከ መስጠት የተደረገውን የሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ይቁም ! ሕግ ይከበር፡፡ ሕዝብ ይከበር! ማለት በአክራሪነት ሊፈረጅ ታይቷል፡፡ ‹‹መንግስት በሃይማኖ መንደር አይግባም፡፡ ሃይማኖት በመንግስት አልፍኝ አይገባም፡፡›› የሚለው ሕግ መንግሥት የመንግስት ባለሥልጣንን አይዳኝም እንዴ?!የሚል መጠይቃዊ ግርታ መልስ ናፍ ቋል፡፡ የመንግስት ጣልቃ ገብነቱ በቤንች ላይ ሲሆን በትሩ ጠንካራ፡ ሥፍራው ዋርዜዳ መሆኑ ይገለፅበል፣በማልሳቱ ደግሞ ለምን ለቤተ-መንግስት ሲሆን «በፖለቲካው ዘርፍ እና በፖቲቲ ተግባ ያልተሳካላቸው መሸሸጊያቸው ይሄራሉ ሃይማኖት እና ሚዲያን ነው» የሚል የጉኩረት ማስለሚያ ማሸማቀቂያ ይፈጠራል ይህ ለሚታዊ ጋዜጠኞች ልማት አልባ የዜና ፍጆታ ቢሆን እንጂ ማንንም አያሳምንም፡፡

‹‹ሞር ሲል አልወደም›› የሚል የነባር አታሞ መደለቅ ለማንስ ሰላም ይሰጣል ?

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ‹‹የአሕባሽ አስተምህሮት አይጫንብን!›› የሚል የተቃውሞ መርህ አንግበው ሲቃወሙ ‹‹በሃይማኖት ያለማስገደድን መርህን ሰንቀው›› እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ተቃውሞው የቀረበላቸው ባለድርሻ አካለትም ይህ ስላማዊ ዋያቂ የዲሞክረሲያዊ ህገ-መንግስታዊ መብትን መሰረት ያደረገ ‹‹ሃጌታ እና ፍታደኝነትን›› የለየ መፍትሄ ሩቅ ሊሆንባቸው አይገባም፡፡የአገሬው ሙስሊሞች እጃችንን ጠምዝዛቹህ የአህባሽ አስተምህሮትን ልጋታቹህ አትበሉን የሚል የመረረ የጋራ ድምፃቸውን ሆሽብር ቸለም ቅብት፡ የሰላም አደፍራሽ አድርጎ መፈረጅ ተገቢ አይደለም፡፡ መቼም በሰልጣን ላይ ያለው መንግስት መንግስትነን ሐረር ዘሪሚያ ዩንቨርስቲ...አዲስ አበባ መምህራን ኮሌጅ ሰንዳፋ የፖሊስ ኮለጅ ዩንቨርስቲን እናዝበታለን የሚለው መከራከሪያ ውሃ ባያነሳም በክፈልነው ግብር የተመሰረተው የትምህርት ተቋም ውስጥ የአሕባሽ ሥልጣና መስጫ የተደረገበት ምክንያት መንግስት ለእኛ ኢትዮጵውያን ሙስሊሞች አስቦ የተለየ ድጋፍ ማድረጉ ፍታህዊነቱን አያንፀባርቅም፡፡በሃይማኖት እኩልነት መርህ፡ መንግስት የሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ደንብን የተላለፈበት ማሳያ ቢሆን እንጂ፡፡ ያንን ሁሉ አልፎ የአሕባሽ አስተምህሮት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በደማችን እና በሕይወት ግብር ባቆምናቸው መስጊዶቻችን በመንግስት የማስፈፅም አቅም እና የማመቻቸት እገዛ ባለመረጭናቸው ፡ ባልወከልናቸው የመጅሊስ ሹማምንቶች እና ባለመጅሊስ መዋቅር አስተምህሮቱን አንጋትም፡፡ እንዘሀ ልሚለው የጋራጉድምቸው፡ ሰላማዊ ተቃውሚቸው፡‹‹ሰላም ሲበዛ እራስ ያማል›› አይነት ሰላስ እየተሰጠ መሆኑ ያሳስባል፡፡ ‹‹ሮያቂቸንን እየጠማዘዙብን ነው፡፡›› ‹‹ወገባዊ ክብራችን ምንድን ነው፡፡ ‹‹የመንግስት ሽብት ግራ ፈጅጋባን ነው፡፡›› ‹‹የድምፅ አቅማቸን ይመን ይህል ነው፡፡ የሚል ሙጠይቅ እዘህም እዘያ እሰማለሁ፡፡ ሰላማዊ ተቃውሞ፡በአንድ ሰላት በጅምላ ጀመአዎች የእኛ ሞገስ ቂኔን ክብረት ውስጥ በመሆኑ ከዚህ የበለጠ ደረታችንን የምንሰጥበት የሚያኮራ የደንቃ ሕይወት ቦለም›› የሚል የፅኑነት መርህ ከእሳት ወደ ኋለት መጨመሩ ለምሳሌ እልባት የወሰደው ጊዜ የፈጠረው ፍተሃዊ መሆን ግምት የሰፋ ነው፡፡ለሰላማዊ ተቃውሞው የተሰየ የውንጀላ ማስቀየሻ እና ፍርጃ መሰጠቱ ደግሞ ፊርጀ ብዙ ጥርጣሬ ከማጫሩ በዘለለ የሚጨምር ፍጆታ አያሚላም፡፡በርካታ ኢትዮጵውያን ሙስሊሞች ቀር

ከዋናው ጋር ተመሳክሮ ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ለንዳይኖረን ሁሌም ‹የሒጃብና የጀመዓ ሶላት መብታችን ይጠበቅ!› የሚል ማላዘን እጣ ክፍላችን እንዲሆን አድርገውብናል። ከዚህ ውጪ እንዳናስብ የማድረግ ሜራ ሠርታችሁብናል። ሙስሊም ተኮር በሆኑ ጉንተላዎች እንድንገነፍል፣ ‹አላሁ አክበር!› ብለን ድምጻችንን ለዓለም እንድናሰማ ትጎነትሉናላችሁ። እኛም በዚህ የጅል ሜራ ወጥመድ ውስጥ ባለመግባታችን ‹ምስጋና ይግባው ለዓለማት ጌታ!› እንላለን።››

‹‹እናንተ ‹መንግሥት ሃይማኖትን ተንተርሶ ሕዝብን መበደል ያቆመበትን ሥርዓት አምጥተናል› ብላችሁ ብትደሰኩሩንም፣ **አሁንም እንደ ሕዝብ እየተበደልን ነው። ‹ሥርዓት ሲቆሽሽ፣ አመራር ሲጠለሽ፣ በትረ ሥልጣኑን ጥቂቶች ሲፈነጩበት፣ በነፃነት የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያልጸደቀውን ሕግ ሲጭኑብን፣ መብታችንንና ጥቅማችንን ሲነፍጉን፣ የተቃውሞ ጥያቄያችን ምላሽ ሲያጣ፣ ማኅበራዊ እድገትና ብልጽግና ሲያሽቆለቁል ማነው የተኛው?› ብሎ መጠየቅ፣ የማያስተኛን ማፈላለግ የአንተ የሸኽ ሩጎኒይ የወፈፌ ጥያቄ ነው› አትበሉኝ።**››

በሐረር ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ውሎ አዳራቸውን በዚሁ ካምፓስ ያደረጉ ከየክልሉ የተውጣጡ የመጅሊስ አባላትና የሙስሊሙ ተወካዮች ላይ አፍጥጠው… ‹‹እኔ ሸኽ ሩጎኒይ ‹ማነው የተኛው?› ስል ጠየቅኳቸው። ወይዘሮ ክሊንተን እዚሁ መጋላ ፊንፊኔ በሚገኘው የአፍሪካ አዳራሽ ለአፍሪካ መሪዎች ‹እናንተ መሪዎች እንቅልፍ ላይ ካልሆናችሁ ሕዝብ ጨቋኝ ገዢዎችን ላለመቀበል እየታገለ ነው› ሲሉ እኔ ሸኽ ሩጎኒይም እናንተን እላለሁ፡- ‹ሥርዓቱ የፈለፈላችሁ መንጋ ሙሰኞች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች! ብቸኛ የአገር ተቆርቋሪ መስላችሁ እንቅልፍ አትንሱን። በሕግ ሽፋን ሕግ ወጥ ተግባር የሚፈጥሩብንን ሽብርተኞች አግዱልን። ምክር ቤቱ የሚያውቀው፣ እኛ ያልተስማማንበትንና የላፀደቅነውን የትምህርት ሚኒስቴር ደንብ አትንጫጩብን› ስንላችሁ ‹አክራሪ› አትበሉን። የሃይማኖት ተቋማችንንም መልሱልን› ስል እጠይቃለሁ። ጩኸታችንን ስሙ! እኛም ‹ማነው የተኛው?› ብለን እንጠያየቅ። እናንተም ‹አክራሪ፣ ሽብርተኛ› እያላችሁ ሥጋት አትሁኑብን። እኔ ሸኽ ሩጎኒይ…!››



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ _____

http://ethcriminalawnetwork.com/

‹‹ያ ጀማዓ! የምንከተለውን መገሠብ እነሱ መርጠው ሲያጠምቋችሁ፣ እኛ ላንሰማችሁ ነገር እናንተ እኛን ‹ጋቱ› ስትባሉ ‹ለምን?› ለማለት ፈራችሁ?›› ሲሉ ጠየቁ ሸኸ ሩጎኒይ - በአዳራሹ ከተሰበሰበው ሕዝብ መሐል ተቀምጠው።

‹‹በአዳራሹ ውስጥ ያሉ ከየክልሉ የተውጣጡ ‹የሕዝበ ሙስሊሙ ተወካዮችና›› የእለት ጉርስ ናፋቂዎች የወሰዱት ሥልጠና ለምን አስፈለገ?›› ሲሉ ዋቂቶቹ እርስ በእርሳቸው ተንሾካሾኩ። ከመሐከላቸው ሊጋው ወጣት ‹‹ሼራ ነው፣ አንድነታችንን የማደፍረስ ሼራ! እርስ በርሳችን እንድንጠራጠርና እንድንናቆር የማድረግ፣ የመከፋፈል ተንኮል። እኛ ወሐቢይ፣ ሱፊይ፣ አሕባሽ፣ የዐብደላ ሐረሪ ጀመዓ፣ ኹራፋት በመባባል ተሰነጣጥረን ስንጠቋቆም፣ ስንነካከስ፣ ስንዘላለፍ ትልቁን ጠላታችንን እንዳናይ ዝም ሊያሰኙን ነው። ይህ የንፋስ አቅጣጫ የማስለወጥ ስልት ነው›› አለ።

ሌላው አዛውንት ፈገግ ብለው በሽክሽክታ ‹‹የሚያደርገውን የሚያውቅ ሰው የሚያደርገውን ለእናቱ እንኳን አይናገርም። ወንድሞቼ ዝም ነው። ዝምታ ዋሩ ነው። እራሱ ይፈነዳል - ሶብሩ...! በርግጥ ወጣቶች የለውጥ አፋጣኞች ናቸው። እኛ ደግሞ አዛውንቶች ነን። የሃይማኖታችን ተስፋ የማይዘገን ጉም እንዲሆን እኛኑ ጥይት፣ እኛኑ መሣሪያ የማድረጉ ሚራ ያሳስበናል፣ ግን እንሶብራለን። ሙያ በልብ ነው። ልቅሶ ወደ ውስጥ ነው። ወሳኙ ፈተና ከፊታችን አለ!›› ሲሉ ሁሉም በዝምታ አንገቱን አቀረቀረ። ከረጅም ሽክሽክታ በኋላ እርስ በርሱ ዝም ሲባባል አዳራሹ በዝምታ ተዋጠ። ለሸኸ ሩጎኒይ መልስ የሰጠ ባለመኖሩም ሸኸ ሩጎኒይ ተቅበጠበጡ። ከተሰበሰበው ሕዝብ መሐል እመር ብለው ተነስተው እየተጣደፉ ሄደው መድረኩ ላይ ቂብ አሉ፡- ‹‹ያ ጀማዓ! የተከበሩ ዶክተር ሽፈራውን ‹ዳዕዋ› እንዴት አያችሁት? ‹በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ያልተጠመቁ ከሸብርተኝነት አይፈወሱም፣ ከአክራሪነት አይላቀቁም› ሳይሉ መውረዳቸው እናንተ ስታጨበጭቡ እኔ ሸኸ ሩጎኒይ ፈራሁ። በነዓነቴ ተሸማቀቅኩ። እላቸው የማያውቁትን ሕዝብ የሚመሩ መስሎኝ ላቅን ሳቅኩት... ቂቂቂቂ... ካካካ...! ያ ኡመተል ኢስላም! እኔ ሸኸ ሩጎኒይ ‹በእኛው› የመጅሊሱ ፕሬዝዳንት ‹ሸኸ› ዐብዱላሂ ስሞታ ተሸማቀቅኩ። ‹ዲሞክራሲውን ለጠጣችሁት› በሚለው ስሞታቸው አፈርኩ። በአጭሩ አላቀኝ... ቂቂ...! ‹የአዜ ርዝራዥ... የደርግ ንክኪ አለባቸው እንዴ?› ስል ጠየቅኩ። ምን ማለታቸው ነው? ሁላችንንም በአንድ ሙቀጫ አጭቀው ወይ ትንፍሽ ሊሉን ነበር? ምነው ዝም አላችሁ?! ወኔያችሁ ባዘቀ፣ ፍርሃት አራዳችሁ?! ዳሩ ችግር ሰውን ዝምተኛ፣ ወይም ጨኺ፣ አሊያም ንክና ለፍላፊ ያደርጋል። መናገር ብቻ ሳይሆን ዝምታም ሸብር ነው። እኔ ሸኸ ሩጎኒይ እስኪበቃኝ እናገራለሁ። ማንን ፈርቼ ዝም እላለሁ? ‹ገቦ ብለን ሕዝብ እናደምጣለን› ማለት እኛን ሕዝቦችን ማድመጥ እንጂ የኪራይ ሰብሳቢዎችን ወሬ መጋት ማለት አይደለም። ያ ጀማዓ! ልል የፊለግኩት ገብቷችኋል? እነሆ ሁሉንም አብረን አያየነው አይደል?! ዮተማሪዎች መታፈስ የግንቦት 20 ድላችን ሆኖ ‹ግንቦት 20› በሚለው ዙፋን ታጅበ አጂብ አሰኝቶናል። ያው ሁሉንም አብረን እንዳየነው ነው። ጠብ ያለ ነገር የለም። ‹ሱሪያቸውን አሳጥረዋል፣ ሂሚቻውን ኡሳድገዋል፣ ጂልባብ ለብሰዋል፣ ሻፊት አይቅሙም፣ መውሊድ አያከብሩም፣ ከሶላት በኋላ ዱዓ አይቀበሉም› አጥባቂዎች ናቸው! የአክራሪነትና የሽብር ሥጋታችን ናቸው› ብሎ የሥጋት አየር መሜን፣ ‹እኛን ምሰሉ› ብሎ ዜጋን እንቅልፍ መንሳት የሃይማኖታችን አማሪጮች ሁሉ የሥጋትና የሽብር ቀለም መቀባት ያሳስበናል። የዐይናችን ቀለም ደስ ያላላቸው ሁሉ ሽብርተኛ የሚል ታርጋ ይለጥፉብናል። መንግሥታችንም እኔ ሸኸ ሩጎኒይ የሕዝብ ልላን ሆኜ የውምግውን ብሶት ብነግረውም፣ በደላችንን ባስረዳውም፣ ‹ባልመረጥናቸው መሪዎች ተዘረፍን› ብለውም አልሰማ ብሎኛል። እናንተ የአላህ ባሪያዎች! መንግሥታችን እኛን ካልሰማ እኛ ሕዝቦቹ መንግሥታችን ማን እንደሆነ መጠየቅ ያለብን ሊያመስላችሁም? እኛ እኮ ሕዝቦች ነን። የአሮሞ መስሊሞች... የአቦ ጂፋር ልጆች... የሠልጣን አሊ ሚራህ ቤተሰብ የሆንን አፍሮች፣ በምኒልክ ወረራ በጨለንቆ ጦርነት ደማችንን እንደንርፍ ያፈሰሰብን፣ አንገታችንን ያስደፋን ሐረሪዎች። የወሎ ዐሊሞች፣ መላ ስልጤዎች፣ የደቡብ ጎሐች፣ ሶማሌዎች! ያ ጀማዓ! ልል የፊለግኩት ገብቷችኋል? ያኔ እጃችንን እያውለበለብን ‹አይዟችሁ በርቱ› ስንል ተቀበልን። ‹‹ሰላም በትግል›› ለሚለው መርህ ከንድ ሆንን። ‹‹ፋኖ አህአዴግ›› ሲባል የፖለቲካ ችቦ ለኮስን...! ‹‹ዘመቻ ወታገን›› ሲሆን የድል ብስራትን አበሰርን። የትጥቅ ትግልን ‹‹ቦርን›› ‹‹ተጨቋኝ ብሔርና ተጨቋኝ ሃይማኖት ነፃ ሆኗል› አሉን። መንፈርጠጡን አከተመ። የትግል ወኔያችን ተሸነገል። ቁጭታችን ሳቅ፣ መንታችን በዛ፣ ያው ሁሉንም እያየነው አይደል? በ 20 ዓመት በሃይማኖት ተቋማችን የግንቦት 20 ልጅል የምንችለውን የልማት ፍሬ ማንም ነቅሶ ሊያሳየን አይቻለውም። በግቢያችን ውስጥ ያለው ውመር ሰሙተር ት/ቤት እንኳን አልተመለሰልንም። ታሳቂ አንዋር መስጊድ ግሊያን እንዳስረከበን ነው። ሁሉንም እያየህ አይደል? በ 20 ዓመት ውስጥ መሪ ድርጅታችን እኛን ስለማገልገሉ ያየነው ነገር የለም። የሸ/መኞች መጦሪያ ቤት ሆኗል። ባልመረጥናቸው እርጉም ሐዋርያት ተወርሯል። ሃይማኖታዊ ክብራችንን አንኳሰዋል። ባሬም እያለቅስን ነው። እንባችን አልደረቀም። ‹ሥጋጃ ብያት› ጓዶች ይመ..ቱ!› ተብሎ እንዳልተማለ... ‹ስንጣባ ነጻ እናወጣችኋለን› ተብሎ ቃል እንዳልተገባልን... አክሱም ባሬም እነሆ! 20 ዓመት አዛን የማይሰማባት፣ መስጊድ የማይጎነባባት፣ ሙስሊም ዜግነት ያጣባት የአክራሪነት አገር መሆኗን ዐይተናል።

‹‹እናንተ የአላህ ባሪያዎች! ልጆቻችንን ማስተማር አልቻልንም እኮ! መስጊዶች ፈርሰዋል። ሀጃችን ተከብሯል። ይህ ሁሉ ሸብርም አክራሪነቱም መሆኑን ነግረናል፣ በሕይወት መስዋእትነትና በደም አበላ መስጊድ እንገነባለን። ‹‹ዲናችንን ተዋርደናል። ሸሪዓችን ‹‹ሸብርተኛ›› ዝም ስንል ‹አክራሪ› ተሉናላችሁ። ታዲያ ማነው ላያንተላሳ ለአላህ ብለ የቆመ? እኛ ተሸማቀናል። ፍርሃትን ፈርተናል። እምነታችንን አሸንፈናል። ተንቀናል... ተገልለናል...! ‹‹ተው ቻለው ሆዴ› የሚለውን ገጠሬ ‹‹ተው ሸመን መሪዎች› ብለን ንሸደናል። ቤተ ለቤተ ሄደን ቀስቅሰን ያስመረቀናችሁ የጋርላማ አባሎች በድል ማግስት ‹ሕዝብ አሸንፏልና› እንዳላላችሁን እነሆ ፍሽንም አልሰማችሁንም። ጽፈንም አላነበባችሁም። ዛሬም ተገፍተናል። አንገታችንን ሸብረናል። ሥጥተናል። ያ ውለማም ተኝታል። ያ ደረሳም አንቀላፍቷል። ያ ነጋዴም ህልመኛ ሆኗል! ያ ሎጋ ወጣትም ቅጥታም ሆኗል። አቅጣጫው ጠፍቶታል። መጠለያ ታጥቷል። ‹ኢማም የሌለው የጁመዓ ሶላት ይቻል ይሆን?› ሲል ባብ ያፈላልጋል። ያ አላህ! ኑ ሲሉን የምንመጣ... ሂዱ ሲሉን የምንሄድ... ማንነታችንን ያጣን... የታሪክ አሻራችንን ፍቀው ‹‹እንደገና›› እያሉ ተረተ ሰዎቹን ከልካይ በሌለበት አገር እንቅልፋችንን አጠዝቶታል። ለሚሊሞች መሰላል መሆናችን እንደቀጠለ ነው። ገፍላ ውስጥ ሰጥመናል። ልል የፊለግኩት ገብቷችኋል? እነሆ ሁሉንም አብረን እያየነው አይደል? ራሳችንን ፈልገን ባጣንበት አገር እኛ ለሽ ብለን ተኛን! **ወላሂ በመንግሥቴ አፍሬያለሁ! የእድሜ ሽበቴን የእንጨት ሽበት አድርጎ ክብር አሳጥቶታል። የምንለውን የማይሰማ፣ የምንጽፈውን የማያነብ፣ ያከረፍንበትን የማይጠይቅ፣ የሰጠነውን መረጃ የማይመረምር፣ ለሕሳባችንም ሆነ ለቅሬታችን ክብር የሌለው ማነው?** ብሎ መጠየቅ እኔ ሸኸ ሩጎኒይ ደክሞኛል! እዚህ የተሰበሰባችሁ ሙስሊሞች እወክላለሁ የምትሉት ሕዝበ ሙስሊም ሽሃዳ ያለውን ሁሉ መሆኑን አላምንም? ተግታችሁት የምትወጡትን እኔ ሸኸ ሩጎኒይ አልቀበለውም። እንደ ቆሎ ብትዘሩ የኅመን ዘር ያህል ለውጥ አታመጡም። ያላችሁትን እንሰማለን፣ አላህ ያዘዘንን እንሠራለን።››

‹‹ያ ጀማዓ! ለዚህ የኢንተርኔትና የፌስ በክ ትውልድ፣ የዲሽ አፍቃሪ ሕዝብ ምንድን ነው የምትነግሩት? እህህ...! ልጆቻችንን በፈተና ሰዓት ‹ጅልባብ አጥልቃችኋል› ብለው በሌሊት አፍነው፣ ‹ሽብርተኛነት ጠርጥረናቸዋል› ብለው ዘብጥያ አውርደው ሽብር ሲነዙባቸው ማነው እስቲ ከእናንተ መሐል በተቋምም ሆነ በግል ታዛ የሆናቸው? እነሆ ይህን አብረን አላየንም? 20 ዓመት ሙሉ ወደ ዩኒቨርሲቲ የተጓዙ ተማሪዎቻችንን የማዋከቡ ዘመቻስ? ከትምህርት የማዘናጋት ሚራ ሲፈጸምባቸው አላየንም? የፈተና ሰዓት ሲደርስ ሒጃብ በመንጠቅ፣ የጀመዓ ሶላት በመከልከል የተከረተ አቅጣጫቸውን ሲያደፈርሱባቸው...። እኛም በዚች አገር ምንም ማና

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ‹‹ማነው የተኛው? ማነው አክራሪው? ማነው ሽብርተኛው?››

‹‹እኔ ሸኸ ሩጎኒይ እንቅልፍ ነስቶኛል?››

‹‹ምኑ?››

‹‹እንቅልፍ ነዋ!››

‹‹ቂቂቂ....ካካካ.....ቂቂቂ..!››

‹‹አሁን ይሄ ምን ያስቃል?! እህህ... ድሮስ እንቅልፍና ሳቅን ጌጡ ካደረገ ትውልድ ምን ይጠበቃል?... ተኛ! ሳር እስኪበቅልብህ። ጨኸ! ‹ማንቼና አርሴ› እያልክ። ቃም! በሺሻ እየታጠንክ። ሳቅ! ኮሜዲ ፊልም እያሳደድክ። አውደልድል! ሕሊናህን ሽጠህ፣ ማንነትህን አርክሰህ፣ ‹እንደ ፍራሽ ልነጠፍላችሁ› እያልክ.... ነፃነት የሌለህ ደደብ.. ! የጋሪ ፊረስ...! እህህ... ያበሽቃል!

‹‹ምኑ?››

‹‹መንግሥት ነዋ! ትውልድ ነዋ! ከአላህ ባርነት ተፋትቶ የሥርዓት ባሪያ የሆነው ዑለማው ያሳፍረኛል። ደረሳው ያበግነኛል። ነጋዴዎቹና ወጣቶቹ ያሳዝኑኛል። ‹በአንድ ዓይነት አመለካከት ካልተጠመቃችሁ ለአክራሪነት ተጋላጭ ናችሁ› ብለው ሚንሃጅ ሲመርጡላቸው፣ ሲጭኑባቸው፣ ‹እኛ እናውቅላችኋለን› ሲሏቸው መኝታን መምረጣቸው ያውካል።››

‹‹እንዴ ሸህ ሩጎኒይ ምን ሆነዋል?››

‹‹ምን ያልሆንነው ነገር አለ? ምን እስክንሆን እንጠብቅ?››

‹‹ማለቱ... ሰው በኑሮው ውድነት ይሸሽቃል፣ ይጨነቃል እንጂ እንዴት ሽቅብ ተንጠራርተው በተከበረው በትረ ሥልጣን ይንጨረጨራሉ። እንዴት ቁልቁል ወርደው ትውልድን ይረግማሉ? የድፍረቶት ድፍረት ‹ሞፍን ተከታይ› ማለቶት ሲገርመን፣ መጨውን ዘመን... የሚመጣውም ዘመን... የማይመጣውም ዘመን ብለን ያነገሥነውን፣ በተጋጋል ስሜት የተንበረከክንለትን፣ ያንበረከክንን፣ የተሸቆጠቆጥንለትን፣ የሰገድንለትን እርስዎ ‹እናንተ የሥርዓት አምልኮ የባርነት ቀንበር የተሸከማችሁ›› ብለው ክበረ ነክ የሆነ ሥድብ ይሳደባሉ! ‹ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኻል› እንዲሉ መናደድ ያለበት ማነው? እርሶ ናት እኛ? አሁን እርሶ ለየትኛው እድሜዎ ይናደዳሉ!?››

‹‹ናዳ ይውረድብህ! ስኳር ሲያቀምሱህ፣ ያለብቃትህ ሲሾሙህ፣ በተስፋ ሲነርቱህ፣ የጋሪ ፊረስ ሲያደርጉህ፣ በአቋራጭ ሲያከብሩህ በአቋራጭ ሞትን የምታመልጥ መሰለህ? ጥገኛ ነህ። ቅንቡርስና ድንች! አሁን ለምን እንደጥላ ትከተለኛለህ? ኡ... ኡ...! ኡ ኡ!›› በማለት እየጮኸ ተርገፈገፉ ሸሽ ሩጎኒይ - በስድስተኛ ስሜታቸው እየተቆጠጡ። ይኸው ጠቋሚያቸው ዳግም ጉንተላውን ቀጠለ። በሸክሸክታ። ‹‹ያ ሸኽ! ጫኺዎች ብዙኣን ናቸው። ስሜታዊነት የሐቅ ጸር ነው። ልማታዊ መንግሥታችን ልማታዊ ባለሐብት አድርጎናል። ታንክን ወደ ማረሻ ለውጠናል። ረሃብን ተረት አያደረግን ነው። እህሆ የእኛ ሰላም ሞልቶ ሰላም ለማሰኘበር የሱዳን ግንጣይ ወደ ሆነችው አቢይ የሰላም ዐርበኛ ሆንን ሂደናል። የሱሚለ ተልዕኮም ተሳክቶልናል። ለዩኑት የቡት ሥራቸው እንዴሆን አድርገን ላይስማሙ እንዲስማሙ አድርገናቸዋል። እናን ሙስሊሞችን መንግሥታችን ከሃይማኖታዊ መንግሥት ሞቆና አላቅናል ! ሰላም ነፃነትና እኩልነት...›› ብሎ ሊቀዋል ሲል ሸኽ ሩጎኒይ ፈጥነው ‹‹ዝቃ! በቃህ! ሁሉንም አብረን እያየነው አይደል? በቃሬ አዛር በሃይማኖታችን ምክንያት አድሎ እየተፈፀመብን መሆኑን ለማየት የንስር ዐይን አያስፈልግም። ‹ትምህርት ከየትኛውም ሃይማኖት ነፃ ይሁን› ያስማማናል። ትውልዱን ግን ሃይማኖት አልባ የሚድረግ ነፃነት ገዳቢ አካሄድ አምባገነንነት ነው። ከውሪቱ ደልዘለለው የሃይማኖት ነፃነትና መብታችን ለእንዳንተ ዓይነቱ ድል የሌለህ የድል አጥቢ ዐርበኛ የካድሬነት ዲስኩርህ ያንገሸግሸኛል። ማፌሪያ ናችሁ! በቂቂን...! ታሮች! እህህ... ጭፍ የልገኝህ ግልግል ይውጣል። ለምን ታተክኒኛላችሁ!? ደሴታችንን ሃይማኖት እየነጠቃችሁ፣ በሽብር ተጠርጣሪ እያላችሁ በአክለለ ሌለት መብለም ተማሪዎችን እያፈሳችሁ ወላጆችን ሁሉ ያሸበራችሁት እኛን አይደላችሁ? ከእናንተ በላይ ሽብርተኛ አለ? ሕገመንግሥቱን እየጣሳችሁ የምንለብሰውን ‹‹እንምረጥላችሁ›› ተሉናላችሁ፣ ‹የምንተገብረውንና የምንከተለውን ሃይማኖታዊ አሴተ አንጫንባችሁ› ተላላችሁ፣ ‹እኛ የሚበጃችሁን እናውቅላችኋለን› እያላችሁ የአክራሪነት ካባችሁን ትጭኑብናላችሁ። እናንተው በኑሮ ታሸብሩናላችሁ፣ እናተው በሰላይና በኪራይ ሰብሳቢዎች ታጉላሉናላችሁ፣ እናተንው በሃይማኖት ተቋማችን የመረጥነውን ሳይሆን የፈለጋችሁትን ትሾሙብናላችሁ፣ እናንተው መስሊም ሚሪጆችን ከትምህርታቸው እያስተጓጎላችሁ ‹አክራሪ፣ ሽብርተኛ› እያላችሁ እንቅልፍ ትነሱናላችሁ። ምነው ታዲያ ከዚህ በላይ ጸረ-ሰላም፣ ጸረ-ልማት፣ ጸረ-ዲሞክራሲ ሽብር አለ ወይ? አሁን እናንተ የሃይማኖት ነፃነትና እኩልነት ስትደሰኩሩ አታፍሩም ገምቻችን መኝታ መሰላችሁ? ያ አላህያ ኧረ ተወኝ...ያ አትኒካካኝ ይልቅ። መናገር እንጂ ኸገዘብን መስማት ላልታደለው ብዙሪ ሥልጣኔ እንደ አፈርኩበት ንገርልኝ! ኡህ...! በቃ...! በቃ...! በቃን ብሉልኝ... አሉ ጉንጉሸሸው ሸሽ ሩጎኒይ - በስድስተኛ ስሜታቸው ተጠምዶ።

እላቸው እጃቸውን እያወናጨፉ፣ ደረታቸውን እየደለቁ፣ ክንፈሬቸውን እየነከሰ። ‹‹ሃዘኛ ሚኒስቴሩ አረፈ›› ሲሉ፣ ጥርሶቹውን ነክሰው ቁልቁል ወደ አሪት ኪሎ ቤተ መንግሥት ወረዱ።

‹‹ያ ኡምመተል ኢስላም! ልላችሁ የፈለግኩትን በቀጥታ ተረዱ፣ በእንቅልፍ ልብ አታላምጡ። እዚህ ከከፈሚያ ደኒበርሲቲ አዳራሽ የተሰበሰባችሁት የትኛው አቅማችሁ አንሶ እንደሆነ ራሳችሁን ጠይቁ። ያ ኢስላማዊው ሕዝቅ ጎደ፣ የሙቆም ወሊያችሁ ጎን አፈሰሰው? እኛ ባልመረጥነው መሪ አንተዳደርም፣ በካድሬ ሥልጠና የሃይማኖት ተቋማትን መምራት አይቻልም። መጅሊስ ከሳሩሩ ነው። ‹ወሐቢይ፣ ሱፊይ፣ ሠለፊይ፣ ተብሊግ፣ ኸራፋት፣ መድኸሊ፣ ኸዋሪጅ› ይላል! አሁን እናንተ ቸኩረው የምታደርጉበት አሕባሽ፣ የፀብደላ ሐረሪ ጀመዓ እያለ ተቋሙን የጋራ ቤት አድርገው መምራት ያልቻሉ ናቸው› ብለን ጨኸናል። ‹እኛ የምንለማቸውና የምናግዟናቸው፣ የአላህ ፍራቻ ያላቸው ኸለፋዎቻችን... መሪዎቻችን ጉደኞች ናቸው› እያልናችሁ ነው። እርስዎ የተከበሩ የፌዴራል ጉዳይ ሚኒስቴር ዶክተር ሽፈራው... እርሶና መሥሪያ ቤትዎ ይህን የሕዝብ ጨኸት መስማት ሲገባዎት የማግለል ችቦ ሆነው እዚህ ሐረር ሕረማያ ዩኒቨርሲቲ መጥተው ከመሳካላቸው መገኘቶት እኔ ሸሽ ሩጎኒይን አሳፍሮኛል። የሕዝብና የመንግሥት ግዜና ሐብት መባከኑም ያሳስበኛል። ‹የተቋማችን አቅም በሚሰበሯት ፍቃድ ውሳኔ የተንጠለጠለ ነው። የሕዝብ መስሊም ውክልናው እህህ... የሚያሰኝ ነው። ቤቱ አምባ ገነኖች የተሰባሰቡበት ነው። ሐጅና ዑምራን ጠለላ አድርገው ሕዝብን ያስለቀሱ፣ በመሰና የተዘፈቁ በርካቾ ናቸው። እሪ! የመሪ ያለህ! ስንል ጮኸን ‹‹ሰሙን›› አሉን። ‹መጅሊስ ምርጫ ያልተካሄደበት ቤት ነው› ልልን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶት ይህን ቅሬታችንን አናነው አሁን ክቡር ሚኒስቴር እዚህ መገኘቶት ‹ይህ መንግሥት ወዴት እየሄደ ነው› እንድል አድርጎኛል።››

‹‹ይልቅ እናንተ ኡመተል ኢስላም የፊሰሰው ሃዘታችሁ ያሳስባችሁ። ለደከመው ኢማናችሁ ዳሃ አድርጉ፣ ሰጪ አላህ ነው። አትንበርከክ። ተውበት አድርጉ። የተነጠቀውን ነፃነታችሁን ልታስመልሱ ይገባል። ሞት አለ! ነገ እንሞታለን። በምርታና ያለነገ ዲን የለም። ዓለም ሰፊ ናት። ዓለም ጠባብ ናት። ዓለም አንድ መንደር ሆናለች። ሥጋቱንም... ጎሳሱንም... ዘገባውንም... ጁንዱላውንም... ሸሂዱንም... ለውጡንም... እያየን ነው።››

ከሚዛ ፌርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሚሊዮን ዶላር አመለጠን። እኔ ሸኸ ሩጎኒይ የአሜሪካ ሽለላ አስቆኛል። አስክሬን በሊለበት የገዳይ ፉከራ! እ... ሃሎ... እ? እየሰማሁ ነው። እ...? ‹ታጋይ ቢሞትም ትግል አይሞትም እንዳይሆንባት ፈርታ ነው› ነው ያልከኝ? እ...? እኔ መቼም በሶማሌ የአሜሪካ ወታደር ሬሳ በጎዳና እየተጎተተ ለዓለም ሲታይ... የቢን ላዲንን ጀናዛ ማንም ላያይ ባህር መግባቱ... ክብር ነው ወይስ የሰብዕዊ መብት ጥሰት? ቂቂቂ... ቂቂ... ካካካ...! ሳቅኩላችሁ! ምን...? ሃሎ... ሃሎ... ጆሮህ ያፈላል...?›› ‹መቼም ቢላደን ለኑሮው ተድላ ሲል ዱር እንዳላደረ አሜሪካ ታውቃለች? እ...? ይህን አጀንዳ የማስቀየር... የትኩረት አቅጣጫን የመለወጥ የጃጀ ታሪክ ዛፉት...። እ... ሃሎ! የለመዳችሁት ነው። መወንጀል... ስም መለጠፍ... መከሳፋፈል... እ... ሃሎ... እየሰማሽኝ ነው?››

‹‹አዎ! እ...? ምን አልክ? ሃሎ... ወፈፌ?! ማነው ወፈፌ? ሃሎ... ሃሎ...! ምንድን ነው ያልከው? እብድ? ያሁኑ ይባስ! አንተ! ማነው እብድ!? ሃሎ...! ሃሎ...! ያ ኡመተል ኢስላም? የሚለኝን ትሰማላችሁ? ...ሃሎ...! ሃሎ...! አንተ ማነህ?! ሃሎ..ሃሎ..!›› ሲሉ ጆሯቸው ላይ ተዘጋ። ‹‹ይኸው ነው! አይሰሙንም! የሚፈራ ካገኙ ያስፈራራሉ›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ ቆጣ ብለው።

‹‹ያ ጀማዓ! ዛሬ በአዱኛ ነገ በአኺራ ፈላህና ነጃ እንድንወጣ... ዲን ኢንቲሻር እንዲያደርግ መልፋት ያስፈልጋል። የዲን ልፋት ማለት...›› ብለው ላይጨርሱ ድንገት ቆጣ ብለው ‹‹ለምንድን ነው የከበባችሁኝ? ለምንድን ነው የምትከተሉኝ? ድንች ናችሁ! ወጣት ጡረተኞች! አንብዳጅ...! ፉሩሽካ! ለምን ከበባችሁኝ!?›› ብለው በንዴት ዓይናቸውን አፈጠጡ - ሸኸ ሩጎኒይ። መልስ የሰጣቸው የለም። ሁሉም በስስትና በፍቅር ይመለከታቸዋል። ‹‹ተናገሩዋ!›› በማለት ጮኹ። በዙሪያቸው ያሉት እንደ ግሪሳ ግር ብለው ሸኸ ሩጎኒይን ተሰናብተው ወደ ታላቁ አንዋር መስጊድ ተመሙ። ሸኸ ሩጎኒይ የተንቀለቀለውን የወጣቱን ስሜት አይተው... ‹‹ለውጥ... ጎዳሴ... ታሪክ...!›› ብለው ብቻቸውን አጉተመተሙና እየበረረ የመጣውን ታክሲ አስቁመው ዘው አሉ።

***

ሸኸ ሩጎኒይ ጦር ኃይሎች አካባቢ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ቅጥር ግቢ ደርሰዋል። ወደ ቅጥር ግቢው ውስጥ ለመግባት ሲሉ ዘበኛው አገዳቸው።

‹‹ወዴት ነው?›› አለ ዘበኛው።

‹‹ወደ ፕሬዝዳንቱ ቢሮ?›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ።

‹‹ስብሰባ ላይ ናቸው።››

‹‹ወዳ ዋና ዐሐፊው ቢሮ።››

‹‹ስብሰባ ላይ ናቸው።››

‹‹እሺ ወደ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ቢሮ።››

‹‹እሳቸው እኮ ተባረዋል።››

‹‹ቂቂቂ...! ኪኪኪ...! እህህ...! እሺ እ... ወደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ቢሮ።››

‹‹የትኛው?››

‹‹ምን ማለት ነው? እኔ ሸኸ ሩጎኒይ ግለሰቦች ምን ያደርጉልኛል? ቢሮውን ነው እየጠየቅኩ ያለሁት...። ተቋሙን ነው ይስተካከል የምለው። እስቲ አሳልፈኝ›› ብለው አልፈውት ሊሄዱ ሲሉ... ‹‹አይገባም!›› አለ ዘበኛው።

‹‹እንዴ! ምን ሆነሃል...?! ስብሰባውን መምራት ያለብኝ እኮ እኔ ነኝ!››

‹‹እርሶ ወደዚህ ግቢ እንዳይገቡ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶኛል...! ፎቶዎት ተሰራጭቷል። ይኸው ቢጋዜጣችን ላይ ወጥተዋል።

‹‹የእናንተን ጋዜጣ እኮ እናንተ ብቻ ናችሁ የምታምኑት!›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ።

ዘበኛው በንዴት ጦፍ ብሎ... ‹‹እንዴ! ምን ማለት ነው? በቃ! መግባት አይችሉም›› አለ።

‹‹ስብሰባውን ማን ይመራዋል?››

‹‹እንጀ! እርሶ መሪዎቻችንን አሳጥተዋል። በሕዝብ ያልተመረጡ መሆናቸውን ለሕዝብ እያጣሩዋቸው ነው። ይህ ሕዝብ ያውቃል፣ ኩርፊያው አይታወቅም። ሕሙኝ...›› አለ ዘበኛው በሽክሽክታ። ‹‹እ... የእንጀራ ነገር ሆኖ ብሎኝም አደናቂዎች ነን...! አፉ የሥራ ምድቤ የማይታወቅ ታዋቂ ቦታ ነበር፣ በኋላም የአንድ ክፍለ ጋላፊ ሆንኩ። አሁን ይኸው ዘበኛ ሆኛለሁ። እዚህ ግቢ ጥሩ እንትን ካለች? ፅዩ... ፅዩ...! ሞባይል ይዘዋል?››

‹‹አዎ›› አለ ሸኸ ሩጎኒይ።

‹‹ያስጠለፉብኝታል። ለመንግሥት ነግረዋል...›› አለ በሽክሽክታ ለሸኸ ሩጎኒይ። ሸኸ ሩጎኒይ በረጅሙ ሳቁ... ቂቂቂ... ካካካ... ኪኪ...!

‹‹ምን ያስቅዎታል?›› አለ ዘበኛው ተደግሞ... ‹‹የሚገርዘህ ፍርሃት አስፈሪዎችን፣ አሳዛኞች ያስቁኛል... መንግሥት ለሰፈው ሕዝብ የመሳ ነውነ›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ። ‹‹ለሪ በሙ [illegible] በር ልየዝ ጋርሳማ ሆኖ ለክልሉ ኦንዶሚሚንት ደጋፍ ሳይሰጥ ሥራ ሥራ ሥራ ሥራ መሪሲስ ሆኖ ነክሉ ያውርዳና›› የሚል አምባ ገንንነት አ...›› ብሎ ዘበኛው ሊቀጥል ሲል ሸኸ ሩጎኒይ ፊጠን ብለው አጭረጡ። ‹‹የሚለበጥን ሕይወቱ ማስተጓጎልና ነፃነታቸውን ማፈን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዓላማ አይደለም።››

‹‹እንዴት? እርሶ ኢህአዴግ ኖት እንዴ?›› ‹‹አይደለሁም። ሙስሊምና አገር ወዳድ ዜጋ ነኝ...! ኪራይ ስብሳቢና ባንዳዎችን ለማጋለጥ የድርጅት አባል መሆን አያስፈልግም›› አለ ሸኸ ሩጎኒይ። ዘና ብለው ሲናገሩ ዘበኛው ተደፋፈረ ‹‹እህ...! እዚህ ግቢ ውስጥ እኮ እርሶን... ወሃቢይ እያሉ... እ... ማለቱ ከአዲስ አበባ መጅሊስ ጋር በመሆን የፌደራል መጅሊስን ሊያፈርሱ ነው ይባላል። እ... ይህ እውነት ነው እንዴ?›› ሲል ጠየቀ ዘበኛው ፈራ ተባ እያለ።

ሸኸ ሩጎኒይን ቅልስልስ ብሎ ዐይቶ ‹‹እ... እነሱ ‹እኛ ከሕዝብ ልብ የራቅን ብንሆንም ለመንግሥት ከይም ሥሩ የቀረብን ነን። መንግሥት ምንም ካላለን ማንም ያሻውን ቢጮኽ ከጩኸት አያልፍም› ብለዋል። እ...››

‹‹ማን አለ?›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ ዘበኛው ላይ አፍጥጠው። ‹‹ሞባይሉን ዘጉት?›› አለ ዘበኛው። ‹‹አልዘጋሁም! ቦቅቧቃ! ልግባበት!›› ብለው አልፈውት ሊሄዱ ሲሉ ‹‹ብሕግ አምላክ! መግባት አይችሉም!›› ‹‹እገባለሁ!›› ‹‹አይገቡም! ኡ!ኡ! ነው የምለው!›› አለ ዘበኛው። ሸኸ ሩጎኒይ ተናደዱ... ‹‹ተወው! አልገባም...! ደህና ዕድን›› ብለው ሊሄዱ ሲሉ ‹‹ኧረ በሕግ አምላክ! መመለስ አይቻልም›› አለ ዘበኛው። ‹‹ምን ሆነሃል? አብዝሃል አልክኝ፣ ደግሞ ለምንድን ነው የማልመለሰው?›› ‹‹ሞባይሉን ዘግተውታል?!›› ሲል ጠየቀ ዘበኛው። ‹‹አልዘጋሁም!›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ በሰጨት ብለው። ‹‹ብመጅሊሱ የተመረጡ ሰዎች ብቻ ስብሰባ የሚጠሩበት፣ በመጅሊሱ የተመረጡ ሰዎች ብቻ የሚገለገሉበት ተብሎ ሊላ ጣጣ እንዳያመጣብኝ እርሶ ኡይገቡም፣ አይሄዱምም! መግባትም ጣጣ ያመጣብኛል። መመለስምም እችግር ይከተኛል። በቃ! እ...›› ብሎ ዘበኛው ሸኸ ሩጎኒይን ተቀብለስልሶ ዐይቸው።

‹‹ውርድ ከራሴ...! ያ ኡመተል ኢስላም...!›› አሉና ፈጠን ብለው ከዘበኛው ቤት ወንበር አውጥተው ዘበኛው ሳይ ሳይ እንጣጥ ብለው ወጡ። ‹‹ኡ ... ኡ! ኡ... ኡ! የመሪ ያለህ!›› ብለው ጮኹ! ዘበኛው በድርጊታቸው ደነገጠ... ዐይኑ ፈጠጠ። አፉን ከፍቶ ደርቆ ቀረ። በመጅሊሱ ውስጥ በየቢሮው አድፍጠው የነበሩት ሠራተኞች ‹‹እሬ! የመሪ ያለህ!›› የሚለውን ጩኸት ሰምተው ከየቢሮዎቸው ወጡ። ሸኸ ሩጎኒይ ቀረጽ... ሳቁ። ‹‹ቂቂቂ... ኪኪ ቂቂ... ሳቅኩላችሁ!›› አሉ። አፍዋጦ የከበባቸውን የመጅሊስ ሕዝብ አዘቅዝቀውና አፍዋጠው ተመለከቱት። ‹‹አዩ ሸኸ ሩጂይ...! የሚበጃ ልዑካን ወደ መጅሊስ አልመጡም?›› አለ ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ መጅሊሱ የመጣና አሜሪካ ግቢ የሚያውቃቸው ወጣት። ሸኸ ሩጎኒይ ፊቸው መለሰለሰ... ‹‹ይህ መቼም ‹አገርን በአንድ ሃይማኖት የመወከል ሚራ የግብፅ ልዑካን በቤተ ክህነት ተገኝተው ከፓትሪያርኩ ጋር ውይይት አድረገው ቃሄዳቸው ...ቂቂቂ... ብሎ መንፈርጠር የዚህ ትውልድ ዜማ ነው። ‹‹ሸራተን ሰደቃ ላይ ለመገኘት ፈጣን መሆናችን አትርሳ። በኢትዮጵያ የግብፅ አል አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሞላበትና ከማማሸ በላይ የአገሪቱ ሕዝብ ሙስሊም ባለበት፣ ዘጠና በመቶ በላይ ሕዝቧ ሙስሊም በሆነባት ግብጽ የአባይን ጎዳሴ ግደቧ ብንፈ የመሰቀም ርዕይ ሲሰነቅ የግብፅ ልዑካን መጅሊሱን ያለማንጋገሩ የታታሪ መሪ ችግር ነው...! ኤሎ! ኪራይ ሰብሳቢዎችና ነጭ ለባሾች በተንሰራፋባት ኢዛር ባንዳና ቦንዳን ሙለየቱ እንዴት ይቻላል?›› አለ ሸኸ ሩጎኒይ - በመጅሊስ ግቢ ከዘበኛው ጣሪያ ላይ ሆነው። ‹‹ለጎዳሴው ግድብ ቦንድ ገዝተዋል?›› ስትል ሐቀኛ ከመጅሊስ ሠራተኞች አንዷ። ‹‹አዎ! ‹የአባይ ውሃ ብክነት ቁጭት ፊቸር በቦንድ ግር ከተገደበ በመጅሊስ ውስጥ ያለው የሮሮ እንባ በምን ይገደቢ› ስል ሚሉይ ያለህ›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ።

‹‹የመጅሊስ ምርጫ መቼ ነው?›› ሲል ጠየቀ ወጣቱ።

‹‹ምርጥ ሰዎች የጠፉ ጊዜ›› ብለው መለሱለት - ከዘበኛው ጣሪያ ላይ ዘለው ለመውረድ እየተንደረደሩ። መጅሊስ ግቢ ውስጥ ጩኸት በረከተ። እሳቸውም ‹‹እኔ ሸኸ ሩጎኒይ!›› ብለው ተንደርደሩ...።

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ‹‹ቦንድና ባንዳ ለዩልን!››

‹‹ስብሰባው ጠፋል!››
‹‹የምን ስብሰባ?››
‹‹የመጂሊሱ!››
‹‹ለምን?›› አለ የሸኸ ሩጎኒይ ስድስተኛ ስሜት።
‹‹‹እሪ! የመሪ ያለህ› የሚለውን የሕዝበ ሙስሊም ትኩሳት ለማቀዝቀዝ፣ ጩኸቱን ለማብረድ፣ ምላሽ የተነፈገ የመሪ ጥያቄያችንን የምላሽ አቅጣጫ ለማሳት፣ ተግባር አልባው ኑ... ጩኸኑ... ጩኸትን ተንፍሱ› ስብሰባ! ቂቂቂ... ስብሰባ! ቂቂቂ... ካካካ...!›› ብለው በረጅሙ ሳቁ ሸኸ ሩጎኒይ።
‹‹ምን ያስቆታል?›› አላቸው ስድስተኛ ስሚታቸው።
‹‹ስብሰባው ነዋ!›› አሉ ሸኸ ሩጎኒይ።
‹‹ስለ ስብሰባውማ ነገሩኝ!››
‹‹ምን ብዬ?››
‹‹እኔኮ ተሰበሰበ፣ ‹ግቢያችን ሰፊ ስለሆነ ትርምሱን አልሰማንም› አሉ። ተደናገጡ፣ እርስ በርሳቸው ተወነጃጀሉ፣ ደግሞም አቀዱ›› አለ 6ኛ ስሚታቸው።
‹‹ማፈሪያ ሁላ! ደግሞ ምን ታቀዱ?!›› ሲሉ ጠየቁ ሸኸ ሩጎኒይ። ‹‹ጩኸት በማብዛት ሥልጣን የማራዘም እቅድ ነዋ! ‹ከሥልጣን ውረዱ› የሚልን ጩኸት በካድሬ ስልት፣ በከፋፍለህ ግዛ መረብ ውስጥ የማስረግ እቅድ። የመሪን ጥያቄ የገደል ማሚቶ ጩኸት አድርጎ ማስተንፈስ... ዋእ... ተጋድልና! ከሥልጣን መውረድ ብቻ ሳይሆን እንሞታለን! ይህ ሊሰመርበት ይገባል፣ ትግል ነው አሉኝ እኮ!›› አለ የሸኸ ሩጎኒይ 6ኛ ስሚት። ቀጠለ፣ ይኸው 6ኛ ስሚታቸው እቅዱን በዝርዝሩ ለመግለፅ እንዲህ አለ፦ ‹‹ሠራተኛን የማሸበርና የመከፋፈል እቅድ! ከሕግ የበላይ በመሆን ሥውር እጆችን የመደጎም እቅድ! ሕዝባዊ ጥያቄዎችን ወደ ግለሰባዊ ችግሮች ባህሪና ወደ እርስ በርስ የመጅሊሶች ሽኩቻ የማስቀየስ እቅድ! ባንዳ ልሳኖችን ወደ ባርነታቸው እንዲመለሱና እንዲጮኹ ፍርፋሪ የመጨመር እቅድ፣ በድርጅት አባልነት ስም ዜጋን የማስፈራራት እቅድ! የመንግሥት ክፍልን የተሳሳተ አቅጣጫ የማሳየት እቅድ! ‹እንዴት እንወንጀል?› የሚል ስብሰባ! ትኩሳትን የማብረድ እቅድ! ‹አብረን እንሠራለን! ኑ! እንሰባሰብ! ስሁተታችንን ንገሩን!› የሚል ግርግር! ባዶ ቅስቀሳ! ፉከራ! ጥሮፓጋንዳ! የማይፈፀም ቃል መግባት! ሽንገላ! ‹በርች በራር!› ይላል ጉራጌ! መቼም በማያባራው ሳቁ ልሳቅላችሁ። ቂቂቂ... ቂ!››
‹‹ዋእ...! በሚሊኒየሙ ግብ አባይን ጥቅም ላይ በማዋል ራዕይ፣ በጎዳሴው ግድብ ቦንድ ሽያጭ... ሕዝብ ሲጠመድ፣ መንግሥት ፋታ ሲያጣ ሥልጣንን የማቆየት የባንዳ እቅድ ሥራ የሠሩበትን ሰነድ በፍርድ ቤት አረጋግጠ ላቀረበልኝ የአንድ ወር ቀለብ ከነጫቱ እችለዋለሁ! የመጅሊሱን ሥልጣን በፍርድ ቤት ማፅደቅ

ስድስተኛ ስሜታቸው ጎነተላቸው። ‹‹የዐብደላ ሐረሪ የአሕባሽ ባላደራ ሊባኖሳዊውን ዶ/ር ሰሚር ‹አሁን አሁን ለኔ የልብ ወዳጅ ሆነዋል› ያሉትን ዶ/ር ሽፈራውን ጠይቅ እንጂ ይህ ለመመራት እና ትዕዛዝ ለመፈጸም ዝግጁ የሆነ፣ መሪውን የማያውቅ ሕዝብ ምን ያድርግህ?›› አሳቸው።

ሸኸ ሩኃኒይ ተቆጡ... ‹‹ፉሩሽካ! ትምክህተኝነትህ! ‹እኛ እናውቅልሃለን› ብለህ የሕዝብ ድምጽ የምትንቅ አምባገነን አትሁን። አሁን ለምን ትከተለኛለህ? አያችሁ? እሱ ለእኔ እንደማይታየኝ እናንተም የሃይማኖት ተቋማችንን የሚሾፍሩት ባለሥልጣናት፣ ትናንሽ ወሬ በመልቀም የሚተዳደሩት ሰላዮች አይታዩዋችሁም። እኔ ሸኸ ሩኃኒይ ‹ቡና የሚቸበችብ መሪ እንፈልጋለን› አላልኩም። ወጣትነቱ የከረፋው፣ ሳይወለድ የሞተ፣ ፍርፋሪ ባገኘበት የሚጮህ፣ ዲን ሳይሆን ብር የሚያሳስበው፣ ገንዘብ ለማግኘት ‹እናቴንም ቢሆን እሸጣለሁ› የሚል የነቀዘ ትውልድ አናይም። እኛ የአላህ ባርያ፣ የሕዝብ አገልጋይ ነን! ለዓላማ ስንል ሐራምን እንዳፈርም። የቢሾፍቱ ሜጉላ ሽርሽር... ቂቂቂ... ያ ሥውር ተልዕኳችን እስኪሟላ... ዋእ...! ብቻ ተዉት! ታሪካዊ ስህተት ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ ጥላቻንም የቻልን ሕዝቦች ነን። አሁን እዚህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ድረስ መዋቹ ሚኒስትሩን ‹የአሕባሽ ቦንድ የት ይገኛል?› ብዬ ልጠይቅ ብል አላስገባ አላችሁኝ?››

‹‹ወገኖቼ! የተወደዱ ሚኒስትራችን ዶ/ር ሽፈራው የመንግሥትን ሥራ በድለው፣ የቤተሰባቸውን ጉዳይ ሰውተው፣ ማኅበራዊ ሕይወታቸውን አጣበው እንቅልፍ ያጡት ለኛ ለሙስሊሞች ሲሉ ነው። ትልቅ ባለውለታችን ብቻ ሳይሆኑ ትልቅ የታሪክም ተጠያቂ ናቸው። አባይን የደፈሩት አቶ መለስ ለቦንድ ሽያጭ ሕዝባዊ ንቅናቄ ሲፈጥሩ አቶ ሽፈራው ደግሞ አሕባሽን ለማስፋፋት ባደረጉት ጥረት ሕዝባዊ ቁጣ በአቶ መለስ ላይ እንዲፈጠር እያደረጉ ነው። ይህ በሙተካካት መርህ የአሕባሽ ቦንድ እንዲሸጥ ተገቢውን መነቃቃት ፈጥሯል። በእርግጥ በታላቁ አንዋር መስጊድ፣ እንዲሁም በከተማዋ ዋና ዋና መስጊዶች በቁጣ የተናጡት የአሕባሽ ቦንድ ሽያጭ የት እንደሆነ ዶ/ር ሽፈራውን ሊጠይቁ ነው!› ብለው ከአውቶቡሱ ጣሪያ ላይ ቀልጠፍ ብለው ወረዱ።

ድንገትም ‹‹ወደ ሚኒስትሩ ልግባበት!›› ሲሉ አምቧረቁ - ሸኸ ረኃኒይ።

‹‹አይገቡም!››

‹‹ለምን?››

‹‹ቀጠሮ የላቸውም!›› አለ መረጃ ክፍሉ የስልክ እጀታውን እንደያዘ።

‹‹እሳቸው ግን አሉ?›› አሉ ሸኸ ሩኃኒይ።

‹‹ስብሰባ ላይ ናቸው!››

‹‹ከነ ማን ጋር?››

‹‹ይህማ የመንግሥት ጉዳይ ነው!››

ሸኸ ሩኃኒይ ተናደዱ። አሉም፡- ‹‹አውቃለሁ! ሥልጠናዎች ይቀጥላሉ። በየመስጊዶቻችን የሚሰማው የተቃውሞ ድምጽ መልስ ላያገኝ ወደ ጎጇችን ብትመልሱንም ያልተመለሰው ጥያቄያችን ከልባችን አይመለስም። በዚህም ምክንያት የሚታመሩብን ልጆቻችን መስዋዕትነት የተሞላችን ብርሃን ነው። ስማ ወገኔ...›› ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ ፌዴራል ፖሊሱ ‹‹በቃ! ግቢውን ይልቀቁ!›› ሲል እንደ ጅብራ ከፊታቸው ተደቀነ።

‹‹አዎ! እኔም የምለው ‹በቃ› ነው። አሻፅብ... ዩሪድ... ኢስቃጠል... መጅሊስ!›› እያሉ ከፌዴራል ጉዳይ ሚንስቴር ግቢ ሲወጡ ከሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት መውጫ ትይዩ የፌዴራል ወታደሮችን ደይዘ ግልጽ ቶዮታ መኪና ሲመጣ ላይ ላይ ዘለው ቂብ አሉ። ወታደሮቹ በስስት አዩዋቸው። ሸኸ ሩኃኒይ በስሱ ፊገግ ብለው ‹‹አብሽር! እኔ ኮማንደር ሸኸ ሩኃኒይ እባላለሁ! የመጅሊሱ ፕሬዚደንት አማካሪ ነኝ! ሹፌሩን ቀጥል በለታ! እኔ ሸኸ ሩኃኒይ...!››

ECHR

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process 3

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ዶ/ር ሽፈራው! የአሕባሽ ቦንድ ከወዴት ይገኛል?

‹‹እኔ ሸኸ ሩኃኒይ ነኝ! ማሻአላህ! በትውልዱ ጽናት ኮርቻለሁ! አልሐምዱሊላህ! ተክቢር!›› አሉ ሸኸ ሩኃኒይ። ሚክሲኮ አደባባይ አካባቢ ፌዴራል ጉዳዮች ሚንስቴር ደጃፍ ላይ ናቸው። ጊዜው የምሳ ሰዓት መውጫ አካባቢ ነበር። ከጥበቃው ጋር ተፋጥጠው ብቻቸውን ያወራሉ። ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚገቡት እና የሚወጡት ሠራተኞች በድል አድራጊነት ስሜት ያዩዋቸዋል። ‹‹የታደሉ የነጻ ትውልድ አባት፣ የሰላማዊ ትግል መሪ፣ የሰላም አባት›› እያሉ አፍ ለአፍ ገጥመው አሞጋገሷቸው።

‹‹ሚኒስትሩ ጋር መግባት እፈልጋለሁ›› አሉ ሸኸ ሩኃኒይ ቆፍጠን ብለው። ‹‹የሚኒስትሩ ቢሮ የመጅሊስ ቢሮ ሆነ እንዴ?›› ሲል ስድስተኛ ስሜታቸው ጠየቃቸው። ‹‹ምነው? ቢሯቸው የሚመላለሱ ወሬ አቀባይ ሙስሊሞች በዙብህ? ጠርዋር! የአሕባሽን ቦንድ ለመግዛት የሚመዘገብ ይሆናል። ቆርቆሮ ራስ! ይኸው እንደጥላ ይከተለኛል። ኧረ ሰዎች መላ በሉኝ! የዚህን ስድስተኛ ስሜቴን ጉዳይ! ቆይ ለመተካከት የአቋም መመዘኛው መሳደብ ሆነ እንዴ? ወይስ እንዳጎረሱት መጠን መሮኝ?››

‹‹ያ ጀማዓ! ‹ተመልከት አኺራህን፣ ተክተል አሚርህን› የሚል ትውልድ ላይ በመድረሳችን ለአላህ ሽኩር ይገባው። አልሐምዱሊላህ! መቼም እንደ ተክበሩ ሚኒስትር ሽፈራው በሙስሊሙ ዙሪያ ታላቅ ሙፍቲህ፣ ሙፈሲር፣ የሸሪዓ ቃዲ፣ ፓስተር እና ፖለቲከኛ መሆን ዓለም ነው! ስሙ! ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በዱክትርናቸው መጠራት ባይፈልጉም እኔ ሸኸ ሩኃኒይ የተከበሩ ሚንስትር ሽፈራው ‹ዱክትርናቸውን› ያገኙት ከየትኛው ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ እንዲነግሩኝ እፈልጋለሁ። መቼም አገሩ ሊባኖስ እንደሚሆን እገምታለሁ። በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሃይማኖቶች ጉዳይ ቢሮ ውስጥ የሙስሊሞች ቁጥር ከቁጥር የማይገባ መሆኑን ስሞግት ምነው እናንተ ‹አቶ ሽፈራው የእኛ አባቢ!› ብላችሁ፣ ሹክ ብላችሁ አሳቀቃችሁኝ? እኔም ‹ተባዝተው ስንት ይሆናሉ?› ስል ጠየኩ›› አሉ ሸኸ ሩኃኒይ።

ይሄኔ ስድስተኛ ስሜታቸው ፈጥኖ መለሰላቸው። ‹‹በሸጡት የአሕባሽ ቦንድ ልክ! ሙናፊቅና ባንዳዎች ተቆጥረው!›› ሲል መለሰ። ሸኸ ሩኃኒይ በረጅሙ ሳቁ። ‹‹ቂቂቂ... ታሪክ ታሪክን ይፈጥራል! ያ ጀማዓ! አሕባሽን ተጸያፋችሁ፣ ዲናችንን ብላችሁ፣ የአላህን የእምነት ገመድ ይዛችሁ በአንድነት ጥላ ሥር የተሰበሰባችሁ ሁሉ ለአሕባሽ የታሪክ ባለውለታነት የአሕባሽ ቦንድ የሚሸጥበትን እያፈላለግን ነው። ያ ኡምመቱል ኢስላም! አሁን እናንተ እኮ ኢማን፣ ጽናት፣ የማይበርድ መነቃቃት፣ አኺራን በማሰብ በአሚር የመመራት ቁበቢ የሰነቃችሁ ባለውለታ ትውልድ ሆናችኋል። እኔ ሸኸ ሩኃኒይ በአላህ ሥም አመሰግናለሁ! እነሆ! የእምነት ትውልድ እና ለፍርፋሪ አዳሪ ተለይቷል። ዲኑን የሸጠ ተሸማቋል። ዲኑን የሻደመ በዱንያ የፊቱ ጉር ሞልቶ በጉዞው ነጻነት ይሰማዋል። ሰላምን ተልዕኮው አድርጓል። ሁሉም በአኺራ ይሰበሰባል። ያኔ ታዲያ አላህ ሥራችንን ያያል። ይመዝናል። ማነው የባሪያውን ቀልብ የሰበረው? ማነው ከአላህ ባሪያ ጋር የተጨነቀው? ማነው ለሙሽሪነት ያነበደበው? ያ ኡምመቱል ኢስላም! ሊነጋ ሲል ይመሻል፣ ሁሉንም እናየዋለን። ያኔ ምርቃና ይሰበራል! የሕልም ፍርፋሪውም ጠፔ ይሆናል። የሰባራ ሳንቲም የአወጣጥ አግባብ ይጠየቃል። መንግሥት ባልበት አገር የተነሣው ሽብር፣ የጎደፈው ክብር የፍትሕን ደጃፍ ያጣብባል። ፍቅር አልባው የዓላማ ጋብቻ መናኛት እንደምታንደቀድቀው ሺኻ በኖ ይቀራል። አሁን የተከበሩ ሚኒስትር ዶክተር ሽፈራውን የማናገር መብቴን ለምን ትገፈኛለህ?›› አሉ ሸኸ ሩኃኒይ።

ዘበኛው ተቆጣ ‹‹አይቻልም!››

‹‹እንዴ! እሳቸው ግን ‹ይቻላል› ነው የሚሉት። አቶ መለስ ‹አባይን የደፈሩ› ተብለው ሲንቆለጳጰሱ አቶ ሽፈራውም አሕባሽን ለማስፋፋት እንቅልፍ አጥተው ሲባዝኑ እያየህ ድካማቸው ጋራ መገፋት ሆኖ ላገባቸው ‹የአሕባሽ ቦንድ ከወዴት ይገኛል?› ለማለት ብመጣ ፈት ትንሣኝ? ውርድ ከራሴ! እኔ ሸኸ ሩኃኒይ በሕዝብ ሙስሊሙ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብነታቸውን ከግመገማ የሚያድንላቸው ኔትወርክ ላመላክታቸው ነበር የመጣሁት። ኤጭ! ባጣማ አትሁን! ውርድ ከራሴ ብያለሁ! አንተ በሥልጣናቸው የመማገት አቅም ባይኖርህም በእንጀራቸው መማገትህን እንዴት አየኸው? ስማ ተልዕኳቸውን ማይፍረስ፣ ከነጻነት ናፋቂዎች ጋር ማበር የሰማመማል። ከሮሮከራሴ መርህ ተነሥቼን፣ ከሕጻ መንግስቱ መሮበ ቸንጮሮን ሮጮመኘውን ያሌማት...›› ብለው ሊቀጥሉ ሲል ስድስተኛ ስሜቱ ነቃተላቸው። ‹‹እንዴ! ምነው? ካድሬዎች አቶ መለስን ይከርፍሉ! እርስዎ ሚንስትሩን ኮርጁ?››

ሸኸ ሩኃኒይ ተቆጡ። በቀኝ እጃቸው የያዙትን ሙስባሕ መገዘው በፍጥነት ተስቢሕ አደረጉ። ‹‹የመጅሊስ አመራሮች ከሕዝብ ልብ ብቻ ሳይሆን ከሕዝብ ዐይንም ሸሽተዋል። ሚኒስትሩ ተጋፍጠዋል። ‹አሕባሽ የለም› የሚል የአሕባሽ ቦንድ ሽያጭ! ዋእ...!›› ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ የሸኸ ሩኃኒይ ስድስተኛ ስሜት ጣልቃ ገባ፡- ‹‹አሁን እዚህ ይህን ሁሉ ከተናገርክ ሚኒስትሩ ምን ሊሰሙ ነው?›› አላቸው። ሸኸ ሩኃኒይ ፊጥነው መልሱን ሰጡ፣ ‹‹እሱን አንተ አትጨንቀኝም! ዱሮም ሸ.መኞች ሕዝባቸውን ሳይሆን ትናንሽ ሰላዮችን ሚያመጭ ነው የሚፈልጉት! ደግሞ ምን አገባህ? የእርጎ ዝንብ! ዋላ ቢስ! ዋላ አትሁንብኝ!››

ተቁነጠነጡ፣ አጉረመረሙ። ዘበኛው ግራ ገባው። የፌዴራል ወታደሮች በጎቃት እና በተጠንቀቅ ቆሙ። ሸኸ ሩኃኒይ በተጠንቀቅ ወደ ቆሙት የፌዴራል ወታደሮች በፍቅር እና በስስት እያዩዋቸው ቀረቡ። በሁለት ወታደሮች መሐል ታጀቡ። ‹‹እናንተ የአገር ጀንበር ጠባቂ፣ የሕዝብ ሰላም ባለውለታዎች! ከመሳቸችንም በላይ በንቃት፣ በሕይወት መስዋትነት የምትጠብቁን ኖችሁ... መገኛችሁ አለኮረቻረፈልል። መንፈሳዊ ነጻነታችን ርቆናል። ‹ቆረቆንዳ ሁሉ፣ እንደ በቀቀን ጩኸ› ተንሻፈቡ› ብለው ተሳልቀውብናል። ፍልፍልፎች› ብለውም ዘልፈውናል።››

‹‹ያ ወገን! የምትጠብቁት የመሥሪያ ቤት ሹም ወዳጄ ናቸው፣ ያልወከልነውን፣ በተቋማችን የተሾነውን አቶ አሕመዲንን ‹የተከበሩ ሸሕ አሕመዲን› ሲሉ ወዳጅነታችን ቀዘቀዘ እንጂ። በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ አሕባሽ ጠመቃውን እንዲገፋበት ‹ደግ ለቀቅ የምናደርገው መሆን የለበትም› ሲሉ ተቃወምኩ። እሳቸው ግን የአሕባሽ ቦንድ ሽያጭ የት እንደሚገኝ ሳይነግሩን ‹ይቋረጥ ይሆን?› ለሚለው ሥጋታቸው ዋስትና ጠየቁ። ተልዕኮው ሲገመገም ሁሉም ሙስሊም ከአባይ ቦንድ በተጨማሪ የአሕባሽ ቦንድ ሊገዛ ይገባል የሚል ይመስላል። አባይን የደፈረ ብቻ ሳይሆን አሕባሽንም ያስፋፋ ይሸለማል። ከአገረ ሊባኖስ፣ ከታላቋ አሜሪካ፣ ከመሠረዋ የሁዳ የታማኝ አገልግሎት ሜዳሊያ ይዞ መጣልን።››

‹‹ያ ኡምመቱል ኢስላም! ተክቢር በሉ! የምንለምነው መብት ባይኖረንም የምንታገልለት ነጻነት ሕያው ያደርገናል። ኢንሻአላህ የአላህ ነስር ቅርብ ነው። ‹ያሂይማኖት ካባ የደረቡት ዩቲቋማችን ካድሬዎች ይውረዱልን! ለፍርድ ይቅረቡ!› እላለሁ። እኔ ሸኸ ሩኃኒይ ለዚህ የለውጥ ትግል ጠማሬ ጊዜ ጠብቆ ድምጼ እንደተሰማ ሁሉ ‹ሕልማም ርዕዬም በእነዚያ ታዳጊዎች መነሻ ሰብሮን ሰንቆ ‹የአላህ ነስር ቅርብ ነው› አሰኝቶኛል። ወገኖቼ! በመንግሥታቸው የሚሠጉ ሕዝቦች መሆን እንደማንፈልገው ሁሉ በሃይማኖት መሪዎቻችንም የምንሠጋ ሙስሊሞች መሆን የለብንም!›› አሉ ሸኸ ሩኃኒይ፣ ቤት እንደሚመጥር ደላላ ከእርምጃቸው ዘገን ዘገን እያሉ።

ወቀሳቸውን ቀጠሉ። በግቢ ውስጥ ቆሞ ወደነበረው አውቶብስ አናት ላይ ወጥተው ቁልቁል ከአጥር ግቢ ውጭ ያለው መንገደኛ እንዲሰማቸው ጩኸታቸውን አቀለጡት። ከጎዳናው መሐል እና በጎዳናው ዋጋ ጥግ ብዙዎች ጆሮ ሰጧቸው። ‹‹ያ ወገኔ! እኔ ሸኸ ሩኃኒይ አባውንት ነኝ። አሜሪካኖች በሌለሁት አሜሪካ ግቢ ጥርሴን የነቀልኩ! እናንተ ወታደሮች! አንተ ቁበቋ! የአሕባሽ ቦንድ የት እንደሚገኝ ታውቃላችሁ?›› ሲሉ ድንገት ወደ ዘበኛውና ቡተጠንቀቅ ወደ ቆሙት የፌዴራል ወታደሮች አመጣው ውሸኛ ሸኸ ሩኃኒይ በላቸው ዙሪያ መኮለኮል፣ ከሳቸው ጎን በአካል መታየት የፈሩ... ግን በልባቸው ያበሩ፣ በድብቅ የሚደግፏቸው ሁሉ እርሰ ዝግሳቸው ተጠያየቁ።

http://ethcriminalawnetwork.com/

ወዲያው በእልህ ‹‹አዎ እከሳለሁ! እንከሳለን!›› ሲሉ ‹‹ማንን!?›› ስትል ፈጥና ጠየቀች ...ላሳቸውን ከከበቧቸው ሰዎች መሐል። ቁመተ ዘንካታ የምትባል፣ ምራቋን ዋጥ ያደረገች ደርባባ ሴት ወይዘሮ ናት። ‹‹እኮ ማንን?›› አለች። የብር አሎሎ የመሳሰሉትን ትላልቅ ዐይኖቿን አጉረጥርጣ፣ አፍጥጣ ዐየቻቸው። ሸኽ ሩኃኒይ ፈጥነው ‹‹ብቅል አውራጅ...! ማንሽን ልበል? ጃል! ምነው አፍሣችሁ ታዩኛላችሁ? ዐቅቧቃ ሁላ! ተክቢር! ወንዶች ተክቢር በሉ! ሴቶች እልል በሉ! ሕፃናት ነሽዱ! እኛ እኮ ሁላችንም ወሐቢይ ሆነናል። ሰምታችሁኛል? **ወደ መስጂድ ስለተመላለስን፣ በሃይማኖታችን ቀጥ ብለን ስለቆምን፣ የነፌጉንን መብት ስለጠየቅን ‹ወሐቢዮች፣ አክራሪዎች ናችሁ› አሉን።** ‹የትናንትናዎቹ ሙስሊሞች አይደላችሁም። እናንተ ወሐቢይ... ሽብርተኛ... አክራሪ ናችሁ› አሉን። ተክቢር!›› አሉ ጮክ ብለው።

የከበባቸው መንገደኛ ሕዝብ ደነገጠ። እርስ በርስ እየተንሾካሾኩ አጉረመረሙ። እሳቸው በንዴት ጠፈው፣ ዐይናቸውን እንዳፈጠጡ ከጉብታው ላይ እንደጎረምሳ ዱብ አሉ። ድንገት ደርባባዋ ሴት ወይዘሮ የውተት አረፋ በመሰለው ጥርሷ ፈገግ ብላ እየተስለመለመች፣ የሐር ነዶ የመሰለውን ረጅም ወጉሯን ከጀርባዋ ነስንሳ ሰበር ሰካ እያለች ወደ ሸኽ ሩኃኒይ ቀረበች። ሸኽ ሩኃኒይ ደነገጡ። ‹‹አዑዙቢላህ...!›› ወደ ኋላ ሸሹ። ከእግር ቅልጥሟ የሚበልጠውን ረጅም ክንዷን ዘርግታ ሰበር ሰካ እያለች ልታቅፋቸው ተጠጋቻቸው። ሸኽ ሩኃኒይ ሸሿት። ሴቲቱ ፈገግታዋ ደመቀ፣ ‹‹ያ ሸኽ... ከምትወድህ ሴት መሸሽ ሐራም አሊክ!›› እያለች ስትጠጋቸው ሸኽ ሩኃኒይ ሲሸሹ ‹‹ምነው ሴት ትፈራለህ?›› አለች እየተስለመለመች። ሸኽ ሩኃኒይ ፈጥነው ‹‹አላህን ብቻ ነው የምፈራው። ሴት... ገንዘብ... ሥልጣን ይህን ዓለም ፍትህ አልባ እያደረጉት መሆኑ ሐቅ ነው። በዚህ ላይ...›› ብለው ሐሳባቸውን ሳይጨርሱ ሴቲቱ ላያቸው ላይ ክምር ብላ፣ ጭምቅ አድርጋ፣ ከንፈራቸውን በከንፈሯ ከድና ጨመጨመቻቸው።

ሸኽ ሩኃኒይ ደነገጡ! በያሙ፣ በኅዳና፣ በጠራራ ፀሐይ አስገድዳ ሐራም ፈፀመችባቸው። ‹‹ጭውውውውው›› አለባቸው። ሁሉም በአግራሞትና በገሠታ ሲመለከታቸው በንዴት ጋዩ። ከከበባቸው ሕዝብ መሐል ከዘራቸውን ተመርኩዘው በጥሞና ያደምጡ ከነበሩ አዛውንት ከዘራቸውን ነጥቀው የከበባቸውን ሕዝብ አሳደዱት። ከሴቲቷ ጋር ተፋጠጡ። ተስለመለመች። ‹‹አዑዙቢላህ! አላሁ አክበር!›› ብለው አልፈዋት ሄዱ። ሴቲቱም ደንግጣ ሮጠች። ሴቶችም እየተጨፈጨፉ እግሬ አውጭኝ ሲሉ አንዱ ሌላውን አደናቅፎ እላይ በላዩ ተነባብሮ ወደቀ። በአካባቢው ጩኸት በረከተ። ግርግሩ በዛ። የመኪኖች ፍሰት ተስተጓጎለ።

‹‹እኔ ሸኽ ሩኃኒይ ወሐቢይ ነኝ! ወንዶች ተክቢር በሉ፣ ሴቶች እልል በሉ፣ ሕፃናት ነሽዱ! አላሁ አክበር!›› አሉ እንደ መንጋ የሚነዱትን ሕዝብ ቆም ብለው ተመልክተው። ‹‹ይህ ሕዝብ ምን ሆኗል!?›› ሲሉ ጠየቁ። እዚያው እንደቆሙ ትካዜ ገብቷቸው አዘኑ። ድንገት በርካታ ፖሊሶች ከስናራው ደረሱ። ጥቂቶቹ ሕዝቡን ሲያረጋጉ ብዙዎቹ ሸኽ ሩኃኒይን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ፣ ከዘራቸውን ለመንጠቅ ከበቧቸው። ሸኽ ሩኃኒይ መሬት የሚጉተት ሙስሊሐቸውን በአንገታቸው ዙሪያ አድርገው ድንጋይ አነሱ። የመኪናው ጡሩንባ፣ የሕዝቡ ሽብር በዛ፣ ግርግሩ በረከተ። ከግርግሩ መሐል የነበሩት የደንብ ልብስ የለበሱ ፖሊሶችና ደህንነቶች ሸኽ ሩኃኒይን እያዩ ጥርሳቸውን ነከሱ። ዐይናቸውን አሳረጠረጡ። ወዲያው በዐራት አቅጣጫ ከበው በቁጥጥር ሥር አደርጓቸው። በእጃቸው ካቴና አጠለቁባቸው።

እሳቸውን ከከበቧቸው በርካታ የሕግ አካላት ከመካከላቸው ረዘም ያለው ቀይ ሰው ‹‹ወዴት እየሄዱ ነው?›› ሲል ጠየቀ፣ ሸኽ ሩኃኒይ አልሰሙትም። የራስ ቅሉን በአረንጓዴ አማይማ የጀቦነው ሰውዬ ነጭ መነፅሩን በጣቶቹ ከአፍንጫው ላይ እያስተካከለ፣ ባጠለቀው ቲሚስ ኪስ ውስጥ ሁለቱን እጅቹን ከቶ መሬቱን በሚያየው እየደቀደቀ ‹‹ለምን ሕዝብ ይውሰለስ?›› ሲል ጠየቃቸው። እሳቸውም በንቀት እየተመለከቱት ‹‹እየተፈፀመ ካለው ሽብር የእኔ ሁከት የሰላም ነው። ጉዮ ለሆነው ሕዝቡ... ‹ሕዝብ ሆይ! ይህ ሕዝብ ምን ሆኗል?› ልለው ይገባል። ብሉቱን በሽንት ቤት ግድግዳና በፈስ በክ ድሪዝ መቦንፈስ በቀቶ ‹ቢቃ!› ሊል ይገባል...። ዋእ! ተውኝ! የተባልኩትን የምል፣ አድርግ የተባልኩትን የማደርግ ብቻ ከሆነ እኔ ከበቀቀን ምን ተሻልኩ?! ‹እንደ ትናንቱ ‹ብኢትዮጵያ የምትገኙ ሙስሊሞች› ሆናችሁ አንገታችሁን ካልደፋችሁ፣ በሃይማኖታችሁ ካልተሸማቀቃችሁ ለአገር አሥጊ ናችሁ› መባላችን ለምን? ይህን ነባቱን ከመጋፋት የበለጠ ምን ሽብር አለ? መንግሥት በገርገር የሃይማኖት ጉዳዮቻችን ጣልቃ ገብቶ፣ አንድን ወገን ወግኖ ‹እኛ በመረጥንለት የሃይማኖት አስተምህሮ የማይፈሰ፣ እኛ ከሰጠነው የጫማ ተጥሮ በላይ የማይጫማ የማይፈልግ ካለ ልሞሩን እንከረክማለን› ሲል የበተረ ሥልጣን አደባባይ ስንሰማ የሚሸከም ጫንቃ እኔ ሸኽ ሩኃኒይ የሉኝም። ሐቁን ጋረሸን ካለችኝ እኔ ሸኽ ሩኃኒይ ወሐቢይ ነኝ። ከአባቶቼ የመጣብኝ የበቆሸሸ ጨርቄ ደቂ መዝሙር... የአሕባሹ ዶክተር ሰሚር በየአገሩ በእስልምና ወንዶ የኖረን ሕዝብና ዑለማ አክፍረው ደም ማቃባታቸው ላይኾስ የአገሬን ሙስሊም ለማክፈር፣ እርስ በርስ ለማጋጨት መንግሥት ክንዳቸው መሆኑ፣ የተከበሩ ሚኒስቴር ዶ/ር ሽፈራው እሳቸውን ሲያንቆለጳጵሱ በረጅሙ ሳቅኩ። ጅብ አያውቁት አገር መጥቶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል። እኔ ሸኽ ሩኃኒይ አልኩኝ፡- ‹ይህ ሃይማኖትን ቁርበት የሚልበስ የቡኮላካ ‹ታሪክ›... ተረት... የአገሬውን ባለሥልጣን ያጠመቀው ዕዮናዊው ይሁዳ ሐጋይ ኤርሊች መሆኑን ስድስተኛ ስሜቱ ሹክ ብሎኛል። ይሁዳው የፍልስጤምን እምባ አተቅጽያ ውስጥም ማየት ይናፍቃል። አስራኤላዊው ተረት ጸሐፊ ‹መብቱን የሚጠይቅ፣ በሃይማኖቱ ፅናት ያለው፣ በማንኑቱ ኩሩ የሆነ ሁሉ ወሐቢይ ሆኗል› ብሏል፣ እናም እኔ ሸኽ ሩኃኒይ ወሐቢያ ነኝ! እጄን በካቴና ብትጠፈንጉ፣ እግሬን በእግረ መቅ ብትጠፍጉ አጅሬን ታበዙታላችሁ እንጂ ስቃዬን አታደምጡትም›› አሉ ሸኽ ሩኃኒይ - በካቴና የተጠፈረውን እጃቸውን እያወዛወዙ።

‹‹ለምን ዝም አይሉም?›› አለ እሳቸውን ከከበባቸው ፖሊስ መሐል አንዱ ተናደዶባቸው። በሰዳፍ ለ[illegible] ሲል ሌላኛው አፈፍ አድርጎ ተከላከለላቸው። ‹‹አሁን ወዴት እየሄዱ ነበር?›› ሲል ጠየቃቸው። ‹‹ወደ ፌዴራል ጉዳይ ሚኒስቴር ወደተከሰሱ ዶ/ር ሽፈራው።››

‹‹ለምን?›› አለ ሌላው የደንብ ልብስ ያልለበሰው የሕግ አካል። ‹‹መጅሊስ በሐረር ለሰበሰባቸው፣ በግዴታ ለጠራቸው፣ በእንጀራቸው ለመጣባቸው የመጅሊስ አባላትና ኢማሞች ስለ አሕባሽ አስፈላጊነት ከልማታዊ መንግሥት ጠንሳሚታ አንጻር ፈትዋ እንዲሰጡኝ። በየትኛው ኪታብ፣ ምን በሚለው ባብ ላይ እንደቀሩት፣ ማን እንዳስሞገሳቸው ልጠይቃቸው...! ያመንግሥት ሞድሎ ያለ ጣልቃ ገብነት ትናንትን ናፋቂነት መሆኑን ግልጽ ልናገር ነው።››

‹‹ለምን አያርፉም?››

‹‹ለምን አርፋለሁ? እኔ እኮ የአገር አዛውንት ነኝ። ለዲኔም ጁንዱላህ ነኝ። ‹መንግሥት የኢስላምን ወሰን አልፎ ሊራመድ አይገባም› ልለው ይገባል። ‹የአስተላለፉበና የእምነት ነፃነት ይከበር› አላለሁ። ተብሊግ፣ ሱፊይ፣ ሰለፊይ፣ ኢኽዋን፣ ወሐቢይ የኢስላማዊ አስተምህሮት መንገድ እንጂ የአክራሪነትና የሽብር መንገድ ነው ብዬ አላምንም። ኢስላም ሰላም ነው። ይህን በሚለቱ ወሐቢይ ብለውኛል። አዎ! ወሐቢይ ነኝ! ‹መስጊድ ኦና ሆኖ፣ ኢስላማዊ መርህ ከሕይወት መንገድ ተፈናቶ፣ ሙስሊሞች በእምነት ገመድ ወንድማማችነትና እህትማማችነታቸው ላልቶ ካላየን› የሚሉትን በመቃወሚ ወሐቢይ ብለውኛል። አዎ! ወሐቢይ ነኝ!›› አሉ ሸኽ ሩኃኒይ።

‹‹ወደ ማረፊያ ቤት ውሰዷቸው›› አለ ቀጠን ያለውና የደንብ ልብስ ያልለበሰው ፖሊስ። ሸኽ ሩኃኒይ ፊታቸው በደስታ ደመቀ። ‹‹ስማ! እስር ቤት ለእኔ ‹ከል› ነው። ቁርአን እንሐፍሳለን፣ እናስተነትናለን። የሚባክንብን ጊዜ የለም። እንሂድ... የእኔ ዘብጥያ መውረድ አጋጣሚው ለበጎ ነው። ያልተሰማውን ወቀሳ ለናርድ በታሰሩበት ሰበብ ይሆናል። እንሂድ! አላህን ግብ ያደረግክ፣ የነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጎዳና ጎዳናዬ እንዲሆን የወናዙ ነኝ ብለህ ለሰማኸኝ ዑለማዎች ክብር የምሰጥ፣ ኢማሞችን የማልዘልፍ፣ አገሬን የምወድ ወሐቢይ ነኝ! እንሂድ..!›› አለ ሸኽ ሩኃኒይ። ‹‹ከዋናዉ ሸኽ ሩኃኒይ ...›› እያለ....።

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ‹‹እኔ ወሐቢይ ነኝ!››

‹‹በቃ ሆንኩላችሁ!››
‹‹ምን?››
‹‹እናንተ የፈለጋችሁት ሳይሆን እኛ የፈለግነው ሆነ። ቢኢዜኣህ ገና ማር ቅጠሉ ሁሉ ይሆናል?››
‹‹ያ አላህ?!››
‹‹ምነው?››
‹‹ምንም... ብቻ ፈራሁ...! እ... እንጃ ግን ሠጋሁ..!
‹‹በምኑ?››
‹‹መንግሥትና መጅሊስ በጥምረት በተከተሉት ፖሊሲ! በዚህ ላይ ደግሞ...።››
‹‹በቃ! በቃ! ተወው...! እርግጥ **ሕገ-መንግሥትን የሚጥስ መንግሥትና የአላህን ቅጣት የማይፈራ መጅሊስ ሲጣመሩ ያስፈራል። ዜጋን ሥጋት ውስጥ ይከትታል። ኡምማው ወከባ ይበዛበታል። የቁጭት ጎሜ ይቋጥራል።** እልህ ውስጥ ይዶላል። መንግሥታዊና ሃይማኖታዊ ሽብር ይፈጠራል። ሃይማኖት የፖለቲካ ማስፈጸሚያ ሲሆን ደግሞ ትንንሽ ‹አማልክት› ይፈላሉ። ሕብዝን በፍርኃት የሚያሸብሩ፣ ሰማይን ደግፈው የያዙ ይመስል እንዲሰገድላቸው የሚፈልጉ። ሁሉም ስለ እነሱ ካላቀነቀነ፣ መቶ በመቶ ካልደገፈ፣ የተለየ ሐሳብ ካንሸራሸረ፣ የሚጭኑበትን ካልተቀበለ ‹አክራሪ፣ ሽብርተኛ፣ ወሐቢይ› ይባላል። ሰው ለሥርዓቱ... ሰው ለፈጣሪው...›› ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ ስድስተኛ ስሜታቸው ፈጠን ብሎ ‹‹ሰዉ ‹የድምፅ ካርዳችን ባክኗል። ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትናችን ተንዷል። **መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት አንዱን የሰላም ጎርፍ፣ ሌላውን የሽብር ማዕበል በማድረግ ከፋፍሎናል**› ሲል ያጉረመርማል። ፈስ ቡክን አጣቢል። ‹**የተከበሩ ሚኒስትር ዶክተር ሽፈራው መሪ ተዋናይ ሆነዋል**› ሲል ይወቅሳል። *መንግሥታቸውና* እሳቸው ለ‹ሽይኹል ፊትና› ለአገሩና ለኢማሙ ምስጋና ማቅረባቸው፣ ጉዳዩን ለሚያስፈፅምላቸው መጅሊስ መንግሥታቸው ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል መግባታቸው ጣልቃ ገብነቱ የእግር እሳት ሆኗል። የሚኒስትሩ ዳይሬክቶሬት ‹የአዋጅ ሥልጣን አለን› ይላል። አሕባሽ መስፈርታችን የሆነውን ሰላማችንን የሚያረጋግጥ፣ ልማታችንን የሚያፈጥን፣ የዲሞክራሲ ሂደታችንን የሚያሳካ በመሆኑ ይሁዳው ‹ምሁር› አንድ አቅጣጫ አሳይቶናል። በአዲስ ርዕያችንም ላይ የጋራ አቋማችንን አድርገናል። እኛ መንግሥት ነን! ወሐቢይን በጋራ እንደቁሳለን!› ይላሉ። እንጃ... ሰው ሁሉ እልህ ተጋብቷል። ‹ወሐቢይ ሆንን› ይላል። እ... መቼም እርሶ ወሐቢይ አይሆኑም....!››

‹‹ውሃ ይብላህ! የፈለግኩትን የመሆን ሰብዓዊም፣ ዲሞክራሲያዊም መብት አለኝ። እኔ ከሁሉም በላይ ሙስሊም ነኝ። የምኩለውን መስመርና መዝሐብ ፌዴራል ጉዳይ ሚኒስቴርና መጅሊስ የሚጭኑብኝ፣ አላቁጠውና አብኩተው የሚጋግሩኝ ምንትስ አይደለሁም። ስማ... ፊቱን ወደ መስጂድ የመለሰው ሙስሊም በሃይማኖቱ ቀጥ ያለ ሁሉ ለእንዳንተ ዓይነቱና ለእነርሱ ወሐቢይ ነው። ዋእ...! ወሳሂ በመንግሥታችን አፅርን! ግልጽ አቋሜን ልንግረው እፅልጋለሁ። ‹ተክቢር! ብዙ ‹አላ› በማለት ድቢ አስንሞግለሁ...! አላ! መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ‹ጥጥና ጣልቃ ገብነት ፈፅሟል። አንዱን ደግፎ ሌላውን በማውገዝ ‹ሽብርተኛ፣ አክራሪ፣ ወሐቢይ› በማለት ከፋፍሎናል። ‹ኢተቂላህ! አድብኩ ኣላስሀ›። አሎ ሸኽ ሩጎኒይ ስድስተኛ ስሜታቸውን ተቆጥተው።

ስድስተኛ ስሜታቸው ደንገጡ ፊራ ተባ ብሎ ‹‹አዮ ሸኽ ሩጎኒይ... ለማለት የፈለግኩት እ... ማለቴ...›› ብሎ ሊቀጥል ሲል ሸኽ ሩጎኒይ ፈጠን ብለው ‹‹ምንም አተበል! ሕሊና ቢስ ጥገኛ ካልሆንክ ‹**ውለማዎችን በመሳደብ ውለማነት አይገኝም!** ከሙሽሪኮች ጋር አብሮ ‹ሽይኹል ፊትና› ለመሆን የቁናት መራዊት ሙስሊሙን መበዋበዋ፣ እርስ በርስ ማናቆር፣ አላህን ከሀደው፣ ሕዝብን ከሃዲው፣ መንግሥትን ከሀዲው በመጠረጠር እርስ በርስማመው ይከፋፍላል። ይህ በታሪክ ይታመቃል። ይህን በፈጠር ማስተንበን ይቻላል። ይህ የተለመጀ ባህሪያቸው ነው። የሙስሊሙን አንድነት ማጀናፀስ ወሳሂ የሰላምና የልማት ተልዕኮን አደጋ ውስጥ የሚከት ነው። እናንተ ብታከናሩንም እኔ የኢህራ ወንድሞቹ መሆናችሁን ልናቀው የሚያስችል አቅም የለንም። ወሳሂ እናንተ አሁን እጃችሁን እንጂ ልባችሁን እንዳልሰጣችሁ ስድስተኛ ስሜቴ ሹክ ብሎኛል። መቼም እኔ እንደናንተ መንግሥት እንደ ዘይቲ ባለመጣው ውለማ ልበ አይሸነፍም። አልጠመቅም! እናንተ እስ የአገሬን ውለማ ንቃችኋል..! አላህ ሸሂዴ ነው እኔ ወሐቢይ ነኝ! ይኸው ነው አቋሜ! ተመልከት እስክ አቋሜ አየምርም?! እንዳንተ ለለውጥ ይልተዘጋጀ ግተር እቋም የለኝም። የጃጀና የገረጀፊ አስተሳሰብ ያዝር አልዘርም። ፈተናችሁን በሶብር እናሳልፋለን። የተደገፋችሁት መንግሥት መንግሥት ስማያትን አያወርጣችሁም። ወላሂ ለሆዴ ስል ከፈሰው ጋር አልነፍስም። የት፣ መቼም በመስሊሞች አንድነት አቋም ላይ የጸናሁ ነኝ። የሰላም አምባሳደር ነኝ። እኔ ሸኽ ሩጎኒይ ኩሩ ነኝ። ተክቢር! ወንዶች ተክቢር በሉ...! ሴቶች እልል በሉ...! ሕፃናት ናሽዱ!››

‹‹**የአገሬ ሕዝብ ሆይ! ጉዳ ስሜ! መንግሥት ዘይት ብቻ ሳይሆን ውለማም ከውጭ ማስመጣቱ የእድሜያችን ትሬንስፎርሜሽኑ** እቅድ ሆኗል! ይህ ረመዳን መሉ ጥቂን እያመጣው የሚባዳይን ተከሪት ተጋፍጦታል። አላህ ዐውና ብሎ በጎንደሙም ሞሉቶ በረሀመቱ ይቀበለን! ጀኑቱል ፊርደውስ ይወፍቀን! አሚን በሉ!›› ሲሉ ሁሉም በጎዳናው የተከለከለው ‹‹አሚን!›› የሚል ምሳሽ ሲሰጥ የሚከለከ አካባቢ በተሰማው ድምፅ ተናጠ። ሰው በዜብራ መንገዱን ለማሳበር ተከልከሉ፣ መቲናውን ተኮ ሸኽ ሩጎኒይን በናፍቆትና በስክት ይመለከታቸው ጀመር። ተጣያጅ የመጣው ሁሉ መንገዱን ከማሳበር ይልቅ እጣቸውን ማድመጥ ጀመረ። የጉዳዩ ሁሉ ጉዳይ አድርጎ በጎዳናው ለድጋፍ ወይም ለተቃውሞ የመጣ ሕዝብ ይመስል ተኮለኮለ።

ሸኽ ሩጎኒይ ዕጹ ልብስ ለብሰዋል። ሱሪያቸው ከቁርጭምጭሚታቸው ርቆ የተጎለተለ ነው። የሂማቸው ዋቁረት ሐር ይመስላል። ርገመቱ ሹርባ ያሠራል። በእጃቸው ከያዙት ዳንስ ካሉት መጽሐፎች መካከል ‹‹መሩቲሑል ፊረጅ› ኡሱለ ሠላሳ› ‹Mile stones›› የሚሉት ርዕሳቸው በግልጽ ይታያል። የሙስሐቸው ርገመት መሬት ይንተታል። በጎጭ መደብ በተለያዩ ደማቅ ቀለማት ከአምስት ያላነሰ ክበት ያለበት ከፈታቸው ያምራል።

‹‹አህ... እህ›› በማለት ንርጅቸውን ጠራርገው ከመንገድ ዳር ካገኙት ጉብታ ላይ ወጡ። ‹‹ሕዝቢ ሆይ! ይህ ሕዝብ ምን ሆኗል?›› ሲሉ ጠየቁ። ሁሉም እርስ በርሱ በጥርጣሬ ተፋጠጠ። አካባቢው በዝምታ ተዋጠ። ፍርኃት በጎዳናው ሰፈነ። ብዙዎች ብርክ ይዟቸው። ያሰቡትን የሚያውቁባቸው መሰላቸው። ሸኽ ሩጎኒይ በጎዳናው የፈሰሰውን ሕዝብ ቁልቁል እየተመለከቱ ‹‹ለምን ዝም አላችሁ?›› ሲሉ ጠየቁ። በጎዳና መሐል የነበባቸው በፍርኃት የተዋጠው ሕዝብ መልስ አልሰጣቸውም። ልባቸው አዘነ። ነፍነትን ናፈቁ። ‹‹ሺዓ-ቅለሁ! ሕዝብ በፍርኃት ማቅ ውስጥ ተጀቡኗል። ሕዝብ ዝምታን ይመርጣል። ይህ ሕዝብ ብሶቱን የማይሰሙ፣ ሐሳቡን የማይቀበሉ፣ እምነቱን ሳይሆን እምነታቸውን የሚጭኑበት አምባገነኖች ተፈራርቀውበታል። ስህተቱን ለመስማት የማይፈቅድ በጉረ ሥልጣን ተጭዋዊሏል። ለመታረም ዝግጁ ያልሆነው መጅሊስ አማሮታል። ብሶት አርግዟል። ‹ሁብሩን ጀሚል› ብሎ ዝምታን መርጧል። ‹‹ይ ታሪክዊ ሐባሳ በታሪክዊ ለውጥ ውስጥም ‹አዲስ ዙፋን አንጂ ለውጥ መቼ መጣ?› በሚል የማቁንቁን ፍርኃት ውስጥ ይወዘወዛል። ሕዝቢ ሆይ! ዘመን በዘመኑ ነው መጠየቅ ያለበት። ‹አንድ ብሔር፣ አንድ እምነት፣ አንድ ቋንቋ› የሚል መርህ ተረት ሆኗል - በዚህ ዘመን። ‹ግባችን ኮሚውኒዝም ነው። መመሪያችን ማርክሲዝም ነው› የሚለው ታሪክ በዚህ ሥርዓት ሥርዓተ ቀብሩ ተፈፅሟል። አሁን ያለንበት በጉረ ሥልጣን የሃይማኖት ነፃነትን፣ ሕገ-መንግሥታዊ መብታችንን ነክቷል...፣ ለጣልቃ ገብነቱ ፍርድ ቤት ልንጉረው ይገባል›› አሉ ሸኽ ሩጎኒይ ተቆጥተው።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፋይል 26
http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚያደርጉት በግላቸው ተንቀሳቃሽ ኮፒተር (ላፕቶፕ) ነው። በዚህ ዝግጅት ላይ እንደዋነኛ ችግር የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ ችግር ይጠቀሳል።

እያንዳንዱ የቢቢኤን ፕሮግራም አዘጋጅ ለኢንተርኔት ከደመወዙ ውጪ በወር ብር 200 ክፍያ ያገኛል። ዘወትራዊ ባይሆንም የኢንተርኔት አጠቃቀም ላይ የተደጋገመ የኔት ወርክ ኮኔክሽን ችግር የገጥማል። በተለይም አፕ ሎድ በሚደረግበት ጊዜ እየተደጋገመ የኔት ወርክ ወይም የኮኔክሽን ችግር ያጋጥመዋል። በዚህን ጊዜ ጋዜጠኞቹ የተደጋገመ ችግር በመሆኑ ከተመደበላቸው የ200 ብር ወጪ በላይ እንደሚያወጡ ላሳውቅ እወዳለሁ።

**ማስታወሻ**

**የቢቢኤን ዝግጅትን ይዘት ለማሳድግና አድማሱን ለማስፋት ወቅታዊን ጉዳይ በድረ-ገፅ በፍጥነት ለማሰራጨት ፤ከወንድም ላዲቅ በቀረበው ሀሳብ አሁን ባለው! ላይ! የባለሙያዎች! እና! የይዘት! እይታ! ተጨማሪ! ማለትም! ማህበራዊ! ፣ባህላዊ! ፣ሥነ-ጥበብ! ለማካት! ሁለት! ባለሙያዎች! ማስፈለጉ! ታምኖበታል፤በዚህ! ጉዳይ! ላይ! ዘክሪያን! እና! ሁሴን! ከድርን! ያነጋገርኩ! ሲሆን! በመሰረታዊ! ጉዳይ! ላይ! ተስማማተናል።! እንዲት! የሚለው! ዝርዝር! ጉዳይ! እና! የክፍያ! ጉዳይ! ቀጣይ! እርምጃ! ሲሆን! በዚህ! ጉዳይ! ላይ! ከሀሳብ! አመንጪ! ወንድም! ላዲቅ! የምንነጋገርበት! ይሆናል።!**

ከዋናው ጋር ትመሳከሯል

ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ወንድም ሳዲቅ መሐመድ

የቢቢኤን ( BBN) የብድር ብሮድ ካስቲንግ ኔት ወርክ የድረ ገፅ ራዲዮ(intrnet) እና የማህበራዊ ውይይት (Paltok room ) ራዲዮ ላይ ሥራውን ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በአገራችን ኢትዮጵያ፡-

- ወቅታዊ ጉዳይ
- ፖለቲካዊ
- መስሊሙን ትኩረትን ያደረገ የመብት ጥሰትና እና መብት ይጠበቅ ጉዳይ (በተለይም)ተማሪዎችን በተመለከተ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ዙሪያ
- የአህባሽን ጉዳይ በተመለከተ
- የመጅሊስን ጉዳይ በተመለከተ

ከፈጅ ጋር በተያያዘ ሌላ ጉድ አለላችሁ! ፈጽራል መጅሊሶች ቦሐጅ ጉዳይ ለመደራደርና ለመፈራረም ወደሳኡዲ ሊሄዱ ነው! ሪጉዙ የሚሄዱት አራት ሰዎች ሲሆኑ አህመዲን አብዱላሂ፣ አባም እና የፈጅ አስፈጻሚው አቶ አማን ሁሴን ይገኙበታል። እዚያ መሀመድኑር ናጂባል ኢትዮቃያዊ ነው አስከሃሬ ሙስናውን፣ የቤት ኪራዩን ሁሉ ሲያመቻችላቸው የቆየው። ይህ ሰውዬ ለራሱም 6 አባዱላ ሚኒባስ ያለው ሀብታም ነው። ያሃጅ መስና ዋና አመቻች እሱ ነው። ሳኡዲ ውጠየ ተቃውሞ ይገጥመናል ብለው ስለፈሩ መሩቱ ሃጂ ኡመርን ይዘው ሊሄዱ ነው ያሰቡት። አባቸው ይስሚመ አይሰማሙ ቀርጡን ያወቅኩት ነገር ባይኖርም ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚገኘው የአራብኛ ሰዎች ፓስፖርት ግን ዲፕሎማቲክ ጃሙኣ ሸባ ተመቶበታል። (የሁሉም መጅሊስ አመራር አባላት ፓስፖርት ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው የሚተመጠው) ጉዞውም አገል ዮሰት ነው። ያሳዝናል ሊባረሩ ጥቂት ጊዜ ቀርቷቸውም እንኳን ከሌብነታቸው መቆጠብ አይፈልጉም!!! አላህ አክበር! ምን አይነት የብር ፍትር ነው የያዛቸው???!!!

ሙስሊም ወንድሞቼ እና እህቶቼ ሆይ! እስቲ እናስተውል... እኛ አወሊያ ተሰብስበን መፈክር ስላሰማን ብቻ ብዙ የለራን መስሉን እንረካለን። አልሀምዱሊላህ አላህ አጅራችንን ያበዛዋል። ሙስሊሞችን ጠምዶ የያዘው ዶክተር ሽፈራውና ድርጅቱ ግን በርካታ ስራ በሚሊዮን ብር በጀት እየሰራ ነው!!! እኛ በጥቂት ነገር ስንረካ እነሱ ግን ወስጥ ለውስጥ ብዙ ድንጋይ ይፈነቅላሉ። አላህ እንደ የእጅጅና መእጅጅ ቁፋሮ መና እያደረገባቸው እንጂ!!! አሁንም ቢሆን ብዙ ስራ ይጠበቅብናል። ገና እስቶጋሪውን ትግል እየጀመርነው ነው! ተስፋ በፍጹም አንቆርጥም!!! እስከመጪረሻው አላህ ያደርሰናል... እስካሁንስ እዚህ የደረስነው በአላህ ፕሮግራም እንጂ መች በእኛ ልፋት ሆነና!!! ከምንጊዜውም በበለጠ ምርጫውን ሰመጠምዘዝ የሚካሄዱትን ሽፍጦች ለመቃወም እና ሁሌም በሰላማዊና በሰላማዊ መንገድ ብቻ መብታችንን ለመጠየም ቁርጠኛ መሆን አለብን!!! እኔ ይሽው ለእናንተ መረጃውን በማድረስ ሃላፊነቴን ተወጥቻለሁ! ሁላችሁም ይህን ፅሁፍ ታግ እና ሼር በማድረግ፣ ፕሪንት አድርጎ በፎቶኮፒ ለሰዎች በማዳረስ በትእግስት ሃላፊነታችሁን ተወጡ!!!

‹‹አላህ ከትእግስተኞች ጋር ነውና!››

‹‹የአላህን ሃይማኖት ብትረዱ አላህም ይረዳችኋል።›› ቅዱስ ቁርአን

Flamanllah

# ጉዞው ቀጥሏል

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፌርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

## ሆድ ሲያውቅ...

ኢስላምን የማንኳሰስ ዘመቻ ከተጀመረና እኛም ወደ አላህ መጮህ ከጀመርን ሶስት ወራት ተቆጠሩ። በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች አጋፋሪነት፣ በፌደራል ጉዳዮች አዝማችነት ኢስላምን የማጥላላቱና ሙስሊሞችን ከእምነታቸው የማለያየቱ ሥራ በጥልቀት እየተሄደበት ነው። እኛም እዚህ መጮህ ከጀመርን ወዲህ አምቀውት የነበረውና ህዝበ ሙስሊሙን በማስተኛት ሃይማኖቱን እንዴት ሊሸረሽሩት እንደነበር ያሴሩት የነበረው ሴራ እየተጋለጠ ነው። ሰሞኑን የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በተቀነባበረ ሴራ ኢስላምን የማጥቃት ዘመቻ እያካሄደ ነው። ባለፉት ሁለት ሳምንታት በሠንደቅ ጋዜጣና በሪፖርተር ጋዜጣ በጠረጴዛ ዙሪያ የነበሩትን ሴራ ሚኒስትሩና ዳይሬክተሩ ተንፍሰውታል። የዳይሬክተሩ ለያዥ ለገራዥ ያስቸገሩ የድንፋታ ቃላትን ለሴላ ጊዜ ላቆየውና ሚኒስትር የተባሉት ዶ/ር ሽፈራው አሁድ መጋቢት ፱ ቀን ፪ዐዐ፬ በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ እስልምናን እንዴት ከመስፋፋት ገትተው የራሳቸውን ሃይማኖት ሊያስፋፉ እንደሚዶልቱ ያስረዳሉ።

ጋዜጠኛው «መንግሥት በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ ገብቶ እየተጫወተ ባለው ሚና የቸግሩን አቅጣጫ ለመቀልበስ እየተከተለው ያለው አካሄድ ትክክል ነው ይላሉ?» በሚል ላቀረበላቸው ጥያቄ ረዘም ያለ ሐተታ ከዘበዘቡ በኋላ «የዲን ዕውቀቱን በሚማሩበት የሠላም የፀጥታና የደህንነት ጥበቃ ተደርጎ ሊሆን ይችላል...» የሚል ግልጽ በእስልምና የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ሂደታቸውን አጋልጠዋል። ለመሆኑ በመስጂድ የዲን ትምህርት ስንማር የደህንነትና የፀጥታ ጥበቃ ተደርጎልን ያውቃል እንዴ? የኛ ደህንነት፣ ፀጥታ ጠባቂዎችን አላህ ነው። በአይሁዳዊ መርዝ የተለወሰ አስተምህሯቸውን ለማስፋፋት ግን የደህንነት፣ የፀጥታ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም የአላህን ዲን አይደለማ የሚያስተምሩት፤ ውሸትን የያዘ፣ በሚናገረው የማይተማመን ሁሌም ሲጋት፣ ሁሌም አላህ ፍርሃትን ልቡ ውስጥ ያሳድርበታል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተሰጣቸው ኒዕማ አንዱ ጠላቶቻቸው ገና በሩቁ እንዲፈሯቸው መደረጉ አይደል? እነሆ ጠላቶቻችን ኢስላምን ለመመረዝ በሚያደርጉት ሴራ በፍርሃት እንደሚወጠሩ ሚኒስትሩ ተናገሩ።

ሕፃናት ጥፋታቸውን ለመደበቅ ይዋሻሉ። ስናፋጥጣቸው ግን አምነው ይመለሳሉ። የባለስልጣናት ቅጥፈት ግን ከስም፣ ከክብር፣ ከወንበር መዝቀጥን ያመላክታል። መንግስት እኒህን ሰው እንዴት በጉያው እንዳቀፈ አይገባንም! ይህንን ውሸት እንብቡትማ

«አሁን የኢትዮጵ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ያመጣቸው መምህራንም ቢሆኑ በራሳቸው ጊዜ የመጡና ትምህርቱን ያስተማሩ እንጂ ይህንን ትምህርት ካልተቀበልክ በስተቀር የሚሉበት መንገድ የለም...» ሱብሀን አላህ ውሸት! መምህራኑን ያስመጡት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግሥት በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በተጻፈው ደብዳቤ መሆኑን ከሊባኖስ የመጣው ዶ/ር በግልጽ በአደባባይ ተናግሯል። ሊባኖሳውያኑ የመጡት በራሳቸው አይደለም በጥሪ ነው።

«መንግሥት ሙስሊሙን ህዝብ እየጠየቀ ያለው መርሆችን አክብሮ....»

የኢትዮጵያ መንግስት የኢትዮጵያ ሙስሊምን በሙሉ በጥላቻ ዓይን ማየቱንና ተንኮል እየጎነጎነለት እንዳለ የሚያሳየው ይኸው የሚኒስትሩ ንግግር ነው። «አህባሽ ካልሆንክ ጠላት ነህ ማለት ነው» እያሉ ነው። ሚኒስትሩ ያሉት «መንግስት ሙስሊሙን ህዝብ....» ነውንጂ «በአክራሪነት የሚጠረጥረውን ሙስሊም» አይደለም። ሙስሊሙ ሕዝብ በሙሉ በፌደራል ጉዳዮች ተንኮል እየተሠራበት እንዳለ እየተገለጸ ነው። ምን ሊያደርጉን ይሆን? እኛ ግን የሴረኞችን ሴራ [illegible] ጌታ አለን። አላህ ተንኮላቸውን በሙሉ ያጋልጠዋል! ኢንሻአላህ!

ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን ማንም ሳይነግረን ቀድመን ተረድተናል። ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል መሆናቸውን፣ የመንግሥት ሃይማኖት የሚባል እንደሌለ በደንብ እናውቃለን። ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ የመንግስት ባለስልጣን ከማንም በፊት ጸብ ውስጥ



የሚገባው ከኛ ከሙስሊሞች ጋር ነው። ሚኒስትሩ ግን ሆን ብለው እኛን ሙስሊሞች ለክርስቲያኖች ሥጋት እንደሆንን አድርገው ያቀርባሉ። እኛ እኮ እንኳን ኢስላማዊ መንግስት ልንመኝ አይደለም ህገ መንግስታዊ መብቶቻችን እንዲከበሩልን እንኳ እየጠየቅን አይደለም። የፌደራል ጉዳዮች ሰዎች ግን በተቋማችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ያልተገባ እና ኢ-ኢስላማዊ እንቅስቃሴ «ይቁምልን» ስንል በመንግስታዊው አዲስ ዘመንና በሌሎችም አፈ ቀላጤዎቻቸው ጥያቄያችንን ወደ መንግሥት ግልበጣ ሊያዘሩት እየሞከሩ ነው። አሁንም መልስን እንናገር ጥያቄያችን «**ህገ-መንግስታዊ የሆነው መሪዎቻችንን የመምረጥ መብት ይከበርልን**» ነው። **አዎ! ህገ-መንግስታዊ መብቶቻችንን ተነጥቀናል! ይመለሱልን! ድምፃችን ይሰማ! ድምፃችን እስኪሰማም እንጮህለን! አዎ! እንጮሃለን!**

ዜና-ከገጽ 4 የዞረ

## የኢቴቪ የምሽት ፕሮግራም ህዝበ ሙስሊሙን አስቆጣ!

አርብ መጋቢት 7/2004 ከምሽቱ ሶስት ሰአት በኋላ ኢቴቪ ህዝበ ሙስሊሙን አስመልክቶ ያቀረበዉ ፕሮግራም ብዙሀኑን ሙስሊም እንዳስቆጣ ተገለፀ። በፕሮግራሙ ላይ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተወካዮች ከፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጋር የካቲት 26 ያደረጉት ውይይት ለፕሮፖጋንዳ እንዲመች ተደርጎ ተቆራርጦ የቀረበ ሲሆን ከስድስት ሰአታት በላይ የፈጀው ውይይት ልከ እንደ ኤፍ ኤም 98.1 ፕሮግራም የተወከሮቹን ንግግር በመቆራረጥ በ 30 ደቂቃ ውስጥ ጨምቀው አቅርበውታል። በዚሁ ፕሮግራም የፌደራል ጉዳዮች ለሙስሊሙ ጥያቄ መልስ እንደሰጠ በማስመሰል ለማቅረብ የተሞከረ ሲሆን የሙስሊሙ ተወካዮች ለህዝቡ ባቀረቡት ሪፖርት ግን «የፌደራል ጉዳዮች ሰጠሁት ያለው ምላሽ ላዩ ሲታይ ምላሽ የሚመስል፣ ውስጡ ግን ብዥታ ያለበት እና ተጨማሪ ማብራሪያ የሚጠይቅ ምላሽ እንደነበር» መግለፃቸዉ የሚታወስ ነዉ።

በፕሮግራሙ ላይ ዶ/ር ሽፈራዉ ምላሽ ያሉትን ካቀረቡ በኋላ በህገ ወጡ መጅሊስ የተመሠረተዉ የኡለማዎች ም/ቤት ዎና ፀሀፊ አቶ ኢዘዲን ለሙስሊሙ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ሲዳዳቸዉ ተሰተውለዋል። የህዝብ ዉክልና እንዳላቸው በማስመሰልም «ምርጫዉን ለማካሄድ እየተዘጋጀን ነው» ብለዋል።

አቶ ፊቲህ የተባለው የአህባሾች ዋና አስተማሪም የኡለሞች ም/ቤትን በመወከል «አህባሽ የሚባል ነገር የለም!» ሲል የገለፀ ሲሆን ካሁን ቀደም በፋና ኤፍ. ኤም በቀበረው ፕሮግራም «እኛ አህባሾች እምነታችን ይህን ይመስላል» ሊያለ ገለፃ ያደረገ የነበረ መሆኑን በማስታወስ ብዙዎች በመካዱ እጅግ መገረማቸውንና ማፈራቸውን ገልጸዋል። ሊያይዘውም አስተያየት ሰጪዎቹ «ጥያቄዎቻችን አልተመለሱም! መጅሊሶች እስኪወርዱ፣ የአህባሽ የግዳጅ ጠመቃ እስኪቆምና አወሊያ ለህዝበ ሙስሊሙ እስኪመለስ ድረስ ለላማዊ ትግላችን ይቀጥላል! ጥያቄዎቻችን ሳይሸራረፉ ሊመለሱ ይገባል!» ሲሉ ገልጸዋል።

## «ወሃብያ» እና «ወሃብያ ያልሆኑ» በሚል ሙስሊሙን ለሁለት መሰንጠቅ አደገኛ አካሄድ መሆኑ ተገለፀ።

## «ጣልቃ ገብነቱ አሁንም እንደተጠናከረ ነው!» አስተያየት ሰጪዎች

ባገባደድነው ሳምንት የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የመጅሊስን ምርጫ ለማካሄድ እንዲረዳኝ በሚል ለሁሉም ክልሎች እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ መስጂዶች ተመዝግበው እንዲላኩለት ፎርም በትኗል። ችግሩ ግን መመዝገቡ ሳይሆን መስጂዶች «የወሃቢያ» እና «ወሃቢያ ያልሆኑ» (በነሱ ቋንቋ «አህለ ሱና») ተብለው ተለይተው እንዲመዘገቡ መጠየቁ መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸዋል። ፎርሙ በእጃቸው እንደደረሰ የነገሩን የከፋል ምንጮቻችን የዚህ ሴራ ውጤቱ እጅግ የከፋ እንደሚሆን ስጋታቸውን ገልፀዋል።

በርካታ አስተያየት ሰጪዎቻችን እንደገለፁት ከሆነ «ህገ ወጡ መጅሊስ የሚያካሂደውን የመጅሊስ ምርጫ በማስተባበር ስም ፌደራል ጉዳዮች ጣልቃ በመግባት ሙስሊሙን ለሁለት በመሰንጠቅ «ወሃብያ» እና «ወሃብያ ያልሆኑ» በማለት ላልተፈለገ ቀውስ ሊጋብዙት እንደሚችሉና ይህሄዳል የተባለውን ምርጫም ለማጭበርበር መሳካት በሚያመቻቸው መስጂዶች ላይ ብቻ በማካሄድ ድራማ ሊሰሩ እንደሚችሉ» ይገመታል። «ፎርሙን የሚሞሉት በየእርከኑ ያሉ የመጅሊስ ጽ/ቤቶች ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህንን ዜና ለሁሉም ሙስሊም በማስተላለፍ ጉዳዩን በንቃት መከታተል ይገባናል» ሲሉም ጨምረው አሳስበዋል።



http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምጻችን ይሰማ

6

የተቃውሞ ድምጽ

ጁሙዓ መጋቢት 14፣ 2004– 11ኛ የተቃውሞ ሳምንት


# ዜና

## የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች አለም አቀፍ የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ መቋቋሙ ተገለፀ።

የኢትዮጲያውያን ሙስሊሞች አለም አቀፍ የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ መቋቋሙ የአወሊያውን ህዝብ ሙስሊም ተቃውሞ ትዕይንት ተከትሎ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከመላው ዓለም ተገኝተው በሚመከከሩበት መደበኛ የኢንተርፌዝ ስብሰባ ላይ ተገለፀ። መደበኛ ሳምንታዊ ስብሰባው ለ 4ኛ ጊዜ ሲካሄድ ከተለያዩ ሀገራት በርካታ ኢትዮጵያውያን ኡለማዎችና ምሁራን በወቅታዊው የሙስሊሞች ሁኔታ ላይ ገለፃ አድርገዋል። የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን፣ እንዲሁም የህዝበ ሙስሊሙን ጉዳዮች በመዘገብ ላይ የሚገኙ የሚዲያ ተቋማትም ኢፍትሃዊ የአዘጋገብ ስልት መጠቀማቸውን በመጥቀስ ጉባኤተኞቹ አውግዘዋል። ‹‹የመጅሊስ አካላት በህዝቡ የተተፋ ሆነው ሳለ መንግስት ይህንን የወደቀ አካል ለማንሳት እያደረገ ያለው ጥረት አሳዝኖናል›› ነበር ያሉት። በተጨማሪም በትግራይ ሙስሊሞች ላይ የሚደረገው ፀረ ኢስላማዊ ዘመቻ እንዲቆም ጠይቀዋል። በመላው ዓለም ያሉ ሙስሊሞች በሀገሪቱ እየደረሰ ያለውን በደል ከመታገል እንደማይመለሱም አስታውቀዋል።

የህግ ባለሙያው ዑስታዝ ካሚል ሸምሱ በስብሰባው ላይ ተገኝተው የኢትዮጵያውያን ትግል ከምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ያብራሩ ሲሆን ትግሉን በቀጣይነት በህጋዊ መንገድ ለማካሄድ የሚቻልበትን ህጋዊ አግባብም አብራርተዋል። በውጭ የሚኖሩ ሙስሊሞች በትግሉ ውስጥ እያደረጉ ላለው ተሳትፎም አመስግነዋል። በዚህ ስብሰባ ከዚህ በፊት የተዋቀሩትና በጋራ እንሰራለን ያሉ ከ34 ሀገራት በላይ የተውጣጡ ኮሚኒቲዎች አንድ አለም አቀፍ የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ማቋቋማቸውን አስታውቀዋል። በዚሁ ኮሚቴ ውስጥ ሶስት ቃል አቀባዮች መመረጣቸውንም ይፋ አድርገዋል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለውን የህዝበ ሙስሊሙን ሁኔታ አለም አቀፍ ሚዲያዎችን በመጠቀም ለአለም ህዝብ ለማድረስ እንደሚሰሩም መስማማታቸው ተገልፆዋል። የቃል አቀባዮቹ ምርጫ የተደረገበት ስብሰባ የተካሄደው ቀደም ብሎ ሲሆን ከ34 ሃገራት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ተሳትፈውበታል። አረብኛና እንግሊዘኛ መናገር መቻላቸው ላይ ተመስርተው ቃል አቀባዮቹን መምረጣቸውንም ይፋ አድርገዋል።

## የመጅሊሱ ተቃውሞ ከመዝሃብ ጋር ያልተገናኘ መሆኑ ተገለፀ።
## ‹‹በመጅሊስ ላይ ባለው ሂደት ውስጥ ወሃቢያ የሚባል ነገር የለም!››

ኡስታዝ አቡበክር አሕመድ (የኮሚቴው ሰብሳቢ)

የሙስሊሙን ማህበረሰብ የወከለዉ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኡስታዝ አቡበክር አህመድ የመጅሊሱ ተቃውሞ ሂደት ከመዝሃብ ጋር ያልተገናኘ መሆኑን ገለጹ። የሪፖርተር ጋዜጠኛ ጉዳዩን አስመልክቶ ለጠየቃቸው ጥያቄ ሲመልሱ «ወሃቢያ ስል ተቋማዊ ሆኖ ባለቤት ይዞ የመጣ አካል ካለ ያ አካል ነው ባለቤት ሆኖ የሚቀርበው፣ ሰኝ የሚል አካል ካለ ወሃቢያ ነኝ ብሎ ስለሚያምንበት ሴክት መግለጽና ማስረዳት ግድ ይለዋልም፣ ይገባዋልም› ብለን ነው የምናምነው። እዚህ ባለው ግን በአህባሽና በመጅሊስ ላይ ባለው ሒደት ውስጥ ወሃቢያ የሚባል ነገር የለም። ከሙስሊም ማኅበረሰብ ጋር እየተካሄደ ያለ ተቋምን ወይም መሠረታዊ እምነትን በተመለከተ እየተደረገ ያለ ፍጥጫ እንጂ ከሌላ ሴክት (የአምነት ክፍል) ጋር የተያያዘ አይደለም!» በማለት ተናግረዋል።

ይህንኑ በማስመልከት በፌስ ቡክ ላይ ለሰብሳቢው ድጋፋቸውን የገለፁ በርካታ ሙስሊሞችም «ይህ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የመብት ጥያቄ እንጂ የአክራሪዎች ወይም የወሃቢያ ጥያቄ አይደለም! ጥያቄዎቻችንን የተለያዩ ሰያሜ እያወጡ በመከፋፈል ሚድበስበስ ይቁምም! እኛ ሙስሊሞች ነን!» የሚሉ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል።

ወደ ገጽ 4 ተዛውሯል



## መጅሊስ ለመንግስት ህግና ስርዓት ተገዥ እንደማይሆን በይፋ አረጋገጠ!!!

ባሳለፍነው ቅዳሜ ጦር ሃይሎች በሚገኘው የመጅሊስ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ በሚገኘው መስጂድ ህገ ወጡ መጅሊስ ከየመስጂዱ ከመረጣቸው ኢማሞችና አንዳንድ ግለሰቦች ጋር ስብሰባ አካሄደ። በስብሰባው «ምርጫ የሚባል ነገር ሊኖኖርም። እናንተ ኢማሞች መስራት ያለባችሁን በየመስጂዶቻችሁ ባለመስራታችሁ ይህ ሁሉ መንጫጫት የተፈጠረው። እናንተ ከጎናችን ከሆናችሁ ምንም የሚመጣብን ነገር የለም» በማለት መጅሊስ የገለፀ ሲሆን ይህም መንግስት «የህዝበ ሙስሊሙን ጥያቄ ተቀብያለሁ፤ ምርጫ ይካሄዳል፤ ልዩነታችን በአተገባበር ሂደት ላይ ነው» በማለት ያስቀመጠውን አካሄድ የማይቀበለውና የማይተገብረው መሆኑን በተግባር አረጋግጧል።

ተሰብሳቢዎቹ በስብሰባው ማጠቃለያ 16 አባላት ያሉትና በአንዋር መስጂድ ኢማም የሚመራ ኮሚቴ አዋቅረዋል። የተዋቀረው ኮሚቴም የህዝበ ሙስሊሙ ወኪሎች በሄዱበት በመሄድ የትግላችንን ሂደት ለማኮላሸት እንደሚሰራ አስታውቋል። በአለቱ የተሰበሰበው ሰው በቀጣይ እያንዳንዱ ቢያንስ 20 ሰው ይዞ በመምጣት አጋርነቱን እንዲያሳይ የተጠየቀ ሲሆን «ቀጣይ ስብሰባችንን አወሊያ እናደርጋለን» በማለት ሲዝቱ እንደነበርም ስብሰባውን የተካፈሉ ምንጮቻችን ጠቁመዋል።

«ህዝበ ሙስሊሙ መጅሊስን ሊሸከምበት የሚችለው ሞራል ከመቼውም ጊዜ በላይ አልቋል!» ሲሉ አስተያየት የሰጡ ሙስሊሞችም ህዝቡ መጅሊስ በአፋጣኝ ሊወርድ የሚችልበትን መንገድ በዛሬው ጁምዓ ይወያያል ተብሎ መጠበቁን ገልጸዋል።

## በንፋስ ስልክ ሊካሄድ የነበረው የአህባሽ ቡድን የፕሮፓጋንዳ ሙከራ መክሸፉ ተገለፀ።
## በኑር መስጊድ ዋና ሰላትና በአንዋር ሁለተኛ ጀመዓ ሰላት ላይ የቁኑት ዱኣ ተጀምሯል!

በትናንትናው እለት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በሚገኝ አንድ መስጂድ ውስጥ በመጅሊስ ተደራጅተው እንደተላኩ የተጠረጠሩ ወጣት ሴቶችና ወንዶችን ያካተተ የአህባሽ ቡድን በወንዶችና በሴቶች መስጂድ መድረክ በሃይል ለመቆጣጠርና ሚይክራፎን በመጠቀም የአህባሽን ፕሮፖጋንዳ ለመርጨት መሞከሩ ከመስጂዱ ጀመዓዎች ተገለፀ። ሆኖም የመስጂዱ ኢማም እና አጠቃላይ ጀመዓው እንደከዚህ ቀደሙ ሰአህባሽ እጅ ላለመስጠት ባሳዩት ቆራጥ አቋም የበጥባጭ ቡድኑ አባላት ተልዕኮ ሊከሽፍ ችሏል። «ይህ መጅሊስ መራሹ የአህባሽ እንጃ ለፀረ ኢስላም ስበክው ይፋ መድረክ እና ታዳሚ በማጣቱ አቅጣጫውን ወደ ነውጥ በመቀየር በመስጂዶች ውስጥ ረብሻና ግጭት ወደ መቀስቀስ እስትራቴጂ መግባቱን አመላካች ነው» ሲሉ በርካቶች አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን መንግስት ይህን መሰሉን ስርዓት አልበኝነት በአፋጣኝ እንዲቆም የማስደረግ ግዴታ ያለበት መሆኑንም አሳስበዋል።

በሌላ ዜና በበርካታ መስጂዶች (መሳለሚያ ቢላል መስጂድ፣ ሚክሲኮ ተባረክ መስጂድ እና ሌሎችም) በሁሉም ፊርድ ሰላቶች የቁኑት ዱኣ እየተደረገ ሲሆን በተቃራኒው የታላቁ አንዋር መስጂድ ኢማም ግን «በሃገራችን ዝናብ እያጣን ያለነው እነዚህ ወሃብዮች በሚሰሩት ስራ ነው» ሲሉ ካለፈው ሃሙስ ጀምረው ተደጋጋሚ ዲስኩር በማሰማት ላይ ናቸው። አንዋር መስጊድ ውስጥ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በሁለተኛው ጀመዓ ላይ ቁኑት የተጀመረ ሲሆን የመጀመሪያውን ጀመዓ ስግደው የጨረሱ ሰዎች ሳይቀሩ ዙሪያውን «አሚን! አሚን!» እያሉ በአንድ ስሜት ዱኣውን እየተቀበሉ መቆየታቸው ታውቋል።

በታላቁ ኑር (በኒ) መስጂድ የቁኑት ዱኣ በሁሉም ፊርድ ሰላቶች የተጀመረ ሲሆን የመስጂዱ ዋና አስተዳዳሪ ኡስታዝ መንሱር ባስተላለፉት መልእክት «በአሁኑ ወቅት ሙስሊሙ ዱኣ ያስፈልገዋል። በጣም መእሲያና ዙልም በሙስሊሙ ላይ በዝቷል። መእሲያ ሲበዛ አላህ በተለያዩ ነገሮች ይቀጣናል። ዝናብም ሊከለክለን ይችላል። አሁን ያለንበት ወቅት ይህ ሁኔታ እየተስተዎለበት ይገኛል። ስለዚህ በመስጂዳችንም በኢማማችን አማካኝነት የቁኑት ዱኣ እንጀምራለን። ዱኣዉ ሲደረግ አሚን ማለት ብቻ ሳይሆን ከመጀመሪያዉ ጀምረን እርስ በእርስ አውፍ ልንባባል ይገባል» በማለት የቁኑት ዱኣውን መጀመር አብስረዋል።

የመስጂዱ ኢማም የሆኑት ታላቁ አሊም ሼህ ሙህመድ ሀሰን ፈድሉ በዘህር ሰላት የቁኑት ዱኣዉን ያስጀመሩ ሲሆን አላህ የሸረኖችን ሴራ እንዲያከሽፍ፣ ሴረኞችን በራሳቸዉ ህጃ እንዲጠመዱ እንዲያደርግ፣ ለዲናቸዉ እየታገሉ ያሉትን ወንድሞች እንዲረዳና የሙእሚኖችን ልብ አንድ እንዲያደርገው አላህን ተማጽነዋል።

በሸህ ሆጀሌ መስጂድ፣ በአወልያ፣ ሰላም መስጂድ፣ በቄራ ሰላም መስጂድ፣ በአየር ጤና አንሷር መስጂድና በተለያዩ በርካታ መስጂዶች ካሁን ቀደም የቁኑት ዱኣ መደረግ መጀመሩ የሚታወስ ነው።

ወደ ገጽ 3 ተዛውሯል



http://ethcriminalawnetwork.com/

# ዳምጣሮን ደብዳቤ

05-08-04

## 14ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ

**የአገራችንም ሙስሊም ሕብረተሠብ በአንድነት ከጫፍ እስከ ጫፍ ያነቃነቀው ሠለማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ዛሬ ጁምዓ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎችም ቀጥሎ እንደሚውል ይጠበቃል።**

የሳምንቱ ጉዞ

አዲስ አበባ፡- ባለፈው ጁምአ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ በርካታ መስጂዶች መጅሊስን እና አህባሽን በመቃወም ከፍተኛ የተቃውሞ ተክቢራ ከጁምአ ሰላት ቡሀላ አሰሙ። ባለፈዉ ሳምንት ጁምአ በተክቢራ ህዝበ ሙስሊሙ ተቃዉሞዉን ከገለፀባቸዉ መስጂዶች መካከል በመሀል አዲስ አበባ ፒያሳ በሚገኘዉ ታላቁ ኑር መስጂድ የተደረገዉ የተቃዉሞ ተክቢራ በጣም ድንቅና አስገራሚ እንደነበር በቦታዉ የተገኙ ምንጮች ገልፀዋል። ከኑር መስጂድ ቅጥር ግቢ ዉጪ የነበረዉ ህዝበ ሙስሊም በከፍተኛ ሁኔታ ተቃዉሞዉን በተክቢራ በአስፋልት መንገዱ ላይ ሲገልፅ የነበረ ሲሆን ከመስጂዱ ጎን በሚገኘው ህንፃ ላይ ሆኖ የአ.አ ፖሊስ የህዝቡን ሰላማዊ ተቃዉሞ በቪዲዮ ካሜራ ሲቀርፁ እንደነበር ምንጮች ገልፀዋል።በተመሳሳይ ዜናም በተመሳሳይ መልኩ በባዶሽ መስጂድ የነበረዉ የቲቃዉሞ ተክቢራ አካባቢዉን ድብልቅልቅ አርጎት እንደ ነበር በመስጂዱ የተገኙ ሙስሊሞች ገልፀዋል። ሰላማዊ በሚገኘዉ ቢላል መስጂድም ከሰላት ቡሀላ ሰለሙስሊም ወንድማማችነት የቀረበዉ ሙሀደራ የታደሚዉን ልብ የነካ ነበረ በመጨረሻ ሁሉም ሙስሊሙ እጅ ለእጅ በመያያዝ በአንድነት የመጅሊስን አመራሮች በተክቢራ መቃወሙን ከመስጂዱ የተገኙ ምንጮች ገልፀዋል። ይህንን ተቃዉሞ በሰላማዊ መንገድ በተክቢራ የመገሱዉ ሂደት ሰሶስተኛ ጊዜ በዛሬው ጁምአ በሁሉም መስጂዶች ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ይጠበቃል።

በቃሊቲ ቼሪያሲያ ከሚገኘው መስጂድ አካባቢ ሃምሳ የሚሆኑ ሙስሊም ወጣቶች ባለፈው ጁመዓ መጋቢት 28 ከጁምዓ በኋላ መታሰራቸው ተሠማ። ወጣቶቹ ለእስር የተዳረጉት "መጅሊስ ይውረድ" የሚል ቲሸርት በመልበሳቸው ምክንያት መሆኑ የተገለጠ ሲሆን ምክንያቱ በግልፅ ባልታወቀ ሁኔታም በቁጥጥር ስር ያዋላቸው የፖሊስ አካል ከታሳሪዎቹ ፊቃድ ውጭ እያስገደደ በካሜራ ቀረፃ ማካሄዱን ምንጮች አመላክተዋል።

በመጨረሻ ሱመያ መስጂድም ይህን የምታነቢትን ድምፃችን ይሰማ በትነሃል በማለት አንድ ልጅ የታሰረ መሆኖ ተገልጧል። ይህ ዘገባ እስተጠናቀረበት እስካሁኗ ሰዓት ድረስም በእስር ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።በአሁኑ ጊዜ ህዝበ ሙስሊሙ በየመስጂዱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በተክቢራ የመጅሊስ አመራሮችን እየተቃወመበት ያለዉን ሂደት ለማጨናገፍ የአዲስ አበባ መጅሊስ በስሩ ባሉት መሳጂዶች ላይ ይህንን ተቃዉሞ ያቀናጃሉ ብሎ ያሰባቸዉን ወጣቶች እና ሰዎች እንዲታሰሩ እና ክስ እንዲመሰረትባቸዉ እንቅስቃሴ መጀመሩ ተሰማ :: ይህንን ክስ የመመስረቱን እና የህግ ሂደቱን እንዲከታተሉ ሶስት የመጅሊስ አባላትን የሰየሙ ሲሆን እነሱም ሀጂ አባስ ኸማል, ሼህ ሲራጅ ኢድሪስ, እና አቶ ባርጊቾ ሁሴን መሆናቸዉንም ምንጮች ገልፀዋል:: እነዚህም ሰዎች ከጥበቃ ክፍል ጋር ስራ መጀመራቸዉንም ምንጮች ጨምረዉ ገልፀዋል:: ይገርማል እኮ ያልመረጥናቸው የመጅሊስ አመራሮች የማን አለብኝነትና የጥፋት ተልእኮ የሚያቆመው የት ላይ ነው? ስለምንስ የሚመለከተው አካል ሰምናሰማው ድምፅ ምላሽ ዘገየ?

እሁድ በአየር ጤና አንሷር መስጂድ በአይነቱ ልዩ የሆነ ታላቅ የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም ተካሄደ::በዚህ ፕሮግራም ላይ ታላላቅ አሊሞች፣ የመስጂድ ኢማሞች፣ የተለያዩ መስጂዶች የመስጂድ ኮሚቴዎች፣ ሙስሊም ባለሀብቶች፣ ታዋቂ ሙስሊም አርቲስቶች፣ የህዝበ ሙስሊሙ ተወካዮች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሙስሊም ምሁራኖች፣ ታዋቂ ዳሪያን የተለያዩ ሚዲያዎች እና ጋዜጠኞች ተነፍሰዉበታል:: በፕሮግራሙ ላይ ከ3500 እስከ 4000 የሚደርስ ሙስሊም ህብረተሰብ ተካፍሏል::በዝግጅቱ ላይ በርካታ ፕሮግራሞች የቀረቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል ኢስላማዊ መቻቻል ፣ የኢትዮጲያ ኡለሞች የነበረባቸው ሀላፊነት፣ በኢስላማዊ አንድነት ዙሪያ ጥሩ ትምህርት ለታዳሚው ቀርቧል::



በቦታው የተገኙ ታዋቂ ዓሊሞች በአሁኑ ጊዜ በግዴታ መልክ እየመጣ ያለው አዲሱአስተሳሰብ ከኢትዮጲያ አሊሞች አስተሳሰብ የተለየ መሆኑን፣ የአክራሪነት እና ፅንፈኝነት አደጋ በኢትዮጲያ ውስጥ በሚባለው ደረጃ እንደሌለና ፣ እንደዚ አይነት ችግር ቢኖርም እንኳ መፈታት ያለበት ሀገር ዉስጥ ባሉ አሊሞች እንጂ ከውጪ በሚመጡ ሰዎች መሆን እንደሌለበት እና በተለይ የሚዲያ ሰዎች ዉሸት ከመዘገብ አላህን ፈርተዉ እንዲቆጠቡ በማለት ግንዛቤ ሰጥተዋል። ፕሮግራሙ በመጅሊዱ ለተገኘዉ ህዝብ የለደቃ የምሳ ግብዣ በማድረግ በሰላም ተጠናቋል።

መጅሊስ በአዲስ አበባ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች ወረዳ እስከ ቀበሌ ባለው አደረጃጀት (የሱፍይ ስም ዝርዝር ፣ዕድሜ፣የት/ደረጃና የስራ መስክ) የያዘ ቅጽ እየበተነ ጉና በነዋሪው እንዲሞላ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ የከተማዋ ነዋሪዎች አመለከቱ። በህዝቡ የተመረጠው የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ደግሞ በህብረተሰቡ ተቀባይነት የሌለው ምርጫ ለማካሄድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሊቆሙ እንደሚገባ አሳስበዋል።በህብረተሰቡ ተቀባይነት የሌለውን መሰል እንቅስቃሴ ኮሚቴው እንደሚያወግዘው በመሆኑም መሰል እንቅስቃሴዎችን ለሚመለከተው የመንግስት አካል በማሳወቅ ፣ መሆኑንም አብራርተዋል። ህዝበ ሙስሊሙን ሱፊይ፣ውሃብያ እያሉ መከፋፈል ጊዜ ያለፈበት ,ው ስለሆነም መላው ህዝበ ሙስሊም የኢትዮጲያውያንን ሙስሊሞች ለመከፋፈል የሚደረገው ጥረት አካል የሆነውን ይህን ቅጽ እናወግዘዋለን።

በተመሳሳይ ዜናም የሙስሊሙን ጥያቄ አህባሽን የመቃወም እንዲልሆነ ለማሳየት እና ጥያቄዎቹን ለማጨናገፍ መጅሊስ አቶ አልሀሰን የቤኒሻንጉል ተወካይ፣ አቶ አለላ ወህቢ ወደ ወሎ ባቲ፣ አቶ ሀሚድ ደግሞ ወደ ሻሸመኔ በመላክ ከፈደራል ጉዳዮች ሚኒስተር መስሪያ ቤት ከተላኩ ሰዎች ጋር በመሆን ህዝቡን ለማሳመን ያደረጉት ጥረት አለመሳካቱን ምንጮች ገልፀዋል። እነዚህ የመጅሊስ ሰዎች እሱካሁን በተላኩበት ቦታ እንዳሉም ምንጮች ጨምረዉ ገልፀዋል።

ባሌ፡-የባሌ ሙስሊሞች ከመንግስት አካል ጋር አህባሽን በተመለከተ ባደረጉት ዉይይት ጠንካራ ተቃዉሞ አሰሙ። በውይይቱ ላይ ለመሆኑ በኦርተዶክስ እምነት ላይ ፕሮቴስታንት ወይም ካቶሊክ ሲመጣ ኦርቶዶክስ አማኞችን አዲስ የመጡትን አስተሳሰቦች በቤተ ክርስቲያናችሁ አስተምሩ እናንተም ኑና ተማሩ የሚል ጫና ተደርጎ አያዉቅም አሁን ለምንድ ነው እኛ ሙስሊሞች በሰላም እየኖርን ሳለን በእምነታችን ጣልቃ ገብቶ ኑ አዲሱን የአህባሽ እመነት ተቀበሉ አለበለዚያ አክራሪዎች ናችሁ የምንባለው።ያም ሆነ ይህ እኛ የባሌ ሙስሊሞች ለመጪው አስተሳሰብ እምነታችንን የማንለቅና የእምነት ተቋሞቻችንንም የማናስደፍር መሆናችን የሚመለከተው አካል ሁሉ ከወዲሁ እንዲያዉቅ እንሻለን በማለት አቋማቸውን ገልጸዋል።

ደሴ፡- በደሴ ከተማ በፍርቃን መስጂድ ከአስር ሺዎች የሚበልጡ የከተማዉ ሙስሊሞች ከፍተኛ የተቃዉሞ ሰልፍ አካሂደዋል።ይህ ተቃዉሞ በየሳምንቱ ጁምአ እንዲቀጥልም የከተማዉ ሙስሊሞች መስማማታቸዉን እና ዝግጁነታቸዉን መግለፃቸዉን ለማውቅ ተችሏል።

መቀሌ፡- የመጅሊስ አመራሮች በመቀሌ ከተማ አርስ በአርስ እየተተካኩ እንደሆነ ተገለፀ። በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ በሚገኘው የክልሉ የመጅሊስ ፅህፈት ቤት አስተዳደር የነበሩት ሼህ ከድር ለተሻለ ስልጣን በሚል ወደ አዲስ አበባ መቀየራቸውን ተከትሉ በስፍራው የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኛ ነበሩ ግለሰብ ስልጣኑን እንደተረከቡ ተገለፀ። ይህንንም ተከትሉ የአካባቢው ነዋሪዎች የአመራሮቹ የስልጣን መቀያየር እንደማይገርማቸው እና መቼም ቢሆን መጅሊስ እንደማይወክላቸው ገልፀዋል።የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉንም በሚል እየተንቀሳቀሰን ባለንበት ሰዓት የመጅሊስ አመራሮች የሚያደርጉት መተካካት ምንም ለውጥ አያመጣም ያሉት የክአካባቢው ነዋሪ ህብረተሰቡ የመረጣቸው ሽማግሌዎች እየተንቀሳቀሱ እንደሆነም ተናግረዋል።

አፋር፡- በአፋር ክልል በ4 ዞኖች ውስጥ በሚገኙ በርካታ ዉሰሞች በተደረገው ውይይት የአህባሽ አስተምህሮት ለህዝቡ እንደማይጠቅምና አላስፈላጊ እንደሆነ በመስማማት ተቃውሞአቸውን አሰሙ። የክክልሉን የመጅሊስ አመራሮች እና የመንግስት አካላት ያሳተፈው ይህ ጉባኤ በርካታ ሌሞች የተሳተፉበት እንደነበር በአብሰባው ላይ የተሳተፉት ዑለማዎች ገለፁ። የክልሉ መጅሊስ የአህባሽን አስተምህሮት እንደሚቃወምና ችግሩ ያለው የፌደራሉ መጅሊስ ላይ እንደሆነ ገልፀዋል።

ሀረርጌ፡-በምስራቅ ሀረርጌ ከሚገኙ 19 ወረዳዎች ውስጥ አንዷ በሆነችው በጭናቅሰን አካባቢ የወረዳው አስተዳዳሪ ሙስሊሙ ህብረተሰብ የአህባሽን መንገድ መከተል እንዳለበት መግለፃቸው ተጠቆመ። የጭናቅሰን ወረዳ አስተዳዳሪና የወረዳው የፀጥታ ዘርፍ ሃላፊ ህብረተሰቡ ውሃብያና አህሉልተውሂዶችን መዋጋት እንዳለበትና ሰምርጫና ለስልጠና ከ19ኙም ወረዳዎች ሦስት ሦስት ሰዎች መዘጋጀት እንዳለባቸው ገልፀዋል።የአካባቢው ሙስሊም ህብረተሰብ በበኩሉ የወረዳው አስተዳዳሪ በሀይማኖታችን ጣልቃ መግባት የምንከተለውን ሀይማኖት ሊመርጥልን አይገባም ትክክለኛውን የነብዩ(ሲ.ወ) መንገድ እየተከተልን ነዉ ማለታቸዉን ለማወቅ ተችሏል።



http://ethcriminalawnetwork.com/

## እነሆ አቤቱታችን ይደረስ

ሙስሊሞች ላይ የሚደርሰው አድልዎ ይቁም ህገ መንግስቱ ተጥሶ የምፈልግላችሁና የመረጥኩላችሁ እምነት ይህ ነው፣ ተቋማችሁንም እኔ በመረጥኩላችሁ ሰውና በመረጥኩላችሁ መንገድ ብቻ ነው የምታስተዳድሩት የሚል አካሄድ መንፀባቅ ጀምረዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በመጅሊስ እንዝህላልነት ዘርፈ ብዙ የሆኑ ችግሮች በሁሉም መልኩ ተጋርጠውብናል። በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ተሳትፎዎቻችን ላይ ግልፅ የሆኑ አደጋዎች ተደቅነውብናል። ተቋሞቻችንን የማስተዳደር መብት ከመነፈግ በተጨማሪ በሁሉም መስክ አገራዊ ተሳትፏችን የሚገደብበት ሁኔታ ማስተዋል ከጀመርን ሰነባብተናል።

በጥቅሉ በዚህ ዘመን ጭቆናው በታከተከና በብልሀት ታግዞ እና ከፍቶ ዳግም መተካቱን የሚያሳዩ ምልክቶችን ስናይ ቆይተናል።

ይህም ሆኖ ግን ላለፉት ሃያ ዓመታት አገሪቷ በዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ላይ ነች በሚል ግምት እና እምነት የሚደርሱብን በደሎች መቆሚያ ያገኛሉ የሚል ተስፋ ሰንቀን በትዕግስት እና እርጋታ ቆይተን ነበር። ሆኖም ተስፋችንን የሚያመነምን ነገሮች መከሰታቸውን የተረዳነው ላለፉት 10 ወራት ሲከናወኑ የነበሩ በአንዳንድ የመንግስት ኃላፊዎች የሚታገዝ የመጅሊስ ኢ ህገ-መንግስታዊና ህገ ወጥ ተግባሮችን ከተመለከትን በኋላ ነው።

በተለይም ‹‹ይሄን አንጃ ተከተሉ፣ እምነታችሁ ይህ ይሁን››የሚለው የመጨረሻ አይን ያወጣ ድፍረት ትዕግስታችንን ሁሉ አሟጦብናል። አላማው አስልምናን ከኢትዮጵያ ምድረ ገጽ ለማጥፋት ነው ብለን እስከናስብ ድረስ ስልታዊ እስልምናንና ሙስሊሞችን የማኮላሻ ተግባሮች ተመልክተናል። ይሄ ሁሉ ግፍና መከራ ከገጠር እስከ ከተማ የሚፈጸምብን ደግሞ ለህይማኖት ነጻነት እውቅና የሰጠው ህገ መንግስት፣ የሰብአዊ መብት እንዲሁም እንባ ጠባቂ ተቋማት በስራ ላይ እያሉ ነው።

ዛሬ ግን ይሄ ከቤት እስከ ከተማ፣ ከቀበሌ እስከ ትምህርት ቤት፣ ከመስጊድ እስከ አንዳንድ መስሪያ ቤቶች የዘለቀው ግፍና መከራ ‹‹ይብቃን›› ብለን ተነስተናል። ምንም መብታችን ቢነፈግም፣ምንም ያህል ህገ መንግስታዊ መብቶቻችን ቢጣሱም፣ ብሶታችን አንድ ህዝብ መሸከም ከሚችለው በላይ ቢገዝፍብንም ህገ መንግስታዊ መብቶቻችንን በህግ አግባብ እና በሰላማዊ መንገድ ከመጠየቅ ውጪ ሌላ አማራጭ አልተጠቀምንም።

ግን ደግሞ ይህን የተነፈግነውን መብታችንን መጠየቃችን ዛሬ አሸባሪ አስብሎናል። በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ መብት በጠየቅን በየሚዲያውና በአንዳንድ የመንግስት ባለሥልጣናት ጭምር ‹‹የሸሪአ ህግ ሊያውጁ፣ ሃማኖታቸውን በግድ ሌሎች ላይ ሊጭኑ፣ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ሊንዱ የሸመቁ ቡድኖች›› አስባለን። ታድያ የህጋዊነትና የሰላማዊነት ትርጉሙ ምንድን ነው? ያሻችሁን እምነት ስትጭኑበት ዝም ማለት?፣ የፈለጋችሁትን ጌታ ስትከምሩብን አሜን የሚል? የተመቻችሁን ጽዮናዊ አንጃ ስትግቱት በዝምታ የሚቀበል ነው ሰለማዊ ማለት?

አዲሱን የአህባሽ አስተምሮ በግድ አትጫኑብን፣ ተቋሞቻችንን ያልወከልናተው ሙበናኖች አይምሯቸው፣ እንዲሁም የመንግሥት ባለስልጣናት የሃይማኖት ተቋማችን ውስጥ እያከናወኑ ያለውን ያልተገባ ህገወጥ የጣልቃ ገብነት አካሄድ በመቃወም ህጋዊና ሰላማዊ ተቃውሟችንን በማሰማታችን፤ እኚሁ የመንግስት ባለስልጣናት በኢትዮጵያ ተጨባጭ የማይታሰበውን፣ ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች መሰረታዊ ጥያቄዎች ጋር ተጣጥሞ የማይሄደውን ሃገሪቱን በሸሪዓ የማስተዳደር፣ እምነትን በግድ የመጫንና ህገመንግስቱን የመናድ ውንጀላ በሙስሊሙ ላይ ለጥፏል። ውንጀላው ምንም እንኳ በጣም የከፋና የማይጠበቅ ቢሆንም ይሄን ተጠቅሞ የህዝብን ጥያቄ ለማኮላሸት መሞከርና ህዝበ ሙስሊሙን ከፋፍሎ ለዘለቄታው መብቱን እየነፈጉ መኖር የማይቻልበት ዘመን ላይ መድረሳችንን ግን ፈጽሞ ማንም ሊዘነጋው አይገባም።

ህዝበ ሙስሊሙም አሁን የከፈተውን አይኑን ዳግም ላይከድነው ለራሱና ለጌታው አላህ (ሱ.ወ) ቃል ገብቷል። አላህም የሚረዳው ዲኑን ለረዳ እና ላገዘ መሆኑን በቅዱስ ቃሉ ደጋግሞ ገልጿል።

ስለዚህ ‹‹ሙስሊሞች በኢትዮጵያ ምድር ኢስላማዊ መንግስት መመስረት ይፈልጋሉ›› የሚለው ውንጀላ ከመንደር ወሬነት የዘለለ የህሳብም የተግባርም ማረጋገጫ የለውም። የፈታችን ጁምዓ ሚያዚያ 12 ቀን 2004 በአወሊያ የምንሰባሰበው ልክ ከዛሬ 38 ዓመታት በፊት ሚያዚያ 12 ቀን 1966 ዓ/ል የተካሄደውን የወንድም እህቶቻችንን ጸረ ጭቆና ትግል ለማሰብም ጭምር ነው። በልዩ ሁኔታ የምናስታውሰውን ታሪካችንን የምናድስበትና ዳግም አንድነታችንን የምናፀናበት ልዩ ቀናችንም ነው።

ይህንን ቀን በልዩ ሁኔታ የምንዘከረው ቢሆንም፤ ለአሁኑ ትግላችን ቁርጠኝነትን፣ ጽናትን፣ ተስፈኝነትን፣ ወኔና እልህን ከምንም በላይ በአላህ ላይ ፍጹም መመካትን (ተወኩል) በውስጣችን በመሰነቅ ነው። ምክንያቱም አላህ ዲኑን ለረዱ፣ ላገዙ ሁሉ ብርታትና ድልን እንደሚሰጥ ቃል ገብቶልናል። ይሄን ደግሞ በተግባርም በአሳዛኙ ሕይወት ላይ አይተነዋል።

### የደሊል እና ደለለኛ ጨዋታ

ደለለኛ፡-አናንተ ብላችሁ ብላችሁ መንግሥትን ገልብጣችሁ የሸሪአ መንግሥት ልታቋቁሙ ነው አሉ?

ደሊል፡- ካሉ ልክ ናቸው!

ደለለኛ፡- ለመሆኑ መንግስትን በምንድነው የምትገለብጡት?

ደሊል፡- በካራቴ ነዋ!

ደለለኛ፡- ኧ በካራቴ! ደግሞ መንግሥት በካራቴ ይወድቃል እንዴ? ... ይሆ...ጎደኞች ናችሁ... ለመሆኑ በየትኛው የካራቴ ዘዴ ነው የምትገለብጡት?

ደሊል፡- በቴኳንዶ፣ በጁዶ፣ በውሹ፣ በካራቴ፣ በአይኪዶ፣ በኪክ ቦክስ

ደለለኛ፡- ኧረ በቃኝ በቃኝ ለመሆኑ ማነው አሰልጣኛችሁ?

ደሊል፡- ዶ/ር ሽፈራው ኃይለማርያም

ደለለኛ፡- ዶ/ር ሽፈራው አልከኝ!? ዶ/ር ሽፈራው ሲቀልድባችሁ ነው

ደሊል፡- የሚያውቁት እሳቸው ብቻ ናቸው ‹‹ካራቴ ያዋጣል››ያሉት እሳቸው ናቸው።

*የዘንድሮ ሚያዚያ 12 በዚህ ታሪካዊ በሆነው ታላቅ ቀን ሁላችንም ከቢተሰባቾን ጋር አወሊያ ይንገኙኝ።ለመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ ምእምናን ጋር በጋራ በመሆን ድምፃችንን እናሰማለን!!!*

ሊያንስ ለ15 ሳቃች ኮፒ ለቋርገው ያመተባበቃ!



http://ethcriminalawnetwork.com/

ሀይ ንቁ! መጅሊስ የምርጫ ቦርድ ለመጫወቻ ዝግጅቱን ጨርሶ የኔ ናቸው በሚላቸው መስጊዶች በሰላም ኮሚቴ ሰም አምስት . . . አምስት ሰዎችን መምረጥ ጀምሯል። ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የምርጫው ሂደት ከጅምሩ እስከ መጨረሻው ድረስ የይስሙላ ሳይሆን ፍፁም ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን አበክረን እንገልፃለን። ህገ ወጡ መጅሊስ ገለልተኛ አስመራጭን ሊመርጥልን አይገባም። በእጩ ተመራጮች ላይም አስተያየቱን እንዲሰጥ አንፈልግም። የመጅሊስ አመራሮች ምርጫውን ለማጭበርበር በየመስጊዱ እና በየቦታው እያሸረቡ ያለውን ሴራ መንግስት በፍጥነት እንዲያስቆምልን እንጠይቃለን።

የህዝቡን ድምፅ ማጭበርበር የወንጀሎች ሁሉ ቁንጮ ነውና ይህን የማያስቡ አካላት ከወዲሁ ጀምረው ከእኩይ ተግባራቸው እንዲታቀቡ እናሳስባለን። አላሁ አክበር . . . ድሮ በጓሮ በር አሁን ደግሞ በተጭበረበረ ምርጫ ስልጣን ለመያዝ እየታገሉ ያሉ የመጅሊስ አመራሮች ቦታውን እውቀት ላለው እና ህዝበ ሙስሊሙን አቻችሎ እና አንድ አድርጎ የመንግስትን ልማታዊ እንቅስቃሴ ላይ ሚደግፉ መሪ ቦታውን እንዲለቁልን እንጠይቃለን። አላሁ አክበር!

**ሚዲያ**

በመጅሊስ እና በደጋፊዎቻቸው ሆን ተብሎ የተዛባ መልእክት በማሰራጨት ህዝብን ለማሳሳት የሚሞክሩ ሚዲያዎች ህገ - ወጦችን ከመደገፉ ይልቅ የመላውን ህዝበ ሙስሊም ድምፅ እንዲያስተጋቡ እንጠይቃለን። አላሁ አክበር

አልሀምዱ ሊላህ! መጅሊስ እና ደጋፊዎቹ ህዝበ ሙስሊሙን ለማደናገር ያቀዱት የሚዲያ ኘሮግራም አልተሳካላቸውም። እንሽ አላህ . . . ወደ ፊትም በሚዲያዎች ለሚደረግ እንቅስቃሴ እኛ ሙስሊሞች እውነቱን በማወጣት በግንባር ቀደምነት መሳተፍ አለብን።

**አንድነት**

አንድነት . . . ነሽ ተምሳሌት የነፃነት።
ነናንተ የእስላም የቁርጥ ቀን ልጆች ሆይ
ነንድነት ኃይማኖታዊ ግዴታችን ነው።
አላህም እገዛ ከሀብረት ጋር ነው።
ላዚህ መብታችንን ለማስከበር
ንድነታችን ወሳኝ እና ወሳኝ ነው። አንድነታችንን መጅሊስም ሆነ ደጋፊዎቹ ሊሰነጥቁት አይችሉም። አላሁ አክበር
ቲ አንዴ ሁላችንም እጅ ለእጅ እንያያዝ? አሻፅብ ዩሪድ እስቃጠል መጅሊስ (3) ጊዜ . . . እንበል

**ፅቻል**

እስላም የመቻቻል ሀይማኖት ነው። ነገር ግን መጅሊስ እና ደጋፊዎቻቸው የኢትዮጵያን ሙስሊሞች ስቲያን ወገኖቻቸው ወደ ፊት ሰጋት እንደሚሆኑ ለማስረዳት ይውተረተራሉ። ህገ - መንግስቱን በሃይል ንደው ማዊ መንግስት ለመመስረት እየተንቀሳቀሱ ነው በማለት የሀሰት ክሳቸውን ፣የበሬ ወለደ ተረታቸውን ስራዬ በሚዲያ ይዘምራሉ። እኛ የኢትዮጵያውን መስሊሞች ግን መቸም ቢሆን ለክርስቲያን ወገኖቻችን ስጋት ንም። አላሁ አክበር . . . .

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ሃይማኖታችን፣ ቀለማችን፣ ዘራችን፣ ፆታችን እድሜያችን ቢለያይም ሀገራችን ግን ናት እሷም ለምለሚቱ ኢትዮጵያ። ስለዚህ ኢትዮጵያችን ትደግ . . . ትመንደግ . . . ኢትዮጵያችን ለፅገው እኛ እጅ እና ጓንት ሆነን ስንሰራ ነው እንጂ ሆን ተብሎ መስሊሙን እና ክርስትያኑን ሆድ እና ጀርባ ግ አይደለም። አላሁ አክበር . . .

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ድምፃችን ይሰማ! ተክቢር አላህ አክበር . . . አላሁ አክበር . . . አላሁ አክበር . . . በጓሮ በር የገቡ የመጅሊ አመራሮች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከወንበራቸው እንዲወርዱልን እና ኦዲትም እንዲደረጉልን እንጠይቃለን። አላሁ አክበር

1. ጥያቄያችን በሰላማዊ መንገድ የተጠየቀ ህገ መንግስታዊ የመብት ጥያቄ ስለሆነ ሳይሸራረፍ ሊመለስ ይገባዋል። አላሁ አክበር!
2. በሰላማዊ መንገድ የጠየቅናቸው የመብት ጥያቄዎች ላይድበሰበሱና ሌላ የፖለቲካ ትርጉም ሳይሰጣቸው መመለስ አለባቸው። አላሁ አክበር!
3. ጥያቄያችን ፍፁም ህይማኖታዊ ሆኖ እያለ አንድ አንድ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት እና ህገ ወጥ የመጅሊስ አመራሮች በአገሪቱ ላይ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ነው እያሉ፣ የበሬ ወለደ ተረት እየዘመሩ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰማምታታት እና ውዥንበር ውስጥ ለመክተት የሚያደርጉትን ጥረት በፅናት እናወግዛለን። አላሁ አክበር!
4. ለመሆኑ ይህን የመብት ጥያቄ እየጠየቀ ያለው ምን ያህል ሰው ነው? መላው የኢትዮጵያውን ሙስሊሞች አይደለም እንዴ? ነው። ስለዚህ የመጅሊስ አመራሮች እና አንድ አንድ የመንግስት ባለስልጣናት ይህን የህዝብ ጥያቄ በመናቅ ጥቂቶች፣ ፅንፈኞች፣ አክራሪዎች፣ አሸባሪዎች፣ ፀረ ዲሞክራሲዎች፣ ፀረ ልማቶች ፀረ ህገ - መንግስት እያሉ የሚያናፍሱትን ሐሰተኛ ወሬ አበክረን እንቃወማለን። አላሁ አክበር!

መጅሊስን ስንቃወም ዝም ብለን ሜዳ ላይ ተነስተን መልካቸው ስላላማረን አለባበሳቸው ስላልማረከን ሳይሆን የእስላም መሠረትን በግልፅ ሲሸራረፉ ቁርዓን የአላህ ቃል አይደለም ብለው ሲያስተምሩ፣ ደክመን ስለቸን ሳይሉ የእስላም እውነተኛ አስተማሪዎችን መብት ሲተሰትሉ እና ሲሸራረፉ በአይናችን በማየታችን ነው። ከዚህም ባሻገር በምርጫ ያልመጡ ህገ ወጥ አካላት በመሆናቸው ነው። ስለዚህ መጅሊሶች እኛ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን አይወክሉንም። አላሁ አክበር!

<u>አህባሽ</u>

እኛ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከእስልምና አስተምህሮት ያፈነገጠውን የአህባሽ ፍልስፍና በግድ አንቀበልም። ምክንያቱም እኛ እኮ ሙስሊም ነን ያውም የህበሻው . . . . የቢላላም ዘር ነን

ቢላል ለእስላም ሲል . . . . ተርቧል ተጠምቷል
እጅግ ተደብድቧል . . . . ስቃዩንም አይቷል
ሁሉን ነገር ትቶ አህድ . . . . አህድ ብሏል
ሽርክን አጣጥሏል . . . . ለመላኢው ትውልድ
በሃይማኖቱ ላይ . . . . ፅናት አስተምራል

ስለዚህ ጥያቄያችን በአግባቡ እስከሚመለስ ድረስ ሰላማዊ እና ታሪካዊ ትግላችን በፅናት ይቀጥላል። አህባሽን መቼም ቢሆን አንቀበልም አላሁ አክበር!

አህባሽ ከእስላም ሃይማኖት ውጭ መሆኑ ከ600 በላይ የአለም ታላላቅ ኡለማዎች ፈትዋ ሰጥተውበታል . . . ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች አህባሽን በግድ የምንቀበልበት ሞራሉም ሆነ ፍላጎት የለንም። አህባሾች ከእስላም ጋር የዓቂዳ (እምነት) ልዩነት ያለባቸው መሆኑን እየታወቀ በመጅሊስ አመካኝነት በህዝበ ሙስሊሙ ተቋማት ውስጥ የሚሰጡ የአህባሽ ስልጠናዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙልን እንጠይቃለን። አላሁ አክበር . . . . ብቸኛው ተቋማችን መጅሊስ፣ መስጊዶች እና መድረሳዎች የህዝበ ሙስሊሙ የእምነት ተቋማት እንጂ የአህባሽ የጥፋት ተልዕኮ ማስፋፍያ ቦታዎች ሊሆኑ አይገባም። አላሁ አክበር . . . .

12/11/2ወሣ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

# የኢትዮጵውያን መስሊሞች

## ኣጭር መልእክት (SAS)

1. ኣቐ ::ኢትዮጵውያን መስሊሞች ላክርስቲያን ወገኖችንን ሆነ ለህገ-መንግስታችንሲሊ መቸም ቢሆን ስጋት እንደማንሆን አበክሮን እንገልፃለን።
2. እንዲ ፀሀይ ብርሃን ጭንትው ያለው ጥያቄያችን ተባቢውን መልስ ባለማገኘቱ ስለማዊው ትግል ይቀጥላል። ምክንያቱም ይህን የፍትህ ጥያቄ አንዳንድ የመንግስት ጋዜጠች እንደሚያናፍሱት የቡድን ጥያቄ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያውያን መስሊሞች ጥያቄ ነው።
3. የታሪካዊው ትግል መጀመሪያ የሆነው አወሊያችን በተለየ መልኩ በኢስላም ልጆች ተክቢራ ደምቃ ለሁሉም የኢትዮጵያ መስገዶች ታበራለች
4. <u>የለህባሽን አንቫ እና የታሪክ</u> ሰለባውን መጅሊስ በመቃወም ሁሉም የኢትዮጵያ መስጅዶች ከጁምዓ ሰላት ቡኃላ ኢማሙ ልክ እንዳሰላመቱ በ33 (ሰላሳ ሶስት) ተክቢራ በህዝቡ መሪነት ይደምቃሉ. . .

ኣሏሁ አክበር!!

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ለጉለሾ ኪዳነ ምህረት "ሠላሳ ቦታ"

ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ግለሰቦች ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ ለመቃብርነት ከተመረጡት ቦታዎች ውስጥ አብዛኞቹ ከዚህ በፊት ለመቃብርነት ያገለግሉ የነበሩ ቦታዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ

=> ለወንጀለኛነት ማረጋገጫ ትክክለኛ መስፈርትን መወሰኑስ ለምን ጠቃሚ ነው? ለሚለው ጥያቄ መመለሻ ማብራሪያ ከዚህ በታች ተዘርዝሯል። (A)

=> ሁለቱ "ትክክለኛ መስፈርት" አንዱ ከሌላው የሚለይባቸው ዋነኛ ልዩነቶች ከንፁሀኑ ሰዎች ጥበቃ፣ ከወንጀል ምርመራ ሂደት ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲሁም ለወንጀል ቅጣት መሰረት በመሆን ረገድ ያላቸው ልዩነት ነው። (B)

(*) ትክክለኛ መስፈርት መወሰኑስ ለምን ጠቃሚ ነው?

(A) ∑ የትክክለኛ መስፈርት ለወንጀል ቅጣት መሰረት በመሆን ረገድ ያለው ጠቃሚነት፦

(*) - መሠረታዊ ሕገመንግስታዊ መብት ይዘቱ መንግስት ሊጥሰው የማይገባ ወሰን ነው፤

- ይህን መብት ለማስከበር የሚደረገው ማንኛውም ጥረት ከሕገመንግስቱ መነሻ ሊያደርግ ይገባል፤

- ተከሳሽ ወንጀል ተገኝ መሆኑ ከታወቀ በኋላ ሊቀጣ የሚገባው ከሕገመንግስቱ መሰረታዊ መብቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ ሊሆን ይገባል፤

- መንግስት የአመለካከት ወንጀልን ለመከላከል ሲል ከሚያደርገው ጥረት ጋር በተያያዘ ከሕገመንግስቱ ጋር ሊጣጣም ይገባል --- ወዘተ

(B) ይህን የተመለከተ ትክክለኛ መስፈርትን መወሰኑስ

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ገጽ ፲፭

ቁጥር ፲፭፻፲፭

⇨ ከሰንቻዊ መለኪያ ከሆነ ሁለት ሆሄ የመጠቀም ሚከለክል ደንብ መኖሩን ማመልከት።

تطبيق التشريع:- * መለኪያ የሆነው ሁለት ሆሄ

(*) → የሰነዱ ወይም ማስረጃው መጠሪያ ስም ገቢ የሚደረግ መሆኑ መመርመር። (ፍሬውን ለተማሪው ካለ ከመቀጣቱ በፊት)

(*) → የሰነዱ(ማስረጃው) ትክክለኛ መሆኑን (ፍሬው) መመርመር (ፖለቲካዊ) ለውጥ ያመጣ ከሆነ ደንበኛውን መጠየቅ።

→ መጠየቁም ካላቸው ሰነዶች ውስጥ ያስፈለጉትን መለየት ያስፈልጋል።

(*) [ ለሻፍሁ የሰነዱ ያላቸው የሚያስመስክር መጠየቃቸው መመርመር ]

---- ይህ ሁለት ፍርዳ ያለ ደንበኛውን መጠየቅ።

---- የተቀባው ሁለት የጋራ ደንበኛውን መጠየቅ መቀጣ የሚያስመሰክሩ ሰነዶች የዚህ ሁለት ሰነዶች ደንበኛውን መጠየቅ።

---- ይህ ሁለት ግለሰብ ደንበኛውን መሠረተ ሀሳብ ማግኘት የሚፈቅድ ከሆነ ከሆነ ለማረጋገጥ ሌላ ሰነድ ማቅረብ ያስፈልጋል።

* ይህንን ሁለት ሰነዶች ለማሠረዝ የሚያስችሉ ሠነዶችን ቅርብ ሆኖ ያለ ሰነድ ለማሠረዝ ደንበኛውን ለማረጋገጥ ሰነዶችን ማስመሰል ሲሆን ይህም ይኖርበታል።

ካንቺ ሰነድ ያተገ
ሳስመሰሩ ሚሳው
12-12-04

ከዋናው ጋር ተመሳክሮል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ቃለ-መጠየቅ

ክስ

1 ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ቴአትር
2 ጫጫታ ሰላም ⊗ ዘ ዓ

ለመገበ ⇒ ሸለገሰ

ጌድመጠ ⇒ ጎንጨ

ለመሐ ⇒ ረገጨ

መጠ ⇒ ተንኮለ፡ መንጫጨ

ቆለታ ⇒ ሸመቀቀ፡ ቀለቃቸ

ገደለ ⇒ ተወያይተሐል ገና፡ ደረሰ

መቻቻል ⇒ ሰላመትም፡ መጀረጨ

የምትወንጀሉ፡ ወንጀ ⇒ ቃሚዎች፡ ሸመቀቀ

የምትወንጀሉ ሰዎች ⇒ ጎረቤ፡ ከሳሽ

ሀሳብመሰጠ ማረጋገጫ ⇒ ምስጢ፡ ሸገገሰ.

09-13-42-28-47

⊗ መጫወቻ

መወለቢያ፡ ተከሳሽ፡ ጌድመጠ ገመ ሸለገሰ ቆለታ ይመቸ፡ ከጠቀታ.

3:00 - 6:00 ሰዓት ይመቸ. ከከሰሰ፡ መጨቃጨቅ አለበት.

ECLN

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process 3

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሚሳሀሎት ጋር ሠላሜ

NT03

ይሚሳሀሎት ጉዳዮችን በመሥራት።

መጅሊስን የተቃወመው ጥቂት የህብረተሰብ ክፍል ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ፣ኡለማዎች ፣ዳኛዎች፣ መስለም ሙራዎችና ተማሪዎች ፣ የዕድሜ ባለፀጋዎች፣ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መሆናቸውን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይወቅልኝ እያልን ሃሳባችንን እናሰማለን።

## መጅሊስን ስንቃወም

እኛ ኢትዮጵያዊያን መስለሞች መጅሊስን ስንቃወም ስሜታችንን ተከትለን ስውር የፖለቲካ አጀንዳ አንግበን የሰለጠነ ጥሞት ዋሮችን ወይም ዓለማዊ ጥቅም አንጉተን ሳይሆን የአስልምና ትእዛዛት ታሽጎ ሲቀር ወለኑ ሲጣስ ደባ ሲሸረብበት በዓይናችን በማየታችንና በጆሮአችን በመስማታችን ምክንያት መሆኑን አበክረን ለማስገንዘብ እንወዳለን።

አህባሽን የምንቃወመው ከአስልምና ጋይሚኖት ያፈነገጠ በፈተናው ሼህ /በአብዱላህ አል ሃረሪ/ የተፈለሰፈና በአይሁዶች የተቀነባበረ ድጋፍ የሚረዳ አስልምናና ሙስሊሞችን ለማዳከም በመንግስት አንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሙሉ ድጋፍ ሰጪነት ህገ መንግስታዊ መብታችንን በኃይል በመደፍጠጥ ብሎም የህገ መንግስት አንቀፆችን በመጣረር በግድ የአህባሽን ፍልስፍና ተቀበሉ በመባላችን ነው።

## አህባሽ/የፈተናው ሼህ/ ስሚያራምዳቸው ፍልስፍናዎች በጥቂቱ

1ኛ. ቁርዓን የአላህ ቃል አይደለም ማለቱ።
2ኛ. ሲሃቦችን/የነብዩ ሙሐመድ /ሰ.ዓ.ወ./ ባልደረቦችን ቡተናጠል ትችት /ወቀሳ/ ቢሰነዘርባቸው ችግር የለውም ማለቱ።
3ኛ. ሙስና/ጉቦ/መቀበልም ሆነ መስጠት መፍቀዱ
4ኛ. ታላላቅ የኢስላም ሊቃውንቶችን በከሃዲነት መፈረጁ እና ወዘተ ...

ለመሆኑ አንዳንድ ባለስልጣናት የህገ-መ ሚዲያዎችን በመጠቀም በመላው አገሪቱ ያሉ ሙስሊሞች እየጠየቁ ያሉትን ጥያቄ ወደ ፖለቲካ አጀንዳ በመጠምዘዝ ህገ-መ ያልጠየቀውንና የመጠየት ዓላማው ያልሆነውን ከሸሪዓ ህግ አንተዳደር አስላማዊ መንግስት እንመስርት የሚሉትን የኃይማኖት ግጭት በመፍጠር ሀገሪቱ ወደ ከፋ ብጥብጥ ሊከታት ነው እያሉ የሚያስተላልፉት መልዕክት ከአንድ ህዝብን ከሚመራ አካል የማይጠበቅና የበሬ ወለድ ተረት ተረት መሆኑን መላው የአገሪቱ ማህበረሰብ ጠንቅቆ አንደሚያውቅ አለማወቃቸው በጣም ያስገርማል።

## ምርጫ

የመጅሊስ አመራሮች ምርጫ በጊዜ ገደብም ሆነ በድንገት ይደረግ ሊባል ይችላል። ነገርግን በመላው ሀገሪቷ የሚገኙ ሙስሊሞች በንቃት በመከታተል ምርጫው አንዳይጭበረበር የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብናል።ለዚህም ሊመሩን የሚችሉ ብቁ ኪ.ሉቻችንን ከወዲሁ በየአካባቢያችን በጥንቃቄ በመመልመል ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

በመሆኑም የረጋ ውሳኔ ቅቤ ይወጣዋልና በየመስጂዳችን በተከበረና ያልመረጥናቸው የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉንም፣ የአህባሽ አስተምርን አንቀበልም የሚሉ መፈክሮችን በማሰማት ሰላማዊ ትግላችን

ሰላማዊ መሆኑን ያረጋግጣል።

ኢንሻአላህ
አላሁ አክበር!

ካፒ አደርገው ያለተካፈሉ

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

65398

3ፎርም ሽጠት = 32000
150 ኪሎ ስንዴ 2000
2000 ፎርም ኤንቬሎፕ = 5000
30 ሰዓት ዝግጅት = 745
ጠበቃ እሸቴ ደሳለኝ = 1000
አቃቢ ህግ ምስክር = 300
ለአስተርጓሚ = 300
ለአስተርጓሚ ትራንስፖርት 600
ለአስተርጓሚ ቀለብ 30
ለአስተርጓሚ 60 ሰዓት 720
ትራንስፖርት ተመላሽ = 1030
ትራንስፖርት አስተዳደር = 270
ሽልማት ሲሳይ = 200
ለደንበኛ የተለያዩ ቅጂዎች = 860
አስተዳደር የተለያዩ ወጪ = 327
መሰናዶ ቁጥር የተሠጠበት = 1200
8 ፎርም ጠቅላ = 5500
ትራንስፖርት የተከፈለበት = 500
ጠቅላላ ወጪ = 5000 + 1200

ዝግጅት 2000 + 150 ኮፒ = 2150
አቃቢ ህግ = 1600
ትራንስፖርት = 2020
ለአስተርጓሚ ቀለብ = 300
ለአስተርጓሚ ትራንስፖርት = 300
ዝግጅት ተመላሽ = 300
ወጭ ያልሆነ ወጪ = 100
ለደንበኛ ሂሳብ = 864

ለ 250 ፎርም = 300

Hoyt ተመላሽ 110 ሰዓት = 235
ለ 250 ፎርም = 300

ECHN

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምፃችን ይሰማ ቁ.12

## 21ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ

24-09-2004 E.C

### የአንድነት መዝሙር!

አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!
1. አንድ ነን እኛ ማንነጣጠል በዲናችን
አንድ ነን እኛ ማንም አይለየን በምነታችን
የማይሻረው የአላህ ቃል ነው መመሪያችን
ታላቁ ነብይ የህይወት መንገድ ምሳሌያችን
ታላቁ ነብይ የህይወት መንገድ ምሳሌያችን
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!

2. አገር ወዳድ ነን ለሰላም የቆምን የፍትህ ዘቦች
አገር ወዳድ ነን ለሰላም የቆምን የፍትህ ዘቦች
ለእድገት ለልማት ጸንተን የምንኖር ታጋይ አርበኞች
ፍቅር አርማችን ሁሉን የምንወድ የሰላም ዜጎች
ፍቅር አርማችን ሁሉን የምንወድ የሰላም ምንጮች
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!

3. ኩፍርና ኒፋቅ ቢጋራ ሆነው ቢተባበሩ
ኩፍርና ኒፋቅ እኛን ለማጥመም ቀን ሌት ቢጥሩ
ወደጅህልና ህዝቡን ለመከተት ቢፍጨረጨሩ
መስሊሙ ነቅቷል ሁሉም አንድ ሆኗል ይኸው አፈሩ

አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!

4. የነጃሽ ልጆች የቢላል ዘሮች ያበሾች ኩራት
ምሳሌነቱ ለአለም ፍትህ የሆነው ብስራት
እጅ ለጅ ሆነን ፍትህ ፍሊጋ ቆመን በጽናት
እጅ ለጅ ሆነን ፍትህ ፍሊጋ ቆመን በጽናት
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!
አላህ---- አላው አከበር! አላው አከበር! አላው አከበር!

አንድ ነን እኛ ማንነጣጠል በዲናችን
አንድ ነን እኛ ማንም አይለየን በምነታችን
የማይሻረው የአላህ ቃል ነው መመሪያችን
ታላቁ ነብይ የህይወት መንገድ ምሳሌያችን
ታላቁ ነብይ የህይወት መንገድ ምሳሌያችን

5. የተሳሰረው በኢማን መንገድ በጥንካሬ
የተሳሰረው በኢስላም መንገድ በጥንካሬ
ላይነጣጠል ባንድነት ቆማዕል ቃል ንቢቷል
ዛሬ
መስሊሙ ብሏል ኢስላም ህይወቴ ኢስላም
ነው ክብሬ!
መስሊሙ ብሏል ኢስላም ህይወቴ ኢስላም
ነው ክብሬ!

**ሁላችንም ይህንን መዝሙር በመሸምደድ አወሊያና በሌሎች መስጂዶችም በምናደርጋቸው ተቃውሞ በአንድነት እንዘምራለን!**

ላለፉት ዓመታት በመልም አስተዳደር እጦት ኢ-ኢስላማዊ የሆኑ ፈታኝ ግፍና በደሎችን ሲያስተናግድ የቆየው መስሊም ማህበረሰብ እልህ አስጨራሹን የትእግስት ገመድ የበጠሰው እና ወደ ጎላ የማይል ሰላማዊ ህዝባዊ ተቃውሞ የከተተው ግን የአህባሽን አስተሳሰብ መጅሊስ የራሱ መሪ አቋም አድርጎ የመላው ኢትዮጵያ መስሊም አቋም እንዲሆን በግድ ለማጥመቅ በመንቀሳቀሱና በከባድ መሉአትነት የተገኙትን መስጂዶቻችንንና መድረሳዎቻችንን ጨምሮ አጠቃላይ ኢስላማዊ ተቋማት በዚሁ በኸይ አስተሳሰብ ስርአት ስር እንዲወደቁ ማድረጉን ተከትሎ ነበር።

በዚህ መልኩ ዛሬ ላይ የደረሰው ሰላማዊ ተቃውሞ መነሻው የአህባሽ አስተሳሰብ የግድ ጠመቃ እንቅስቃሴ ቢሆንም ለዚህ ሁሉ መንስኤው ደግሞ የመጅሊስ አመራር ከኢስላማዊው አስተምህሮና ስነ-ምግባር ውጪ እና ፍፁም ኢ-ዲሞክራሲያዊ በሆነ ህገ-ወጥ አሰራር ቢታው በማይገባቸውና በማይመጥኑት አመራሮች በመወረሩ ነው።

ከሰልጣናቸው እንዲወርዱና ለዚሁ ህገ ወጥ መተካካት ይጠቀሙበት የነበረውን ብልሹ የአሰራር ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ተበጣጥሶ አግባብ በሆነ መልኩ ይስተካከልልኛ፤ የግዴታ የአህባሽ አስተሳሰብ ማስረፅ ስልጠና ቆሞ ይህ አስተሳሰብ ለዘመናት በመስሊሙ መሉአትነት የተገኙትን መስጂዶቻቸውን፣ መድረሳዎቻቸውን እና አጠቃላይ ኢስላማዊ ተቋማት ላይ እጁን ያነሳልን፤ የአወሊያ ተቋም የህዝበ መስሊሙ አንጡራ ሃብት ነውና በህዝበ መስሊሙ በተመረጡ የቦርድ አመራሮች ይተዳደር በማለት ነበር አቤቱታውን ለመንግስት ያቀረበው። ይህ ሆኖ ሳለ ግን ዛሬም ላይ

1ኛ. የግዴታ የአህባሽ ስልጠና እንደውም በፈደራል ጉዳዮች መሪነት እየተከነወነ ይገኛል።

2ኛ. ሰልጣኞቹም በብዙ ቦታ በመንግስት አስገዳጅነት የነበ በመሆኑ የእምነት ነፃነታቸው መብት ቢገፈፍም አብዛኞቹ አስተሳሰቡን በግልፅ እንደሚቃወሙትና ከወጡም በኋላ ያለውን ሴራ ለህዝቡ አያጋለጡ ይገኛል። ስለዚህ ከህገ-ወጡ መጅሊስ አልፎ በመንግስት ጣልቃ ገብነት የአህባሽን አስተምህሮ ማስፋፋት አውንም ፍፁም ህገ ወጥ ተግባር መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

### ምርጫ መሰል የቅርጫ እንቅስቃሴ

የህዝበ መስሊሙ ሰላማዊ ተቃውሞ መሰረት ፍትህን ፍሊጋ እንጂ ፍትሃዊነትን የሰማይና ምድር ያህል ርቀት ባለው ማደናገሪያ ውሸንብሮች ደልሎኝ አይደለም። ይህ ሊታወቅ ይገባዋል። ለዚህም አሳማኝ ምክኒያቶች አሉ።

አይደለም ለሰላሳ ምናምን ሚሊዮን የሚቆጠር ማህበረሰብ መንፈሳዊ መሪ ለመምረጥ ይቅርና የአድር መሪ እቅክ ለመምርጥ ዝግጅት ተደርጎ፣ ለአባላቱ በቂ ግዜ ተሰጥቶ፣ ዝርዝር የምርጫ አፈፃፀም ስርዓቱ በአባላቱ ፀድቆና ሁሉም የሚያምንበት ግልፅ የምረጫ አካሄድ ተዘጋጅቶ ነው የሚመረጠው። ይሁንና መላው የኢትዮጵያ መስሊም የጭንቅ ያለህ! እምነቴን በነፃነት ልተግብር!! መሪዎቼን በእምነት ተቋሜ በነፃነት ልምረጥ!! ምርጫውን ለማካሄድበት የሚደረጉ ሩጫዎች ይቁሙ!! የምርጫ ቀን ከወዲሁ ለምርጫ ዝግጅት እንዲረዳ ምርጫው ከሚከናወንበት በርከት ያሉ ቀናት በፊት ለህዝብ በመገናኛ ብዙሃን ይፋ ይደረግ!! የምርጫው ቀን ሊደርስ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት ምርጫውን ይፋ በማድረግ ህዝቡ ስለምርጫው እንዳይወያይ ፋታ በመንሳት በአጭር ግዜ ውስጥ እንደነገሩ በሆነ ምርጫ የፈለግነውን እናስመርጣለን በማለት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በአፋጣኝ ይቁሙ!! የህዝብ ከወከባና ማጅበርበር የፀዳና በሰላማዊ መንገድ የእምነት መሪዉን የመምረጥ መብት ይከበር!! መጅሊሶች ወርደዋል የሚል ወሬ በማናፈስ በተጨባጭ ግን በምርጫው ዙሪያ መጅሊሶችን ተጠቅሞ ህገ-ወጥ ምልመላና ምርጫ የማካሄድ እንቅስቃሴ ይቁም!! እያለ ህገ-መንግስት ባለበት ህዝ ለሃያ አንድ ሳምንታት በዚህ መልኩ አሉሉ ..... የጭንቅ ያለ እያለ የሚጮህበት ለምን ድምፁ አልተሰማም? ድምፁን ላለመስማት ለምን ተፈለገ? ከህገ-ወጡ የመጅሊስ አመራሮች ጋር አጅና ጓንት ሆኖ እየተሰራ ግልፅ በሆነ መድረክ በመቶ ሺዎች የተመረጡትን የህዝብ ተወካይ ኮሚቴዎቻችንን ለማወያየት ለምን አልተፈለገም? ይህ ሁሉ ያልሆነበት ምክኒያት ለምንድን ነው? የተለየ ዓላማ ከሌለ እነኚህ ሁሉ ጥያቄዎች ግልፅ ምላሽ ያሻቸዋል። ምርጫው አካባቢያዊ ሳይሆን አገራዊ እንድምታ ያለው በመሆኑ ወጥነት ያለው ግልፅ የምርጫ ሥርዓት ወጥቶለት የሚከናወን እንጂ በዘፈቀደ እንደየ ባለሰልጣናቱ ፍላጎትና አስተያየት ሊሆን አይገባውም።

ዝርዝር የምርጫ ሥርዓትና አፈፃፀም መዘጋጀት የሚገባው የህዝበ መስሊሙ ተሳትፎ ታክሎበትና ቀድሞ በመጅሊስ አመራሮች የተዘጋጀው የምርጫ ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ መነሰረዝ እንዳለበት ታምኖ ወደ ሥራ ውስጥ ሊገባ ያስፈልጋል ። ምንም እንኳን ይፋ በሆነ መልኩ ከሚከተለው አካል ባይገለፅም፤ የመጅሊስ አመራሮች መውረድና ምርጫ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነ በየ አካባቢያችን ያሉ የጉበር ይወጣ ጥድፊያና ወከባዎች እያተስተዋሉ ነው ። መስሊሙ ህብረተሰብ ቢያፋ እየገለፀ ያለውም ወደ ፊትም የሚፈለገው የዚህን የህዝበ ሙስሊም ሰላማዊ ተቃውሞ እና ጥያቄ መፍትሔ እንዲያፈላልጉ የተወካሉ አካላትን መንግሥት አቅርቦ እንዲያነጋግራቸውና አያሰለፈ ያለውን ውሳኔ በግልፅ በነሱ በኩል ሊያስተላልፍ ነውና ይህ ሊሆን ይገባል እንላለን ። ለየአካባቢው የሚደረገው የምርጫ/ ቅርጫ እንቅስቃሴ መንግስት እጁን እንዲያወጣና ሕዝቡ በጠየቀው አግባብ ገለልተኛ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተዋቅሮ ዝርዝር ሕደቱን ሊያስኪደው ይገባል ። ከዚህ ቀደም እንደሚደረገው የትኛውም መሰል እንቅስቃሴዎች ሊፋዊ የሆነ መግለጫ አስካልተሰጠበትና የህዝበ መስሊሙ ወኪል በሆኑት ኮሚቴዎች በኩል አስካልተላለፈ ድረስ ተቀባይነት እንደማይኖረው ማረጋገጥ ይገባናል ።



http://etherimihalawinetwork.com/

. በወረባቦ አካባቢ የተካሄደውን የሰደቃና የአንድነት ፕሮግራም ተከትሎው ወደ ሐይቅ በመመለስ ላይ እያሉ መንገድ ላይ የፌዴራል ፖሊሶች ህዝብ የተሳፈረበትን መኪና በማስቆምና ፍተሻ በማካሄድ ከተሳፋሪው መሀከል የነበሩትን ዳዒ ሙሐመድ ፊረጅንና የደጋኑን ሸኹ- ሸኽ ኢድሪስን ለይተው በማስወረድ ለማሰር ሙከራ ሲያደርጉ የተመለከተው ህዝብ ድርጊቱን በመቃወም ካሰራችሁ እኒሱን ብቻ ለይታችሁ ሳይሆን ሁላችንም በአንድ ላይ ወደ ፖሊስ ጣቢያው እንሄዳለን እነሱን በፍፁም ከኛ ነጥላችሁ ልትወስዷቸው አንፈቅድላችሁም በማለት የከረረ ውይይት ተፈጠረ። ይህን ጉዳይ የነመ ፕሮግራሙን የተከፈሉ የወረባቡ አካባቢ ምእመናን ወዲያውኑ ወደ ሃይቅ የመጡ ሲሆን አጠቃላይ ቁጥሩ ከሁለት ሺህ የሚልቅ ምእመናን በቦታው ላይ እስከ ምሽቱ 3፡00 ድረስ በፖሊስ ተከቦ ቆይቶ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ሳቢያ ዳዒዎቹና ሼኹ ተለቀው በጀመሳው እጀባ ደሴ ድረስ ተሸኝተዋል። ይሁንና መሃመድ ፊረጅን ጨምሮ ከአዲስ አበባ የሄዱ ብዙ ዳዒዎችን ለመያዝ ከደሴ እስከ አዲስ አበባ ድረስ በመኪና እያሳደዱና በየከተማው ኬላ ላይ እያሰሱ ከፍተኛ ከትትል ቢያደርጉም በአላህ ፈቃድ እነርሱን ሳያገኟቸው ዳዒዎቹ በሰላም አዲስ አበባ ገብተዋል።
. በሀላባ ቁሊቶ ለሶስት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም እንደሚዘጋጅ ተገለጸ። ዛሬ ጁምዓ የሚጀመረው የሀላባ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም አላማ ኢስላም ሰላም እንደሆነ ማሳየት እንደሆነ ምንጮቻችን ጠቁመዋል። በዝግጅቱም ላይ ታዋቂ ዳዒዎችና ከ10ሺ በላይ የሚሆን ህዝብ ይሳተፋል ተብሎ እንደሚጠበቅ አብራርተዋል።
በአንድነትና በሰደቃ ፕሮግራሙ ላይ ከመስሊሙ ህብረተሰብ ባሻገር የሌሎች እምነት ተከታዮች እንደተጋበዙ ጠቁመዋል።
. የደህንነት አካላት ሳይሆኑ እንዳልቀረ የተገመቱ ሰዎች የአወልያን የጥበቃ ሰራተኞችን በመሰብሰብ ሐምሌ 8 (ስምንት) የመስጂዱን በር በመዝጋት ማንንም ሰዉ እንዳያስገቡ ቀጭን ትዕዛዝ አስተላልፈዉ መሄዳቸዉ ተሰማ። ይህ ትዕዛዝ ፕሮግራሙን ለማደናቀፍ መንግስት እያቤረዉ ከሚገኘዉ ሴራ አንደኛዉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።
በተያያዘ ዜና ረቡእ እለት ከአሰር ሰላት ቡኋላ የኮልፌ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ሀላፊ ከማንደር ልኡል፣ የኮልፌ ክ/ከተማ የፍትህና ፀጥታ ቢሮ ሀላፊና የኮልፌ ክ/ከተማ አስተዳደር ከአወልያ መስጂድ ኮሚቴና ከአወልያ አስተዳደር ጋር ሰብሰባ ማካሄዳቸዉ ተሰማ። በስብሰባዉም የአወልያ የመስጂድ ኮሚቴ የፈታችን እሁድ ሐምሌ 8 የሚካሄደዉን ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራሙን እንዲያስቆሙ በመንግስት በኩል መጠየቃቸዉ ነዉ የተገለፀዉ። የመስጂዱ ኮሚቴም እኛ ይህንን ማስቆም አንችልም። ይህ ፕሮግራም የግለሰቦች ሳይሆን የህዝቡ ነዉ። ፕሮግራሙ ፍፁም ሰላማዊ ነዉ። ከሌሎች መስጂዶች የተለየ ነገር አይደረግም። [redacted]ለየዉ በሁሉም መስጂዶች ይካሄድ የነበረዉ በአንድነት አንድ ቦታ መሰባሰብ ብቻ ነዉ በማለት ፕሮግራሙን ማስቆም እንደማይችሉ ገልፀዎል። የመንግስት አካላትም ፈታቸዉን ወደ አወልያ አስተዳደር በማዞር ለአወልያ መስጂድ ኮሚቴ ፕሮግራሙን እንዲያግድ ደብዳቤ ፃፍ። ለኛም ደብዳቤ ፖፍልን። ለመረጃነት ይጠቅመናል በማለት ትዛዛቸዉ ሲያቀርቡ የአወልያ አስተዳደርም እኛ ደብዳቤ ብንፅፍ የሚሰማን የለም። እኛ በመጅሊስ ዮኮሾምን ስለሆነ እኛ የምንፅፈዉን ደብዳቤ የሚቀበለን የለም። ደብዳቤ በመፃፍ ጊዜያችንን ከማቃጠል ዉጪ ሌላ ምንም አናተርፍም በማለት አስተዳደሩም ሐምሌ 8 የሚካሄደዉን ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራሙን ማስቆም እንደማይችል ገልፀዋል። ሰብሰባዉ እስከ ምሽቱ 2ሰአት የቆየ ሲሆን መግባባት ላይ ሳይደርሱ መጠናቀቁን ምንጮቻችን ገልፀዋል።

## የማስመሰያዎች ማጋለጫ

ውድ ሙስሊሞች የአላህ ሰላም በናንተ ላይ ይሁን። ባሳለፍነው ሳምንት ብዙ የተደበቁ ጉዶችን አየን!! ሰማን!! ሃሰትን ለማጋለስ የሚደገው ሩጫ በማን አለብኝ ስሜት በገሃድ ታየ። እኛም መንግስት በጓዳው ውስጥ ተደብቆ ሲፈፅማቸው የነበሩ የሃሰት ፕሮፓጋንዳዎች እና የመብት ጥሰቶችን በግልፅ ለሚመለከተው ሁሉ ባለፉት ቀናት ስላሳየልን እናመሰግነዋለን። ከእንግዲህ ህፃኑም ይሁን አዛውንቱ ሙስሊሙም ሆነ ሙስሊም ያልሆነው እየተፈፀመብን ሰላለው ግፍ ከበቂ በላይ በሆነ ደረጃ እውነታዉን አራሳቸው አሳይተውልናል።
በገፅ አንድና ከላይ የሰፈሩ ጫናና ትንኮሳዎችን ለተመለከተ ሁሉ የሚከተለውን ለማረጋገጥ ይገደዳል። ህግን ልናስከብር ነው የቆምነው ባሉበት አንደበታቸው ህግን ተላልፈዋል! መብትን ጥሰዋል! የእመነትና ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ነፍገዋል! ጨርቃችንን ጥለን ቆመን ያጨበጨብንለትን ህገ መንግስት እናስከብራለን እያሉ ህገ መንግስትን ሸርፈዋል! በተጨባጭ የሌለ ስእል በመሳል ሀብረተሰቡ ላይ ሽብር ነዝተዋል! የሚፈልጉትን ወንጀል ለመስራት ቀድመው ያንኑ ወንጀል ሰርተዋል በማለት የንፁሃንን መልካም ስም አጥፍተዋል! እውን ይህ ሁሉ በደልና ግፍ ከመንግስታችን የምንጠብቀው ነበርን? እስከዛሬ ድምፃችንን እየሰጠን የመረጥነው የህልውናችን መሰረት የሆነው እምነታችን ላይ ይህን መሰል ግፍ እንዲፈፀምብን ነውን? ይህ ነው ምላሹ?
ቀድሞ የነበሩ አፂዎች አንድ ላይ በጋራ ይኖር የነበረውን ማህበረሰብ አኗኗር ባለመቀበል በሙስሊሙ ላይ አነጣጥረውና ጦራቸውን ሰብቀው የቻሉትን ሁሉ ግፍ በአባቶቻችን ላይ ፈፀሙ። ለሊስላምና ሙስሊሞች ያላቸውን ጥላቻና ጠላትነታቸውን በግልፅ አወጁ። ሙስሊሞቹን ለማጥቃት የሚያማዟቸውን ሙናፊቆች ከጎናቸው አሰለፉ። ዛሬም ይኸው ሁኔታ መልኩንና ገፅታውን ቀይሮ በዲሞክራሲ ስም ከፊት ለፊታችን እየተጋፈጠ መሆኑን እንድናብሰለስል አድርገናል። በቀደምት ሙስሊም አባቶቻችን ዘመ መጤ አስተሳሰብ በግድ በዲናችን ላይ ለመጫንና መስጂዶቻችንና መድረሳዎቻችን ከዚህ መጤው የአህባሽ አስተሳሰብ ውጪ እስከዛሬ የቆየንበትን ትከከለኛው የዲናችን አስተምህሮ እንዳይኖር በማድረግ ትውልድን ለማከላሸት የሚደረጉ መፍጨርጨሮችን ተመልከተናል።
ይህ ሁሉ ግን በዲሞክራሲ ሰም ነው የሚደረገው። ለሙስሊሙ ዘብ የቆሙ በማስመሰል። ሙስሊምን ከአሸባሪ ቡድኖች ለበጠበቅ ነው በማለት። በአጠቃላይ እራሳቸውን ለኛ ሙስሊሞች ጥብቅና የቆሙ በማስመሰል በስውር የሚፈልጉትን ድብቅ አጀንዳ ለማስፈፀም ሲራወጡ መመልከት ምንኛ ያሳዝናል!! ድብቅ አጀንዳቸውን ለማስፈፀምና ይህን ግፍ አልቀበልም ያለን ሁላ ለመድፈቅ እንዲረዳቸው ድብቅ አጀንዳ ያላቸው ቡድኖች ናቸው በማለት የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ጠምዝዘው በንፁሀኑ መብት ጠያቂ ላይ ያላከካሉ። ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል!! ይኸው ነው እንግዲህ እየሆነ ያለው።
በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ አህባሽን ለማንሰስና አህባሽ መራሽ መጅሊስ ለማቋቋም የሚውተረተሩት ይሆን ድብቅ ሙስሊሙን በዲሞክራሲ ስም ከፋፍሎ የመምታት አጀንዳ ለማስፈፀም ካልሆነ በቀር ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ ለምን አስፈለገ። ህሳባቸው ይህን መሰረት ካላደረገ ዲሞክራሲን እናሰፍናለን እያሉ «በገር በር የገቡ የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉንም እና ወርደው በምትካቸው በፍትሃዊ ምርጫ የእምነት መሪዎቻቸንን እንምረጥ» በማለታችን ይህ ሁሉ ቂያማ ለምን ይወርድብናል?
መብታችን ተገፎ ተሰባስባችሁ ሰደቃ አታድርጉ የምንባልበት፣ ተወካዮቻችን በየቦታው እየተያዙ ዛቻና ማስፈራሪያ የሚለቀቅባቸው ዘመን መጣ? እዚህም እዚያም ትንኮሳዎች ጉድ እኮ ነው!! ይህ ህገ-ወጥ ተግባር ነው!! ህገ መንግስቱን የሚሸራርፍ የመብት ጥሰት ነው!! መብታችንን ለማስከበር ደግሞ እስከመጨረሻው እንታገላለን!! ይህ ደግሞ የማይሸርና የማይሸረሸር አቋማችን ነው!!
እኛ ሙስሊሞች ነን። ሀገርና ሰላም ወዳድ ዜጎች። ለሃገራችን ሰላም፣ ልማት፣ እድገትና ብልፅግና ዘብ የምንቆምና ጠንክረን የምንሰራ ሰላማዊ ዜጎች። የዘመናት መገለሎችን የሸረሙ ህገ መንግስቱ እንዲከበር ከማንም በላይ በፅኑ የምንፈልግ ህግ አክባሪ ዜጎች። የሌላውን መብት አክብረን ከሌላ እምነት ተከታይ ወገኖቻችን ጋር በመቻቻል ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የህብረተሰባዊ ግንኙነት እንዲጎለብት ተግተን የምንቆም ዜጎች። በአንጻሩ በዲናችን ህልውና ላይ ለሚመጣብን ዲናችንን ለመጠበቅ ስንል ያለንን ንብረታችሁ መስዋትነት ለመከፈል ዝግጁ የሆንን ዜጎች ነን።
በመሆኑም መንግስት እየተደረጉብን ያሉ የመብት ጥሰቶች ቆመውና የተፈጠሩ ችግሮች ታርመው በሰላማዊ መንገድ አልባት እንዲያገኙ እሁንም እንጠይቃለን። ትንኮሳው ሁሉ ይቁም? በየወረዳዉና በየአካባቢው የሚደረጉ ሰብሰባዎች ዓላማቸው የህዝብ የሆነውን የምርጫችን በመስጂዳችን ጥያቄና አስመራጩ የመጅሊሱ አሉባልታ ሰይሆን እኛ ነምነን በየአካባቢያችን የምንሰይማቸው አካሎች ይሁኑ የሚለውን ጥያቄ ለመቀልበስ መሆኑ ቀርቶ ጥያቄዎቹን ተቀብሎ ለመደገፍ የሚደረጉ እንዲሆኑ ጥሪ እናቀርባለን።

## ታላቅ ሀገር አቀፍ የሰደቃ የአንድነት የዱዓና የዘሰዐ ጥሪ!!

ከአወልያ የፈታችን እሁድ ሀምሌ 8 የሚካሄደዉን ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራሙን ለማከሸፍ ከፍተኛ ጥረቶች እየተጎረገ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። በዚህም ሙስሊሙን በየአካባቢው በመሰብሰብ አወሊያ አትሂዱ ብሎ ባዶ ሽብር ከመንዛት ጀምሮ እስከ እናቶችንና ትልልቅ ሰዎችን በየሰፈሩ ከከፍተኛ አመራሮች ለማካሄድ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።
ለፊው ሳምንት የተደረጉ የሰደቃ ፕሮግራሞችን ለማከላሸት ጥረት ሲያደርጉ የከረሙትና ኮሚቴዎቻችንንም ላይ የፎከሩት የአወሊያውን ታላቁ ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራምን ለማስተጓጎል አስበው እንደሆነ ግልፅ ነው። በመሆኑም በኮምቦልቻና በሌሎችም አካባቢዎች የታየዉን ከፍተኛ የዲን ፅናት በበለጠ ማልዙ በማንገብ ሁሉም የአዲስ በባ ነዋሪ እንዲመጣ ታላቅ ጥሪ ተላልፏል። ከሌሎችም ከተሞችና አካባቢዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ እንግዶች ፕሮግራሙን ለመካፈል አዚሂ አዲስ አበባ ከዘረ ጀምሮ ንደሚገቡ ታውቋል። ይህ ታላቅ ሀገር አቀፍ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም አስመልከቶ ሁሉም ሙስሊም የአቅሙን አስተዋፅአ በማበርከት በአጭር ጊዜ ውስጥ የተገኘዉ ደግላሽ ስደናቂ ነበር። ይህም የመዲናችን ሙስሊም ባለው አቅም ሁሉ የሚያደረገው ጥረት ከፕሮግራሙ ስፋት አንፃር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባው ጥሪ ታላልፏል። ይህንኑ ማደናቀፍ የሚያደረጉት ሙከራ ሊኖር ቢችል እንኳ የያዝነው ፕሮግራም ህገ-መንግስቱን ያከበረ እስከሆነ ድረስ ምን ጊዜም ቢሆን ወደ ፊት እና ወደ ፊት ብቻ በመጓዝ ጌት ስራዎቻችን ለአፍታም ቢሆን አይገባም። በመሆኑም የአወሊያ ሐምሌ ስምንት ፕሮግራም ዝግጅት ተጧጡፎ መቀጠሉን እያሰበናችሁ ሁሉም ሙስሊም ዛሬ ጀምሮ በቦታው በመገኘት የበኩሉን ሁለንተናዊ ትብብር እንዲያደርግ በድጋሚ ጥሪውን በአላህ ስም ተላልፏል። አላህ ሽይር ይወፍቀን።



http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምፃችን ይሰማ!!

ቁ18

06-11-2004 ዓ.ም

27ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ !!


## በኮሚቴዎቻችን ላይ የተፈፀመው ትንኮሳና የህዝበ ሙስሊሙ ቁጣ

በመላዉ አለም የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጲያዉያን ሙስሊሞች በፌርማቸዉ አረጋግጠዉ የወከሉት የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሼህ አህመድ ሸዴ ሁሴን ኡስታዝ አህመዲን ጀበል ረቡዕ ቀን ኢስታዝ ካሚል ሸምሱ ደግሞ ሃሙስ ቀን በደህንነቶች ተወሰደው ከንቱ ዛቻና ማስፈራሪያ ተነግሯቸዋል።

ከነዚሁ ዛቻና ማስፈራሪያተብዬዎች መካከል ኡስታዝ አቡበከር አህመድን ከዚህ ቡሀላ በኢትዮጲያ ዉስጥ ለሚፈጠረዉ ችግርና የፈታችን ሐምሌ 8 በአወልያ ይካሄዳል በተባለዉ ፕሮግራም ላይ ለሚፈጠረዉ ችግር ሀላፊነቱን የምትወስደዉ አንተነህ ሲሉ። በአጠቃላይ ለ3ቱም ደግሞ እናንተ ሀገሪቱን ለማተራመስ እየተንቀሳቀሳቹ ትገኛላቹ። ሀገ ወጥ ናቹሁ። በሰደቃ ስም ሀገሪቱን እያመሳችሁት ትገኛላችሁ። ከዚህ ቡሀላ ማንኛዉም አይነት ሰደቃ የሚባል ፕሮግራም እንዳንሰማ። ከዚህ ቡሀላ ኮሚቴ ነን የምትሉትን አማርኛ አቁሙ። እናንተ ህገ ወጦች ናችሁ በማለት ማስፈራሪያቸዉን ለመቀጠል ጪምሩ ጀግኖቹ የኢስላም ልጆች እኛ ህገወጥ አይደለንም፣ ህገ ወጥ እናንተ ናችሁ በማለት መልሰዋል። ደህንነቶቹም እኛ እኮ እዚህ ያመጣናችሁ ለስብሰባ አይደለም። እናንተን አንድም ሙስሊም እልመረጣችሁም። ህዝብ በድምፁ የመረጠዉ ኢህአዴግን ብቻ ነዉ። ከዚህ ቡሀላ ኮሚቴ የሚባል ነገር መንግስት አይቀበለዉም። መንግስት ዝም ሲላችሁ የፈራችሁ መሰላችሁ ወይ? ከዚህ በላይ መንግስት አይታገሳችሁም። ከዚህ ቡሀላ የምናስራችሁ ወይም ፍርድ ቤት የምናቀርባችሁ እንዳይመስላችሁ። መንግስት የራሱን እርምጃ እንደሚወስድባችሁ እወቁ። ፍርድ ቤት በመውሰድ ጊዜ አናባክንም። አንዲት ችግር በፈጠር የመጀመሪው ጥይት እናንተ ላይ ነው የሚያርፈዉ። በማለት ማስፈራሪያቸዉን አሸናንደጎዱት። የሙስሊሙ ኮሚቴዎችም ያላአንዳች ፍርሀት አስደናቂ ምላሻቸዉን ሰጡ። እባካችሁ ይህንን ማስፈራሪያችሁን ተዉ!! እኛ የምንፈራችሁ መስሏቹ ከሆነ አትሳሳቱ። አንድም እናንተን የምንፈራበት ምክንያት የለም። ለምን አስካሁን እርምጃ አትወስዱብንም ነበር። ይኸዉ አሁን አጠገባችሁ ስለሆንን ቀጠሮ ለምን ትሰጣላችሁ? እዚዉ የፈለጋችሁትን እርምጃ ዉሰዱዋ? እኛ ሞትንም ሆነ እስራትን የምንፈራ አይደለንም። መረጃ ካላችሁ ፍርድ ቤት ዉሰዱና ክስ መስርቱ። ምን ታስፈራራላችሁ? እንኳን መስፈራራት ይቅርና ለእምነታችን ሕይወት ለመስጠት ዝግጁ ነን በማለት ኢስላም ምን ያህል ፅናት እንደሰጣቸዉ አሳይተዋቸዋል።

ይህ ህግን አስከብራለሁ የሚለው አካል የፈፀመው ህገ ወጥ ተግባርና የህገ መንግስት ጥሰት ነው፣ ህዝበ ሙስሊሙን መናቅ ነው፣ ትእቢተኝነትና ዲናችንን ዝቅ ማድረግ ነው። ስለዚህ ይህን አስነዋሪ ድርጊት የፈፀሙ አካላት ህዝብን ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባል። ይህን ተንተርሶ በታላቁ አንዋር መስጂድ ረቡእ ከዓስር ቡኋላና ሀሙስ ከገሀር ሰላት በኋላ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ምዕመናን ተቃውሟቸውን አሰሙ። የተቃውሞ ዋነኛ መነሻ ህዝበ ሙስሊሙ በወከላቸው የኮሚቴ አባላት ላይ እየደረሰ ያለው ከፍተኛ የማስፈራራት ዘመቻ ይቁም በሚል እንደሆነ ተጠቁሟል። በተቃውሞ ወቅት ከተሰሙት መፈክሮች መካከል "ኮሚቴዎች ላይ የሚደርሰው ማሰርና ማስጠንቅ ይቁም፣ ድምፃችን ይሰማ፣ መብታችን ይከበር፣ጥያቄአችን ይመለስ የሚሉት ለአብነት ያህል ይጠቀሳሉ። ቀደም ሲል የህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄዎችና የተቃውሞ ድምፆች የሚሰሙት በዕለተ ጁምዓ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ትላንትና ከትላንት ወዲያ ባልተለመደ መልኩ በታላቁ አንዋር መስጂድ ቅጥር ጊቢ ከፍተኛ የተቃውሞ ድምፅ እንደተሰማ ምንጮች ገልፀዋል። ይህ የተቃውሞ ድምፅ ዛሬም እንደሚቀጥል ይጠበቃል።

በተመሳሳይ ሀሙስ ዕለት የሺህ ሆጂሌ መስጂድ ኢማም ሼህ አብዱ ሰላም ጠዎት ላይ በፖሊስ ከተያዙ ቡሀላ ጣቢያ ተወስደዉ ማስፈራሪያ እንደተሰጣቸዉ ተገልፆል። ወጣቱን የሚያነሳሳ ትምህርት እያስተማርክ መሆኑን ደርሰንበታል።ከዚህ ቡሀላ ይህን ትምህርት መስጠት ማቆም አለብህ ለማስፈራራት ሞክረዋል። ሼህ አብዱ ሰላምም በበኩላቸዉ መንግስት በህይመኖታችን ላይ በግልፅ ጣልቃ ገብቷል። እጁን ሊያወጣ ይገባዋል። መንግስትን አይደለም እራቷ ህዝቡም ቋራዉን እንዲቆም እየጠላዉ ነዉ በማለት ያለአንዳች ቁርሀት የመንግስትን ጣልቃ ገብነት በአስፈራሪዎቹ ፊት አዉግዘዋል።

## ሊያት ያሉ ክስተቶችን ያስተናገዱ የሰደቃና የአንድነት ፕሮግራሞች

ባሳለፍን ሳምንት በመዲናችን አዲስ አበባ ቢታላቁ ኑር ሰፈር በኒን መስጂድ፣ በፉልውሃ መስጂድና በመገናኛ ሱመያ መስጂድ ታላቅ የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራሞች ተከናል። በተለይ በኑር ሰፈር በኒን መስጂድ የተካሄደው ለየት ያሉ ክስተቶችን አስተናግዷል። ይኸውም ለተወሰነ ሰዓት ምእመናኑ ወደ መስጂድ እንዳይገባ ታግዷል፤ ለሰደቃ ፕሮግራሙ የተዘጋጀው አንድ መኪና ኩሊስ እንዳይገባ በፖሊሶች ታግቶ ተወስዷል። ቡኋላ ላይ ግን በተምርና በውሃ ምእመናኑ ምሳውን አሳልፎ ፕሮግራሙ እስከ አስር ድረስ ተካሂዷል።

በክፍለሃገር በወረባቡ፣ በሰልጤ፣ በጉራጌና በሌሎችም አካባቢዎች የተደረገ ሲሆን በተለይ በኮምቦልቻ የተካሄደው የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም ልዩ ክስተቶችና ለዲናችን ሲባል የተሰሩ ጀብዶች የተስተዋሉበት በመሆኑ ይህንን ገድል በጥቂቱ ልጉተርክላቹ ወደድን።

ከፕሮግራሙ በፊት በፖሊስ ከተወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ ለፕሮግራሙ ግብዓት የሚሆኑ እንጀራ ይጋገርበታል ተብሎ የታሰበ ቤት ሁሉ እንዲፈተሽ፣ ከተገኘ እንጀራው ተወርሶ ግለሰቡን ማሰር። ይህንም ለማድረግ ጭስ በሚታይበት ቤት ውስጥ ሁሉ ፍተሻ ተደርጎ የተወሰኑ ግለሰቦች ታስረዋል። ሌላው የፖሊስ እርምጃ ለፕሮግራሙ የተገዙ በሬዎችን መውረስ የሚል ሲሆን በሬዎቹ ሐሙስ ቀን ከሚሴ ከተማ መዝሐታቸውን መረጃ ስለነበራቸው ከዛ ቀን ጀምሮ ከፍተኛ አሰሳና ክትትል ሲያደርጉ ሰንብተዋል። ያከተማዋ ትራፊክች በመኪና ተጭኖ ወደ ከተማዋ የሚገባ ከብት ካለ እንዲይዙ የታዘዙ ሲሆን ሌሎች ፖሊሶች ደግሞ ከብት ሊያድርባቸው ይችላሉ የተባሉ የግለሰብ ግቢዎችን ጨምሮ በአቅራቢያ ያሉ ሜካዎችን ሁሉ ቀን ከሌት በመፈለግ ሲባዝኑ ከርመዋል። ለከተማዋ ኢማሞችና ሙአዚኖች በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት በሁሉም ጁምዓ በሚሰገድባቸው መስጂዶች ጁመዓ ሊሰግድ ለተሰባሰበው ሙስሊም ህብረተሰብ "አሁድ በተዘጋጀው የሠላቢኖች ሶደቃ ላይ ("ጣልቃ ያልገባው") መንግስትና መጅሊስ ስላልፈቀዱት እንዳትገኙ በአላህ ስም እንጠይቃለን"በማለት አውጀዋል። ለእርድ የተገዙት 9 በሬዎችና 10 ሙከቶች ታርደው የታረደው ሲጋም ለመከተፍ የፈጀው ሰዓት ከ፡30 እና 40 ደቂቃ አይበልጥም ነበር። እጅግ የሚገርም ክስተት። የተጠባውን ስጋ በ[illegible]ተቶ በኩል ሴቶቹ በሚገርም ፍጥነትና ቅንጅት ሰርተው የጨረሱበት ጊዜ ለማመን ይከብድ ነበር። እጆቻቸውና ዓይኖቻቸው እኩል በስራ ተጠምደው ነበረ አንዳ በመከተፍ ሌላው ደግሞ በተፈመባቸው ግፍ በማንባት።

አሁድ የከተማው ነዋሪዎች ሌሊቱን ሙሉ በስራ ቢያሳልፉም የድካም ስሜት አይስተዋልባቸውም። የእንባዶቻቸው በየበራቸው መቆጣጫ ውስጣቸውና ሰላም ቢኖረውም ከመስራት ወደ ኋላ አላሉም። በከተማዋ ውስጥ ምንም ዓይነት የትራንስፖርት አገልግሎት የለም። ስብሰባ ተገኙ በሚል ስራ እንዲቆም ተደርጓል። ፕሮግራሙ ላይ ልንዳደርሳ ስንት የተለፋበት ህብረተሰብ በነቂስ መምጣቱ አስደሳች ነው። ከደሴዎቹ ንብርኤልና መካነ ኢየሱስ አብያተ ክርስቲያናት ከመጫጩ ሁለት ሰፋፊ ድንኳኖች ፀተዉ ማሪ ፡ ከሱት ቦታዎች ላይ ከመስጂዱ ቅጥር ግቢ ውጪ ሁሉ ዳስ ተጣለ።

ፕሮግራሙ ላይ ለመታደም ከየአቅጣጫዉ ይተም የነበረው ሙስሊም ማህበረሰብ በሶስቱም ቦታዎች ላይ ታጉተ፡ ከ14ሬ፡ ከነቱ፣ ከጧርባና ከደጋን ይመጣ የነበረው እጅግ በርካታ የህብረተሰብ ከፍል ወርሰይ ከምትባልና በግምት 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኝ ቦታ ሲታገቱ። ከከሚሴ፣ ከሐርቡ የመጡት ዳግሞ ፎንተኒ ከሚባልና በግምት 18 ኪሎ ሜትር ርቀት ካለት ቦታ፣ ከደሴ የሚመጡት ወደ አውቶቡስ መነኻሪያ ቢሄዱም ወደ ከምቦልቻ የሚሄድ መኪና ባለመኖሩ (በመከለከሉ) 24 ኪሎ ሜትርንም በእግራቸው መጓዝ ግድ ሆኖባቸዋል። የፀጥታ ኃይሎች በእግር የሚጓዙትንም ለማገድ ጥረት ያደረጉ ቢሆንም ህዝቡ ዋናውን መንገድ በመተው በዱር በገደሉ ሰለተጓዙ ለመከላከል ሰራተኛሉ። በእግርጉዞ ብዙ ኪሎሜትሮችን ጋራና ሸንተረሩን ማቋረጡን ተያያዙት። በዚህ ጉዞ አንድ አረጋዊ "እንዴ ጋሽ አህመድ አንኳ ይህ ነው ማለታቸው ተወስደዉ። ከዚህ በተጨማሪ መንገድ ላይ በነበራቸው መተዛዘን፣ ወንድማማችነት፣ መረዳዳትና መደጋገፍ በአላህ ፍቃድ በሰላም ከምቦልቻ ደርሰዋል። ይህ አንድ ላይ የተሰባሰበ ህብረተሰብ በሰላም ቸና ዋና መስመሮች ወደ ኩተማዋ ሲገባ ያስማ የነበረው ተከቢራና መፈክር ያልታሰበ ሌላ የፕሮግራም ድምቀት አስገኝቷል። የከምቦልቻ ነዋሪ ሆነው በኢማሞች ትዕዛዝ፣ በፍርሀትና በተለያየ ምክንያት ወደ ፕሮግራሙ ለመሄድ ፍላጎት የሌላቸውን ጭምር ሃሳብ አስቀይሯል። በእግር ተጉዘው ፕሮግራሙ ላይ ከታደሙ የህብረተሰብ ከፍሎች ውስጥ ህጻናት፣ አረጋዉያን፣ እናቶችና የአካል ጉዳተኞች ይገኙበታል። ይህ ሁሉ መስዋዕትነት የተከፈለበት ፕሮግራም ድምቀት ለጉድ ነበር።

በፕግራሙ ስለ ህገ መንግስት ተወስቶ ህዝቡ መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ ሲደረግ በተለይም የህዝብን የመንቀሳቀስ ህገ መንግስታዊ መብት በመደፍጠጥ በሰዎች ላይ እንግልትና መጉላላት ፈጠሩ አካላት ለህግ እንዲቀርቡ ተጠይቋል። ይህ ሁሉ እንግልትና መጉላላት ሲደረግበት ህዝቡ ያሳየው ፍጹም ሰላማዊነትም አድናቆት አስገኝቶለታል። ከዚህ በተጨማሪ ስለ አንድነትና ወንድማማችነት፣ ስለ መቻቻል፣ ስለ ምርጫ፣ ስለ ኮሚቴው ጉዞና ወደፊት ስለሚደረገው እንቅስቃሴ በስፋት ገለጻ ተደርጓል። አህባሽ ካደናበራቸው ውሥጥም "እንዲህ ነው እንዴ?" ያሉም ነልጠፉም። በከተማዋ ላይ ነግሶ የነበረውን የጥቂት አህባሾች አምባገነንነት ጋብ አድርጎታል። ለዚህም ይመስላል መፐርግራሙ ማጠናቀቂያ ላይ አንድ ታዳሚ የሰማህ አሰማ ያልሰማህም ስማ፣ ነህባሽ ተዘርጅል ከምቦልቻ ከተማ። የሚል ስንኝ የቋጠሩት። ከዚህ በተጨማሪ በፕሮግራሙ ይዘትና ሰላማዊነት የሌሎች እምነት ተከታዮች፣ የጸጥታና የደህንነት ሰዎች መረጃዎችውንና በተለይ ጸጥታ ሰዎች ባልሆነ መረጃ ላይ ተመስርተው የፈጸሙትን እንዲመረምሩና ነገሮችን እንዲያጣሩ እንዳስገደዳቸው ተናግረዋል።እርግጥ ነው የከተማዋ ህብረተሰብ ከፍተኛ የዳዕዋ ጥማት አለበት። ነህ ፕሮግራምም ይህን ጥማት ይቆርጥልኛል ብሎ ተማምኗል። ኮምቦልቻ የዚህ ዓይነት ፕሮግራም አይታም ሰምታም የምታውቅ አይመስልም።



http://ethcriminalawnetwork.com/

# ሙት ይዘ ይሞታል

በአላህ ፍቃድ መሐሉ ዳር የሚሆንበት ጊዜ እየተቃረበ ነው። በኢስላም ላይ ያሴሩ ኢስላምን ጠላቂው ጌታ ዓይናቸውን ጭለማ፣ እጃቸውን ቁጢማ፣ አንደበታቸውን ቀጣፊ፣ እርስ በርሳቸው ተጠፋፊ እያደረገው ነው። ሕዝበ-ሙስሊሙ ልቡ አንድ ቃሉ የጋራ ሆኗል። ከአጥናፍ አጥናፍ ሳይነጋገር ይግባባል፤ በአድሜ በፆታ በመደብ ቢለያዩት ክሒቅ መንገድ «ዝንፍ አልል» ብሏል። ይህን አላህ እንጂ የትኛው የሙስሊም አስተባባሪ የትኛው መዋቅር ሠራው ሊባል ነው?

ይህም ሁሉ ሆኖ ነገሩ የፊታችን ሰኞ የሚቋጭ ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። መላውን ሙስሊም የሚያስደስት ዜና ከሰው አንጠብቅም። አላህ ነው ሐቅን የሚያስጨብጥ፤ አላህ ነው ቀጥተኛውን መንገድ የሚመራን። ከአላህ መንገድ የወጡት አኼራቸውን በአፋንያ ጥቅም የሸጡ ለሥምና ለዝና ለገንዘብ የሚሞቱ መግቢያ ቀዳዳ ሳጡ ብቻቸውን ወደ አዘቅት መውደቅ አይፈልጉምና በጥንቃቄ መራመድ ያስብን አሁን ነው። «ሙት ይዘ ይሞታል» እንዲሉ በማሉት የመከራ ጉድጓድ ንጹሐንን መክተት ይከጅላሉና በተንኮላቸው መረብ እንዳንጠለፍ ጥንቃቄ ያሻል።

ባለፉት 60 ቀናት አወሊያ መጥተን አላህን ከማላቅ ከማጥራትና ከማወደስ በቀር አንዳች ያደረግ ነው ነገር የለም። ሁሉን የሚያደርገው አላህ ነው። የኛ ኃላፊነት በየቂን የአላህን ገመድ በጋራ መያዝ ነውና ኢንሻአላህ ይዘናል። መርጠን ጣጣውን ያሸከምናቸውን ከሚቴዎቻችንን ያህል እንቅልፍ አላጣንም፤ ቀንና ሌት አልተጨነቅንም፤ የነሱን ያህል በሃሳብ አልባተትንም፤ በውጥረት አምሽተን አላነጋገም፤ እነሱን በገንዘብ አልረዳንም፤ ግና አላህ ዝይር ጀዛቸውን ይክፈላቸው።

እውነት ሞንምና ሞታ ከምናያት የባጢልን ድር እንበጣጥሳለን ብለን ተነስተን ነውና እነዚህን ወንድሞችና አባቶች ኃላፊነቱን ያሸከምናቸው አላህ ምንዳቸውን በጀነት ይክፈላቸው። እኛንም አላህ ያስደስተን። የአላህን ፍቅር፣ ውዴታና ጀነት ከጅለን እንጂ የመጅለስ ክፉ አመራሮች ተወግደው ደግ አመራሮች ቢመጡ ኪሳችን የሚገባ አምስት ሳንቲም እንዳለ አስበን አይደለም። ግና ዲነል ኢስላም ተዋርዶ ከምናይ ብለን ነው በፀሐይ ሐሩር የምንንቃቃው አላህና ረሱሉ የጣሉብንን ሃይማኖታችንን የመጠበቅ አደራ ነው እየተወጣን ያለነው። በኢኽላስ ለአላህ ብለን እንጂ ማንም ሰማስደሰት አልተሰበሰብንም። ለዚያም ነው አላህ የአንድነት ገመድን ያስጨበጠን-ምስጋና ለሱ ውዳሴ ለአላህ።

ታዲያ ዛሬም ቢሆን በአስተዋሉት በሰከነ ኢስላማዊ መንፈስ መራመድ እንዳለብን አንዘንጋ። የብልጣ ጫሎች መጠቀሚያ እንዳንሆን። ውድቀታቸውን እንድንጋራቸው ብዙ ቀዳዳ ይቆፍሩልናልና የትኛውንም ክፍተት ለጣቸው።

እንዲህ ዓይነት አደብ (ሥርዐት) ያለው ተቃውሞ በአገራችን ታይቶ እንደማይታወቅ ብዙዎች ውስጥ ለውስጥ እያጉተመተሙ ነው። በተለይም፤ የጥፋት ኃይሎች እኛን መመረጣ ዘዴ በማጣታቸው በኛ ድርጊት ተገርመው ለአዲሱ የተቃውሞ ስልት ማኮላሻ አዲስ ጥናት እያደረጉ መሆኑን ሰምተናል። ኢንሻ አላህ ለሰላማችንና ለኢስላማችን ቃላችን አይጠፉም፤ አንድነታችን አይፈርስም። ለፍቅር እንጂ ለፀብ ቦታ የለንም፤ ለሰላማችን እንጂ ለጥፋት አልተዘጋጀንም።

ምንም ስለሌለ የሚበልጥ ከዲኔ

ጠንክሬ ቆማለሁ ምንጊዜም በወኔ።

ነው ዜማችን የጋራ ቃላችን!!!



# የትግላችን አቀበቶች

በዓለማችን ውስጥ አላህ ብቻ በሚያውቃት በአንደኛው ጥግ ሥር የ«ዋሽዎቹ ሰዎች» ከተደፋባቸው ዋሽ ለመውጣት ቀን በቀን በቁፋሮ ላይ ቢሆኑም፣ ከዋሻው ውጪ ያሉ በየትኛውም የዓለማችን እራፊ መሬት ላይ የሚገኙ ሙስሊሞች የየክልላቸውን አቀበቶቻቸውን ለመውጣት እዩተጋሉ፣ እየለፉ፣ እየባዘኑ ይገኛሉ። ከአሜሪካ እስከ ቻይና፣ ከዴንማርክ እስከ ደቡብ አፍሪቃ የሚገኙ ሰዎች አቀበቶቻቸውን ለመውጣት በመልካምም ይሁን በእኩይ መንገድ ተጠምደዋል። ከነዚህ ትጉ አቀበት ወጭ ሙስሊሞች መካከል የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አባላቸው ናቸው።

ሙስሊሞች በዚህች ምድር ቆይታቸው እንዲያሳኩት [illegible] አላህ (ሱ.ወ) የተሰጣቸው ተልዕኮ አለ። ነገር ግን፤ በራሳቸው ድክመት እና በጠላቶቻቸው systematized and institutionalized (የተጠናና ተቋማዊ) ባሕሪ ባለው ሴራ ምክንያት ከዓለማችን ተቆራርጠን፣ ከቅኔዎቻችን ሩቅ ከክለን እንገኛለን። የጠላቶቻችን ሴራ ዓለም አቀፋዊ ከመሆኑ ጋር ጠላቶቻችን የተደራጁ፣ ኪሳቸውና መሳሪያ ያበጡ እንደመሆናቸው ከመሰኮታዊው ዓላማችንና ተልዕኮዎችን ጋ ተቆራርጠን እንደነቀር ለዘመናት በቆሰሉት የአበሳና የመከራ ቁልል ላይ የሚጨምሩት ቁልል ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ይገኛል። ሆኖም፤ ከአቀበቱ ወዲያ እየሾለኩ የሚመጡ ጨረሮች ተስፋ ሰጪ ሆነውናል። ለይደግስ አይጣላም አይደል የሚባለው!?

የኢትዮጵያ ሙስሊም ታሪኩ በሙሉ የትግል ታሪክ ነው። ለአንዲትም ቀን ከትግል ተቆጥቦ አያውቅም። ድምፁ ጠፍቷል ማለት ትግሉን ትቶታል ማለት አይደለም። እጅግ አስፈሪ በሚባል ዝምታ ውስጥም የማዕበል ያህል የሚናጥ ትግል ያደርጋል። በሌላ ሞዳሊቲ እኩልነት ፈጣጣና ስለታም አቀበት ላይ የሚያደርገው የፍትህና እኩልነት ትግል የተሰበረ የሚመስል ቢሆንም፤ ከሰውነቱ የሚንዠቀዠቀው ላቡ፣ የኢፍትሃዊነት አስቀያሚ አሰትን ከሚሸፍኑት የእጆቹ ጣቶች የሚፈሱት ደሙ፣ ከጉሮሮው የሚሰማው የአልህ ሲቃ ላቡና ደሙ የኢፍትሃዊነት ሆነው፣ ሲቃው የመለከተ ያህል ከአዕናፍ እስከ አዕናፍ ይታሚል። ይሰማል። የአመፃን ጅበልን «የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የጭቆናና የትግል ታሪክ» መጽሐፍ ውስጥ ገብተው አስተ[illegible] የላቡና የደሙ ፏፏቴ ገዝፎ ታዩታላችሁ፤ ሲቃውም ከኮለለ ጣፋጭ ዜማ መሪዋ ሆኖ ታደምጡታላችሁ። ይሽው ኢሁን ደግሞ ከኢትዮጵያ ዕብርት አዲስ አበባ አወሊያ ከሚባለው ቦታ ላይ ወቅቱን ጠብቆ እየተሰማ ይገኛል። አሁንም ሳይደግስ አይጣላምና ከዚህ ከመንገድ ራቅ ብሎ በአዋጅ ተከልሎ በጠባብ መሬት ውስጥ እና በፎቆችና ዛፎች ጫካ መሃል በሚገኘው ሜዳ ላይ ከከተመው ሕዝብ የሚሰማው ድምፅ ጩኸባይ ፏፏቴ በልጦ፤ ከመረዋ ድምጽ ተሽሎ በድፍን ኢትዮጵያ እየተሰማ ነው። አላህ (ሱ.ወ) ምን ያደት? ምን አቅቶት? እንዳሉ ስለማናውቃቸው በዋሻው ውስጥ ስለተቀበሩት ሰዎች ድምፅ ያሰማን ይረዳ አይደለም እንዴ?

ጠላቶቻችን ግን አያርፉም፤ አይተኙም። ቢያጡ እንኳን በአካፋ ከሚወረውሩብን የአበሳና የእፍረት ክምር፣ የኢ-ፍትሃዊነትና የአድልዎ ጭቃ በተጨማሪ በቀኖችንም በግራችንም እየተመላለሱ ሊያስፈራሩን ይሞክራሉ። ከአቀበቱ ሥር ሆነው እግራችንን ይጎትታሉ። ግና አላህ ግን ከኛ ጋር ነው።



http://ethcriminalawnetwork.com/

ደብዳቤውም ‹‹ከዚህ በፊት እናንተ መጅሊሶች ወሃቢያንና ሌሎች ከሽብርና ፅንፈኝነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እያነሳችሁ የነገራችሁንን ነገር በሙሉ አምነን በመቀበል በሥልጠና መድረክቻችሁ ሳይቆር የናንተን ቃል እንደ ገደል ማሚቶ ስናስተጋባ ቆይተናል። ሆኖም፣ የምታውሩትና የምታስወሩት ነገር ምን ያክል እውነትነት እንዳለውና ተጨባጭ እንደሆነ ማስረዳት የሚችል መረጃ አዘጋጅታችሁ አሁን ባስቸኳይ አቅርቡ። በዚህም ወሃቢያ የምትሉትን በሚገባ አብራርታችሁ፣ አክራሪ ነው፣ አሸባሪ ነው፣ ፀረ ህገ መንግስት ነው፣ ፀረ ህዝብና ፀረ መቻቻል ነው ስትሉ ምን ማለታችሁ እንደሆነ ተጨባጭነት ያለው ሰነድ አቅርቡ›› የሚል ይዘት ያለው ነው። አቶ አህመዲን ተደናግጦ የራሱን ስራ አስፈፃሚዎች 4:30 ላይ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራቸውና ጉድ ፈልቶብናል ምን ይሻለናል፣ መንግስት እኛን አሸቀንጥሮ ሊጥለን አስቧል መሠለኝ ምን ትላላችሁ፣ መላ ፍጠሩ ያለበለዚያ በቆፈርነው ጉድጓድ መቀበሪያችን ጊዜ እየገሰገሰ ነው ሲል ይዞት የመጣውን ደብዳቤ በማስረዳት ያወያያቸዋል። እነሱም ይህ ጉዳይ ዲናሞቂ እውቀት የሚጠይቅ ነገር ነው፣ ለዚህ ደግሞ እኛ አቅም የለንም፣ ጉዳዩ በቀጥታ ለ"ዑለማ ምክር ቤት "ይመራ እና እነሱ ያዘጋጁ ሲሉ ይደመድማሉ።

አህመዲንም አዲሱን የ"ዑለማ ምክር ቤት" ሊቀመንበር የሆነውን ግለሰብ ያስጠራና ስለ ጉዳዩ ያጫውተዋል።/በነገራችን ላይ በአቶ አህመዲን እና በ"ዑለማዎች ምክር ቤት" ሊቀመንበሩ መካከል ቅራኔዎች እንደተፈጠሩ ተሰምታል። የቅራኔውም መንስኤ የሆነው የመውሊድ በዓል ዝግጅት ነበር። ነገሩ እንዲህ ነው፡- በሉማ ሆቴል የመውሊድ በዓል በሚከበርበት ወቅት የውጭ ሀገር እድምተኞችም ነበሩ።በዚህ ጊዜ አቶ አህመዲን መድረኩ ላይ የሚነበብ ጽሁፍ ያዘጋጅና ወይም እንዲዘጋጅ ያደርግና ታዳሚው የዑለማዎች ምክር ቤት ያዘጋጀው እና የዑለማዎች ምክር ቤት ሀሳብ እንደሆነ እንዲሰማው ለማድረግ ፅሁፉን ለዑለማዎች ምክር ቤት ሊቀመንበሩ ይሰጣቸዋል። እሳቸውም መድረክ ላይ ቀርበው የተሰጣቸውን ከማንበባቸው አስቀድመው ወረቀቱን በሚገባ ሲመረምሩት የማያሳምን ነጥብ ያገኙበታል። በመጨረሻም የራሳቸውን ወረቀት አዘጋጅተው መድረኩ ላይ ያነባሉ። በንባባቸው መሀል ታዲያ ስለ መውሊድ ቢድዓ መሆን፣ ባይሆን መጥፎ ቢድዓ አይሆንም፣ ይሁን ቢባል እንኳን ሙስተሀብ ይሆናል እንጂ መውሊድን ማክበር ግዴታ አይሆንም፣ የፈለገ ማክበር ይችላል ያልፈለገ ደግሞ ሊተወው ይችላላል፣ ይህ ህዝቡን የመከፋፈያ መንገድ ፈፅሞ ሊሆን አይችልም... አያሉ ሊናገሩ አቶ አህመዲን ከመቀመጫው ተነስቶ የሰውዬውን ንግግር በመሃከረ ማይክራፎኑን ከቀማ በኋላ የሊቀመንበሩን ንግግር ተቃውሞ ራሱ በሚፈልገው መንገድ ንግግሩን ቀጥሏል።/

ሊቀመንበሩም ጉዳዩን ከ"ዑለማዎች" ጋር ልምክርበት ይልና ‹‹ዑለማዎቹን›› ሰብስቦ እስከ 7፡30 ድረስ በውይይት ይቆያሉ። ሆኖም እነሱም ‹‹ደብዳቤው የመጣው ለመጅሊሱ ፕሬዝዳንት እንጂ ለ"ዑለማዎች ምክር ቤት" አይደለም፣ ይህ እኛን አይመለከተንም፣ ጉዳዩ በራሱ ከባድ ነገር ስለሆነ እኛ አንችልም፣ ኪአቅማችን በላይ ነው›› በማለታቸው ምክንያት አቶ አህመዲን ያሰበው ሳይሳካ ቀረ።

ይሁንና ከጥፋት ተንኮሉ ያልተመለሰውና መሰሪ አጀንዳውን ዳር ለማድረስ ቆርጦ የተነሳው አቶ አህመዲን የታዘዘውን ደብዳቤ ራሱ ጽፎ ሊያስገባ እንሚችል ይገመታል። አላህ ህዝቡን ከዚህ መሰሪ ግለሰብ ሽር ይጠብቀው የዘውትር ዱዓችን ነው።

‹‹እንኳን የአወሊያ ሰው አይደለም፤
የአዲስ አበባ ሕዝብ እንኳ ጨርቄን ጥሎ ቢሄድ ከስልጣኔ
ላይ ቅንጣት አይቀንስም።››
‹‹አቶ›› አህመዲን አብዱላሂ (የመጅሊሱ ‹‹ፕሬዚደንት››)
ለአወሊያ ኮሌጅ ተማሪዎች



ይህ ሁሉ ህዝብ

# ድምፃችን ይሰማ! 3

የተቃውሞ ድምፅ

የካቲት 23/2004 - 8ኛው የተቃውሞ ሰልፍ

ዜና

## የክልል ልዑካን ቡድን ተቃውሞኣችውን ለማሰማት ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ነው።

በኢትዮጵያውን ሙስሊሞች ላይ በግድ ሊጫን የታሰበውን የአሕባሽ አስተምህሮና በሕገ-ወጥ መንገድ መጅሊሳችንን የተቆጣጠረውን የነ አህመዲን ቡድንን የመቃወሙ ሂደት ባሳለፍነው ሳምንትም በከፍተኛ ደረጃ ቀጥሏል። ለድምጻችን ይሠማ ሪፖርተሮች የደረሱ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በተለያዩ የሐገራችን አካባቢዎች የሚገኙ ሙስሊሞች ልዑካኖቻቸውን እየላኩ ነው። ከነዚህም ውስጥ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ አወዳይ፣ አዶ አህመዲን ተመርጨየበታለሁ ከሚለው ሐረር ያለው ኮምቦልቻ፣ ኢሊባቡር፣ ጅማ፣ ባሌ፣ ምስራቅና ምዕራብ አርሲ፣ አዳማ፣ ምዕራብ ሽዋ ከሚገኙት ከጃጁና ባኮ፣ ሻሸመኔ፣ ደሴ እና አፋር ይገኙበታል። እንዲሁም ፊርማ ማሰባሰቡ ቀጥሎ አስካሁን በድምሩ 1 ሚሊዮን የሚደርሱ የተቃውሞ ፊርማዎች ተሰብስበዋል ተብሎ ይገመታል። አስካሁን ማሚሾቹ የተቃውሞ ፊርማውን የያዙት ልዑካን ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ የተቀሩት ዛሬ ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል። ጥያቄያቸውንም ለፈደራል ጉዳዮችና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባሉ። በደሴ፣ ወሎ፣ ጭሮ፣ ጎንደርና በዙርያው ብቻ እስከ ከ100 ሺህ ፊርማ ተሰብስቧል። አቶ አህመዲን ተመርጨየበታለሁ ከሚለው ሐረር ያለው ኮምቦልቻም 22 ሺ ፊርማዎች ተሰብስበዋል።

በተያያዘ ዜና የሐረር ዑለማዎች ሐረር በሚገኘው 4ኛ ክፍለ ጦር ተሰብስበው የጋራ የአቋም መግለጫ አውጥተዋል። በመግለጫቸውም ‹‹ሁላችንም ሙስሊሞች ነን። መውሊድ ምክንያት አንከፋፈልም።›› ብለዋል። በጅማ፣ በመቀሌና በደሴ ከተማዎችም ባለፈው ሳምንት ዝግጅት-መጅሊሱ ሰመጅሊስ ሕገ-ወጥ አመራሮች ያለውን ተቃውሞ በተከበራ ገፅታ ሲገልፁ ሆኖም፣ በመቀሌና በደሴ ‹‹አስተባብራችኋል›› የተባሉ ሰዎች ታስረዋል። በሌላ ዜና የሻሸመኔ ከ[illegible] የክ ገጥ መጅሊስ ሥራ አስፈፃሚ ተወያየ በኋላ ለፌደራል መጅሊስ አመራር እውቅና እንደማይሰጥ በመግለጽ ከዕለተ ቀጠሮው ፊርማ አሰባስቧል።

### የሕገ-ወጡ ውሳኔ ውጤት

### የ‹‹ዑለማዎች ምክር ቤት›› እና የመጅሊስ ሥራ አስፈጻሚዎች መስማማት አልቻሉም።

ባሳለፍነው ሳምንት በሕገ-ወጥ መንገድ መጅሊሳችንን የተቆጣጠረው ቡድን አባላት የሆኑት አቶ አህመዲን አብዱላሂ እና ሰሞኑን በምክትልነት የተሾመውን አቶ ዓዛምን ጨምሮ የክልል መጅሊስ ተወካዮች በኦሮሚያ ክልል ደራ ከተማ ውስጥ መውሊድን በማክበር ሽፋን በቦታው ተገኝተው ነበር። ‹‹አብሽሩ››፣ ‹‹የምናሰመሩትና የሚወራው ነገር በሙሉ ትርጉም የለሽ ነው››፣ ‹‹መንግስት ከኛ ጋር ነው፤ ‹‹እንደሚደግፈን ቃል ገብቶልናል››፣ ‹‹በ15 ቀናት ውስጥ ስልጠና መስጠታችንን እንቀጥላለን፤ እናንተም በሚስጥር ሰዎችን መልምላችሁ አዘጋጁ›› ...ወዘተ በማለት አቶ አህመዲን ለተገኘው ሰው ንግግር አድርጓል።

ሆኖም፣ የጥፋት ወጥመዳቸውን በመተብተብ ላይ በነበሩበት ቦታ የመንግስት ባለሥልጣናት አቶ አህመዲንን ባስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ አዘውት፣ ሰውዬው እየተጣደፈ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት በመነሳት አዲስ አበባ ይገባል። በማግስቱ (ሰኞ) ሚት አራት ሰዓት ላይ ከተገናኙ በኋላ ባለሥልጣኑ ቀጭን ትዕዛዝ የሚያስተላልፍ ደብዳቤ በእጁ ይሰጠዋል። ወደ ገጽ 4 ዞሯል



http://ethcriminalawnetwork.com/

# ይድረስ ለውድ ኮሚቴዎቻችን

ባሸከምናችሁ ውክልና ለዲነል ኢስላም ስትሉ ሁሉ ነገራችሁን እርግፍ አድርጋችሁ ትታችሁ በአስር ላይ የምትገኙ ውድ ኮሚቴዎቻችን እንደምን አላችሁ? ለሰባት ወራት የገል ስራችሁን ጥላችሁ የሰጠናችሁን ሀላፊነት ዳር ለማድረስ ሌትና ቀን ደፋ ቀና ስትሉ ያየን ሁላ ውድ የኢስላም ልጆቹ መሆናችሁን ደግመን እረጋግጠናል። የሰጠናችሁ ውክልና በእርግጥም የሚገባችሁ ብርቅዬ ኡስታዞቻችን ናችሁ። በዚህ ሁላ ጊዜ ከህዝብ የወጣችሁ የህዝብ አገልጋዮች በመሆን የከፈላችሁት መሰዋትነት ታላቅ ነበር። ለሹመኛ ባለማጎብደድ የህዝብ ሙስሊሙን የልብ ትርታ ለሚመለከተው ሁሉ ቦሚያስደንቅ ሰላማዊ ሂደት አድርሳችኋል። ዲናችንን ለመበረዝ የተላከውን መጤ አስተሳሰብና ሳንወድ በግድ የተጫነብንን መጅሊስ በመቃወም ለተነሳንለት ቁርጠኛ ዓላማ በቁርጠኝነት ታግላችኋል። የአላህን እርዳታን ብቻ በመከጀል ለቆምንለት ዓላማ ታግላችኋል። ግዜያችሁን፣ ስራችሁን፣ እውቀታችሁን ያላችሁን ነገር ሁላ ለህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄና ለዲን መከበር ስትሉ መሰዋት አድርጋችኋል። ይህ እናንተን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሽተን የምንናገረው ሳይሆን በትክክል መሬት ወርዶ ያየነው እውነታ ነው። አላህ ይህን የገዘፈ መልካም ስራችሁን ይቀበላችሁ? እኛ በሀገርም በውጪም ያለን ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የናንተ ተወካዮቻችን መልካም ስራ መስካሪዎች ነን።

በአርግጥ የናንተን ውድ ልጆቻችን የመታሰር ዜና በሰማን ሰዓት ቁጣችን የምንይዘው የምንጨብጠው አሳጥቶናል። ምክኒያቱ ደግሞ በናንተ ላይ የተፈፀመው የህግ ጥሰት በኛ ውክልና የሰጠናችሁ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ የተፈፀመ ህገወጥና ኡ-ህገ መንግስት ተግባር ነውና። በመሆኑም ይህን ስርዓት የለሽ የህግ ጥሰት በመቃወም በታላቁ አንዋር መስጂድ ቁጣችንን በጥቂቱ ስንተነፍስ በሺዎች የምንቆጠር ታስረናል ጫሳም አርፎብናል። ይሁንና ለሰባት ወራት አብረን ሳለን ያሳያችሁን ሰላም ወዳድነት፣ አርቆ አሳቢነት፣ ህግ አክባሪነት፣ ከስሜታዊነት ርቆ ለዲን ተቆርቋሪ መሆንና እስከ መጨረሻው በመታገል ለዲናችን ዘብ መቆምን ነበርና ይህ ለዲናችን ስንል የምንከፍለው ትንሹ መሰዋትነት ሆኖ ተግላችንን ወደ ወላኝ ምእራፍ አሸጋግሮታል።

ውድ ኮሚቴዎቻችን ያ ስንመለከተው የቆየነው መልካም ስራችሁ፣ ትላንት ውሽትን አጋልጦ ሀቅን ሲናገር በጉጉት በየሳምንቱ እንሰማው የነበረው ድምፃችሁ ዛሬ ከአጠገባችን ሲርቅ ልባችን በሀዘን ተሞልቷል። ያ ይተላለፍልን የነበረው ብልህነትና አስተዋይነት የተሞላበት መልክታችሁ ሲቋረጥ ውስጣችን ቆስሏል። አይናችን አይናችሁን ማየት ባለመቻሉ በረጅሙ አንብቷል። ትላንት የገባችሁትን ቃል ዛሬ ፈፅማችኋል። ለአሰባሳቢ ሲባል የሚከፈለውን መሰዋትነት እንከፍላለን ትሉን ነበር እነሆ መራራውን መሰዋትነት ከፈላችሁ። እናንተ ውድ የኢስላም ልጆች በምን ሁኔታ ላይ ሆናችሁ ይሁን? ለዲን ስትሉ የሞቀ ቤታችሁን፣ ልጅና ሚስቶቻችሁን ጥላችሁ አሁን የምትገኙበት ጨለማ ቤት እንዴት አድርጎት ይሁን? ያ አላህ ባሪያህን የምትንከባከብ ጌታ ነህና አንተው ተንከባከብልን? ሀያሉ ጌታችን ከበደለኞች ተልኮል ሁሉ ጠባቂ ነህና እኚህ ውድ ልጆቻችንን አንተው ጠብቅል? ያ አላህ???

ውድ ኮሚቴዎቻችን አይናችን አይናችሁን ለማየት ናፍቋል፣ ጆሮዋችን ድምፃችሁን ለማዳመጥ ጓጉቷል፣ ልቦናችን መልዕክታችሁን ለመስማት ተንጠልጥሏል። በናንተ መታሰር የሚቆም አንዳችም ነገር የለም፣ ይልቁንም የበለጠ ጥንካሬን የበለጠ ፅናትን ይሰጠናል እንጂ። ይህንን ደግሞ ላለፉት አራት ተከታታይ የረመዳን ጁመዓዎች በታላቁ አንዋር መስጂድና በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ከተሞች የታየው ከፍተኛ ተቃውሞ እድ መስካሪ ነው። ይህንን ማን በነገራችሁ። የተከፈተብን የመብት ጥሰት ከማን እንደሆነ ለይተን በግልፅ አውቀናል። መብት የማስከበር ሂደቱን ለማድረስ ደግሞ ፀንተን እንታገላለን። እናንተ ሁል ግዜም ኮሚቴዎቻችን ናችሁ። የናንተን መታሰር መቼም ቢሆን አንታገሰም። በናንተ የሚመጣብንን አንደራደርም። እስክትፈቱ ትግላችን ይቀጥላል። እናንተ ታስራችሁ ምርጫ የሚባል ነገር አይታሰብም። እናንተ ታስራችሁ የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት የምርጫ ሂደት ህገ ወጥና በምንም መልኩ የማንተበሰው ነው። ተፈታችሁ እንደተለመደው ተነጋግረን የምንደርስበት አቋም ሳይኖር ቤቲቪም ይሁን በሬድዮ እንደፈለጋችው ቢለፍፉ እነርሱ እንዳልሰሙን እኛም እንሰማቸውም። ጆሮዋችን እንደሆን እኛው ዘንድ ነው ያለው። በሚድያ የሚሰሩት ሽፍጥና ድራማ የለመድነው ስለሆነ አይገርመንም። እውነታውን ለማወቅ እነርሱ የሚናገሩትን ገልብጠን በተቃራኒ መረዳት ከጀመርን ውለን አድረናል።

ውዶች በመጨረሻም የሁሉ ነገር ባለቤት አላህ ነው። አላህ ከናንተ ጋር ይሁን። እኛም እስከመጨረሻው ከጎናችሁ ነን። የትግላችን ሁለተኛው ገፅ ዱዓችን ነው በዚህ በተከበረው የረመዳን ወር ቀን በያም አፋችን አላህ እንዲነሰረን በደለኞችን እንዲይዝልና እናንተን እንዲያስፈታልን ስጉበቱን አ በማድረግ ላይ ነን። የዱዓችንን ውጤት እያየነውም እንገኛለን። እነርሱ የመጣብን ፊትና እንዲመለስና አማን እንድንሆን በማሰብ የምናደርገ ሰደቃና ዱዓ ለማሰቆም ታገሱ። ዱዓን በጉልበት ማስቆም ግን አይቻል። አነርሱ እዚህ ሲከለክሉ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በዓለም አቀፍ ደ በተለያዩ ሀገራት አደረጉት። ውድ ኮሚቴዎቻችን በአሁኑ ሰዓት እናንተም በእስር ላይ ሆናችሁ ለይል በመስገድና ዱዓ በማድረግ ላይ መሆናች ሰማን። ድሮም ቢሆን የትክክለኛ ኡስታዞች ተግባር ይህ ነው። እኛም በዚህ አሸሩል አዋሺር ለይል በመስገድ በጀመዓና በተናጠል በሁ መስጂዶቻችን ውስጥ እጆቻችን ወደ አላህ ተዘርግተው አይኖቻችን እያነቡ ዱዓ እያደረግን ነው። መቼም ከዚህ ሁሉ የብሶት አንባ መሀል አላህ ብሱ ምላሽ የሚሰጠው እንደሚናር ምንም ጥርጥ አይናረንም። ‹‹ ሀስቡን አላህ ወኒዕመል ወኪል›› መመኪያችን አላህ ነው ምን ያምር መመካ

## ጥቂት ከሳምንቱ ክስተቶች

- ‹‹መልክ ጥፉን በስም ይደግፉ›› እንዲሉ አህባሾች ስማቸውን ቀይረው እራሳቸውን አህለ ሱና ሱፊ ማህበር እያሉ መጥራት ከጀመሩ ጥቂት ሰ ሆኗቸዋል። ይህ ማህበር መንግስት በአዳማ ጨፌና መሰል በሆኑት ትላልት አዳራሾቹ ውስጥ ከአህባሾች ጋር መክሮ ያቋቋመው መሆኑን ህ ሙስሊሙ ሁላ ያውቃል። ሰሞኑን ከነዚሁ አህባሽ የማህበሩ አባላት መሃል በኮልፌ ክ/ከተማ በወረዳ ስድስትና አካባቢው የሚገኙ ሙስሊሞ በኮልፌ ኮምፕሬሲቭ ት/ቤት ስብሰባ በመጥራት መድረሳ ልንሰራ ነው፣ እንዲህ ልናደርግ ነው፣ ምርጫው ፍትሃዊ ነው በሚቲ ተሳተፉ አሏ የማህበሩ ተወካይ ነኝ ...ወዘተ ሲል አቶ ሙባሪክ የተባለ ግለሰብ የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳዉን አሰምቷል። ይሁንና በቦታው የተገኘው ሙስሊ ማህበረሰብ መጀመሪያ እኛ የኢቲቪ ፍጆታ አንሆንም በማለት ካሜራ ቀራጩን ከአዳራሹ ያስወጡት ሲሆን በመቀጠል የሰውየውን ቅጥፈት በግጋለጥ እኛ አንድ ነን፣ ማንም አይለያየንም፣ እናንተን ማን መረጣችሁ፣ ከምንም ነገር በፊት ኮሚቴዎቻችን ይፈቱና መሰል ለቃሞችን አስተላልፈዋል። በቦታው የተገኘው የመንግስት ተወካይም ምንም ማድረግ ስላልቻለ የሰማውትን አስተላልፋለው በማለት አፍረው ሽልክ ወጥተዋል። አላሁ አክበር!!

<u>መልዕክት:</u> ይህን መሰል ስብሰባዎች በየቦታው በማድረግ ህብረተሰቡ የሚያዳምጣቸውን ግለሰቦች በማባበል እየመለመሉ የኡለማ ም/ቤቱን መመሪያ ደግፈው ስለምርጫው ቅስቀሳ እንዲያደርጉላቸውና ብዙሀኑ ሰምጂ ሳያውቁት አላማቸውን ሊያስፈፅሙባቸው እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው። ስለሆነም እነዚህ ሰም ቀይረው የመጡ አህባሾችንም እያደረጉት እንቅስቃሴ ሁላችንም በየአካባቢያችን በንቃት በመከታተል ተገቢውን ምላሽ ልንሰጣቸው ይገባል።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምፃችን

ቁ-21 | ዕለተ ሰኞ 07-12-2004

31ኛ ሳምንት የተቃውሞ ድምፅ !!


## ኮሚቴዎቻችን ይፈቱ!! ጥያቄዎቻችን ይመለሱ!!

**የህዝበ ሙስሊሙን ውክልና ይዘው ለምርጫው ፍትሀዊነት ሲታገሉ የነበሩ ኮሚቴዎቻችን ታስረው የሚደረግ ምርጫ በምንም መልኩ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም!! ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም!! ዲሞክራሲያዊ ሊሆን አይችልም!! ሀይማኖታዊ ሊሆን አይችልም!! በመሆኑም ለምርጫው መደረጉ ቅድመ ሁኔታው ኮሚቴዎቻችን መፈታታቸው ነው::**

## እኛ የአላህ ባሮች ነን!! ጌታችን ደግሞ አላህ ነው!!

በመላው ኢትዮጵያ የምንገኝ ሙስሊሞች ላስቀመጥናቸው ቀላልና ግልፅ የመብት ጥያቄዎች መከበር መታገል ከጀመርን እነሆ ለምንት ወራት ሆነን:: በዚህ ሂደት ውስጥ አምስት ወሳኝ የሆኑ ተፈታታኝ ግን ደግሞ በድል የተወጣናቸው ምእራፎች አሳልፈናል::

1. ገና ከጅምሩ ህዝባዊ ጥያቄዎቻችንን አንጥረን በማውጣትና ኮሚቴዎችን በመምረጥ እንዴት እንሂድባቸው ብለን ስንመክር ‹‹በአወሊያ ተማሪዎች ጥያቄ ሰበብ የራሳቸውን ድብቅ ፍላጎት ለማሳካት የተሰባሰቡ አክራሪዎች›› ተብለን ነበር:: ይህ ግን አላማችንንም ሆነ አካሄዳችንን ቅንጣት ታህል ሳይሸርፈው ሃገራችን አይታ የማታውቀውን ያልተደራጀ ግን ደግሞ መላው ሙስሊምን ያንቀሳቀሰ ሰላማዊ የመብት ትግል ማድረግ ችለናል:: ምዕራፍ አንድን በገጠሙን ፈተናዎች ሳንበገር በድል ተወጥተነዋል::
2. ለጥያቄአችንና ለሂደታችን አግባብነትና ሰላማዊነት መንግስት እያሞገሰና እያንቆለጳጳሰ በኮሚቴዎቻችንም ሆነ በሚዲያው በኩል እየነገረ በተግባር ደረጃ ግን መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልነበረበት የየካቲት 26 ቀጠሮ:: ይህ እለት ወሳኝ ምእራፍነቱ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለመንግስትም የነበረ ሲሆን ውይይቱ ባልተጠናቀቀበት ሁኔታ ኮሚቴዎቻችን ለመግሪብ ሰላት በወጡበት ከመንግስት በማይጠበቅ ስርአት በድብቅ በተሰ መግለጫ ‹‹ጥያቄዎቹ መመለሳቸውና ይህም ከኮሚቴው ጋር መግባባት ተደርሰበታል:: በመሆኑም ከዚህ በኋላ በአወሊያም ሆነ በሌሎ ቦታዎች የሚኖሩ መሰባሰቦች ህጋዊ አይደሉም›› ተባልን:: ለሃቅና ለህዝብ ፍላጎት በማደርና ለዓላማ በመፅናት በእድሜያችን አይተ በማናውቀው ቁርጠኝነት ውድ ኮሚቴዎቻችን ግን የውይይቱን ሙሉ ይዘት ከነሽፍጡ በመንገር ጥያቄዎቻችን በሚገባ እንዳልተመለሰ የመጨረሻ የሚባለውን ሰላማዊ ሂደት ለበላይ አካል ጥያቄዉን በማቅረብ እንደሚገፋበት በግልፅ አወጁ:: ይህ ሁለተኛው ምዕራፍ ከቀደመ የከበደ ቢሆንም በአላህ እገዛና በህዝባችን ፅናት በድል ተወጥተን አለደማሚ የሆነ ታሪክ በመስራት ቀጠልን::
3. ጥያቄአችንን ለመመለስ ፍቃደኛ ያልሆኑ ግን ደግሞ ስልታዊ በሆነ መንገድ ማኩላሸት ያልተቻላቸው አካላት በሶስተኛው ምእራፍ የተከተለ መንገድ አለምን ያስገረመ ዛቻና ማስፈራሪያ ነበር:: ‹‹ሰላማዊና ህገ መንግስታዊ›› ጥያቄ አቅራቢዎች ባሉበተ አፋቸው ‹‹ለሰላማዊ ሂ ፍላጎት የሌላቸው ፀረ ሰላም ቡድኖች›› እያሉ ህዝብን ለመለያየትና ሂደታችንን ያለውጤት ለመቅጨት የፕሮፖጋንዳ ሃይላቸውን በመ ተጠቀሙት:: በዚህ ምእራፍ ግን ሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን መላው የሃገራችን ህዝብ በመንግስት በማፈር ከሰላማዊው ህዝበ ሙስሊም ተሰለፈ:: መንግስት በሰራው አፍራሽ ፕሮፖጋንዳ ሰበብም ሂደታችን በርካታ እድገቶችን አሳየ:: እኛን የሚያስቆመን የጥያቄዎቻችን መመ እንጂ ባዶ ማታለልም ሆነ ዛቻና ማስፈራሪያ እንዳልሆነ በመግለጫው ማግስት ሁሉንም ያስገረመ የተቃውሞ ትእይንት በአንዋርና በሌ ቦታዎች ተካሄደ:: ምዕራፍ ሶስትን በድል አለፍነው::
4. የመንግስት ቀጣይ የሆነው ሂደታችንን የሚከላሸት እርምጃ ደግሞ ለማስታወስ በሚከብድ መልኩ መስጂዶቻችንን ተፈንክተውና ተቆር ደም በተለወሱና በስቃይ በሚያቃትቱ ቁስለኞች እንዲሞሉ ያደረገው የሃምሌ ስድስቱ የሌሊት ጨለማ አሰቃቂ ድብደባና እና እሱን ተከ የተባባሰው የህግ ጥሰት ነው:: አወሊያን መነሻ በማድረግና በአወሊያ የተወሰደውን ህገወጥ አሰቃቂ ድብደባና ክቡር መስጂዳችንን የማ ተግባር የተቃወመው የመዲናችን ህዝበ ሙስሊም ላይ በዛው ሌሊት ተመሳሳይ ኢ-ሰብዓዊ የህግ ጥሰት በሌሎችም መሳጂዶች ተፈፀመ:: የህግ ጥሰቱን ለመሸፋፈን ሚዲያዎቹን በሙሉ ከእውነትና ከህዝብ ተቃራኒ በማሰለፍ ‹ህጋዊ› መስሎ ለመገንት ሲሞክር በኩል ደግሞ ከዚህ እርምጃ በኋላ ‹‹መብቴ ይከበርልኝ›› የሚል ዝር የሚል ሰው አይኖርም አይነት መተማመን አሳድሮ ነበር:: የሚያስፈራው አላማ የሌለውን እንጂ እኛ በአላማ የተነሳነውን ሰላማዊ ንፁሃን ሙስሊሞችማ የሚያርስብን በደል የሚመጣልንን እርዳት እና የኛን ጥንካሬ ይጨምረዋል እንጂ እንደማይቀንሰው በቀጣይ ቀናት በሀገር አቀፍ ደረጃ ብሎም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የ ተቃውሞዎች ምስክር ናቸው:: አራተኛው ምእራፍም ብዙ ዋጋ ያስከፈለን ቢመስልም ከትግል ሂደት አንፃር ግን በድል የተጠናቀቀ ነበር
5. የመጨረሻ ያሉትን እና ይህን እርምጃ በመውሰድ መጪው ግዜያት በነሱ ቋንቋ ‹‹ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ውሏል›› እንደኛ አተ ደግሞ ‹‹የህዝብ ድምፅ የሚታፈንበትና መብቱ የሚረገጥበት›› ሁኔታ እንደሚቀጥል ማስተማመኛ ያሉትን እርምጃ ወሰዱ:: ይ የምንወዳቸውን፣ የምንናፍቃቸውን፣ በአካል ብቻ ሳይሆን በድምፅ እንኳን ሊርቁን የማንፈልገውን፣ ከነስቃያቸው አብረን መሆን ካል በነሱ ቦታ ራሳችንን ለመስጠት ቃል የገባንላቸው በምንም መስፈርት የማንደራደርባቸውን ውድ ኮሚቴዎቻችንና ዱአቶቻችንን አ በሆነ መንገድ በመያዝ ለእስር ዳረጓቸው:: ይኼኛው ምእራፍ ለነሱ ‹የሁሉ ነገር መጨረሻ› አድርገው ነበር የወሰዱት:: ለኛ ደግሞ ‹ ምዕራፍ ጅማሮ›› ነበር:: በእርግጥም እውነቱ ይህ ነው:: በትግል ሂደት የህዝብ ታማኝ ተወካዮች ህግ ተጥሶ ሲታሰሩ ይችሉ ይሆናል ‹‹የታሰሩት ይፈቱልን›› ወደሚለው ከተቀየር ትግሉ መዳከሙን የሚያሳይ ሲሆን ‹‹መብታችን ይከበር የታሰሩትም ይፈቱ›› እያልን አሁን ያለንበት ደረጃ ግን ትግሉ መቼም ሊቀለበስ በማይችል ጠንካራ መሰረት ላይ መቆሙን ማረጋገጫ ነው:: አምስተኛው ምእራፍ በድል ሰ በመሆኑም እያንዳንዱ የሚያጋጥሙን መሰናክሎችና የምንወስዳቸው እርምጃዎች ሰውኛ በሆነ ግምገማ ትክክለኛ ለመሆናቸ አንጠራጠርም:: ባሳለፍናቸው የትግል ወራት ያገኘናቸው ድሎችና የሚያሸማቅቁንም የሚያሳፍሩን አንዳችም ምክንያት የለም:: ይልቁንም በሰራ


ከዋናው ጋር ተመሳክሮ ትክክለኛ ቅጂ መሆኑ ተረጋግጧል

ፌርማ-21

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፍ.ቁ ፩፻፲፭ ሰኔ 12 ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

አዲስ አበባ

ወይዘሮ ምህረት ሀብተማርያም ተከሳሽ ከአቶ ገብረ ሥላሴ ገብረ ሕይወት ጋር ስለፈጸሙት ስለተፈጸመባቸው ሥርቆት ወንጀል ክስ ቀርቦ ተከሳሽ ክሱ ደርሶአቸው ከተረዱ በኋላ ጥፋተኛ አይደለሁም ብለው ክዱ። ከሳሽ ምስክሮቹን አሰማ። ምስክሮቹም ተሰምተው ተከሳሽ ሊጠይቁ የሚፈልጉት ምስክር ካለ ተጠየቁ። ተከሳሽ ምስክር የለኝም ብለው ተናገሩ። ከሳሽ ተከሳሽ ሊጠይቁ የሚፈልጉት ምስክር ካለ ተጠየቁ። 

004D

12-12-04

ETCLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ECLN


ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ETCLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሮ ቀርቧል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

-3-

የንግሥገሳና ሕይወታቸው አክሎአቸው "ሰላማዊነት" የሚለውን ቃንቃው ገጽ ÷ ከመሳው የነበው ዘር ሳይሳ ሁሉ የተካሄ መሰከንቱ የሚከለፕ፤ የሰዉነትና የማ ጉበሬነት መሆኑን ሰውየው ሰንጋንጉን የነው ልዩ መብት ጉበኖችም ሁሉ ፖለቲከኛ ገፀት የሚመሰክሉት ና የሚጸሐፉሙ መሆኑ ግልፅ።

ከመመሪ ግለሰ
ግንኙ ሰው ደተገኙ

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

የመሠረቱና ፀረ-ሰላም ኃይሎችን ድብቅ ዓላማ በአንቂዎቹ ለማስቀረት
ስልጠናው ወሳኝነት ይኖረዋል ። ››

ለመሆኑ መስሊመ ኑበረተ-ሰብ ከአያት ቅድመ አያቶቹ የተረከበው
ነባር ሐይማኖት የትኛው እንደሆነና ‹‹ በፀረ-ሰላም ኃይሎች ›› የተበረዘውና
የተከተለው የሐይማት ቀኖና ደግሞ የትኛው እንደሆነ እንዲያውቅና
እንዲገነዘብ የማድረግ ሀላፊነት ያለበት ማነው ? የኢሕአዴግ ሻማምንት
ወይስ የሐይማኖቱ ሊቃውንት? ይህ ዓይነቱ መንግስታዊ የሐይማኖት
ስብከትስ ምን አይነት ሕጋዊ መሰረት ይኖረዋል? እኔ በበኩሌ የዚህ ስሞነ
የኢሕአዴግ ‹‹ ሐይማኖተኛነት ›› እንቆቅልሽ እንደሆነብኝ አለሁ ።

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ



http://ethcriminalawnetwork.com/

አስደግፈው ሲያብራሩ እንዲህ ብለው ነበር ‹‹ ቅንጅትና ኢሕአዴግ አንድ ላይ ሊደራጁ አይችሉም ። ይችላሉ እንዴ ? (ከሰልጣኞቹ የተወሰነው ‹‹ አይችሉም ›› የሚል ሀብረ-ድምፅ ያሰማሉ) እንደዚሁም ውሃብያና ሱኒያ አንድ ላይ ሊሆኑ አይችሉም።››

ይህ ግልፅ የሆነ የሐይማኖት ጣልቃ ገብነት ነው ። አቶ ፀጋዬ ፖለቲካዊ እምነትና ግንዛቤያቸውን መሰረት አድርገው ቅንጅትና ኢሕአዴግ አንድ ላይ ተባብረው መስራት ፍፁም እንደማይችሉ ነግረውናል ። ይህ ምንም ይሁን ምን ከአንድ ፖለቲከኛ የሚጠበቅ ንግግር ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ የመንግስት ሹመኛ የተኛው የሐይማኖት ቡድን ከየትኛው የሐይማኖት ቡድን ጋር በጋራ መስራት ወይም አለመስራት እንደሚኖርበት ቀኖናዊና ሐይማታዊ ብይን መስጠቱ ፀረ-ሕገመንግስትና አስነዋሪ ድርጊት ከመሆኑም በተጨማሪ በአላዋቂ ሳሚነት ለተዘጠበት የማይዳርግ ተግባር ነው ።

ባለሰፊው ገፁ አዲስ ዘመን ጋዜጣም በርዕሰ-አንቀጽ ደረጃ ይህንኑ የሐይማኖት ጣልቃ ገብነት ሲያስተጋባ ነበር ። አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዘመስከረም 19/2004 እ.ኤ.አ. በመንግስት አዘጋጅነት የተከናወነውንና ሐይማኖትን ከፖለቲካ ያቀላቀለውን ‹‹ስልጠና ›› ሲያሞካሽ እንዲህ ይለናል ..

‹‹ሰሞኑን በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል በየደረጃው ለሚገኙ የእምነቱ ተከታዮች ለዐላማዎች ለአመራሮችና ለተደራጁ የእምነትና በእምነት ነክነት ላይ ያተኮረ ለ12 ቀናት የቆየ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል። የስልጠናው ዋነኛ ዓላማ በእኩልነት የሚያምኑ ፀረ ሰላም ኃይሎች መ.ስ.ሊ.መ. ንብረተ-ሰብ ትክክለኛውንና የሰላም ተጓዥ ሲያደርጉ የተረከበውን የእስልምና እምነት እንዲጠብቅ ማሳሰብ ነው። እምነቱን ለመከለስ ከሚንቀሳቀሱ አክራሪዎችና ዕንፈኞች አንዲጠበቅ ለማስገንዘብ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

አዲስ ዘመን ጋዜጣ በርዕስ አንቀፁ (በርስ -አንቀፁ የሚለው ይሰመርበታል)
ባስነበበው ዕሑፍ ላይ ገሃዳዊና ሊያሻማ በማይችል መልኩ ተንፀባርቋል ::

የፌዴራል ጉዳዩ ዶ/ር ሺፈራው ኃ/ማርያም በሐረር ሐረማያ
ዩኒቨርስቲ ውስጥ ተገኝተው ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮ ጠቅላይ ጉባኤ
ጋር በመሆን ከ700 መቶ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ንግግር ባደረጉበት ወቅት
‹‹ወሐቢያ›› ብለው በሰየመቱን ሐይማኖታዊ ስብስብ የነቀፉ ሲሆን ይህ
ቡድን ጥንታዊውን የእስልምና ሐይማኖት ለማደስ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን
ሲነገር ‹‹ ለአንድ ሺህ አራት መቶ አመታት ያህል ስናምንበት የቆየውን
አምነት ዛሬ እነርሱ መጥተው ሊለውጡት አይገባም ::›› ብለዋል ::

ዶክተሩ በአንድ ሐይማኖት ውስጥ የሚገኙና የተለያየ አስተሳሰብ
የሚያራምዱ ሐይማኖቶችን በመካካለል አንዱ የጥንታዊውን ሐይማኖታዊ
ቀኖና ጠባቂ ሌላውን ደግሞ የጥንቱን ቀኖና በራሽና ከላሽ አንደሆነ
አድርገው በመፈረጅ የቀኖና ተቆርቋሪ ለመሆን ያነሳሳቸው ምክንያት ምን
እንደሆነ ባይታወቅም ፍጹም ባለ ሐይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥ ገብተው
የነገሩ- ሐይማኖት ብይኖችን ለመስጠት መሞከራቸው ሕገ-መንግስቱ
ከሐይማኖት ረገድ የደነገገውን መርህ እየተላረሩ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ::
ይህ ደግሞ እጅግ አሳፋሪና ነውረኛ ተግባር ነው ::

የአዲስ አበባው የፍትህ ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ ዑመር ኃ/ማርያም
ደግሞ በመንግስት አዘጋጅነት ለአስራ ሁለት ቀናት የ[illegible]
ከሐይማት የቀላቀለው ‹‹ስልጠና›› ቡኋላ ቀቀበት ወቅት [illegible]
ግቢ ተገኝተው ‹‹ ለሰልጣኙ›› ባደረጉት ሰፊና አ[illegible]
ሐይማኖትን ከፖለቲካ ፣ፖለቲካን ከሐይማኖት [illegible]
ሲያሰሙ ተደምጠዋል :: በዚህ ሰፊ ዲስኩራቸው ውስጥ የሆነ
ሐይማኖታዊ ብይን በመስጠት በርሳቸው ግምት የተለያዩ አንጃ
የመሰሏቸውን የሐይማኖት ቡድኖች በጋራ ሊሰሩ አንደማይችሉ ብምሳሌ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

መስተዋለ ለብዙሃች ግርታን በመፍጠር እያጠያየቀ ይገኛል ። ይህ ክስተት በኢትዮጵያዊያን ህዝብ -መ-ስለ-ሚች ውስጥ መልካቸው የተለያዩ ውሸ-ንብሮችን መፍጠሩም አልቀረም ።

ኢሕአዴግ ፤ በህዝብ -መ-ስለ-ም ዘንድ ከመንግስት አለ-ታዊ ተዕዕኖ ነፃ እንዳልሆነ በሰፊው ከሚታመነው ተቋም (የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ) ጋር በጋራ በመሆን ባዘጋጀው በዚህ ሰፊ ዘመቻ አማካኝነት ፖለቲካን ከሐይማኖት የቀላቀለ የጥምቀት ስልጠናዎች ሲሰጥ ሰንብቷል ። « ስልጠና » በሚል በተሰየመው በዚህ መጠነ-ሰፊ የጥምቀት ዘመቻም የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ዶ/ር ሽፈራው ጋ/ማርያምን ፌዴሬሽኑ ሊሰጥን የኢሕአዴግ ሹማምንት በግንባር ተገኝተው ፖለቲካዊ ጥምቀትና ሐይማኖታዊ ሰበካን ያቀላቀለ ዲስኩር አስገራሚና እንግዳ በሆነ መልኩ ከማድረጋቸው በተጨማሪ ከሃገር ሊባኖስ « ተጋብዘው » የመጡ ባዕዳን ጎረቤትም ተገኝተዋል።

ከመስከረም 4/2004 ጀምሮ ለአስራ ሁለት ተከታታይ ቀናት በቆየው በዚህ «ስልጠና» ላይ በሺዎች የሚቆጠሩና አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላት የተመለመሉ ግለሰቦች የተገኙ ሲሆን (ከመመልመያ መስፈርቶቹ ውስጥ አንዱ መንግስትን ተቃውሞ የማያውቅ ነበር) በየዕለቱ የሚታሰበና ሰ «ሰልጣኞቹ» የሚታደል የውሎ አበል ነበር ። ለረር ለረማያ ዩኒቨርስቲ፤ ኮተቤ የሚገኘው መምህራን ኮሌጅ ፤ሲ.ኤምሲ አካባቢ የሚገኘው ኢትዮ-ቻይና ግቢ ፤አዳማ፤ባህርዳር ፤ሰመራ ፤አዋሳና ጋንቤላ የመሳሰሉት አካባቢዎች ደግሞ «ስልጠናው» የተሰጠባቸው ቦታዎች ነበሩ ።

የኢሕአዴግ መንግስት እያካሄደ ያለው ይህ የሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገብነት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ዶ/ር ሽፈራው ጋ/ማርያም እና የኢሴቲስ አለባው የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ፀጋዬ ጋ/ማርያም በደረጉት ንግግር እንዲሁም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

005E

በአቤቱታ አለሙ

ሃሳቱ ለአስተዳደር የተገኘ
ሃለፈ
ካሳሁን ታደሰ

እሁድ የተገኘ
አስተዳደር ሳህሉ
12-12-04

# የዚህ ሰሞኑ የኢሕአዴግ ‹‹ ሐይማኖተኛነት ›› እንቆቅልሽ

ራሱን በዓለማዊነት (Secular) ያስተዋወቀ የመንግስት አካል ሚዛናዊ ባለ ሐይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥ ተዘፍቆ የቀሳውስት/ የሸይኽችን ሚና ተክቶ ለመስራት እስከተንቀሳቀሰ ድረስ ከተጠያቂነት ሊድን የሚችልበት አንዳችም ቀዳዳ ሊኖር እንደማይችል ሁሉም በቀላሉ የሚስማማበት ጉዳይ ይመስለኛል ::

ዓለማዊ የሆነ የመንግስት ስርዓት እንዲህ አይነት እጅግ አሳፋሪና አይን ያወጣ ተግባር ላይ መሰማራት ከጅመረ ይህ ተግባሩ ሚናውን መለየት እንደተሳነው እንደሚያሳብቅበት ግልፅ ከመሆኑ በተጨማሪ ይህ ተግባሩ በህበረተሰቡ ውስጥ ሊያስከትል የሚችለው መከፋፈል እጅግ ውስብስብ መሆኑ አይቀርም በባል አጋናኝ የሚያስኝ አይሆንም ::

ሐይማኖት በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ መግባቱ ተገቢ እንዳልሆነ ሁሉ መንግስትም በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደማይኖርበት በኢፌዲሪ ሕገ -መንግስት በግልፅና በማያሻማ መልኩ የተደነገገና የሀያቅ ጉዳይ መሆኑን ሁሉም ያውቃል :: በመሆኑም የትኛውም የመንግስት አካል ሚዛናዊነት ባለ ሐይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥ እጁን ካስገባ ከሳይ የተመሰከተ ሕገ-መንግስታዊ ጋይለ-ቃል መጣሻ በማድረግ ድርጊቱን በፍጹ በጥር መቀጥቀጡን ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል ::


የኢሕአዴግ መንግስት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 3 ውስጥ ከተደነገገው መርህ ጋር ሊጣጣም በሚይችል መልኩ ፖለቲካን ከሐይማኖት የቀላቀሉ ግልፅ እንቅስቃሴዎችን ሲያካሂድ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

## ድርጅታዊ መዋቅር




ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

## 5. ማጠቃለያ

በአወሊያ አካባቢ የተነሳውና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተዛመተ ያለው ፀረ-መጅሊስ ተቃውሞ በሌሎች ፖለቲካዊ ኃይላት ከመጠለፉ በፊት አስተማማኝ እልባት ሊያገኝ ይገባል። ጉዳዩ እጅግ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ በመሆኑም "በሃይማኖት ጉዳይ አልገባም" የሚል ምላሽ መንግስት ቢሰጥም ችግሩ ግን ለዘለቄታው በዚህ መንግስታዊ አቋም የሚፈታ አይሆንም። ችግሩን መጅሊሱም አቅሙንና ይዘቱን መርምሮ ይፈተዋል የሚል ግምትም የለንም። በመሆኑም መንግስት በገለልተኛ የማኅበረሰቡ ተሰሚ ግለሰቦችን ሽማግሌዎች እንዲፈታ እገዛ የማድረግ ኃላፊነት (ፀጥታን የማስከበር ሂደት በመሆኑ) እንዳለበት እናምናለን። የቀረበው ምክረ-ሃሳብ መንደርደሪያ ታሳቢም ሆነ መዋቅር ለውይይት በር ለመክፈት ዕንጂ በመሰረቱ የዚህ ሸምጋይ አካል ዋና ሚና የተፈጠረው ችግር በሰላማዊና ፍትሃዊ መንገድ እንዲፈታ ማገዝ ነው።

የምክረ-ሀሳባችን መነሻ የሃይማኖት ጉዳይ በመሆኑ በሀገራችን የሃይማኖት ታሪክም ሆነ በወቅቱ ተጨባጭ ሂደት ላይ ያለ በቂ ጥናት በግርድፉ የሚቀርቡ ማጠቃለያዎች ለወቅቱ ተጨባጭ ቀውስ እንደ ዳራ መታየት ያለባቸው መሆኑን እያስታወስን ያቀረብነው ሀሳብ በፍጹም ሀገራዊ ስሜትና ወዳጅነት መሆኑን በማክበር እንገልጻለን። በዚሁ አጋጣሚ ይህን የሽምግልና መነሻ ሃሳብ እንድናቀርብ እድሉን ለሰጡን የመንግስት ኃላፊዎች በሙሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የዑለማዎች ም/ቤትም ከወጣትና አዛውንት ዳዒዎችና ሸሆች ተዋቅሮ በየምክርቤቶቹ ሥራ አስኪያጆች በሚመሩ ቅጥር ሠራተኞች የሚተዳደር መዋቅር እንዲኖረው ቢደረግ፤ የዑለማዎች ም/ቤት አባላትም በየአምስት ዓመቱ መስጊዶችን መሠረት ባደረገ፤ የመዝሀብ ብዙሃንነትን ባገናዘበ ውስን የምርጫ ሥርዓት (በሊቃውንት፣ በዳኢዎችና ምሁራን ብቻ የታጠረ) እንዲዋቀር ቢደረግ፣ የዑለማዎች ም/ቤት ፕሬዚዳንትም የሀገሪቱ መጅሊስ ሙፍቲ ሆኖ እንዲያገለግል ቢደረግ የተሻለ ሥራ ለመስራት የሚያስችል ይመስለናል።

ይህ አማራጭ ከደርግ ሥርዓት ከተወረሰውና ለውጥ ካልተደረገበት የመጅሊስ አደረጃጀት ተመራጭ የሚያደርጉት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ) ተግባራዊነቱ አዳጋች የሆነውን የመጅሊስ የይስሙላ መዋቅር ያስቀራል።
2ኛ) የምርጫ ወጭን ይቀንሳል።
3ኛ) የቁጥጥር ብቃትን ያዳብራል።
4ኛ) የተፋጠነና የተሻለ አገልግሎት ይሰጣል።
5ኛ) ዑለማዎች በመጅሊሱ መዋቅር ያጡትን ኃይል በማጎናጸፍ ሕዝቡን በአግባቡ እንዲመሩ ድርጅታዊ አቅም ይፈጥራል።
6ኛ) የዘመነኛ ትምህርትም ሆነ የሃይማኖት ግንዛቤ የሌላቸው ወገኖች በውክልናና ምርጫ ሽፋን ወደ መጅሊሱ መዋቅር የሚገቡበትን እድል ያጠባል።
7ኛ) ሙስናን የመቆጣጠር አቅም ይፈጥራል።
8ኛ) በአነስተኛ የሰው ኃይል ተጠያቂነት ያለበት ሥራ ይከናወናል።
9ኛ) አብዛኛው ሕዝበ ሙስሊም እንደ ማዕከል የሚያየው መስጊዶችን በመሆኑ በመስጊድ ዙሪያ ያሉ ኃይላት በመዋቅሩ መታቀፋቸው አሉታዊ ተግባራትን ለመቃኘት ያግዛል።

በአንጻሩ የዚህ አማራጭ ደካማ ጎኖች የሚከተሉት ናቸው፦

1ኛ) አማራጩ ላለፉት 20 ዓመታት ያልተለመደ በመሆኑ በጥርጣሬ የሚያዩት ኃይላት ሊኖሩ ይችላሉ።

2ኛ) በመዋቅር ግዝፈት ላይሆን በአገልግሎት ጥራት ላይ መሠረት ያደረገ በመሆኑ የመጅሊሱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለጊዜው ቁጥራቸው አናሳ ሊሆን ይችላል።



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ቦርዱ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውን ኃላፊነት ይጣልበታል፡፡

1. የመጅሊሱ አወቃቀር ለሕዝበ ሙስሊሙ የተቀላጠፈ አገልግሎት የሚሰጥ፤ ለመንግስት የልማት ግብም አጋር በሚሆንበት ሁኔታ የሚደራጅበትን መንገድ በባለሙያ አስጠንቶና የውጭ ተሞክሮዎችን አገናዝቦ ለውይይት ያቀርባል፡፡

2. በሃይማኖቱ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ የሃይማኖት ሊቃውንት ላእላይ ምክር ቤት ያደራጃል ወይም የሚደራጅበትን ጥናት ያቀርባል፡፡

3. የሃይማኖት ሊቃውንት አመራረጥ፣ ኃላፊነትና ተግባር፣ እንዲሁም የመጅሊሱን አባላት አመራረጥ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከት ረቂቅ ደንብ ያዘጋጃል፡፡

4. የፌደራል መጅሊሱን የየዕለት ሥራዎች እስከተወሰነለት የጊዜ ገደብ ድረስ ያከናውናል፡፡

ባላደራ ቦርዱ እነዚህን ተግባራት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያጠናቅቅ የጊዜ ገደብ ይጣልበታል፡፡

## ለ. አዲስ የመጅሊስ አመራር አባላት ማስመረጥ

ቦርዱ ያቀረበው የመዋቅር ጥናት እና ያዘጋጀው ረቂቅ ህገ-ደንብ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ውይይት ዳብሮ ተቀባይነት ሲያገኝ በዚያ አግባብ አዲስ የመጅሊስ አመራር ይመረጣል፡፡ የባለ አደራ ቦርዱም ስልጣኑን ለእርሱ ያስረክባል፡፡

## ሐ. ናሙናዊ መዋቅር

መወቅር ማዘጋጀት የባለ አደራ ቦርዱ ኃላፊነት ቢሆንም ከዚህ በታች በቀረበው ናሙና መሰረትም ቀጥተኛ የአደረጃጀት ለውጥ ቢደረግ የሚፈጠር ክፍተት የለም፡፡ መጅሊሱ ከቤተ ክህነት ወይም ከሌሎች ሃይማኖቶች አንጻር የሚታይ መንፈሳዊም ሆነ አስተዳደራዊ ኃላፊነት ያልተሸከመ በመሆኑ ማለትም በሥሩ ያሉቀራቸው ንብረቶችም ሆኑ ሰፊ የሰበካ ጉባኤ አባላት እንደሌሉት ማገናዘብ ከተቻለ የሚከተለው አደረጃጀት ቲግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡

ጠቅላይ ም/ቤቱም ሆነ የክልል ከፍተኛ ም/ቤቶች በጥንቃቄና በውድድር ሥርኣት በሚሾሙ ሥራ አስኪያጆች (ሴክሬተሪዎች) እንዲመሩ፤ ከታዋቂ ግለሰቦች በተውጣጣ ቦርድ እንዲተዳደሩ፣ የቦርዱን አባላትም ሆነ የሥራ ኃላፊነት የዑለማዎች ም/ቤት እንዲወስን፣



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ይገባል፤ በእርግጥ የኢስላም ሃይማኖት ለመሪዎችም ሆነ ለድርጅቶች ቅድስና ስለማይሰጥ ሕዝቡ መንፈሳዊ መሪዎቹንም ሆነ መሪ ድርጅቱን የሚታዘዘው በእምነቱ መሠረት ፀንተዋል ብሎ ሲያምን ብቻ ስለሆነ የይስሙላ መሪዎችና ድርጅቶች መንፈሳዊ ዋጋ አይኖራቸውም። የማስተባበርም ሆነ ፍትሃዊ የመቆጣጠር አቅም አይኖራቸውም። እስካሁን ያየነው አወቃቀር ብቃት ያላቸው ሰዎች ወደ መዋቅሩ እንዲመጡ የማያስችል፣ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ፣ በርካታ የሰው ኃይል የሚሻው፣ ለቁጥጥር አመች ያልሆነ፤ ለልማትና ዕድገት መደላድል ሊሆን ያልቻለ በመሆኑ መጅሊሱ እንደ ዘመናዊ የሲቪል ሰርቪስ መ/ቤት የሚዋቀርበት አግባብ መደራጀቱ የተሻለ እንደሆነ እናምናለን። በኛ ሃይማኖት የተቋሙ መዋቅር በራሱ መንፈሳዊ አይደለም። አላማውን ማስፈጸም በሚያስችል የትኛውም አግባብ ሊደራጅ ይችላል። ይህ ጊዜ የሚጠይቅ ሥራ በመሆኑ በወቅቱ የተነሳውን ጥያቄ ለማስተናገድና ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት የሚከተሉት ተግባራት ደረጃ በደረጃ ቢከናወኑ መልካም ናቸው ብለን እናምናለን።

## ሀ. የባላደራ ቦርድ ማቋቋም

ሙስሊሙ ህብረተሰብ በየትኛውም የአስተሳሰብ አቅጣጫና መስመር ላይ ቢሆንም አሁን ላለውና ያልተመረጠ የፌደራል እስልምና ጉዳዮች አመራር ያለው አመለካከት ጤናማ ባለመሆኑ ከተቋሙ የሚመጣን ማንኛውንም ለውጥም ሆነ መፍትሄ ለመቀበል ዝግጁ አይመስልም። በመሆኑም አዲስና ብቃት ያለው አመራር ወይም በባለ አደራ ቦርድ መተካቱ በመጅሊሱ ላይ ለሚታለመው ለውጥ መሠረታዊ መነሻ እንደሆነ ይሰማናል። ባለ አደራ ቦርዱም የሚከተሉትን አባላት ያቀፈ ቢሆን ለተግባሩ ስኬታማነት መልካም ነው ብለን እናምናለን።

1. በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ ተደማጭነትን ያላቸውን የሃይማኖት ሊቃውንት፣
2. በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ እውቅናና ቁቅባይነት ያላቸው ምሁራን፣
3. በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ እውቅናና ቁቅባይነት ያላቸውን ሚዛናዊ ወጣት የሃይማኖት አስተማሪዎች (ዳኢዎች)፣
4. እውቅ የሐገር ሽማግሌዎችን



ከዋናው ጋር ተመሳሳይ ነው
ፌርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከማጣት የመነጨ ናቸው—በዋነኛነት። መሰረታዊውን መሰረታዊ ካልሆነው በቀላሉ ሊያስገነዝብ የሚችል ኃይል ቢደራጅና የተራራቁ የሚመስሉ ኃይላት የእውቀት ብርሃን ቢያገኙ፣ ጠንካራና ሰብሳቢ ተቋም ቢዋቀርላቸው ጊዜያቸውን፣ እውቀታቸውንና ገንዘባቸውን በክርክርና በውዝግብ የማሳለፍ አላማ ያላቸው ብዙሃን አይደሉም። ኢትዮጵያውያኑ ሙስሊሞች በጥቅሉ ከ"እኩልነት" ከ"ፍትህ" ከ"ሚዛናዊነት" የተለየ አጀንዳ ይዘው ይነሳሉ የሚል ግምገማ የለንም። ቢሆንም ቢሆንም ተቋማዊ አስተዳደር፤ አቅጣጫ የሚያሳይ የሃይማኖት መሪ በሌለበት፣ ሁነኛ ሰብሳቢ በታጣበት ሂደት (ባለፉት 20 ዓመታት በዚሁ ሳጥን ውስጥ አልፈናል) ልማታዊ ያልሆኑ ሃይማኖተኞችና ሰባኪዎች መፈጠራቸው ሊያስገርም አይገባም፤ችግሩን በወቅቱ ለማረቅ ጥረት ያደረጉ ምሁራን አበረታች ጥናታዊ ሚና ያሳደረው ለውጥ ቀላል ባይሆንም ሁነኛ ተቋማዊ ድጋፍ ባለመቸሩ ተፈላጊው ግብ ላይ ሳይደርስ ቀርቷል።

ዛሬ ላይ ለመፈራረጅና ውግዘት ቅድሚያ ሳንሰጥ ተቋማዊና ትምህርታዊ ችግሩ ጎልቶ የሚታየውን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጉዳይ ሁነኛ እልባት ላይ እንዲደርስ ማድረግ ይጠበቅብናል። ችግሩም ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን የሚችል ነው የሚል ግምትም የለንም። መፍትሄው በርግጥ ዛሬ ላይ ቀላል ነው፤ ከዋለ ካደረ ግን መዘዙ ይከፋል እንጂ የሚድን አይመስልም። ለወቅታዊው ትኩሳት ሁነኛ የመፍትሄ አቅጣጫ መስጠት በሰከነ መንፈስ ችግሮቻችንን እንድናይ ፋታ እንደሚሰጠን እንገነዘባለን። መንግስት ሊቆጣጠረው የማይችል ክስተትም ይኖራል የሚል የዋህ ግምት የለንም። በዚህ አጋጣሚ መንግስት የተፈጠረውን ችግር በትእግስትና አርቆ አሳቢነት ለመፍታት የከፈተውን የውይይት አግባብ ሳናደንቅ አናልፍም።

### 3. የመፍትሄ አቅጣጫ

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ምክር ቤት የሰብሳቢነት ሚናውን መጫወት በሚችልበት መንገዱ ከተደራጀ በእስልምና ሃይማኖት ረገድ ለመንግስትም ሆነ ለሕዝበ-ሙስሊሙ ወይም ሕዝበ ክርስቲያኑ የሚያሰጋና ገንቢ ያልሆነ ሁኔታ ይፈጠራል የሚል ዕምነት የለንም። መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ የማይገባ ቢሆንም ሃይማኖቶች የሚደራጁበትን ሥርዓትና መዋቅር ከእምነቱ ተከታይ አዋቂዎች ጋር በመመካከር የመዘርጋት ኃላፊነት እንዳለበት እንገነዘባለን። የኢ/እ/ጉ/ጠ/ም/ቤት ከተቋቋመለት አላማ አንፃር የሚበጅ አደረጃጀት ሊኖረው



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ
http://etheriminalawnetwork.com/

ሳይሆን ምናልባት ስኬት እንደሆነ እንዲሰማው ተደርጓል። የመጅሊስ ከፍተኛ አባላትም ሆኑ በክልልም ሆነ በተዋረድ አሉ የሚባሉት አመራሮች ከተመሪው ጋር የሚያስተሳስራቸው ምክንያት ስለሌለ ምናልባት በበዓላት በቴሌቪዥን መስኮት ከሚያያቸው ጥቂት አመራር ውጭ ስለተቋሙና ሥራዎቹ ሕዝቡ የሚያነሳው ገንቢ ነገር የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። በውምራና በሐጅ ምክንያት ወደ ተቋሙ የሚፈሱ ሥራ ወይም ፀሎት ፈላጊዎችም ቁጭትና እንግልት ተበርክቶላቸው እንደሚመለሱ የአደባባይ ምስጢር ነው። የመጅሊሱ አመራር በምን መስፈርትና አሰራር እንደሚሾሙ ሕዝቡ የራሱ ግምገማ አለው፤ በድንገት ሲሰናበቱም እንደ ጥፋታቸው ልክ በሕግ ሲጠየቁ ወይም በስኬታቸው ሲሸለሙ አያስተውልም።

ይህ መንፈሳዊ አባት የሌለው ሕዝብ በተጠናከረ መዋቅርና ድርጅት (መጅሊስ) ሥር መሆኑ ያስከትላል ተብሎ ከሚፈራው (ለኛ ተጨባጭ ያልሆነ) ስጋት በላይ በተበታተነ መልኩ መተው ገንቢ አቅጣጫ እንዳልሆነ እንገነዘባለን። በመሆኑም የኢትዮጵያ እ/ጉ/ጠ/ም/ቤት ባለፉት 20 ዓመታት ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶች በአግባቡ አጢኖ በአዲስ አደረጃጀትና መንፈስ ቢዋቀር ለሁሉም ወገን የሚፈይድ ችግር ፈች ተቋም እንደሚሆን አንጠራጠርም። ዛሬ በሕዝበ ሙስሊሙ መካከል የሚታዩና ከጥቂት ዓመታት በፊት ጎልተው የታዩ ግና የመቀዝቀዝ አቅጣጫ አሳይተው በቅርቡ ዳግም ነፍስ ሲዘሩ ያየናቸው የአስተሳሰብም ሆነ የሥነ-ምግባር ልዩነቶች አስተማማኝ ተቋም ያለመኖሩ ውጤቶች እንደሆኑ እንገነዘባለን። ተቋሙ የሀገር ውስጥ ዑለማዎችንና ምሁራኑን ሳያማክር፣ የሙስሊሙን ሕብረተሰብ ንቃተ ሕሊናና የሃይማኖት ግንዛቤ ሳያጤን የወሳዳቸው እርማጃዎችም የችግሩ መነሻ መሆናቸውን ሳንጠቁም አናልፍም።

የኢስላም ሃይማኖት ትምህርት፣ ባህሪና ይዘት ከሀገር ሀገር የሚለያይ ባይሆንም፤ እንደ አዲስ በተሃድሶ የምንፈጥረው "ኢትዮጵያዊ እስልምና" ሊኖር የማይችል መሆኑን ብናምንም ከኢስላም አጠቃላይና ሁለንተናዊ መርሀ-ግብሮች መካከል በሀገራችን ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉትን ተፈጻሚ ከማይሆኑት አንጥሮ አውጥቶ አጠቃላይ አመራር የሚሰጥ ተቋም ካልተፈጠረ ሀሳብ በጉምሩክ ኬላ ሊገደብ አይችልምና ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ የአስተሳሰብ ትርምስ መታየቱ አይቀሬ ነው። ጅምሩን ተሸራርፎም ቢሆን አይተናል። በርግጥ ኢትዮጵያውያኑ ሙስሊሞች በመሠረታዊ የሃይማኖት አስተምህሮ ጎራ ለይተው ሲጋጩ አላስተዋልንም። የግጭት አጀንዳዎች (ከሃይማኖቱ አስተምህሮ ጎዳይ) መሠረታዊ ያልሆኑ፣ አብዛኞቹም በግዛት (ዋጁብ) ምህዋር ውስጥ ያልተካተቱ፤ ከእውቀት ማነስ፣ አባትና ሰብሳቢ



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የትምህርት፣ የፖለቲካ፣ የቢሮክራሲ፣ ከችርቻራ ውጭ ባለው የዘመናዊ ንግድ ተሳትፎ የ20 ዓመታቱ የኢ.አ.አ.ዴ.ግ. ሥርዓት እንኳ በተፈለገው ሚዛን ሊያነቃቃው ያልቻለበት ሁናቴ አለ። ለምን ብሎ መጠየቅ የዜግነት ኃላፊነት ጭምር ነው። ከፊል አካላችን መንቀሳቀስ ካቃተው እንደልብ መራመድ የሚቻል አይደለም። በዚህ ረገድ ልማታዊ የሃይማኖት ተቋም ሙስሊሙ ቢሳናፀፍ ለመንግስትና ለሀገር አጋዥ እንደሚሆን ሕዝበ-ሙስሊሙ ቢያምንም ለዘመናት ኢስላምና ሙስሊሞች የኢትዮጵያ ፈታኝ ኃይላት እንደሆኑ የሚቀርበው የታሪክ፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ሀያሴ አሁንም እንደ ጉንፋን እያገረሸ የመንግስትን ጤናማ ግብ ሊያሰናክል እናስተውላለን። በሃይማኖት ተቋማት መካከል ለመገናኛ ብዙሃን ሽፋንና ግብአት ካልሆነ በቀር ልማታዊ ውይይት፤ ቀና መንፈስ እንዲፀናና በጠላትነት መተያየት እንዲከስም የሚያስችል መዋቅራዊ ለውጥና ተሀድሶ እውን አልሆነም። የአንዱ ዕድገት የሌላው ውድቀት እንደሆነ የማሰብ አባዜ ተጸናውቶናል። በርግጥ ይህ ወንጌላዊም ቁርአናዊም መንፈስ ነው ብለን አንገምትም። ሃይማኖት መተባበርን፣ ፍቅርን፣ እርቅን...መስበክ ሲያቆም "ሃይማኖት" ሳይሆን ሌላ ስያሜ ቢሰጠው የተሻለ ይሆናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ችግር ይበልጡኑ ውስጣዊ እንደሆነም እንገነዘባለን። ውስጣዊውን ችግር ለመፍታት ግን ውጫዊ ኃይላት ሚና የላቸውም ለማለት አንደፍርም። በርግጥ በኦርቶዶክስ፣ በካቶሊክም ሆነ በወንጌላውያኑ አብያተ ክርስቲያናት የተደራጀ ተቋምና ሥርዓት በመዋቀሩ በእምነቱ ሥር ለሚነሱ ውዝግቦች ተቋማዊ ምላሽ የመስጠት አግባብ ሊኖር ይችላል። ሁነኛ ተጠሪ አለ ብለን እናምናለን። የ34 ሚሊዮን ሙስሊም ጉዳይ ግን በሚያደናግር፣ መቆሚያ በሌለው የችግር አዙሪት ውስጥ ሲተራመስ መቆየቱ የዓመታት ሂደት ነው። ሕዝበ-ሙስሊሙ ከመንግስት ጋር በዚህ ረገድ መጠያየቅና መወያየት የሚቻል ስለማይመስለው ወይም በሌላ ምክንያት አጀንዳውን ትቶት ቆይቷል። የ1987 የአንዋር መስጊድ ግርግር የፈጠረው ጠባሳም በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ሕዝበ-ሙስሊሙ ከተቋሙ ጋር ቀጥተኛ መንፈሳዊ ግንኙነት ስለሌለውም ቢረሳው አያስገርምም። ለመሪ ድርጅቱ መዋጮ አይከፍልም፤ ከተቋሙ የሃይማኖት ትምህርትና ሰበካ ወይም አመራር አይሰጠውም። የልማት አስተዋጽኦም ሆነ ተሳትፎ እንዲያደርግ ሁናቴዎች አልተመቻቹለትም። የሙስሊሙ ተቋም በተከታዮቹ መካከልም ሆነ ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር እንዲሁም ከመንግስት መዋቅር ጋር በጋራ ጉዳዮች የሚያተጋው የግንኙነት ድልድይም አልተዘረጋም። ይህ በእውን የሚታይ ምናባዊ ድልድይ (ተቋሙ) ከናካቴው ቢሰበርም የሚመጣ ጉዳት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አይደለንም። በርግጥ የጎረቤት ሃገራትና የዓረቡ ዓለም የለውጥ አየር ውጤት የስትራቴጂስቶች ኢላማ እንደሚሆኑ ብናጤንም ኢትዮጵዊው ሙስሊም ሕገ መንግስታዊ መብቶቹ እስከተከበሩለት ድረስ የአፍሪካ እንጂ የመካከለኛው ምስራቅ አካል ይሆናል የሚል ግምት የለንም።

መንግስታችን የኢስላምን እና ሙስሊሞችን መብት ለማስከበር በወሰዳቸው እርምጃዎች በዓለም አቀፍ ኃይላት የደረሰበትንና ሊደርስበት የሚችለውን አይዲዮሎጂያዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና፣ የኃይል አሰላለፍ ሚዛንን የማስጠበቅ ፈተና፣ አህጉራዊ ሚናና የሀገር ተጨባጭ ገፅታ ውጥረት እንገነዘባለን። ፖለቲካዊ ውሳኔዎች አንዱን ወገን ሲያስደስቱ ሌላውን እንደማያስደስቱ፣ ለሀገር አጠቃላይ ጥቅም ሲባል ከዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ (ከኃያላኑ) ጋር የሚያጋጩ ውሳኔዎች እንደሚንሸራሸሩ፣በአንጻሩም የሀገራችንን የሃይማኖት ስብጥር ያመሳከሩ መንግስታዊ ውሳኔዎች የውጭ ኃይላትን አንዴ ሲያስደስቱ በአብዛኛው ሲያስከፉ የቆዩ መሆናቸውንም እንረዳለን። ተራው ሕዝብ ግን እነኝህን ወሳኝ እውነታወች ይገነዘባል ወይም እነደ መጅሊስ ባሉ ተቋማት ይህ ግብአት በሚገባ ቦታውን እነዲይዝ ሥራ ተሰርቷል ልንል አንችልም። መንግስት እንደማንኛውም ሴኩላር መንግስት ሁሉንም ወገን ኃይላቱ በሚሹት ምጣኔ ሊያስደስት እንደማይችልም እናጤናለን። የህዝበ-ሙስሊሙ ጥያቄም ወሰኑን ያልተላለፈ ሀገሪቱ የበርካታ ብሔር ብሔረሰብ እንዲሁም ሃይማኖቶች መጠለያ መሆኗን ያልዘነጋ መሆን እንደሚኖርበትም በሚገባ እናምናለን።

## 2. የወቅታዊ ሁኔታ ትንተና

ሕዝበ ሙስሊሙ ወይም የሕዝበ ሙስሊሙ ከፊል ኃይላት እምነታቸውንና ማኅበረሰባዊ ሕልውናቸውን በዋነኛነት የሚመለከቱ አጀንዳዎችን ለመንግስት አቅረበዋል የሚል ግምገማ የለንም። ወቅታዊ ያልሆነ፣ የሌሎች እምነቶችን ሕልውና የሚፈታተን፣ ሕገ መንግስቱን አደጋ ላይ የሚጥል ጥያቄም አልቀረበም። አስተማማኝ መሪ ድርጅት ካለማዋቀር ጋር የተያያዘ ጊዜያዊ ችግር እንጂ የመንግስትን አጋርነት የዘነጋ የግብ መሳከር ሊኖር እንደማይችል እንገምታለን። ችግሩ ሳይፈታ እድሜ ከተሰጠው ግን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ማምራቱ ላይቀር ይችላል።

ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ምንም እንኳ የቁጥር ችግር ባይኖርበትም በሚና አናሳ መሆኑ የጤናማነት ምልክት እንዳልሆነ አርቆ አሳቢዎች ያስተውላሉ። የሙስሊም ኢትዮጵያውያን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የ1966ቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ ያስገኘው ታላቅ ትሩፋት የሺህ ዓመታት የመንግስትና የሃይማኖትን ጋብቻ ፍች ማብሰሩ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ጅምሩን ደርግ ወደ ሌላ አለማዊ ፅንፈኝነት (ወታደራዊ ሥርዓት) ባይቀለብሰው መልካም ነበር። አልሆነም። ይሁንና በእምነትና ሃይማኖት ካርድ ሳይሆን በዜግነት ላይ የተመሠረተ አለማዊ ኢትዮጵያ መገንባት አማራጭ የሌለው፣ በማንኛውም ወገን ሊቀለበስ የማይገባ አቅጣጫ መሆኑን እናጤናለን።

እነሆ ከላይ እንደጠቀምነው ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ያለፉት ሥርዓታት ሲሸፋፍኑት የቆዩትን ተጨባጭ የብሔር ብሔረሰብና የሃይማኖት ኢ-ፍትሀዊ ግንኙነቶች ሰብሮ ለመውጣት ያስቻለ ሕገ-መንግስት ሲያፀድቅ ከታሪክ የተወረሱ የተዛቡ ግንኙነቶችን ለማረም መሆኑን በሕገ-መንግስቱ መግቢያ ላይ አስፍሯል። በዚህ አቅጣጫም ለዓመታት ተጉዟል። መንግስት በሃይማኖት፣ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ እንደማይገባ፤ መንግስታዊ ሃይማኖትም ሆነ ሃይማኖታዊ መንግስት እንደማይኖር አውጇል። ይህ በተለይ ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የነፃነት በር ነው።

በታሪክ የተወረሱ የታዛቡ ግንኙነቶች ምን ዓይነት ገፅታ አላቸው? ሚዛናዊ ግንኙነት እንዲኖር ምን መደረግ አለበት? የተበላለጡ የጎብረተሰብ ክፍሎች በተመጣጣኝ እርከን ላይ እንዲደርሱ፤ ወይም ክፍተቱ ሰፍቶ ጥርዙቱ (marginalization) ልክ እንዳያጣ ምን እርምጃ ይሻል ወዘተ የመንግስት ጭንቀቶች እንደሆኑ ይሰማናል። በርግጥ የማትጊያ እርምጃዎች ለሴቶችና ለታዳጊ ክልሎች ሲደረጉ እንደነበርና አሁንም በዚሁ አቅጣጫ የተተለሙ ፕሮግራሞች እንዳሉ አይካድም። ግና በሃይማኖቶች ሚናና ግንኙነት ረገድ የተብላላ አቅጣጫ የተወሰደ አይመስልም። ዳሩ ግን የዚህች ሀገር ችግር ከሃይማኖትና ከዚሁ ጋር ከሚተሳሰሩ ባህሎችና አመለካከቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው እንደሆነ ይሰማናል። በሽግግር ላይ የምንገኝ ሕዝቦች እንደመሆናችን ወደ ጥንቱ አለያም ወደ ተጀመረው የለውጥ ፍሰት ልናመራ እንደምንችል ይገመታል። በርግጥ ኢትዮጵያዊው ሙስሊም ወደ ሃይማኖታዊ መንግስት ብኸታ ሊሄድ ይችላል ከሚለው ስጋት ጎን ለጎን ክርስቲያናዊ መንፈስ ወደ ጥንቱ መሲሃዊ መንግስት እንዳይመለስ መስጋቱ ታሪካዊም ፖለቲካዊም ምሳሌያ አያጣም። ስጋቱ ቀላል አይደለም። በታሪክ የተንሳፀፍኩት ፍጹማዊ የበላይነት ተሸራርፎብኛል ብሎ በፅኑ በሚያምነው ኃይልና እኩልነት እሻለሁ በሚለው ኃይል መካከል የተዳፈነና አደባባይ መውጣት ያቃታቸው ወይም እየወጡ ያሉ ስሜቶች በወጉ ካልተባለሱና ሁሉን አቀፍ አቅጣጫ እንዲይዙ ካልተደረጉ ሀገራችን የተያያዘችውን ሕዳሴ በሙሉ ኃይል እንደተጓዘች እንቅፋት ላለመሆኑ እርግጠኞች

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መሆኑ እሙን ነው። ይሁንና ከታሪክ የወረስናቸው አስተሳሰቦችና የአፈጻጸም ግድፈቶች እንዲሁም ሀገሪቱ በማሳየት ላይ ያለችው ለውጥ ያልተመቻቸው ኃይላት ሀገሪቱን ወደ አሀዳዊ መንግስትና የአንድ ሃይማኖትና ባህል ጥንታዊ የበላይነት ለመመለስ በሚያደርጉት ጥረት የመንግስታችን ወሳኝ ድል እነዳይቀለበስ ወይም እነዳይሸራረፍ እንሰጋለን።

የአክሱማዊት ኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ እርሱን በሰፊው በተካው ሰለሞናዊው ሥርወ መንግስት (1285-1974) ስለ ሃይማኖት ነፃነት ተጠቃሽ መረጃ ማቅረብ ለታሪክ ሰዎች አዳጋች ይመስለናል። በርግጥ በ7ኛው ክፍለ-ዘመን አክሱማዊው ንጉስ (አስሀማ-ነጃሺ) ለመጀመሪያው የኢስላም አባላት የሰጠው ዲፕሎማሲያዊ ከለላ በታሪክ ከሚጠቀሱ የዴሞክራሲ መገለጫዎች ዋነኛ በመሆኑ ታላቅና የመላው ኢትዮጵያውያን ኩራት ነው። የሃይማኖተኞች ችግር እንጂ የሃይማኖቶች ግጭት የለብን መሆኑን አመላካች ክስተት ነው። ስለ ክርስትናና ኢስላም ኢትዮጵያዊ ግንኙነትም ስንገልጽ ይህ ታሪካዊ እውነታ በዋነኛነት የአስተሳሰባችንን ቅኝት እንዲመራ እንሻለን። በዛጉዌ ሥርወ መንግስትም (1130-1285) በክርስትናና በኢስላም ኃይላት መካከል የነበረው ግንኙነት ከወራሹ ሥርዓት አንጻር የተሻለ ገጽታ እንደነበረው አይካድም። በዚህ ወቅትና በአክሱማዊት ኢትዮጵያ የመጨረሻ ዘመነ-ዓመታት ኢስላም በኢትዮጵያ እንደ ሰሜኑ ክርስትና መንግስታዊ መዋቅር የዘረጋበት መሆኑም ይታወቃል። የሸዋ ሱልጣኔት በቀጣይም የኢፋት ሱልጣኔት፣ የአዳልና የሐረር፣ የቤኒ ሻንጉል እንዲሁም የጂማና የግቤ ኦሮሞ-ሙስሊም ሥርዓቶች፣ በወሎ የወረ ሼኾችና የማመዶች መስተዳድር፣ በዘመነ መሳፍንት የታየው አፍቃሪ ሙስሊም የኦሮሞ ባላባቶች ሥርዓትና ወዘተ ሀገራችን ክርስቲያናዊ ብቻ ሳይሆን ኢስላማዊ ባህሪ የተላበሱ ሥርዓቶችን ጎን ለጎን ያየች ለመሆኗ አብይ ማስረጃዎች ናቸው።

ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአፄ-ምኒልክ "ኢምፓየር" እስከተገነባበት ባለው ዘመን ይህች ሀገር ይበልጥኑ ደጋማ በሆነው አቢሲኒያና በቀዳ ስፋት በነበረው ቆላማው ኢትዮጵያ በይበልጥ በሚኖሩ ሙስሊሞች መካከል ዘመን ተሻጋሪ ግጭት (ዋነኛ ምንጩና ምክንያቱ ሃይማኖት ወይም ኢኮኖሚ ወይም የሁለቱም ድምር ስለመሆኑ መሞገት አንሻም) መስተናገዱ አይካድም። በአንድ ሃይማኖት ሥር የተነሱ የቅኝና የሥነ-መለኮት ግጭቶችን በውይይትና በመቻቻል የማስተናገድ ሰፊ ባህል እንደሌለን ሁሉ ከኢስላምና ሙስሊሞች ጋርም የተለየ ግንኙነት አልነበረም። ሙስሊሞች የፖለቲካ ኃያልነት ባሳዩበት ዘመንም (በቂ ጥናት ባይኖረንም) ከእምነት ገደብና መረብ ወጥቶ ሌላውን እንደ ዜጋ የማቀፍ መንፈስ አላየንም።



http://ethcriminalawnetwork.com/

# በወቅታዊው የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ዙሪያ የተከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ የቀረበ ምክረ-ሀሳብ

2004

## 1.መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የአይሁድ፣ የክርስትና የኢስላምና የባህላዊ እምነቶች ማህደር መሆኗ ይታወቃል። ወቅታዊው ሃይማኖታዊ ውዝግብ በአንደኛ ደረጃ ከእምነት ነጻነት ታሪካዊ ትውፊታችን ጋር ጥብቅ ግኑኝነት ያለው ነው። በሁለተኛ ደረጃ ኢስላምና ሙስሊሞች በሀገራችን የፖለቲካ ሥርአታት ከታዩበትና ከሚታዩበት መነጽር ጋርም የሚቃኝ ነው። በመሆኑም ከነኝህ መነሻዎች አንጻር መንደርደሪያ ሃሳብ ማስፈር በወቅቱ ለተፈጠረው ተዳግሮት ጽንሰ ሃሳባዊ መሰረት ይሰጣል ብለን በማመናችን ሰፋ ያለ ቦታ ሰጥተነዋል።

የሃይማኖትና እምነት ነጻነት አስተሳሰብ ከዴሞክራሲ ሥርዓት ምስረታ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው በመሆኑ የዴሞክራሲ ግንባታ ላይ በሚገኝ ሀገር የሃይማኖትና የእምነት ነጻነት ተገንጥሎ ሰፊ ታሪካዊ መሠረት ያለው እንደሆነ ማቅረብ ቀጣይነትና ዘለቂታ ላለው የሃይማኖትና እምነት ነጻነት የሚፈይደው ግብአት አናሳ ነው። እንደውም ሕዝባችን ያልወረሰውን ባህል እንደ ባህሉ አካል አድርጎ አግዝፎና አስውቦ ማቅረብ ለለውጥና ተሀድሶ እንዳይንቀሳቀስ ጋሬጣ ሊሆን ስለሚችል መጠንቀቁ ብልህነት ነው። በዘ.ህ ረገድም ተጨባጭ ለውጥ እውን እንዳይሆን የሚፈጠር ዲፕሎማሲያዊ አጥርም ይመስላል። ሀገራችን ለዘመናት ብሔር፣ ብሔረሰብና ሃይማኖት ተኮር ያለመግባባት ብሎም ግጭት ያላስተናገደች ይመስል አ.ህ.አ.ዴ.ግ. ሀገሪቱን በጎሳ ከፋፍሎ አዲስ ችግር ፈጥሯል፤ የሃይማኖት መቻቻል በሰፈነበት ሀገር የሃይማኖት ግጭቶችን አፋፍሟል የሚሉ ትችቶችን ደጋግመን እንሰማለን። ይህ ያለፉ ታሪካችንን አስረጅ ሰነድ ሊቀርብላቸው በማይችሉ "ተረቶች" የመሪጉንተን ውጤት ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ የዘማናት የተዛቡ ግንኙነቶችን በመሰረቱ ችግሮችን ሥልጣን ላይ ባለው መንግስት፣ ፖሊሲና አዋቃቀር ላይ ሙለጠፍ ሥርአቱ መንግስቱን የመዋቢያ ስውር ስልት መሆኑን እንገነዘባለን። መንግስት ለሚመሰረት ደረገው ሕገ-መንግስታዊ ትግል የሃይማኖት ጥያቄ ወደማመጣጠን ደረጃ እያደረሰው መሆኑንንም እናጤናለን። ፌደራላዊ ሥርዓቱም ለብሔሮችና ብሔር ብሔረሰቦች በሰጠው ሰፊ የእድል ሕገበ ሙስሊሙ ኢትዮጵያ ተጠቃሚ



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

ተከሳሽ ጠበቃ የተገኙ
አቶ ሙሉጌታ ወ/ሩፋኤል

ከማረሚያ ቤቱ ከመጡት ጋር ስለመጡበት አግባብነት ሁኔታ መከላከያ ምስክሮቻቸው ስለመሆናቸው ያረጋገጠ ሲሆን ከአሁን በፊት ያልተሰሙ ስለመሆኑ ገልጸዋል

→ ይህ ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት ተከሳሽ ጠበቃ ያቀረቡትን መከላከያ ምስክሮች ለመስማት ቀጠሮ ሰጥቶ ነበር ነገር ግን ምስክሮቹ ሳይመጡ ቀርተዋል ስለዚህ ዛሬ ምስክሮቹ ካልመጡ ክርክሩ ይቋረጣል ብለን ነበር

→ የፍርድ ቤቱ ሂደት መከበሩንና ከተሰጠው ~~ትዕዛዝ~~ አንጻር ከሳሽ ጠበቃ ምስክሮቹን ለማቅረብ ጥረት ማድረጋቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምስክሮቹ ከመጡ ክርክሩ ይቋረጣል ብለን ነበር

→ ሆኖም ከሳሽ ወይም ጠበቃቸው ስለሌሉ ክርክሩ ሊቋረጥ ስለማይችል ምስክሮቹን ማሰማት ያስፈልጋል

— የአቃቤ ህግ ማጠቃለያ —
ማጠቃለያ H - አቃቤ ህግ

→ ይህ ጉዳይ የተጀመረው ጉዳዩን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለማየት ስልጣን ካለው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው ከዚህ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይዛወራል ተብሎ ስለታሰበ ነው ጉዳዩ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዛወረው

→ ተከሳሾቹን መቃወሚያ አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት ተከሳሾቹ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው ብለው ስላመኑ ክርክሩን ለመቀጠል ፈቃደኛ ሆነዋል

→ አቃቤ ህግ ባስቀርባቸው ቀንና ሰዓት ምስክሮቹን ማሰማት ቢችልም ምስክሮቹን ለማሰማት ፈቃደኛ ስላልሆነ ክርክሩ ይቋረጣል

→ ከሳሽ ጠበቃ ምስክሮቹን ለማሰማት ፈቃደኛ ስላልሆኑ ክርክሩ ይቋረጣል

ተከሳሽ ጠበቃ የተገኙ
አቶ ሙሉጌታ ወ/ሩፋኤል

ECHR

ከማረሚያ ቤት ተመላክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

* ክሳሱ ለዐት የተገኙ ክሠሠሩ ግለሰብ

⇒ ስለሆኖም ወንጀሉ ከሚፈጸምበት ቦታ ሸሽቶ ወይም ከሚፈጸምበት ጊዜ በኋላ ከሚፈጸምበት ቦታ ተገኝቶ ሲያዝ ከሚከሰስበት ወንጀል ጋር ተያያዥነት ያለው ወንጀል ፈጽሞ ከሆነ ተመሳሳይ ቅጣት ይጣልበታል።

⇒ የጣቃ፡ ሃይል የሌለ ጽሕፈት ቤት ሠራተኛ ከሥራ ወይም ተግባር ጋር በተያያዘ ጉዳይ

⇒ ሐሰት የፃፈ፣ የተጻፉ፣ የተሠሩ፣ የሰረዙ፣ የቀየሩ፣ የሠራተኛ ማህተም ወይም ፊርማ ያለበት ነጭ ወረቀት የሰጠ ወይም ያስረከበ ሃላፊ ነው ተብሎ ይገመታል።

⇒ ጉቦ ሰጭ፣ ጉቦ ተቀባይ፣ ሰላይ፣ አስመሳይ፣ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ምስክር፣ ተርጓሚ፣ ባለሙያ፣ መርማሪ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ዳኛ ወይም ሌላ ማንኛውም ከሥራው ወይም ከሙያው ጋር በተያያዘ ሐሰተኛ ሰነድ ያዘጋጀ ወይም ያስረከበ ሰው ነው

⇒ የሥራቸው የአካባቢው ሕዝብ ተወካዮች ከሆኑ ሰዎች ጋር ሲመሳጠሩ ከሆነ ሰዎች ነው

⇒ ወይም ትክክለኛ የመንጃ ፈቃድ ያለው ሆኖ የመንጃ ፈቃድ ያልተሰጠው ሰው ነው

* ሐሰተኛ ሰነድ የተገኙ ክሠሠሩ ግለሰብ

⇒ የመንግስት፡ ወይም የሕዝብ ድርጅት መሪዎች የመንግስት ሰነድ፣ ሕትመቶችን ሰነዶች የመንግስት ማህተም ፊርማን ያጭበረበሩ። ወይም የሕትመቶችን ሐሰተኛነት መከላከል ሃላፊነት ሳይወጡ ቀርተው ከሆነ ተመሳሳይ ቅጣት ይጣልባቸዋል ወይም ሌላ ማንኛውም ሰነድ ያዘጋጀ ወይም ያስረከበ ሰው ነው

⇒ ጉዳዩ ከሚመለከተው ሰው ጋር ተመሳጥረው ሐሰተኛ ሰነድ ያዘጋጁ ወይም ያስረከቡ ሰዎች ናቸው

⇒ የሕትመቶች መከላከል ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች ሐሰተኛ ሰነዶችን ለይተው ሳያሳውቁ ቀርተው ከሆነ

⇒ ሰነዶቹ ሐሰተኛ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው ባለሙያ ወይም ከሚመለከተው ሰው ጋር ተመሳጥረው ሐሰተኛ ሰነዶችን ያዘጋጁ ወይም ያስረከቡ ሰዎች ናቸው

⇒ ሰነዶቹ ሐሰተኛ ስለመሆናቸው ከሚመለከተው ባለሙያ ወይም ከሚመለከተው ሰው ጋር ተመሳጥረው ሐሰተኛ ሰነዶችን ያዘጋጁ ወይም ያስረከቡ ሰዎች ናቸው

LCHN

http://ethcriminalawnetwork.com/

LCEN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ECLN

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

-8-


የሃርሰን ገጽታ ያለዚህ ሌላ ያንቀጽመልዕ።


ኢለላማል የመገለገል ትርጉሙም ያለው ስለሆነ ይህንን የሚከላከል የመንቀሳቀስ ነጻነት ሲሆን ይህንን ነጻነት የመገደብ ሙከራ ደግሞ ሕገ መንግስቱን የሚጻረር ነው።


በአጠቃላይ ይህ ሁሉንም መሸፈኛ፣ ኢለላማል ስለሆነው ዘርፍ ሳይለይ ያንዳዘራሁ ጽርፈት፣ የሀሳብንም ርትርነት የመጠቀም የመንቀሳቀስ መብት መሆኑን ያለን የመገለገል የፈጠራቸው ፈጠራ ሳይ ያንዳንዱ ሰው ስለሆነ ያለን ሰው ያንዳንዱንም ሰው ያንዳንዱንም ቀጥሎ ያለን ሰው ያንዳንዱንም ሰው ያንዳንዱንም ሰው ያንዳንዱንም

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ECHR









ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሳጥር ቁጥር ቤተ-ጊዮርጊስ
አስመስክሮ ስለመስጠት ማመልከቻ

ለጉዳዩ ይሰጠን ዋስትና ጠቅሶ ከሣሽም፣ ተከሳሾቹ ንጉሥ ሆነ መንፈሳዊ ሰው፣ ተከሰሰበት ሆነ ከሳሽ ገዳም፣ መጓጓዣም ፓስፖርት የሌለው ዘርፈን ስለሆነ በአቃቤ ህግ ጉዳ-መከሳት (ቁጥር) ላይ ሆነ ሌሳው ይጓጓዘተሰጠ ክርክር የመጣራቸው ጉዳት የመለተጸጸር የመሰጠውት ግዛት፣ ወይም ሳይ-ቢፓ ለርሱ ጠንቱ የመቆር ጉዳ-ከሣይሆን ፣ በገሳት-ግዛት ከዘመት ተጠርቦ የዘርጋጠኑ ተጠቃሚ ይታየ~~ተጠቃሚ~~ ይሰጠ ይሰጠ ይሰጠ

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

The Federa Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution

http://ethcriminalawnetwork.com/

Ⓐ —1—

ጉቦ ተቀብለዋል ለተባሉ የመንግሥት ሓላፊዎች ጥቆማ ስለመስጠት

"ጉቦ ተቀብለዋል" ስለተባሉ የመንግሥት ሓላፊዎች ጥቆማ ስለመስጠት የወጣው አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፭/፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ጉቦ ተቀብለዋል ስለተባሉ የመንግሥት ሓላፊዎች ጥቆማ ለመስጠት የሚፈልጉ ሰዎች ጥቆማቸውን ለማን እንደሚሰጡ ግራ ተጋብተው ስለነበር ጥቆማ ሰጪዎች ጥቆማቸውን ለሚመለከተው አካል በቀላሉ እንዲሰጡ ለማስቻል ይህ ማስታወቂያ ወጥቷል።

ጉቦ ተቀብለዋል ስለተባሉ የመንግሥት ሓላፊዎች ጥቆማ ለመስጠት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አማራጮች መጠቀም ይቻላል።

፩. ጥቆማ ለመስጠት ፈልገው ወደ ኢንቨስቲጌሽንና ፕሮሴኪውሽን ሚኒስቴር ሕንፃ ሲመጡ ከመግቢያው በር ላይ ለሚገኙ ጥበቃዎች ጥቆማ ለመስጠት እንደመጡ በመግለጽ ወደ ጥቆማ ተቀባዩ ክፍል እንዲመሩ ማድረግ፤

፪. ጥቆማ ሰጪው ወደ ጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሲመጣ ጥቆማ ሰጪው ማንነቱን ሳይገልጽ ጥቆማውን ለመስጠት ከፈለገ ጥቆማውን በቃል ወይም በጽሑፍ ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ ማቅረብ፤

፫. ጥቆማ ሰጪው ማንነቱን ገልጾ ጥቆማውን ለመስጠት ከፈለገ ጥቆማውን በቃል ወይም በጽሑፍ ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ ከማቅረቡ በፊት ስሙን፣ አድራሻውን እና ስልክ ቁጥሩን ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ መስጠት፤

፬. ጥቆማ ሰጪው ጥቆማውን ለመስጠት ወደ ኢንቨስቲጌሽንና ፕሮሴኪውሽን ሚኒስቴር ሕንፃ ሲመጣ ጥቆማውን ለመስጠት ከፈለገ ጥቆማውን በቃል ወይም በጽሑፍ ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ ከማቅረቡ በፊት ስሙን፣ አድራሻውን እና ስልክ ቁጥሩን ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ መስጠት፤

፭. ጥቆማ ሰጪው ጥቆማውን ለመስጠት ወደ ኢንቨስቲጌሽንና ፕሮሴኪውሽን ሚኒስቴር ሕንፃ ሲመጣ ጥቆማውን ለመስጠት ከፈለገ ጥቆማውን በቃል ወይም በጽሑፍ ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ ከማቅረቡ በፊት ስሙን፣ አድራሻውን እና ስልክ ቁጥሩን ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ መስጠት፤

፮. ጥቆማ ሰጪው ጥቆማውን ለመስጠት ወደ ኢንቨስቲጌሽንና ፕሮሴኪውሽን ሚኒስቴር ሕንፃ ሲመጣ ጥቆማውን ለመስጠት ከፈለገ ጥቆማውን በቃል ወይም በጽሑፍ ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ ከማቅረቡ በፊት ስሙን፣ አድራሻውን እና ስልክ ቁጥሩን ለጥቆማ ተቀባዩ ክፍል ሠራተኛ መስጠት፤


ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ _____

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process


ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/




ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/


ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ




ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECHR


http://ethcriminalawnetwork.com/



ECHR







ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/


ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ክፍል ተከሳሽ ራሱ ይሞላዋል

ስም ፊርማ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ECHR


http://ethcriminalawnetwork.com/



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ


799

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/



ECLN


http://ethcriminalawnetwork.com/



ECHR

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation Department

http://ethcriminalawnetwork.com/



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ECHN

http://ethcriminalawnetwork.com/

0D3C

- የ"የ.ጸ." ሠራዊትን መሰረተ
- መንግስታዊ ኃላፊነት ወንጀል
- የፀረ-ወሳኝ ህዝብ ተቃውሞ ዘመቻና ሰራዊትን በጸረአመፃዊ
- ተልዕኮ፣ ተልዕኮ አፈፃፀም፣ ተልዕኮ አተገባበር፣ ለአገልግሎት አተገባበር
- ለዘመቻ ሦስት መሠረተ ንድቀቃት ጨምሮ ጨምሮ ጨምሮ
- ተመሳሳይ የፀረ ወር ና የፀጥታ ሠራዊትን ከጎኑ የመደገፍ ተፅዕኖ መሳሪያዎች
- ጦር ኢንተለጀንስ መሰረታዊ - ሀገሪ ተኩ - መሰረታዊ-ኢንተለጀንስ
- ጦር ሚሳይሎች - ኒውክሌር - የሕዋ ጎን ሰፊ-
- ጦንኳ ዘመቻ - የኬሚካል ጸረ-ሽብር ሰፊ - ማራዘሚያ ሃይሎች
- ኒውክለር መሳሪያ - ኒዩ ኢንጂነሪንግ ሰፊ - ጦር ዕዝ
- ጦር ኃይላት - መሰረታዊ ዘዴ - ሚሳይል መጎ
- አጠቃላይ ጋር የመንግስት መሰረታዊ ትን መዘርጋት
- ማለት ኣቀፍ ጨዋ ኬጋ የመንግስት ሀገሪ መሰረታዊ

ኮሎኔል ጌታሁን

ማዘዥ መኮ

ዓ/ተ/ጉ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ኃላፊነት ስለ ቦታገና

ሀ) ችሎቱ ስለማለው:- ከሁለቱም ፍላጎት

ውጭ በሚሆን:- በእስተወራሪ መብ ከሳሽ (ሠራተኛ) ስለመመለስ ና ለወሰንበት ተገቢ ስለመሆን ና መሰረታዊ ጉዳዮችን ከዚህ በታች ከሚገኙት ችሎቱ ከሰጣቸው ነጥቦች አኳያ ከሚገኙት ያለው ችሎቱ ከሰጣቸው ነጥቦች መፀደቅ ትክክል ስለመሆኑ፤

:- በአንደኛነት ቀጠሮ የሰራ ውሳኔዎችን መመርመርና ችሎቱ ያጠፋቸውን ነጥቦች የሰራ ውሳኔዎች ነው፡ የሚገኙበት መስፈርቶች መሆኑንና ሰራተኛው ስለ ከሳሽነት መሰየሙ፤

:- በተሰጥ መመን የሚሰጡ መረቀቆችን መገዘብና መመርመር ስለመገዘቡ የተሰጠው መፍትሄዎች ትክክል መሆናቸው፤

---

መመለስ ያለባቸው ነጥቦች:-

- በመጀመሪያው ክስተት ችሎቱ ስለ መስፈርቱ ዘርዝ የመረመረው ክስተቱ ከሰነዶች መመልከት ያለበት ችሎቱ ችሎቱ መሆኑ፤
- አከራካሪ ችሎቱ ክርክራቸው መሰረት ያደረገው ችሎቱ መሆኑ፤
- በስራው ሰዓት ጋር ተያይዞ የሆነው ክስተት የሰጠውን ሰነድ መመርመር ስለመቻሉ ወይም ችሎቱ ከሰጣቸው ነጥቦች ውጭ ስለመሆኑ፤ ከሰጣቸው ነጥቦች ችሎቱ ስለመመርመሩ፤ የሰራ ተገቢ ነጥቦች መወሰን፤

ችሎቱ ስለ ፍ ፵ + ፫፻፭ = ፲፯,፪፻፵ − ፳,፰፻፰ × ፲ ÷ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

99 ቀበሌ × 4 መርማሪ = 396 መርማሪ

396 መርማሪ × 50 ሰው = 19,800 – 20,000

እያንዳንዱ ሰው ለአሉ 10 ሰው ያስራቸዋል

ለወጪው 200,000 ሰው ተጨማሪ መገለጫ ነው

=II=

* የጋራ ፍላጎት * ትኩረት * ገዘፍ

* ዘላቂነት፡- ቀጣይ፣ የተመሰረተ፣ የተከናወነ፣ ሁሉንም ተሳታፊ፣ የተቀናጀ

=II=

* Volunteers * መሰረታዊ እንቅስቃሴ መከታተያ/መከታተያ

* እንቅስቃሴ መከታተያ/መከታተያ

* መመሪያዎች/መስፈርቶች መመሪያዎች/ህጎችንና ደንቦች

ለይቶ ማወቅ፣ ቅደም ተከተል የጋራ ሠራተኞች

* ገበሬዎች * Tutor

* ከሠላም-ፈጠራዎች የመጡ ሰዎች/ወንጀሎችን መከታተል

=II=

* የፍርድ ቤት ውሳኔዎች * የመንግስት ውሳኔዎች

* መደራጀት በሚለው ላይ አንቀጽ ውሳኔዎች

* የትራፊክ-መተላለፍ ውሳኔዎች

=II=

* ወደፊት ከሆነ * አስቀድሞ ወይም ከሆነ ሁኔታ whether

* መደራጀትን፣ እንቅስቃሴን፣ ወላጅነትን የመቆጣጠር

* እነሱንም ጠንካራ የመሆንን

* እሽግ ላይ ተሰራ ከማለት እነሱንም ጠንካራ ማድረግ የመቆጣጠር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution

706

ከዋናው ጋር የመሰከርኩት

ECHN

http://ethcriminalawnetwork.com/

# ጠንካራ መጅሊስ የምንፈልገው ለምንድነው?

ይህ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሙስሊሞች በአንድ በኩል እና በመጅሊስ አመራሮችና አንዳንድ ፖለቲከኖች በሌላ በኩል ሆነው እየተካረረ የመጣው ግጭት አዲስ አይደለም። የኢስላምንና ሙስሊሙን ጥንካሬ የሚወዱ በአንድ ወገን፣ የኢስላምንና ሙስሊሙን መዳከም ከተቻለ መክሰም የሚሹ በተቃራኒ ወገን ተሰልፈው የሚያካሄዱት ትግል ከመጀመሪያው ሰው እና ነብይ አደም(ዐ.ሰ) ጀምሮ የነበረ ነው።

ከነብዩላህ አደም (ዐ.ሰ) ጀምሮ እስከ ነብዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ያሉት ነብያት፣ የነብያቱ ወራሾች የሆኑት ዓሊሞች እነ ሸህ ዳና፣ ሸህ ዒሳ ቃጥባሬ፣ ሸህ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅ፣ ሐጅ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፣ ሐጅ ሙሐመድ ራፊዕ፣ የወለኔው ሸህ፣ የሾንኬው ሸህ፣ ሸህ አባዲር እና ሌሎች በሕይወት የሌሉ ሆነ ያሉ ዓሊሞች፣ ጻድቃኖች መልካም አማኞች በሙሉ (የአላህ እገዝነትና ርህራሄ በሁሉም ላይ ይሁን) ኢስላምና ሙስሊሙ ጥንካሬ ብርታት እና እድገት ለፍተዋል፣ ጥረዋል፣ ሕይወታቸውን ገብረዋል።

ከነዚህኖቹ የአላህ ወዳጆች በተቃራኒ ከኢብሊስ ጀምሮ እነ ፊርዓውን፣ ነምሩድ፣ ቃሩን፣ አብረሃ፣ አቡጀህል፣ አቡለሃብ፣ የአይሁድ አመራሮች፣ ሙናፊቆች እንዲሁም መሰሪ ፖለቲከኞች (ሙስሊም ሆኑ አልሆኑ) በአንድ ላይ ኢስላምንና ሙስሊሙን ለማዳከም ሌት ተቀን ሲያውጠነጥኑ፣ ተንኮል ሲሸርቡ፣ ሲገድሉ ሲያስገድሉ፣ ሙስሊሙን ለመከፋፋል ከጀርባው ሲወጉና ሲያስወጉ የኖሩ ናቸው።

በአወሊያ ይኸው ለስድስተኛ ሳምንት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች በቦታው ላይገኙ የቀሩ በሚሊዮኖች ልብ ውስጥ ያለው ምኞት በነቢያቱ፣ በዓሊሞች፣ በጻድቃኖችና በሰማዕቶች ልብ ውስጥ የነበረው የኢስላምና ሙስሊሞች የመጠናከር ዓላማና ምኞት ነው። በተቃራኒው ደግሞ እነዚህን ከአደም ጀምሮ የነበሩ በአሁኑ ወቅት በየትኛውም የዓለማችን ጥጋ ጥግ ያሉ ቀናኢ አማኞች የሚደግፉትን የኢስላምና ሙስሊሙ መጠናከር የዘመናት ተልዕኮ ለማሳካት ይዘው የተነሱትን በአወሊያ የተሰባሰቡ ሙስሊሞችን ለማስመታት፣ ‹‹አክራሪ ናቸው››፣ ‹‹አሸባሪ ናቸው›› እያሉ የሚያስወሩ፣ ማስታወቂያዎችንና ደብዳቤዎችን የሚለጥፉና የሚልኩት የመጅሊስ አመራሮችና አንዳንድ ፖለቲከኞች ኢስላምና ሙስሊሙን መዳከም ብሎም መጥፋት የሚፈልጉ ደጋፊዎችን፣ አብርሃን፣ ፊርዓውንና ነምሩድን የሚመስሉ ናቸው።

እነዚህ ሰዎች የአነዚህን ጎጂዎች ዓላማ ባይዘምሩም ዋና የሚጭቱ መልክ እንዲህ አይሆንም ነበር። በኢትዮጵያ መጅሊስም ላይ ጦርነት አያውጁምም። የኢስላምንና ሙስሊሞችን ጥንካሬ በሚፈልጉ ስራዎን ላይ ፡ የፀሐፊ ሐሳብ ላይበግልም የኢስላምንና ሙስሊሞችን መጠናከር ፈልገው በተሰባሰቡት ላይ ‹‹አሸባሪ ናቸው›› ብለው ጣቶቻቸውን ባልቀሰሩ፣ ምላሳቸውን ከላቃቸው ባላላቀቁ። እነዚህ ሰዎች የኢስላምንና ሙስሊሞች መጠናከር ፈልገው የመጅሊስ ይጠናከር ጥያቄዎች ካነሱ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጎን ቢቆሙ ነበር። መጅሊስ በተለመደ ደረጃ መያድ (NGO) ሆኖ እንዲቀር የኢስላምንና ሙስሊሞች መዳከም ከማሴራቸው ጎን ባልተሰለፉ፣ የጅሉንም አጀንዳ ለማስፈጸም ባልተጉ፣ ባልተንቀሳቀሱና ባልቀሰሱ ነበር።

የመጅሊሱ ደካማ ጎኖች የተየሌለ እንደሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም የሁሉም ድክመቶች መንስኤዎች ግን ሁለት ናቸው። አንደኛው መጅሊስ አወቃቀሩ ደካማ ነው። መሰረቱ፣ ማገሩ፣ ምሰሶው፣ ግድግዳውና ጣሪያዎቹ በሙሉ መያድ (NGO) ወይም ግብረሰናይ ድርጅት መዋቅር ስለሆኑ የአሸዋ ላይ ቤት በሉት የሸረሪት ድር ይስማማዋል። በቀላሉ ለጥቃት፣ ለተፅዕኖና ለማፍረስም ጭምር የተጋለጠ ነው። ሁለተኛው ችግር መሪዎቻችንን አለመምረጥ ነው። ከየት ይምጡ ማን ያምጣቸው የማናውቃቸው ሰዎች አይምሩን። መጅሊስ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ቀልብ ነው። ይህ ቀልብ ከተበተካከለ ሙስሊሙ ይበተካከላል። ይህ ቀልብ ከተበላሸ ሙስሊሙ በሙሉ ይበላሻል። ስለዚህ በቀልባችን ላይ አዛኝ ናዛኝ ኾሆን ያለብን ማንም ሳይሆን የኢትዮጵያ ሙስሊም ነው። የዕድገታችንም ሆኖ ውድቀታችን ዕጣ ፈንታ ለኛ ሊሰጠን ይገባል።

እነዚህን ሁለት መሠረታዊ የድክመቶች ሁሉ መንስኤዎችን ስንገለብጣቸው መጅሊስ ጠንካራ ይሆናል። ማለትም መጅሊስ በመያድ ወይም ግብረ ሰናይ ድርጅታዊ መዋቅር ሳይሆን በቻርተር ሊቋቋም፣ ሁለት መሪዎቻችንን ስንመርጥ ኢስላምና ሙስሊሞች ይጠናከራሉ። ይሄኔ የነሙፍቲህ ዳውድ፣ የነ ሸህ ዳና፣ ሸህ ጫሊ፣ ሸህ ጦልሃ ጃፅፋር፣ ሸህ ዒሳ ቃጥባሬ፣ የወለኔው ሸህ፣ የሸህ አባድር፣ የሸንኬው ሸህ፣ የአልከሰዬ ሸህ፣ የአብረሄት ሸህ፣ ሐጅ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፣ ሸህ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅ፣ ሐጅ ሙሐመድ ራፊዕ ሀልም ዕውን ይሆናል። የዘመናት ምኞታቸው ይሳካል። ስለሆነም፣ መጅሊሱ ጠንካራ እንዲሆን የምንፈልገው የሸኾቻችን ህልም፣ ትግልና ምኞት እውን ለማድረግ ነው። ሸኾቻችን ከኢስላምና ሙስሊሞች ጥንካሬ ውጪ ሌላ ምኞት አልነበራቸውም። ሌት ተቀን የሰፉት፣ በረሃ ለበረሃ የተንከራቱት፣ አቀበት ቁልቁለቱን የወጡት የወረዱት፣ አላህን አጥብቀው ሲለምኑት የነበረው ለዚሁ ህልማቸው ነበር።

አስቲ የእኛን እናትና አባቶቻችንን ፊቶች የሞሉን መስመሮች፣ የተሰበሩ አንገቶቻቸውን፣ እንባ አዘለው የፈዘዙ ዐይኖቻቸውን እንመልከት፣ የአነርሱን አባቶችና እናቶች እንዲሁም አያት ቅድመ አያቶች ታሪክ ሲነገር አድምጡ፣ አንብቡ። በየትምህርት ቤቱና ዩኒቨርሲቲው ያሉትን ወንድሞችንና እህቶቻችን ታሪኮች አድምጡ። ሁሉም የሚነግሩን አንድ ነገር ብቻ ነው-በኢስላምና በሙስሊምነታቸው ምክንያት ተዋርደዋል፣ ክብራቸው ተገፏል። ይህ እጅግ በሚያሳዝን አኳኋን አስካሁን ድረስ የዘለቀ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እውነታ ነው። ኢትዮጵያ አገራችን አገራቸው እንዳልሆነች ያህል ባይተዋርነት ይሰማቸዋል። በነገራችን ላይ እነዚህ እንዲህ አይነት ስሜት እንዲሰማን የሚያደርጉን ሰዎች፣ ባለስልጣናትና ቢኖክራቶች ሱፊይ ብንሆን ‹‹ወሃቢያ›› ደንታ የላቸውም። ሁላችንም በነርሱ ፊት ሙስሊሞች ነን። ይህ ውርደት የሚደርስብን ኢስላምን የተቀበለን ሙስሊሞች ስለሆንን ብቻ ነው! እንዴትም አድርጋችሁ በአሁኑ ወቅት ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታ ሆነ ታሪካችንን መለስ ብለን አይተን ብናጤነው ከዚህ ውጪ ማብራሪያ ልናገኝለት አንችልም። ብቸኛው የመጠናከሪያ መንገድ የሆነው መጅሊስ ተጻከሞ እንዲቀር ያለሳለሰ ጥረት ለዚሁ ነው። በአገራችን ቦታችን ዝቅተኛ እንደሆነ፣ መቼውንም እኩል እንደማንሆን እያስገነዘቡን ነው። በተለያዩ ቃላት እየሸነገሉን ባሪያ ሲጠግብ አናት ላይ ይወጣል እንደሚባለው አስካሁን ያገኛችሁትን ውበት በቂ ነው፣ ከዚህ በላይ ምን ትፈልጋላችሁ እያሉን ተዋርደን አንድንቀር ነው ፍላጎታቸው። መጅሊስ ጠንካራ እንዲሆን የምንፈልገው ሌላው ምክንያት ለዚህ ነው። ይህ የዘመናት ውርደትና መሸማቀቅ ሊቆም ይገባል። የእናትና አባቶቻችንን፣ የእህትና ወንድሞቻችን በሙስሊምነታቸው የሚደርስባቸው እንባ ሊጠረግ ሊደርቅ ይገባል። ፊቶቻችን የምናያቸው እናትና አባቶች በሙስሊምነታቸው ሲደርስባቸው በነበረው ውርደት ምክንያት የተሰበረ ልባቸው ተጠግኖ፣ የተደፋው አንገታቸው ቀና ብሎ፣ በወለዱት ልጆች ተደስተው አየመረቁን ወደ አኼራ መሄድ አለባቸው። በአገራችን ሙስሊም መሆናችን ብቻ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ የምንቆጠርበት ጊዜ ሊያቆም ይገባል። አንገታችንን ቀና ማድረጊያው ጊዜ መቼም ሳይሆን አሁን ብቻ ስለሆነ መጅሊሱ ጠንካራ እንዲሆን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ይፈልጋሉ!!!





http://ethcriminalawnetwork.com/

# ድምፃችን ይሰማ!

**የተቃውሞ ድምፅ**

## መጅሊሱ በክልሎች ያልጠበቀው የህዝብ ቁጣ ገጥሞታል።

መጅሊሱ ያመጣውን የአህባሽ አስተሳሰብ ተክትሎ በመጅሊሱ ላይና በአህባሽ ላይ የተነሳው ተቃውሞ በክልል ከተሞችም በአስገራሚ ፍጥነት እየተስፋፋ ይገኛል። የ‹‹ድምጻችን ይሰማ›› ሪፖርተሮች ከክልል ከተሞች ባገኙት መረጃ ቢትዮጵያ ከሰሜን ጫፍ እስከ ደቡብ ጠርዝ እንዲሁም ከምእራብ ኢትዮጵያ እስከምስራቋ ሀረር ድረስ መጅሊሱ ላይ የተቃውሞ ድምጾች እየተሰሙ ይገኛሉ።

በአፋር ክልል መጅሊሱ የሾማቸውን የኡለማ ምክር ቤት አባላት የከተማው ኡለማዎች በማፍረስ አዲስ የራሳቸውን የኡለማ ምክር ቤት ያቋቋሙ ሲሆን ኡለሞቹ መጅሊሱ እንደማይወክላቸው በይፋ በመግለጽም በክልሉ ለሚገኙ ዞኖች ሁሉ የአህባሽን እና የመጅሊሱን አስከፊነት የሚያስተምሩ ሰዎችን መላካቸው ተሰምቷል።

የምእራብ አሮሚያዋ ጮራ ከተማ ሌላዋ ከፍተኛ ተቃውሞ እያሰሙ ካሉ ከተሞች የምትመደብ ናት። በዚህች ከተማ የሚገኙ ሙስሊሞች መጅሊሱ እንደማይወክላቸው የሚገልጽ ፔቲሽን በማስፈረም ላይ ናቸው። በትግራይ ክልልም በተመሳሳይ መልኩ በመቀሌ፣ በሽሬ፣ በአድዋ፣ በኩኩፍቱ፣ እና አላማጣ ከተሞች ህዝቡ ከስላት በኋላ የተክቢራ ድምጽ እያሰማ ይገኛል። ፔቲሽንም በሁሉም ከተሞች እየተፈረመ ነው።

በኦሮሚያ ልዩ ዞን አሰላ ከተማ መጅሊሱ ህዝብ ያልመረጣቸውን ግለሰቦች በመሰብሰብ ቢሾምም ህዝቡ ግን ‹‹ሌቦች አይመሩንም! ለዘራፊ መስጊዶቻችንን አናስረክብም!›› የሚል መፈክር እያሰማ ይገኛል። የዞኑ አስልምና ጉዳዮች አዳዲስ ተመራጮች በበኩላቸው ‹‹ከብቶቻችን ስለሆናችሁ ወዳሻን እንወስዳችኋለን›› በማለት አሳፋሪ ንግግር ተናግረዋል። በምዕራብ አርሲ ሻሸመኔ ከተማ ‹‹መጅሊስ አይወክለንም!›› በሚል የተቃውሞ ፊርማ እየተሰበሰበ ይገኛል።

ከዚህም በተጨማሪ በሌሎች ከተሞች ጸረ መጅሊስና ፀረ አህባሽ እንቅስቃሴዎች በመካሄድ ላይ ናቸው። በወልቂጤ፣ በጂማ፣ በምእራብ ወለጋ ሁለት ከተሞችና በሐረር ገለምሶ ከተማ መጅሊሱ እንደማይወክላቸው የሚገልፅ ፔቲሽን ህዝቡ በመሰብሰብ ላይ ነው። በሀረሯ ገለምሶ ከተማ ብቻ ከሃምሳ ሺ ሰው በላይ ፔቲሽን ላይ ፊርማውን አስቀምጧል። ይህ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በሌሎችም የክልል ከተሞች ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን በአውሮፓና አሜሪካ ተመሳሳይ የፊርማ ማሰባሰብ ተግባር እየተካሄደ ነው።

**መጅሊስ ፊርማ በማሰባሰብ ዲናችንን ለአደሁዩ ሰመሸዋ ስለተደራደረ እንጠንቀቅ!!!**
**የመጅሊስ ሹመኛች ከዚህ ቀደምም ሲሸጡን ተደራድረዋል። ዛሬም ነገም አይተኙልንም። ስለዚህ፤ እንፈልጋችውም!!**

**በጉልበት ዲናችንን አሳልፈን አንሰጥም!!! ከሙናፊቆች ሴራ እንጠንቀቅ!!!**

**ሕዝብ ያልመረጣችው የመጅሊስ ሹመኛች ያልመረጣችውን ሕዝብ ስብሰባ የመጥራትም ሆነ የማወያየት ሥልጣንም ሆነ የሞራል ብቃት የላችውም!!!**

**የ መ ጅ ሊ ስ አመራሮች ግን ለምንድን ነው ምርጫ የሚፈሩት?**



## መጅሊሱ እና አሕባሽ ላይ አገር አቀፍ ተቃውሞው ተፋፍሞ ቀጥሏል!!

## የመጅሊስ ክስረት በአዲስ አበባ መስጂዶች!

### የመጅሊስ ስብሰባዎች በህዝብ ተቃውሞ እየተበተኑ ነው።

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜና እሁድ በአዲስ አበባ የተለያዩ መስጂዶች ከህዝብ ጋር ሊደረግ ታስቦ የነበረው ውይይት ብአብዛኛው ሳይሳካ መቅረቱ ተሰማ። በስብሰባው አጀንዳ እንደተገለጸው ‹‹መጅሊስና አህባሽን አስመ[illegible] የተፈጠሩ ብሽፆታዎችን የማጥራት አላማ አለው›› ተብሎ በብዙ የከተማችን መስጂዶች ተሰጥፎ በነበረው ማስታ[illegible] ቢገለጽም በተካሄዱት የሁሉም መስጂዶች ስብሰባ ግን መጅሊሱ ራሱ ትልቅ ቀውስ ውስጥ እንደሚገኝ አመላካች ሆኖ ተገኝቷል።

ስብሰባው ከተካሄደባቸው መስጂዶች አንዱ ታላቁ አንዋር መስጂድ ነበር። በመስጂዱ የሴቶች መስገጃ አዳራሽ ውስጥ በተካሄደው በዚህ ስብሰባ በግምት ከ 250 እስከ 350 የሚደርሱ ሰዎች ተገኝተው ነበር። በመድረኩ ላይ የነበሩት ሁለት ሰዎች የመስጂዱ አሥተዳዳሪ እንዲሁም ኢማሙ ሐጂ ጧሃ ነበሩ። ኢማሙ ፕሮግራሙን በንግግራቸው በመክፈት ‹‹ስለሱፊያ እናስተምራችሁ›› ሲሉ የተደመጡ ሲሆን ይህንንም በማስተማር ላይ እያሉ ከተሳታፊዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል። ተሳታፊዎቹ ‹‹እኛ የመጣነው ስለሱፊያ ለመስማት ሳይሆን ስለአህባሽ ለማድመጥ ነው፤ እኛም ሱፊዮች ነን፤ እኛ ከሱፊያ ጋር ችግር የለብንም፤ በሰላምም አብረን እየኖርን ነው›› የሚል ጥያቄ ቢያነሱም ኢማሙ በገለጻቸው መቀጠሉን መርጠዋል። ይህ ያልጣማቸው በግምት ከተሳታፊዎቹ ሩብ የሚሆኑት ወጣትና አረጋዊ ተሰብሳቢዎች ‹‹ለጥያቄያችን ምላሽ ካልሰጡን ልናዳምጥዎት አንሻም!›› የሚል አጸፌታ ለኢማሙ በመስጠት በተክቢራ መስጊዱን ለቅቀው ወጥተዋል። እነዚህ ሰዎች ‹‹መጅሊስ ነጂስ! አህባሽ ይወገዳል!›› የሚል መፈክር ደጋግመው ያሰሙ ነበር - መስጂዱን ለቅቀው ሲወጡ ሐጂ ጧሃ መስጂዱን ለቅቀው የወጡትን ሰዎች ‹‹የዶሮ ጭንቅላት፣ መሃይማን›› ብለው ሲዘልፉ በጆሮዋችን አድምጠናል።

ኢማሙ ከተቀሩት ተሰብሳቢዎች ጋር ስብሰባቸውን ለመቀጠል ቢሞክሩም ሕዝቡ ‹‹ወደአህባሽ አጀንዳ ይግቡልን!›› በማለት ኢማሙን ሲያስጨንቃቸው ታይቷል። ተሰብሳቢዎቹ በድፍረት ‹‹ለምን ከውጪ አስተማሪዎች ማምጣት አስፈለን? አገራችን በቂ አሊም የላትም ወይ? የመጅሊሱን ባለስልጣናት መቼ መረጥናቸው? አህባሽ አንድነታችንን እያደፈረሰው ስለመሆኑ አያምኑምን? መንግስት ለምን በሃይማኖታችን ጣልቃ ገባ?›› የሚሉ ጠጣር ጥያቄዎች ከተሳታፊዎች ወደኢማሙ ቢሰነዝሩም ኢማሙ ጥያቄዎቹን አድበስብሰው ከማለፍ ውጪ አልነበራቸውም። ‹‹ስልጠናው ሱፊያውን ማደራጀት ስላስፈለገ በጥናት ጋው እየተሰራ ያለው›› የሚል ምላሽ በመስጠት የህዝቡን ቁጣ ለማርገብ ቢጥሩም ህዝቡ ግን በቁጣና በአልህ ‹‹ንግግሮትን መስማት አንፈልግም! እርስዎም አህባሽ ሆነዋል! አላህ አክበር! መጅሊስ ነጂስ!›› ሲል ተሰምቷል። ፕግራሙ በዚያው የተቋረጠ ሲሆን ለመቋረጡ ዋነኛ ምክንያት የነበረውም ኢማሙ ጥያቄዎችን አልቀበልም ማለታቸው ነው። ይህም ህዝቡ በሞሰ ቁጣው እንዲነነፍል ምክንያት ሆኗል።

ፕሮግራሙ በዚህ መልኩ በክስረት ሲጠናቀቅ የመስጂዱ ጓዳሞች ኢማሙን ከሸው ከመስጊዱ አውጥተዋቸዋል። የመድረኩ በዚያ መልኩ ያለውጤት መጠናቀቅ ግን ለኢማሙና ለመጅሊሱ ትልቅ ክስረት መሆኑን አመላካች ሆኗል። ምክንያቱም መጅሊስና ጀሌዎቹ አንዋር መስጂድን ዋነኛ የጀሃድ ማዕከላቸው አድርገው ሲመለከቡት የቆዩ መሆኑና የህዝቡ ሁኔታ ግን በተቃራኒው ሆኖ መታየቱ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዛሬ በፒያሳው ኑር መስጂድ፣ በሐጂ ዩኑስ መስጂድ፣ በፍልውሃ ተውፊቅ መስ[illegible] በአሊቫ መስጂድ እና በቡራዩ ኩርቱ መስጂድ፣ በኮካ መስጊድ፣ በኮልፌ ኢማም ሐሰን መስጊድ፣ በአባጂፋር መስጊድ፣ በፌደራሉይ ለጋሲዮን መስጊድ፣ እንዲሁም በሰላሣዲን መስጊድ የተካሄዱ ስብሰባዎች በአንዋር መስጂድ አይነት ትዕይንቶች የተበተኑ ሲሆን የፍል ውሃው ተውፊቅ መስጂድ ግን አንድም ተሰብሳቢ ሳያገኝ ቀርቷል። የኑር (የበኒን) መስጂድ ምክትል ኢማምና የቢላል መስጂድ ዋና ኢማም በስብሰባው ከህዝብ አህባሽን አስመልክቶ በማስረጃ የቀረቡላቸው ጥያቄዎች መደናገጥ ውስጥ ከትተዋቸው ታይቷል። አቋማቸውን ለመለወጥ እና ከህዝብ ጋር አንድ ላይ ለመቆም ፍላጎት አሳይተዋል። ‹‹ጉዳዩ ይጣራም›› ብለዋል። የሁሉም መስጂድ ኢማሞች በመድረኮቹ ከመጅሊሱ በተሰጣቸው ትእዛዝ መሰረት የአህባሽን መልካምነት ለማስተማር አቅድ ይዘው የነበረ ሲሆን ሁሉም ሳይሳካ ስብሰባዎቹ በክስረት ተጠናቅቀዋል።

በሌላም በኩል ረቡአ ምሽት በራዲዮ ፋና በተዘጋጀ ፕሮግራም የውይይት ፕሮግራም ከመጅሊሱ ኡለማ ምክር ቤት የተወከሉ ሰዎች (ሐጂ ጣሃን ጨምሮ) ስለአህባሽ አስተምህሮ መልካምነት ደስኩረዋል። አየቀጠፉ የነበረው ሁሉ እንዳይጋለጥባቸው በመስጋታም የመረጡትን ጥያቄ ብቻ እያቀረቡ መልስ የሰጡ ለመምሰል የጣሩ ሲሆን ምንም አይነት ተከራካሪ በቀጥታ በድምጽ ጥያቄ እንዳያቀርብ አድርገዋል። ሐጂ ጣሃ ቅዳሜ በአንዋር መስጊድ አብደላ ሐረሪ ብዙ መክሬር የሌለባቸውን ዑለሞች ያከፈሩ መሆናቸውን በህዝብ ፊት አምነው የነበረ ቢሆንም በራዲዮው ዝግጅት ግን ይህንን እውነታ ሙሉ በሙሉ ክደዋል።



ኮፒ አድርገው ለማንሰተላለፍ ሃላፊነቶን ዓወጡ!!

http://ethcriminalawnetwork.com/

18.

ከላይ የተዘረዘሩትን መስማዶች በሙሉ በም/ቤቱ እውቅና ተሰጥቶአቸዉ የተሰሩ አለመሆናቸዉንና በም/ቤቱም ተመዝግበዉ በም/ቤቱ የሚተዳደሩ አለመሆናቸውን እናስታዉቃለን

Haji Ahmed Hirad Mahammed
President

ጉራጌ ዞን
ጎልማሳ ጋር
ትምህርት ተጠሪ
ያልተሰጠበት ሰነ
05

ECLN

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

811

http://ethcriminalawnetwork.com/

Gumii Ol'aanaa Dhimmoc a
Islaamummaa Naannoo Oromiya
የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል እስልምና
ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት

المجلس العالى للشؤن الاسلامية
في إقليم أوروميا
Oromiya region Islamic
Affairs Supreme Council

Lakk: ዑዘo/710/ዐ-ጋ5

Guyyaa: 5-1-2-ጋ5

الرقم _____

التاريخ _____

በኢ/ፌደ/ፖ/ልስ የወንጀል ምርመራ ዘርፊ

ሰታ/ክቲክ ምሪመራ የዳሬክቶሬት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡-ከመስሪያቤታችሁ በቁጥር 10790/04 በቀን 02/13/04 የተጻፌ ደብዳቤን መልስ መስጠት ይመለከታል

ሸህ ሀጅ ኢብራሀም ተሀፉ የተባሉ ግለሰብ በተጠረጠሩበት የሽብር ፊጠራ ወንጀል ለማስረጃነት ይረዳቸዉ ዘንዲ


1. በኦሮሚያ ክልል አረሲ ዞን አሰለ ከተማ 04 አቡበከር መስጂዲ
2. ›› ›› ›› ›› ›› 08 ልዩ ቦታዉ በሠላ ሚዳ አመሪ አብኑልሀጣብ መስጊዲ
3. በኦሮሚያ ክልል አረሲ ዞን አሰላ ከተማ ቀበሌ 09 ዉስጥ የሚገኝ መስጂዲ
4. ›› ›› ›› ›› ›› ›› ›› 13 ›› ›› ››
5. ›› ›› ›› ›› ›› ›› ማሬማሚያ ቤት ›› ›› ››
6. ›› ›› ምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ መስጊዲ
7. ›› ›› ›› ›› ›› አዳባ ከተማ ቀቤሌ 01 ›› ››
8. ›› ›› ምስራቅ ሸዋ ዞን ወሊንጭት ከተማ ቀቤሌ 01 ›› ››
9. ›› ›› ›› ›› ፊንታስ ወርዳ ዉስጥ የሚገኝ ሁለት ››
10. ›› ›› አረሲ ዞን ጉና ወረዳ ነገሌ ከተማ ቀበሌ 01 ጀማአል ኬራት መስጂዲ
11. ›› ›› ›› ›› ›› ›› ናኖዬቶ ቀቤሌ ዉስጥ ሸየተሰራ ያለ መድጂዲ
12. ›› ›› ›› ›› ሙሌ ከተማ ቀቤሌ 01 ዉስጥ የሚገኝ መስጅዲ
13. ›› ›› ›› ›› የጦሳ ወረዳ ሀንደደ ቀበሌ ገበሬ ዕህበር ዉስጥ የሚገኝ መስጊዲ
14. ›› ›› ›› ›› ሴሩ ከተማ ቀበሌ 01 ዉስጥ የሚገኙ አሀን ሸየተሰራ ያለ መስጊዲ
15. በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ ወረዳ ሰፈራ መንደር የሚገኝ መስጅዲ
16. ›› ›› ባሌ ዞን ጊንሪ ወረዳ ጉተራ ዋላሊስ ቀበሌ ገቤሬ ማህበር ክ6 ለመት በፊት የተሰራ መስጊዲ

በም/ቤቱ ፍቃዲ መሰረት አለመስራታቸዉንና በም/ቤቱ ተመዝግበዉ የሚተዳደሩ መሆን አለመሆናቸዉ በመግለፅ በደብዳቤ እንድናሳዉቃቸሁ መጠየቃቸዉ ይታወቃል በመሆኑ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ _____

TEL. ስልክ 011 5505095 FAX ፋክስ 0115 514931 TELEX ቴሌክስ P.O.BOX ፖ.ሳ.ቁ.14226 በስልክ

ECHN
http://ethcriminalawnetwork.com/




ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ...
- ...
- ...

5 - Job discription ...

4. Account ...

5. በ1 Account ... (Religions)

...

...

...

ስብሰባ ስለማዘጋጀት

ስብሰባ ዓይነቶች

1, ዓመታዊ መደበኛ ስብሰባ 2. አስቸኳይ ስብሰባ

3, ወቅታዊና መደበኛ ስብሰባ 4. ልዩ ወይም መደበኛ ስብሰባ

አስፈላጊነቱ

1, የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤተኞች ነጋሪ

ሀ. ሂደቱ ጊዜን ውጤት ሀብ ብቃት ወጪን ይቀንሳል. ወጪ ይጠብቃል.

2. Short financial Report

ገቢውን ወጪውን የተከናወነ financial ሁኔታ ለተቋሙ ጠቅላላ ጉባኤተኞች ያቀርባል. ተቋሙ ይተዳደራል.

Part. delupit ስብሰባውን የሚመሩ ሰዎች ለሚሰሩት የሚመሩ ሰዎች ያሉን ግዴታ ግልጽ ይሆናል

ስብሰባ ሲጠራ

ስብሰባ መጥራት 'ማስጠራት' ነው

active ጠቅላላው ጉባኤ ውስጥ ያሉ ሁሉም አባላት ጠቅላላው ጉባኤ ስብሰባ ስለሚጠራ ማወቅ አለባቸው. ሁሉም actively ስብሰባው ላይ ተሳትፎ ማድረግ

ጉባኤ communicate ማድረግ.

የሚመሩ ጉባኤተኞች መቼ ና ቦታ. ተቋሙን ወክሎ ስብሰባ ለመጥራት ይችላል።

e-mail facility + አለው facility

ይዘት:

(5) Accountant ሚጠቀሙ

የሚሰጡ ወጪ ገቢዎችን የሚመለከት ሂደቱ ይገልጻል.

6. Job discription ስራ ዝርዝር ይገልጻል. ስራ ገለጻ ወይም ስራ ዝርዝር ይባላል.

7. Power ሃላፊነት.

የሚሰጠው ሀላፊነት. ስልጣን መሆኑ ለሚሰጠው ጠቅላላ መሆኑ ይለመለክታል ሀላፊነቱን.

8. follow up

ክትትል

9. landline + cdma (monthin a week

10 የተሰጠው ጠቅላላ መለያ ቁጥር ይጠቀማል.

11 email. ለጠቅላላ ጉባኤ creat ይደረግ.

12. Job discription ሀላፊነት ግልጽ ይሆናል:

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

Federal And Social Affair

ጉዳዩን ገፅ 44 ላይ ያለ ውሳኔያችን ተመልክተናል.

ከይግባኝ መዝገቡ የተመለከተው. Report. ሠራተኞች

- ዳዕራ. ለጊዜው ተዘግቷል.
  ከዚያንስ. ሰው እንዳ ተርጉሞት. ለመጨመር
  እያከናወነ ነው. ናሙ
- curriculum ጊዜያዊ ይሰጣቸዋል ይልመሰ
  የሚለውን. ከፍተኛ: ለመከላከል.
- መገናኛ. መሰረታዊ መጽሐፍ መሰረዝ. ናሙ

እንዲሰጣቸው ጋር የመሠረታዊ መሠረታዊ function.
ለ. ሀሳብ (ጊዜው ገደደ) መሰረዝ

ይመሰ. 35 ለመስጠ ከገቢ መሰረዝ ለመጠ
መጀመሪያ ተመንቷል: ከፍተኛው መጠን ከመ
መሰረዝ ለይ የሚገኝበት ጉዳ Environment
ተፅዕኖ ነው።

የታዘዝነው ለምናደርገው

1- ጉዳዩ መርምረናል
2. ውሳኔያችን ሰጥተናል
3- ፋይሉ ዘግተናል

እስከ የተገኘ

አመልካቹ መጠሪያ (A) ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ...

- ...

- ...

...

...

ቀን 22/08/04

- የመንግስት አጠቃላይ ሃላፊነት ወንጀል ሲሆን ይህንን ለተግባር ለማዋል ዋናው መሪያችን ወይም ለፖሊሲዎች ይገባል።

⊛ ለተመሰረቱት ኢኮኖሚያዊ ፍትህ ተቋማትም ሆነ ሌሎች አስፈላጊ ተግባራት የመንግስት ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ለሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል። ይህንንም ለማስፈፀም ወሳኝ የሆነው የፖለቲካ ውሳኔ ነው።

⊛ ወንጀሉ ወሰን የለሽ ስለሆነ ዓለም አቀፍ ትብብር ወሳኝ ነው። ከዚህም ውስጥ ጎረቤት ሀገሮች ጋር ያለው ትብብር ከፍተኛ ነው። ይህንንም ለማጠናከር ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፖሊስ ድርጅት ኢንተርፖል ጋር ያለው ግንኙነት ከፍተኛ ነው።

- ብዙ ጊዜ ህገወጥ መንገዶች ወንጀሎች ስትራቴጂ ወንጀሎችን ለመከላከል ስልት ይቀይሳሉ። ስለዚህ ይህንን ለመከላከል ስልት ያስፈልጋል።

- ህገወጥ ፋይናንስ ወንጀል የሚፈፀመው ከሌሎች ወንጀሎች ጋር በመሆኑ ወንጀሉን ለመከላከል ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ተያይዞ ሊሰራ ይገባል።

- የቁጥጥሩ ሂደት የመንግስት ፣ የህዝብ መደራጃዎች ሚዲያዎች ፣ ተጠቂዎች ፣ ኦዲተሮች ፣ ሌሎች ፣ ወዘተ ሁሉንም ያሳተፈ መሆን ይገባዋል።

- ህገወጥ ገንዘብ የሚፈጠረው ከየትኛውም አቅጣጫ መሆኑን ማወቅ ይገባል።

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

## ሆድ ሲያውቅ...

**To:** "Africa tv" <135925759803559@groups.facebook.com>

قام Hussein Fetu بالنشر في Africa tv

**Hussein Fetu**
18 يوليو 07:54 مساءً

17ቱ ኮሚቴዎች bittasseru ሕዝቡ ለሌሎች 34 ኮሚቴዎችን መርጦ ትግሉን ይቀጥላል ብለን ነው የምናምነው፡፡ 34ቱ ቢታሰሩ ሕዝቡ 68 ሌሎች መሪዎችን መርጦ ትግሉን ይቀጥላል፡፡ ትግሉ እንዲሁ ይቀጥላል...፤ በትግል ሂደት የመጀመሪያ መሪዎች ሊጠቁ. ሊሰናከሉና ሊታሰሩ ይችላሉ፡፡ የሰዎች መታሰር ትግልን የሚገታ ነው እንዴ? ይህን ጽሑፌን የሚያነብም ሆነ መልዕክቱን የሚሰማ ሁሉ ምንም ይከሰት ምን ሂደቱ ሰላማዊነት ፈጽሞ እንዳይደፈርስ አደራ እላለሁ! ኮሚቴው ቢታሰር፣ አልያም ቢወነጀልና ጥቃት ቢደርስበት እስከ ዛሬ ከነበረው ሂደት በላይ ልዩ ጥንቃቄ አድርጎ የተነሳንለት የመብት ጥያቄያችንን እስከ ፍጻሜው ለስኬት ለማብቃት መታገል ግድ ይለናል! ሕዝቡ አንድነቱንና መደማመጡን ጠበቆ በሰከነና በተናበበ መልኩ ትግልን መቀጠል ግድ ይለዋል፡፡ ተመካከሩ፣ ቀጣይ ሰላማዊ ትግላችንን ሕዝባችንን ፈጽሞ ለአደጋ በማያጋልጥና ሕገመንግሥቱን ባልተቃረኑ መንገዶች ሁሉ ሊቀጥል ይገባል፡፡ በትግል ሂደት ዉስጥ የሁሉም ዜጋ ሚናና አስተዋጽኦ ሊኖር ግድ ይላል፡፡ ‹‹የኛስ ሚና ምን ይሁን?›› የሚለውን ቆም ብለን አስበን የየበኩላችንን እንወጣ! ልዩ አላማ አንግበው ሂደታችንን ለዉድቀትና ለጥፋት ሊዳርጉ ለሚጣጣሩ ሁሉ አይሳካላችሁም እንበላቸው! እንደማይሳካላቸውም እናሳያቸው፡፡ ምክንያት ሲያጡ ምክንያት እንዳይፈጥሩ ነቅተን እንጠብቅ! ፕሮፓጋንዳና ከንቱ ዉንጀላ ተስፋ እንዳያስቆርጠን፡፡ ይልቅ እልህና ወኔ ይጨምርልን! ለኛ መታሰር ብቻ ሳይሆን ትግላችንን ዉጤት እንዴት ያግኝ? የሚለው ያስጨንቀን፤ ለሁላችንም አላህ(ሱ.ወ) ጽናት ይሰጠን ዘንድ ዱዓ እናድርግ!

عرض المنشور في فيس بوك · تعديل إعدادات البريد الإلكتروني · الرد على هذا البريد الإلكتروني لإضافة تعليق.

ECLN





http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

# [Africa tv] የሰው ልጅ የማሰብነጻነት ሊኖረው ይገባል ይሉናል ዲሞክራት ነንባዮቹ ስለምን...

Tuesday, July 17, 2012 2:05 PM

**From:** "Harmend Minas" <notification+p_h7511m@facebookmail.com>
**To:** "Africa tv" <135925759803559@groups.facebook.com>

قام Harmend Minas بالنشر في Africa tv

**Harmend Minas** 18 يوليو 12:05 صباحاً



**የሰው ልጅ የማሰብነጻነት ሊኖረው ይገባል ይሉናል ዲሞክራት ነንባዮቹ ስለምን ሕዝበ ኤስላሙን በአጼዎች የግፍ አገዛዝ መርህ፣ የእኛ እናውቅልሀለን ፣ ወይ ተጠመቁ ወይ ሀገር ልቀቅ .....እያለ በማንፈልገውና ኤስላምን በማይከተል እምነት ይህ መንግስት ሊያጠምቀን አሊያምስም እየሰጠ ሊያስረን ተነሳ.....ወላሂ እንኳን ላንተ ለደም መጣጩ ይህንስም አልበጀውም መተማ በቁሙ ታረደ:: ስንቱንኡለማ እንዳላረደ.....!!**

عرض المنشور في فيس بوك · تعديل إعدادات البريد الإلكتروني · الرد على هذا البريد الإلكتروني لإضافة تعليق.

ECLN

ከዚ ጊዜያዊ የተኘ ጉዳ
መመሪያ ሉጎ
26/12/04

ታዛቢ
ከሳ ጊዜያዊ መ/ቤት
ሀገር ተከራከሪ
ጠበቃ ስም
ቁጥር 426-12/04

ከዚ ጊዜያዊ ዲሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ምርመራ ጽ/ቤት ማህተም ቤቱ

ከሳ ጊዜያዊ መ/ቤት
ሀገር ተከራከሪ
ጠበቃ ስም
26/12/04

ከዚ ጊዜያዊ ዲሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የመርመርያ ጊዜ 3

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ



882

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

# [Africa tv] የወያኔ መንግስት ህዝብ አፍኖ አስከመቸ ይኖራል ሰው በየ ቦታው በየቀኑ...

Monday, December 19, 2011 9:03 AM

**From:** "Amin Derraw" <fbmessage+p_h7511m@facebookmail.com>
**To:** "Africa tv" <135925759803559@groups.facebook.com>

Amin Derraw تم النشر في Africa tv.

Amin Derraw 19 ديسمبر 08:03 مساءً


'ወያኔ ግስት ህዝብ

የወያኔ መንግስት ህዝብ አፍኖ አስከመቸ ይኖራል ሰው በየ ቦታው በየቀኑ እየታሰረ ነው ይህንን መንግስት የተካወሙ፣ ጋዜተጎች እየታሰሩ ነው የሃይማኖት መሪዎች ከ መስጊድ እና በስተክርስትያን አየተባረሩ ነው ያገራቺን የምነት ቦታዎች እየፈረሱ ነው ዋጋ ያወቱትም አየተሸቱ ነው፣ በታም የሚያሳዝነው ግን በአማሪካ አና በይሮፕ የምንኖር ሰዎች ወያነ መንግስት ዛሬ ይሻለዋል ነገ አያሉ እሁንም የወያነ ደጋፌ ሆነው መቅረታቸው ነው፣ በተለይ ሙስሊም ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ይህ መንግስት ካለፉት ይሻላል የሚሉ አገራችን ወደፊት ማደግ የምትችለው በመለስ ዘናዊ መሪነት ብቻ ነው የሚሉ ከመለስ ዘናዊ ጋር እጅ እና ጉዋንት ሆነው የሚሰሩ ናቸው፣ አልፈው ተርፈው በውች የሚኖረውን ሙስሊም መለስን ካልደገፉቹህ አማነጭ አይደላቹህም የሚሉ በየ ቦታው ወያኔ ሲመታ የሚያቸበችቡ እና ከ ወያኔ ጋር ኮንትራት የፈረሙ ለት ለክን ለወያኔ የከሙ መጅሊስ ዳያስፖራ የሚል ስም የተሰታቸው ናቸው፣ ባለፈው ፮ ወር የሙስሊሙ ጉዳይ በተለያዩ ዘና ማሰራቻ መሰማቱ ያስቆታቸው ሙስሊሞች በውች የሚኖር ሙስሊም ተቃዋሚን መደገፍ የለባቸውም እያሉ ለወያኔ የቻሉትን ያህል እየታገሉለት ነው ነገር ግን ሙስሊሙ በዊች የሚኖረው ወያኔ በቃን አያሉ ነው።

عرض المنشور في فيس بوك · تعديل إعدادات البريد الإلكتروني · الرد على هذا البريد الإلكتروني لإضافة تعليق.

ECLN









http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[International Muslim Facebook Group] {ለተጨነቅን ኢትዮድያውያን ሁሉ!}** Wednesday, May 30, 2012 3:18 AM

**From:** "Dagi Ash" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "International Muslim Facebook Group" <369004106472442@groups.facebook.com>

Dagi Ash posted in International Muslim Facebook Group

**Dagi Ash** 10:18am May 30

{ለተጨነቅን ኢትዮድያውያን ሁሉ!}

1."ከማይፈፀም እሽታ በወቅቱ የሆነ እምቢታ የእሽታ ያህል ነው::!"{ለኢትዮድያ ፌደራል ጉዳዮች!} 2. "ወንድምህን መግደል ዕድቅ ከሆነ ለቃየን(ቃቢል) መቅደስ ሰርተህ አምልከው::!" {ለኢትዮድያ የፌደራልም ሆነ ክልል ፖሊሶች!} 3."አዋቂ ሰው ማነው?ከሊሎች የሚማር::!" {ኢትዮድያ ውስጥ ላሉ የሌላ እምነት ተ[illegible]ማት: በሙስሊሞች ከሚደርሰው ግፍ 'ነግ በኔ' በሉ!} 4."በርጋታ ተራመድ ቀውጢ ቀን ሲገጥምህ ትእግስትን ተመርኮዝ ህሊናህን ስለህ ዛሬ ጭልጥ ብላ ስትሆን ትላንትና ዞረህ ታያታለህ አልፈህታልና::!"{ብዙ መከራን ላሳለፉ ኢትዮድያውያን ሙስሊሞች: ይህም ቀን ያልፋል አይዞን እንበርታ!} 5."የጅረቶች ብዛት የዝናብ መዓት ....የውቅያኖስን ጣዕም እንደማይበርዙት ሁሉ የመከራ ውርጅብኝም የቆራጥ ሰው ህሊናን በድን አያደርገውም እንዳያ ያለ ሰው የታያልነት ሚዛኑን ይጠብቃልና::!"{ለአሚሮቻችን እና ለወጣቶ!} 6."የሌሎችን ስህተቶች ተገንዝበው ራሳቸውን ከስህተት የሚያርቁ ሁሉ ከፀፀት ነፃ ናቸው::ምክንያቱም ውሻንብር በሞላበት እና በሰፈነበት ዓለማችን ውስጥ ዋነኛ የታሪክ መዝገብ የሰው ልጅ ልምድ እንደ ማንኛውም የእውቀት ዘርፍ ተጨባጭና አስተማማኝ ነው::!"{ለጠቅላይ ሚንስትራችን!} 7."ትዕግስትና ወኔ የማያሸንፉት ምንም ነገር የለም::!"{ለተጨነቁ ኢትዮድያውያን ሁሉ!} 8."አልማዝ ሳይሞረድ እንደ ማያንፀባርቀው ሁሉ የነፃነት ጥያቄ ያለ መከራ ቦግ አይልም::!"{ለዚህ ዘመን ሙስሊሞች!} 9."ህይወት የምትመዘነው በዘመን ብዛቷ ሳይሆን በምታስመዘግበው የወኔ ክብደቷ ነው::!"{ለወጣቶቻችን!} 10."ፍርሃትን ለራስህ በጉያህ ሸሽገህ ወኔህን ከሌሎች ጋር ተካፈል::!"{ለፌስ ቡክ ተጠቃሚዎች በሙሉ::!}

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

DRAFT

http://ethcriminalawnetwork.com/

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLEN



http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[FEZEKIR CENTER] አሰላሙአለይኩም ያ ኡመተል ቁርአን**

Thursday, July 12, 2012 4:09 PM

**From:** "Abubeker Raja" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Abubeker Raja posted in FEZEKIR CENTER

**Abubeker Raja** 11:08pm Jul 12
አሰላሙአለይኩም ያ ኡመተል ቁርአን

ከጊዜ ወደ ጊዜ በፌስቡክ Social Networks ያለን ተሳትፎ እየጨመረ መምጣቱና የመረጃ የመለዋወጡ ሂደት የአንድነት አካሂዳችንን እያሳመረው መምጣቱ ይታወቃል:: አልሀምዱሊላህ!!!

ይህንንም ከግንዛቤ ውስጥ በመክተት ይመስላል በአዲስ አበባና በየክልሎች ባሉ መስጅዶች ስያተደረጉ ያሉትን የአንድነት የሰደቃና የዱዓ ፕሮግራም መሰረት በማድረግ በፌስቡክ ድህረ ገጽ ስያግሩፖቻችን እንድናዘጋጅ ሀሳብ ተሰንዝሯል :: በሀገር ውስጥ የሌሉና እነዚህን የአንድነት ፕሮፈስ ሊያላብሱ የሚችሉ ዝግጅቶች ላይ መሳተፍ ላልቻሉት ወንድሞችና እህቶች ጥሩ እድል ነው ተብሎ ይታሰባል::

የፕሮግራሙን አካሄድ በተመለከተ ሁሉም ፌዝቡከርስ(ሙስሊም የፌስቡክ ተጠቃሚዎች) ፕሮግራሙ የመጀመሩን ፖስት ከተመለከታችሁ በኋላ የሚሰማችሁን ሀሳብ በአንድነት ዙሪያ ፖስት በማድረግና ኮሜንት በመስጠት የተወሰነ ጊዜ እናሳልፋለን:: ይህም ማለት ባገኘነው የአንድነት መድረክ ያገኘነውን ጥቅም በመጠቀም፣ አንድነታችንን ጠብቆ ለመሄድ የሚያስችሉ መንገዶችን በመጠቆምና በመሳሰሉት ርእሶች አጠር ያሉ ጽሁፎችን ከምክር አዘል መልዕክቶች ጋር እናቀርባለን:: ጎን ለጎን ዱዓ ማድረግ የቻልን ሁሉ ነስር እንድናገኝ ዘንዳ አላህ እንለምናለን!!!
ሌሎቻችን 'አሚን' በማለት የጸሎቱ ተካፋይ እንሆናለን::
አያስማማም ያ ጀምዓ? መስማማታችሁን ግለጹልን!!!

እስቲ እንግዲህ በዚህ መከልከል፣ ማገትና ማገድ ከተቻለ በአብረን እናያለን
አላህ ይርዳን!!!




ETCHRLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

እንደምለው ቢያንስ ህገ-መንግስቱ ከተፃፈበት ቀለም በላይ ዋጋ ይኑረው፡፡ ኢህአዴግ ከመንፈሳዊ ተቋማቱ ላይ እጁን ይሰብስብ፣ ቢያንስ የተጠቀሰውን አንቀፅ ያክብር፡፡ አምን! ኃ/ስላሴ ተሳስተዋል፡፡ ሃይማኖት ሰይፍ፣ መንግስትም ሃይማኖታዊ ሰይፍ ሰንዛሪ እጅ ሊኖረው አይገባም፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲም ስሁት ነው እላለሁ፡፡ ምዕመናንን ለነፃ የእምነት ፍቃዶቻቸው አልተዋቸውምና፡፡

ኢህአዴግ መጅሊስን እና ሲኖዶሱን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማጥመቂያ መድረክ ማድረጉን ይገታ ዘንድ ምዕመናኑም በርትተው ይተጉ ዘንድ እጣራለሁ፡፡ በኑሮ ውድነት እና በአፋኝ አገዛዝ የምትሰቃዩት አንሶ ከአላህ እና ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ሰማያዊ ግንኙነት የፓርቲው ካድሬዎች ሲወስኑባችሁ ካለፍርሃት እምቢ በሉ፡፡ ‹‹ነፍስን እንጂ ስጋን የሚገሉትን አትፍሩ›› እንዲል የአንደኛው ሃይማኖት መጽሐፍ፡፡ ኢህአዴጋውያንም ተጠንቀቁ፣ ‹‹የመጅሊስ ይጠረጋል›› ንቅናቄ እናንተ ወደምትፈሩት የአረቡ ዓለም መሰል አብዮት ስላለመቀየሩ ማን እርግጠኛ መሆን ይችላል? ሰዓቱ እየቆጠረ ነው! እናም ‹‹ሙስሊም የኢህአዴግ አባላት፣ ክርስቲያን የኢህአዴግ አባላት፣ ኢ-አማኝ የኢህአዴግ አባለት ተሰብሰቡ፣ ተሰለፉ፣ ተበተኑ›› የሚለው ፖለቲካ ከ‹‹መአቱ›› አያድንም፤ አምን! አያድንም፡፡

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ተጠቃሚ ያደርግሃል የእምነትህን መሪም ከካድሬው መህል ይቀርብልሀል፣ ልክ እንደ ፖሊሲ
ፀሎትና የፀሎት ስርዓትንም ይቀርፁልሃል›› ይሉሃል፡፡

መንፈሳዊ ክንፍ ለምን?
በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ከዛሬ 20 አመት በፊት ጀምሮ ወሳኞች ‹‹ጥቂቶች ቆራጦች›› የህወሓት አመራሮች ናቸው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የህወሓት ሊቀመንበር ብቸኛው ወሳኝ ሰው ሆነዋል፡፡ በእርግጥ ይህ ማለት ሌሎች አስፈፃሚዎች ከጎናቸው የሉም እንደማለት አይደለም፡፡ እንዲህማ ሊባል አይችልም፤ ምክንያቱም የተለያዩ አጋዥ ክንፍ አሳቸውና፡፡ ለምሳሌ ብአዴን አንዱ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ክንፍ ነው፣ ኦህዴድ ሌላኛው ኦሮሞ ተናጋሪ ክንፍ ነው፣ የደቡብም፣ የሀረርም፣ የአፋርም.... ክንፍ አለ፡፡ ሆኖም ይሄ ብቻውን በቂ አይደለምና ‹‹መንፈሳዊ ክንፍ››ም አስፈለገ፡፡ እናም ብልሆቹ የህወሓት አለቆች የኦርቶዶክስ መንፈሳዊ ክንፍ፣ የእስልምና መንፈሳዊ ክንፍ፣ የፕሮቴስታንት መንፈሳዊ ክንፍ...እያሉ እሳት የላሱ ካድሬዎችን ፓትርያሪክ፣ ኢማም፣ ፓስተር... ሲሉም መደቧቸው፡፡
እናም እነዚህ መንፈሳዊ ክንፎች ለ‹‹ሰውየው›› የማያልቅ አብዮታዊ ምስጋና፣ የማያልቅ አብዮታዊ ፀሎት ማቅረብ እንዳለባቸው የሚዘነጉ አይደሉም፡፡ ለዚህም ነው ሰርክ በተግባራቸው በመጠመዳቸው ከአማኞቻቸው ጋር አይናና ናጫ የሆኑት፡፡ ሆኖም እነሱ ፓርቲው የሚደሰትበትን ሲሹ አያንቀላፉም፡፡ ለምሳሌ ቢዮንሴን የተባለች አዝማሪ የሚሊንየሙ እንግዳ ሆነ በመጣች ጊዜ ፓትርያርኩ በተገኙበት መንፈሳዊ ምስጋና የሆነው ‹‹ወረብ›› ቀርበላታል፡፡ እንደሚታወቀው ቢዮንሴ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችው ለቁልቢ ገብርኤል ንግስ አይደለም፤ ለዳንኪራ እንጂ፡፡ ብፁነታቸው ግን ምን እንዳደረጉ ያየነው ነው፡፡
ወደእስልምናም ፊትህን መልስ፣ ‹‹ሀይማኖታችንን ለእኛ ተዉልን፣ በእምነታችን፣ በስራአት-አምልኮአችን፣ በቅዱስ ቁርአናችን ጣልቃ አትግቡ›› ያሉ ሙስሊሞች ‹‹አሸባሪ፣ አክራሪ፣ ተሳላኪ፣ ፅንፈኛ...›› እየተባሉ ይፍረጃሉ፡፡ ለሌላ እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዊ ወንድማቸውም ስጋት እንደሆኑ ከአለም አቀፍ አሸባሪ ድርጅቶች ጋር እያቆራኙ ያስፈራሯቸዋል፡፡ ለዚህ አይነቱ ጥቃት ሙስሊሙን በዋናነት የሚያመቻቹት የኢህአዴግ ‹‹መንፈሳዊ ክንፍ›› መሪዎች ናቸው፡፡ መቼም ኢትዮጵያዊ ሙስሊም፣ ለኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ስጋት ነው የሚሉት ጨዋታ የምትመች አይደለችም፡፡ አሸባሪነትም ከእስልምና ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ ሌላው ቀርቶ እስልምና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገባ ማስታወሱ በራሱ ለዚህ በቂ መልስ ይመስለኛል፡፡ እንደሚታወቀው የእስልምና እምነት ከሳውዲአረቢያ በተነሳ ጊዜ ወደ ሰሜን አፍሪካ ሲሰፋፋ ‹‹እስልምና›› ብቻ አይደለም የተስፋፋው፣ የአረብ ባህልም ነው፡፡ Banu-hilal እና Banu Suliman የተባሉ የአረብ ጎሳዎች ወደ ሰሜን አፍሪካ ሲሰፋፉ እስልምናን ብቻ ይዘው ሳይሆን አረባዊ ባህላቸውንም ጨምረው ነው፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ግን ቅዱስ ቁርአኑ ብቻ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን አይሁድ እንዳልሆነው ሁሉ፣ ኢትዮጵያዊ ሙስሊምም አረብ አይደለም፡፡ እናም ኢትዮጲያውያን ሙስሊሞችን ‹‹አሸባሪ›› እያሉ ማሸማቀቁ ‹‹ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ...›› ካልሆነ በቀር ውሃ የሚቋጥር አይደለም፡፡
በእርግጥ ኢህአዴግ የራሱን ‹‹መንፈሳዊ ክንፍ›› ማደራጀቱ ከፓርቲው የጠቅላይነት ባህሪ ስንነሳ የሚጠበቅ ነው፡፡ በአናቱም የማኪያቪሌ ምክር አለ፣ ከፋፍለ ግዛ (Divided and Rule) በዚህ ቀመር መሰረትም እስልምናን ለክርስትና፤ ክርስትናን ለእስልምና ስጋት አድርጎ ማቅረብ አንዱ አስተምህሮት ነው፡፡ እናም እኔ እልሃለሁ ‹‹ይሄ ቀመር ተባኖበታል››
እ.ኤ.አ. በ1962ዓ.ም የታተመው የGeorge Lipsky "Ethiopia its people its society its culture" በሚለው መጽሐፉ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በ1945 ዓ.ም. እንዲህ ማለታቸውን ጠቅሷል "The church is like sward, the government is like an arm-therefore the sward can not cut by it self with out the use of the arm" (ሃይማኖት ሠይፍ ነው፤ መንግስት እጅ ነው፡፡ ሠይፍ ደግሞ ያለእጅ አይቆርጥም)
ከዚህ ሁሉ ውጥንቅት መውጫ መንገዱ አንድ እና አንድ ነው፡፡ እጅግ ብዙ ጊዜ ደጋግሚ

http://ethcriminalawnetwork.com/

ምስክር ይሆን ዘንድ ከዶ/ሩ ንግግር ልጭለፍልህ፡-
"When I was invited by D.r Shiferaw. I took some time to check the situation in Ethiopia before meeting with you... I believe the Ethiopian government Prime Minister Meles Zenawi, Shiferaw The Minister Of Federal Affairs and other Ministers understand the issues very well and they are taking the proper and wise steps. I thank all of them for their hospitality"
(በዶ/ር ሽፈራው ተጋብዤ ከመጣው በኋላ ከእናንተ ጋር ከመገናኘቴ በፊት በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ ለማወቅ ሞክሬአለሁ... የኢትየጵያ መንግስት፣ ጠቅላይ ሚስትር መለስ፣ የፌደራል ጉዳዮች ሚንስትሩ ዶ/ር ሽፍራው እና ሌሎችም ሚንስትሮች ጉዳዩን በደንብ ተረድተውታል ብዬ አስባለሁ፡፡ መደበኛና ትክክለኛውን መንገድም መርጠው ስለተደረገልኝ አቀባበልም አመሰግናቸዋለሁ)
ይህንን ነው እያልኩህ ያለሁት፡፡ ‹‹ወላጇ እያለች አዋላጇ አማጠች›› እንዲሉ ከኢ/ማሙ፣ ከመአዚኑ፣ ከሙፍቲው... ይልቅ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ክቡራን ሚኒስትሮቻቸው ‹‹አስፈላጊ ነው፤ አምነንበታል፣ ወደነዋል...›› የሚሉበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ እናም አልገባህም እንጂ የፖለቲካ መሪዎች መንፈሳዊ መሪዎችህም ነን እያሉህ ይገኛሉ፡፡
ሌላው ሐምሌ 12/2000 በታተመችው ‹‹አዲስ ነገር›› ጋዜጣ ላይ የተዘገበው ዜና እንደሚያትተው ደግሞ አቶ ማህቡብ መህመድ የመጅሊሱ ዋና ፀሐፊ የነበሩትን ሐጂ የሱፍን ተክተው ለሶስት ቀን ከሰሩ በኋላ በሶስተኛው ቀን ከሀላፊነታቸው እንዲነሱ በም/ፕሬዘዳንቱ ፊርማ መገደዳቸውን ተከትሎ ምክንያቱን ሲጠይቁ ‹‹መንግስት የፀሐፊነቱ ቦታ ለምን ተለወጠ ብሎ ስለጠየቀ ነው የሚል መልስ ሰጥተውኛል፡፡ እኔም መንግስትን እጠይቃለሁ›› አሉ ይላል፡፡ ይኼ ነው እንግዲህ የሃይማኖት ነፃነት፤ በህገ-መንግስቱ ‹‹አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ ናቸው፣ 2.መንግስታዊ ሀይማኖት አይኖርም 3.መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም›› የሚለው ድንጋጌ ትዝ ሲል ነው ህገ-መንግስቱ የኢህአዴግ መቀለጃ ወይም መሸወጃያ የሚሆንብን፡፡ መንግስታዊ ሀይማኖት የለም የሚባለውንም እርሳው! የመጅሊሱም ሆነ የሲኖዶሱ መሪዎች ቅርበታቸው ለሰማያዊው መንግስት አይደለም፤ ለምድራዊው የኢህአዴግ መንግስት እንጂ፡፡
መቼም በስልጣን ላይ ያለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጣልቃ ገብነት ከዚህ እስከዚህ ሊባል ስለማይችል አንድ ሁለት ማሳያዎችን ልጥቀስ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- በያዝነው አመት በመስከረም ወር በኩተቤ ኢትዮ-ቻይና ቴክኒክና ሙያ ካምፓስ የጀግናው ኢህአዴግ ካድሬዎች የእስላማዊ ሀይማኖታዊ ስልጠና እየሰጡ ነው፤ ቁርአንን ግን መሰረት አድርገው መስሎህ እንዳትስት፡፡ ምክንያቱም የስብከቱ መሰረት የፓርቲያቸው ፕሮግራምና የያዙት ስልጣን ነው፡፡ እናም ከአስልጣኞቹ አንዱ የአዲስ አበባ ፍትህ ቢሮ ሀላፊ አቶ ጸጋዬ ኃ/ማርያም እንዲህ አሉ ‹‹ቅንጅትና ኢህአዴግ አንድ ላይ ሊደራደሩ ይችላሉ?›› ጠየቁ፤ ተሳታፊዎቹም ‹‹አይችሉም›› ሲሉ በቡድን መለሱላቸው፡፡ ሀላፊውም ይበልጥ ቆፍጠን፣ ኮስተር ብለው ቀጠሉ ‹‹አዎ! እንደዚሁም መሆኑ አይቀርም፤ ኢህአዴግ እና ሱኒ አንድ ላይ ሊሆኑ አይችሉም!›› አሉናም የኢህአዴግን ‹‹በመቃብሬ ላይ ካልሆነ በስተቀር ድርድር የለም›› ፖለቲካን ደገሙት እልሃለሁ፡፡
መጋቢት 2003 ከታተመችው ቁጥር 10 ‹‹የሙስሊሞች ጉዳይ›› መጽሔት ደግሞ ማጣቀሻ አንውሰድ፡፡ ማጣቀሻውም ስለመንግስት ጣልቃ ገብነት የገለፀችበት ዘገባ እንዲህ ይላል፡- ‹‹በ1994 በኦሮሚያ ክልል በህዝቡ ምርጫ ወደ መጅሊስ አመራርነት የመጡ ባለስልጣናት ‹ደረሰብን› ባሉት በደል ምክንያት ለወቅቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ዳዊት ዮሐንስና ለኦህዴድ ዋና ፀሐፊ አቶ አባዱላ ገመዳ በጻፉት ደብዳቤ መንግስት ድንጋጌ በመጣስ የመንግስት ሹመኞች በህገ-ወጥ መንገድ ከስራ አግደውን በምትካችን ህዝብ የሚያውቃቸውን ወንጀለኞች ሾሙብን፡፡››
ይህ ነው እንግዲህ ከደርግ ‹‹ፈጣሪ የለም››ነት ወደኢህአዴግ ‹‹ልማታዊ ፈጣሪን›› ማምለክ የተደረገው ሽግግር፡፡ እናም የሸገር ልጆች እንዲህ ሲሉ ይነግሩሃል፡- ‹‹ኢህአዴግን እንደግል አዳኝ ከተቀበልክ ስራ ይሰጥሃል፣ የትምህርት እድል ይመቻችልሃል፣ ብድር ይፈቀድልሃል፣ የኮንደምንየም

http://ethcriminalawnetwork.com/

ብዬ አላስብም፡፡ እናም ደግሜ ደጋግሜ እጠይቃለሁ፡፡ ከዚህ በላይ የሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ማለት ምን ማለት ነው? እመነኝ ይህ አይነቱ አሰራር በሁሉም ሃይማኖት የሚተገበር ነው፡፡ ...ሌላ ተጨማሪ መረጃ ለማቅረብ ያህል በነባስታቶቹ ይገፋና ይገለል የነበረው የኢትዮጵያ ሙስሊም ወንድምና እህቶቻችንን ጉዳይ እንየው፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ‹‹ኃይማኖት የግል ነው፤ አገር ግን የጋራ ነው›› ያለው ነጋድራሰ ገብርህይወት ባየከዳኝ እንደነበረ ይነገራል፡፡ አፄ ኃ/ስላሴም ተቀብለው አስተጋቡት፤ ሆኖም በእላቸው ወናላቸው፡፡ እኔም እሰልሰዋለው ኢትዮጵያና ሌሎች ነብያት ያላቸውን ትስስር ያህል፤ ኢትዮጵያና ነብዩ መሀመድም አላቸው፡፡ እናም ኢትዮጵያዊ ለመባል በምድሪቷ መወለድ እንጂ የአንድ ሃይማኖት ተከታይነት በፍፁም ቦታ የለውም፡፡ ኢትዮጵያ የማንም አይደለችም- ከኢትዮጵያውያኖች በቀር፡፡ የማንም ወደብም፤ ደሴትም፤ ባህርም አይደለችም፡፡

ለዚህም ነው የአወሊያ ተማሪዎችን ጥያቄ ተከትሎ በርካታ ሙስሊሞች ኢማም፤ ሙአዚን፤ ሙፍቲ፤ ኡላማ፤ ዳኢ፤ ደረሳ፤ ኡስታዝ፤ ሀጂ፤ ሼኽን.... ከቁራን እንጂ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አንቀበልም ሲሉ በየጁማው ሀብረ-ድምፃቸውን እያሰሙ ያሉት፡፡

የእስልምና እምነት ተከታዮች ጥያቄ ሲጨመቅ እንዲህ የሚል ሆኖ ታገኘዋለህ፡- መጅሊሱ (የእስልምና ጠቅላይ ጉዳዮች ም/ቤት) የሚመሰረተው በሙስሊም ምዕምናን ምርጫ ብቻ ነው፡፡ ወይም ስልጣን ላይ ያለውን መጅሊስ አንፈልገውምና ይውረድ ሊባል የሚችለው በሙስሊሙ እንጂ በዶ/ር ሽፈራው ኃ/ማርያም አሊያም በኩማ ደመቅሳ ፍላጎት አይደለም፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ‹‹አህባሽ›› የሚባል የእስልምና አስተምህሮትን ‹‹ተቀበል››፤ ‹‹አልቀበልም›› በሚል በመጅሊሱና በምዕመናኑ መካከል የከረረ ውዝግብ ተፈጥሮ እያየን ነው፡፡ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርም የአንድ ‹‹ኡላማ››ን ያህል ስለ አህባሽ እስላማዊነት እየሰበኩ እንደሆነ እየሰማን ነው፡፡ ለምሳሌ በሐምሌ 2003 ዓ.ም. በሐረር ሐረማያ ካምፓስ በፌዴራል ጉዳዮችና በመጅሊስ ትብብር በተዘጋጀው ‹‹የአህባሽ›› ስልጠና ላይ ዶ/ር ሽፈራው እንዲህ አሉ፡-

‹‹ከመጅሊሱ አውቅና ውጪ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ይቁሙ ብላችሁ ያሳረባችሁት አለ፡፡ ሼክ አህመዲን የሚያነሱት እንደተጠበቀ ሆኖ በኛ በኩል ከፍቃድ ውጪ የሚደረግ ትምህርት፣ ዳዕዋ፣ ስብከት፣ ከፈቃድ ውጪ የሚሰሩ መድረሳዎች፣ ከፈቃድ ውጪ የሚሰሩ መስጊዶች፣ ከፈቃድ ውጪ የሚሰሩ ኹጥባዎች ሁሉ መቆም አለባቸው ነው የምንለው››

የተከበሩ ሚኒስትር ለዳዕዋ እና ስብከት ፈቃድ ጠይቁኝ ማለታቸው በእጅጉ አስቂኝ ነው፡፡ መቼም በዚህ አያያዛቸው ሚኒስትሩ መስጊድ ለመሄድም ሆነ ለመስገድ ‹‹ቲን ነበር›› (Tin Number) አውጡ ከማለት የሚመለሱ አይመስሉኝም፡፡ ‹‹የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የብቸኛ ጠቅላይነት ጨዋታ ህግጋትም›› ይሉሃል ይህንን ነው፤ ሌላ አይደለም፡፡

አሺ እንቀጥል፡- የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ወይም የመጅሊሱን አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊነት (መንፈሳዊነቱ እንኳ ለጊዜው ይቆይ) እንመልከት፡፡ ደህና! እስቲ ደግሞ መጅሊሱ በ04/11/03 ‹‹ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር›› የፃፈውን ደብዳቤ እንየው፡፡ ‹‹ጉዳዩ ትብብር ስለመጠየቅ›› ይላል የደብዳቤው ርዕስ፡፡

‹‹የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴርና የኢ/ኦ/ጉ/ጠ/ም/ቤት በመተባበር ለጠቅላይ ም/ቤቱ ስራ አስፈፃሚዎችና ለሁሉም ክልሎች ኦ/ስ/ጉ አስፈፃሚዎች እንዲሁም የሁሉም ስራ አስፈፃሚዎች ከሐምሌ 16/11/03 ጀምሮ በሀረር ካምፓስ በሀረማያ ዩንቨርስቲ ሀገራዊ ስልጠና ይሰጣል፡፡ በዚሁ ስልጠና ሁሉም ስራ አስፈፃሚ ወደተባለው ቦታ ስለሚመጡ ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ዞን ያሉትን የእስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ባዶ ስለሆነ በእናንተ በኩል ለሁሉም ክልሎችና ዞኖች መስተዳደሮች የሙስሊሙ መሪዎች ለስልጠና የሄዱ መሆኑ ታውቆ አስፈላጊውን የስራ ትብብር፣ ክትትል፣ እንዲሁም ለም/ቤቶቹ ጽ/ቤት አስፈላጊ ጥበቃ እንዲደረግልን መመሪያ እንዲያስተላልፍልን በአክብሮት እንጠይቃለን›› ይላል ደብዳቤው፡፡

ሌላ እንጨምር ዶ/ር ሰሚር የተባሉ ሊባኖስያዊ የአህባሽ ሰባኪ ወደ ኢትዮጵያ አህባሽን ለመስበክ መጥተው ነበር መቼም ዶ/ሩን የጋበዛቸው መጅሊሱ ወይም የአንዱ መስጊድ ኢማም እንዳይመስልህና እንዳትሳሳት፡፡ ምክንያቱም ሰባኪውን የጋበዘው አውራው ፓርቲ ነውና፡፡ ለዚህም



http://ethcriminalawnetwork.com/

ሊያሾማቸው አይችልም፡፡ ነገር ግን ተሾመዋል-ጊዜው የአሸናፊዎች ነውና፡፡ መቼም የአቡኑ ወደመንበሩ መምጣት ከኢህአዴግ ጋር መያያዙ አከራካሪ ጉዳይ አይመስለኝም፡፡ በእርግጥ ማስረጃ የሚፈልግ ዊክሊክስን መጎብኘቱ ብቻ በቂ ነው፡፡ አምን! በወቅቱ የኢህአዴግ ሁለተኛ ሰው፣ በዚህ ዘመን ደግሞ ‹‹ፓስተር›› የሆኑት ታምራት ላይኔ ለአሜሪካው አምባሳደር ዶናልድ ቡዝ ‹‹እኛ ከጫካ አዲስ አበባ ስንገባ በስልጣን ላይ የነበሩት ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ከስልጣናቸው እንዲባረሩ የተደረጉት በእኔ ፊርማ ነው›› ሲሉ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋልና፡፡ በዚህ ብቻ የሚገታ እንዳይመስልህ የአባታችንና የፓርቲያችን ፍቅር፣ ምክንያቱም ‹‹የግንቦት 20 ፍሬ›› የሆኑት አቡነ ጳውሎስ ከእምነቱ ተከታዮች እና ከአንዳንድ ጳጳሳት የሚደርስባቸውን ተቃውሞ ሁሉ እያፈኑ እና እየደፈጠጡ እዚህ የደረሱት በማን ድጋፍ ይመስልሃል? መቼም ‹‹ሚካኤል በሰይፉ ጠብቋቸው ነው›› እንደማትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ሊላው ቢቀር ድህረ ምርጫ 97ን ተከትሎ የተነሳውን ተቃውሞ አስታኮ በ1998 ዓ.ም. የጥምቀት በዓል ሲከበር፣ ሾላ አካባቢ የሚገኘውን የካ ሚካኤል ያጀቡ ምዕመናኖች የዘመሩትን መዝሙር ትረሳዋለህ ብዬ አላስብም፡፡ ምንአልባት ማስታወሱ አስፈላጊ ከሆነም መዝሙሩ ይኸው፡-

‹‹ጳጳሱ ፌዴራል ናቸው
ሚካኤል ፍረድባቸው››

እሺ! እንግዲያስ ብፅዑ ወቅዱስነታቸውን ሚካኤል ካልጠበቃቸው የጠበቃቸው አንድ ሀይል አለ ማለት ነው፡፡ እናም እኔ እልሃለሁ እመነኝ ያ ሀይል የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንጂ የሌላ የማንም አይደለም፡፡ ለምሳሌ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ ‹‹በስም›› ከፓትርያርኩም ስልጣን በላይ እንደሆነ የሚነገርለት ‹‹ሲኖዶሱ›› ጠቅላላ ጉባኤውን አድርጎ ነበር፡፡ የአድል ጉዳይ ሆኖም በዛ ጉባኤ አቡነ ጳውሎስ ስልጣን ከያዙ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሲኖዶሱ ሰምትውት የማያውቁት ብርቱ ተቃውሞ ቀረበባቸው፡፡ በወቅቱም ስለነበረው ሁኔታ አዲስ ነገር ጋዜጣ የሰራውን ዜና እንደወረደ ላቅርብልህ፡-

‹‹ለሳምንታት በውዝግብ ውስጥ የቆየው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ አስቸኳይ ጉባኤው ትናንት አርብ ሐምሌ 10 ቀን ከሰዓት በኋላ ተጠናቀቀ፡፡ ጉባኤው ለዚህ ሳምንት ከተያዙለት አጀንዳዎች ብዙዎቹን አልተመለከታቸውም፡፡ ፓትርያርኩ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ላይ የጣሉትን እገዳ ሲኖዶሱ ማንሳቱ የተገለጠ ሲሆን ፓትርያርኩ ከአስተዳደር ስራ እንደወጡ ቀርቦ የነበረው ሀሳብ ሳይነሳ ቀርቶ ፓትርያርኩ በነበሩበት ሁኔታ ቀጥለዋል›› ይልና የጋዜጣው ዘጋቢ ሶኖዶሱ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰበትን ምክንያት እንዲህ ሲል ያቀርበዋል፡፡ ‹‹ጉባኤው ሐሙስ ጠዋት ይመለከተዋል ተብሎ የነበረው አጀንዳ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ረዳት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሳሙኤልን ጉዳይ ነበር፡፡ ይህን አጀንዳ እያሰላሰሉ ወደየማረፊያቸው ከተበታተኑት ጳጳሳት አምስቱ ግን ሌሊቱን ያሳለፉት እንዳሰቡት አልነበረም፡፡ ረቡዕ ምሽት ከ4፡00 ጀምሮ አምስቱ ሊቃነ ጳጳሳት ያልጠበቋቸውን እንግዶች ለማስተናገድ መገደዳቸውን ለጳጳሳቱ ቅርብ የሆኑ ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ በውዝግቡ ሰሞን የሲኖዶሱ ጊዜያዊ ስብሳቢ ሆነው ተመርጠው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ማረፊያ ቤት ባልታወቁ ሰዎች መገንጠሉን የቤተ ክህነቱ ምንጮች አረጋግጠዋል፡፡ ማንነታቸው ያልታወቁት ሰዎች በአካባቢው በተሰማው ድምፅ ጳጳሱ ወደነበሩበት ውስጠኛ ክፍል ሳይገቡ መሪዳቸውን ብፁዕነታቸው ለፖሊስ በሰጡት ቃል ማረጋገጣቸውንም ገልፀው ምንጮች ተናግረዋል፡፡ የብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ እና የብፁዕ አቡነ ሩፉኤል ቤቶች በሮችም መጻኅደዳቸውንና የማስጠንቀቂያ ንግግሮች ከውጭ መሰማታቸውን ለጳጳሳቱ ቅርብ የሆኑ ምንጮች ባለቤቶቹን ዋቢ በማድረግ ይናገራሉ፡፡ በሌላ በኩል ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ እና የሥራ አስኪያጁ አባል የሆኑት ብፁዕ አቡነ መልከፃዲቅ ግን መታወቂያ አሳይተውናል ባሏቸው ሰዎች ተከታቸው ተወስደው መመለሳቸውን የሲኖዶሱ ምንጮች አረጋግጠዋል፡፡›› ብላለች ‹‹አዲስ ነገር›› ጋዜጣ፡፡

መቼም እነዚያ ዛሬም ድረስ ቢሆን ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎች በር የገነጠሉት መቋሚያና ፅናፅን ታጥቀው እንዳይመስልህ፡፡ ወይም ሁለቱን ጳጳሳት ‹‹መታወቂያ በማሳየት›› የወሰዷቸው ግለሰቦች ያሳዩአቸው መታወቂያ የቲዎሎጂ (የመንፍሳዊ ኮሌጅ) መታወቂያ ነው የሚል ቀልደኛ ይኖራል


http://ethcriminalawnetwork.com/

የእነአሞራውና የእነቾሺ ገብሩ መስዕዋትነት ታክሎበት እንዳይሆን እንዳይሆን ሆኖ ወደቀ፡፡
ከውድቀቱ በኋላም በአዋጅ የተሻረው ፈጣሪ በህገ-መንግስት ተመለሰ ተባለ፡፡ እነሆም ሰለፈጣሪ
መመለስ የተበሰረበት ህግ ምዕራፍና ቁጥር፡-
‹‹ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው
የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ የመቀበል፣ ሃይማኖትና እምነቱን ከሌሎች ጋር
በመሆን ወይም ለብቻው በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣
የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል፡፡›› (የኤፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 11፣ ንዑስ
አንቀጽ 1)
በእርግጥም አሸናፊዎች ባለንፈሬ ታጋዮች የሃይማኖት ነፃነትን በተመለከተ ይህንን ብቻ አይደለም
በህግ የደነገጉት፡፡ ሌላም አላቸው፤ በግልፅ እንዲህ የሚል፡-
‹‹በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች
ሃይማኖታቸውን ለማደራጀት፣ ለማስፋፋት የሚያስችላቸውን የሃይማኖት ትምህርት፣ የአስተዳደር
ተቋም ማቋቋም ይችላሉ›› (የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 11፣ ንዑስ አንቀፅ 2)
መቼም ይሄ እፁብ ድንቅ አዋጅ ነው፡፡ ያውም ራሳቸውን የምድር አማልክት ባደረጉ ወታደሮች
የተመሰረተ መንግስት በወደቀ ማግስት የተሰማ አዋጅ! ግና ምን ዋጋ አለው! ‹‹ነበር ባይሰበር›› ሆነ
እንጂ? (‹‹ነበር ባይሰበር››ን ወደታች እናየዋለን)
...ከዚህ ቀደም ደግመን ደጋግመን እንድተነጋገርነው ደርግና ኢህአዴግ በአፈፃፀም እንጂ በአካሄድ
ፍፁም የተለያዩ ናቸው፡፡ ደርግ አንጃ ግራንጃ አያጠዛም፣ ዴሞክራሲ፣ ነፃ ፕሬስ፣ ሰብዓዊ መብት፣
ሰማያዊ መብት... ቅብርጥሶ የሚባል ‹‹ግርዶሽ››ም የለውም፤ ወይም አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም
ደርግ ‹‹ነፍሴ›› ምንም ይሁን ምን መቀበል እንጂ መቃወም እንደማይቻል በግልፅ ‹‹እኛ
ወታደሮች ነን ደማችን ቶሎ ይፈላል›› ብሎሃልና፡፡ እንደአየኸውና እንደሰማኸውም ህዝባዊ
መንግስት፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሃይማኖት ነፃነት... ያሉ ሀገር ወዳዶች፣ ሀገር ወዳድ ነን ባሉ
ወታደሮች እንደወጡ ቀርተዋል፡፡
ኢህአዴግ ‹‹ነፍሴ›› ጋ ስትመጣ ግን ይኼ የለም፡፡ ሲጀመርም የኢህአዴግ ልጆች ወታደሮች
አይደሉም-ታጋዮች ናቸው፡፡ በቃ! ታጋይ ማለት አንተ ስትራብ አብሮ የሚራብ (በእርግጥ አመራሩ
ለረሃብተኛ የመጣ ስንዴን፣ ረሃብተኛው እንደቅጠል ቢረግፍም ሽጦ ጠመንጃ ከመግዛት
አይመለስም፡፡ ይሄ ግን ሁልጊዜ አይደለም፡፡ አልፎ አልፎ ነው፣ ሁልጊዜማ ዕርዳታም የለ)፤ ብቻ
ታጋይ ማለት ድርጅትን እንጂ መሪውን የማያመልክ፣ የማያንቆለጳጵስ (የነፃን አያድርገውና)
ነው፡፡ የትኛውም ታጋይ በበረሃ ቆይታው ያለውን ችግር ፊት ለፊት ይናገር ነበር፡፡ መለስም ላይ
እንኳ ቅሬታ ቢኖረው ‹‹ተጋዳሊ መለስ...›› ብሎ ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ በግልግማ ይተቻቸዋል፡፡
በረከት ስምኦንንም ሆነ አዲሱ ለገሰንም እንዲሁ ታጋዩ እኩል ምክንያት ጠቅሶ ይከራከራል፡፡ ይህ
የሆነው ለምን መሰለህ? ታጋዩ እርሻውንም ሆነ ትምህርቱን ትቶ የተሰባሰበው ‹‹የተጨቆኑ ህዝቦች››
አሉ ተብሎ ሲነገረው ‹‹ነፃ ላውጣ›› በሚል ስለሆነ ነው፡፡ በተቀረ ማንንም ጠይቅ ወይም የትግሉን
ታሪክ (ሚዛናዊ ሆነው የተፃፉትን) አንብብ ያ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ከቤቱ የወጣው አንተና እኔን ስልት
በቀየረ አዲስ ጨቋኝ ለመጨቆን አልነበረም፡፡
የሆነ ሆኖ ኢህአዴግ እና መለስ ወይም መለስ እና ኢህአዴግ የሃይማኖት ነፃነት አውጀዋል አልኩህ
እንጂ በሃይማኖት ጣልቃ አይገቡም አላልኩህም፡፡ እንዲህማ ልልህ አልችልም፡፡ እንዴትስ
እልሃለሁ? ለምሳሌ እነ መለስ ደርግን አሸንፈው አዲስ አበባ ሲገቡ ከበረሃ ይዘው የመጡት የብሔር
ፖለቲካ እና በቋንቋ ላይ የተመሰረተውን የፌዴራሊዝም ስርዓት ብቻ አይደለም፡፡ ለኦርቶዶክስ
ክርስትና እምነት ተከታዮች ‹‹ፓትርያርክ››ም ይዘውላቸው ነው የመጡት፡፡ ያውም ዶ/ር ብፁዕ
ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን፡፡
በእርግጥ እኒህ ብፁዕ አባታችን ‹‹እግዚአብሔር የለም›› በሚለው ደርግ ወደእስር ቤት
ተወርውረው ምድራዊ መከራን ተቀብለዋል፤ ሆኖም ይህ ብቻውን ከእምነቱ ቀኖናና ዶግማ
(Dogma) ውጭ በሆነ ሁኔታ ‹‹እግዚአብሔርም አላህም ከወዴትም አይደለም፣ ከሰማይም
አይደሉም፣ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንጂ›› በሚለው እምነት የለሹ ኢህአዴግ ፓትርያርክ ሆነው


http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

# [ETHIO ISLAMIC ART AND DA'AWA GROUP] ሲኖዶሱ እና መጅሊሱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማጥመቂያ?

Tuesday, March 20, 2012 4:32 AM

**From:** "Ali Shiferaw" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "ETHIO ISLAMIC ART AND DA'AWA GROUP" <ethioislamicart@groups.facebook.com>

Ali Shiferaw posted in ETHIO ISLAMIC ART AND DA'AWA GROUP.

ሲኖዶ እና መጅ

**Ali Shiferaw** 11:32am Mar 20


ሲኖዶሱ እና መጅሊሱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማጥመቂያ?
በተመስገን ደሳለኝ

ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ሼህ፣ ኢማም፣ ኡላማ፣ ደረሳ፣ ፓስተር፣ ዘማሪ፣ ካድሬ፣ ጠርናፊ፣ ተጠርናፊ፣ ሊግ፣ ማህበር፣ ፎረም፣ ግንባር ቀደም አርሶአደር፣ ልማታዊ ባለሀብት፣ ልማታዊ ጋዜጠኛ፣ ልማታዊ አርቲስት፣ ልማታዊ ማስታወቂያ ሰራተኛ፣ ልማታዊ እድር፣ ልማታዊ ማህበር፣ ልማታዊ... ማን ቀረ? ማንም፡፡ እናም በዛሬ ጊዜ እመንም አትመንም የእነዚህ ሁሉ ምንጭ መለስ እና ኢህአዴግ ናቸው፡፡ በተቀረ የእምነት/ሀይማኖት መገኛ ቤተክርስቲያን እና መስጊድ መሆናቸው ከቀረ ዘመን አልፎበታል፡፡ ስብከትም ሆነ ዝማሬ አሊያም ዝየራ ከመፃህፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁራን ሳይሆን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ከተሰኘው እስታሊናዊ መፀሀፍ ነው፡፡ መምህሩም አንድ አሳቸው ‹‹ዘላለማዊው›› ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ለሲኖዶሱም ሆነ ለመጅሊሱ እየሱስና ነብዩ፣ ወይም ሙሴና ሙሳ ቦታ የላቸውም፡፡ ሆኖም በዚህ ቅር አትሰኝ፣ ምክንያቱም ለአብዮታዊ ዲሞክራሲና ለ‹‹ሰውየው›› ገለታ ይድረሳቸውና አብዮታዊያን ‹‹ሙሴ›› እና ‹‹ሙሳ››ን አዘጋጅተውልኻል፡፡

አፅመ-ታሪክ
እንዲህም ይጀምራል፡- ከዕለታት አንድ ቀን ጠረፍ ጠብቁልን ያልናቸው ወታደሮች ተሰባሰቡና መንግስት መሰረቱ፡፡ የተመሰረተው መንግስትም ምድራዊ አይደለምና ሊተች፣ ሊነቀፍ፣ የስራ ማቆም አድማ ሊደረግበት፣ የተቃውሞ ሰልፍ ሊወጣበት... አይገባም ሲሉ አዋጅ አወጁ፡፡ አዋጁም እንዲህ እንደዛሬው መወንጀያ ከመሆኑ በፊት ‹‹የኢትዮጵያ ትቅደም አሳማን የሚቃወም...›› በሚል የሚጀምር ‹‹አማላይ›› እንደነበር ወደዚንባቤ ጎራ ብለህ ማረጋገጥ ትችላለህ፡፡ ምናአልባትም ዚንባቤ የሚርቅህ ከሆነ በቅርቡ ከእስር የተፈቱትን ‹‹የቀድሞ ትናንሽ አሻልክት››፣ የደርጉ መስራች ባለስልጣናትን ፈልገህ ጠይቃቸው ‹‹ተፀፅቼአለሁ›› ብለዋልና ሳይደብቁ ይነግሩሀል፡፡ የሆነ ሆኖ ባለፈው መንግስት ውስጥ የነበረው ‹‹ሀይማኖት››አንድ ነው፡፡ መጠሪያውም ‹‹ሶሻሊዝም›› የተሰኘ ሲሆን አማልክቱም ከፍ ሲል ሌኒንና ጓደኞቹ፣ ዝቅ ሲል መንግስቱ ኃ/ማርያምና ግብረ አበሮቹ ነበሩ፡፡ በተረፈ እግዚአብሔር፣ አላህ፣ ኢየሱስ፣ ቡድሃ፣ ባሂ... ጂኒ ቁልቋል በ1967ቱ አዋጅ ተሽረዋል፡፡ መሻራቸውንም ተከትሎ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ከጳጳሳቱ፣ ከሼሁ፣ ከፓስተሩ ተመርጠው መስዋዕት ሆኑ፡፡ ከዚህ በኋላም እውነት እውነት እልሀለው ለ17 አመታት ያህል ምድሪቱን ሞልተዋት የነበሩት መንጌ እና ጓደኞቻቸው ብቻ ነበሩ፡፡ እነሆም ይህ ከስጋም ከነፍስም የተጣላው የመንግስቱ ኃ/ማርያም መንግስት በመለስ ዜናዊና ጓደኞቻቸው ብርቱ ትግል፣ተራራ መውጣትና መውረድ (ማንቀጥቀጥም) ተጨምሮበት፣ እንዲሁም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/



View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECHR



http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[FEZEKIR CENTER] አሳዛኝ የግፍ ዜና**

Wednesday, May 23, 2012 5:02 AM

**From:** "Amdihun Yusuf" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Amdihun Yusuf posted in FEZEKIR CENTER

አሳዛኝ የግፍ ዜና

**Amdihun Yusuf** 12:02pm May 23

አሳዛኝ የግፍ ዜና

ኢናሊላሂወኢና ኢለይሂ ራጂኡን

በሴት ሙስሊሞች ላይ የሚደረሰዉ ግፍና መከራ እንደቀጠለ ነዉ:: ይህም የግፍ ዜና ምንጮቻችን እንደዘገቡልን እናቀርበዎል:: ጉዳዩ እንደሚከተለዉ ነዉ በቅርቡ የፈጸሪል ጉዳዮች ከየክፍለ ከተማዉ የተመረጡ ሰዎችን በመጥራ ስብሰባ አካሂዶ ነበር:: በዚህም ስብሰባ ላይ ከኮልፌ ክ/ከተማ ሶስት ሰዎች የተሳተፍ ሲሆን ሁለት ወንድ እና አንዲት ሴት ይገኙበታል:: በዚህ ስብሰባ ላይ የኮልፌ ክ/ከተማ ነዎሪ የሆነችዉ ፍርዶስ የተባለች እህታችን ትገኝበት ነበር:: በዚህ ስብሰባዉ ላይ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ/ር ሽፈራዉ ተገኝተዉ ስብሰባዉን አስተባብረዉ እንደነበር ምንጮች ገልፀዎል:: በስብሰባዉም ላይ ዶ/ር ሽፈራዉ እጅግ አፀያፊና ድንበር ያለፉ ንግግሮችን በህዝበ ሙስሊሙ በተመረጡት ኮሚቴዎች ላይ በመናገራቸዉ ይህንን የሰዉየዉን ዘለፋና ስም ማጥፋት መሸከም እና መታገስ ያቃታት እህታችን ፍርዶስ ዶ/ር ሽፈራዉ ለተናገረዉ ንግግር እልህ በተሞላበት ቃል ተቃዉሞአን በመግለፅ "ዶ/ር ሽፈራዉ ሴት የሴት ልጅ ነህ" በማለት የስብሰባ አዳራሹን ጥላ ወታለች:: ከአዳራሹ ወታ ወደግል መኪናዎ(የመኪናዎ ስም ቶዮታ ቪትዝ ነዉ) በማምራት ወደ መጣችበት ለመሄድ እንቅስቃሴ ስትጀምር በሁለት ሳንደግሩዘር መኪና ደህንነቶች ተከትለዉ ያስቆሟትና አፍነዉ እያንም መኪናዎንም ይዘዎት የሰወሯለ:: ከዚ ቡሀላ ነበር እህታችን ፍርዶስ ላይ ይህንን ኢ ሰብአዊ ድርጊት የፈፀሙባት:: እህታችን ፍርዶስን ያለምንም እርህራሄ በኤሌክትሪክ ሾክ አቃጠሏት:: ወድያዉኑ እህታችን መናገርም መንቀሳቀስም አቆመች::ይህንን ኢ ሰብአዊ ድርጊት ከፈፀሙባት ቡሀላ መኪናዎን እና እያን መኖሪያ ቤታ በር ላይ ጥለዎት ሄዱ::ቤተሰቧ እጅግ በመደናገጥ ልጃቸዉን ለመታደግ ጥረታቸዉን ተያያዙት:: የፍርዶስ አባት የልጃን ሂወት ለመታደግ ለህክምና በፍጥነት ወደ ዉጪ ሀገር (ሳኡዲ አረቢያ) ይዚት ይሄዳል:: ነገር ግን በኤሌክትሪክ ሾክ ከጥቅም ዉጪ ባደረጉዎት ደህንነቶች ምክንያት የአላህ ዉሳኔ ሆነና ፍርዶስ ለህክምና በሄደችበት ይህንን መራራ ስቃይ ተገላግላ ወደ አኹራ ነጎደች:: ኢና ሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂኡን! ይህ ሁላ ግፍ ሳይበቃ ይህንን የፈፀሙትን ግፍ እንዳይሰማባቸዉ ለማድረግ ወላጅ እናቷን አፍነዉ ወስደዉ እስካሁን ድረስ እናቷ የደረሱበት አልታወቀም::

እንደምታስታዉሱት በቅርቡም በአንዲት የሸዕፈር መስጂድ ጀምአ አባል በሆነች እህታችን ላይ ተመሳሳይ አፈና አካሂደዉ አንድም ሰዉነቷን ሳያስቀሩ እራሷን ስታ አስችተዉሮት ድረስ በመደብደብ አዉራ መንገድ ላይ ጥለዎት ሄደዉ እስካሁን አልጋ ላይ እንደሆነች የሚታወስ ነዉ:: ኧረ ያ አላህ መከራችን ይብቃቹ በለን:: በሙስሊሞች ላይ የሚደርሰዉን ግፍና መከራ ላልሰሙት እናሰማ! ሁሌም በዳይ እንደበደለ አይቀርም! የእጁን ያገኛል ኢንሻላህ! ይህንን የመንግስት አካላት እየፈፀሙ ያሉትን ግፍና በደል ላልሰሙት በማሰማት እና እህታችንንም አላህ ጀነት እንዲያስገባልን በዱአ እንለምነዉ

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[Rmadan (ረመዷን)] እኛ ሙስሊሞች ያቀረብነው ሐይማኖታዊ የመብት ጥያቄ ዛሬም ምላሽ ሳይሰጠው...**

Thursday, June 28, 2012 11:45 PM

**From:** "Ibn Nuru" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "Rmadan (ረመዷን)" <371653972893346@groups.facebook.com>

Ibn Nuru posted in Rmadan (ረመዷን)

**Ibn Nuru** 6:45am Jun 29

እኛ ሙስሊሞች ያቀረብነው ሐይማኖታዊ የመብት ጥያቄ ዛሬም ምላሽ ሳይሰጠው ስድስት ወር ሆኖታል. 1966 ጨቁአኝ በሚባለው ሀይለ ስላሴ ጊዜ ሙስሊሞች ባደረጉት የአንድ ቀን ተቃውሞ ኢድ አረፋና መውሊድ በይፋ እንዲከበሩና መጅሊስ እንዲመሠረት ተፈቅዶአል ከዛን ጊዜ ሠላማዊ ሠልፍ አድራጊዎች ውስጥ የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስተር አንዱ ናቸው በአንድ ቀን ለልፍ ሙስሊሐሙ አምባገነን በሚባለው መንግስት ከላይ የጠቀስኩአቸው ነገሮች ተፈቅደውለታል ዛሬ ራሱን ዲሞክራሲያዊ ነኝ የሚለው መንግስት ግን መስጂድ ማዕከል ያደረጉ ጥያቄዎች ሲቀርብለት ከመመለስ ይልቅ ይባስ ብሎ አሸባሪዎች እያለን ይገኛል ሙስሊሞችን እያሠረ እና እያንገላታ ይገኛል አሁንም ጥያቄያችን ሐይሞኖታዊ ነው መልስ ስጡን ለፈደራል ጉዳዮች ሲቀርብ ሕጋዊ የሆነ ሐይማኖታዊ ጥያቄ ነው ተብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ሲቀርብ ሕገ-ወጥ ሊሆን አይገባም እኛ ሙስሊሞች ሌላውን የሚንገድልበት ምክንያት የለንም እኛ የምንሞትለት አላማ ግን አለን እሱም እምነታችን ነው የዛሬን ጁመዐ አወሊያ እንገኝና ድምፃችንን እናሰማ

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

196
የመዝገብ ቤት
DRAFT

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[Anti Ahbash- New Group] የ አለማችን መርጥ ቀልድ ።**

Wednesday, May 30, 2012 11:00 AM

**From:** "Aisha Bint Abubeker" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "Anti Ahbash- New Group" <antiahbashnew@groups.facebook.com>

Aisha Bint Abubeker posted in Anti Ahbash- New Group

**Aisha Bint Abubeker** 6:00pm May 30

**የ አለማችን መርጥ ቀልድ ።**

መንግስት የመጅሊስን መርጫ አስመልክቶ ሰሞኑን እየቀለዳቸው ያሉ ቀልዶች እኛን ኢትዮጲያን ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ክርስቲያን ወንድሞቻችንን ሳይቅር እያሳቀና እያሳዘነ ይገኛል።

ነገሩ እንዲህ ነው ....
"መንግስት በመርጫው ውስጥ ሾልከው እንዳይገቡ የሚፈልጋቸው ሰዎች ስላሉ እነዚህ ሰዎች በመርጫው ላይ መሳተፍ የለባቸውም " በማለት በየስበባው ይችን አርፈተ ነገር ሲደጋግማት አድምጠናል።ለመሆኑ መንግስት የሚፈልጋቸው እና የማይፈልጋቸው እነማን ናቸው? መርጫውስ የሚደረገው የመንግስትን ፍላጎት ለማሞላት ነው ወይስ የሙስሊሙን ጥያቄ ለመመለስ ?

ለመሆኑ መንግስት የማይፈልጋቸው ሰውች በምርጫው ቢሳተፉ ችግሩ ምንድን ነው ?ለዚህ ጥያቄ መልሱ እነዚህ ሰዎች በምርጫ ከተሳተፉ ህዝቡ ሰለሚመርጣቸው እና ሰለሚያሸንፉ ነው።ታዲያ ዲሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው ? ህዝብ ያሻውን የመምርጥ መብት አለው !በፈልገው ሰው የመተዳደር መብት አለው! እግሌ ስላልፈለገ ወይም ሰለፈለገ ተብሎ የሚደረግ መርጫ በ አለም ላይ ታይቶም ተስምቶም አያውቅም።

እርግጥ ነው መንግስት የሚፈልገው ባለፈው በፓርላማ ጠቅላይ ሚንስቴሩ እንደተናገሩት "ታቦት ሸኚ" መስሊም ነው።ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች የምንፈልገው መሪ እንደነ ኡመር አይነቱ ጀጋና እና አላህን ፈሪ መሪ ነው።እነሱ የኛን መሪ የመርጥ መብት የላቸው፤እኛ ደግሞን ደጋግመን እየጠየቅን ያልነው መንግስት ወይም ሌላ አካል የሚፈልጉትን መሪ ሳይሆን እያንዳንዱ ኢትዮጲያዊ ሙስሊም የሚፈልጉትን መሪ እንመርጥ ነው።መንግስት ቆሮቆረውም ጎረበጠውም የመጅሊስ መርጫ የሙስሊሞች ብቻና ብቻ ነው። እኛ የፈልግነውን እንጂ መለስ የፈልገውን መሪ አንፈልግምና ።

ድል የኢስላም ነው!! አላሁ አክበር።

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[United against Ahbash in Ethiopia] ትላንት ፌደራል ፖሊስ በአወልያ ንፁሀን ሙስሊሞች ላይ ጨለማን ተገን በማድረግ...**

Saturday, July 14, 2012 5:53 AM

**From:** "Nebil Suleyman" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "United against Ahbash in Ethiopia" <210731789049964@groups.facebook.com>

Nebil Suleyman posted in United against Ahbash in Ethiopia

**Nebil Suleyman** 12:52pm Jul 14

ትላንት ፌደራል ፖሊስ በአወልያ ንፁሀን ሙስሊሞች ላይ ጨለማን ተገን በማድረግ በፈፀመዉ ጭፍጨፋና ድብደባ የአወልያ የዉስጥ የመስጂዱ በሮች መሰባበራቸዉና ለአህ(ሱ.ወ) ሱጁድ የሚወረድበትን የመስጂዱ ምንጣፍ በጫማቸዉ በመግባት ድብደባ ሲፈፅሙ እንደነበር የተገለፀዉ:: በተመሳሳይም በቂራ ሰላም መስጂድ የፌደራል ፖሊሶች የመስጂዱን በር በመስበር መስጂዱ ዉስጥ የነበሩትን ንፁሀን ሙስሊሞችን ከነጫማቻዉ በመግባት ከፍተኛ ድብደባ መፈፀማቸዉ ነዉ የተገለፀዉ:: ጥይትም ሲተኩሱ የነበረ ቢሆንም በጥይት ተመቶ የሞተ ሰዉ እንደሌለ እና በድብደባዉ ግን በርካቶች መሰበራቸዉ ነዉ ከቂራ አካባቢ ምንጮቻችን የተገለፀል::

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLN

3-6

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic


**[all eth muslims] ትላንት ፌደራል ፖሊስ በአወልያ ንፁሀን ሙስሊሞች ላይ ጨለማን ተገን በማድረግ...** Saturday, July 14, 2012 2:54 AM

**From:** "Zubayr Peace" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "all eth muslims" <ethmuslims@groups.facebook.com>

Zubayr Peace posted in all eth muslims

**Zubayr Peace** 9:53am Jul 14

ትላንት ፌደራል ፖሊስ በአወልያ ንፁሀን ሙስሊሞች ላይ ጨለማን ተገን በማድረግ በፈፀመዉ ጭፍጨፋና ድብደባ የአወልያ የዉስጥ የመስጂዱ በሮች መሰባበራቸዉና ለአህ(ሱ.ወ) ሱጁድ የሚወረድበትን የመስጂዱ ምንጣፍ በጫማቸዉ በመግባት ድብደባ ሲፈፅሙ እንደነበር የተገለፀዉ:: በተመሳሳይም በቂራ ሰላም መስጂድ የፌደራል ፖሊሶች የመስጂዱን በር በመስበር መስጂዱ ዉስጥ የነበሩትን ንፁሀን ሙስሊሞችን ከነጫማቸዉ በመግባት ከፍተኛ ድብደባ መፈፀማቸዉ ነዉ የተገለፀዉ:: ጥይትም ሲተኩሱ የነበረ ቢሆንም በጥይት ተመቶ የሞተ ሰዉ እንደሌለ እና በድብደባዉ ግን በርካቶች መሰበራቸዉ ነዉ ከቂራ አካባቢ ምንጮቻችን የተገለፀል::



View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ከሚመለከታቸዉ
ለማን ለሚመለከተዉ ተጠርጣሪ
25/12/04

ታዛቢዎች
1. ሀብታሙ ሽጉጤ
አንተሁ አለሜ ኪሮስ አቀፍለሁ
25/12/04

2. ሚኪያስ መስፍን ያዘነ
ወርቅነህ ሀይሉ
25/12/04

168

DRAFT



http://ethcriminalawnetwork.com/

በአንዳሩ ደግሞ በየ አርቡ እያየን ያለነው ጉዕይንት ሰዎቹ ጥቂቶች አለማሆናቸውን በብዛታቸው፤ አሸባሪም እንደማይመስሉም፤ በሰላማዊ እና ማራኪ ተቃውሞቸው እየታገሉን ነው። ጥያቄው ይብቃኝ ይልቅስ...
እመክራለሁ
"ጥቂቶች..." እየተባለ በኢቲቪ ደጋግሞ ስለተነገረ ብዙሃኑን ጥቂት ማድረግ አይቻልም። ሰዎች ለምን? ብለው በጠየቁ ቁጥር "አሸባሪ" ማለትም አያዋጣም። እውነት እውነት አላችኋለሁ ዱላ በበዛ ቁጥር ደንዳና ያደርጋል። እና ተዉ!
ለማንኛውም ዛሬም የሙስሊም ወንድሞቻችን ተቃውሞ ቀጥሎ ውሏል። ተቃውሞው በፍፁም ፀጥታ እጅ ለእጅ በመያያዝ የተደረገ ሲሆን ሃምሳ ሺህ የሚሆኑ ሙስሊም ወንድሞቻችን ተካፋይ እንደነበሩ ሰምቻለሁ! (የቁጥር ማስተካከያ አንድ ወዳጄ "አቤ ከኢቲቪ ነው እንዲ የሰማከው በአንዋር መስጊድ ብቻ አንድ ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ ተገኝቷል።" ብሎኛል። አመሰግናለሁ ወዳጄ!

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECHR

130



http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

# [Ethiopian Muslims] የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ አወሊያ ግቢ ነበር እንዴ!?

Friday, July 20, 2012 2:15 PM

**From:** "Ahmed Gragn" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "Ethiopian Muslims" <ethiopianmuslims@groups.facebook.com>

Ahmed Gragn posted in Ethiopian Muslims



**Ahmed Gragn**
9:14pm Jul 20

**የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ አወሊያ ግቢ ነበር እንዴ!?**
Ye Africa Heberet sebseba AWOLIA gebi neberende?
አቤ ቶኪቻው!
እኔም እንደ ኢቲቪ ወሬ በችርቻሮ ጀምሪያለሁ። ትላንትና ልብ ብላችሁ እንደሆነ ኢቲቪ ነብሴ አንድ የአቶ በረከትን መግለጫ ሶስት ይሁን አራት ዜና አውጥቶለት ነበር። ይሔ ዜና በችርቻሮ ይባላል። እኔስ ከየት እማራለሁ ታድያ... ለነገሩ የምር የማይታለፍ ጉዳይ ሆኖብኝ ነው። ስለዚህ በቀጥታ ወደ አቶ በረከት መግለጫ እንሂድ...!
ትላንት አቶ በረከት ስምያን ለጋዜጠኞች መግለጫ በሰጡበት ወቅት ካነሷት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የሙስሊም ወንድሞቻችንን ተቃውሞ ነበር።
"የአክራሪ ሙስሊሞች ጥያቄን በተመለከተ መንግስት እስካሁን ድረስ አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥቦ በህብረተሰቡ እንዲመከሩ ሰፊ ስራ ሲሰራ ቆይቷል። የአፍሪካ ህብረት ስብሰባን ለማወክ ያደረጉት ጥረትም በመንግስት ብስለት የተሞላበት ጥንቃቄ ከሽፏል" ሲሉ ተናግረዋል።
አቶ በረከት ይህንን ሲሉ ቴሌቪዥን የሚመለከተው ህብረተሰብ በርካታ ጥያቄዎችን እጠየቃቸው ነበር። ዳሩ የቴሌቪዥን ተናጋሪ አፍ እንጂ ጆሮየለውምና አልሰሙም። አስቲ እኔ ጥያቄውን ላስተጋባውና ጆሮ ባይኖራቸው ኔትዎርክ እና አይን ይስጣቸው ብለን ፀልየን እንዲያነቡት እናድርግ!
የሙስሊም ወንድሞቻችን ተቃውሞ እየተደረገ ያለው አወሊያ ግሩ ሲል ደግሞ አንዋር መስጊድ ነው። መንግስት "ብስለት የተሞላበት" በሬ፣ ኩኪስ፣ እና የተለያዩ ምግባ ምግቦችን ሰረቃ እና ንጥቂያ ያካሄደው ከአወሊያ እና ከመሮካቶው አንዋር መስጊድ ነው። (በነገራችን ላይ የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ እንዳኢታወክ በሚል ሌሊቱን የተከናወነው ብስለት የተሞላበት ተግባር ይሄ ነበር። እንዲህ ነው እንጂ ብስለት! ብለው ያድንቁ እና እንቀጥል) የሙስሊም ወንድሞቻችንም ጥሪ እዛው ነበር። የአፍሪካ ህብረት ስብሰባው ዳግሞ ሳር ቤት ነው። ታድያ መርካቶ እና አስኮ በሚደረግ ጉባኤ እና ሰደቃ ፕሮግራም የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ እንዴት ነው የሚስተጓጎለው...!? ተስብሳቢዎቹ የመጡትስሰላት ነበር እንዴ!? ብለን ጥያቄ አንድ አንላስን።
እኔ የምለው ጋሽ በረከት እርስዎ ሙስሊም ወንድሞቻችንን "ለማህበረሰቡ አስመካርን እንጂ ምንም አስተዳደራዊ እርምጃ አልወሰድንባቸውም" ብለው ከመናገርዎ በፊት እኮ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ራሱ ጮክ ብሎ ወደ ሰባ ምናምን የሚሆኑ ሙስሊም ወደጆቻችንን እንደታሰሩ በኩራት ነግሮናል። ከመግለጫዎም በጓላ በነበረው ዜና ተጨማሪ ሙስሊሞች መታሰራቸውን የራስዎ ቲቪ አውርቶልናል። በፌስ ቡክ ላይም በርካቶች የተገረፉ ጓላቸውን በፎቶ አሳይተውናል። ምክሩ ይሄ ነው ማለት ነው...? ማሰር እና መግረፍስ ምክር ከሆነ አስተዳደራዊ እርምጃ ሲወሰድ ምን ይሆን የሚደረገው...!? ጥያቄ ሁለት ይበሉልኝ!
በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን "ጥቂት አሸባሪዎች" እየተባለ ዜና ሲሰራ ተመልክተናል።

http://ethcriminalawnetwork.com/

ለመሆኑ ኢቲቪ ሃይማኖቱ ምንድነው!? ህገ መንግስቱ "የመንግስት የሚባል ሃይማኖት የለም ሁሉም ሃይማኖቶች በመንግስት አይን እኩል ናቸው!" ይላል። ታድያ አንዱን አክራሪ እያሉ ማኮሰስ አንዱን የሰላም አባት እያሉ ማሞካሸት ይሄ ነው ሃይማኖትን በእኩል አይን ማየት?

ቆይ አንዴ፣ ከላይ የጀመርኩትን ሳልጨርስልዎ ነው ለካ ወደሌላ መስመር የገባሁት፣ እናልዎ "የኮምቦልጆ ሙስሊሞች አክራሪነትን እንደሚቃወሙ አስታወቁ" ብሎ ቴሌቪዥናችን እኛ ሰዎቹ ላይ ምልክት የማናደርግ መስሎት ይሁን ወይ ደግሞ ሰዉ ኑሮውን እንጂ እኛን አይከታተልም በሚል ተስፋ መቁረጥ እንጃ እነዛኑ ሰዎች መለሶ "አንዳንድ የአዲሳባ ሙስሊሞች" የሚለው ዘገባ ላይም መልሰን አይናቸው!

ወይ ኢቲቪ... እኛ እኮ እንኳንስ ሰዎች ላይ ይቅርና የልማት ከብቶች ገና ጥቅል ነመን ላይ ምልክት የምናደርግ ትጉሃኖች ነን! ከዚህ በፊትም ለጎጃም ያየነውን የልማት ጥቅል ነመን ለደቡብ አይተነው ስንደነቅ ነበር። አሁንም የተደረገው ተመሳሳይ ነው!

አረ በናታችሁ በዚች በትንሹ ካልታመናችሁ ትልልቅ ነገሮች ላይ እንዴት ነው የምናምናችሁ? ዉ.....ዉ.....ዉ! የምሬን ነው ይሄ ነገር ያሳሰበኝ።

ለማንኛውም አሁን ደግሞ እንደደረሰኝ ወሬ ከሆነ (ደሞ መሆኑም አይቀርም!) ባለፈው ሌሊት በአወሊያ ግቢ የፖሊስ ልብስ ለብሰው የገቡ ሰዎች በግቢው ውስጥ ራሳቸው የጦር መሳሪያ በማስቀመጥ የተቃዋሚዎቹ ኮሚቴ ህዝቡን መሳሪያ ሊያስታጥቅ ነበር። በሚል ዶክመንተሪ ፊልም ሊሰራ እንደሆነ ተሰምቷል። (በቅንፍም ኢቲቪ ቢሰማም ባይሰማም እመክራለሁ በናታችሁ አንዳንዴም አራዳ ሁኑ "ከተነቃ ይቀራል!" በሉ እና ይሄንን ዶክመንተሪ ከመስራት ተቆጠቡ!)

ሌላ ደግሞ የመንግስት አቃቤ ህግ በህዝበ ሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ላይ ክስ ሊመሰርት መሆኑንም ውስጥ አዋቂ ምንጭ ጠቅሶ አንድ ወዳጄ ወሬ አቀብሎኛል።

አቃቤ ህጉ ክሱን የሚመሰርተዉ 1ኛ). ህገ ወጥ ስብሰባና ህገ ወጥ ሰላማዊ ሰልፍ በመጥራት የአፍሪካ ህብረት ስብሰባን ለማጨናገፍ ባደረጉት ጥረት በሚል ሁሉንም የኮሚቴዉ አባላት፣

2ኛ) በህገ ወጥ ስብሰባዎች ላይም ህዝብን በመንግስት ላይ እንዲያምፅ በማነሳሳት ሁከትና ረብሻ ለመፍጠር በመሞከር በሚል ክስ ደግሞ የኮሚቴዉን አባላት በተለይም የኮሚቴዉን ሰብሳቢ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ፣ የታሪክ ምሁሩን ኡስታዝ አህመዲን ጀበልን እና ኡስታዝ ካሚል ሸምሱን ለመክሰስ ተዘጋጅተዋል::

እናም የመንግስትም ሆነ የመንግስት ቴሌቪዥን ነገር በጣም ያስደንቃል። እስቲ ጠይቁልኝ እነዚህ ሰዎች ሃይማኖታቸው ምንድነው?

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[ETHIO ISLAMIC ART AND DA'AWA GROUP] abe tokeichow**

Wednesday, July 18, 2012 4:10 AM

**From:** "عبد الله ابن عباس" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "ETHIO ISLAMIC ART AND DA'AWA GROUP" <ethioislamicart@groups.facebook.com>

عبد الله ابن عباس posted in ETHIO ISLAMIC ART AND DA'AWA GROUP

ደምሴን ይስማ

**عبد الله ابن عباس**
abe tokeichow

11:10am Jul 18

**አንድ ብስጭት፤ ኢቲቪ ሀይማኖቱ ምንድነው!?**
Posted on July 18, 2012

... እስቲ ቆይ ወደ ርዕሰ ጉዳያችን ከማምራታችን በፊት አንድ ዋዛ ብጤ እናምጣ አሁን በቅርቡ አንድ ወዳጄ አንድ ፌታኝ ጥያቄ ጠይቆኝ ነበር። ምን አለኝ መሰልዎ "አቶ መለስ እና ኢቲቪ ተጣልተዋል እንዴ!?" አለኝ ሲቀጥልም፤ "ያኔ ጋሽ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ጋና ትንሽ ሲወራባቸው "ፕሬዘዳንቱ በህክምና ላይ ናቸው አትደናገጡ!" ብሎ የነገረን ቴሌቪዥናችን ዛሬ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጊዜ ዝም ማለቱ ምን ቢያስቀይሙት ነው!?" ብሎኛል።

የምር ግን ገቡ የለ ወጡ የለ ሀገር ሁሉ በርሳቸው ጉዳይ ሲጨነቅ ኢቲቪ ሀጥ ማለቱ የምርም ተጣልተው ይሆን እንዴ...? ያሰኛል። ስለ ኮብልስቶን መቀበር እና መቀጥቀጥ ደጋግሞ የሚነግረን ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ህመም ሲቀጠቅጣቸው እና "ቀብራቸው ደረሰ" እያለ ሀገሩ ሲያሟርትባቸው እርሳቸውን ከኮብል ስቶን አሳንሶ አንዳችም ነገር ትንፍሽ አለማለቱ በእውነት የታሪክ ተወቃሽ ያደርገዋል።

የእውነት ግን ወዳጄጂ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ነገር ስንቱ ተወርቶ ስንቱ ቀርቶ... አይነት ነገር ነው። አሁን መቼለታ የኮምቦልቻ አካባቢ ሙስሊም ነዋሪዎች በአዲሳባ የተቀሰቀሰውን የሙስሊሙን ተቃውሞ አወገዙ ብለው በአወልያ ላለፉት ስድስት ወራት ፍፁም ሰላማዊ ተቃውሞ እያሰሙ የነበሩ ሙስሊሞችን የሚቃወሙ ሰዎች ቃለ ምልልስ አድርገውላቸው ነበር።

በበኩሌ፤ የአወሊያ ሰላማዊ ተቃዋሚ ሙስሊሞችን የሚቃወሙበት አላማ ምንም ይሁን ምን መሰማት እንዳለባቸው ብዬ አምናለሁ። እነርሱን መቃወም እንደሚቻልም አምናለሁ። እነሱን የሚቃወሙ ሌሎች ሙስሊሞች እንደሚኖሩም አምናለሁ። ይሄ ጤናማ ነው።

ነገር ግን ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ለአንዱ ወግኖ አንዱን ማብጠልጠሉ በእውነቱ ደባሪ ነገር ነው። የክልል እና የፌደራል ባንዲራ ይዘው ጎዳና ወጥተው ኮምቦልቻንም ይሁን፣ ባቲንም ይሁን፣ ከምሴን በሰልፍ ሲበጠብጡ የነበሩትን እየደገፈ፤ ላለፉት ስድስት ወራት ጎዳና ላይወጡ ውስን ቦታ ብቻ በቤተ መስጊዳቸው እና በአወሊያ ግቢ ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩትን ማውገዝ በእውነት ነውር ነው...?

ECHRN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፍትህ የተቋማት ነፃነት፣ የመናገር፣
የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ፍትሓዊ የኢኮኖሚ
ተጠቃሚነት፣ በጥቅሉ ለተወሰኑ ቡድኖች ብቻ
ሲያዘነብል፣ ማህበረሰቡ ቀድሞ መታወቂያው የነበረው
ኢትዮጵያዊ ማንነቱ በእጅጉ እንዲቀየር ከማድረጉም
በተጨማሪ ነባሩ አገራዊ ጨዋነት ከመሰረቱ እንዲናድ
ያደርገዋል የሚል አቋም አላት። ለዚህም ነው ለአክራሪነት
መስፋፋት ከማንም እና ከምንም በፊት ኢህአዴግ ራሱ
ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባል የምትለው።
ፍትህ በዘጋቢ ፊልሙ ላይ መንግስት
አክራሪነትን ለማስወገድ በሚል በማስረጃነት ያቀረባቸው
የታሪክ እውነቶች አሁን ላይ ሆኖ ለሚሰማ እና ለሚያይ
ታዳጊ ትውልድ በሚመጥን መልኩ የቀረበ አይደለም
የሚል እምነት አላት። በመካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ
የተደረጉ ጦርነቶች፣ በጊዜው የወደሙ ንብረቶችና
ጎብቶች መነሻቸው ሃይማኖታዊ ብቻ እንደሆነ
አድርጐ ማቅረቡም ትልቅ የታሪክ ስህተት ነው።
ለዚህም ነው አንድን ዘጋቢ ፊልም ከመስራት አስቀድሞ
በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቂ እውቀት ሊኖር
ይገባል የምንለው።
ፍትህ ደግማ ደጋግማ እባካችሁ ያልተባፈ
ታሪክ አታንብቡልን፣ ያልተከሰተ ድርጊት አትንገሩን፣
ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ይበልጥ
አጀንዳውን ከማራገብ ውጭ ፋይዳው ሀገራዊ ጥፋት
ነው ብላ ማሳሰብ ትፈልጋለች።

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECHR



http://ethcriminalawnetwork.com/

ከላይ ባነሳናቸው ጥቂት መስፈርቶች አንጻር
እንኳን ካየነው ኢቲቪ በተደጋጋሚ ብዙ ስህተቶችን
ፈጽሟል፡፡ ፍትሕ ኢቲቪ ከዚህ ቀደም እንደሰራቸው
ስህተቶች ሁሉ ባሳለፍነውም ሳምንት መጀመሪያ
ለዕይታ ያበቃው ‹‹ብዙ ሃይማኖቶች አንዲት አገር›› 
የሚለው ዘጋቢ ፊልም ላይ አደገኛ የሆኑ ስህተቶችን
ዳግም ፈፅሟል የሚል እምነት አላት። ሃይማኖትን
የሚያክል ትልቅ ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ ከጀርባው
የመንግሥትን የፖለቲካ አጀንዳ ለመጨመር መታተር
ተገቢ ካለመሆኑ በተጨማሪ ዜጎችን ማሳቱ አይቀሬ
ነው። ይህ ዘጋቢ ፊልም በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም
አመታት ሰፍኖ የቆየው የሃይማኖቶች መቻቻል እና
መከባበር በአሁኑ ጊዜ መልኩን እያጣ መምጣቱን
ለማሳየት የታቀደ ነው። አዘጋጁ ለዚህ ማስረጃ ይሆናሉ
ያላቸውን የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስቶ ከተለያዩ
የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች፣ ከማህበረሰብ ክፍሎች
እና ከፖለቲካ ተንታኞች የተውጣጡ የግለሰቦችን
አስተያየት አቅርቧል። ዘጋቢ ፊልሙ፤ በአገራችን
ምልክቱ እየታየ መጣ ስለተባለው የሃይማኖት አክራሪነት
ምንነትና ምክንያት እንዲሁም መፍትሄውን ለመፈለግ
በሙመስል መልኩ ነገር ግን በእጅጉ በተሳሰተ መንገድ
የሚባክን ነው።
ፍትህ ለሃይማኖቶች ወግ አጥባቂነትም
ይሁን አክራሪነት ምክንያቱ በአገሪቷ እየተንሰራፋ
የመጣው የጠባብነት አመለካከትና የዜጐች በህግ ፊት
እኩል ያለመዳኘት መሆኑን ታምናለች። ዜጐች በብሔር
ማንነታቸው፣ በእምነት ልዩነታቸው እና በቡድን
መብቶቻቸው ላይ አድልዎና መገለል ሲደርስባቸው
ለጋራ ችግራቸው የጋራ መፍትሄ ለማበጀት ሲሉ
ከነበሩበት ስብስብ የተነጠለ ማንነትን እንዲያበጁ
ይገደዳሉ። እነዚህ መገፋቶች ዞሮ ዞሮ መብትን
ከማስመለስ አኳያ የሚታዩ በመሆናቸው ምክንያት
መሰረታዊ ጥያቄያቸው ሃይማኖታዊ ወይም ብሔር
ተኮር መሆኑ ይቀርና ፖለቲካዊ ይሆናል።
በፍትህ እምነት በሃይማኖት ጉዳይ
የተጀመረው እሰጥ አገባ በስተመጨረሻ ‹‹ተበደልን›› 
የሚሉ ወገኖች ለችግራቸው መፍትሄ የሚበጅለት
የመንግስት ስልጣንን በመያዝ ብቻ ነው ወደሚል
አመለካከት በማዘንበል አስቀድመው የተነሱለት የመብት
ጥያቄ ፈር እንዲስት ማድርጉ አይቀሬ ነው። ኢህአዴግ
በኃይማኖት ተቋማት ላይ ባሳረፋቸው ጣልቃ ገብነቶች
ምክንያት ብዙ ምእመናን ተከፍተዋል፡፡ የዚህ ኩርፊያ
ድምር ውጤት የሆነው ደግሞ መንግስት አሁን
እየተከሰተ ነው የሚለው ‹‹የአክራሪነት መስፋፋት›› 
እንደ አንድ ማሳያ አድርገን ልንወስደው እንችላለን።

12



http://ethcriminalawnetwork.com/

8/31/2012 12:35 PM

YAHOO! MAIL Classic

**[FEZEKIR CENTER] የኢቲቪ ዘጋቢ ፊልሞች አቀራረብ አንድምታ**

Monday, July 9, 2012 7:39 AM

**From:** "عبد الله ابن عباس" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

عبد الله ابن عباس posted in FEZEKIR CENTER

2:38pm Jul 9

**عبد الله ابن عباس**
**የኢቲቪ ዘጋቢ ፊልሞች አቀራረብ አንድምታ**

fetehe.com
የአገራችን ትልቁ እና ብቸኛ የሆነው
የቴሌቪዥን ጣቢያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በገሃዱው
... ፓርቲ ፖለቲካ የተጠለፉ ርዕሰ ጉዳዮች ያላቸው
ዘጋቢ ፊልሞችን በማቅረብ ይታወቃል። ይህ ሁኔታም
ከዜጐች እለታዊ እና ወርሃዊ ገቢ ላይ በሚሰበሰብ ግንዘብ
መተዳደሪያውን ያደረገው ይህ ግዙፍ የቴሌቪዥን
ጣቢያ፣ ስሙ የህዝብ ቢሆንም ተጠሪነቱና አገልግሎቱ
አገሪቷን ለሚያስተዳድረው አውራ ፓርቲ ብቻ ለመሆኑ
ከብዙ ማሳያዎች አንዱ ይህ ነው።
እንዲሁም በተደጋጋሚ በዚሁ የቴሌቪዥን
ጣቢያ ላይ የሚተላለፉ ዘጋቢ ፊልሞች ሚዛናዊነት
የሚጐላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ ተሰርተው
ለእይታ ከቀረቡም በኋላ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚኖራቸው
ተቀባይነት እምብዛ ነው። ፍትህ ዘጋቢ ፊልሞች ለዕይታ
ሲቀርቡ የኢ.ፌ.ቲ.ቪ ድርጅት ልብ የማይላቸው ነገር
ግን ከአገራዊ ፋይዳቸው እና ማህበረሰባዊ ተጽዕኗቸው
አንጻር ልብ ሊባሉ ይገባል የምትላቸውን ሁለት
ነጥቦች በጥቅሉ ማንሳት ትፈልጋለች። የመጀመሪያው
ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል የምትለው ነጥብ፣ ዘጋቢ
ፊልሞቹ ሲሰሩ ለዚህ ኃላፊነት የሚዘጋጁ ግለሰቦች
ለወቅታዊው መወያያነት የመረጡትን ርዕስ ወደ ፊልም
ከመቀየራቸው በፊት በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ተገቢውን
መረጃ መሰብሰብ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ መረጃዎች
በእውነታ ላይ የተመሰረቱ ሆነው ለየትኛውም ቡድን
ያላደላና የመጨረሻውን ፍርድ ለሕዝብ የሚተው መሆን
ይጠበቅበታል። ሁለተኛው ትኩረት ሊሰጥው የሚገባው
ነጥብ፣ ለዘጋቢ ፊልሙ ርዕስ መርጦ የሚሰራው ግለሰብ
ባነሳው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ልምድና ችሎታ ያለው
መሆን እንደሚገባው ፍትሕ ትጠቁማለች።

FCLN





http://ethcriminalawnetwork.com/

የደረሰው የውስጥ አዋቂ መረጃ አመልክቷል።

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[Anti-Ahbash EthioMuslims Group] በአዲስ አበባ ሙስሊሞች እየታፈሱ ነው፤ አህዴዶች ጥያቄ አነሱ** Wednesday, July 18, 2012 2:44 PM

**From:** "Lenberot Firekot" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "Anti-Ahbash EthioMuslims Group" <ethioantiahbash@groups.facebook.com>

Lenberot Firekot posted in Anti-Ahbash EthioMuslims Group

**Lenberot Firekot** 9:43pm Jul 18

**በአዲስ አበባ ሙስሊሞች እየታፈሱ ነው፤ አህዴዶች ጥያቄ አነሱ**

TweetShare

(ዘ-ሐበሻ)፡ በአዲስ አበባ በተለያዩ ወረዳዎች የሙስሊሙን እንስቃሴ እየመሩ ነው ወይንም ይደግፋሉ የተባሉ ወጣቶች በሰፈር ጥቆማ እየታሰሩ መሆኑን ለዘ-ሐበሻ የደረሰው መረጃ አመለከተ። የኦሮሞ/ሕወሐት ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (አህዴድ) የሙስሊሞቹ ጥያቄ ካልተፈታ በኦሮሚያ ክልሎች የሚፈጠረው ነገር ያሰጋናል፤ መንግስት ባሰሸኳይ መላ ያበጅለት የሚል ጥያቄ እያቀረበ መሆኑ ተጠቆመ።

ባለፈው ሳምንት የተወሰኑ ሙስሊም ወንድሞች እና እህቶች መብታችን ይከበር ባሉ ከተገደሉ፣ ከተቀጠቀጡና ከታሰሩ ወዲህ የሙስሊሞቹ ጥያቄ ከዚህም በላይ ሊቀጥል ይችላል በሚል መንግስት በየሰፈሩ ወጣቶችን እያሰረ መሆኑን የጠቆሙት የዘ-ሐበሻ ምንጮች፣ እነዚህ ታሳሪዎች ወደ ክፍለ ከተማ ተወስደው ይታሰሩና ከተመረመሩ በኋላ የሚለቀቁት ተለቀው ቀሪዎቹ ከአዲስ አበባ ውጭ እየተወሰዱ በመታሰር ላይ መሆናቸውን አጋልጠዋል።

እንደ የዘ-ሐበሻ ምንጮች ገለጻ መንግስት የፈለገውን ቢያስርም የሕዝቡ ሙስሊሙ እንስቃሴ እንደሚቀጥል የፊታችን አርብም ትልቅ ነገር ይጠበቃል። ሙስሊሙም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ድምጹን ያሰማል ተብሏል። በአሁኑ ወቅት ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ እስርቤቶች ውስጥ በርካታ ሙስሊሞች ታስረዋል።

ይህ በ እንዲህ እንዳለ በሌሎች ተቃዋሚ ድርጅት አመራሮች ላይ እንደተሰራው ዓይነት (አኬልዳማ ድራማ) በሙስሊሙ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ ላይም ተጀመረ። ምንጮቻችን እንዳጋለጡት ከሆነ መንግስት ቢለዋ በማስያዝ ሰዎችን ከኮምቦልቻና ከሌሎች ከተሞች ገንዘብ ከፍሎ ወደ አዲስ አበባ በማምጣት ቪዲዮ እየቀረጸ ነው። በቅርቡ በቲቪ በምናየው በዚህ ቪድዮም ሰላማዊውን የሙስሊሙን ትግል ቢለዋ የያዙ በማስመሰል "ሕዝቡን ሊጨርሱት ሲያስጨርሱት ነው" ሊል ተዘጋጅቷል።

ከታሰሩትና ታስረው ከተፈቱት መካከል አንዳንዱን በባዶ ወረቀት ላይ ከታች ምንም ሳይጻፍበት በግድ እንዲፈርሙ መታዘዛቸውን የሰሙ አስተያየት ሰጪዎች በቅርቡ በምናየው አኬልዳማ መሰል አስፈሪ የወያኔ የሆረር ፊልም ላይ ራሱ ወያኔ የሚጽፈውን ለክስ የሚመች ጽሁፍ እናነባለን ብለዋል።

ይህ በ እንዲህ እንዳለ አህ ዴድ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ባለስልጣናት አቶ መለስ ከታመሙ በኋላ አፍ ማውጣት ጀምረዋል። እንደነዚህ ባለስልጣናት አገላለጽ "ኦሮሚያ ብዙ ሙስሊሞች የሚኖሩባት ክልል ነች። በአዲስ አበባ የተነሳው ጥያቄ በቶሎ ካልተመለስ በኦሮሚያ ክልል የሚስፋፋው እንቅስቃሴ ለደህንነት የሚያሰጋ በመሆኑ በአስቸኳይ የፌደራል መንግስቱ መፍትሄ ሊያፈላልግለት ይገባል" እያሉ ነው። "በኦሮሚያ ሙስሊሙ ከተነሳ ከባድ ችግር ውስጥ እንገባለን" እያሉ ያሉት አህዴዶች የሚፈለገው ተከፍሎ የሙስሊሙ ጥያቄ እንዲመለስ እየጠየቁ መሆናቸውን ለዘ-ሐበሻ

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[FEZEKIR CENTER] ትግላችን እጅግ የሚያስደንቅና ታሪካዊ ቢሆንም አንዳንድ ደካማ ጎኖች ግን...** Saturday, July 14, 2012 5:38 PM

**From:** "Abu Nurjenna Shemse" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Abu Nurjenna Shemse posted in FEZEKIR CENTER

**Abu Nurjenna Shemse** 12:38am Jul 15

ትግላችን እጅግ የሚያስደንቅና ታሪካዊ ቢሆንም አንዳንድ ደካማ ጎኖች ግን እየታዩብን ነው፤ ይህ ደካማ ጎን ዝምብለን ማለፍ የሌለብን ጉዳይ ነው፤ ካሜራ ይዘን የሚፈጠሩትን ነገሮች በመቅረጽ በመረጃ መልክ ማስቀመጥ እንዳለብን ብዙ ግዜ ተነጋግረናል፤ ሆኖም ወደ ተግባሩ ስንመጣ የሚደረጉብንን ጥቃቶች አንድ ፐርሰንት እንኳን መቅረጽ አልቻልንም፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ እኛው ተደብድበን ተጨፍጭፈን መንግሰት ፖሊስ ደበደቡ በር ሰበሩ እያለ ውሸት እየነዛ ይገኛል፤ ይሄንን ስንሰማ ሁላችንም እንደምንቃጠል ግልጽ ነው፤ ግን ዉሸት ለመሆኑ ምን መረጃ አለን??? እኛ ውሸት መሆኑን በቅርብ ስለምንከታተል ልናውቅ እንችላለን ግ...ን ሌሎች ሰዎች እንዲሁም የሌላ እምነት ተከታዮች ውሸት መሆኑን በምን ይወቁ? የወንድሞቻችንን ደም ያፈሰሱት ለፍርድ ይቅረቡ ብንል መረጃችን ምንድነው? በተለያዩ ቲቪ ቻናሎች እንዲተላለፍልን ብንፈልግ ቪድዮ ከሌለን ምን ያስተላልፉልናል??? ቪድዮ መቅረጽ ያለውን ጥቅም ስላልተረዳን አይመስለኝም፤ ግን ትኩረት ሰጥተን ወደ ተግባር መግባቱ ላይ ድክመት ይታይብናል፤ ለምሳሌ ዛሬ በዚህ ታሪካዊ ቀን የተቀረጸ ቪድዮ ያን ያህል የለም! የትግል ምዕራፎቻችንን በመረጃ ካልያዝናቸው ደግሞ ችግሩ ለኛው ነው፤ስለዚህ ይሄን ድክመት ለማስወገድ ሁላችንም እነእንትና አሉ ሳንል ከእጃችን ካሜራ ሊለየን አይገባም፤ ምናልባች ቪድዮውን ቀርጸን በፌስቡክ መልቀቅ ካፈለግን በዚህ Voem111@gmail.com ኢ-ሜይል ይላኩት ፤ካሁን በኋላ ያለውንም እየቀረጽን ማስቀመጥ ከቻልን ትልቅ ነገር ነው፤ የምንቀርጸው የግድ ከፖሊስ ጋር ያለውን ፍጥጫ ብቻ አይደለም፤ ፖሊስ የደበደባቸውን ቃለ መጠይቅ በማድረግ፤ በቦታው የነበሩትን ወንድሞች ቃለመጠይቅ በማድረግ ፤የሞቱ ወንድሞች ካሉ ጀኛዛቸውን በመቅረጽና ለቤተሰቦቻውን ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ ልናሰባስብ ይገባናል፤ አሁንም ቢሆን ብዙ ወንድሞቻችን ታመው ተኝተዋል እነሱን ሂደን በመቅረጽ ቶሎ በኢሜይል እንላከው፤ ነገ የሚፈጠረው ነገር አይታወቅም ሁላችንም ካሜራ እንያዝ ፤ በኢሜይል እንዴት መላክ እንደሚቻል ማብራሪያ ካስፈለግዎት በግል ሜሴጅ መላክ ይችላሉ፤ ይሄንን ችግር ለማስወገድ ፈቃደኛ ነዎት?

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.



http://ethcriminalawnetwork.com/

የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ልንሰጥህ ነው:: በየመስጂዱ የምታደርገውን የማስተባበር ስራ አቁም! አለበለዚያ ዋጋህን ታገኛለህ! አሉኝ" ብለዋል።
" ..... በዚህ ጊዜ ጣልቃ ገባሁና መረጃ ካላችሁ ፍርድቤት ዉሰዱና ጠይቁኝ እንጂ ለምን ታስፈራሩኛላችሁ? እኛ እንኳን ልንፈራ ለእምነታችን ህይወታችንን ለመስጠት ዝግጁ ነን አልኳቸው" ያሉት ኢስታል አህመዲን፤ " ይህን ስላቸው ፤ላንተ ፍርድቤት በመውሰድ ጊዜ አናባክንም! ዋጋህን እንሰጥሃለን! አንዲት ችግርዉፈጠር ፤የመጀመሪያው ጥይት አንተ ላይ ነው የሚያርፈው!! ትሰማ እንደሆን ስማ!! በማለት ሊያስፈራሩኝ ሞክሩ" ብለዋል።
ከዚያም፦ "...ካዋጣችሁ ቀጥሉ " የሚል ምላሽ መስጠታቸውን የጠቆሙት የኮሚቴ አባሉ፤ በመጨረሻም ፦ "ታርፍ እንደሆነ እረፍ! አላርፍም ካልክ በህይወት እንደፈረድክ እወቅ !' ብለው እንዳሰናበቷቸው አመልክተዋል።
ይህን በሚሏቸው ጊዜ እርሳቸውም በድጋሜ ፦" ካዋጣችሁ ቀጥሉ!" ማለታቸውን የጠቀሱት አቶ ኢስታል፤ ከዚህ ሁሉ ማስፈራሪያ በሁዋላ ለቀዋቸው መምጣታቸውን ገልጸዋል።
አቶ ኢስታል በጽሁፋቸው መጨረሻ ፦ "የዋህ ሰዎች!!! ህጋዊውንና ህገመንግስታዊውን የህዝበ ሙስሊሙን መብትን የማስከበር ሂደት በተራ ማስፈራሪያ ሊያቆሙት ይሞክራሉ እንዴ!? በመገረምእራሴን ጠየኩ" ብለዋል።
ከስድስት ወራት በላይ ያስቆጠረው የሙስሊሞች "የመብታችን ይከበር!" እንቅስቃሴ ካለፉት ጥቂት ሳምንታት ወዲህ በመላ አገሪቱ ዳግም እያገረሸእንደሚገኝ ይታወቃል።
በመሪዎች ላይ የሚደረገውን ወከባ እና ማስፈራሪያሙስሊሙ በነገው አሊት በነቂስ ወጥቶ እንዲቃወም የተለያዩ ወረቀቶች እየተበተኑ፣ መልእክቶች በፈስ ቡክ እየተሰራጩ ነው።
በሌላ በኩልም የህዝበ ሙስሊሙ ኮሚቴ መሪዎች ከታሰሩ ምን መደረግ እንዳለበት የሚገልጥ ወረቀትበስፋት እየተሰራጨ ነው።
በዚሁ ወረቀት ላይ መሪዎቹ ቢታሰሩ ፣ ሰላማዊ ትግሉ ያለምንም መደናበር እንዲቀጥል፣ መሪዎች የሚደርስባቸውን ማስፈራሪያና ዛቻ በመረጃ ለህዝቡና ለሚዲያዎች ማሳወቅ፣ ለአለማቀፍ ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ማሳወቅ፣ ወደ ሚታሰሩበትቦታ በመሄድ በመሰባሰብ ረብሻ ሳይፈጠር የጉዳዩንግዝፈት ማንጸባረቅ፣ በመላው አገሪቱ ሰላማዊ ትግሉን ማጠናከር፣ በመንግስት ተቋማት ላይ ያሉ ሙስሊሞችና ፍትህ ወዳድ የሆኑ ክርስቲያኖች አድማመምታት፣ በመጀመሪያ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች አድማ ማድረግ፣ በውጭ የሚገኙትም ተቃውሞ ማድረግ፣ ሚሉት ይገኙበታል።
ወረቀቱ በመጨረሻም " ድል ያለመስዋትነት እንደማይገኝ ስለምናውቅ ለ34 ሚሊዮን ሙስሊም በቂ የሆነ አስር ቤት ወይም ልትገሉንም ከሆነ 34 ሚሊዮን ጥይት አዘጋጁ ወይም ጥያቄያችንን ሳይሸራረፉ መልሱልን" ይላል።
በደሴ ከተማ የተያዙት ሼህ መከተ ሙሴ እስካሁን የደረሱበት አልታወቀም። በርካታ ሙስሊም ወጣቶችም በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ታዘቢዋኝ
ነ.ሚዲ-ኤፅ፡ ካሣሁን.
ኦክሳኦ፡ ኪሮሜፅ፡ ኪወመ፡ አፊቻለሁ
SAMI 25/12/04

79

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

**[FEZEKIR CENTER] የሙስሊም እንቅስቃሴ መሪዎች ታስረው ተለቀቁ**

**From:** "Ahmed Gragn" <notification+zjf4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Thursday, July 12, 2012 4:06 PM

Ahmed Gragn posted in FEZEKIR CENTER

**Ahmed Gragn**

11:05pm Jul 12

**የሙስሊም እንቅስቃሴ መሪዎች ታስረው ተለቀቁ**

የሙስሊም እንቅስቃሴ መሪዎች ታስረው ተለቀቁ

ሐምሌ ፰ (ስምንት) ቀን ፳፻፬ ዓ/ም

አስወጋጅ ጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት የሆኑትን አህመዲን ጀበልን እና ሁሴን አዘነን ጨምሮ ቀናት አስር ለቀቀ።

ተቃውሞ ስብሰባን እንደያቀርቡ ለማድረግ ነው ሲሉ ምንም ሳይፈጽሙ ታስረው የነበሩ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ዛሬ ሰኞ ሐምሌ ፱ (ዘጠኝ) ቀን ፳፻፬ ዓ/ም ከእስር ተለቀቁ።

ኢብኮ ዜና፦ የኢህአዴግ መንግሥት የደህንነት ጽ/ቤት ትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብን ችግሮች ለመፍታት ከሚቴ አባላት የሆኑትን አህመዲን ጀበል እና ሁሴን አዘነ ጨምሮ ስብሰባን እንደያቀርቡ ለማድረግ ነው ሲሉ ምንም ሳይፈጽሙ ታስረው የነበሩ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ዛሬ ሰኞ ሐምሌ ፱ (ዘጠኝ) ቀን ፳፻፬ ዓ/ም ከእስር ተለቀቁ።

ሁሉቱ የኮሚቴ አባላት ለአሁድ ሕዝባዊ የጸሎትና የመጅሊስ ምርጫ ተቃውሞ ስብሰባ ለማድረግ ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላይ በመኪና በሚንዥረጥ ጊዜ ነበር ዘንባወርቅ አካባቢ የደህንነት ኃይሎች በጊቢ አጥ መኪና በመከተል መንገድ በመዝጋት እንዲወርዱ ያስገደዷቸው። መሪዎቹም ማንነታቸውን ሳናውቅ ከመኪና አንዲወርዱ በማለት በር በኃይል ሰብረው ገብተው ሲሆን የደህንነት ኃይሎች የመኪናውን በር በኃይል ሰብረው ገብተው ከመኪና አንዲወርዱ በማለት በር ዘግተው ደብድበዋቸዋል።

የተቀመጡ ሲሆን የደህንነት ኃይሎች የመኪናውን በር በኃይል ሰብረው ገብተው ከመኪና አንዲወርዱ በማለት በር ዘግተው ደብድበዋቸዋል።

መሪዎቹም ማንነታቸውን ሳናውቅ ከመኪና አንዲወርዱ በመዝጋት እንዲወርዱ ያስገደዷቸው። ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላይ በመኪና በሚንዥረጥ ጊዜ ነበር ዘንባወርቅ አካባቢ የደህንነት ኃይሎች የመኪናውን በር በኃይል ሰብረው ገብተው ከመኪና አንዲወርዱ በማለት በር ዘግተው ደብድበዋቸዋል።

ሁሉቱ የኮሚቴ አባላት ለአሁድ ሕዝባዊ የጸሎትና የመጅሊስ ምርጫ ተቃውሞ ስብሰባ ለማድረግ

[ISLAM] ብራቦ ሙስሊሞች !!! ትላትን ማታ በተከሰተው የመብት ረገጣና ጭፍጨፋ...

YAHOO! MAIL Classic

Saturday, July 14, 2012 4:33 AM

**[ISLAM] ብራቦ ሙስሊሞች !!! ትላትን ማታ በተከሰተው የመብት ረገጣና ጭፍጨፋ...**

**From:** "Abdurehman Nasser" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "ISLAM" <ABDURAE99@groups.facebook.com>

Abdurehman Nasser posted in ISLAM

11:33am Jul 14

**Abdurehman Nasser**

ብራቦ ሙስሊሞች !!! ትላትን ማታ በተከሰተው የመብት ረገጣና ጭፍጨፋ ሳይደናገጡ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በአሁኑ ሰዓት በአንዋር መስጂድ ዋናውን ማይክሮፎን በመጠቀም ጥያቄያችን ሰላማዊ ሃይማኖታዊና ከጽንፈኝነት የጸዳ ነው የእምነት እንጂ የፖለቲካ አጀንዳ የለንም አሁንም ቢሆን ለሃገራችንና ለህዝባችን ሰላምን እንመኛለን ለሰላም ዘብ እንቆማለን በማለት ሙስሊሞች ሰላማዊና ሰላም ወዳድ መሆናቸውን እያስመሰከሩ ነው! ሁሌም ሰላምን እንሰብካለን! መንግስት እያወጣው ባለው መግለጫ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች እየተደናገጡ ነውና ባለንበት ቦታ ሁሉ ሙስሊሙ ከሌላው አማኝ ጋር ችግር እንደሌለበትና ጥያቄው ሙስሊሞችን ብቻ የሚመለከት መሆኑን በመንገር ሰላምን እየሰበክን የመንግስትን ሴራ ማክሸፍ አለብን! ኢንሻአላህ!!! ድል ኢስላምን የበላይ ለማድረግ ለሚታገሉት አላህ ያድርገው!!!!!

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/




Copyright © 1994-2012 Yahoo! Inc. All rights reserved. Terms of Service - Copyright/IP Policy - Guidelines
NOTICE: We collect personal information on this site.
To learn more about how we use your information, see our Privacy Policy - About Our Ads.

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

[Anti-Ahbash EthioMuslims Group] ዱአ ዱአ ዱአ ተስፋ ከቆረጥክ እራስህን - Search Results ... http://us.mc1208.mail.yahoo.com/mc/welcome?.gx=1&.tm=1341...

Hi, Kamil | Sign Out | Newest version of Y! Mail | Help

Trending: Sherman Hemsley

Search | Search Web

Mail | My Y! | Yahoo!

What's New? Mobile Mail Options

Get the newest Yahoo! Mail

Mail | Contacts | Calendar | Notepad

Check Mail | New

Previous | Next | Back to Search Results

Mark as Unread | Print

Delete | Reply | Forward | Spam | Move...

Saturday, July 21, 2012 11:44 PM

**[Anti-Ahbash EthioMuslims Group] ዱአ ዱአ ዱአ ተስፋ ከቆረጥክ እራስህን**

**From:** "Asif Asim" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

**To:** "Anti-Ahbash EthioMuslims Group" <ethioantiahbash@groups.facebook.com>

Folders
- Inbox (20482)
- Drafts (16)
- Sent
- Spam (995) [Empty]
- Trash [Empty]
- My Photos
- My Attachments

Chat & Mobile Text [Show]
I am Available
Settings

My Folders [Add - Edit]
- kam
- kamilo
- Notes
- Suny

Asif Asim posted in Anti-Ahbash EthioMuslims Group

6:43am Jul 22



**Asif Asim**
ዱአ ዱአ ዱአ ተስፋ ከቆረጥክ እራስህን
ተጠራጠር ሙእሚን ተስፋ አይቆርጥም ሌላው
ለሚዲያ ስነ ልቦና መሸነፍ የለብንም ጎበዝ
ወሳኝ ሰአት ላይ ነን እንደምንሰማው ኢህዲግ
ውስጥ ብዙ ሰዎች ኢየተቃወሙት ነው
በሙስሊሙ ጉዳይ አባዱላ ዛሬ ስብሰባ ረግጦ
ወተዋል ከኛሰብርና ሰላማዊ መሆን ይጠበቃል

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

Delete | Reply | Forward | Spam | Move...

Previous | Next | Back to Search Results

Select Message Encoding | Full Headers

FDLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

